
ታሳቢዉ 2ኛ ዕትም

# የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ

## (ከፊውዳል አርስቶክራሲ እስከ አብዮታዊ ዲሞክራሲ)



ጥሩነህ ገምታ

ለመጀመሪያ ጊዜ ሐምሌ 2008 በፊንፊኔ ከተማ ታተመ ።

ለሁለተኛ ጊዜ ሊታተም ከተዘጋጀ በኋላ በአቅም ማነስ ምክንያት

ሳይታተም ቀርቶ በአየር ላይ ተደራሽ እንዲሆን ተደረገ።

ፀሐፊዉን በኢሜይል አድራሻ gamtaeebba@gmail.com ማግኘት ይቻላል።

የሽፋን ሥዕል (ከምስጋና ጋር) አብዲሳ በላቸው

## የመጀመሪያ እትም መግቢያ

የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ በሚለዉ ርዕስ ላይ ለመፃፍ አስቤ የነበረዉ ከአዲስ አበባ ዩኒቬርስቲ የፖለቲካል ሣይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት የትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ድግሪዬ ማሟያ ከተፃፈዉ ጽሑፍ ጊዜ ጀምሮ ነዉ። በዚያን ወቅት አማካሪዬ የነበሩት ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ፤ ይህ አርእስት ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በስፋት ሊፃፍበትም የሚችል መሆኑን እንደምክርም እንደአስተያየትም በቃል ጣል አድርገዉልኝ የነበረዉን መሠረት በማድረግ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለመፃፍ ያደረብኝ ሐሳብ ከውስጤ ሳይጠፋ ቆይቶ የነበር ቢሆንም፤ ያጋጠሙኝ የሕይወት ውጣ ውረዶች እንኳን ጽሑፍ ማዘጋጀት ቀርቶ በሕይወት መኖር ራሱ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ አስገብቶኝ ስለነበር ቅድሚያ አልተሰጠውም። በተለይ በደርግ መውደቂያ አከባቢ የነበሩ ሁኔታዎችና ቆይቶም ከ2001 እስከ መጋቢት 2002 ድረስ ለፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ ስሰራ በነበረበት ጊዜያቶች የነበሩ ሁኔታዎች ለግል ሕይወቴ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቤ ጭምር እጅግ አሳሳቢና አስጨናቂ ነበሩ። ቢሆንም ግን በዚህ መሀከል ባሉት ጊዜያት ለዚህ አርእስት የሚሆኑ ጽሑፎችና ሰነዶችን ከማሰባሰብና ከማንበብ አልተቆጠብኩም ነበር።

አንዳንድ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች እንደሚሉት በያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ ቢያንስ አንድ መደብል የሚሆንና የሚፃፍበት አርእስተ ጉዳይ አይጠፋም የሚሉት ነገር፤ እኔም ዉስጥ ይኖር ይሆን? ብዬ ማሰብ ከጀመርኩ ቆይቻለሁ። መቆየቱ ጠቅሞኝም ጎድቶኝም ሊሆን ይችላል። የጠቀመኝ ብዙ ተጨማሪ ሰነዶችን ለማሰባሰብና ለማንበብ በመቻሌ ሲሆን፤ የጎዳኝ ደግሞ አንዳንዶች ተያያዥ ጉዳዮችን ረስቻቸዋለሁ፣ አንዳንዶች ደግሞ ጊዜ ያልፉባቸዉና የዛሬ የኢትዮጵያ የፖለቲካ የዕድገት ደረጃ በእርግጥ በዓይነት እንኳን ባይሆን የመጠን ልዩነት በስፋት የሚታይበት ስለሆነ እንድጥላቸዉ ወይም እንድተዋቸዉ አስገድደውኛል።

የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ጉዳይ ለመፃፍ ከየት ጊዜ መጀመር ይሻላል

ብዬ ላሰብኩት ሁኔታ ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን መነሳት በቂ እንደሚሆን ግንዛቤ አድርጌአለሁ። ምክንያቱም የፖለቲካ ፓርቲ ነባራዊ ሁኔታዎች ማቆጥቆጣ የጀመሩት በዚሁ ጊዜ ውስጥ ስለሆነ ነው። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ አካል መመሰቃቀል የጀመረዉ ከአፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ ጀምሮ (ከዚያ ቀደም ያለ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም) ስለሆነ፤ በውስን ደረጃም ቢሆን ያንን ቢያጠቃልል ከተነሳሁበት ዓላማ አንፃር ምሉዕ ያደርግልኛል ብዬ ስላሰብኩ፤ ከዚያዉ እንዲሆን አድርጌአለሁ። በዚህም የኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ጽሑፌ የቴዎድሮስ፣ የዮሐንስ፣ የምኒልክ፣ የኃይሌ ሥላሴ ማለትም ፊዉዳል አርስቶክራሲ ባልኩትና፣ እንዲሁም የደርግና የሕወሓት አገዛዞች ማለትም አብዮታዊያንን በሚወክል መልክ ተከፋፍሎም፣ ተደበላልቆም ቀርቧል። የአጭር ጊዜም ቢሆኑ በመሀል የሚገኙ አገዛዞችም (ተክለ ጊዮርግስና እያሱ) በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ የየራሳቸዉ አሻራ ስለነበራቸዉ በቆዩበት የጊዜ መጠንና ለማከናወን በሞከሩት ሥራ አንፃር እንዲታከሉበት ተደርገዋል። ከዚህ ጋር አንድ ሊታወቅ የሚገባ ነገር አለ። ብዙ ሊፃፍበት የሚችል የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ በኔ አነስተኛ ሙከራ ጅምር ቢሆን እንጂ ብዙ ሊታወቁና ሊፈተሹ የሚገቡ ጉዳዮች እንደሚኖሩ አምናለሁ።

ሁለት ጽንሰ ሐሳቦች፤ አርስቶክራሲና አብዮታዊ ዲሞክራሲ፤ ዋናዉን የመጽሐፉን አርእስት አፅንዖት ለመስጠት ተቀምጠዋል። ሁለቱም የአገዛዝ ሥርአቶች መሆናቸው ግንዛቤ ተወስዶ በግርድፉም ቢሆን የእነዚህ ሁለቱ ጽንሰ ሐሳቦች ትርጉም ማግኘት ለተነሳሁበት የመጽሐፉ ይዘት ተፈላጊዉን ነገር ያላብሳል የሚል እምነት አለኝ። በመዝገበ ቃላት ትርጉም መሠረት አርስቶክራሲ በሕብረተሰብ ዉስጥ ከፍተኛዉን ሥፍራ የያዘ ሰዉ ወይም የያዙ ሰዎች አገዛዝ ነዉ። በጄሃሪ (ገጽ 421) ሥራ ዉስጥ ቦል የሚባል ፀሐፊ እንደሚለዉ አርስተክራሲ የሚባለዉ ሥርአት የፖለቲካ መሪዎቹ ራሳቸዉን ከሥልጣን ምንጭ ከሆነዉ ሕዝብ በላይ አድርገዉ የሚያስቀምጡበት፣ የፖለቲካ ክብርና ተቀባይነትን በኃይል በማስገደድ ለማስጠበቅ የሚሰሩበት የፖለቲካ ሥርአት ነዉ እንዳለው ሁሉ፤ በዚህ ጽሑፍም ተገቢ ቦታዉ ላይ እንደሰፈረዉ ሁሉ አብዮታዊ ዲሞክራሲም ከዚሁ ያልተለየ መሆኑን ለማየት ስለምንችል

አርስቶክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ የቅርፅ ቢሆን እንጂ የይዘት ልዩነት እንደሌላቸዉ ያስገነዝብልኛል ብዬ አምናለሁ።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ የዉጪ ኃይሎች ሚናም ቀላል እንዳልነበር ስለሚታወቅ፤ ቀንጨብ አድርጌ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የሱዳን፣ የሱማሊያና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወይም የአፍሪካ ሕብረት እና በኢትዮጵያ ፖለቲካ የኤርትራ ተፅዕኖ ምን እንደሚመስል አንስቻለሁ። በመጨረሻም ጥሩነህ ገምታ ማነዉ የሚለዉን ትንሽ ለማስጨበጥ የተወሰኑ ገፆችን አክዬበታለሁ። ከፖለቲካ ተሳትፎ አንፃር የ60ዎቹ በብዙ መልኩ ቢቀድሙኝም፤ የ70ዎቹ እንቅስቀሴ ዉስጥ ተሳትፎ ነበረኝ። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ብዙ ተሳትፎዬ ከተቃዉሞ ጎራ ስለሆነ፤ ከሞትና እስር በመለስ የሕይወት መመሰቃቀል አጋጥሞኛል። እዚህ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በተለይም እምቦቆቅላ ሕፃናት ከወላጆቻቸዉ ጉያ እየተወሰዱ ወይም የወላጆቻቸዉ ዓይን እያየ በተገደሉበት አገር ዉስጥ፤ በእኔ ላይ እንግልት ደርሷል ብዬ ለማጉላት ሳይሆን፤ ስለአንድ ነገር የሚፅፍ ሰዉ የጀርባ ታሪኩ ምን እንደሚመስል ቢታወቅ፤ ካልታሰበ ስህተት ይገላግላል ብዬ ነዉ እንጂ፤ ለመንገላታትማ ከኔ የበለጠ የተንገላቱ ሰዎች እንደነበሩና ዛሬም እንዳሉ አጥቼ አይደለም። ከፍ ሲልም ሕይወታቸዉን መስዋዕት ያደረጉም ቁጥራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ሳይታወቀኝ ቀርቶ አይደለም።

ይህ <u>የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ</u> ጽሑፍ የተዘጋጀዉ በአብዛኛዉ ቀደም ሲል በተፃፉ መረጃዎች (በእንገሊዘኛው ሰከንደሪ ሶርስ በሚባል) ላይ የተመሰረተ ነዉ። ከቋንቋም አንፃር የሦስት ቋንቋዎች የአማርኛ፣ እንግሊዘኛ እና አፋን ኦሮሞ ድብልቅ ነዉ። እንዲያዉ ተዛማጅ ናቸዉ ካልኳቸዉና የመተርጎም አቅም ካልፈቀደልኝ በስተቀር ሳልተረጉማቸዉ እንዳሉ በጥሬያቸዉ ተጠቅመባቸዋለሁ። ምክንያቱ ደግሞ አንድም የትርጉም ሥራ የራሱ ዲስፒልን የሚፈልግ ሲሆን፤ ሌላዉ የበለጠ ትኩረቴን የሳበዉ አንባቢዎቼ ኦሪጅናሉንና ዋቢ ያደረኩዋቸዉን ጽሑፎች በትርጉም ሥራ ሂደት ዉስጥ ሳይዛቡ ባሉበት ሁኔታ እንዲያገኙና ፍርዳቸዉን እንዲሰጡኝ በማለት በዚህ ድጋሚ ሕትመትም በነበሩበት

ሁኔታ እንዲቆዩ ተደርገዋል።

በመጨረሻም ይህ ጽሑፍ የፓርቲ ፖለቲካ ጉዳይ ስለሆነ ከወገንተኝነት ነፃ ሆኜ ጽፌአለሁ የሚል መመፃደቅ እንዳልዳዳኝ ለአንባቢዎቼ መግለፅ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እኔ የዚህ ዓለም፤ በተለይም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በኤኮኖሚ፣ ወዘተ በተከፋፈለ ኢትዮጵያ አገር ዉስጥ ሕይወቴን ያሳለፍኩ ኢትዮጵያዊ ሰዉ ስለሆንኩ፤ ብዙ ሰዎች እንደሚያረጉት እኔም የራሴን አቋም አካትቻለሁ። የአካዳሚ ሥራ ከሚሰሩ በስተቀር (እነሱም አንዳንዴ አያደርጉትም አይባልም) ያንን የማያደርግ ሰዉ ደግሞ የለም። የዜጎችን ማንነት የሚሸረሽሩ ሁኔታዎች የመኖራቸዉን ያህል ገንቢ አስተሳሰብ የሆኑም ሐሳቦች ብዙ ናቸዉ። ገንቢ የሚባለዉን አስተሳሰብ ለመቀላቀል ሲባል በኢትዮጵያዊያን መሀከል አይነኬ ይባሉ የነበሩትን የዘርና የሃይማኖት ነገሮች ነካክቻለሁ። ለምሳሌም ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን አበሻ ማለት ምን ያህል ይጥማል ወይም አይጥምም የሚለዉን ሰዎቻችን እንዲነጋገሩበት፤ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ተመስርቶም በኢትዮጵያዊያን መሀከል ሲታዩ የነበሩ መበላለጥን አስመልክቶ ለመግለፅ የፈለኩት፤ በሕዝቦች መሀከል ጥላቻን ለመቆርቆስ ሳይሆን በሽታችንን ከገለፅን በርግጠኛነት መድኃኒት ማግኘት ይቻላል ብዬ አስቤ ነዉ። ወይም ፖለቲከኞች እንደሚሉት ችግራችንን መግለጽ ከቻልን ለመፍትኼዉ ግማሽ መንገድ እንደተጓዝን ይቆጠራል ለማለት ፈልጌ ነዉ። ወይም መጥፎ ሰዎች እንዳያሸንፉ ጥሩ ሰዎች እጃቸውን አጥጠፈው መቀመጥ የለባቸውም የሚባለውን የአዋቂዎች ብህል ለማሳየት ፈልጌ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ይህንን መጽሐፍ በስሜት ተነሳስቼ የፃፍኩ ባይሆንም የተሳሳትኩ ነገር እንደሚኖር አልጠራጠርም። በሰዉ ሥራ ዉስጥ መሳሳት ቢኖርም ትልቁ ነገር መሆን ያለበት ስህተትን በአስተዉሎት ተቀብሎ አለመስተካከል መሆኑ ሊሰምርበት ይገባል። ይህ መጽሐፍ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለተከሰተዉ የፓርቲ ፖለቲካም ሆነ አመራር ችግሮች መፍትኼ ለማፈላለግ ለምን ብሎ ራሱን ለሚጠይቅ ሰዉ መልሱን ለማግኘት የበኩሉን መነሻ ሐሳብ ሊያመነጭ ይችላል ብዬ አስባለሁ። ስለሆነም በክብር የሚቀበሉልኝ የመኖራቸዉን ያህል የሚከፉብኝ እንደሚኖሩ በእርግጠኛነት እጠብቃለሁ።

በፓርቲ ፖለቲካ ጉዳዮቻችን የሚገቡ የሩቅና የቅርብ ኃይሎች ምን ያህል ጠቀሙን? ምንስ ያህል ጎዱን? ተገቢ መልስ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው። ለመሆኑ እኛ ኢትዮጵያዊያን ስለድክመታችን፣ ስለኋላቀርነታችን፣ ስለሰፊ ልዩነታችን፣ ፖለቲካን ከቅመኝነትና ከጠላትነት አመለካከት ባሻገር ምን ያህል ጣታችንን ወደራሳችን ቀስረናል? መልስ መስጠት ያለብን ጊዜ ላይ ደርሰናል ማለት ሳይሆን እጅግ አልፎን ሄዷል። ልንደርስበት የምንችል ቢሆንም የሚያስከፍለን ዋጋ ግን ትልቅ ነዉ፤ የአገራችንን አንድነት እስከ መፈታተን ሊደርስ በሚችል ደረጃ ማለት ነው። በዉሸት ዲሞክራሲና በዉሸት ዕድገት መኮፈሱን ትተን እራሳችንን መመገብ ባለመቻላችን እፍረት ሳይሰማን፤ በዓለም ሕብረተሰብ ፊት ለመቆም መቻላችን ወይም መገደዳችንን ሁለንትናችንን መፈተሽ እንዳለብን ሁሉ፤ አሁን ዓለም ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር ሕዝባችሁን መምራት አልቻላችሁም እስኪንባል ድረስ መጠበቁ እንዴት እንደሚያሸማቅቅ ማሰቡም አስቸጋሪ ነዉ። ብንባልም ነገሩ ትክክል በመሆኑ ይህንን ገልፆ መፃፍ ደግሞ ከራስ ጋር ትግል ማድረግ ይጠበቃል ለማለት የመጀመሪያ ሰዉ ባልሆንም እኔም የበኩሌን አስተዋጽኦ እንዳደረኩ ይቆጠርልኝ አላለሁ።

በመጨረሻም፤ የኢትዮጵያ ገዥዎች ለሠሩት ወንጀል ክህደት ዓመላቸው እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶ፤ የነበርኩበት ሥርአት ምን እንደሚመስል በተጨባጭ ለማሳየት ያህል መንግስቱ ኃይለማሪያም ዝንብ እንኳን አልገደልኩም ብሎ መመፃደቁ አሳፋሪና የሚያሳዝን ሲሆን የኃይሌ ሥላሴ 54 ባለሥልጣኖች በሱ ብቸኛ ቀላጤ እንዲገደሉ ትዕዛዝ የሰጠበትን ደብዳቤና በግሌም የዓደኛ ክህደት ምን ያህል ዉስጣዊ ዕረፍት እንደሚነሳ አንባቢያን ይገነዘቡ ዘንድ፣ ዋቢ ሰነዶች ስካን በማድረግ እንዲቀርቡ አድርጌአለሁ። ኢትዮጵያችንን በሁለት እግር ማቋም ያልተቻለበትን ምክንያቶችና ዜጎች ስለወደቁበት የሚፅፉ ብዙ የመስኩ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ቢሆንም፤ እኔም ከባህሩ ጨልፌ ልጨምርበትና አስተዋጽኦዬን ለማበርከት ስለአሰብኩ እንድትቀበሉኝ ከጉልበቴ ዝቅ ብዬ እጠይቃለሁ።

## ታሳቢዉ የ2ኛ ዕትም መግቢያ

ይህ ዕትም ከመጀመሪያው ዕትም በይዘት የተወሰነ ልዩነት ተደርጎበታል። ምክንያቱም ሁኔቶች በዕውን በቦታ እና በጊዜ እያሉና በመጀመሪያው ዕትም ውስጥ መካተት የነበረባቸውና ሳይካተቱ የቀሩ ሐሳቦች እንዲካተቱ ተደርገዋል። እነዚህ ተካተቱ ያልኳቸው ሐሳቦች ብዙም የተለዩ ነገሮች ሳይሆኑ ከበፊቱም መካተት የነበረባቸው፤ ነገር ግን በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሳይካተቱ የቀሩ ናቸው። ከ2008 ዓም ወዲህ በአገሪቱ ውስጥ የአገዛዝ ሳይሆን የገዥዎች መለዋወጥ ተደርጓል። በኢህአዴግ መከፋፈል ምክንያት የሀገሪቱን ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕይወት የበላና በትርሊዮን የሚቆጠር ንብረት ያወደመ ጦርነት ተካሂዷል። ክስተቶቹ የራሳቸውን ጥናት የሚፈልጉ ቢሆንም ቀንጨብ አድርጎ ማካተት ባስፈለገበት ቦታ እንዲካተት አድርጌአለሁ። በተጨማሪም አንባቢያን በተቀመጠው አድራሻ በኩል አስተያየት ሰጥተውኛል። በተለይም የመጫና ቱላማ መረዳጃ ማህበር ሊቀ መንበር አቶ ድሪቢ ደሙሴ በዚህ አርዕስት ላይ ብዙ ሊነበብና ሊፃፍበት እንደሚገባ ሰፊ ሐሳብ ያስጨበጠኝ ሲሆን፤ የእሱንም ሆነ የሌሎችም አስተያየት ለ2ተኛው እትም ተጠቅመበታለሁ። አፍ እላፊ የሰነዘሩ ቢኖሩም ስድባቸዉን እንደ መልካም አጋጣሚ በመዉሰድ የቃላት አጠቃቀም ሳይቀር በዚህ ሥራዬ ውስጥ ያሻሻልኳቸው ስላሉ በማንበባቸው ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

አንድ የሚታወቅ ነገር ቢኖር በቦታ፣ በጊዜ እና በሁኔታዎች ውስጥ በመጠን ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚለዋወጡ ነገሮች የመኖራቸው ጉዳይ ነው። በቦታ፣ በጊዜ እና በሁኔታዎች ውስጥ የማይለውጥ ነገር ቢኖር ራሱ ለውጥ ነው በማለት የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ይገልጹታል። ምናልባት ለውጥ ራሱ በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታዎች ውስጥ ሳይለዋወጥ ቀጥ ብሎ የሚሄድ ሳይሆን ቦታ፣ ጊዜ እና ሁኔታዎች በሚፈጥሩበት ተጽዕኖና መስተጋብር ውስጥ አንድም በፍጥነት፣ በማዝገም ወይም ወደኋላ በመጠማዘዝ የሚለወጥ እንጂ ቀጥ ብሎ የሚቆሙበት ጊዜ ስለሌለ፤ 2ኛ ዕትም መጽሐፌም በነዚህ አጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ለውጥ ተደርጎበታል። ምንም እንኳን

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በመጠንም ሆነ በዓይነት፤ በሌላም አባባል የመንግስት ሥልጣን በታ ላይ ግለሰቦች ተቀያየሩ እንጂ አገዛዙ እንደ ሥርአት አልተቀየረም፡፡ በመሆኑም የመጠን እንጂ የሕዝብን ፍላጎት የሚያረካ የዓይነት ለውጥ አልታየም፡፡ ለምን እንዳልታየ በዚህ 2ኛ ዕትም ውስጥ ተንፀባርቋል፡፡

ለምን የመጠን እንጂ የዓይነት ለውጥ አልሆነም ብለው የሚጠይቁኝ ካሉ ይህ መጽሐፍ በተፃፈበት የሕይወት ዘመን ውስጥ የኢትዮጵያ የአገዛዝ ሥርአቶች ከአምባገነንነት ፈቀቅ ብለው የዓይነት ለውጥ ያመጡበት ጊዜ ስላልተሰማኝ ነው ብዬ እመልሳለሁ፡፡ ለውጥን ስለሚጠላ ወይም ስለሚፈራ ሳይሆን ለውጡ በዜጎች ሕይወት ላይ የፈጠረው ትርጉም ያለው እርምጃ አንድም አነስተኛ ነው ወይም ጨርሶ የለም የሚባል ደረጃ ላይ ስለሆነ ነው፡፡ በተለይም የመጽሐፉ ትኩረት በሆነው የፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ገዥ ቡድን ወይም ፓርቲ ከፈጠረው የስም ለውጥ በስተቀር የዴሞክራሲያዊነት ባህርይ የተላበሰበት ጊዜ እና ሁኔታ የሌለ ስለሆነ ነው፡፡

ከ2010 ዓም አጋማሽ ወዲህ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ለየት የሚሉ ነገሮች ተከስተዋል እንኳን ቢባል ሕዝብ የጠየቀውና የተጠበቀው ተሃድሶ ዓይነት ሳይሆን ሕዝቡን ለቁጭት የሚዳርግና ላቅ ካለም ለአብዮት የሚያነሳሳ ሁኔታ ነው፡፡ ማለትም ሕዝብ ሁኔታዎች እየታደሱ እንዲሄዱለት የሚያቀርባቸው ጥያቄዎችና ገዥ ኃይሎች አደረግን የሚሉት ተሃድሶ ሳይጣጣም እየቀረ ሲሄድ ተሃድሰው የዓይነት ለውጥ ካላመጣ ሕዝቡ መሪዎቹ ላይ እምነት ያጣና የሕዝቡ የተሃድሶ ጥያቄ ወደ አብዮት ይገባል ለማለት ተፈልጎ ነው፡፡ እንግዲህ የመፅሐፉ አርእስት እንደሚለው የፓርቲ ፖለቲካው ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ከግልባጩ ´መደመር` ያልተለየ ስለሆነ ዕትሙም ይህንኑ አካትቶ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ወደ መጨረሻ አከባቢ ደግሞ አንባቢን በእንጥልጥል ላይ ከመተው ብዬ የመውጫ ማጠቃለያ ሐሳብ ብዬ አካትቻለሁ፡፡
መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

ጥሩነህ ገምታ ወዬሳ

## ማስታወሻ

ሐዉልት ሊቆምላቸዉ የሚገቡ ብዙ ዜጎች ቢኖሩም ቀጥሎ የሚጠቅሳቸዉ ወገኖቼ በሕይወት ያሉትም ሆኑ ለሞቱት ይህች መጽሐፍ ማስታወሻ እንዲትሆንልኝ በአክብሮት አበረክታለሁ።

- ለአባቴ ገምታ ወዬሳና እናቴ በርኪ ቶኮን፤ እናንተ በሕይወት ባትኖሩም እራሳችሁ ከትምህርት ቤት ደጃፍ ላይ ሳታልፉ እኔ ፊደል እንዲቆጥር በማድረጋችሁ እኮራባችኋለሁ።
- ለታላቅ ወንድሜ አበራ ገምታ፤ እኔ ወንድምህ እንዲማር አንተና ባለቤትህ ወይዘሮ ካሰች ተሰማ የከፈላችሁት መስዋዕትነት ምንጊዜም አይረሳኝም። የባለዕዳነት ምስጋናዬን ተቀበሉኝ።
- ለዶክተር መረራ ጉዲና ጃፊ፤ ሕይወትህን ሁሉ ለሕዝቦች ነፃነትና አንድነት የሰጠህ ሰዉ ነህና አርአያነትህ ምንጊዜም የሚዘነጋ አይሆንም።
- ለአቶ ከበደ ፍሪሳ ጉተማ፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትምህርት ጊዜ “Kana Beektu Lataa” ብለህ መፃፍ ከጀመርክበት ጊዜ ጀምሮ፤ በተለይም ስለኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት የከፈልከዉ መስዋዕትነት ስምህን ሕያዉ ያደርገዋል። አንተ ቢታልፍም ዓላማህ ሕያዉ ነዉ።
- ያለእንከንሽ በአሸባሪነት ተፈርዶብሽ ስድስት ዓመት ከስምንት ወር መታሰርሽ ሳያንስ በሽታ እንዲትሸምቺ የተደረገሽዉ ሕጋዊ እህቴ ወይዘሮ አበራሽ ያደታ ናዶ፤ የዚያ ሁሉ ዓመታት ጭንቀቴ ማስታወሻ እንዲሆንልኝ ይህንን መጽሐፍ በማስታወሻነት አበረክትልሻለሁ።
- የሕይወትና የተሞክሮ ታሪካቸዉ ደጎስ ያለ መደብል የሚወጣቸዉ ሰዎች አሉ። ከነዚህም ዉስጥ ድርቢ ደምሴ ቦኩ (የመጫ-ቱላማ መረዳጃ ማህበር ሊቀ መንበር) አንዱ ነዉ። ይህ ሰዉ ለራሱ ችግር አለመንበርከኩ ብቻ ሳይሆን ከ300 በላይ የኦሮሞ ወጣቶች ከአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ሲባረሩ ከለላ

ሆኖላቸው ላሳየዉ አርአያነት ይህች መጽሐፍ ማስታወሻ እንዲትሆን አበረክትለታለሁ።

- ለእዉነተኛ ዓላማ በመቆማቸዉ፣ በዘራቸዉና በአመለካከታቸዉ ልዩነት ብቻ በተለያዩ የኢትዮጵያ አገዛዝ ሥርአቶች ሥር ለተገደሉ፣ ለታሰሩ፣ ለተሰደዱ፣ ለተንገላቱ፣ ለተገረፉ፣ ከወዳጅ ዘመድ ተነጥለው ለታሰሩ፣ አካል ስንኩል እንዲሆኑ ለተደረጉ፣ ደብዛቸው ለጠፋ ወገኖቼ ሁሉ፤ ሐዉልት ላቆምላቸዉ ባልችልም፤ ይህች መጽሐፍ ማስታወሻ ትሁንልኝ ዘንድ እያበረክትኩ፤ መስዋዕትነታችሁ ጨለማዉን እንደሚገፍ እምነቴ ነዉ።

ፀሐፊዉ

## ምስጋና

በዚህ ጽሑፍ ለሚታዩ ግድፈቶች ኃላፊነቱ የኔዉ የፀሐፊዉ መሆኑን እያረጋገጥኩ፤ ቀጥሎ ለተመለከቱት ሰዎችና ድርጅቶች ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

✓ ከያንዳንዱ ጠንካራ ወንድ ጀርባ ጠንካራ ሴት አለች የሚባለዉ አባባል፤ ከአባባል የሚያልፍ መስሎ አይሰማኝም ነበር፡፡ ባለቤቴ ወይዘሮ የሺሐረግ ያደታ ናዶ፤ ስለዚህ ጽሑፍ የሚታዉቀዉ ብዙም ነገር ባይኖርም፤ ከትዳራችን በፊት ጀምሮ በአጋጠሙኝ ዉጣ ዉረዶች ሁሉ እና ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ጭምር ከአጠገቤ ሆና የሰጠችኝ ብርታት ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የምተማመንባት ነዉና ምስጋናዬን ተቀበይኝ እላታለሁ፡፡ በተለይም እሰራበት የነበረዉ መስሪያ የኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን መዘጋት በኋላ ሁለተኛ ልጃችን ሱራን እያጠባሽ ያበላችኝ ወይስ የጠጣነዉ  የጥቁር ማሽላ ቅቅል በሷ ብሩህ አእምሮ የታሰበ ስለሆነ ፍጽሞ አይረሳኝም፡፡

✓ ልጆቼ ዘላለም (ከነባለቤቷና ልጆቿ)፣ አብዲ፣ ሱራና ኤባ ይህንን ጽሑፍ ስጽፍ ቤተሰባዊ የጋራ ጉዳዮቻችን ወደ ጎን ትቼ እንድሰራ በመፍቀድ ስለተባበራችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

✓ የጊዜ ርዝማኔና የሁኔታዎች መለዋወጥ ያደበዘዘዉ ቢመስልም ለዛሬ ሕይወት መድረሴ የጓኛዬ የማቴዎስ አመንቴ አዋጂ ዉለታ የሚረሳኝ አይሆንም፡፡ ወንድማዊ ምስጋናዬን ሳላቋድስህ ብቀር ሕሊዬ ይወቅሰኛል፡፡

✓ በመደገፍም ሆነ በመቃወም የተጠቀምኩባቸዉ ዋቢ መረጃዎቼ የአእምሮአቸዉ ጭማቂ ስለሆነ ባለቤቶቹን ሳላመሰግናቸዉ አላልፍም፡፡

✓ የመጀመሪያ የጽሑፉን ረቂቅ ከጓደኛነት ባሻገር እንደወንድም የሆነኝ

አቶ ስብሃቱ ባንጃ አንብቦ ገንቢ አስተያይ ስለሰጠኝ ባለዉለታዬ ነህና አመሰግናለሁ፡፡ የመጀመሪያ ዕትም መጽሐፌን አንብበው የድጋፍም ሆነ የነቀፋ አስተያየት የሰጣችሁኝን ሁሉ ለ2ኛ ዕትም የተጠቀምኩበት ስለሆነ ምስጋናዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ፡፡

## መቅድም

በሕይወት ዉስጥ አንድም ይፈጥናል ወይም ያዘግማል እንጂ ለዉጥ ፍፁም የማይቀር ነገር ነዉ። በፈለግነዉ ጊዜ የሚመጣ ስላልፈለግነዉ ደግሞ የሚቀር ሳይሆን ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ሲፈቅድ ለዉጥ አይቀሬ ነዉ። ከዚህ ጋር አንድ ዕዉነት አለ፤ ለዉጥን ፈጥነዉ የሚቀበሉና ለዉጥን ለመቋቋም የሚፈልጉ ሰዎች ስለመኖራቸዉ ሲታሰብ፤ እንዲያዉ በዚህ ጉዳይ ተፈጥሮአዊ የሚመስሉ ሁኔታዎች መኖራቸዉንና ለለዉጥ የማይገዛ ሰዉ ወይም ግለሰብ ቢኖር ግን መዉደቁ አይቀሬ መሆኑን ዘገይቶም ቢሆን መረዳቱ አይቀሬ ይሆናል።

ሰዎች እንደቆሙለት ዓላማ ልዩነት ላይ በመመረኮዝ ለዉጥ ፈጥኖ እንዲመጣ ወይም ፈጥኖ እንዳይመጣ ማዓተት፤ ከተቻላቸዉም ሙሉ በሙሉ የማስቀረት ወይም የመቀልበስ ባህርይ ይኖራቸዋል። ዘርዘር አድርገን ስንመለከት ደግሞ ሕዝባዊ ዓላማ ያነገቡ ግለሰቦችና ቡድኖች ለዉጥ እንዲመጣ ብቻም ሳይሆን የሚመጣ ለዉጥ ራሱ ፈጣን፣ አሳታፊ፣ የብዙኃኑን ሕዝብ ፍላጎት የሚያረካና ዘላቂነት ያለዉ እንዲሆን ይፈልጋሉ። ከዚህ በተቃራኒ የቆሙ ኃይሎች፤ በተለይ ከሕዝብ ፈቃድ ዉጭ ሥልጣን የያዙ ኃይሎች በያዙት የሕዝብ ዜና ማሰራጫዎች በመታገዝ ለለዉጥ ያላቸዉን ፍላጎት ገደብ ሊያበጁበት፤ በሌላም ሁኔታ ቢጮኹም ለለዉጥ ያላቸዉ ተነሳሽነት አንድም የለም፤ ወይም አናሳና የማስመሰል ይሆናል። ለዉጥ ስለመኖሩ በቃላት ደረጃ ቢናገሩት እንኳን ለዉጡ እነሱን የሚነካ አይመስላቸዉም። እነሱን ጠራርጎ በሚሄድ መልኩና ቁመቱም ቢሆን ለዉጥ አይቀሬ ነዉ።

የለዉጥ ፈላጊ ኃይሎችም ሆነ ፀረ ለዉጥ ኃይሎች የየራሳቸዉ የፖለቲካ መስመርና የፖለቲካ ፓርቲዎች ይኖራቸዋል። ሰዎች ምክንያታዊነት አለዉ የሚሉትን ፍላጎታቸዉን ለማሟላት ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ አካል በማቋቋም ፍላጎታቸዉ እንዲሟላ ያደርጋሉ። ከግለሰብ ጀምረዉ በቡድን ተደራጅተዉ እንደአደረጃጀታቸዉ ዓላማ እና ግብ ቡድናዊም ሆነ ሕዝባዊ ዓላማ እንዲፈጸም ትግል ያደርጋሉ።

በምሳሌ እናስደግፍ ብንል፤ ኮሎምቢያ ዉስጥ የምንቀሳቀሰዉ የዕፅ አማላላሽ ቡድን በራሱ አኳያ ከመደራጀቱም በላይ እስከ አፍንጫዉ ድረስ በመታጠቅ ቢዝነሱን ያከናዉናል፤ መንግስታዊ መዋቅርን እስከ መቆጣጠር ይዳዛል። የፈለገዉ የሰዉ ሕይወት ጠፍቶ የእሱ ዓላማ ገንዘቡን ማጨቅ ነዉ። የካታሎኒያዊያን ድርጅት የካታሎኒያን ግዛት ከእስፓኝ አገዛዝ ነፃ ለማድረግ ይታገላል። የፍልስጤኤም ሕዝብ ከእስራኤል የአፈናና የመሬት ቅሚያ ተላቆ ልዑላዊት ፓለስታይንን ለመመስረት ይታገላል። የዩጋንዳና የኢትዮጵያ መንግስታት የአንድ ወይም የአዉራ ፓርቲን አምባገነንነት በሕዝቡ ላይ ለመጫን ሲሉ የሚቃወሙትን ኃይሎች ስም ከማጠልሸት እስከ ግድያ የሚደርስ እርምጃ ይወስዳሉ። የእነዚህ ሁሉ ፍልሚያ የሚካሄድበት የትግል ሁኔታ የፓርቲ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ልንለዉ እንችላለን።

በፓርቲ ፖለቲካ ግንኙነትም ሆነ ልዩነት ያላቸዉ ሦስት አካላት ይገኛሉ፤ ገዥ ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲ/ዎች እና የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነ ሕዝብ አሉ። ፓርቲዎች የተለያዩ የሕዝብ ጥያቄዎችን በመርህ ወይም በፖሊሲ ሥር በማቀናበር ሕዝቡ ራሱ በዚህ መርህ ሥር እንዲሰለፍላቸዉ ያደርጋሉ። ገዥ ግለሰብ ወይም ገዥ ፓርቲ ወይም ገዥ ቡድኖች የመኖራቸዉን ያህል ተቃዋሚ ፓርቲ/ዎች ደግሞ የገዥዉን ክፍል ፓርቲ ፖሊሲ በመቃወም ፖለቲካዉ ለሁሉም እንዲስማማ ለማድረግ ባይችሉ እንኳን (ለሁሉም የሚስማማ ፖለቲካም አይኖርምና) ለማመጣጠን ትግል ያደርጋሉ። እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር፤ ገዥ ክፍል ገዥ ስለሆነ ብቻ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ ፖሊሲ የለዉም ማለት ስህተት መሆኑ ነዉ። ምክንያቱም ሕገ መንግስታዊ ሥርአትን ጠብቀዉ ሥልጣን ላይ የሚወጡና ከሥልጣንም የሚወርዱ ፓርቲዎች በብዛት ስላሉ፤ ገዥ ነን ከማለታቸዉ ይልቅ ለመረጣቸዉ ሕዝብ አገልግሎት መስጠታቸዉ ይጎላልና ነዉ።

በአንድ አገር ዉስጥ የሚኖሩና በአንድ ሕገ መንግስት ሥር የሚተዳደሩ ሁሉም ዜጎች ሁሉም እኩል ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ መጠበቅም የዋህነት ይመስላል። ምክንያቱም ድብቅና አስከፊ የሰዉ ልጅ ባህርይ በብዙ

ሕዝቦች መሀከል ስለሚታይ ነዉ። ሁሉንም ዜጎቿን ተጠቃሚ የሚታደርግ አገር ቢትኖር (በሙያና በብቃት ላይ የተመሠረተ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ) ብሎ መመኘት ደግሞ ሞኝነትም አይሆንም። ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ማለት ሚዛናዊ አስተዳደርና ሚዛናዊ የሀብት ክፍፍል ማለት ነዉና በጎነቱ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ማለት የተቃዋሚ መስመርን ጎጂ የሚያደርግ ወይም በተቃዋሚ ፓርቲ/ዎች ኪሳራ ወይም በገዥዉ ፓርቲ ኪሳራ ማትረፍ ማለት አይደለም።

በፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ ሦስት አካላት፤ ማለትም ገዥ ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲና ሕዝብ ይኖራሉ ብያለሁ። ገዥና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተፋላሚዎች ናቸዉ። ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ስለሆነ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ሰጪ ነዉ። የሕዝብን ዉሳኔ የማይቀበል ገዥም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ በሕዝብ መሀከል የሚኖራቸዉ ተቀባይነት አይኖርም። በተለይ ጨቋኝ አገዛዝ፤ ከአገዛዙ በመነጨ ሁኔታ ገጽታዉ የተበላሸ ስለሆነ፤ ከተቃዋሚ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር የሚኖረዉ ገጽታም ያንኑ ያህል ያደፈ ይሆናል። በተለይ ዉስጣዊ የገዥዉ ፓርቲ ፖሊሲ ለዜጎች የማይመች ከሆነ በዉጪዎች ዘንድም የሚኖረዉ ገጽታ ያን ያህል የሚበላሽ ስለሆነ፤ ከዉጪ ይመጣል ተብሎ የሚለፈፈዉ እንቨስትሜንት ወይም ባለሀብት ራሱ በራስ የመተማመን ስሜት አይፈጠርበትምና ብቅ አይልም። ስለሆነም በአገር ደረጃ ያለዉ የአመራር ፖሊሲ በአንድ ወገን የተንሸዋረረ ከሆነ ያች አገር ትክክለኛ የዕድገት መስመር፣ ትክክለኛ የፓርቲ ፖለቲካ ወይም አስተዳደር እያራመደች አይደለችም ብሎ መደምደም ይቻላል።

የፖለቲካ መስመር ማለት እያንዳንዱ ሰዉ በአንድ ቡድን ዉስጥ ታቅፎ በዋናና መሠረታዊ ጉዳዮችን በማማከል ሊሰሩ የተስማሙበትን ዓላማ የሚያራምዱበት ነዉ። ሁሉም አባላቱ አንድ ዓይነት አቋም አላቸዉ ማለት አይደለም። ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ጥናት የግለሰቡን፣ የቡድኑን፣ የአገሩን፣ ከዚያም የዓለም አቀፉን ሕብረተሰብ የዉሳኔ አሰጣጥ ሂደትን፤ ከፍ ሲልም በመንግስት ደረጃ የዉሳኔ አሰጣጥና አተገባበር ሂደትን ያጠቃልላል። ከዚህ የዉሳኔ አሰጣጥና አተገባበር

የሚመነጨዉ የፖለቲካ ባህል ደግሞ የሕብረተሰቡን እሴት መሠረት አድርጎ፤ አብዛኛዉ ሕዝብ ሊከተል የሚፈቅደዉን የፖለቲካ አመራር ማሳየት የሚችል ነዉ። አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚከተለዉ የፖለቲካ ባህል ብልሹ ከሆነ፤ የዚያ ግለሰብ ወይም ቡድን በሕብረተሰቡ መሀከል የሚፈጥረዉ በጎ ስሜት አይኖርም፤ ወይም አለ ከተባለም በጣም አናሳ ይሆናል። ምክንያቱም በፍርሃት የሚደገፍ ፖለቲካ፤ ፈሪዉ ራሱ ፍርሃቱን የጣለ ዕለት የሚያስከትለዉ አንደምታ የጥፋት ይሆናል። ስለሆነም በፓርቲ ፖለቲካ እሳቤ ዉስጥ የሕግ የበላይነት ተሰምሮበት ሊከበር ይገባል። ሊሰመርበትና ሊታወቅ የሚገባዉ ነገር ቢኖር የፓርቲ ፖለቲካ ማለት ገዥዉን ግለሰብ ወይም ቡድን መደገፍ ወይም መቃወም ማለት ብቻ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ብዙ የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት የፓርቲ ፖለቲካ አማራጭ ሐሳቦችን ለሕዝብ ማቅረብና የሥልጣን ምንጭ የሆነዉ ሕዝቡ እራሱ መሆኑን አምኖ መቀበልና ሕዝብ የሚሰጠዉን ዉሳኔ ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግን ግንዛቤ ማስጨበጥ እራሱ የፓርቲ ፖለቲካ ነዉ።

ፓርቲዎች እንደተቋቋሙበት የፖለቲካ መስመር ወይም ዓላማ መሠረት ፖሊሲ አዉጪዎች ሆነዉ ሕዝብና መንግስትን የሚያስተሳስሩ ኤጄንቶች ሲሆኑ፤ የፓርቲዉ አባላትና ደጋፊዎች ሕዝብን በማስተባበር ለሥራ የሚያነሳሱ ናቸዉ። በመሆኑም አንድ ፓርቲ በአጠቃላይ ወይም የአንድ ፓርቲ የአከባቢ አመራር ከሕዝብ ፍላጎት ዉጭ ዉሳኔዎችን የሚያስተላልፍና የሚተገብር ከሆነ፤ የዚያ መንግስትና የሕዝቡ ግንኙነት እንደተቋረጠ ይቆጠራል። ለምሳሌ በአገራችን የሚገኙ ገዥ ፓርቲም ይሁን ተቃዋሚዎች የተቋቋሙበትን ዓመት በዓል የሚያከበር ከሆነና የአንድ አከባቢ ሕዝብ ወይም የመንግስት ሠራተኛ ከፍላጎቱ ዉጭ ለበዓሉ ማድመቂያ ወይም ለተዛባ ምርጫ መዋጮ እንዲያዋጣ የሚገደድ ከሆነ፤ ወይም የያዘዉን ሥልጣን ተገን በማድረግ የሰዉ ኃይልን ጨምሮ ማንኛዉንም የመንግስትን ሀብት ለፓርቲዉ ሥራ የሚጠቀምበት ከሆነ፤ በፓርቲዉ ምክንያት የሕዝብና የመንግስት ግንኙነት እንደተቋረጠ ይቆጠራል። ምክንያቱም፤ በፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ ፓርቲዎች ሕዝብንና መንግስትን የማገናኘት ሚናቸዉን መጫወት

የሚችሉት በመጀመሪያ ለራሳቸዉ ታማኝ መሆን ሲችሉ ብቻ ነዉ። በኢትዮጵያ ዉስጥ እንደዚህ ዓይነት የተዛባ ግንኙነት ስለመኖሩ ብዙም ክርክር የሚያስፈልግ አይደለም።

የፓርቲ ፖለቲካ በምናወሳበት ጊዜ ፖለቲካ ራሱ ምንድን ነዉ? የሚለዉን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል። ይህንን ጥያቄ መመለስ ቀርቶ መስማትም የማይፈልጉ ሰዎች ቀላል ቁጥር የላቸዉም። ፈልገነዉም ሆነ ሳንፈልገዉ የፖለቲካ ነገር ከመላ ሕይወታችን ወይም ኑሮአችን ጋር የተያያዘ ነዉ። ለምን እንደማይፈልጉት መናገር የሚፈልጉት በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸዉ። እንዲያዉም አንዳንዶች በምክንያት ባልተደገፈ ሁኔታ ፖለቲካንና ኤሌክትሪክን አያይዘዉ እራሳቸዉ ፈርተዉ ሌሎችንም ማስፈራራት የሚፈልጉ ኃይሎች ቁጥር ሰፊ ነዉ። ብዙዎች ካለማወቅም የተነሳ ስለሚሆን ፖለቲካና ሁለንትናዊ ሕይወት እንዴት እንደሚያያዙ ማሳወቅ ከሚመለከታቸዉ የሚጠበቅ ይሆናል።

ፖለቲካ የሚለዉ ቃል ሦስት ትርጉሞች፤- የፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ የፖለቲካ ሂደትና የፖለቲካ ሥልጣን ትርጉሞችን ያዘለ ነዉ። በፖለቲካ እንቅስቃሴ ዉስጥ የሕዝብ ጥያቄ የሚነሳበትንና በተነሳዉ ተቃርኖ ላይ ተመስርቶ የሕዝብ ፍላጎትን የሚያሟላ ለጥያቄዉ መልስ የሚገኝበት ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል። ይህንን የሕዝብ ጥያቄ የሚያነሳሱ የፖለቲካ ኃይሎች የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ሠላማዊና ኢ-ሠላማዊ የትግል ስልቶችን፤ ወይም ሁለቱንም በመቀላቀል የሚጠቀሙ ኃይሎች እንዳሉ እንረዳለን።

የፖለቲካ ሂደት ደግሞ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ቀጣይ ሲሆን፤ የፖለቲካ ሰዎች፣ ቡድኖችና ማህበራት ሁለት አቅጣጫዎች ይኖራቸዋል። አንድም የራሳቸዉን ፖሊሲ እያሰረጹ፤ በሌላም በኩል በወቅቱ ሥልጣን ይዞ የሚገኘዉን ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ፓርቲ በፖሊሲ አቀራረፅና አተገባበር ላይ የሕዝብን ፍላጎት እንዲያንፀባርቅ ጫና በመፍጠር በጥልቀት መስራት ነዉ። በፖለቲካ ሂደት ዉስጥ በተቻለ መጠን የራስን ፖሊሲ ማስረፅ፣ ወይም የፖለቲካ እንቅስቃሴ በማድረግ ገዥዉ አካል የፖሊሲ

አካሄዱን እንዲያሻሽል አሊያም ጨርሶ እንዲነሳ ግፊት ማድረግ አንዱ ተመራጩ መንገድ ይሆናል። በፖለቲካ ሂደት ዉስጥ በተቻለ መጠን የራስን ፖሊሲ ማስረፅ ሥልጣን መያዝ ወይም በሥልጣን ላይ ያለዉም አካል የተወሰነ የሕዝብ ይሁንታ ካለዉ በምክንያታዊነት በማሳመን የፖሊሲ አቀራረፅና አተገባበር ላይ ለዉጥ እንዲያደርግ ገንቢ ግፊት ማድረግ ነዉ።

የፖለቲካ ሥልጣን የሚባለዉና አንድ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ፓርቲ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አድርገዉ የፖለቲካ ሂደቱ ሥር ከሰደደ በኋላ ሕዝባዊ ተቀባይነት በማግኘቱ ሥልጣን የሚያዝበት ሁኔታ የሚፈጠርበት ሲሆን፤ ይህ አካሄድ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አምባገነንነት ሥር በሰደደባቸዉ አገሮች ዉስጥ በቀላሉ የሚታሰብ አይሆኑም። የፖለቲካ ሥልጣን የያዘ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ፓርቲ የመረጠዉንም ሆነ ያልመረጠዉን ሕዝብ ጥቅም በማይጎዳ ዓይነት ሁኔታ ዘለቄታዊነትን ጠብቆ ዉሳኔ መስጠት ሲገባ፤ እንዲያዉም ከምርጫዉ ዉጤት ጋር በተያያዘ የጠረጠሩትን ተቃዋሚ ብቻ ሳይሆን ያልመረጡትንም ጭምር በጥቅሉ ማመስገንና ያልመረጠዉን ለማርካት ተግቶ እንደሚሰራ ቃል መግባት ይጠበቅበታል። በኢትዮጵያ ዉስጥ ግን የዚህ ግልባጭ ሁኔታ ሲሰራ አስተዉለናል። ይኼዉም፤ አርሶ አደሮች ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ሲጠይቁ የመረጣችሁት ተቃዋሚ ፓርቲ ያቅርብላችሁ የሚል በቀል አዘል መልስ የሚሰጣቸዉ ስለሆነ ነዉ። ስለሆነም የፓርቲ ፖለቲካ በምንልበት ጊዜ ምቹና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሁኔታን ለሕዝቡ መፍጠር ሲሆን፤ ዜጎችም በአገራቸዉ ጉዳይ የመሳተፍና ነፃ አስተሳሰብ ማራመድ መቻላቸዉ የሚታይበት ነዉ። ነፃ፣ አሳታፊና ዲሞክራሲያዊ ሁኔታዎች ሲኖሩ ፓርቲዎች የፖለቲካ ፕሮግራማቸዉን ቀርጸዉና ለሕዝብ አቅርበዉ ይሁንታ ወይም አሉታ መልስ ያገኙበታል። የፓርቲ ፖለቲካዉ ጉዞ ሻካራና ምህዳሩ የጠበበ ከሆነ፤ ዜጎች የመኖር ተስፋቸዉና የዜግነት ኩራታቸዉ መንምኖ ለሥራ ያላቸዉ ተነሳሽነት ይቀንሳል። ከዚህ መሠረተ ሐሳብ በመነሳት ነዉ የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ምን ዉስጥ እንደነበረ፣ እንዴት እየሄደ እንደሆነና ወደፊትስ ምን ሊጠብቀው እንደሚችል የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይህ መጽሐፍ ጥረት ያደረገዉ።

ስለፓርቲ ፖለቲካ ይህን ያህል ከተባለ፤ ፓርቲ ማለት ራሱ ምን እንደሆነ አንባቢያን ገና ከመግቢያው ጀምረው ግንዛቤ ማግኘት እንዳለባቸው ይታመናል። በእንግሊዘኛው ቃል ፓርት ማለት የአንድ ትልቅ ወይም ግዙፍ ነገር የተወሰነ ክፍል ወይም ክፍልፋይ (some but all of a thing) ማለት እንደሆነ መዝገበ ቃላቱ ሲገልፅ ኢንካርታ መዝገበ ቃላት (እኔው እንደተረጎምኩት)፤ ፓርቲ፣ ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው ሰዎች በአንድ ድርጅት ሥር ለዓላማቸው ግብ መምታትም አባሎች ለሥልጣን በታ የሚመራረጡበት አደረጃጀት እንደሆነ ይገልፃል። ልብ ይበልልኝ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው እንጂ አንድ ዓይነት ዓላማ ያላቸው አልተባለም።

ፓርቲ ለሚለው ቃል ትርጉም በመስጠት ያብራሩት ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌታሁን ዴለቦ፣ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ነው። እንደ እሳቸው አገላለጽ "የመደብ ዓላማቸውን በፖለቲካ፣ በኤኮኖሚና በማህበራዊ ፕሮግራም ያስተሳሰሩና ለእንቅስቃሴያቸው ርዕዮተ ዓለማዊ መሠረት በመስጠት ለበላይነት የሚታገሉ የአንድ መደብ ግምባር ቀደም አባላትን ያቀፈ የፖለቲካ ድርጅት ፓርቲ ይባላል" ብለዋል። ስለፓርቲ ፖለቲካም ሆነ ስለፓርቲ ትርጉም ይህን ያህል ከተጨበጠ የመጽሐፉ ርዕሰ ጉዳይና ትኩረት ስለአደረገው የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሁኔታ እናመራለን። መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

ጥሩነህ ገምታ ወዬሳ

**ማዉጫ**


አርእስት ገፅ
የመጀመሪያ ዕትም መግቢያ ....................................................i
የ2ኛ ዕትም መግቢያ............................................................v
መቅድም .........................................................................ix
**ምዕራፍ አንድ፡ ማዕከላዊ ንጉሳዊ አገዛዝ ጅማሮና ፍፃሜዉ**
የየጁ ሥርወ-መንግስት ፍፃሜና የካሳ ኃይሉ (ቴዎድሮስ) መነሳት ..1
ነጋሲያን ተክለጊዮርግስና ዮሐንስ አራተኛ ....................................35
አፄ ምኒልክና የተስፋፊነት ወረራ ........................................... 40
ኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ሥርአቱና የፓርቲ ፖለቲካ ጥንስስ.............60
የገበሬዎች ንቅናቄ.............................................................. 73
የራያና አሰቦ ሕዝብ ትግል..................................................... 74
የባሌ ገበሬዎች ትግል ........................................................... 76
የጎጃም ገበሬዎች ትግል ......................................................... 78
የወጣት ተማሪዎች ንቅናቄ...................................................... 79
የፋሽስት ጣሊያን ወረራና የዉጪ ተፅዕኖ ................................... 84
የሠራተኞች እንቅስቃሴ ......................................................... 91
ምዕራፍ ሁለት፡ **የወታደራዊ ደርግ አነሳስና ሊዳፈን የነበረው የፓርቲ ፖለቲካ ጥንስስ**..........................................................................103
መላዉ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ/መኢሶን........................... 118
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ/ኢሕአፓ .........................123
ቀይና ነጭ ሽብሮቹ.............................................................133
ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎች................................................169
የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ ................................. 185
የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ ...................................................188
ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት.....................................233
**ምዕራፍ ሦስት፡ ከሕወሓት/ኢህአዴግ እስከ ኢፌዲሪ መንግስት ምስረታና ተግዳሮቾ ........................................................................**250
ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ..........................................358
ቀለም አልባው ሽብር ...........................................................363
**ምዕራፍ አራት፡ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ የዉጪ ኃይሎች ሚና**
የተባበረዉ የአሜሪካ መንግስት/USA.......................................380
እንግሊዝ .........................................................................398
ሱዳን ..............................................................................407
ሱማሊያ...........................................................................413
በኢትዮጵያ የኤርትራ ፖለቲካ ተፅዕኖ ..................................... 417
ዓለም አቀፍ ድርጅቶች.......................................................... 426
**ምዕራፍ አምስት፡ ከፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ እንደመውጫ፡** 43I
**ምዕራፍ ስድስት፡ ስለፀሐፊዉ** ..............................................443
አባሪ 1..............................................................................
አባሪ 2..............................................................................
አባሪ 3..............................................................................
አባሪ 4..............................................................................
ዋቢ መፃሕፍት.....................................................................

# የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ

## (ከፊውዳል አርስቶክራሲ እስከ አብዮታዊ ዲሞክራሲ)

ምዕራፍ አንድ፡ **ማዕከላዊ ንጉሳዊ አገዛዝ ጅማሮና ፍፃሜዉ**

## የየጁ ሥርወ-መንግስት ፍፃሜና የካሳ ኃይሉ (ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) መነሳት

ከማስፋፋትም ሆነ ከማጥበብ አንፃር ሲታይ የአገረ መንግስት ግንባታ ሂደትና የሕዝቦች አብሮነት በአንድ ወቅት ላይ ተጀምሮ በዚያዉ ወቅት የሚጠቃለል አለመሆኑን ከኢትዮጵያም ሆነ ከተቀረዉ የዓለም አገሮች ታሪክ ግንዛቤ መዉሰድ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአጭርም ሆነ በረጅም ጊዜ ዉስጥ በአንድ ሥርአት ሥር መተዳደር ጅማሮም ሆነ በአገረ መንግስት ግንባታ ሂደት አብሮነትን የገነባዉ ሕዝብ ወይም መነጣጠል አጋጥሞ ከሆነ አብሮነቱም ሆነ መነጣጠሉ በምን ምክንያትና ሁኔታ እንደሆነ ማወቁ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤና ትዕግስትን የሚጠይቅ ነዉ። ከሌላ ወገን ጋር ብቻ ሳይሆን ከራስ ጋር ሞግቶም ሽንፈትን የመቀበል ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ይህንን የምለው ያለምክንያት አይደለም፤ በኢትዮጵያ የአገረ መንግስት ግንባታ ፖለቲካ ሂደት ውስጥ በተለይም በፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ከራስ ጋር የሚያሟግቱ የተወሰኑ ነጥቦችን ስለማነሳ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ሆኑ ሌሎች እንዲሁ፤ በኃይልም ሆነ በመግባባት አገራዊ አንድነትን ወይም ትስስርን በመፍጠር አብሮ መቆየትም ሆነ የትስስራቸው ውል እየከሰመ ሲመጣ፤ እንዲህ በቀላሉ የሚቻል ባይሆንም የዕድገት ሂደትን ተከትሎ መነጣጠልም እንደሚችሉ ይታወቃል። ከዚህ ጋር ደግሞ የተፈጠረዉ ትስስር ሲጀመርም በመግባባት ላይ የተመሰረተ ካልሆነ፤ በተለይም ወቅታዊ የአመራር ሁኔታዉ ግድፈት ኖሮት ከመሻሻል ይልቅ ጉድለቱ እየሰፋና እየገዘፈ በሄደ ቁጥር የነዚያ ሕዝቦች ትስስር እየላላ ሄዶ መራራቅን ሲበዛም መለያየትን ሊያስከትል እንደሚችል አሁንም ግንዛቤ መዉሰድ ይገባል። ነገሩን ግልፅ ለማድረግ በሕዝቦች መሀከል የመራራቅና የመለያየት ሁናቴ ሊከሰት የሚችለዉ ያንዱ ሕዝብ እሴትና ጥቅም በሌላዉ ሕዝብ እሴትና ጥቅም

ላይ ጫና የሚያሳድርበት ከሆነ ወይም የጫና ፈጣሪዉ ሕዝብ የገዥ ክፍል የሆኑ እሴቶች በተገዥዉ ሕዝብ እሴቶች ላይ በደል የሚያደርስ ከሆነ የመራራቁ ዕድል እየሰፋ እንደሚሄድ ይታወቃል። ማለትም ያንዱ ሁለንተናዊ የበላይነት በሌላኛዉ ኪሳራ ጎልቶ የሚወጣ ከሆነ፤ በመሐከላቸዉ መናቆር ተፈጥሮ እየሰፋ በመሄድ፣ መተሳሰቡ ደግሞ እያነሰ ይሄድና በመተሳሰብ ተኖረ ተብሎ የሚለፈፈዉ ታሪክ ራሱ ወደተረትነት ዝቅ ይላል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ልዩነትን የሚያሰፉ አምባገነናዊ ሥርአቶች የሰፈኑባቸውና አንድነታቸዉ የፈረሰባቸው የምስራቅ አዉሮፓ እና ምስራቅ አፍሪካ አገሮችን (ይኼው ስጋት ያለበትን ኢትዮጵያን ጨምሮ ማለት ነው) ምሳሌ መዉሰድ ይቻላል።

በዚህ ምክንያትም ነዉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአብሮነት ሕይወት የሕዝቦች ይሁንታ አግኝቶ ሳይሆን ገና ከጅምሩም በጠመንጃ ወረራ ላይ የተመሰረተ ስለነበር፤ እነሆ እስከዛሬም ከዚያ አባዜ እንዳይላቀቅ ተደርጎ ይገኛል። የኢትዮጵያ ታሪክ በውስጥ ግጭትና ከጎረቤት ሕዝቦች ጋር ጦርነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ነበር ብሎ አንዱ ቢናገር እዉነትን መግለጹ እንጂ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት አስብሎ ጣት የሚያስቀስርበት አንደምታ እንደማይኖረዉ ይታመናል። በተለይም አሁን በሃያ አንደኛዉ መቶ ዓመት ላይ ሆነን የፖለቲካ አካሄዱ በዲሞክራሲ ስም እየተማለ ስልጡን የሚባል የፖለቲካ አመራር መያዝ ስላልተቻለ፤ ሁሉንም የአገሪቱን ዜጎች በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ሥርአት የማይፈጥርና ሁሉንም ዜጎች በአገር ግንባታ ሂደቱ ዉስጥ የማያሳትፍ ስለሆነ፤ አንዱ ተጠቃሚ ሌላዉ ተጎጂ፣ አንዱ አሳዳጂ ሌላዉ ተሰዳጅ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጠራል። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ዕድገት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ተጠሪም ስለሆኑና የኢትዮጵያዊያንን ትስስር በጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንበት አንዱ መንገድ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አካሄድ (በአጼዎች ዘመን የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ባይታወቅም) በትንሹ አንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት ያህል ማለትም ወደኋላ ተመልሶ ከአፄ ቴዎድሮስ የአገዛዝ ዘመን ጀምሮ መፈተሹ ስለእዉነቱ የኢትዮጵያ ታሪክ ግንዛቤን ለማስቀመጥ ያግዛል ብዬ አምናለሁ።

የአፄ ቴዎድሮስን የግል ስብእና ለማንቋሸሽ ካልሆነ በስተቀር ምን የፓርቲ ፖለቲካ በዚያን ጊዜ ነበረና ነዉ ይህንን ጽሑፍ ከዚያ መጀመር ያስፈለገዉ? ብለዉ የሚጠይቁኝ ሰዎች አይጠፉም የሚል ጥርጣሬ ሊኖር ስለሚችል፤ እኔም መልሴ የዚያን ዘመን የፖለቲካ ሥርአት መልክ ጋር ተያይዞ ሰዎች በየአከባቢያቸዉ እየተሿደኑ ደም አፋሳሽ ውጊያ የተዋጉት ከቴዎድሮስ ጊዜ በፊትም የነበረ ቢሆንም በቴዎድሮስ ጊዜ ግን በጣም የባሰበትና የአንድን አከባቢ ሕዝብ ጨርሶ ለማጥፋት ከፍተኛ የቡድን ውጊያዎች እንደነበሩ በማሳወቅ በአርእስተ ጉዳዩ ላይ መፃፍ ይቻላል ከሚል እሳቤ እንደሆነ አመላክታለሁ። እንዲያዉም የቴዎድሮስ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ የመጥፎ አስተዳደር ወይም ሥርአት መነሻ ምሳሌ ጊዜ ተደርጎ ቢወሰድ አግባብ እንደሆነ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ማግኘት ይቻላል። ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ስለኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ግንባታ ነሐሴ 16/2012 ዓም በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ ለተሰበሰቡት የፓናል ተወያዮች ባቀረበዉና ባልታተመ የጥናት ጽሑፉ ውስጥ “የዛሬይቱ ሰፊዋ ኢትዮጵያ ሕብረ ብሔራዊ የነገስታት መንግስት የተፈጠረችው በ2ኛው የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግማሽ፤ የዘመነ መሳፍንት ከሚባለው ዘመን በኋላ ስለሆነና ዛሬም በጣም ሰፊ ቀውስ ውስጥ የከተተን ታሪካዊ ዳራም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ” ሲል እንደጠቆመዉ፤ እኔም ለዚህ ጽሑፍ መነሻዬን ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ለመጀመር ያቀድኩትም በተጠቀሰው ምክንያት እንደሆነ እገልፃለሁ።

ያፄ ቴዎድሮስን ጊዜ የመረጥኩበት ተጨማሪ ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዕዉነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ አካል ዉስጥ ባለራዕይ መሪ  ነበረ ወይስ የአፄ ቴዎድሮስ በትር ያረፈባቸዉ ሕዝቦች በአብዛኛዉ የወሎ ኦሮሞ ስለሆኑ፤ በኦሮሞ ሕዝቦች ላይ የደረሰዉ ችግር ሌሎች ሰዎችን ሳያሳስባቸዉ ቀርቶ እንደሆን፤ በብዙ ሰዎች አእምሮ ዉስጥ የሚመላለሰዉን ያህል በኔም እንዲሁ ሲመላለስ ስለነበረ አንድ ነገር መባል እንዳለበት አምኛለሁ።

ሁለተኛም የሦስት ሺህ ዓመት ዕድሜ አለዉ እየተባለ የሚፃፈዉም ሆነ የሚነገረዉ የኢትዮጵያ ታሪክ በእዉነቱ የማን ታሪክ ነዉ? የሁሉም የዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን ታሪክ ነዉ? ወይስ እንደ ዕብድ የሰዉ ልጅ ወስደዉ ልጄ ነዉ የሚሉት ዕብድ ዓይነት ሆነው የሌላ ሕዝብ ታሪክ ተወስዶ ነዉ? የሚለዉ ተጠየቅ የሁሉንም ወይም የአብዛኛዉን ሕዝብ ስሜት ይነካካልና ከታሪኩም ሆነ ከዛሬዉ ግንኙነት አንፃር ጭምር የሚጎረብጥ አንደምታ ስላለበት፤ ይህንን የሚጎረብጥ ክፍሉን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ ግንዛቤ እንዲወሰድበት ማድረግ የማይዘለል ሥራ የሚያስፈልግ ስለሆነ መነሳት ባለበት ቦታዎች ላይ አንስቻለሁ።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 25) የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከ1847 እስከ 1983 በሚለው መፅሐፋቸዉ ዉስጥ “ለካሣ ኃይሉ በኋላም አፄ ቴዎድሮስ ነፍጥ ማንሳት የመጀመሪያ ምክንያት የሆነዉ የግብፅ ተስፋፊ ሠራዊትን ለማገድ በአባቱ በኩል ወንድሙ የሆነዉን [የአጎቱ ልጅ] የደጃች ክንፉን የድንበር መከላከል ፌልሚያ ዓላማ በመውረስ በተስፋፊዎቹ ላይ የወሰደዉ እርምጃ ጉልበቱን እያጠናከረለት በመምጣቱ ነበር” ብለዋል። ቴዎድሮስ፤ የግብፅን ተስፋፊነትም ሆነ የቱርኩን ወረራ ተራ በተራ መክቶ በአሸናፊነት በመውጣቱና የውስጥ ባላንጣዎቹን አንበርክኮ፤ በ1847 ዘዉድ ስለጫነ የዘመናዊት ኢትዮጵያ (ዘመናዊነትና ሕዳሴ በአንድ ነገር ብቻ የሚገለፅ ከሆነ) መሠረት የጣለ ተደርጎ እንደሚገመት ይጠቀሳል። ሌሎች የአበሻ ታሪክ ፀሐፊዎች ደግሞ ካሳ ኃይሉ በመሳፍንት አገዛዝ ተበታትኖ የነበረዉን አገዛዝ ማዕከላዊ አስተዳደር ለመመስረት በአንድ የታሪክ አጋጣሚ የተከሰተ ሰው አድርገው ይቆጥራሉ። ዕዉነቱ ግን በታሪክ አጋጣሚም ይሁን በታሪክ መርገምት ይከሰት አይታወቅም፤ አፄ ቴዎድሮስ የደብረ ታቦር ሕዝብ ሕገ መንግስታዊ የንጉስ አስተዳደርን (constitutional monarchy) መሠረት ለመጣል ጅምር የሆነውንና ነገስታት ወይም ንጉሶች የፖለቲካ ኃይል (charisma) እንጂ የፖለቲካ ሥልጣን (executive power) እንዳይኖራቸዉ አድርጎ፤ ሕዝብ በውክልና ሥልጣን በመስጠት ራሱን በራሱ የሚመራበትን የየጁዎቹን

የእንደራሴነት አመራር፤ ምናልባትም ዛሬ ሰለጠነ የሚባለዉ ሕብረተሰብ የሚመራበትን የፌዴራል ሥርአት በኢትዮጵያም በአዲስ መልክ መሠረት ለመጣል የሄደበትን ታሪካዊ አካሄድ አጨናግፎ የአንድ ሰዉ ፈላጭ ቆራጭነት አገዛዝ የተጀመረበት ጊዜ ነበር።

የሥልጣን ሽግግር በሁለት መንገድ ማለትም በሠላማዊ ምርጫና በአመፃ (continuity and discontinuity) በሚፈጥር መልኩ የሚተላለፍ ይሆናል። ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር የሚባለዉ የቀደመዉ መሪ ሲሰራ የቆየዉን አዲሱ ሳያፈርስ፤ ወይም ነባሩን አመራር አጥላልቶ ሥራዉንም ሳያፋልስ፣ አዲሱ አመራርም የወጣበትን ሕብረተሰብ እስከ ማጥፋት ሳይደርስ እና የቀዳሚውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተረክቦ እያዳበረ የሚጓዝበት ነዉ። በአመፃ ወይም በአብዮት የሚመጣዉ የሥልጣን ሽግግር ግን ካለፈዉ ሥርአት ተያይዘዉ መተላለፍ የነበረባቸዉን በጎ ነገሮች ሳይቀር ያጠፋና ብዙ የሀገር ሀብትና የሰዉ ሕይወት ጭምር እንዲባክን ያደርጋል። ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር በማይኖርበት ሕብረተሰብ ዉስጥ ቀጣይነት ሊኖራቸዉ የሚችሉ እሴቶች ይቀሩና ምትክ የሌለው የሕዝብ ሀብት ለዘረፋ ይዳረጋል። የተካበተ ዕውቀት ያላቸዉና በሥልጣን ተረካቢዉ ዉስጥ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ዜጎች (ገለልተኛ የሚባሉ የመንግስት ሠራተኛ የመሳሰሉ ሁሉ ሳይቀሩ) ወይ እራሳቸዉ እንዲጠፉ/እንዲሞቱ ወይም ዕዉቀታቸዉ እንዲባክን ይደረጋል። አማፂያኑ ቢጠቀሙበትም እንኳን ለጥፋት ዓላማ እንጂ ለበጎ አይሆንም። በዉጤቱም የሕዝብ እሴቶች ተያያዥነት ወይም ተከታታይነት ወይም ቀጣይነት ይቋረጣል ማለት ነዉ።

በዚህም መሠረት ነዉ አፄ ቴዎድሮስ በወቅቱ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት ዉስጥ ሥር ሊሰድ ይችል የነበረዉንና በዚህ ባለንበት ወቅት ላይ እንደ አዲስ ተጀምሮ ብዛት ያላቸው ዜጎች የምንወዛገብበትን ያልተማከለ አስተዳደር ወይም ፌዴራላዊ አስተዳደር ማለትም ከንጉሳዊ አገዛዝ ወደ ሕዝብ እንደራሴነት መሸጋገር የተጀመረዉን ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ያጨናገፈ የአጋጣሚ መርገምት የሆነ ሰዉ ነበር ለማለት የተፈለገዉ።

እንዳዉም በኢትዮጵያ ዉስጥ ሲነድና ሲቀጣጠል የቆየዉና ዛሬም ድረስ የሚታየዉ በኃይል ላይ የተመሠረተ የሥልጣን ሽግግር ከአፄ ቴዎድሮስ ሥልጣን መቆናጠጥ ጋር መሠረቱን የጣለ መጥፎ ቅርስ መሆኑ አያጠራጥርም።

አፄ ቴዎድሮስ ሥልጣንን የቀማዉ ከየጁ ሥርወ-መንግስት የመጨረሻ እንደራሴ ከትንሹ ራስ አሊ ወይም ከዳግማዊ አሊ ነበር። በማንኛውም መስፈርት የሥልጣንም ሆነ የሌላ ሀብት ቅሚያ ሰላማዊነትን አያመለክትም። ትልቁም ሆነ ትንሹ አሊዎች የየጁ ሥርወ መንግስት ቀጣዮች ነበሩ። ትልቁ ራስ አሊ ቢትወደድ ተብለዉ የደብረ ታቦር ሕዝብ የሰጠውን የሕዝብ እንደራሴነት ውክልና በመያዝ ነበር ሥልጣን ላይ የወጣዉ። ልብ ሊባል የሚገባ ነገር ቢኖር በዚያን ጊዜም ቢሆን ንጉስ አልነበረም ለማለት አይደለም። ነገር ግን ንጉሰቹ ወይዛዝር ወይም ግንብ ጠባቂ ንጉስ ተብለዉ መቀመጥና ሕዝቡ ለተወሰነ ሥነ ሥርዓት ሲፈልጋቸዉ ብቻ ከመገኘት በስተቀር የሕዝቡን የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን ተከታትሎ የሚፈጽመዉ ሕዝብ የወከለዉ ቢትወደድ እንደራሴዉ ነበር፤ ንጉሱ በሕዝብ ዘንድ ግርማ ሞገስ ቢኖረውም በተጨባጭ የማስፈጸም ሥልጣን የሌለው ማለት ነው። ሕገ መንግስታዊ ሞናርኪ እንደ ማለት ነው። ሕዝብ ጊዜው በፈቀደው አሰራር እንዴራሴውን ይወክላል፤ የወከለዉን እንደራሴ ካልፈለገው ወይም ጥፋት ካገኘበት ሕዝቡ ራሱ ሊያወርደዉ ሥልጣን ያለዉ ጭምር መሆኑን ያሳያል ማለት ነዉ። ያለምንም ጥርጥር የፖለቲካ አመራሩ በአፄ ቴዎድሮስ ባይጨናገፍ ኖሮ በዚያን ወቅት ሊያቆጠቁጥ የነበረዉ የሕዝብ የሥልጣን ምንጩነት የነበረበት አስተዳደር ዛሬ ዲሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ አስተዳደር ወይም ሕገ መንግስታዊ ሞናርኪ ወደምንለዉ ያድግ እንደነበር ብናስብ አልተሳሳትንም። ስለዚህ የአፄ ቴዎድሮስ መነሳትም ሆነ ሥልጣን መቆናጠጥ የኢትዮጵያን ወደ ሕዝባዊ የውክልና ሥርአት የፖለቲካ ጉዞን ከጅምሩ ያቀጨጨ ነበር ለማለት እንችላለን። አፄ ቴዎድሮስ የደብረ ታቦርን ሕዝብ እንደራሴ የመወከል ሥልጡን ጅማሮን ያጨናገፈ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የአከባቢ አስተዳደሮች ወደዚያ የውክልና ሥልጣን

እንዳያድጉ ያደረገ መጥፎ ምሳሌ ነበር ሊባል ይገባል ያልኩትም ለዚሁ ነዉ።

በሌላም በኩል ከአፄ ቴዎድሮስ በፊት የነበረውንና እሱ አስተካከለው ተብሎ የተጠቀሰዉ የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ማለትም እአአ ከ1761 እስከ 1845 የነበረዉና ቢያንስ ለሰማኒያ አራት ዓመታት በየጁ ሥርወ መንግስት እጅ የቆየዉን ሥርአት፤ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ምንም አግባብነት በሌለዉና ከመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም ከመፃፈ መሳፍንት ቁጥር 21-25 የተጠቀሰዉን ወደ ወቅቱ ኢትዮጵያ በማምጣት “በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉስ አልነበረም፤ ሰዉ ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየዉን ያደርግ ነበር።” ተብሎ የተፃፈዉን ያለቦታዉና ሁናቴ ወስዶ በመተርጎም ዘመነ መሳፍንት ብሎ በመሰየም ነው። በመጽሐፉ ላይ የተፃፈዉን እንኳን በአግባቡ እንረዳ ቢባል ንጉስ ባልነበረበት ሁኔታ “ሰዉ ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየዉን ያደርግ ነበር” የተባለዉን ብንወስድ መልካም መስሎ የታየዉን ማድረግ ያኔም ሆነ ዛሬ ምንም ክፋት እንደማይኖረዉ ነዉ። መልካም መስሎ የታየዉን ይፈጽሙ የነበሩት ደግሞ ማንም ሳይሆን የአከባቢው ገዥዎች ናቸው። ወይም እንደ ኢትዮጵያ የታሪክ ጸሐፊዎች በዘመኑ የነበሩ መሳፍንቶቹ ናቸዉ ማለት ነዉ። እንግዲህ፤ አፄ ቴዎድሮስ ወደኋላ የመለሰው ይህንን መልካም መስሎ የሚታየዉንና የተደረገዉን ሥራ ስለሆነ የቴዎድሮስ ሥራ ከልማቱ ጥፋቱ ያመዝናል ማለት የሚቻለውን ድርጊት የታሪክ ተመራማሪዎች ሊያመዛዝኑት የሚገባ ጉዳይ ይሆናል።

በርግጥ ከካሳ ኃይሉ በፊት ማለትም እንደ እነሱ አጠራር በዘመነ መሳፍንት ከአመራር አንፃር ደካማ ጎኖች አልነበሩም ብሎ መካድ የማይቻል ቢሆንም፤ ከ1761 ጀምሮ ካሳ ኃይሉ ሥልጣን እስከቀማበት 1847 ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ የአከባቢዉ ገዥዎች ደካማ ጎን ነበሩ ተብለዉ የሚጠቀሱት፤ የትግራዩ ራስ ሚካኤል ስሁል ሲበዛ አምባገነን የነበረና የሥልጣን ጊዜዉም በአጭር የተቀጨ፣ አሊ ዳንጉል የየጁ ኦሮሞ መሪ የነበረ ከሌሎቹ የሕዝብ እንዴራሴዎች በመነጠል የራሱን ሥርወ

መንግስት ለመመስረት ጥረት ያደረገና የክርስትና ሃይማኖት መሪዎች በጥምቀቶች በመከፋፈል አንዱ በሌላዉ ላይ የበላይነትን ለማግኘት ይወዛገቡ የነበሩበት ሁኔታ የሚጠቀስ ይሆናል። በመሀከላቸዉ በተፈጠረዉ አለመግባባትም የማሙዶች የሥልጣን ሽኩቻ አብሮ ሊያገረሽ የቻለበት ጊዜም ነበር። በዚህም ምክንያት የገዥዎቹ እርስ በርስ መሻኮት የወሎን ግዛት የጦረኞች መረማመጃ በማደረጉና በማዳከሙ የሸዋና የትግሬ መሳፍንቶች አንዱ በሌላዉ ላይ የበላይነትን ለማግኘት የተፋለሙት በወሎ ምድርና አከባቢዉ ላይ በመሆኑ ማዕከላዊ አስተዳደሩም የተዳከመበት ጊዜ ነበር።

በየጁ ሥርወ-መንግስት ጊዜ የነበረዉ የሰሜኑ ግዛት በተለይም ደብረ ታቦርና አከባቢዉ እንዲህ በተለያዩ መሳፍንቶች የተከፋፈለች ያልነበረች ቢሆንም፤ የአፄ ቴዎድሮስ መነሻ ምክንያት ታቦር ዋሚ (2006፡ 295) <u>የውገና ድርሰቶችና እዉነተኛ ታሪኮች</u> በሚለዉ መፅሐፉ አህመዲን ጀበልን ጠቅሶ እንደፃፈዉ “ይህ የታሪክ ወቅት ራሱን ከሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ጋር የሚያዛምደዉ ገዥ መደብ ኃይል የተዳከመበት እና በሰፊዉ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ሙስሊም በነበሩና በኋላ ግን ክርስትናን በተቀበሉ የኦሮሞ ራስ ቢትወዴዶች ተጠናክረዉ የነበሩበት ወቅት ነዉ።” ብሏል። ምንም እንኳን እነዚያ መናቆሮች ቢኖሩም ተክለፃድቅ መኩሪያ በታቦር ዋሚ (2006፡ 296) እንደተጠቀሰዉ “ከሁሉ መሳፍንት የየጁና የወሎ ተወላጆች ከትልቁ ራስ አሊ ጀምሮ እስከ ትንሹ ራስ አሊ ድረስ ያሉት በርታ ብለዉ ስለተከታተሉ፤ ከትግራይም ከነራስ ወ/ስላሴ፣ እንደጃች ሳባጋዲስ፣ ከጎጃም እነራስ መርዕድ፣ ከዳሞት እነደጃች ዘዉዴ፣ ከላስታ እነራስ አስራት፣ በየጊዜዉ ቢነሱም በጠቅላላዉ በዘመነ መሳፍንት ደንበኛ የማዕከላዊ የጎንደር መንግስት ገዥዎች እነዚሁ ወራሼህ የሚባሉት የየጁ ኦሮሞ ባላባቶች እነራስ አሊ ነበሩ።” በማለት ገልጿል።

አፄ ቴዎድሮስ እያንዳንዱን የአከባቢ ገዥ ተራ በተራ ከደመሰሰ በኋላ በሁሉም ገዥዎች ላይ ንጉሴ ነገስት ሆኖ ለመቆየት አስበ ሕልሙም ይዞለት የተወሰነ ጊዜ ቢቆይም፤ ግን ብዙም ባለመው ሁኔታ

አልዘቀለትም። ያንን ሕልም ለማሳካት ከውጭ አገር መንግስት በተለይም ከእንግሊዝ ንግስት ቪክቶሪያ መሳሪያ ለማግኘት ደብዳቤ ተፃፅፏል፤ ምንም የጦር መሳሪያ ዕውቀት የሌላቸውን የውጭ አገር ሚስዮናዊያን ሳይቀሩ የጦር መሳሪያ እንዲሰሩ አስገድዷል፤ አንዲት መድፍ ለመስራት የቤተክርስቲያን ንብረት ሳይቀር ዘርፏል። እያንዳንዱ እርምጃ ተመልሶ የንጉሱን የሥልጣን ገመድ ያሳጠረ ነበር እንጂ ለመፍጠር ያቀደዉ አገዛዝ ኢትዮጵያን ለማዘመን ቀዳሚ መሠረት የጣለ ነው ብለው ደጋፊዎቹ እንደሚያወድሱለት አልነበረም። ከአከባቢዉ ዝቅተኛ ገዥዎች እና ሊገዛቸዉ ከአሰባቸዉ ሕዝቦች ጋር ተመልሶ አንዳችም ወዳጅነት ሳይፈጥር አሳፋሪ ሞትን ሞቷል። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 31) ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሐፉ "... ቴዎድሮስ ሀገሪቷን በዘመናዊ መንገድ ለመምራት የሚያስችለዉን ንድፍ በደንብ ካለመቅረፁም ሌላ፤ በሚወስዳቸዉ ተቃራኒ እርምጃዎች ምክንያት ከዓላማው ሊደናቀፍ በቃ።" ብሏል። ስለሆነም አፄ ቴዎድሮስን ራዕይ የነበረዉ መሪ አድርጎ ማሰብ የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን የሰሜኑ የኢትዮጵያ ሕዝብን በተለይም ገዥዉን ክፍል የበላይ አድርጎ አጉልቶ ለማውጣት ሲያያዝ የመጣ ተንኮልና የሸፍጥ ፖለቲካ ከመሆን አይዘልም።

በርግጥ በወቅቱ የአዉሮፓ መንግስታት ያደርጉት እንደነበረዉ ሁሉ ቴዎድሮስም በሁለንተናዊ መልኩ አንድ በኤኮኖሚና በወታደራዊ አሰላለፍ ጠንካራ የሆነች የኢትዮጵያ ግዛት እንዲትኖር፤ በተለይም በአደረጃጀት የጎለበተ፣ በሥነ ሥርአት የታነጸና በመሳሪያ የተሟላ ሠራዊት እንዲኖር አልሞ መነሳቱና በተለይም የቴክኒክ ክህሎት አገሪቱ ዉስጥ እንዲገባ መሻቱ አንድ እርምጃ ወደፊት ለመራመድ ራዕይ እንደነበረዉ ግንዛቤ ቢያስጨብጥም፤ በሃያ አንደኛ መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ስንመለከት ግን፤ እስከዛሬዉ ሃያ አንደኛዉ መቶኛ ዓመት ድረስ ያልዘመነች ኢትዮጵያን መሠረት የጣለ መሪ አድርጎ ማሰቡ ወይም መሳሉ በአሁኑ ትውልድ ዘንድ ሊከብድ ይችላል። ባለራዕይ ነበር ከተባለም ያንን ራዕይ ሥራ ላይ ያዋለበት ስልት ከወዳጅነት ይልቅ የውስጥና የውጪ ጠላት እንዲበዛበት ያደረገ ነበር። በሌላም በኩል በእጅ ጥበብ ሙያ

እንዲሰለጥኑ የሚደረጉት ሰዎች ሳይቀር በሕብረተሰቡ ዉስጥ የተገፉ፣ የተገለሉና ዝቅተኛ ቦታ የተሰጣቸዉ ክፍሎች የሆኑ ሙስልም፣ የኦሮሞ ምርኮኞችና ፈላሾች ስለነበሩ ሐሳቡ ከፋፋይና ዘረኛ የነበረ ነው። በተለይም ዛሬ ድረስ አይነኬ ሆኖ ያለዉንና በቤተመንግስት አከባቢ የሚያሳድረዉ ተፅዕኖ ቀላል ያልነበረዉን የቤተክርስቲያን መሬትና ንብረት መውሰድና ለዜጎችና ለወታደሮቹ ማደሉ የእንጀራ ገመዱን ከመበጠሱም በላይ የአገዛዝ ስልቱ አፄ ታሪካዊ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ለመመለስ የቁም ሕልም ታልሞ ካልሆነ በስተቀር በጎ ምሳሌነቱ የቀጨጨ ነዉ።

በሌላም በኩል ተክለፃዲቅ መኩሪያ ስለካሳ ኃይሉ (ቴዎድሮስ) አስተዳደግ እንደፃፉት "… ሽፍትነቱን ትቶ ከደጃች ጎሹና ከራስ ዐሊ ቤት በነበሩ ጊዜ የቤተ መንግስት አስተዳደግና የወታድርነት ሥራ ሲለምዱ ኖሩ" ከሚለው የአንድ ወቅት ቆይታ ሁኔታ በስተቀር፤ ዐፄ ቴዎድሮስ የነጋሲነት ዘር እንዳልነበረው፤ [በተጨማሪም] "አባታቸው እንጂ እናቲቱ ባላባትነት የላቸውም፤ እንዲያውም [እናቲቱ] በድህነት ምክንያት ኮሶ ይሸጡ ነበር ያሉት" በወቅቱም ቢሆን ቴዎድሮስ የሽፍታ ባህርይ ተላብሶ የሥልጣን ጥማቱን ለማርካት እንጂ የአመራር ክህሎት ለማግኘት የሚያስችለው ሁኔታ ውስጥ እንዳልነበር ያሳያል። በዛሬው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዕድገት ደረጃ ላይ ሆነን ስንመለከት ደግሞ ካሳ ኃይሉ የቅማንት ብሔረሰብ አባል በመሆኑ ከወሎና ጎንደሬዎች በኩል በግልም ሆነ እንደሕዝብ ይደርስበት የነበረውን ተፅዕኖ በሽፍትነት ለመከላከል አስቦ የተነሳ እንጂ በርግጥ ንጉስነት ወይም የሕዝብ አስተዳደር ለመምራት የተንቀሳቀሰ አይመስልም።

ስለሕይወቱና አገዛዙ እዚህ ላይ ገታ አድርገን፤ ስለአፄ ቴዎድሮስ አሟሟት የተፃፈዉ በአብዛኛዉ ለማለት ይቻላል፤ የጀግንነት ጎኑን በማጉላት ነበር። ይኸዉም የእንግሊዝ ዜጎችን ለማስፈታት ለመጣዉ የናፒየር ጦር እጅ ላለመስጠት ብሎ ወዳጆቹን በማሰናበት የራሱን ሽጉጥ ጠጥቶ እንደሞተ የሚተርክ ነዉ። "ንጉሱም በመጨረሻ ባላቸው ኃይል ከጠላታቸው

ተዋግተው ድል ስለሆኑ ባጠገባቸው የቆሙትን የሚወዷቸውን ወታደሮች ስመው እንዲሸሹ ካሰናበቷቸው በኋላ እንግሊዞች ለመማረክ የታችኛውን በር ሰብረው እየተጋፉ ሲገቡ ዐፃ ቴዎድሮስ ወደ ላይኛው በር አልፈው በጨበጡት በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን ገድለው ወድቀው ተገኙ።" በማለት ተክለፃድቅ መኩሪያ ጽፈዋል። ወደ እዉነቱ የሚቀርበዉ ግን ቴዎድሮስ ተጠልለዉበት የቆየዉ የመቅደላ አምባ በታሪካዊ ተቀናቃኞቹ በመስተዋትና ወርቂት ጦሮች ክፉኛ ተከቢቦ ስለነበር፤ በተለይም ልጇ በግፍ የተገደለባት ወርቂት ጦሯን ይዛ ይህንን ሽፍታ (አፄ ቴዎድሮስን) ተጠግታ ቢሆንና አፄዉም ለዚህች ሴት እጅ ከመስጠት ራስን መግደልን መምረጡ አንድ አማራጭ እንደሆነ ለአሟሟቱ ተጨማሪ ግምት ቢሰጠዉ ኖሮ ተገቢ ይሆን ነበር። አፄ ቴዎድሮስ በወርቂት እጅ እንኳን ባይሆን በወርቂት ጫና የሞት ፅዋዉን ለመጎንጨቱ ከተክለፃድቅ መኩሪያ በተቃራኒ ታቦር ዋሚ (2006፡ 381-82) ምንጭ ጠቅሶ እንደፃፈዉ "የናፒየር ጦር መቅደላ አምባ ጥግ ሲደርስ የወርቂትና የመስተዋት ሠራዊት ጥቃቱን አጠናክረዉና አምባዉን ተቆናጥጠዉ ነበር። … ቴዎድሮስም … ወደ ደቡቡ [የወርቂት ጦር ወዳለበት አቅጣጫ ማለት ነዉ] ለማፈግፈግ ሳያስቡ አልቀሩም። ነገር ግን አከባቢዉ … ዙሪያዉን የተዘጋ መሆኑን ስላረጋገጡና መፈናፈኛ ስላጡ እዚያዉ ቆይተዉ የሞት ፅዋቸዉን ለመጎንጨት ተገደዱ።" ሲል፣ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴም (2007፡ 43) "እንደ እዉነቱ ከሆነ ግን የቴዎድሮስ ነገር ያከተመዉ ገና ጦሩ [የናፒየር ጦር] ወደ መሀል አገር መንቀሳቀስ ሳይጀምር ነዉ" ብለዋል። ከፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ ጽሑፍ መረዳት የሚቻለዉ ቴዎድሮስ ገና ያከተመለት ወደመሃል መንቀሳቀስ ባልጀመረ የናፒየር ጦር ነዉ፤ ወይም ደግሞ ከናፒየር ጦር የበለጠ ሥጋት የፈጠረበት የወርቂትና መስተዋት ኃይል ነበረ የሚል አንደምታ ይኖረዋል።

በሽፍትነት ሕይወቱን የጀመረዉ ካሳ ኃይሉ የአስተዳደሩንና ወታደራዊ የበላይነቱን በኃፋት ያጠናከረዉ ንጉስ፤ ለሞቱም የመረጠዉ ሌሎች ንጹሓን ዜጎችን ይገድልበት በነበረዉ መቅደላ መሆኑ፤ ይሰፍርበት

ከነበረዉ ቁና ማመለጥ አለመቻሉን ያመለክታል። እዚህ ላይ ስለአፄ ቴዎድሮስ አሟሟትም ሆነ ስለወርቂት ጉዳይ አዲስ ታሪክ እንዲፃፍ ፍላጎት ኖሮኝ አይደለም። ነገር ግን ወርቂት አስፈላጊዉን ዕርምጃ በአፄ ቴዎድሮስ ላይ መዉሰድ እንደሚገባት ወይም እንደምትችል የቅርብ ግምት ማሳደር አንድ ሊዘለል የማይችልና ሊፈተሽ የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ለማስገንዘብ ነዉ።

ሌላው ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ነገር ቢኖር ቴዎድሮስ ለሰው ፍጡር ርህራሄ ያሳየበት ጊዜ ቢኖር ልጁ "ዓለማየሁ በተወለደበት ቀን ስለ ደስታቸው በጥፋት የታሰሩ አምስት መቶ እስረኞች መልቀቃቸው" እና በቁጥጥሩ ሥር የሚገኙ የውጭ አገር እስረኞችን ላለመግደል የወሰነው ጊዜ ብቻ እንደነበር ከተክለ ፃድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ከምናነብ በስተቀር ሰውዬው ሰብአዊ ርህራሄ ያልፈጠረበት ሰው እንደነበረ ይታወቃል። ሰብአዊ ርህራሄ ካለመላበሱም የተነሳ "በጥፋትም ያለ ጥፋትም የሚያዘውን ሰው ወንዱንም ሴቱንም ሕፃኑንም ባንድነት እየሰበሰቡ ሰቀላ ቤት ውስጥ እያገቡ ቤቱን ከውጭ እየዘጉ አዲስ ቅጣት ፈጥረው ያቃጥሉት ነበር።" በማለት ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ጽፈዋል።

እንግዲህ አፄ ቴዎድሮስ ይወስዳቸዉ የነበሩ ዕርምጃዎችን በማሰብና ያንን የመሰለ ራስን የማጥፋት ዕርምጃ መዉሰዱ አፄዉን የሚያጀግን ሳይሆን እጃቸዉንና እግራቸዉን በተቆረጡ፣ ከገደል በተወረወሩ ዜጎች ዘመዶች ፊት እጁ ተይዞ ቢቀርብ ኖሮ የሚጠብቀዉ ዕርምጃ ምን ሊመስል እንደሚችል፤ በተለይም ልጇ የተገደለባት ወርቂትም ሆነች ሌሎችም እናቶች በርሱ ላይ የሚወስዱትን ዕርምጃ ከመፍራት የተነሳ ቴዎድሮስ ያንን ዕርምጃ በራሱ ላይ መዉሰዱ ተስፋ ቆራጭ እና ማንም ይቅር የማይለዉ ፍጡር መሆኑን ማረጋገጡ እንደሆነ ከማሳየት በስተቀር፤ ሰዉ የሚራራለትም ሆነ እሱንም የሚያስጀግነዉ አንዳችም ነገር አልነበረም/የለምም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ስብዕናቸዉ የወረደና ልክ ከቴዎድሮስ ጋር ተመሳሳይ የአገዛዝ ሥርአት ያራምዱ የነበሩ ጨካኝ ገዥዎች ማለትም እነ ሂትለር፣

ዕዲ አሚን፣ ቦካሳ፣ አፄ ኃይሌ ሥላሴ፣ እንዴት እንደሞቱ መፈተሽ ይቻላል፡፡ ሂትለር መሞቱ ብቻ ሳይሆን አስከሬኑንም በአሲድ ያጠፋ ሰዉ ነበር፡፡ የዩጋንዳዉ ዕዲ አሚንና የማዕከላዊዉ አፍሪካ ሪፑብሊክ ንጉስ ነኝ ብሎ ራሱን የቀባዉ ጂን በደል ቦካሳ ከአገር ፈርጥጠዉ ወጥተዉ በሰዉ አገር ሜዳ ላይ ነፍሳቸዉ ጠፍታለች፡፡ አጽማቸዉ እንኳን ለአገራቸዉ አፈር ሳይበቃ ቀርቷል፡፡ የአፄ ኃይሌ ሥላሴ አስከሬን በስንት ፊለጋ የተገኘው ከመንግስቱ ኃይለማርያም መፀዳጃ ቤት ሥር መሆኑ የጨካኝ ገዥዎች መጨረሻ ምን እንደሚመስል ማሳያ ነው፡፡ እነዚህ ራሳቸውን አንጋሾች ጀግና የሚያስብላቸው ነገር እንዳለመኖሩ ሁሉ፤ በሰከነ አእምሮ ሲታሰብ ቴዎድሮስ እንዴት መገለጽ እንዳለበት ታቦር ዋሚ (2006፡ 627) ከላይ በተገለፀዉ መጽሐፍ የሚከተለዉን ብሏል፡፡ ካሳ ኃይሉ "የቤገምድር ሕዝብ የአስተዳደር ፍላጎትን ሰርዘዉ፤ ለነገስታቶቹ በቤገምድር ሕዝብ ዉሳኔ የተሰጣቸዉን ሥልጣን ነጥቀዉና ለብዙ ዓመታት አገሪቱን ሲያስተዳድሩ የኖሩትን ነገስታቶችን ሥልጣን ጭምር ዘርፈዉ "የሰለሞን ዘርነት" ሳይኖኖርባቸዉ የሰለሞን ዘር ነኝ እያሉ በማስወራት አስራ ሦስት የዕልቂት ዘመናትን የመሩና በጉልበታቸዉ ነግሰዉ አፄ የተባሉ ሰዉ ናቸዉ" ብሏል፡፡ "የቴዎድሮስ ዘመን ተወደደም ተጠላ የእልቂትና የመቅሰፍት ዘመን እንደነበር" ሰለሞን ስዩም <u>የኦሮሞ ጉዳይ እና የኢትዮጵያ ብያኔ</u> ብሎ በፃፈው መጽሐፉ ገጽ 193 ላይ ገልጾዋል፡፡ በዚህ መሠረት፤ ለቴዎድሮስ አደባባይ መሰየምም ሆነ መጀገን የሚገባው አይሆንም፡፡

## ነጋሲያን ተክለጊዮርግስና ዮሐንስ አራተኛ

የጊዜና ሁኔታዎች መመቻቸትን ሲጠብቁ የነበሩት የአፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞች የተለያዩ ቢሆኑም፤ በግንባር ቀደምትነት ግን አባቱ በቴዎድሮስ የተገደለበት የላስታዉ ዋግሹም ጎበዜ፤ በኋላም አፄ ተክለ ጊዮርግስ ተብሎ የነገሰዉን የቀደመ አልነበረም፡፡ ለዚህ ቀድሞ ለመንገሱ እገዛ ሊያደርግለት የቻለዉ ደግሞ የቴዎድሮስ ኃይል እየተዳከመ ሲሄድ የከዱት የቴዎድሮስ ሠራዊት አባላት እና መኳንንቱ ወደ ዋግሹም ጎበዜ

ስለተቀላቀሉ እንደሆነ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ይገልፃሉ። ቢሆንም ግን የተክለ ጊዮርግስ ንግስ ከሦስት ዓመታት በላይ አልዘለቀም። በእህቱ ባል (አማቹ) ተነጠቀ።

ሁሉም ሥልጣን የያዙ የቴዎድሮስ ተቀናቃኞች መንገዶች ሁሉ አልጋ በአልጋ ሆኖ ባያገኙትም የሸዋና የትግሬ ገዥዎች ራሳቸዉን ለማንገስ እሽቅድምድም ዉስጥ ገብተዉ እንደነበር እንረዳለን። በተለይም ደጃች ካሳ ምርጫ በኋላ አፄ ዮሐንስ 4ኛ እንግሊዞች በቴዎድሮስ ላይ ያደረጉትን ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን በከፍተኛ ደረጃ በማመቻቸቱና መንገድ በመምራቱ በውለታነት ተቆጥሮለት በወቅቱ ዘመናዊ የሚባሉ የእንግሊዝ የጦር መሳሪያዎች በእጁ ገብተዋል። ይህንንም ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ የደጃች ካሳን መሰሪ አካሄድን ሲገልጹ “እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ለመውጋት በመጡ ጊዜ ላገሩ እንግዳ በመሆናቸው በጣም ተቸግረው ነበር። በኋላ ግን የትግሬ ሕዝብ በደጃች በዝብዛ ካሳ ትዕዛዝ መውጫ መግቢያውን እያሳየ በራሱ አገር አሳልፎ በውጊያው ጊዜ በጦርነት ስለረዳ የእንግሊዝ የጦር ሠራዊት አዛዥ በጣም ደስ ብሎት ነበርና ዐፄ ቴዎድሮስን ድል አድርጎ በሚመለስበት ጊዜ … ከልክ ያለፈ ጥይትና ስንቅ ለደጃች በዝብዝ ካሳ አስረከባቸው። [ከዚህ በኋላ ይመስለኛል በአገኙት መሰሪያ በመተማመንም ለአማቻቸው ተክለ ጊዮርግስ] … እስከ ዕድሜ ልክዎ ድረስ እገዛልዎታለሁ ብለው የነበረውን ቃል አጥፈው እንደገና ለርስዎ አልታዘዝም ብሎ ላከባቸው።” በማለት ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ጽፈዋል። ተክለ ጊዮርግስ የካሳ ምርጫን እህት አግብቶ ስለነበረ የጋብቻ ወዳጅነታቸዉ የሚይዝ ቢመስልም ከናፒየር ጋር የተሞዳሞደዉ ካሳ ምርጫ የጋብቻ ዝምድናቸዉን ወደ ጎን በማድረግ በአገኘዉ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ በመታገዝ ተክለ ጊዮርግስን በጦር ገጥሞ ሐምሌ 5፣ 1863 አድዋ አከባቢ አሴም በምትባል ቦታ ላይ አሸንፎ ወደ ነጋሲነት ተሸጋግሯል።

መስተዋትና ወርቂት በዕድሜ በመግፋትም ሆነ ባልተቋረጠ የግጭትና ጦርነት ምክንያት በመዳከማቸው፤ በተለይም የመጨረሻ ኃይላቸዉን

በአፄ ቴዎድሮስ ከበባ ላይ ያሳለፉ ስለሆነ፤ ተወላጆቻቸዉም ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ የሥልጣን ተቀናቃኝነታቸዉን አጠናክረዉ ለመግፋት አቅም ባለማግኘታቸዉ ለፖለቲካ ሥልጣን መፋለም ያደረጉት ተነሳሽነት ጎልቶ አልወጣም። ቴዎድሮስን ለማንበርከክ የግንባር ቀደምትነቱን ሚና የተጫወቱት መስታዋትና ወርቂት ወደጎን ተደርገዉ ናፒየር ለካሳ ምርጫ በማድላቱም የአቅማቸው ማነስ ተስፋ ሳያስቆርጣቸዉ አልቀረም።

ጥር 13 ቀን 1864 ዮሐንስ አራተኛ ተብሎ ሥልጣን የጨበጠዉ ካሳ ምርጫ በአስራ ሰባት ዓመታት የአገዛዝ ዘመኑ ምናልባትም የዐፄ ቴዎድሮስ ኃይለኛነት አግዶት የቆየውን የግብፅን ወረሪ ጦር ለሁለት ጊዜ የመከተበት ጦርነትና በመጨረሻም ከደርቡሾች የተቃጣበት ወረራ አንገቱን በማስቀላት ሕይወቱን እስከ መብላት ደርሷል። ዐፄ ዮሐንስ ራሳቸዉ ለቴዎድሮስ መዉደቅ ምክንያቶች የነበሩትን በተለይም ዓላማን ለማስፈጸም የሕዝብ ቅቡልነትን ማጣትን በበቂ ሁኔታ ያልተረዳና የበኩሉን ጥንቃቄ ለመዉሰድም ያስተዋለ አይመስልም ነበር። ምክንያቱም ቴዎድሮስ ከቤተክህነት ጋር በመሬትና ለእግዚአብሔር ለመቅረብ በሃይማኖት ክፍሎች መሀከል የበላይነትን ለመጎናጸፍ ባደረጉት ትንቅንቅና በአከባቢዉ ላይ በክርስትና ሃይማኖት ዉስጥ የሰረፀዉን ልዩነት በትክክል ሳይገነዘብ ለማስተካከል ብሎ የወሰደዉ እርምጃ ምን ጉዳት ላይ እንደጣለዉ ዮሐንስም አልተረዳም። አፄ ዮሐንስ ለሥልጣኑ መሠረት ያደረገዉ የክርስትና ሃይማኖትን በመሆኑ፤ በተለይም የእስልምና ሃይማኖት በዮሐንስ ፋይል ዉስጥ ስለአልገባና የፈረደባቸዉ የወሎ ሙስሊም ኦሮሞዎች ክርስትናን ተቀብለዉ እንዲጠመቁ ወይም አገር ለቅቀዉ እንዲሰደዱ ማድረጉ የጠላቱን ቁጥርና ዓይነት እንዲጨምር አድርጎ፤ ለሕይወቱ መጥፋት መንገዱን ወለል አድርጎ ከፈተበት። ተከትሎም፤ ንጉሱ ደርቡሾችን አባርረዉ ሲመለሱ ወገባቸዉን ለመፈተሽ ጎራ ባሉበት ቦታ ጠልጣላ ያሉት ደርቡሽ አንገታቸዉን መቅላቱ ይወሳል። ኃይሌ ሥላሴ እንኳን ሳይቀር ስለ ዐፄ ዮሐንስ እንከን ስናገር “እስላሞችን በግድ ክርስቲያን ካልሆናችሁ ብለው ግፍ ስለሰሩ እግዚአብሔር በእስላሞች እጅ አሳልፎ ሰጣቸው” ብሎ በሥርአተ ንግሱ ላይ ተናግሮ

እንደነበር ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ጽፈዋል። ከቴዎድሮስ ባልተለየ ሁኔታ “የኢትጵያን አንድነት ለመደምሰስና ሕዝባችንን ባሪያ አድርጎ ሴቶቻችንንም ለማርከስ የሚፈልግ የእስላም ጦር መጥቶብናል …” ብሎ በማወጅ ንጉስ ዮሐንስ ከደርቡሾች አንፃር ብቻ ለመዋጋት የተጓዘበት አኳኋን ወደ ውስጥ ጭምር መመልከት የማይችል ሐሳበ ብኩን አድርጎታል። ይህ በንዲህ እንዳለ በደርቡሾች እጅ ሞተ ቢባልም ከዮሐንስ ሞት ጋር የተቀናቃኙ የምኒልክ ሴራም እንዳነበረበት የተለያዩ የጽሑፍ ማስረጃዎች ስለመኖራቸዉ ታቦር ዋሚ (2006፡ 494) አፈወርቅ ገብረየሱስን በመጥቀስ “የአፄ ዮሐንስ ሞት በአፄ ምኒልክ ሴራ እንጂ በወራሪዉ የደርቡሾች ኃይል፣ ጥበብና ችሎታ [ብቻ] አልነበረም” ሲል፤ ሌላዉ የሩሲያ ቀይ መስቀል መልዕክተኛና የአፄ ምኒልክ አማካሪና አድናቂ የነበረዉ አሌክሳንደር ቡላቶቪች ጽፎ ዶክተር አምባቸዉ ከበደ (2005፡ 191) በተረጎመዉ <u>ከእንጦጦ እስከባሮ</u> በሚለዉ መጽሐፍ ላይ በዮሐንስ ሞት ምኒልክ ደስተኛ እንደነበረ ሲያመላክት “ምኒልክም የዮሐንስን ሞት እንደሰሙ [ምናልባትም የሥልጣን ክፍተት ላለመፍጠር በሚመስል መልኩ] በአስቸኳይ ወደ ጎንደር ሄደዉ የንጉሰ ነገስትነቱን ዘውድ ጫኑ” ብሏል።

ቴዎድሮስ ጦር ሰብቆ በመመላለስ ተወዳጅነት የነበረውን የቤገምድር ሕዝብ አንጡራ ሀብት የሆነዉን የየጁ ሥርወ መንግስትን ያጠፋዉን ያህል፤ አፄ ዮሐንስም ያዉ የፈረደበትን የወሎን ሕዝብ በመጨፍጨፍ የወራሂማኖ መሐሙዶች ሥርወ መንግስትን አጥፍቷል። ክርስትናን ተቀብሎ የተጠመቀዉ ተጠምቆ ያልተጠመቀዉ ደግሞ አገሩን ጥሎ እንዲሰደድ ፈርዶበታል። ይህ ሕዝብን ከፈቃዱ ዉጭ የማስገደድ ድርጊት በትግሬ ገዥዎች ዘንድ አዲስ ክስተት እንዳልነበረ ቀደምት ታሪኮች ያወሳሉ። ከአፄ ዮሐንስ በፊት የትግሬ አከባቢን እአአ ከ1434 እስከ 1468 ይገዛ የነበረዉ አፄ ዘረዓ ያዕቆብ “ሰዉ ሁሉ ካልተጠመቀ በስተቀር እንዲገደል” አዝዞ እንደነበረ የታሪክ ማስረጃዎች አፍ አወጥተዉ ይናገራሉ። ድሪቢ ደምሴ ቦኩ (2011፡ 409) <u>Oromo Wisdom In Black Civilization</u> በሚለዉ መጽሐፉ ላይ እንደጠቀሰዉ “Unless somebody

is christian, even if he/she is the son/daughter of the king he/she should be killed; his/her nose and ears should be cut off.” በማለት አስቀምጧል፡፡ በአፄ ዮሐንስ የአገዛዝ ዘመንም “ቁርአን እቤቱ በመገኘቱ ምግብና ውሃ ተከልክሎ የሞተ አህመድ ሳዲቅ የሚባል ሙስሊም እንደነበረ” አህመዲን ጀቤል 3ቱ አጼዎች እና ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በተባለው መጽሐፉ ላይ ጽፏል፡፡ ከአስተዋጽኦ አንፃር ብንመለከት ግን ከማንኛዉም ጊዜ በበለጠ የውጪ ወራሪ ኃይል የተከሰተውና ከፍተኛ መከላከል የተደረገው በአፄ ዮሐንስ ጊዜ ስለሆነ፤ አፄው እራሱም ሆነ አጋፋሪዎቹ መስዋዕትነትን ከፍለው ባይከላከሉ ኖሮ የዛሬዋም ሆነ የያነዋ ኢትዮጵያ ይህንን ቅርፅ ይዛ አትገኝም ነበር ተብሎ ቢገመት ስህተት ላይ የሚጥል አይሆንም፡፡ ከዚህ በዘለለ ደግሞ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ዮሐንስ ለትግሬዎቹ የአስተዳደር ወይም የፖለቲካ ማዕከል እስከመመስረት የደረሰና ሊኮሩበት የሚገባ ንጉስ ነበር፡፡ ነገር ግን ከውስጥ ችግር ይልቅ፤ ሲያደቡ የኖሩት የውጭ ተቀናቃኞቹ ስለአገር ግንባታ ሥራዎች የማሰብ ዕድል ስላልሰጡት ትግራይን የኢትዮጵያ ማዕከል ለማድረግና የሀገረ መንግስት ግንባታውን ተልዕኮ አንዳችም ጋት ፈቀቅ ለማድረግ ባለመቻሉ የዛሬዎቹ የትግራይ ልሂቃንን ሊያኮራ የሚችል ሥራ አልሰራም፡፡ የዮሐንስ ጅምር ሐሳብ በ1967 ነፍስ እንዲዘራ በቀድሞዉ ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ/ማገብት፤ በዛሬዉ ሕወሓት ሊደገም የታሰበ ቢሆንም የወቅቱን ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታን ያልተከተለ በመሆኑ እምብዛም የተያዘላቸው አይመስልም፡፡ ቀጥሎ በሚመጡት አርእስቶች ውስጥ የምነካካ ቢሆንም የአፄ ዮሐንስን የትግራይን የፖለቲካ ማዕከል ለማድረግም ሆነ የሀገረ መንግስት ግንባታን ሕወሓት አንድም ከነበረባቸው የቆየ የኤኮኖሚ እና አስተሳሰብ ድህነት የተነሳ የሕዝብ እና የግለሰቦችን ሀብት ዘረፋ ላይ ከመሰማራት ወይም የአማራውን የገቸ መደብ ትብትብ ቢሮክራሲ ከራሱ አካሄድ አንፃር ለማሸነፍ ባለመቻሉ ከሩብ ምዕተ ዓመት በኋላ ወደ መጣበት ትግራይ አፈግፍጓል፡፡

## አፄ ምኒልክ፤ የማቅናትና የተስፋፊነት ወረራ

ሕዝብን አስተባብሮ ቴዎድሮስን መውጋት የነበረበት ንጉስ ኃይለ መለኮት በሕመም ስለሞተና ሕጋዊ ወራሹ የሚሆነዉ ልጁ ምኒልክ ገና አቅመ ንጉስነት ሳይሞላው ቴዎድሮስ የሸዋን ነጋሲ ለማስገበር በከፈተው ዘመቻ ውስጥ እሱን ምኒልክን ጨምሮ ሌሎችን ለመማረክና ሸዋዎች ደግሞ ላለማስማረክ በተደረገዉ ድብብቆሽ አፄ ቴዎድሮስ ቀንቶት፤ ከንጉስ ሃይለ መለኮት የተወለደዉ ምኒልክን በአስራ አንድ ዓመቱ ማርኮ ወደ ጎንደር ወሰደዉ። ለአስራ አንድ ዓመታት ያህልም ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በምርኮነት የኖረው ምንሊክም የወርቂት ወገኖች በአደረጉለት ድጋፍ ተረድቶ ከመቅደላ አምባ አምልጦ ወደ ሸዋ ተመለሰ። ምኒልክን በማስመለጥ የወርቂት ወገኖች በተጫወቱት ሚና የተናደደዉ ቴዎድሮስ የወርቂት ልጅን ጨምሮ ወሎዬዎችን ፈጀ።

በወርቂት ታግዞ ወደ ሸዋ የተመለሰዉን ምኒልክን ሸዋዎች በደስታ ተቀብለዉና ወደ አባቱ አልጋ እንዲመለስ ከአጎቱ በዛብህ ጋር ያደረገውን ውጊያ በድል እንዲወጣ አስቻሉት። ከተክለ ጊዮርግስ መሸነፍ በኋላ በንጉሴ ነገስት ዮሐንስ ላይ ለመሸፈትም የሸዋ ሰዎች እንዲተባበሩት ምንሊክ የክተት ጥሪ ከማወጁም በተጨማሪ ከውጪ ኃይላት ጋር በተለይም ጣሊያንን በመማጠን ወደ ደቡብ ነፃ ግዛቶች እንዲዘምት ያገዘዉን የጦር መሳሪያ ድጋፍ አገኘ። አምላክ ያንዱን ጉሮሮ ሲዘጋ የሌላዉን ይከፍታል እንደሚባለዉ ተረትና፤ መጋቢት 2፣ 1873 ዮሐንስ መተማ ላይ በጠልጣላ የሙስሊም አድፋጭ ተገድሎና ራሱ ተቆርጦ እንጨት ላይ ሲሰካ፤ ምኒልክ ንጉሴ ነገስት ዘኢትዮጵያ ሆኖ ሥልጣን ለመያዝ ጊዜ አልፈጀበትም። በመቀጠልም ቴዎድሮስና ዮሐንስ ጀምረውት የነበረዉን የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ ወደ ደቡብ ነፃ ጎረቤት ሕዝቦች አዞረ። የምንሊክን ወደ ደቡብ ዘመቻ ሰዎች እንደሚወግኑት የሕብረተሰብ ክፍል ወረራ ወይም ማቅናት ወይም የሀገረ መንግስት 'መልሶ ግንባታ' ይሉታል። ወረራም ተባለ ማቅናት ወይም ሀገረ መንግስት መልሶ ግንባታ ተባለ ድርጊቱ እንዴት እንደተፈጸመ ፕሮፌሰር

ላጵሶ ጌታሁን ዴለቦ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> በሚለው መጽሐፍ ገጽ 23 ላይ "- - - የተደራጁ የሸዋ መሳፍንትና የጦር አበጋዞች በ1865-1913 በንጉስ/አፄ ምንሊክ ብርቱ መሪነትና አዝማችነት በደቡብ ኢትዮጵያ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችና መንግስታት ላይ በሰፋሪ ነፍጠኛ ወታደሮችና ቄሶች አማካይነት ጠንካራ የገባር ሥርአትና ኤኮኖሚ በመገንባት፤ በአንድ በኩል የክርስቲያን የአፄው መንግስት የፖለቲካ ተሃድሶና ምዕክልና በከፍተኛ ደረጃ አካሄዱ።" በማለት ምን እንደተደረገና ማን ምን እንደሰራ ትንተና ጭምር ሰጥተውበታል። ከዚህ ትንታኔ በመነሳት ደቡብ በምንልበት ጊዜ በወቅቱ ከአማራው ሰሜን ሸዋ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኙና ዛሬ የምናውቀውን የጋራ ወይም የየራሳቸው ሀገረ መንግስት ባይመሰርቱም የራሳቸዉ ነፃ ግዛት ወይም ቢያንስ የራሳቸዉ የጎሳ የውስጥ አስተዳደር የነበራቸዉ ሕዝቦች እንደ ኦሮሞ፣ ወላይታ፣ ሐዲያ፣ ከፋ፣ በኔሻንጉል-ገሙዝ፣ እና ሌሎች ሕዝቦች እንደሆኑ እንረዳለን። ምንሊክ የፈጠረው ኢምፓየር በቆዳ ስፋቱ ቀድሞ ኢትዮጵያ ከምትባለው የሰሜኑ አከባቢ መሬት ሦስት እጥፍ የሚሆንና እስከዛሬም ድረስ እንደ መዥገር የተጣበቁት የነፍጠኛ ልጆች ሳይቀር ዓይናቸውን ያላሹለት የሀብት ይዞታ ያገኙት በአፄ ምንሊክ አማካይነት ነው።

የአፄ ምኒልክ የግዛት ማስፋፋት ዓላማ ከቴዎድሮስም ሆነ ከዮሐንስ በመጠንም ሆነ በዓይነት የሰፋ ነበር። የአፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ዕውቀት ከዛሬዉ ሰሜን ሸዋ እና ከትግሬ አገር ያልዘለለ፤ ነገር ግን መነሻ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ፤ ምናልባትም የእስልምና ሃይማኖትን ከሚከተሉ ከግብፅና ቱርክ ጋር ከተፈጠረበት የጥላቻ ስሜት ጋር የተያያዘ በሚመስል መልኩ ውሽማ ብለው አዝማሪዎቹ የሰየሙለትን ኢየሩሳሌምን ነፃ የማዉጣት ህልም የሚጨምር ሲሆን፤ የዮሐንስ ደግሞ ወደ ባህር መውጫ በር ምፅዋን አካትቶ እንደነበረ ይታወቃል። የአፄ ምኒልክ የደቡብ ግዛቶች ወረራ መነሻ ሐሳብ በሦስት ምክንያቶች ተደግፎ ሰፋ ያለ ነበር። ከእነሱም አንደኛው ቀደምት አባቶቹ አፄ ይኩኖ አምላክ (1270-1314) እና ካህናቱ የቀየሱትን ግዛትና ወንገል ማስፋፋት የጀመሩትን ፖሊሲ በመንተራስ ኦርቶዶክሳዊ የማጥመቅ ሥራን

ለማስቀጠል ሲሆን፤ ሁለተኛው አፄ ምኒልክ ሥልጣን በሚይዝበት ጊዜ ላይ የአውሮፓ ባለእንዱስትሪ አገሮች የእንዱስትሪ ሸቀጦቻቸዉን የሚሸጡበትና በመልሱም ርካሽ ጥሬ ዕቃና ርካሽ ጉልበት የሚያገኙበት ሰፊ ገበያ ፍለጋ ተነሳስተዉ፤ በተለይም አፍሪካን ለመቀራመት በርሊን ላይ እ.አ.አ በ1884 ድርድር ያደረጉበት ጊዜ ስለነበር፤ ምንሊክም የራሱን ግዛት ለማስፋፋትና የነዚያው ስሜት አድሮበት ነበር ተብሎ ቢገመትና ይህንንም ከጣሊያን ጋር ከነበረዉ ጥሩ ግንኙነት የተነሳ የጦር መሳሪያ አግኝቶ ከነሱዉ ጋር ለመስተካከል አስቦ ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል። ሦስተኛውና መሠረታዊ ምክንያት ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለዉ በወቅቱ በሰሜኑ በኩል የነበረዉ የአገሪቱ ክፍል ከተደጋጋሚ ግጭቶችና ጦርነቶች የተነሳ፤ መሬቱም ተራቁቶ ሕዝቡም ለተደጋጋሚ ድርቅና ረሃብ የተጋለጠ በመሆኑና የመሬቱም ምርታማነት በመቀነሱ ለኑሮ የተሻለ ሊሆን የሚችል ደቡብ አከባቢን መፈለግ ምንሊክን የግድ ሳይለው እንዳልቀረ መገመትም የተሳሳተ አይሆንም። ስለሆነም፤ የደቡቡን ሕዝብ አንጡራ ሀብት (መሬትን) በነፍጥ ኃይል ወስዶ ባለአገሩን ሕዝብ እያፈናቀለ ነፍጠኞች ተብለዉ ለሚታወቁ ወገኖቹ አከፋፈለ። ይህንንም ፕሮፌሰር ላጵሶ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው “የደቡብ ኢትዮጵያ አዋማዊ (ክርስቲያንም እስላምም ያልሆነ ሕዝብ) እና እስላማዊ አገሮችንና ሕዝቦችን በጦር ኃይሎች ይዘው በሰሜኑ ሰፋሪ ወታደሮች፣ ገዥዎችና ቄሶች አማካይነት የአፄው ማዕከላዊ መንግስት <u>ገባሮችና ባሮች</u> <u>አደረጉ</u>።” (ሰረዝ የተጨመረ) ብለዋል ።

*እዚህ ላይ ሰፋሪዎች ማለት (ከሣህለ ሥላሴ ጊዜ ከ1810 ዓም ጀምሮ የነበረ ቢሆንም) ከምንሊክ ጋር ደቡቡን የወረረና የየአከባቢውን ባላባቶች ያፈናቀለ ነዉ። እንደ ሰናይት ተክለ ማርያም የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስት ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል መጽሐፍ ገፅ 68 በሸዋ ደቡብ ምንጃር የራሱ አስተዳደር ያለዉ ዳር አገር ይባል። እነዚሁ ሰፋሪዎች ነፍጠኞችም በመባል ይታወቃሉ። ነፍጠኛ ማለት ለኦሮሞ ኤሊቶች ነፍጥ ተሸክሞ ከምንሊክ ጋር ዘምቶ ወደ ደቡብ የመጣና ባለአገሩን ሕዝብ አፈናቅሎ የገባር ሥርአትን ያሰፈነ ኃይል ሲሆን፤ ለዚህ ወቅት የደቡብ ሕዝብ ደግሞ ሰፋሪ ማለት*

*ምንሊክን ተከትሎ የዘመተዉ ኦሮሞን ይጨምራል ነው። ለአሰፋ ጫቦ ደግሞ ሰፋሪ ማለት ወራሪ፣ አማፂ፣ የነፃነት ታጋይ፣ የመንግስት ሠራዊት ይሁን ምኑንም በማይለይበት ዓይነት አገላለጽ የቃሉ ደረቅ (ነጠላ) ትርጉም "ነፍጠኛ ማለት ጠብንጃ የያዘ ማለት ነው።" ብለዋል። ጠመንጃ ጌጡ የሆነውን አርብቶ አደር ይጨምር እንደሆነ አሰፋ ጫቦ ግልፅ አላደረጉም። አሰፋ ጫቦ በምን እንደመዘኑ ባይታወቅም "ነፍጠኛ ማለት የደቡብ አከባቢ ተወላጅ ያልሆነ ግን አገር ለማሰልጠን፣ አገር ሊያቀና የሄዱ ናቸው" ብለውታል። አሰፋ ጫቦ በዚህን ሁኔታ ይግለጹ እንጂ እነዚያ ሰፋሪ ነፍጠኞች ከተወረረው ሕዝብ የተሻለ የአስተዳደር ክህሎት ያልነበራቸው ባዕዳን እንደነበሩ ባለአገሩን ሕዝብ ሲያፈናቅሉ ይኖሩ እንደነበር ተለይተው ታውቀዋል። ሥረ መሠረቱ አማራ ይሆን ኦሮሞ ምንልክን ተከትሎ የመጣዉን ጠመንጃ አንጋች ወራሪ ስም ሲጠራ አማራን ጥላቻ አድርገዉ እንደሚመለከቱትና እኔም ነፍጠኛ ነኝ እንደሚሉት አጉሎች ሳይሆን በመርድ አዝማች አሰፋወሰን አገዛዝ ጊዜም በ160ዎቹ መጨረሻ አከባቢ ጀምሮ ነፍጠኛ የሚለዉ ቃል በተግባርም እንደነበረ ሠናይት ተክለማርያም በመጽሐፋቸዉ ዉስጥ ገልጸዋል።* በዚህ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ደግሞ ነፍጠኛ ማለት የአያቶቻቸውን ፈለግ ተከትለው የስልት ለውጥ ብቻ *በማድረግ የኦሮሞንም ሆነ የሌላው የደቡብ ሕዝቦች ከሐበሾች ተፅዕኖ ሥር እንዳይወጡ የሚሹ ኃይሎች ናቸው። የዘመኑ የነፍጠኛ ልጆች ደግሞ በተራቸው ቀድሞ የተወረሩ የደቡብ ሕዝቦች ልጆች ነፃ አስተሳሰብ እንዳይጎለብት በሃይማኖት፣ በሚዲያ፣ በአርትና በገንዘብ ኃይል በማፈን የአባቶቻቸውን ታሪክ ለመድገም የሚፈልጉ ናቸውና የአካል እንኳን ባይሆኑ የመንፈስና የባህርይ ነፍጠኛ ተብለው ይታወቃሉ። ከዚሁ በተቃራኒ ደግሞ እነዚሁ የዘመኑ ነፍጠኞች አድዋ ላይ የተደረገውን የጣሊያንን ወረራ ለመመከት የተደረገውን ዘመቻን ወደ ጠባብ ፍላጎታቸው ዝቅ በማድረግ ነፍጠኝነትን ጀግንነት ሊያላብሱ የሚሹ ናቸው።*

በኦሮሞም ሆነ በሌሎች የደቡብ ሕዝቦች ዘንድ ነፍጠኝነት የሚገለፅበት ሌላም ሁኔታ አለ። እሱም ከመሬት ጋር የተያያዘ ነው። ይኼውም ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ እንደመጣው ሁሉ ሰው ከመሬት ጋር ያለውን ግንኙነት

አስመልክቶ የኦሮሞ ሕዝብ ያለውን ግንዛቤ በማያያዝ ነው። እንደ ኦሮሞ ተወላጆች ግንዛቤ እግዚአብሔር ሰዉን ሲፈጥር ጥረህ ግረህ ብላ ሲለዉ የሰጠዉ ነገር ቢኖር ሊሰራበት የሚችለዉን አእምሮና የሚሰራበትን መሬት እንደሆነ ነዉ። ሽፋኑ ሊሰፋም ሆነ ሊጠብም ይችላል እንጂ ሰውን ይዞታዉ ከሆነ መሬትና ከሚኖርበት ቀዬዉ ማፈናቀልና መሬቱን መውሰድ ማለት ነፍጠኝነት ብቻ ሳይሆን ሰው ጥሮ ግሮ እንዲኖርበት ፈጣሪ የሰጠውን በረከት እንደመንጠቅ ነዉ። በአጭሩ ነፍጠኝነት ማለት ነጣቂነት ነው። አዉሮፓዊያን ባህር አቋርጠዉ አፍሪካን ለመቀራመት በሚያንዣብቡበት ጊዜ አፄ ምኒልክም ከአውሮፓዊያኑ ባገኘው መጠነ ሰፊ የጦር መሳሪያ ወደ ጎረቤቶቹ ደቡብና ኦሮሚያ መስፋፋቱና ከመሬታቸዉ ማፈናቀሉ ሲመዘን፤ ምንሊክ ጥቁር ከመሆኑ በስተቀር በምንም ዓይነትና  ሁኔታ ከአዉሮፓዊያኑ ቅኝ ገዥዎችና ቀማኞች እንደማይለይ ነዉ። ወይም እንለይ እንኳን ከተባለ መለያው ትንሽ ይሆናል። የምንሊክ አገር ማቅናት ከአውሮፓዊያኑ ቅኝ አገዛዝ የሚያንሰው ቅኝ ገዥዎች ለቅኝ ተገዥ ተወላጆች የሚፈቅዱት የትምህርት ደረጃ እስከ አራተኛ ክፍል ከፍ ሲልም እስከ ስድስተኛ ክፍል የሆነውን አቅኝዎቹ ምንሊካዊያንና ቀጣዮቻቸው እስከ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ ፈቅደዋል። ነገር ግን ከፍተኛ ትምህርት ቢማሩም ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ እንዲቀመጡ አይፈቅዱም፤ ከፈቀዱም ደግሞ ገደብ የለሽ ቁጥጥር እየተደረገባቸው ነው። በመሆኑም በአፄ ቴዎድሮስ በደም ማፍሰስ ግዛትን ማስፋፋት የተጀመረዉን ፖለቲካ ምኒልክም ማቅናት በሚባለው ዘይቤ ናኘበት። የአከባቢ ነፃ ሕዝቦችን መሬት በመያዝ ወደ ዘረፋ ገባ።

ንጉስ ምንሊክ ብዙ ዕፀፆች ቢኖሩበትም ሌሎች ነፃ ሕዝቦችን በወረራ ከያዘ በኋላ ከቀደምቶቹ ቴዎድሮስና ዮሐንስ ለየት የሚያደርገዉ ጉልህ ሥራዎች ዛሬም ሕያዉ የሆኑ አሉ። ከነዚህም ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መክፈት፣ የመኪና መንገድ መክፈት፣ የባቡር ሐዲድ መዘርጋት፣ ሕክምናና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ማቋቋም፣ ንግድ ማስፋፋት እና መሠረታዊ የሕዝብ ጉዳዮችን ለማከናወን ቢሮክራሲዉን ማለትም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ማደራጀት የሚጠቀሱ ናቸዉ።

በርግጥም እነዚህ ተቋማት በኢትዮጵያም ሆነ በማንኛዉም አገር የፖለቲካ ሥርአት ዉስጥ በዜጎች ሕይወት ዉስጥ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስከተሉ የሚችሉ ተፈላጊ ተቋማት ናቸዉ። እነዚህ ብቻ አይደሉም በ1882 የተፈረመዉን የውጫሌ ውል የተዛባ ትርጉም በመስጠቱ የተነሳበትን ተቃዉሞ ለመቀልበስ ወረራ የፈጸመውን የጣሊያንን ጦር በአድዋ ተራራዎች ላይ አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የጥቀር ሕዝብ ድል አድራጊነትን የመጀመሪያ ታሪክ ሠርቷል። ታሪካዊ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ውርሱም በመቀጠሉ አፄ ኃይሌ ሥላሴና መንግስቱ ኃይለማርያም ፀረ አፓርታይድ ትግልን ጨምሮ ፀረ ነጭ ቅኝ አገዛዝ ትግልን በሁለንትናዊ መልኩ አግዘዋል። ምናልባትም ከምንሊክ በፊት የነበሩት በምንሊክ እንደተበለጡ ግንዛቤ ብንወስድ እንኳን፤ ከምንሊክ በኋላ ወደ ሥልጣን እርካብ የተቆናጠጡት የምንሊክን ዘመናዊነት መገንገባቱን ቢቀጥሉበት ኖሮ ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ በጨለማ ውስጥ አትዳክርም ነበር ቢባል አልተሳሳትኩም። በተለይ ለስድሳ ዓመታት ሥልጣን ይዞ እስክጃጅ ድረስ የቆየው አፄ ኃይሌ ሥላሴ የምኒልክን ጅማሮ ባለማስቀጠሉ ከምንሊክ የሀገር ግንባታ ጥረት በተቃራኒ ሆኖ የተፈጠረ ሰው ይመስላል። በሌላም በኩል ኢትዮጵያን እስከዛሬ የገዟት አምባገነኖች በ2016 ዓም 128ኛ ዓመቱ የተከበረለት የአድዋ ድል ዉርስ (legacy) የሁሉም ኢትዮጵያዊያን አገር ሽታ እንዲኖራት ባለማድረጋቸዉ ድሉ የተለያየ ትርጉም እንዲሰጠዉ ተደርጓል።

ከዚህ ጋርም ከምንሊክ ግዛት ማስፋፋትም ተባለ ማቅናት ጋር የሚነሱ ሁለት አቢይ ጉዳዮች አሉ። አንደኛው፤ ዕውነት ምንሊክ የግዛት ማስፋፋት ጦርነት አካሄደ ወይስ ቀድሞም የዝርያቸው ይዞታ የነበረው መሬት ወይም ግዛት መልሶ ያዘ? የሚል ጥያቄ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የምንሊክን ጉልበት እንዲያ ያፈረጠመው የአውሮፓዊያን ዕርዳታ እንዴት ሊመነጭ ቻለ? የሚል ጥያቄ ነው።

ዐፄ ምንሊክን በባለውለታነት የሚገነዘቡት ወገኖች ንጉሱ የማንንም ይዞታ ሳይሆን (ቀደምት አባቶቻቸው እነማን እንደሆኑ ለይተው

ባልገለጹበት) የቀደምት አባቶቹን መሬት መልሶ የያዘ ነው (reunification) ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ የምንሊክ እርምጃ የመንግስት አስተዳደር ስርአትን ወደ ተቀረው የአገሪቱ ክፍል የማድረስ ተልዕኮ እንደነበር ሲገልጹ፤ ይህም የሀገረ መንግስት ግንባታውን ከውስጥ ወደ ውጭ ማስፋፋትን የተገበረ ዘይቤ እንደሆነ አድርገው ያቀርቡታል። ታሪኩ ተፈራ (ኤምኤ) ምንጩ ከየት እንደሆነ ባልገለጸበት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድክመት፣ ጥንካሬ፣ ሴረኝነትና ሽኩቻ ብሎ ባዘጋጀው እትም ገጽ 54 ላይ "… ኢትዮጵያ ከምንሊክ በፊትም የነበረች ሀገር ናት፣ ምንሊክ የተበተነውን ኢትዮጵያ መልሶ ሰበሰበ እንጂ [አዲስ] ኢትዮጵያን አልፈጠረም፣ ኢትዮጵያ ከምንሊክ በፊት በተለያዩ ስሞች ስትጠራ ድንበሯም በተለያየ ምክንያት ሲሰፋና ሲጠብ የቆየችና ብሄሮች ፈጣሪ በሰጣቸው ጊዜ እየተነሱ ሲያስተዳድሯት የቆየች ጥንታዊ ሀገር ናት …" በማለት ኢትዮጵያም ሆነች ብሔሮችም ከምንሊክ ኢትዮጵያ በፊትም እንደነበሩ የጨበጣ የሚመስል ጽሑፍ ጽፏል። በርግጥም በስፋትም፣ በአቀማመጥም በሕዝብ ስብጥርም ለየት ያለ ሀገረ መንግስት ኢትዮጵያ ከምንሊክ በፊትም ኢትዮጵያ በሚባል ስም የነበረች ቢሆንም የምንሊኳ ኢትዮጵያ እና ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ግን ለየቅል እንደነበሩ እሸቱ ኢረና ዲባባ የኦሮሞ ታሪክ (2001፡15) ባለው መጽሐፉ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራትን በመጥቀስ "ስሙ ሳይቀር ግርኮች ኢትዮጵያ ብለው የተረጎሙት በጥንት እብራይስጥ ኩሽ ይባል የነበረውን አከባቢ ሲሆን በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ አብዛኛዎቹ ከግብፅ ቀጥሎ ያለውን ሕዝብ እንደሆነና የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች በአብዛኛው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖሩ በመጥቀስ፤ ከነዚህም መሀከል ኦሮሞ አንዱ መሆኑን ገልጿል" በማለት ጽፎአል። በተመሳሳይ ሁኔታም "The place which was known as Ethiopia at that time was the land of the cush, not that of the Habeshas" በማለት ድርቢ ደሙሴ ከላይ በተጠቀሰዉ መጽሐፉ አክሎበታል። "የድሮ የኢትዮጵያ ወሰን እጅግ ሰፊ መሆኑን በመግለፅ የመስፋፋት ሕልማቸውን ዛሬም በይፋ የሚገልጡት አበሾች የእነርሱ ኢትዮጵያ ቀድሞውንም ቢሆን እንደ አገርም የራስዋ ወሰን ኖሮአት የታወቀችው አውሮፓዊያን አቅኚዎች አፍሪካን ተቀራምተው በዙሪዋ

የሚገኙ አገሮችን በቅኝ ግዛትነት ከተቆጣጠሩ እና አበሾችም ኦሮሞና ሌሎች ነፃ የነበሩ ነባር ሕዝቦችን በመውረር ወደ አብሲኒያ ለመጠቅላል ከበቁበት ከመቶ ሃያ ዓመት ወዲህ ነው” በማለት ተስፋዬ ፉፋ ጉሉማ <u>የኩሽ ሀገር ኢትዮጵያ በሀገረ መንግስት ምስረታ ስንት ግፍ ተሰራ!</u> (2013፡ 40) ብሎ በፃፈው መጽሐፍ ዉስጥ አስነብቧል፡፡ በተመሳሳይም በተክለ ፃዲቅ መኩሪያ መፃሐፍ እንደተገለጸው ምንሊክ የተስፋፋባቸው ቦታዎች ባለቤት እንደነበራቸውና የምንሊክ እርምጃ ቅኝ መግዛት ወይም መስፋፋት (unification/expansion) እንደሆነ  የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አስተሳሰብን ወደ ፖለቲካው አማካይ ሥፍራ ለማምጣትም ሆነ ዛሬም ሆነ ቀደም ሲል ሲባሉ የነበሩ ነገሮች ማለትም ማቅናትና ቅኝ መግዛት የቱ ጋ ሊለያይ ወይም ሊገናኝ እንደሚችል ለመረዳት እንዲያግዝ ቅድመ እና ድህረ ምንሊክ የነበሩ አባባሎችን ከዚህ በታች ከተመለከቱት የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም ምንጮች መመልከት ይቻላል፡፡

1. ቴዎድሮስ ለወታደሩ “**የጋላውን አገር ወሎ**ንና ይልቁንም ትልቁን **የሸዋን አገር** ይዘን ኢትዮጵያ አንድ ካደረግን በኋላ እናርፋለን ማለቱ“፣
2. “የሸዋው ንጉስ ኃይለ መለኮት ግዛታቸውን **እስከ አሩሲ ድረስ ለማቅናት** ሄደው ሲመለሱ” በቋራ ቴዎድሮስ የሚባል አንድ ሰው መንገሱን ሰምተው እንደነበረ፣
3. የየጁ ዐሊ ፋሪስ የሚባለው ሰው ቴዎድሮስ ላይ ሸፍቶ “ጥቂት እንደተዋጋ ሸሽቶ ወደ **ጋላ አገር** ሄደ” የሚለውና
4. “ንጉስ ምንሊክም በእንደዚህ ያለ አካኋን የኢትዮጵያን ግዛት ከማስፋት ጋራ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ እንዲሆን **የሸዋን ሕዝብ በድል ወደ ተያዘው አገር** እየላኩ በድል በተያዘው አገር ወደ ሸዋ አምጥተው በክብር እያሳደጉ በነገድ ተለያይቶ የነበረውን አዛመዱት” በማለት ገልጸዋል፡፡ በክብር ካደጉት ውስጥም ወጣት ምርኮኞች ደጃች ባልቻ አባነፍሶ (ባልቻ ሳፎ) እና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርግስ ድናግዴ (ቁሴ ድናግዴን) ይጨምራል፡፡ ሁለቱም የሐሳብ ልዩነት እንደነበራቸው የሚያመለክተው ደጃች ባልቻ

መማረካቸውን ሲያማርሩ ሀብተ ጊዮርግስ ግን መማረካቸውን እንደመባረክ ይቆጥሩት እንደነበር የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ይገልፃሉ፡፡

5. "ከኢትዮጵያ ደቡብ ያለውን **ታላቁን የሐረርን ግዛት** ራሳቸው [ምንሊክ] ሄደው በ1879 ዓመተ ምህረት አሚር አብዱላሂን ወግተው አስመልሰው ነበር፡፡ … የኢትዮጵያን ግዛት ከሐረር ወዲያ ኢሳንና ውጋዴን አልፎ እስከ ሱማሊያ ወሰን ድረስ አቀኑ"
6. "… ራስ መኮንን ቁጥሩ ሰላሳ ሺህ የሚደርስ የጦር ሰራዊታቸውን አስከትለው ከከፋ ዝምረው **የሺሆጂሌን ግዛት** ወደ ኢትዮጵያ አድርገው እስከ ሱዳን ጠረፍ ድረስ ያለውን አገር አስገበሩ፡፡"
7. "ደጃች ተሰማ ናደው በይሉባቦር በኩል ያለውን አገር የባሮን መሬት እያቋረጡ እስከ ሰባትና እስከ ነጭ አባይ ድረስ ያለውን **አገር አስገበሩ**፡፡"
8. "ራስ ወልደ ጊዮርግስ ከፋን፣ ኩሎ ኮንታን፣ ሊሙን ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ አባይ አልፈው **የኢትዮጵያን ግዛት አሰፉ**፡፡"
9. "ፊታወራሪ ሀብተ ጊዮርግስ 15 ሺህ ያህል የጦር ወታደራቸውን ይዘው በቦረና በኩል እስከ ኬንያ ድረስ ያለውን **አገር አቀኑ**፡፡" ይላል፡፡

ከዚህ በላይ የተቀመጡ ዘጠኙን ነጥቦች ስንመለከት ምንሊክ በማስፋፋትም ሆነበማቅናት የያዙት ቦታዎች ባለቤት የነበራቸው አገሮች እንደነበሩ ራሱ ገላጭ ነው፡፡ ይዞታን ከማስፋፋትም ሆነ ከማቅናት በተጨማሪ ምንሊክ የፈጸሙት ወረራ፤ ወረራውንም ተከትሎ አውሮፓዊያን ቅኝ ገዡዎች ያደረጉት እንደነበረው የሥነ ልቦና፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ የፖለቲካና አስተዳደር ተፅዕኖዎችን በማድረስ የደቡብ ሕዝቦችን ሕልውና የጎዳ እንደነበረና ቅሪቱ እስከዛሬም የቀጠለ መሆኑን ማሰብ ይሳነናል ብዬ አላስብም፡፡ የእነዚህ አከራካሪ ሐሳቦችና የውሸት ትርክቶች (ሥልጣን ላይ ሙጭጭ ማለትን ጨምሮ) የኢትዮጵያን ፖለቲካ እያጦዙትና እያወሳሰቡት ስለሄዱ የኢትዮጵያን የሀገረ መንግስት ግንባታ ክፉኛ ተፈታትነውታል፡፡ ዛሬም እየተፈታተነዉ

ቀጥሏል።

አንደኛውን ነጥብ በዚሁ ልግታና ወደ ሁለተኛው ነጥብ ልለፍ። እሱም የምንሊክን ጉልበት እንዲያ ያፈረጠመው የአውሮፓዊያን የጦር መሳሪያ ዕርዳታ እንዴት ሊመነጭ ቻለ? የሚለው ነው። ከተክለ ፃዲቅ መኩሪያ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> መጽሐፍ ለመረዳት እንደሚቻለው ዐፄ ዮሐንስ ተቀናቃኞቻቸውን የጎጃሙን ተክለ ሃይማኖትና የሸዋውን ንጉስ ለማስገበር በተንቃሳቀሱበት ጊዜ ውስጥ "የንጉስ ምንሊክ የኃይል ሚዛን እየደፋ መሄድ መጀመሩን" [በመገመትና ይህንን ኃይል በስልት ለመቀልበስ ሲሉ ምንሊክ ወራሽ ወንድ ልጅ የሌላቸው መሆኑን አስልተው፤ ይህንኑ የተደፋውን የኃይል ሚዛን በፖለቲካ ጋብቻ ለማስተካከል ሲባል ምንሊክ ልጃቸውን] "ዘውዲቱን ለራስ አርአያ ይድሩላቸው ዘንድ ዮሐንስን ለመኗቸው" በማለት አስፍረዋል።

ከቀደምት ገዥዎች አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ ትምህርት በመውሰድ ሊሆን ይችላል፤ ሌላው የአፄ ምኒልክን አገዛዝ ለየት የሚያደርገው ሥልጣኑን የሚገዳደር ኃይል መገኘት ብቻ ሳይሆን ቢጠረጠር አንኳን እንዲሁ በቀላሉ መነሳት እንዳይችል ተደርጎ ይደቆስ እንደነበር ነው። ለዚህም ሦስት ዓይነት የአገዛዝ ስልቶችን በመጠቀም ሊሆን ነው። አንደኛዉ ምንሊክ የአፄ ቴዎድሮስ ምርኮኛ በነበረበት ጊዜ ተቀናቃኝ በሆኑ ሕዝቦች ላይ ብቻ ሳይሆን፤ ተቀናቃኝ ይሆናል ተብሎ በሚጠረጠር ሰዉ ላይ ቴዎድሮስ ይወስድ የነበረዉ ጭካኔ የተሞላበት ዕርምጃ ምን ይመስል እንደነበረ ምንሊክ በልጅ አእምሮዉ በአካል ተመልክቶ የጭካኔ ትምህርት የቀሰመ በመሆኑ፤ እሱም በተራዉ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎች የዋዛ እንደማይሆን ማወቅ ይቻላል። በርግጠኛነት መገመት የሚቻለዉ ሰዎችን ያለአንዳች ርህራሄ ሲጨፈጭፍ ከነበረዉ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር ያን ያህል ጊዜ ውሎ ያደረው ምንሊክ፤ ለዚያዉም ባልበሰለ የልጅነት አእምሮው፤ ምኒልክና ባለሟሎቹ፤ ራስ ዳርጌና ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል፤ ርህራሄና ሰብአዊነትን ከገዳዩ ቴዎድሮስ ተምረው ይመለሳሉ ብሎ የሚያስብ ወይም የሚጠብቅ ሰዉ ካለ፤ የዚያ ሰዉ የአእምሮ

ጤንነት ላይ ጥያቄ ቢነሳ ለምን ተነሳ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ሁለተኛዉ የአቤቶ ምንልክ በደቡብ አቅጣጫ ሕዝቦች ላይ ያን ያህል ጭካኔ ሊወስድ የቻለዉ ከቤተሰባዊ ግንኙነት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኼዉም፤ አቤቶ ምንልክ ከንጉስ ኃይለ መለኮትና ከወይዘሮ በዛብሽ ተወልዶ በወይዘሮ እጅጋየሁ ሞግዚነት ያደገ ነዉ፡፡ ኃይለ መለኮትም በጉርምስና ዕድሜዉ ላይ ባደረበት ሊቅ ፍላጎቱ የተነሳ ከሞግዚቱ ከወይዘሮ እጅጋየሁ ጋር ግንኙነት በማድረጉ ምንልክ የሚባል ወንድ ልጅ ተወለደ፡፡ አያቱ ንጉስ ሳሕለ ስላሴ የተወለደዉን ልጅ ቢቀበልም ከአባቱ ሞግዚት መወለዱን ሳይጠየፉ አልቀረምና ምንልክ በተወለደ በአርባ ቀኑ ተጠምቆ እስከ አስር ዓመት ልደቱ ድረስ በሌላ ሞግዚት በሌላ ቦታ እንዲያድግ በመደረጉ የእናትም ሆነ የሌሎች ሰዎች ሰብአዊ ፍቅር እንዳልዘረበት ይገመታል፡፡ ሦስተኛዉ ስልት ደግሞ ከፋፍሎ መግዛት ወይም ከፋፍሎ ማዋጋት ምኒልክ የተካነበት መሆኑ ነዉ፡፡ ምኒልክ በሴት እጅ ወይም በሴት ከበባ ራሱን ከገደለዉ ቴዎድሮስና በጠልጣላ ደርቡሽ ተገድሎ ራሱ ከተቆረጠዉ ዮሐንስ ሰፊ ትምህርት የወሰደ ይመስላል፤ ይኼዉም ለማቅናት ወይም ለቅኝ ማስፋፋት ጦርነቱ እንዲዋጉለት የተመዱቡት የጦር መሪዎች ከራሱ ወገኞች ይልቅ የጎበዝ አለቆችን ከቅኝ ተገዥዎች የተገኙ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ለምሳሌም ጎበና ዳጪን ከሸዋ ነፍጥ አሸክሞ የሸዋ ሕዝብ ብዙም ንቅናቄ ሳያደርግ አስገበረ፡፡ የጂማ እና የሌቃዎቹን በማስፈራራትም ሆነ በማታለል የወረራው ተባባሪ ወይም ሞግዚት አደረጋቸው፡፡ ጎበናን የመሰሰሉ የጎበዝ አለቆች የተፈለጉበት ጉዳይ ከአለቀ በኋላ የምኒልክን አገዛዝ እንዳይቀላዉጡ በስልት አንቅረዉ ይተፏቸዋል፡፡ የአተፋፍ ስልቱን ደግሞ ታቦር ዋሚ ዋቢን በመጥቀስ ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሐፉ ገፅ 12 ላይ እንደገለጸዉ "ከተጠቀሙባቸዉና የቅርብ ዘመዶቻቸዉን ካደራጁ፤ እንዲሁም የኦሮሞን ሕዝብ አቅም ማነስ ግምት ዉስጥ ካስገቡ በኋላ አንቅረው ይተፏቸው ነበር" በማለት ጽፏል፡፡ ይህ አንቅሮ የመትፋት ስልት በኃይሌ ሥላሴም ሆነ በደርግና በወያኔ አገዛዝ ጊዜም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በስፋት ሥራ ላይ ውሏል፡፡

"ምኒልክ ጎበናን አንቅሮ የተፋዉ ሙሉ በሙሉ ቁርጠኝነት የሌላቸዉና

ወደፊት ምን ሊከተል እንደሚችል አርቆ ማስተዋል ያልቻሉትን አባ ጀፋርንና ኩምሳ ሞረዳን ይዞ ጅማ እና ወለጋ እንዲገብር ያደረገዉ ምኒልክ በብልጠት ነበር፡፡ የምኒልክን ወረራ ለመቋቋም ሙከራ ያደረጉ የኢሉ አባቦራ፣ የአርሲ፣ የሐረር፣ የወላይታ፣ ወዘተ ሕዝቦችን አርመኔያዊ በሆነ ሁኔታ በመቅጣት እስከዛሬም ድረስ እንዳያንሰራሩ አድርጓል፡፡ አንዳንድ የአበሻ ኢሊቶች በተለይ የአርሲ ኦሮሞዎች እንደተከፋፈሉና ለምኒልክ ጦር አበጋዝ ለራስ ዳርጌ የጭካኔ እርምጃ እንደተጋለጡ የሚጽፉ ቢሆንም፤ ምኒልክ የአርሲ ሕዝብን በአኖሌ፣ የሐረርን ሕዝብ በጨለንቆ፣ የጨፈጨፋቸዉ ተከላካዮቹ ኦሮሞዎች ሽንፈታቸዉን የተቀበሉ ቢሆንም፤ የምንሊክ ዕርምጃ ሲጀመርም ለምን ተቀናቀናችሁኝ የሚል በሚመስል መልኩ ቂም በመያዝ እርቅ ብሎ ወደተጠቀሱት ሥፍራዎች በመጥራት ነበር፡፡

ሦስተኛዉ ስልት አፄ ምኒልክ በቅኝ ግዛት ቅርምት ውስጥ የራሱን ድርሻ ለማግኘት ከአውሮፓ ኃይሎች ጋር የፈጠረው ግንኙነትና ጎረቤት ነፃ ግዛቶችን ለመያዝ ያደረገዉ እሽቅድምድም በወቅቱ ዘመናዊ የሚባሉ መሳሪያዎች ባለቤት እንዲሆን ስለአስቻለውና መሳሪያውንም በተገቢው መንገድ ስለተጠቀመበት (በኦሮሞ መሀከል የተፈጠረው መከፋፈል እንዳለ ሆኖ) ዘልቆ ሊቋቋም የሚችል ሌላ ተቀናቃኝ የአገር ውስጥ ፊውዳልም ሆነ በመሀከላቸው የጥቅም ግጭትን ላለመፍጠር ስምምነትን ከፈጠሩ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ተቀራማቾች (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን) ዘንድ አላጋጠመውም፡፡ ይህንን ስልታዊ የምንሊክ ወረራንና የአውሮፓ ኃያላንን የጥቅም ግጭትም ሆነ ክፍፍልን ያልተገነዘቡ የምንልክ የልጅ ልጆች የአውሮፓ ኃያላን እንደሌላው የአፍሪካ አገሮች ኢትዮጵያ ላይ ባለመስፈራቸው ኢትዮጵያ ቅኝ አልተገዛችም እያሉ ድስኩር ያሰማሉ፡፡ ለአውሮፓዊያን የጥቅም ግንኙነትና ግጭት እንደ ምክንያት የሚጠቀስ ቢኖር የአፍሪካ ቀንድ አከባቢ በተለይም የኢትዮጵያ አቅጣጫ በአንደኛው የአውሮፓ ኮሎኒያሊስት እጅ ከሚወድቅ ከጦርነት ቀጠና ነፃ ሆኖ ሁሉም የአውሮፓ ካፒታሊስቶች በተለይም እንግሊዝ፣ ጣሊያንና ፈረንሳይ ወደ ቀይ ባህር በሰላም የሚተላለፉበት ኮሪዶር

እንዲሆን ስለተስማሙና ወደ አውሮፓ የሚደረገው የጥሬ ዕቃ ፍሰትም ሆነ ወደ ሩቅ ምስራቅ የሚጫነው የፋብሪካ ውጤቶች ምልልስ እንዳይሰናከል ካላቸው የጋራ ፍላጎት የተነሳ ኢትዮጵያን የአንደኛቸው ብቻ ቅኝ ግዛት ሳያደርጉ የቀሩ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ከግምትም ባሻገር ተስፋዬ ፉፋ ጉሉማ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ሆል ኮምብና ሲሳይ ኢብሳ ዘ ሜከንግ ኦፍ ኢትዮጵያ ብለው የፃፉትን ዋቢ በማድረግ እንደፃፈው "ባጭሩ የአፍሪካ ቀንድ አከባቢ በአንደኛው ኃያል የአውሮፓ ኮሎኒያሊስት እጅ ከሚወድቅ ይልቅ ከጦርነት ቀጣና ነፃ ሆኖ ሁሉም የአውሮፓ ካፒታሊስቶች ወደ ቀይ ባህር በሠላም የሚተላለፉበት እንዲሆን፤ እንዲሁም ወደ አውሮፓ የጥሬ ዕቃ ፍሰትም ሆነ ወደ ሩቅ ምስራቅ የሚጫነው የፋብሪካ ውጤቶች ምልልስ እንዳይሰናከል ካላቸው የጋራ ፍላጎት የተነሳ በ1906 ዓም በእንግሊዝ፣ ጣሊያንና ፈረንሳይ መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት አዲስቷ ጥገኛ ኢምፓየር ኢትዮጵያ ሊትፈጠር" እንደቻለች ገልጿል። ስለሆነም ይላል ተስፋዬ ፉፋ "ሦስቱም የአውሮፓ ኃያላን ሀገራት ባደረጉት ስምምነት ኢትዮጵያ በወቅቱ የያዘችው የግዛት ወሰን ተከብሮላት እንዲትቆይ ሐርትስሌት በ1909 በአርትክል 102 መስማማታቸውን" አረጋገጧል።

ስለሆነም፤ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ጣምራ ምክንያቶች ሦስቱም ኃያላን የአውሮፓ ሀገራት ማለትም እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ስምምነቱን በመሀከላቸው በመፈራረማቸው ኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛቷ ብቻ ሳይሆን ምንሊክ በወቅቱ የያዛችው የግዛት ወሰንም ተከብሮለት እንድትቆይ መስማማታቸው ወደ ጎን የሚተው ጉዳይ አይሆንም። ተክለ ፃዲቅ መኩሪያም እንደፃፉት "ከሦስቱ አንደኛው መንግስት [እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ኢጣሊያ] ከሁለቱ መንግስታት አንዱ ተለይቶ የወዳጅነትም ወይም የጠላትነት ፖለቲክ በኢትዮጵያ ላይ ከሠራ ሁለቱ መንግሰታት ከኢትዮጵያ ጋራ ሆነው የጥቅም ተሻሚ ባላጋራቸውን ለማሸነፍ ስለኢትዮጵያ መልካም ስሜታቸውን ሲገልጹ ኢትዮጵያም በነሱ ምክርና ወዳጅነት ተደግፋ ጠላቶቿን በጦርነትም በፖለቲክም ግንባር ድል አድርጋለች" በማለት የፃፉት የተስፋዬ ፉፋን ሐሳብ ያጠናክራል።

ስለማረጋገጫው ደግሞ በ1928 ጣሊያን የ1888ቱን የዓድዋን ድል ለመበቀል ከሌሎቹ ስምምነት በማፈንገጥ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ እንግሊዝ ከዐፄ ኃይለ ሥለሴ ጋር አንዳች ስምምነት ሳታደርግ፤ እንዲያዉም ንጉሱ ወዴት እንደሚሄድ ሳያዉቅ በራስዋ ተነሳሽነት የሱዳንና የሶማሊያ ቅኝ ግዛቶቿን መረማመጃ በማድረግ እና ከፍተኛ የጦር መኮንኖቿን በማሰለፍ ለኢትዮጵያ ወግና ጣሊያንን ወግታለች። በተመሳሳይ ሁኔታም ቀደም ሲልም የኢትዮጵያን የመንግስታት ማህበር አባል መሆን ጥያቄን እንግሊዝ ስትቃወም ፈረንረሳይና ጣሊያን የእንግሊዝን አቋም በመቃወም የኢትዮጵያን የአባልነት ጥያቄ እንደደገፉ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ ገልጸዋል። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛት እንደሚደሰኮረው የመሪዎቿ ወይም የሕዝቧ አይበገረነት ወይም የዓድዋው የኢትዮጵያዊያን በአርበኝነት ጣሊያንን አይቀጡ ቅጣት መቅጣትና ትምህርት ሰጥቶ መመለስ ሳይሆን በሦስቱ ተፎካካሪ ቅኝ ገዥዎች መሀከል የነበረው መስማማት ወይም አለመስማማት ለኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛት አንዱ ወሳኝ ዕድል እንደነበረ በግልፅ ይታያል። አሁንም፤ ሦስቱ አገሮች (ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ጣሊያን) ኢትዮጵያን በሦስት አውራጃዎች ከፍለው ኤኮኖሚዋን እያለሙ ለመጠቀም፤ የጣሊያንና የፈረንሳይና የጣሊያን መንግስታት የማይፈቅዱ ማናቸውም የጦር መሳሪያዎች በወደብ በሮች እንዳይተላለፉ ስምምነታቸውን እ.አ.አ ታህሳስ 13 1906 ዓም በሎንዶን ተሰብስበው፤ እያንዳንዳቸው በፈለጉት መንገድ ለመጠቀም እንደነበረ ዘውዴ ረታ <u>የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ መንግስት</u> ብለው በፃፉት መጽሐፋቸው ውስጥ ገልጸዋል። ይህም ኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛቷ በኃያላኑ ቅኝ ገዥዎች መሀከል በተደረገ ስምምነት እንጂ በኢትዮጵያ ገዥዎች እንደሚደሰኮረው በራሷ ጥንካሬ እንዳልሆነ አመልካች ነው።

ኢትዮጵያ ከሦስቱ ኃያላን መንግስታት በጣሊያን ሙከራ ከመደረጉ በስተቀር በአንዳቸውም ለምን ቅኝ እንዳልተገዛች ሰፊ ቦታ ሰጥተው <u>ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ1798 እስከ 1967</u> (1999) ብለው የፃፉት አምባሳዳር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ ናቸው።

በተጠቀሰው መጽሐፍ በስፋት እንደተገለፀው “ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ከመቀራመት ይልቅ ወደ ባህር በር መመላለሻ በር አድርጎ ለመጠቀም” እንደነበረ ፀሐፊዉ ገልጸዋል። ፀሐፊው እንዳሉት [በእንግሊዝ] “አንቂነት የኢትዮጵያን ነፃነትና የግዛት አንድነት በነበሩበት ሁኔታ ለመጠበቅ ከፈረንሳይና ጣሊያን መንግስታት ጋር በ1899 ዓ.ም የሦሉስ [የሦስተዮሽ] ውል ተፈራረሙ” ብለዋል። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያዊያንን አይበገረነትና ቅኝ አልገዛም ባይነትን አያመለክትም።

በሌላም በኩል የአድዋን ድል ለመበቀል ዳግም በ1928 የመጣችውን ጣሊያንን እንግሊዝ የወጋችው በራሷ ሁኔታ ማለትም “ጣሊያን በሶሪያ፣ በፍልስጤም፣ በሳኡዲና በየመን የእንግሊዝን ጥቅም የሚጎዳ ሥራ በመስራቷ፣ ጣሊያን በእንግሊዝ መንግስት ላይ ጎጂ ፕሮፓጋንዳ በማካሄዷና ትልቁ ችግር ደግሞ የእንግሊዝ መንግስት በጣና ሐይቅ ላይ ግድብ እንዲሰራ ፈቃድ ለመስጠትና የኢትዮጵያንና የእንግሊዝን የምዕራብ የቅኝ ግዛት ወሰኖች ለማስተካከል ያደረገችውን ውል ላለመፈጸም ምክንያት እየደረደረች በማቆየቷ፤ ይባስ ብላም ጣሊያን ከተባበሩት ኃይሎች ጎራ ወጥቶ ከሂትለሩ ጀርመን አክስስ ጎራ በመቀላቀሉ የእንግሊዝ መንግስት የጣሊያንን ወረራ ያወቀበትን የ1930 ዓ.ም ውሳኔውን ሽሮ የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ንጉሠ ነገስትነት ማወቁንና ኢትዮጵያም ነፃ አገር መሆኗን የሚደግፍ መሆኑን ውሳኔ በማሳለፉ ነው።” ይላሉ ተፈራ ኃይለ ሥላሴ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው። ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛት ማለት ኢትዮጵያ በራሷ ጥረትና ጥንካሬ ቅኝ ሳትገዛ ቀረች ለማለት ሳይሆን በዋና ቅኝ ገዥዎቹ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን መሀከል በተፈጠረው መግባባት ወይም አለመግባባት መሆኑን መረዳት አያዳግትም። በመጨረሻም የእንግሊዝ መንግስት ዐፄ ኃይሌ ሥላሴን በካርቱም በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያደረገው ጉዞ በራሱ በእንግሊዝ ፍላጎትና መንገድ እንጂ በእንግሊዝ መንግስትና በኃይሌ ሥላሴ መሀከል አንዳች ጥያቄ ወይም ስምምነት ተደርጎ አልነበረም። እንዲያውም ጣሊያን የኃይለ ሥላሴን መመለስ ከሰማች በአሳቻ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ

ያላትን እምቅ ኃይል በመጠቀም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የሆነቸውን ሱዳንን ትወርራለች በሚል ስጋት፤ ንጉሱ ስለጉዞው ብዙ ዕውቀት ሳይኖራቸው እንደሆነ ተፈራ ኃይለ ሥላሴ በስፋት ገልጸዋል። ይህም ሆኖ ግን ንጉሱ መድረሻውን እንዳያውቅ ተደርጎ ሳይሆን እንግሊዞች ኢትዮጵያን በስልት ቅኝ ግዛት ለማድረግ ካላቸው ሕልም የተነሳ በሎንዶንና በሱዳን-ግብፅ ቅኝ ግዛቶቻቸው ተወካዮች ጋር ስለንጉሱ ጉዞ በቂ መረጃ አለመለዋወጣቸው እንደሆነ ዘውዴ ረታ አብራርተዋል።

በርግጥ ኢትዮጵያን ከቅኝ አገዛዝ ለመከላከል ከሦስቱ መንግስታት ጋር ምንሊክ በጋራም ሆነ በተናጠል ያደረገው የዲፕሎማሲ ግንኙነትና ነፃ ግዛጾችን ለመያዝ ያደረጉት እሽድምድም የሚደነቅ ቢሆንም፤ በተጨማሪም ከ1906 ጀምሮ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ቤት ቢውልም፤ በዚህን ጊዜ ዉስጥ ወይም በዚያዉ ዓመት መሞቱ ተደብቆ ባለበት ጊዜ ዉስጥ ጤናማ ሳለ ያዋቀረው ተደጋጋፊ የቤተክህነትና የቤተ መንግስት ሥርአት የማያፈናፍን ነበር። ነገር ግን የእነዚህ ባለሟሎቹ ታማኝነት ከሱ ተርፎ ለልጅ ልጁ ኢያሱ አልደረሰም። እንዲያዉም እያሱ ከጀርመንና ቱርክ ጋር እንደተባበረ በማስወንጀል ከአልጋዉ እንዲፈናቀል ተደርጓል። በዚህ ምክንያትም ከምንሊክ ጋር የነበረው የኃያላኑ ወዳጅነት በሚታወቅም ሆነ በማይታወቅበት ምክንያት ከኢያሱ ጋር አልዘለቀም። ከዚህ ጋርም የልጅ ኢያሱ ያልበሰሉ እርምጃዎችና በጉግማንጉግ (dogmatic) የምንሊክ ባለሟሎች ዘንድ ያልተለመዱ ድርጊቶች ዛፊሮ የተባለዉን ግሪካዊ የዉጪ አገር ዜጋን ጭምር ያሳተፈ የአድማ ጉባኤ እንዲፈጠርና ልጅ እያሱም ከአልጋዉ እንዲወገድ ተደርጓል።

ከላይ የተጠቀሱት ድርጊቶችና ዕርምጃዎች የኢትዮጵያን ቅኝ አለመገዛት የአነጋጋሪውን ንጉስ የአፄ ምኒልክን ጥንካሬ የሚያሳዩ ቢሆንና የሚሰራ ሰው በሰራው መጥፎ ነገር ሊወቀስ እንደሚችል ተሰምሮበት፤ ምንሊክ ለመስፋፋት ምክንያት የሆነውን የኤኮኖሚ መሠረት የሆነዉን የመሬት ስሪት ምንም ዕውቀት በሌላቸውና ብዙም አስተዋጽኦ በሌላቸዉ የወረሪው ወታደሮቻቸው እጅ እንዲያዝና እንዲቆይ ማድረጉ

ለምርታማነት ምንም አስተዋጽኦ ካለማድረጉም በላይ፤ ለወረራቸዉ መንስኤ የነበረውን የመሬት ፋይዳ ዋጋ አሳጥቷል፤ በአስተዳደርም በኩልም የኦሮሞ ሕዝብ ገዳን ጨምሮ የደቡብ ሕዝቦች ባህላዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የዕድገት ለውጥ እንዳያደርጉ በማድረግ በጣም ኋላቀር ለሆነና ከግብፆች ፍትሓ ነገስትና ክብረ መንግስት ለተወሰደ የባዕድ አምልኮ በማጋለጥ ዕድገታቸዉ እንዲገታ አድርጓል። በወራሪና ተወራሪ ሕዝቦች መሀከል የሚኖረው የሕብረተሰብ የዕድገት ደረጃ የተለያየ መሆኑ ቢታወቅም የወረሪዉ ፖለቲካዊ አመራር ከወቅቱ የተወራሪዉ ሕዝብ ፖለቲካዊ አመራር ያነሰ ከሆነ የአጠቃላይ ህብረተሰቡን የፖለቲካ አመራር ወደኋላ እንደሚጎትት ወይም እንደሚመልስ የታወቀ ሲሆን፤ በቤተክህነት የተተበተበዉ፣ ወራዊና ዓመታዊ ቀናትን እየቆጠሩ ሥራ አስፈች የአምልኮ ሥርአታቸውና የአበሻ የፖለቲካ አመራር ልምድ በምቀኝነት የተሞላ መሆኑ በአንፃራዊ መልኩ ዲሞክራሲያዊነት በነበረዉ የኦሮሞም ሆነ በሌሎች የደቡብ ሕዝቦች የፖለቲካ አስተዳደር ላይ በቀላሉ ሊላቀቁት የማይችሉትን ጫና ፈጥሯል። በምቀኝነት ላይ የተመሠረተዉ የአበሾች የፖለቲካ ጨዋታ ውሎ ሲያድር የራሱን የምኒልክን ቤተመንግስት በመነቅነቅ፤ ጣይቱና ዘዉዲቱ ከቤተመንግስት እንዲባረሩ፤ ልጅ ኢያሱ ከአልጋዉ እንዲፈነገል ብቻ ሳይሆን ሬሳዉ እንኳን እስከዛሬ የት እንደወደቀ ለማወቅ በማይቻልበት ዓይነት ሁኔታ እንዲደመደምና በቤተ መንግስት ውስጥ የተፈጸመው መፈንቅለ መንግስት ተፈሪ መኮንንን ለሥልጣን እንዲበቃ አድርጓል።

ከምኒልክ ሕልፈት በኋላ አልጋዉን ይረከባል ተብሎ ሲታሰብ የነበረዉ የተፈሪ አባት ራስ መኮንን በመሞቱ፤ ዕድሉን ያገኘዉና የተረከበዉ ልጅ ኢያሱ ነበር። ልጅ እያሱ እናቱ ከወሎ ከመጣችዉ ገረድ ተወልዳ እሷም ለአካለ ሔዋን ደርሳ ለወሎዉ ንጉስ መሀመድ አሊ (ራስ ሚካኤል) ከተዳረችው ከሸዋረገድ ምኒልክ የሚወለድ ልጅ ነዉ። ዛሬ ባለንበት ደረጃ እያሱ ሕዝብን ለማስተዳደር ቀርቦ ማወያየት አስፈላጊ መሆኑን የተገነዘበና በዚያ በለጋ ዕድሜዉ የሰጠዉ አመራር ትክክል ወደመባል ይቀርብ ነበር ለማለት ይቻላል። በሌላም በኩል ዛሬ ላይ ሆነን

ስንመለከተዉ አስቂኝ የሚመስለዉ በየአቅጣጫዉ ያሉትን ሕዝቦች ለማቀራረብ ሲባል፤ በኋላቀር ፊውዳላዊ አስተሳሰብ ውስጥ ኢያሱ አስር ያህል ሚስቶችን ማግባቱና ዕቁባቶችን በየቦታዉ ማስቀመጡ (ምናልባት የኢያሱ አስቂኝ ዲፕሎማሲያዊ ዘዴ ሊሆን ይችላል) ቤተመንግስቱ አከባቢ በተኮለኮሉት መኳንንት ዘንድ አልተወደደለትም። እንኳንስ ያኔ ቀርቶ ዛሬም ቢሆን የቤተክህነት እሳቤ የቤተ መንግስቱን ባለሟሎች አእምሮ ሰንጎ በያዘበት ዘመን ላይ እንዲዚህ ያሉ ያልተለመዱ ዕርምጃዎች መውሰዱ ውጤቱ አስቸጋሪ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። በሌላም በኩል ኢያሱ፤ ምንም እንኳን የምኒልክ የልጅ ልጅ ቢሆንም የኦሮሞ ደም ያለበትን ሰዉ ከሥልጣን ማግለል የሚለዉ የአበሾች (የአማራ፣ ትግሬና ኤርትራ) የቆየ አግላይ ፖለቲካ ኢያሱን ለአደጋ ያጋለጠ እንደነበረ መጠርጠር ይቻላል። እዚህ ላይ ቴዎድሮስም የቤተክህነት መሬትና ንብረት ወርሶ ለወታደሩ ማከፋፈሉና ለቴክኖሎጂ ግንባታ ማዋሉ ምን ያህል ጥላቻ ፈጥሮበት እንደነበረ በኢያሱ የአስተዳደር ዘመንም ተመሳሳዩ ድርጊት ለመፈጠሩ ወደኋላ ተመልሶ ሊታይ የሚችል ጉዳይ ነዉ። በዚህም ሆነ በዚያ በኢያሱ አስተዳደር፤ በአያቱ በምኒልክ ጊዜ የተጀመሩ የመዘመን ሥራዎች ቀጣይነት ሊኖራቸዉ አልቻለም። የልጅ ኢያሱ የለውጥ ፍላጎትና እሳቤ መሠረት ሊጥሉ ያልቻሉ ቢሆንም፤ በዚያችዉ አጭር ጊዜ ዉስጥ የወጡት ድንጋጌዎች የሕዝቡን ስሜት የሚነኩ ሆኖ፤ የአሮጌዉ ዘመን የምኒልክ ባለሟሎች የሸፍጥ ፖለቲካ ቀጣይነት እንዲኖረዉ አላስቻለም። የቤተክህነት ሰዎች ሳይቀሩ አቤቶ ኢያሱን በውሸት በመወንጀል ጭምር ወራዳ ሥራ ዉስጥ ገብተዋል። በሥልጣን ላይ ቆይታዉ አጭር ጊዜም ይሁን እንጂ አቤቶ ኢያሱ የወሰደዉ አንዳንድ የአስተዳደር ማሻሻያ እርምጃዎች በወቅቱ የሰዉን ችግር ፈቺ እንደነበሩ ተጠቃሽ ናቸዉ።

1. የወንድሙን ደም ለመመለስ ከወንድሙ ገዳይ ጋር በሰንሰለት ተቆራኝቶ የሚጉላላዉን ሰዉ ድርብ ግፍ እንዳይደርስበት ሲባል ጥፋተኛዉ በእግረ ሙቅ ታስሮ በዘበኛ እንዲጠበቅ አድርጓል።
2. ሌባ ሻይ ተብሎ የሚታወቀዉን የሌባ የምርመራ ዘዴ እንዲቀር ወሰኗል።
3. የመንግስት ግብር የጎደለበት ሰዉ ዋስ ጠርቶ ጉድለቱን እንዲከፍል፤

ዋስ እንኳን ቢያጣ መገረፉ ቀርቶ እንዲታሰርና እንዲከፍል ወስኗል፡፡

4. አስራት ለመሰብሰብ ሹም የሆነዉ ሁሉ በየገበሬዉ ቤት እንዳይዞርና ገበሬዉ እየደገሰ ሹሞችን አብልቶ የሚያሄይበትን የግፍ አሰተዳደር አስወግዷል፡፡ ነገር ግን ይህ ድርጊት በኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት አገርሽቶ ተመልሶበት ሰፋሪ ነፍጠኞች በየገባሩ ቤት እየተዘዋወሩ በመብላትና መጠጣት ብቻ ሳይሆን የገባሩን የትዳር ጓደኞችና ሴት ልጆችን ሲደፍሩ ነበር፡፡
5. ልጅ ያልወለደን ሰዉ ንብረት መንግስት መዉረሱ ቀርቶ ያ ልጅ ያልወለደዉ ሰዉ ሀብቱን ለቅርብ ቤተዘመድ ወይም ለሚያምነዉ ሰዉ እንዲያወርስ መቻሉን አውጇል፡፡ (ከታቦር ዋሚ መፅሐፍ ገፅ 527-529 በማሳጠር የተወሰደ)

ኢያሱ ከሥልጣን የተወገደዉ የቤተመንግስት ኩዴታ (palace coup) በሚባል ዓይነት ስልት ሲሆን፤ ከልጅ ኢያሱ ከሥልጣን መወገድ ጋር የተፈጠረዉ የንግስት ዘውዲቱና የተፈሪ መኮንን መንግስት በዛሬ አተያይ ጥምር መንግስት ይመስላል፡፡ ልጅ ኢያሱ እራሱ በሕዝብ መሀከል ተዘዋውሮ ያደረገውን እንቅስቃሴ ያህል ቤተ መንግስቱንም ከአያቱ ቅሪቶች ለማጽዳት ያደረገው ጥረት ወይ አልነበረም ወይም አነስተኛ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ከወሰዳቸው ዕርምጃዎች የሚጠቀሱ ቢኖሩ እንኳን የራሱ የሥልጣን ተቀናቃኝ ይመስሉ የነበሩ እተጌ ጣይቱን ወደ እንጦጦ፤ ዘውዲቱን ወደ መናገሻ መስደዱ ሥልጣኑ የሚጠገን መስሎት ቢታይም፤ በተጨማሪም የቤተክህነትና የቤተመንግስት ባለሟሎች በየግዛቱ ከሱ ጋር እንዳይዘዋወሩ እገዳ የጣለባቸዉ የቤተ ክህነት ሰዎች የኢያሱን ሥጋ በአክስቱ በዘዉዲቱ አጥንት ለመጥበስ ሲሉ በአገኙት አጋጣሚ እሷን ንግስት፣ ተፈሪን ደግሞ እንደራሴ ብለው በመሰየም ኢያሱ እንደወጣ እንዲቀር አደረጉት፡፡ ከብዙ እስር በኋላም አፄ ኃይሌ ሥላሴ ከጣሊያን ወረራ ሸሽት ወደ አውሮፓ ለመሄድ በተነሳ ጊዜ እያሱን ገድሎ ጉዞ እንደጀመረ በጽሑፍ ማስረጃ ያልተደገፈ ጥርጣሬ ዛሬም ድረስ ይናፈሳል፡፡ እንደ ዘውዴ ረታ፤ <u>የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ መንግስት</u> (2005) ደግሞ ልጅ ኢያሱ የሞቱት በሁለት ምክንያቶች (የቆየ የልብ ሕመም እና በንጉሱ እጅ

መገደል) እንደሆነ የሚጠረጥሩ ሰዎች ስለመኖራቸው ጽፈዋል። የትኛው ያመዝናል ቢባል ደግሞ አሁንም ዘውዴ ረታ በዚሁ መጽሐፍ እንደገለጹት አባ ጤና ኢያሱ የተገደሉት በንጉስ ኃይለሥላሴ እጅ መሆኑ ጥርጣሬው ሰፊ እንደሆነ ነው። ፀሐፊው ምክንያቱን ሲያስረዱም ኃይሌ ስላሴ ወራሪውን ጣሊያንን ለመውጋት ወደ ማይጨው ሊጓዙ ሲሉ ልጅ ኢያሱን ለሙሶሎኒ የፖለቲካ መጠቀሚያ ትተው ለመሄድ አለመፈለጋቸው እና ልጅ ኢያሱ ከተገደሉም በኋላ አስከሬናቸውን ለተወላጆቻቸው አለመስጠት ኢያሱ አባ ጤና ከዚህ ዓለም የተለዩት በሕመም ወይም በድንገተኛ አደጋ ሳይሆን በፖለቲካ ውሳኔ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ንጉስ ኃይለ ሥላሴ የልጅ ኢያሱ ገዳይ ለመሆኑ በማረጋገጥ የፃፉት ተፈራ ኃይለ ስላሴ የቱርክና ጀርመን መንግስታት ወዳጅ የሆነውን የአቤቶ ኢያሱን መንግስት ማስወገዳቸውን ወደ እንግሊዝ መንግስት የላኩት የልዑካን ቡድኑ በአጋጣሚው እንዲገልጹ መደረጉን በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ላይ ገልጸዋል። እዚህ ላይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ሥልጣን የሚቀባበሉት እርስ በርስ በመጠፋፋት እንደነበር ከምንሊክ ዙፋን ወራሾች መተላለቅ መረዳት የሚቻል መሆኑን ነው።

ስለ ልጅ ኢያሱ አሳዛኝ አወዳደቅ ብዙ አዋቂዎች የፃፉ ቢሆንም፤ ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ከላይ ባልታተመ ተብሎ በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፉ ውስጥ ስለአወዳደቁና ተከትሎት ስለመጣዉ የኢትዮጵያ የሀገረ መንግስት ግንባታ ችግር “ልጅ እያሱ በእኩልነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ልዩ ዕድል የነበረውና ያንንም ልዩ ዕድል አውቆ ለመጠቀም ሲሞክር በወጣትነት ዕድሜው ላይ የተቀጨ መሪ ነበር። ኢያሱ ብሔር ግንዱ ኦሮሞና አማራ የነበረ፤ በሃይማኖት ጀርባው ክርስቲያንና ሙስሊምን ያጣመረ የነበረ ሰው ነው። ከወሎ በመወለዱ ትግራይንና ሸዋን ለማገናኘት የተሻለ ድልድይ ለመሆን ይችል ነበር። የሚገርመው ግን በሐበሻ የምቀኝነት ግንኙነት ውስጥ የልጅ እያሱ ወንጀሎች የሚመነጩት እነዚህኑ አዎንታዊ እሴቶችን ለኢትዮጵያ የሀገረ መንግስት ግንባታ ለመጠቀም መሞከሩ ነበር።” ብሏል። እንግዲህ፤

ምንም እንኳን በገዥዎቹ መሳፍንትና መኳንንት መሀከል ክፍፍል የነበረ መሆኑ ቢታወቅም፤ ክፍፍሉ ከታወቀው የፊውዳል ምቀኝነትና ከደብተራ መጠላለፍ አልፎ ከዚህ ቀደምም ሆነ ዛሬ የምናውቀውን የፓርቲ ፖለቲካን ጥንስስ የሚያሳይ አልነበረም። አንድ ተሰምሮበት ሊታወቅ የሚገባ ነገር ቢኖር ግን እያሱን የመሳሰሉ ብሩህ አእምሮ ይዘው የሚነሱ ማናቸውም ሰው ባለፉት ሥርአታትም ሆነ ዛሬም ድረስ በሐበሻ ገዥዎች ዘንድ እንደማይበረክት ነው።

## ኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ሥርአቱ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችና የፓርቲ ፖለቲካ ጥንስስ

በወላጅ ስያሜ ተፈሪ መኮንን በክርስትና ስም ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ማነዉ? እንዴትስ የሥልጣን እሽክርክሪት ዉስጥ ገባ? የተከተለው የአመራር ዘይቤ ምን ይመስል ነበር? ከአፄ ምኒልክ እስከ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ድረስ  የነበረዉ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ምን ይመስሉ ነበር? ቤተመንግስት አከባቢ ከተሰባሰቡት የንጉስ ባለሟሎች የግልና የቡድን ሽኩቻዎች በመላቀቅ በኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ቅርጽ መያዝ የጀመረዉ የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ምን መልክ ይዞ ተከሰተ? እና ዛሬስ ምን ዓይነት የዕድገት ለውጥ አሳይቷል? የሚሉ ጥያቄዎችን በተወሰኑ ደረጃ አንስቶ መዳሰስ የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ እንደ አጀንዳ ተነስቶ ሊያወያይና ቁም ነገርም ሊያስጨብጥ ይችላል ብዬ አምናለሁ።

ሐምሌ 16 ቀን 1884 በሐረር ግዛት በኤጀርሳ ጎሮ አዉራጃ ዶባ ቀበሌ ከአባቱ ራስ መኮንን ወልዴሚካኤል ጉዲሳ እና ከእናቱ የሺእመቤት ዓሊ (እሱም ሆነ ብጤዎቹ ከተፈጠረባቸው የማንነት ቀውስ የተነሳ የየሺእመቤትን አባት ስምና የኦሮሞነት የትዉልድ ሐረግ ለመጥራት ባይሹም) የተወለደው ተፈሪ መኮንን፤ በራስ ፍላጎት ይሁን በባለሟሎቹ ግፊት እንደሆነ አይታወቅም፤ በአባቱ በኩል የተወለደበትን የኦሮሞ ብሔርን በመካድ በአጎቱ በኩል ብቻ ባለበት የደም ትስስር በመሳብ ከአማራዉ ብሔር እንደተወለደ ተደርጎ የሚወሳበት ጉዳይ ነዉ። ይህ

በእንዲህ እንዳለ ስለዘር ሐረጉ መሸፈኛ ከፈለጉለት ምሁራን ዉስጥ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 139) እንደፃፉት “ተፈሪ እንደ ዘዉዲቱ ሁሉ የንጉስ ሣህለ ሥላሴ ዝሪያ በመሆኑ ለዙፋኑ እኩል ብቃት ቢኖረዉም አልጋ ወራሽነቱን ያገኘዉ በዘር ቆጠራ ብቻ ሳይሆን የሌጋሲዮኖቹ ወዳጅ በመሆኑና በመጠኑም አዉሮፓ ቀመስ ትምህርት [ፈረንሳይኛ] ስለነበረዉ ነዉ።” በማለት ተፈሪን ከኦሮሞነት ማራራቅ የሚመስል ሥራ ሰርተዋል። በሚያስተዛዝብ ሁኔታ አገዛዙን ከመጽሐፍ ቅዱስ የይሁዳዊያን የሃይማኖት ቲዎሪና ፕሮፓጋንዳ ጋር በተለይም ራሳቸውን ከንጉስ ሰለሞንና ክርስቶስ ጋር በማያያዝ፤ ተፈሪም ሆነ ባለሟሎቹ አነስተኛ የአማራ ደም ትስስርን በማጉላት የአበሻ ፖለቲካ የበላይነት ልክፍት (addicted snob) ጫፍ ያደረሱበት ጊዜም ሆነ ያበቃበት ጊዜ ቢኖር ይህ የተፈሪ መኮንን አገዛዝ ጊዜ ነበር። ከተፈሪ መኮንን (ዐፄ ኃይለ ሥላሴ) ከሥልጣን መወገድ ወዲህ የዘዉድ አገዛዝ ሙት መንፈስ (zombie) ተመልሶ ሊያንሰራራ ሙከራዎች ቢኖሩም ጊዜዉም ሆነ ትዉልዱ እየራቀዉ ከመሄዱ የተነሳ ተስፋዉ የመነመነ ነዉ።

ክብረ ነገስት፤ ንግስት ሳባና ብቸኛ ልጇ ምንሊክ በዋልስ ባጅ ተጽፎ በፀጋዬ ሸንበር ወደ አማርኛ በተመለሰው መጽሐፍ ገጽ 23 ላይ እንደተፃፈው “የኢትዮጵያ ንጉስ ለሕዝቦቹ አምላክም ንጉስም ነው” እንደሚሉ ሁሉ ተፈሪም ራሱን ከሰለሞናዊ ዘር ጋር ማቆራኘቱ ለመለኮታዊ ሥልጣን ጉዳይ የበለጠ ትኩረት የሰጠበት ጊዜ ስለሆነ ሳያስገርም አያልፍም። እሱም ሆነ ቀደምት ንጉሶች (ተክለ ጊዮርግስና ዮሐንስን ሳይጨምር) ከሙቼ ጀምሮ ከሰሎሞናዊ ሥርወ-መንግስት ጋር እንደሚዳተቱ ፍንጭ የሚሰጡን ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 7) የኢትዮጵያ ታሪክ በሚለዉ መጽሐቸዉ ዉስጥ “ይኩኖ አምላክ በ1262 የመሠረተዉ ሥርወ መንግስት “ሰለሞናዊ” በሚል ስያሜ ይታወቅ ነበር። ይህን ስያሜ ይኩኖ አምላክና ተከታዮቹ የመረጡት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የተወለዱና ‘ሐቀኞቹ’ የኢትዮጵያ ነገስታት መሆናቸዉንና ሥልጣናቸዉም ሕጋዊና መለኮታዊ መሠረት ያለዉ መሆኑን ለማሳየት፤ በአንፃሩም የዛጉዌ አገዛዝ ሕገ ወጥ እንደነበር ለማመልከት ነዉ።”

ብለዋል።

እዚህ ላይ ቀዳማዊ ምኒልክ ማነዉ ለሚለዉ ጥያቄ የሚሰጠዉ መልስ፤ ከንጉስ ሰለሞንና ንግስት ሳባ የሚወለድና የኢትዮጵያ ደም ያለዉ ትውፊታዊ (አፈ ታሪክ) ንጉስ ስለመሆኑ የሚነገርለት ነው። ንግስት ሳባ እራሷ የኢትዮጵያ ወይስ የየመን ንግስት ትሁን/አትሁን ባልለየለት የታሪክ ፈተና ውስጥ ምሁራንም የሚስማሙበትም ሆነ የማይስማሙበት ሁኔታ ቢኖርም፤ ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄ የተሟላ መልስ ባልተገኘበት ጊዜ ዉስጥ አፄ ቴዎድሮስም ሆነ ተፈሪ መኮንን በሰለሞናዊ ጥበብ ስም ሕዝብ ላይ ለመፈናጠጥ የተጠቀሙበት ስልት እንደነበረ መገመት አያስቸግርም። ለማንኛዉም ትውፊታዊ ታሪክ መኖሩ ጠቀሜታዉ ብዙም የጎላ ባይሆንምና ትዉፊት በመኖሩ የከፋ ጉዳትም ባያደርስም፤ እነዚህ ነጋሲያን ሰለሞናዊ የዘር ሐረግን ለምን የሙጥኝ እንዳሉ በጥልቀት መፈተሹ የታሪክ ተመረማሪዎች አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

በመጀመሪያ ነገር ንጉስ ሰለሞን አባቱ ንጉስ ዳዊት ከትዳር ዉጭ ከኦርዮን ሚስት የሚወልደዉ (የማቴዎስ ወንጌል ም.1ቁ. 6ን ይመልከቱ) ሴማዊ ነዉ/ነበር። እራሳቸዉን ከሰለሞን ዘር የሚያቆራኙት ደግሞ ትውልዳቸዉን ከኖኅ ልጆች ጋር፤ በተለይም ራሳቸዉን ከሴም ወይም ከሴሜትክ የዘር ሐረግ ጋር ለማስተሳሰርና ይኼዉ የዘር ሐረግ ከካም ትውልዶች በላይ ምርቃት እንዳለዉ ለማሳየት ፈልስፈውና አልመዉ የተነሱ መሆኑን ልብ ማለት ያሻል። ሴት ልጅ ድንግልናዋን ጠብቃ ካልቆየች በስተቀር የአባቷን ወይም የሳባዊያንን ዙፋን አትወርስም የሚለውን የሳባዊያንን ድንጋጌ በመፍራትም ሆነ ከሥጋዊ ፍላጎት የመነጨ በሚመስል ሁኔታ ጥበበኛዉን ሰለሞንን ለማየት ወደ እየሩሳሌም ተጉዛ ነበር የተባለችዉ ንግስት ሳባ ወይም ማክዳ ዕውን የኢትዮጵያ ትሁን የየመን ንግስት የታሪክ ባለሙያዎቹ ባልተስማሙበት ሁኔታ፤ ከዚህ ትውፊት ጋር የተነሳዉ በሽታ ያልተላቀቃቸው ሰዎች ዛሬም ድረስ ስለመኖራቸዉ አንድና ሁለት የለዉም። ንጉስ ኃይሌ ሥላሴም ሆነ

ቀደምቶቹ (አሁንም ተክለ ጊዮርግስና ዮሐንስን ሳይጨምር) እራሳቸዉን የአበሻ ወይም የየመን ወይም የሁለቱም የጋራ ንግስት ነበረች ከተባለችዉ ከንግስት ሳባ እና የቅድስት አገር ናት በሚሉት የእየሩሳሌም ገዥ ከነበረዉ ከንጉስ ሰለሞን የጥበብና የፍቅር ግንኙነት ላይ ተመርኩዞ ከተወለደዉ  ቀዳማዊ ምኒልክ ጋር የአገዛዝ ግንዳቸዉን ለማስተሳሰር ፈልገዉ ይሆናል። በነገራችን ላይ ቀዳማዊ ምንሊክ ሲወለድ እናቱ ያወጣችለች ስም ኢብነ-መለክ ማለትም የንጉስ ልጅ ማለት እንደሆነና በጊዜ ብዛት ምንሊክ እንደተባለ፤ ትርጓሜዉም የብልህ ልጅ እንደሆነ ወይዘሮ ሠናይት ተክለማርያም፤ የብላተን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ የልጅ ልጅ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስት ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል</u> ብለዉ ባሳተሙት መጽሐፍ ገጽ 4 ላይ ገልጸዋል።

በዕውን ንግስት ሣባ የኢትዮጵያ ንግስት መሆኗ ቢረጋገጥ እንኳን የእርሷ የንግስ ታሪክ የሥርወ መንግስት ታሪክ ነው እንጂ የሕዝብና የአገር ታሪክ አለመሆኑን ዛሬ ተሰምሮበት ሊታወቅ ይገባል። እንግዲህ ይህ የንግስ ነገር ከመስመሩም እየወጣ የሚጎናጸፉት ከሆነ በጣም ኋላቀር በሆነውና ፖለቲካን አምላኪ በሆነው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ውስጥ ቀጥሎ የሚመጣው ገዥ ጭምር ተነስቶ የነጋሲነቱ መነሻ ምን እንደሆነ የሚነግረንን ማወቅና መገመት ቢያስቸግርም፤ በእንዴዚህ ኋላቀር ሕብረተሰብ ውስጥ አንድ የአከባቢ ቃሊቻ ወይም በራሳቸው አኳኋን ንጉስ ነህ ብሎ አንዱ ወይም አንዳቸው ከዘባረቁለት፤ ንጉስ ነኝ የሚል ሰው እንደማይጠፋ ከጥርጣሬ በዘለለ ደረጃ መፍራት እንደሚቻል ቢታሰብ ላያስወቅስ ይችላል።

ዐፄ ቴዎድሮስም ሆነ ኃይለ ሥላሴ ለሥልጣናቸው መሠረት ያደረጉትን የንግስት ሳባን የጥበበኛ ባል (ወንድ) ፊለጋ ጉዞንና የኢትዮጵያ ንጉስ መውለድን ወደ ጎን ትተን፤ እነዚህ ገዥዎች ከምን ተነስተው ነው ንግስናቸውን ከንጉስ ሰለሞን የዘር ግንድ ጋር እንዲያስተሳሰሩ የተገደዱት የሚለውን አንዳንድ ዳሰሳዎችን ከፀጋዬ ሽንበሩ መጽሐፍ ላይ በመመስረት የማወቅ ፍላጎትን መጋበዝ ተገቢ ይሆናል።

1. ቴዎድሮስ ወደ ሥልጣን ወጥቶ በነበረበት ጊዜ ኢየሩሳሌም በሙስሊም አገሮች የተከበበች ስለነበር እና እነዚያ ሙስሊማን የቴዎድሮስ ኢትዮጵያንም ለመውረር እየተንደረደሩ ስለነበር የክርስትና ሃይማኖትን ከሚከተሉ ሀገሮች ጋር በመሞዳሞድ ለራሱም መስፋፋት የጦር መሳሪያን ለማግኘት የዘየደው ስልት ሊሆን ይችላል።
2. ሁለተኛው ጉዳይ ታሪኩ ሰፊ ነው። ይኼውም "የንጉስ ዳዊት ግዛት ከልጁ ከእስራኤል ንጉስ ሰለሞን ወደ ንጉሶች አገር ወደ አብሲኒያ የተዘዋወረበትን ምስጢር" ከገጽ 33-35 ላይ ሲያብራራ የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ይገኙበታል።
   ሀ. ለንጉስ ሰለሞን ያረገዘችው ንግስት ሳባ "ወደ ግዛቴና አገሬ መመለስ እፈልጋለሁ። ልጅህን በተመለከተ ምን ማድረግ አለብኝ?" ብላ ጠየቀችው።
   ለ. ንጉስ ሰለሞንም "ወንድ ልጅ ውለጂልኝ፤ ካደገ በኋላ ወደኔ ላኪው፤ እኔም ንጉስ አደርገዋለሁ። የእኔም ግዛት [ያ ግዛት እየሩሳሌም ወይም ኢትዮጵያ ይሁን ባልተለየ ሁኔታ] የሱ ይሆናል" ብሎ መለሰላት። በነገራችን ላይ ንጉስ ሰለሞን ከሕጋዊ ሚስቱ ማቅሳራ (የግብፁ ንጉስ ፈረኦን ልጅ) ወንድ ልጅ እንዳልወለደ ከመነገሩ ዉጭ ሴት ልጅ ስለመዉለዱም የተባለ ነገር እንዳለ አላወኩም።
   ሐ. "ንግስቷም ቀኗ ሲደርስ ወንድ ልጅ ወለደች። በደስታ ተውጣ ስሙን ዳዊት አለችው።" ዳዊት የአያቱ የሰለሞን አባት ስም መሆኑ ነው።
   መ. የተወለደው ልጅ አድጎ ወጣት ሆኖ "አንድ ቀን … አባቴ ማነው? … ሲል ጠየቃት።" እሷም ነገረችው። ወጣቱም አባቱን ጎበኘ። "ሰለሞንም ልጁን በአባቱ [ዳዊት] ዙፋን ላይ አነገሰው።" ከንግስት ሳባና ከንጉስ ሰለሞን የሚወለደው ወጣቱ ዳዊት በአያቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ነገሰ ማለት ነው። የአያቱ ዙፋን የሚገኘዉ ደግሞ በኢየሩሳሌም እንጂ

በኢትዮጵያ አልነበረም፡፡

ሠ. ከአባቱ ከሰለሞን ጋር ለተወሰነ ጊዜ የቆየው ወጣቱ ዳዊት ታቦት ይዞ ወደ እናቱ አገር ለመመለስ ፈለገ፡፡ ሰለሞንም በተዘዋዋሪ መንገድ ፈቀደለት፡፡ ወጣቱም ታቦቱን ይዘው የሚሄዱለትን አራት ቄሶችን አስገደደና አሽከሞአቸው ጉዞውን ጀመረ፡፡ (ይህ ጊዜ ምልባትም የጵላት ስርቆት በቀዳማዊ ምንሊክ የተጀመረበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡)

ረ. “ወጣቱም በሰላም ወደ አገሩ ሲቃረብ እናቱ ተቀበለችው፡፡ [ኢዩሩሳሌም ሳይሆን አብሲኒያ በሚገኘው] በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ነገሰ ማለት ነው? የአብሲኒያም ግዛት ከዳዊት ዙፋን ጋር ለዘላለም የተሳሰረ ሆነ” ይላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ኢዩሩሳሌም የሚገኘው የሰለሞን አባት የዳዊት ዙፋን ከኢየሩሳሌም ወደ አብሲኒያ ተስፋፍቶ የኢትዮጵያ ነጋሲያንም ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር አዛምደው ተገኙ ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ደግሞ ምንም ማለት ሳይሆን ለክርስቶስ ተወላጁ ሰለሞን የተሰጠዉ የአገዛዝ ጥበብ ለኛም ያካፋልናል በማለት ለሥልጣን መንጠላጠያ ሰበብ ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር ትዉፊታዊ ተረቱ ወንዝ የሚያሻግር ሆኖ አይደለም፡፡ ይህ ትርክት በዐረብኛ ቋንቋም ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ ተፅፎ እንደሚገኝ ፀሐፊው ፀጋዬ ሽንብሩ ገልፀዋል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ መታወቅ ያለበት አንድ ሕዝብ መሪዎቹን ጨምሮ ትውፊታዊ ታሪክ (legend) ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡ ትውፊታዊ ታሪክ በመኖሩ ብዙም አሳሳቢ አይሆንም፤ ወይም ጉዳት አይኖረዉም፡፡ ጉዳት የሚኖረዉ ግን ትውፊቱን ወደኋላ ተመልሶ የሚቆጥረዉ ባለትውፊቱ የሆነዉ ሰዉ ከትውፊቱ ጋር ምንም ቁርኝት ከሌለዉ ሌላ ሕዝብ ጋር ያንን ትውፊት አንስቶ የሚያጣብቅ ከሆነና ትውፊቱም ማረጋገጫ ከሌለዉና የተረጋገጠም ከሆነና ትውፊቱና እዉነታዉ የማይገጣጠሙ ከሆነ ትርፉ ቅሌት ሆኖ እዚያዉ ላይ የሚያበቃ ይሆናል፡፡ ለቀጣይ ትውልድም የታሪክ ነቀርሳና የአብሮነት ሕይወት ጉዞ አሰናካይ

ይሆንና በቀላሉ የማይላቀቁት ችግር ሆኖ እዚያዉ ላይ ያበቃለታል። በዚህም መሠረት አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ምኒልክና አፄ ኃይሌ ሥላሴ (ወደኋላ እንዉሰድ ከተባለ ደግሞ ይኩኖ አምላክን ይጨምራል) የዘር ሐረጋቸዉን ከሰለሞናዊ የዘር ግንድ ጋር ማላከካቸዉ ለቀድሞዎቹም ሆነ ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን የፈየዳቸዉ አንዳች ነገር አልነበረም፤ ቢኖርም ደግሞ መጨረሻቸው በቅሌት ተደምድሟል። ዛሬም ያንን ታሪክ የሚያቀነቅኑ ሐበሻ ወንድሞቻችን ቢኖሩ ከተናጠል ትውፊት ይልቅ ኢትዮጵያዊያን አዲስ የጋራ ታሪካችንን በሕብረ ብሔራዊነት ብንገነባ ተመራጭነት ይኖረዋል። በቅርቡ ሐገራዊ ብሔረተኝነት እና ዘውጋዊ ብሔረተኝነት በኢትዮጵያ (ገጽ 32) ብሎ የፃፈው አምሃ ዳኘው ተሰማ “ይኼ የሰለሞናዊ ዝርያነት ትርክት በሐሰት ፈጠራ ሥልጣንን ከዛጉዌ ሥርወ መንግስት “ሰለሞናዊ” ነው ወደ ተባለለት ሥርወ መንግስት ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ የዋለ ከንቱ ውዳሴ ነው” በማለት የሰላቢዎች መቃብር እንዲጠልቅ ነግሯል።

ከንጉስ ምንሊክ ቀብር (1909) በኋላ ጀምሮ ሁለቱ ንግስት ዘውዲቱና ራስ ተፈሪ በጋራ ሥልጣናቸውን እስከሚያጠናክሩ እስከ 1916 ድረስ የነበረው ጊዜ የሁከትና የመገፋፋት ጊዜ እንደነበርና ነገር ግን በ1913 ልጅ ኢያሱን ገልብጠዉ የጥምር ሥልጣን የሚመስለዉን የተቆናጠጡት ንግስት ዘዉዲቱና እንደራሴዉ ተፈሪ መኮንን ቢሆኑም፤ ተፈሪ ግን ድብቅ ፍላጎቱን በመጠቀም በ1921፣ መስከረም ወር ዘዉዲቱን በማስወገድ ንጉስነቱን የውጪ አገር ልዑካን በተገኙበት አረጋግጦ፤ የንግስ በዓሉን ደግሞ ጥቅምት 23፣ 1923 አከበረ። ከዚህ ቀደም ብሎ ግን በ1916 ተፈሪ ኢትዮጵያን የዓለም መንግስታት ማህበር አባል እንድትሆን ለማድረግ በማስቻሉ ዝናዉ እየገነነ መጣ። ያ የውጪ አገር ጉዞ ለተፈሪም ሆነ ለተከታዮቹ የዓይን መክፈቻ ከመሆኑም ሌላ የተፈሪ ተቀናቃኝ የነበሩ ሳይቀሩ አምነው እንዲያድሩለት ሳያስገድዳቸዉ አልቀረም። ነገር ግን የራያ አሰቦን ሕዝብ በማስተባበር ተፈሪ ላይ አምጾ የነበረዉ ጉግሳ ወሌ መጋቢት 22፣ 1922 አንችም በሚባል ቦታ ላይ ጦርነት ገጥሞ በመሸነፉ፤ ባለቤቱ ዘዉዲቱ ደግሞ ቀደም ሲል የነበረባት ሕመም ላይ የባሏ መሸነፍ

ተደምሮ ድንጋጤ ስለፈጠረባት የሳምንታት ዕድሜ እንኳን ሳትቆይ ሕይወቷ አለፈ፤ ወግ አጥባቂ ባለሟሎቿም አርፈዉ እንዲቀመጡ ሲደረጉ የኋላ ኋላ ሞትም ሰብስቧቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነገር ቢኖር ንግስት ነገሰታት ዘውዲቱ “ባባታቸው ዙፋን ተቀምጠው የተደላደለ ሥልጣን እያላቸው በተስፋ ቆራጭነት ስሜት የሃይማኖት ደጀ ሰላም ከማውዘተር ውጭ ሥልጣናቸውን አጋንነው ሊሠሩበትና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጭቅጭቅ ውስጥ ለመግባት አልፈለጉም” ነበር ብለው ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ ጽፈዋል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከብዙ በጥቂቱ አንድም በተገቢ ጊዜና ቦታ የሚጠቀሙበት የማስተዳደር በቂ ዕውቀት እንዳልነበራቸው ወይም ለተፈሪ የወገኑ የአባታቸው ባለሟሎች የሚያደርሱባቸውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚያስችላቸውን የአመራር ስልት ማጣት አመላካች ነው፡፡

በአልጋ ወራሽነት ጊዜው ውስጥ ተፈሪን በዓለም አቀፍ መድረክ ፊት ከፍ ሊያደርጉ የቻሉ ሁለት ጉልህ ሥራዎችን አከናዉኗል፤ ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ሊግ እና የዓለም ቀይ መስቀል ማህበር አባል እንድትሆን አስችሏል፡፡ በሀገር ዉስጥ ደግሞ፤ (ምንም እንኳን ነፃ ለመውጣት የፈለገ ባሪያ በዳኛ ፊት አረጋግጦ ነፃ መውጣት ይችላል ቢባልም) ሰውን በባርነት መሸጥ እንዲቀር እርምጃ ከመዉሰዱም በላይ ከቀደምት ጊዜያት ገዥዎች ጀምሮ ክፍተት ይታይበት የነበረዉን የሥልጣን ሽግግር ለማመቻቸት በ1923 አስተዳደሩ ሕገ መንግስታዊ መልክ እንዲኖረዉ እርምጃ ወስዷል፡፡ በዚህም መሠረት ከ1889ኙ የጃፓን ሕገ መንግስት ጋር በብዙ መልኩ ቅርብርብ የነበረዉን ሕገ መንግስት በበጅሮንድ ተክለሐዋሪያት ተክለማርያም አማካይነት ተረቆ ለዉይይት ለመሳፍንቶቹ ቀርቧል፡፡

ምንም እንኳን የሕገ መንግስቱ ረቂቅ ለመሳፍንቶቹ ውይይት የቀረበ ቢሆንም መሳፍንቶች በሚባሉ መሀከል በተፈጠረው መወዛገብ የተነሳ በማሻሻያነት አንዳች ያደረጉት ለውጥ አልነበረም፡፡ እንደወጣቱ ንጉስ ፍላጎት “ዓለም በሥልጣኔ እጅግ በገሰገሰበት ዘመን፤ መንግስት በሕዝብ እየተመረጠ፤ ለሕዝብ አገልጋይ ሆኖ ግዳጁን ከመፈጸም በስተቀር

ለሕዝብ የሚያደርገው ቸርነት የለም" በማለት ያሳየውን የለውጥ ፍላጎት መሳፍንቶቹ አልተቀበሉም ይላሉ ዘውዴ ረታ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው (2005፡ 22) ላይ። ዘዉዴ ረታ በመቀጠልም፤ "የአብዛኛዎቹ መሳፍንትና መኳንንት አስተያየት … ለኢትዮጵያ አስተዳደር፤ የፈረንጆቹን አሰራር መቅዳት፤ ከአባቶቻችን ሲያያዝ የመጣውን አኩሪውን ልማዳችንና ሃይማኖታችንን የሚያበላሽ ከመሆኑ በስተቀር ጥቅም ይኖረዋል ብለን አናስብም።" በማለት የተራማጅ መሳፍንቶችን ሐሳብ ውድቅ አድርገዋል። ከዚህም የተነሳ ተፈሪ መኮንን ልጅ ኢያሱ በጉግ ማንጉግ መሳፍንቶች ተጠልፎ በተጣለበት ሁኔታ እንዳይወድቁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ እንዳልቁ እኒሁ ፀሐፊ ሳይጠቁሙ አላለፉም። የተቀረጸው ሕገ መንግስትም ንጉሱን ያማከለ ሥልጣን ስለመኖሩ እና ወራሴ መንግስትም ከአባት ወደ ልጅ እንደሚተላለፍ፤ እንዲሁም የንጉሱ ሥልጣን ከሰለሞናዊ የዘር ሐረግ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑንና ከዚህ ለመውጣት ማሰብ ራሱ የሚያስቀስፍ መሆኑን በሚያመላከት አኳኋን ተቀረጸ። ተፈሪ የመኮንን ወልደሚካኤል ጉዲሳ ልጅ ንግስናውን ከኢዩሳሌሙ ንጉስ ሰለሞንና ከንግስት ሳባ [ማክዳ] የዘር ትስስር ሐረግ ጋር በማስተሳሰር ከቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ትውልድ እንዳይወጣ በሕግም አስደንግጓል።

ከ1916 እስከ 1918 በእንደራሴነት፣ ከ1918 እስከ 1923 በአልጋ ወራሽነት እና ከ1923 እስከ 1966 ድረስ ደግሞ በንጉስነት በጠቅላላዉ ለሃምሳ ሦስት ዓመታት ያህል ሥልጣን ይዞ የቆየዉ የኃይሌ ሥላሴ መንግስት የሁለተኛዉን የዓለም ጦርነት በተወራሪነት፣ በሽሽትና በስደት ያሳለፈ መንግስት፤ በዘመኑ በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ የፖለቲካ ለዉጦች በተከሰቱበትና በተከናወኑበት ጊዜ ዉስጥ በታለፈበት ዉስጥ ሕዝቡ ከኋላቀርነት ባይላቀቅም የፖለቲካ ሥልጣን እሳቤም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች ያቆጠቆጡበትና ሥልጣን መሰላል ላይ ለመዉጣት ያለሙበት ጊዜ ቢኖር በዚሁ በአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ጊዜ ውስጥ ነው።

የወቅቱ የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ በማስገደዱ አፄ ኃይሌ ሥላሴ ከኢትዮጵያ ውጭ በመዳዳዙ ከሌሎች ቀደምት ነገስታት የተሻለ ቢያደርገዉም፤ በተለይም ከአሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ መንግስታት ጋር የነበረዉን ግንኙነት በመጠቀም ያደረገዉ የአመራር ወይም አስተዳደር ማሻሻያ ከአፄ ምኒልክ ዘመን አገዛዝ ጋር ሲመዛዘን የተሻለ አልነበረም። የካቢኔ ሚኒስትሮች ቢሰየሙም የሥልጣን ትስስሩ ከደም ግንኙነት አልፎ ቴክኖክራቶችን (የቴክኒክ ባለሙያዎች) ያካተተ አልነበረም። አልፎ አልፎ ከደም ትስስር ውጭ የተገኙ ባለሥልጣኖች እንኳን ቢኖሩ ራሳቸዉንና የመጡበትን ሕብረተሰብ በጅምላና በችርቻሮ በአደባባይ የሸጡ ርካሽ ሰዎች ነበሩ እንጂ ሕዝባዊነት የነበራቸው አልነበሩም። በተለይ ለተማሩ ሰዎች የተሰጠው ቦታ የለም ባይባል እንኳን እጅግ በጣም አናሳ ነበር። በዚህ መሠረትም የተማሩ የአገሪቱ ሰዎች ከመናኛ ሹመት ሳያልፉ ቁልፍ የሚኒስትርነት ቦታዎችን ፊውዳል ባለሟሎችና የቤተክህነት ሰዎች እንዲተኙበት አድርጓል። በአጭር አገላለጽ ከዓለም የዕድገት ሁኔታ እና የከዚያን ጊዜ ወጣት የሕብረተሰብ ክፍል ፍላጎትና ተነሳሽነት አንፃር ሲታይ የኃይሌ ሥላሴ ዘመን ረጅሙ የኢትዮጵያ የቁልቀል ዕድገት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል። የኃይሌ ሥላሴን የኢትዮጵያ የቁልቁል አመራር ያልኩትን ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ከላይ ያልታተመ ባልኩት ጥናቱ እንደሚከተለው ገልጾታል። “አሳዛኙ ጉዳይ የሕዝብን ጥያቄ በኃይል ለመደምሰስ የሚፈልጉ ኃይሎች የመመሳሰል ባህርይ በሚመስል መልኩ መካሪያቸውም ሆኑ እሳቸው አስተዳደራቸው ለሃያኛው ክፍለ ዘመን የማይመጥን መሆኑን፣ በጣም እወዳታለሁ የሚሏት ኢትዮጵያም በታሪክ ፍራሽ ላይ ተኝታ የምትሸሞነሞን ሀገር መሆኗን ጨርሶ አልተረዱም።” ነበር ብሏል።

ይህ በዚህ እንዳለ በዉስጥ ሁኔታዎች እንኳን ባይሆን በውጪ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ምክንያት በተለይም በአፍሪካ ደረጃ በተቀጣጠለዉ የ1960ዎቹ የነፃነት ትግል ምክንያት የፖለቲካ ትኩሳቱና የፓርቲ ፖለቲካም በኢትዮጵያዊያን አእምሮ ውስጥ መቀረፅ የተጀመሩበት ጊዜ ነበር። ከዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ሁኔታዎች አንፃር በአፄ ኃይሌ ሥላሴ ዘመነ

መንግስት በተለይም ከ1950ዎቹ በኋላ ኢትዮጵያ የነበረችበትን ሁኔታ እንዳርጋቸዉ አሰግድ በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ በሚለዉ መፅሐፋቸዉ (2002፡ 15) "… 1950ዎቹ በአፍሪካ ምድር የጊኒ ቢሳዉ፣ ኬፐቨርዴ፣ የአንጎላ፣ የሞዛንቢክና የናምቢያ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግሎች የተፋፋሙበት፤ በእስያ የሕዝባዊት ቻይና የባህል አብዮት እንቅስቃሴና ፀረ ከላሽነት ትግሎች የተሟሟቁበት፣ የቬየትናም፣ የላኦስና ካምፑቺያ ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሎች የገነኑበት፤ በአሜሪካ የእነ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ሲቪል መብቶች የትግል እንቅስቃሴ የጥቁር ግስላዎች፣ የጥቁር ኃይል ትግል፣ የኩባ አብዮት፣ ወዘተ የተጋጋሉበት ዘመን ነበር።" ብለዋል። በእነዚያ አገሮች ዉስጥ የታየዉ ይህ የትግል ወላፈን ኢትዮጵያ ዉስጥም ተቀጣጥሎ አገዛዙን መለብለብ መጀመሩ ከዓለም አቀፉ ተፅዕኖ አንፃር ልዩ የሚያደርገዉ ነገር አይሆንም። ነገር ግን የንጉሱ አገዛዝ የፖለቲካ ጨዋታዉን ከፍ የሚያደርግ ስንዝር ያህል መሻሻል አልታየበትም።

በአገር ዉስጥም ቢሆን ቀላል የማይባሉና ከሚጠቀሱ የትግል እንቅስቃሴዎች የባሌና የጎጃም ገበሬዎች ንቅናቄ፣ የ1953ቱ የንዋይ ወንድማማቾች (መንግስቱ እና ግርማሜ) የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ፣ በ1960ዎቹ በይበልጥ እየጎላ የመጣዉ የኢትዮጵያ የዩኒቬርስቲና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ፀረ ፊውዳል እና ፀረ ዘውድ አገዛዝ እንቅስቃሴ የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በተለይም በነፃ የትምህርት ዕድል ሰበብ የተማሪዎች ወደ ውጪ አገሮች ጉዞ ማድረግና የለውጥ አየር ስሜት ተላብሰው መመለስ፣ የሠራተኛ ማህበራት መመስረትና መብታቸውን ለማስከበር ጥያቄዎችን ማንሳት መጀመራቸው፣ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት ጋርም ሆነ የአሜሪካ የሠላም ጓዶች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ጋር ተያይዞ ቀላል ነዉ የማይባል የፖለቲካ መነቃቃት መፈጠራቸዉ በኃይሌ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን ውስጥ ለፓርቲ ፖለቲካ መጸነስ መነሻ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያደረጉ ክስተቶች ናቸዉ።

በነዚህ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የተነሳ አፄ ኃይሌ ሥላሴም ሥልጣኑን

ለማጠናከርና መሎኮታዊ ገጽታን ለማላበስ የ1923ቱን ሕገ መንግስት ለማሻሻል እርምጃ ወስዷል። የ1923ቱ ሕገ መንግስት ያረጋገጠው ነገር ቢኖር ቀደም ሲል ሥልጣን ለመያዝ በሚደረገው እሽቅድምድም ውስጥ የፊውዳሎችን እርስ በርስ መገዳደል በማስቆም የነጋሲነቱ ሥልጣን ለኃይለ ሥላሴ የትውልድ ሐረግ ብቻ እንዲሆን መደንገጉ ነው። የ1923ቱ ሕገ መንግስት በ1948ቱ መሻሻል ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ብቻ የያዘ ነበር። አንዱ የፓርላማ መመስረትና የአስተዳደር ማሽነሪዎች መቋቋም ናቸዉ። ፓርላማዉ የሕግ ምክር ቤትና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ቢኖሩትም የበላይ አካሉ ያው ንጉሱ ነበር። በሕግ መወሰኛም ሆነ በፍትህ መስሪያ ቤት ደረጃ የሚወጡ ሕጎችን የመተርጎም ሥልጣን ያለዉ ከንጉሱ በስተቀር ሌላ አካል አልነበረም። ሦስት የአሜሪካ ዜጎች ተሳትፈውበት ተሻሻለ የተባለዉ ሕገ መንግስት ሊሆን የቻለዉ ነገር ቢኖር የንጉሱን ገጽታ በውጪ አገር ሰዎች ዘንድ ከመገንባት የዘለለ አልነበረም። በሁሉም አቅጣጫ የመጨረሻዉና የሁሉም የሥልጣን ጣሪያ የንጉሱ ስለነበር በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈፃሚና በሕግ ተርጓሚ የመንግስት አካላት መሀከል መለያየት የሚባል ቀርቶ ሐሳቡ ራሱ ስለመታወቁ እርግጠኛ መሆን የሚችል አልነበረም። ሲጠቃለል፤ የሕገ መንግስቱ ተሻሻለ ቢባልም አንዳቸዉም ከንጉሱ ሥልጣን የሚቀንስ ወይም ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ አንቀጽ አልነበረበትም። በተለይም፤ የፓርላማ ስብጥሩ ከዘዉድ አምልኪነት ነፃ ካለመሆኑም በላይ ወንበራቸዉን የጥቅማቸዉ ማስጠበቂያ ከማድረግ አላለፈም።

በአንድ አገር ዉስጥ ለሚከሰቱ ጉዳዮች መሠረታዊ የውስጥ ሁኔታዎች መስተጋብር አስፈላጊ መሆናቸዉ የሚጠቀስ ሲሆን፤ ለአፄ ኃይሌ ሥላሴ የ1948 ሕገ-መንግስት መሻሻል አንዱ መነሾ ሐሳብ የመንግስት ሥራ እየተስፋፋ መሄድና በያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የንጉሱን ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን የማስወሰንና የንጉሱ ቁጥጥር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የተወሰኑ የንጉሱን የሥልጣን ቦታዎችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለማስተላለፍ ታስቦ የተሰራ ነበር። ከሕገ መንግስቱ ማሻሻያ በኋላ በንጉሱ ከተሰጡት የሕገ መንግስት መብቶች ሌላ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የበላይ ኃላፊነት

የሚወጣ "ነጋሪት ጋዜጣ" መውጣቱና የሚወጡ ሕጎችን ለሕዝቡ ለማሳወቅ ተችሏል። ከዚህ በኋላ ነዉ ሥራ አስፈፃሚው የመንግስት አካል በወቅቱ ተሻለ በሚባል ሁኔታ የተቋቋመዉ። ሌሎች የሥራ ቤቶች አየር መንገድ፣ አውራ ጎዳና፣ ባንክ እና የመሳሰሉት የዚህ የተሻሻለዉ ሕገ መንግስት ውጤቶች ናቸው።

ከኤኮኖሚ መነቃቃት አንፃር የስኳር ፋብሪካዎችና ሰፋፊ እርሻዎች መቋቋም ችለዋል። ነገር ግን በአፄ ቴዎድሮስ የታሰበው ዘመነኛነት በምኒልክ ተጀምሮ እየተንገጫገጨ በአፄ ኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የኋሊት ጉዞ ያደረገ ሲሆን፤ በተለይም የውጪዊው ፖለቲካ መዘመን ግን እስከ 1953ቱ የንጉሱ አልጋ መነቃነቅና የተማሪዎቹ ንቅናቄ እሳት እስከሚያጭር ድረስ የተቀረው ዓለም ወደ እንዱስትሪ ግንባታ በሚሸጋገርበት ጊዜ ዉስጥ በኢትዮጵያ የለዉጥ ፍላጎቱ በገዥው መሰፍንቶች መሀከል ስላልነበር ጉዞው ሁሉ የማንቀላፋት ያህል ነበር ማለት ይቻላል። በአጭር ቃል ሲገለጽ የኢትዮጵያ ዕድገት ልግመት ሀ ብሎ የጀመረበት ጊዜ ቢኖር የአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ዘመን ነበር ቢባል አልተሳሳተም። በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ የተከሰተ ነገር ቢኖር፤ ቢጨናገፍም ቅሉ፤ የ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ መለኮታዊ ባህርይ ተጎናጽፎ የቆየዉን ንጉሳዊ ሥልጣን በመድፈሩ ዓይን ገላጭ ነበር ለማለት ይቻላል። በተጓዳኝም እንደማንኛዉም የአገዛዝ ሥርዓት የኃይሌ ሥላሴ መንግስትም የራሱን አፍራሾች በውስጡ እያረገዘ መምጣቱ ሐቅ ሲሆን፤ የገበሬዎች ንቅናቄ፣ የወጣት ተማሪዎች ንቅናቄ፣ የሠራተኛ ማህበራት እንቅስቃሴ፣ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ፣ የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድና የኤርትራ ሕዝብ የነፃነት ትግል መቀጣጠል የመሳሰሉት ክስተቶች ለፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ማቆጥቆጥ ቀዳሚና የአገዛዝ ሥርዓቱን የገዘገዙና በዘለቄታውም ለኃይሌ ሥላሴ ንጉሳዊ አገዛዝ መውደቅ ተጠቃሽ ናቸዉ። የእነዚህን ክስተቶች መነሻ ምክንያትና የፈጠሩትን የፖለቲካ አንደምታና ለፓርቲ ፖለቲካ መነቃቃት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከተመዘገቡት የታሪክ ሰነዶች በአጭር በአጭሩ ቀጥሎ አመለክታለሁ።

## የገበሬዎች ንቅናቄ

የኢትዮጵያ የመሬት ይዞታ በሁለት የተከፈለ ነበር፤ በደቡብ በባለመሬትና ጭሰኛ መሀከል የባሪያ እና የባሪያ ጌታ ግንኙነት ዓይነት ሲሆን በሰሜን በኩል ደግሞ የዘር ሐረግ በመምዘዝ የወል ስሪት የሚባል ዓይነቶች ነበሩ። የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከዘር ሐረጋቸዉ ጋር የተያያዘችዉ መሬት ተከፋፍላ ተከፋፍላ የበሬ ግንባር እስከሚታክል ድረስ መወራረስና ማስተላለፍ ላይ የተመሠረተ ነበር። የደቡብ መሬት ግን ከምኒልክ ጋር በወረሪነት፣ በመስፋፋት፣ በአቅኚነት፣ በቅኝ ገዥነት የመጡ የገዥዉ ወገን አባላት፤ ምንም ተባለ ምንም፤ ነባር ነዋሪዎችን እያፈናቀሉ የሚይዙበት የገባር ሥርአት ወይም የነፍጠኛ ሥርአት ነበር።

ነፍጠኞች፤ ባለመሬት ነባር ዜጎችን ከመሬታቸዉ ማፈናቀል ብቻ ሳይበቃቸዉ በገንዘብና ከምርት ዓይነት እርቦ ከማሰፈር አልፈዉ፤ ገበሬዎችን በአዲሱ ባለመሬት ይዞታ ላይ በቀን በቀን የሚያሳርሱ፤ ሚስቶቻቸዉና ልጆቻቸዉ ሳይቀሩ የምግብ እህል በመፍጨትና ከብት ለማሳገድ የሚያሰማሩ፤ እንዲሁም ቀጣዩን የባርነትና የገባርነት ትውልድ እንዳይቋረጥ ለማድረግ ራሳቸዉን ለነፍጠኞቹና ጀሌዎች ድሪያ ማለትም ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት እርካታ ሳይቀር የሚያቀርቡበት አስከፊ ሁኔታ የነበረበት ሥርአት ነበር። ገባሮች ገንዘብ አምጡ ተብለው በገንዘብ የሚከፍሉትን ሲያጡ ልጆቻቸውን ወስደው ከባርነት ላላነሰ አገልጋይነት ይሰጡአቸው እንደነበር አዛውንቶች ይናገራሉ። ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ከላይ በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፋ ውስጥ “ለማቅናት የተሰማራው የፊዉዳል ሥርአት ሰራዊት የገባር ሕዝቦችን ነፃነት ቀምተዋል፣ መሬታቸውን ዘርፈዋል፣ ሕዝቦችን በገዛ መሬታቸው ላይ ጭሰኛና ገባር አድርጓቸዋል፣ ቋንቋን አፍነው በስማ በለው ገዝተዋቸዋል።” በማለት የአስከፊነቱን ደረጃ ገልጿል።

## የራያና አሰቦ ሕዝብ ትግል

ራያ አሰቦ የየጁ ኦሮሞ ሥርወ መንግስት ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ሕዝቦች አንዱ ነበር። ከትንሹ ራስ ዓሊ በአፄ ቴዎድሮስ በመሸነፍ፤ በኋላ የራያ አሰቦ ሕዝብም ከሰሜናዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች ውስጥ እስከ ደርግ ሥልጣን መያዝ ድረስ አንገቱን ቀና እንዳያደርግ በግፍ የተወሰነበት ሕዝብ ነበር። አፄ ኃይሌ ሥላሴ ከመንገሱ በፊት ጀምሮና ለመንገስ በሽግግር ላይ እያለ ማለት ነዉ፤ ከገጠሙት ጠንካራ ተቃዉሞዎች ዉስጥ አንዱ የራያና አሰቦ እና የዋጅራት ኦሮሞዎች የትጥቅ አመፅ ነበር።

የራያና አሰቦ ሕዝብ አመፅ መነሻ ምክንያትም በዚያዉ በትግራይ ግዛት ውስጥ ለመንግስት ይከፈል የነበረው የግብር ክፍያ ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ የተፈጠረበት ጊዜ ይምሰል እንጂ ከይዘቱ አንፃር ሲታይ ግን አገር አቀፍ ፀረ ኢምፓየር የትግል እንቅስቃሴ ነበር ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም፤ የራያዎቹ የትግል እንቅስቃሴ ከሰሜን እስከ ኤርትራ፣ ከምስራቅ በኩል ደግሞ ከከብት ዘረፋ ጋር ተያይዞ እስከ አፋርና አዋሽ ስምጥ ሸለቆ ድረስ የተስፋፋ ስለነበረ ነው። በዚያን ጊዜያት ማዕከላዊው የኃይሌ ስላሴ መንግስት ከጣሊያን ወረራ መልስ ገና ያልተደላደለ ስለነበረ፤ ራያዎች ለአመፃቸው የመረጡት ጊዜ ትክክለኛ ነበር ለማለት ይቻላል። የራያ አሰቦ ሕዝብ መሠረታዊ እንቅስቃሴ የዚያ ሕብረተሰብ ሕዝብ የሰፈረበት አከባቢ በተፈጥሮ ለም በመሆኑ፤ አፄ ዮሐንስ  እና አፄ ምኒልክ በየአገዛዛቸዉ የቀየሱት የአኗኗር ሁኔታ ከአበሾቹ ወግና ባህል ጋር ተሳልጦ (አስሚሌት አድርገዉ) እንዲኖሩ ለማስገደድ ሲባል ወደ አከባቢዉ ብቅ ባሉ ቁጥር የተወሰነ ግዳጅ እየጣሉባቸው ስለሚመለሱ፤ በተለይም የሚጣልባቸውን የግብር ክፍያ ግዳጅ ላለመወጣት እምቢታቸውን የገለፁበት እና አጋጣሚው ግን አፄ ኃይሌ ሥላሴ ሥልጣኑን ለማደላደል የሽግግር ወቅት ላይ በነበረበት ጊዜ ላይ ነበር። ራያዎች ለትግል እንቅስቃሴያቸው መጀመርም በ1920ዎቹ መጀመሪያ ለራስ ጉግሳ አርአያ መከፈል የነበረበትን የዓመቱን ግብር ሳይከፍሉ ይቀራሉ። ራስ ጉግሳ ወሌም በቤጌምድሩ ጦር አዛዥ ራስ ጉግሳ አርአያ

በመታገዝ በወሎ ኦሮሞዎች ላይ እንዲዘምቱ ተደረገ። ሆኖም ግን ራስ ጉግሳ ወሌ ራያ አሰቦ ግዛት ከደረሰ በኋላ ወገናዊነቱን በማስበለጥ ከአመጸኞቹ ጋር ተባበረ። የራስ ጉግሳ አርአያ ጦርም በሁለቱ ስምምነት በሚመስል መልኩ ድል ተመትቶ ወደኋላ እንዲመለስ ተደረገ። አፄ ኃይሌ ሥላሴም የኢምፓየሯ የጦር መሪ የሆነ ራስ ሙሉጌታን ወደ ወሎ ልኮ፤ እንዲሁም ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የመን የተነሱ ሁለት የጦር አይሮፕላኖች በአከባቢዉ ላይ ጭስ እየረጩ በማስበረር ጭምር የአመፅያኑን ሞራል እንዲወድቅና የኢምፓየሯ ጦር ሞራል እንዲገነባ ተደረገ። ከረጅም ቀናት ውጊያ በኋላ በተተኮሰበት የእሩምታ ተኩስ ራስ ጉግሳ ወሌ ሲሞት ጦሩም ተበተነ።

በገበሬ ላይ የተጫኑት ክፍያዎች የሲሶ፣ የደስታ፣ የገባር፣ የግንደበል፣ የሲሞን፣ የወረገኑ፣ የሁዳድ፣ የጭቃ ማር፣ አስራት፣ የአምሻ፣ የዓመት በዓል፣ የፀሐፊ እየተባለ በሕዝቡ ላይ ሲቆለል የቆየዉ ክፍያ ሕዝቡን መቆሚያ መቀመጫ በማሳጣት ማስመረሩ በመቀጠሉ የራያና አሰቦ ሕዝብ ዳግማዊ አመፅ በ1943 እንደገና ሊከሰት ችሏል። የንጉስ ኃይለ ሥለሴን የግፍ አገዛዝ ከቅኝ አገዛዝ ጋር የሚያነፀጥሩት አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን በድህነት ከታጀበው ሺህ ዓመታት ነፃነት ይልቅ የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ ቢሰነባብት ይሻላል የሚል ምርጫ ያደርጋሉ። በዕወነቱ፤ በነፃነትና ቅኝ አገዛዝ መሀከል ምርጫ ማድረግ ለሞራልም የማይመች ቢሆንም የኃይሌ ሥላሴን የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተያይዞ የተፈጸመው ነገር ቅኝ አገዛዙን ያስመኝ እንደነበር ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌታሁን ዴሊቦ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው እንደገለጹት “ኢጣሊያኖች አገሪቱን በወረራ በያዙ ጊዜ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ የገባር፣ የባሪያና የነፍጠኛ ጦር ሥርአቶችን ደመሰሱ። … ብዙ የመንገድ፣ የድልድይ፣ የከተማ፣ የህንፃ፣ የንግድ፣ የእርሻና የእንዱስትሪ፣ የትምህርትና የባህል ግንባታ ሥራዎችን በፍጥነትና በስፋት በማካሄድ … የገባር ሥርአት ላይ ለውጥ አስከተሉ።” በማለት የንጉሱ አስመራሪ የገባር ሥርአት ቅኝ አገዛዝን እንደሚያስመኝ ገልጸዋል። ሞቲ ቢያም (1996፡ 60) “የራያ አሰቦ ሕዝብ ፍላጎት ከኢትዮጵያ መገንጠል ወይም የትግራይ ነፃ

መንግስት መመስረት ነበር።” ብሏል። የራያና አሰቦ ሕዝብ ትግል ሁለንትናዊነትን የተላበሰ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ እንደነበርና በተለይም የራሱን ባህላዊ አስተዳደር የመጠበቅ እሳቤ የተካተተበት ሲሆን፤ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በተማሪዉ ማህበረሰብ ዉስጥ ለተከሰተዉ የብሔር ጥያቄ የፖለቲካ ትግል ይኼዉ የራያና አሰቦ ሕዝብ ትግል አንዱ ተጠቃሽ ምዕራፍ ከፋች ነበር ለማለት ይቻላል።

## የባሌ ገበሬዎች ትግል

የራያና አሰቦ ሕዝብ ትግል ከተዳፈነ ከሃያ ዓመታት በኋላ የባሌ ሕዝብ ትግል ተቀሰቀሰ። በተፈጥሮ አከባቢዉ ልምላሜና ውቤት ብቻ ሳይሆን በባህል፣ ታሪክና በአከባቢዉ ነዋሪዎች በዕድሜ ላይ በተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ የገዳ ሥርዓት አስተዳደሩ አርአያ የነበረዉ የባሌ ሕዝብ ሁሉንም ቅርሱንና እሴቱን በምኒልክ ወረራ አጥቷል። የፖለቲካ አስተዳደሩ በባዕድ እጅ እንደወደቀ ሁሉ የኤኮኖሚዉ መሠረት የሆነዉ መሬትም ተወሰደበት። ዋቄፋና ሃይማኖቱና መልካና ቱሉ የአምልኮት ሥፍራዎቹ በባዕዳን ወራሪዎች በጠመንጃ ተወርሰዉ የባዕድ አምልኮ ቦታዎች እንዲሆኑ ተደረገ። ሊከፍለዉ ቀርቶ ሊገምተዉ የማይችለዉ የግብር ክፍያም ተጣለበት። በተለይም በ1940 ቀላድ ሲጣል ገበሬዎች መክፈል ስላቃታቸዉ የነበራቸዉ ምርጫ መሬታቸዉን አስረክበዉ መሰደድ ግድ ሆነባቸዉ። በሕጋዊ መንገድ ከሚከፈለዉ በላይ ግብር አምጡ፣ ሙክት ሳቡ፣ ለበቅሎ ሳር እጨዱ፣ የሚለዉን የፊውዳሎች የማስገበር ሥርዓት ሊታገሱት የማይችሉት ሸክም ከመሆኑም በተጨማሪ፤ የነፍጠኞቹ ብዛትና የሕዝቡን ጎተራ እስከ ማራቆት የሚደርሰዉ አመጋገባቸዉ እጅጉን አስመርሯቸዉ ለአመፅ ጋበዛቸዉ። ዛሬ አፋን ኦሮሞን መናገር የማይችል ብቻ ሳይሆን መስማትም የማይፈልግ ትውልድ መሠረቱን ባሌ ዉስጥ የጣለው ያኔ የምንሊክ ሰፈራ የተጀመረ ጊዜ ነው። ሕዝቡም የወረደበትን ግፍ የአርባ/ሰማኒያ ቀን ዕድሉ እንደሆነ አድርጎ አልተቀመጠም። በባሌ ጫካዎችና ቆላማ ሥፍራዎች በመሸፈት ማዕካለዊዉን መንግስት በቡድንና በተናጠል

መፋለም ጀመረ። መፈክራቸዉም “በራሳችን መሬት ላይ ባሪያ አንሆንም” የሚል እንደነበርና ጀግኖቹ የባሌ ኦሮሞዎች የኃይሌ ሥላሴን ሠራዊት መቋቋማቸዉ የኦሮሞ ወጣቶችንና ዜጎችን የትግል ሞራል ከፍ ያደረገ ነበር።

የባሌ ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴ ግዙፍ ከመሆኑም በላይ ሕዝቡ ራሱ ለመሪዎቹ ሹመት እስከ መስጠት ደርሶ ዋቆ ጉቱን ጀኔራል ብሎ እስከመፍጠር የደረሰ ሕዝባዊ ንቅናቄ ነበር። የባሌን ሕዝብ የነፃነት ትግል ለማኮላሸት ሲባል ንጉሱ በጨካኝነቱ የሚታወቀዉን ፊታወራሪ ወርቁ ዕንቁ ሥላሴን በ1955 ሸዋ ከመላኩም በተጨማሪ በኦሮሞ ተወላጅ ስም የቀበሮ ባህታዊ የሆኑ ጀኔራል ጃገማ ኬሎ የመሳሰሉትን የጦር መሪ አድርጎ ልኮ፤ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል እንዲዳፈን አድርጓል። የባሌ ሕዝብ ትግል ከዉስጥ ፀረ-ፊዉዳል ትግል እያደረገ ከዉጭም የሶማሌን መንግስትን ወረራ በመቋቋም ታሪክ ሲሰራ እንደነበረ ይታወቃል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የባሌ ኦሮሞ በሱማሌና በባሌ መሀከል እየተመላለሰ ማዕከላዊዉን የኢትዮጵያ መንግስት ሲወጋ መቆየቱ እየታወቀ፤ ሱማሌዎች ግን ኦሮሞን ከድተዉ ለራሳቸው በማድላታቸዉ የኦሮሞ ሕዝብ ትግል እንደተዳከመ የሚገልጹ የአበሻ ኤሊቶች አሉ። ዕውነታው ግን የባሌም ሆነ የሌላው አከባቢ ኦሮሞ ሕዝብ ትግል ወጥ ባለመሆኑና ከዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች አጠቃቀም ጋር አስቀድሞ ያልተዋወቀ ስለነበር፤ የአበሻ መንግስት ገዥዎች የበላይነት እንዲያገኙ ማስቻል ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ መሬቱን እንጂ ሰውን እንደማይፈልጉ አድርገው የወሰዱበት የጭካኔ እርምጃ ኦሮሞዎችን ለጥቃት እንዲጋለጡ አድርጓል።

በሌላም በኩል ከታች በምዕራፍ አምስት ዉስጥ የሱማሊያን መንግስት ሸር ሳይረዱ በመቅረት ወይም በተገኘዉ አጋጣሚ ሁላ ኦሮሞን ለመጉዳት ሲባል የባሌ ገበሬዎችን አመፅ የተቀጣጠለው በሱማሊያ መንግስት ድጋፍ እንጂ ዕውን የኦሮሞ ሕዝብ የመብት ጥያቄ ብቻ እንዳልሆነ የሚገልጹም አሉ። በምንም ዓይነት መስፈርት የዚያ ሕዝብ ትግል የሱማሊያን መንግስት የመጠለያ ድጋፍ እንጂ የፖለቲካ ተሳትፎ

የጠየቀበት ጊዜ አልነበረም። ቢኖር እንኳን ምላሹ ቀና ሳይሆን ለኦሮሞ ሕዝብ ትግል ቸቦ ለኳሽ የነበሩት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ልጆችን ለወሬ ነጋሪ እንኳን እንዳይተርፉ ተደርገው በሱማሌ መንግስት በሚደገፉ ወንበዴዎች በጅምላ ተገድለው በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩበት ክስተት እንደነበረ አመዛዛኝ ሕሊና አይስተዉም። እንዲያዉም የሱማሊያ መንግስት የኦሮሞን መሬት ለመውሰድ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር በማያያዝ በስልት ይዞ የሄደበት አካሄድ ነበር። ቃርሚያው ዛሬም ሳይጠፋ ኢትዮጵያዊያን ሱማሌዎች ልዩ የፖሊስ ኃይል በማሰማራትና የሕወሓት ተቀጥላ በሆነው ከኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ጋር በመሆን የኦሮሞ መንደሮችን በማቃጠልና ሕዝቡን በማፈናቀል በቦረናና በምስራቅ ሐረርጌ የመሬት ነጠቃ አድርገዋል። ተጠቃልሎ ሲታይ ግን ለስድስት ዓመታት ያህል (1963-70) የተካሄደው የባሌ ኦሮሞ ሕዝብ ትግል የንጉሱን ሥልጣን ክፉኛ የተፈታተነ ነበር። ለፓርቲ ፖለቲካ እርሾ ሊሆን የሚችል አስተዋጽኦም አድርጓል።

## የጎጃም ገበሬዎች ትግል

የባሌ ሕዝብ አመፅ ትኩረቱን ስቦ ስለነበረና የአከባቢዉ የሕዝብ ንቅናቄ ረጅም ጊዜም የወሰደ ስለነበረ፤ መንግስት በጎጃም ሕዝብ ላይ ያደርግ የነበረዉ ቁጥጥር ያላላ ከመሆኑም በላይ ከጎጃም ሕዝብ ግብርም ሰብስቦ ስለማያዉቅ፤ የባሌ ሕዝብ ትግል ተዳፍኖ ብዙም ሳይቆይ በጎጃም ዉስጥ ሌላ የሕዝብ አመፅ ተቀሰቀሰ። የአመጹ መነሻም ሳይሰበሰብ የቆየዉን ግብር ለማካካስ የታለመ በሚመስል መልኩ በ1942 በግዛቱ ላይ ተሹሞ የነበረዉ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ የግብር ክፍያዉ በፊት ከነበረዉ በላይ በእጥፍ ከፍ እንዲል ስላደረገ ነው። በተጨማሪም ግብር ለመክፈል እንዲያመቹ መሬት ለም፣ ለም ጠፍና ጠፍ በሚል እንዲገመገምና የግብር ክፍያዉም በዚያዉ ልክ ደረጃ እንዲወጣለት በማድረጉ፤ ሕዝቡ ግን ባሌ ዉስጥ የተጣለዉ ቀላድ በነሱ ላይም ሊጣልና ሊያፈናቅላቸዉ የታቀደ መሆኑን ስለተጠራጠሩ በተለያዩ የጎጃም አዉራጃዎች አመፅ አቀጣጠሉ።

የሕዝብን አመፅ ተከትሎ አመፁን ለማብረድ ሲባል ንጉሱ የግብር ተመኑን በአንድ ሦስተኛ ለመቀነስ አዋጅ ቢያስለፍፍም፤ የጎጃም ሕዝብ ሊቀበለዉ አልፈቀደም። የሕዝቡን አመፅ ለማለዘብና ቅሬታ አስነስቶ የነበረዉን የሸዋ ተወላጁን የደጃዝማች ከበደ ተሰማን ሹመት በማጠፍ ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁሥላሴን በጎጃም ላይ ሲሾም እንዲያዉም የሕዝቡ አመፅ ተባባሰ። ለመባባሱም አንዱ ምክንያት የጎጃም ሕዝብ ወርቁ ዕንቁሥላሴ በባሌ ሕዝብ ላይ ያደረሰዉን መከራ ስለሚያዉቁ፤ እነሱም በወንድምየዉ ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ ተመሳሳይ ጭፍጨፋ እንደሚደርስበት ስለተረዱ ነበር። የጎጃም ገበሬዎች በ1960 ታውጆ የነበረውን የእርሻ ገቢ ታክስ ጭምር ተቃውመው ሰፊ እንቅስቃሴ አድርገዋል። ምንም እንኳን የጎጃም ገበሬዎች አመፅ በመጠንም ሆነ በዓይነት ሰፊና ጥልቅ የነበረ ቢሆንም መንግስት በባሌ ገበሬዎች ላይ የወሰደውን ዓይነት ጭካኔ የተመላበትን እርምጃ በአማራ ወገኖቹ ላይ አልወሰደም። እንዲያውም ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁስላሴን በማንሳት ወደ ከፋ ጠቅላይ ግዛት ከማዛወሩም ሌላ ሳይከፈል ቆይቶ ከነበረው ውዝፍ ግብርም ነፃ እንዲሆን ወስኗል። ይህ በዚህ እንዳለ የጎጃም ገበሬዎች አመፅም ከ1965 ጀምሮ በአገሪቱ ዉስጥ ለነበረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴና ለ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት መሠረት በመሆን አገልግሏል። የገበሬዎች ንቅናቄ በራሱ ብቻ ተወስኖ የቀረ አልነበረም። ምንጫቸው ከገበሬው አከባቢ ለሆኑና የገበሬውን የመብት ጥያቄ በግንባር ቀደምትነት አንግበው ለተነሱት መነሻ እንዲሆናቸዉ በማስቻሉ የኃይሌ ሥላሴን አገዛዝ አዳክመው ግብአተ መሬቱን ያመቻቹ ነበሩ ለማለት ይቻላል።

## የወጣት ተማሪዎች ንቅናቄ

እንደሚታወቀውና የተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች እንደገለፁት ራሱን ችሎ የተማሪ መደብ የሚባል እንደማይኖር ነዉ። ሆኖም ግን ይህ ወጣት ክፍል ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ኢህአዴግ በከፋፋይ ስልቱና በጥቅም መግዛት ደረጃ ላይ እስከ ደረሰበት ጊዜ ድረስ አብዛኛዉን ጊዜ

የየመጣበትን የሕብረተሰብ ክፍል (መደብ) ብሶት ከማንፀባረቅ ወደኋላ የማይል፣ ፍርሃትና ሥጋት የሚባል ጭንቀት የሌለበት ክፍል በመሆኑ የሕብረተሰቡን ችግር ማንፀባረቅ ብቻ ሳይሆን በተለይ ወጣቱ የሚታወቅበት ነገር ቢኖር እራሱም ሆነ ሌላዉ የሕብረተሰብ ክፍል ጥቃት ሲደርስበት ፈጥኖ የሚቆጣና መልስ ለመስጠት የሚነሳሳ ወይም ጥቃትን ለመቋቋም ቀድሞ የሚጋፈጥ ኃይል እንደሆነ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ዉስጥ ጉልህ ሥፍራ እንዳለው ይታወቃል።

በሌላም በኩል ወጣቱ ክፍል አዳዲስ ነገሮችን የመቀበል ተነሳሽነቱ ሰፊ ነው ቢባልም የተቀበለው ነገር ሁሉ ጥሩ ነው ማለቱ ግን ይከብዳል። አዳዲስ ነገሮችን ከመቀበል ጎን ለጎን የየመጣበትን የሕብረተሰብ ክፍል ጥቅም ተጣብቆ የመቅረት አሊያም የመክዳት ባህርይም ይታይበታል። ለማንኛውም ወጣቱ የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ አሻግሮ ለመመልከት የሚችልና ንጹህ አእምሮ ያለው፤ ደልቃቃ ኑሮ ይኖራል የሚባለው ወጣት ሳይቀር ለለውጥ ለመነሳት ብዙም ቅስቀሳ የማያሻው የሕብረተሰብ ክፍል ነዉ። አስቀድሞ የሚያዘጋጀው የበሰለ አመራር ካገኘ ወጣቱ ለነፃነት ትግልም ሆነ ለዕድገት የሚከፍለው መስዋዕትነት ከዚህ በመለስ ነው አይባልም። ተገቢዉን አመራር ካላገኘ ግን አንድም የትግሉ አቅጣጫ ይዋልልበታል፤ ወይም በኢህአዴግ/ብልፅግና አገዛዝ ጊዜ እንደሆነው ሁሉ ለጊዜያዊ ጥቅም ተደልሎ አርቆ የመመልከት እይታዉ የሚጋረድበትና ከተሳሳተ አቅጣጫ የመሄድና የመሰለፍ አዝማሚያውም ያን ያህል ሰፊ እንደሆነ ነዉ።

በኃይሌ ሥላሴ ጊዜ የነበረዉ የኢትዮጵያ ወጣት ክፍልም በሁለንትናዊ ሁኔታዉ ከተመሳሳይ ክስተቶች ያላመለጠ ነበር ማለት ይቻላል። በአብዛኛዉ ሊባል በሚችል መልኩ ግን፤ የኢትዮጵያ ወጣት ተማሪዎች በአብዛኛው ጥሩ አቅጣጫን የተከተሉና የሕብረተሰቡን ችግር ለመፍታት የተጉ ነበር ለማለት ይቻላል። በተለይም በኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን በየመንደሮቻቸው ያስተዋሉትን አስነዋሪና ጥቃቅን የሥልጣን ብልግናን ከመቃወም ጀምረዉ እስከ ትልቁ የኤኮኖሚ ዋልታ “መሬት ላራሹ”

ጥያቄና የብሔር ጥያቄን ወደማንገብ ከተሸጋገሩት ውስጥ ወጣት ተማሪዎች ቅድሚያውን ይይዛሉ። እንግዲህ ለኢትዮጵያ ወጣት ተማሪዎች ንቅናቄ መሠረት የጣሉ መሠረታዊ ነገሮች የነበሩት የኤኮኖሚው ኋላቀርነትና የብሔር ጭቆና፣ የሃይማኖት ልዩነት ጫና እንዲሁም የወቅቱ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ እንደነበር ይታወቃል።

ከፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንፃር በ1953 ዓም ተሞክሮ የከሸፈዉ መፈንቅለ መንግስት "ሥዩመ እግዚብሔር" ነኝ ባዩን ንጉስ መገዳደር እንደሚቻል ለወጣቱ ክፍል በተለይም ለወጣት ተማሪው ማህበረሰብ ፍንጭ የሰጠ እንደነበርና በተለይም ሙከራው የተማረው ወጣት ትውልድ በሕዝብ መሀከል መግባት የጀመሩበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል። በወንድማማቾቹ መንግስቱና ግርማሜ ንዋይ አቀነባባሪነት ተደርጎ የነበረው መፈንቅለ መንግስት ቢከሽፍም ለኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መጠንሰስ የራሱን አሻራ ያኖረ ነበር። አማኑኤል አብርሃም የሕይወቴ ትዝታ (1992፡ 150) በሚለዉ መጽሐፋቸዉ ላይ እንዳመለከቱት "መንግስቱና ግርማሜ በንጉሴ ነገስቱ ላይ የቀሰቀሱት አመፅ፣ እንደእሳት ተዳፍኖ እንዲቆይ ተደረገ እንጂ፣ ጨርሶ እንዳልጠፋ ይታወቅ ነበረ። ይህም እውነት መሆኑ ጎልቶ የታየው፤ በ1966 ዓም አብዮት የተባለው አመፅ በተቀጣጠለበት ወቅት ነበር።" ብለዋል። በመፈንቅለ መንግስቱ ማግስት ንጉሱ የአስተዳደር ለውጥ ያድርግ እንደሆነ ከውጭ አገር ጋዜጠኞች ለቀረበለት ጥያቄ አሉታዊ መልስ የሰጠ ቢሆንም፤ የትግሉ ወላፈን ወደ ሕዝቡ መሠረታዊ ሕይወት ላይ ትኩረት በማድረጉና አገሪቱ የግብርና ኤኮኖሚ ላይ የተመሠረተች በመሆኗ፤ ይህንን ዘርፍ ለማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን በማመንም ሆነ የንጉሱን ሥልጣን ክፉኛ የተፈታተነው <መሬት ላራሹ> የተባለው መፈክርም ለመጀመሪያ ጊዜ በ1958 ላነሱት የኢትዮጵያ ተማሪዎች የመንድማማቾቹ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ዓይን ገላጭ ነበር ለማለት ይቻላል። መሬት የገዥው ክፍል መሠረታዊ የኤኮኖሚ የጀርባ አጥንት ስለሆነ፤ የዚህ የኤኮኖሚ አያያዝ መለወጥ ማለት የሥልተ ምርትና ላዕላይ

መዋቅር ለውጥ ማስከተሉ እንደማይቀር ጭምር ያስታወቀ ስለሆነ፤ ከዚሁ ሥጋት የተነሳ ይመስላል ገዥው መደብም በብዙ ተማሪዎች ላይ ግድያን ጨምሮ ሰፊ የጭካኔ እርምጃዎችን የወሰደው በዚሁ ጊዜ ነበር።

መሠረታዊ ምንጩ ከብዙሃን ሕብረተሰብ የሆነውና በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥም የተቀጣጠለው የተማሪዎች ንቅናቄ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብሎም የከተማው ነዋሪ ሕብረተሰብ ድረስ በመስፋፋቱ፤ በ1962 ሁለት አሳዛኝ፤ ነገር ግን በተማሪውና በሕብረተሰቡ ዘንድ ሊመዘገቡ የሚችሉ ድርጊቶች ተፈፀሙ። አንደኛዉ የንጉሳዊ ቤተሰብ አባልና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዝዳንት የጥላሁን ግዛው ታህሳስ 19 ቀን መገደልና ሌላዉ ብርሃነ መስቀል ረዳ በሚባለዉ ተማሪ የሚመራ የወጣቶች ቡድን ነሐሴ ወር ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነዉን አይሮፕላን ጠልፎ ሱዳን መግባት ነዉ። ሁለቱም ክስተቶች የኢትዮጵያ ተማሪዎችንና የተማሪዎች የትግል ንቅናቄን ያሳደገ ሲሆን ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዕውነታም ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ በግልፅ የታየበት ወቅት ነበር።

የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ግን መሠረታዊ የአስተዳደር ማነቆዎችን ከማስወገድ ይልቅ የተማሪዎች ንቅናቄ ለማፈን ሲባል ከመንግስታዊ ተቋም ጀምሮ <የቤተሰብ ኮሚቴ> የሚባል ስውር ኮሚቴ እስከ ማቋቋም ደርሶ እንደነበር የታሪክ ማስታወሻዎች ያወሳሉ። በተለይም የነጋሲው የፀረ ተማሪ/ምሁር የፕሮፓጋንዳ ረድፍ ግንባር ቀደም ተሰላፊዎች ተብለዉ የሚታወቁ እነ መቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርግስ፣ ፕሮፈሴር መስፍን ወልዴማሪያም፣ ዶ/ር አብርሃም ደመወዝ የሚገኙበት ኮሚቴ ተቋቁሞ የተማሪዉን እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ሲፍጨረጨር እንደነበር ተስፋዬ መኮንን ይድረስ ለባለታሪኩ ብሎ በፃፈው መጽሐፉ ውስጥ አውስቷል።

በሌላም በኩል በ1960ዎቹ ኢትዮጵያ የነበረችበት የኤኮኖሚ ሁኔታ

ከዓለም የኤኮኖሚ ሁኔታ አንፃር ሲታይ ዝቅጠት ወደሚባለዉ አቅጣጫ እየተጓዘች ስለነበር፤ ሥዩመ እግዚአብሔር ነኝ ከሚለዉ ንጉስ አምልኮት በስተጀርባ የፀለምተኝነት ምስጢሩን ለማየት የተቻለበትና አብዮት ያረገዘ ጊዜ እንደነበር ሕዝባዊ ንቅናቄዎቹ የበለጠ ይገለፃል። በተጨማሪም ወቅቱ የወጣት ተማሪዎች እና ምሁራን የምልከታ አቅጣጫ የተቀየረበትና የርስ በርስ መናበብ እንዲጎለብት፣ የርዕዮተ ዓለም ንቃተ ሕሊና ለማዳበርና በመሀከላቸዉ ይከሰቱ የነበሩ መለስተኛ የሐሳብ ግጭቶችን በማስወገድ ሕዝብን ለማስተማርና ከሕዝብ ለመማር ግንዛቤ የዳበረበት ጊዜ የነበረ ብቻ ሳይሆን፤ የተማሪዉ ንቅናቄ የርዕዮተ ዓለም ንቃተ ሕሊናን ለማዳበር መነሳሳት፤ ለፖለቲካ ፓርቲ መመስረት አንዱ ቅድመ ሁኔታ የተመቻቸበት ወቅት ነበር ለማለት ይቻላል። የተማሪ ንቅናቄዎች ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ የማቀጣጠያ ነዳጅ እንዲሆኑት ካስቻሉት ውስጥም ለትምህርት ብለዉ ወደ አሜሪካና አዉሮፓ የሄዱ ተማሪዎች ተነሳሽነትን በመፍጠር ከተማሪ ማህበር በላይ፤ በኋላ በዝርዝር የምንመለከታቸዉን መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ/መኢሶን የተባለዉን የፖለቲካ ፓርቲ፤ በአፍሪካ ደግሞ ቀደም ሲል አይሮፕላን ጠልፎ ሱዳን ገብቶ የነበረዉና በኋላ ላይ ወደ አልጀሪያ ተሸጋግሮ የአልጀሪያ ቡድን በመባል የሚታወቀዉን የነ ብርሃነ መስቀል ረዳን ቡድን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)ን ለመመስረት ጥንስስ የሆነዉን *Revolutionary Organization for the Liberalization of Ethiopia (ROLE)* የተባለዉን ቡድን በአስኳልነት ለመመስረት መቻላቸዉን እናያለን።

እያንዳንዱ ነገር መነሻ እንዳለዉ ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣት ተማሪዎች ንቅናቄ የብስለት መልኩን እየያዘ በመምጣት በኢትዮጵያ ለፓርቲ ፖለቲካ ፅንሰትና የፖለቲካ ፓርቲዎች ምስረታ ላይ የራሱን ጉልህ አሻራ ያሳረፈ፤ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ዉስጥ ሲወሳ የሚኖር ጉልህ እንቅስቃሴ ነዉ። ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 231) “የማይበገሩ የለዉጥ ተፋላሚዎች በመሆናቸዉም ከማንኛዉም የሕብረተሰብ አካል ይልቅ ያለፈዉ ሥርአት ቀባሪና የኢትዮጵያ አብዮት አንቀሳቃሽ ሞተር ለመሆን

በቁ” በማለት የኢትዮጵያ ተማሪዎችን አድንቀዋል፡፡

ከንጉሱ መውረድ እስከ ሕወሓት/ኢህአዴግ ያለውን የወጣት ተማሪዎችን አስተዋጽኦ ለታሪክ ባለሙያዎች እንተወውና ከነጉድለታቸውም ቢሆን በቅርቡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወጣቱ የተጫወተውን አንጸባራቂ ሚና እንኳን ብናነሳ አምባገነኑን የሕወሓት/ኢህአዴግን መንግስት ያፈናቀለው በቄሮ/ቃሬ፣ ኤጄቶ፣ ዘርማ፣ ፋኖ፣ በመሳሰሉት ስም የተደራጀው የወጣቶች ንቅናቄ ስለመሆኑ ታሪክ የመዘግበው አንድ ምዕራፍ ነው፡፡ ከወጣቶች ንቅናቄ ጎን ለግን ለፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ መነቃቃት ሌሎችም የውስጥም ሆነ የውጪ ኃይሎች ስለነበሩ ቀጥሎ አንዳንዶቹን በአጭር በአጭሩ አነሳለሁ፡፡

## የፋሽስት ጣሊያን ወረራና የውጪ የፖለቲካ ተፅዕኖ ለኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ

ለአንድ አገር ቅኝ መገዛት ጥቅም አለዉ ወይስ የለዉም የሚል ጥያቄ ሲነሳ፤ ቀላል ቁጥር የሌላቸዉ ዜጎች ጥቅም እንደሌለዉ በማስረዳት ምርር ያለ ክርክር እስከ ማድረግ ይደርሳሉ፡፡ ከላይ የመሬት ይዞታ አስተዳደርን አስመልክቶ እንደተገለጸው፤ ከዚህ በተቃራኒ የሚቆሙ ወገኖች ደግሞ በቅኝ ግዛቶች ዉስጥ በተወሰነ ደረጃ በሚታዩት የኤኮኖሚ መነቃቃትና የቴክኖሎጂ ሽግግር መኖሩን እየጠቀሱ፤ በሌላም በኩል ቅኝ የተገዙ አንዳንድ አገሮች ያሳዩትን መሻሻል፤ ለምሳሌ  ሱዳንና ኬንያ የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ጎረቤት አገሮችን የዕድገት ደረጃን ከኢትዮጵያ ኋላቀርነት ጋር በማነፃፀር የቅኝ አገዛዝ ጎጂነትን አሳንሰዉ የሚከራከሩም በርግጠኛነት አሉ፡፡

ላቅ ባለ ሁኔታ የሚያስቡ ዜጎች ደግሞ ቅኝ አገዛዝ በፖለቲካ ወይም በኤኮኖሚ የበላይነት ብቻ የማይወሰንና ቅኝ አገዛዝ በተናጠል በፖለቲካ ነፃነት ማጣት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በጥቅል (ፓኬጅ) ስለሚታይ፤ ማለትም የቅኝ ተገዥዉን ሕዝብ ባህል፣ ሃይማኖት፣ የአኗኗር ልማድ፣

የእርስ በርስ ግንኙነትና ሌሎች ነገሮችን ጭምር የሚበርዝ ስለሆነ ተማራጭነት የለዉም፤ እንዲሁም ቅኝ አገዛዝ የቅኝ ተገዥዉ ሕዝብ አንጡራ ባህልና አስተዳደር የዕድገት ሂደት ተፈጥሮአዊ ማህበራዊ አካሄዱን ይዞ እንዳያድግ የሚያቀጭጭ ስለሆነና ድቃላ (hybrid or mulatto) የሆነ አስተሳሰብ ማለትም አንዴ የአገሬዉን ሌላ ጊዜ ደግሞ የቅኝ ገዥዉን አስተሳሰብ ይዞ ብቅ ስለሚል፤ በተለይ ወጣቱ ዜጋ ሁለቱንም ወይም አንዱንም ሳይዝ ቀርቶ የችግር አረንቋ ዉስጥ ስለሚዘፈቅ፤ የአገር ልጅ አገዛዝ ድክመት እንዳለ ሆኖ፤ ቅኝ አገዛዝ የሚመኙት ነገር ሳይሆን አምርረዉ የሚጠሉት ክስተት ነዉ የሚሉ ወገኞች ቀላል ቁጥር የላቸዉም። አንዳንድ ሰዎች ቅኝ አገዛዝን በበቅሎ ይመስላሉ። በቅሎ ከፈረስና አህያ  የተወለደች ድቃላ እንስሳ ሲትሆን ለመሸከምና ረጅም መንገድ ለማቋረጥ ጉልበቷ አስተማማኝ ቢሆንም፤ በባህርይዋ ግን በቀላሉ የሚገሩ የፈረስም ሆነ የአህያ ተፈጥሮ ባህርን ሳትይዝ ቀርታ ኖሮ፤ አሳቻ ሁኔታ ካገኘች ወይም ከደነበረች ባለቤቷን ጭምር ረግጣ የመግደል ተንኮሏ ያን ያህል አስከፊ እንደሆነና ቅኝ አገዛዝም የሚፈጥረዉ ሕብረተሰብ አንድም የቅኝ ገዥዉ አሊያም የቅኝ ተገዥዉ ባህርይ ሳይሆን ቀርቶ ድቃላዉ ባህርይ በራስ መተማመን የሚባል ቃል ከመዝገበ ቃላቱ ጭምር የሚጠፋበት ደረጃ ላይ የሚደርስ ወገኖችን ስለሚፈጥር የሚጠሉ ወገኖች ይኖራሉ። ለማንኛዉም ግን ደረጃዉን ጠብቆ ያደገ ያገር ልጅ እሴት ከቅኝ አገዛዝ ተመራጭ እንደሚሆን ሳያስማማን አይቀርም።

በዚህ ጽሑፍ ዉስጥ ቅኝ አገዛዝን አስመልክቶ ጎራ ለይቶ የሚደረገዉን ክርክር ምንነት አጉልቶ ለማሳየት ተፈልጎ ሳይሆን፤ የጣሊያን ወረራ እንደ ወረራ በቆየበት ጊዜ ዉስጥ ለሽሽትም ይሁን ለትብብር ፊለጋ የተሰደደዉን ንጉሱን ሳይጨምር፤ አገር ዉስጥ ቀርቶ ፀረ ወራሪ የአርበኝነት ትግል ያደርግ በነበረበት ጊዜ ከቀደምት ታሪክም ሆነ ከወቅቱ ሁኔታ አንፃር ወራሪዉን የጣሊያንን ጦር በግልፅና በስዉር ይደግፉ የነበሩ ኢትዮጵያዊያን ስለነበሩ፤ በተለይም የኃይሌ ሥላሴን የስደት ሕይወትና ከስደት መልስ ከባንዳዎችና ስደተኞች ጋር በመመሳጠር የተከናወነዉን

አገዛዝ በመቃወም በወቅቱም ሆነ ከዚያን ወዲህም በንጉሱ ላይ የነበረዉን ቅሬታ ለማሳየት ቅኝ አገዛዝን የሚያሞግሱ ዜጎች መኖራቸውን ለማመላከት ነዉ።

ኢትዮጵያ ላይ ወረራ ተፈጸመ ቢባል እንጂ የወረረዉ የጣሊያን መንግስት ተረጋግቶ የራሱን ፖለቲካ፣ ኤኮኖሚና ሥነ ልቦናዊ አስተሳሰብ ሥርአት (እንደ ፓኬጅ) በኢትዮጵያዊያን መሀከል ሥር እንዲሰድ ያደረገበት ሁኔታ አልነበረም ተብሎ ይታመናል። እንዲያዉም፤ ምንም እንኳን ጣሊያን ኢትዮጵያን ወረረች ቢባልም፤ ከጣሊያኑ ወረራ የበለጠ ጉዳት ያደረሰው ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ጋር የተወዳጁት እንግሊዞችና አሜሪካኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ፈጥረዉ ከነበረዉ የሥነ ልቦና እና ሌሎች ተፅዕኖዎች ከጣሊያኑ ወረራ ቢብስ እንጂ ያነሰ አልነበረም ብለዉ የሚከራከሩ ሰዎች ብዙ ናቸዉ። ይህም ያለ ምክንያት አልነበረም። ከጣሊያን ወረራ በፊት ሕዝቡን በገዛ አገሩ የሰፋሪዎች፣ ገባሮችና ባሮች አድርጎ የቆየው የኃይሌ ሥላሴ መንግስት፤ በጣሊያን የአጭር ጊዜ ቆይታ ወቅት (1928-1933) ብዙ መንገዶችን፣ ድልድዮችንና ሕንፃዎችን መስራት የቻሉ ብቻ ሳይሆን ከመሬት ጋር ተያይዞ ያለውን የገባር ሥርአት ጣሊያን አስወግዶት የነበረውን ንጉሱ ተመልሶ ሥልጣኑን ሲቆናጠጥ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ ጭኖታል። በሌላም በኩል ስለቅኝ አገዛዝ የበላይነትና የበታችነት አምርረዉ የሚጠሉት ኢትዮጵያዊያን ወገኞች በበኩላቸዉ ነፍጠኞች ከአደረሱባቸዉ የጭካኔ እርምጃ የተነሳ በአዉሮፓዊያን ቅኝ አለመገዛታችን ቀረ እንጂ ሁለንትናዊ ጭቆናዉ ቅኝ ከመገዛት የተለየ ባለመሆኑ የሦስት ሺህ ዘመናት ነፃነት የሚባለው በቅኝነት ከመገዛት የተሻለ ነገር አላጋጣመንም የሚሉ ወገኞች ቀላል ቁጥር የላቸዉም። ቀላል ነዉ የማይባለዉና ፀረ ቅኝ ገዥው የሆነው የወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በእንግሊዞች በተደረገ ከፍተኛ ድጋፍ የጣሊያንን ወረሪ ጦር በመዉጋት በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከአገር እንዲወጣ አስገድደዋል።

ነገር ግን ማዕከላዊ ሥልጣን ከትግሬ ወደ ሸዋ በመዞሩና በተለያዩ ጥቃቅን ነገሮች ያኮረፉ የትግራይና የወሎ፣ የጎንደርና የጎጃም መሳፍንት ባንዳ

ሆነዉ ለወረረዉ የጣሊያን ጦር ከማገልገላቸዉ በስተቀር ቅኝ ግዛትን የሚጠየፉትም የማይጠየፉትም ዓይነት ሥነ ልቦና ተገንብቶ እንደነበረ ሕብረተሰቡ የተቀበለዉ የመኖር ስልት እንደነበር ይታወሳል። ባንዳነት የመጣዉ ያለምክንያት እንዳልነበርና “የኔን” ሥልጣን የወሰደብኝን ሰዉ ካጠፋልኝ አገር ተወረረ የሚባል ነገር <ዕዳዉ ገብስ ነዉ> የተባለዉን የሚመስል ነገር ከመከተል በስተቀር የወራሪዉን ባህልና ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ሊከተል የሚፈለግ ትውልድ ማግኘት አይቻልም እንደነበርም ይታወቃል። በሌላም በኩል አፄ ኃይሌ ሥላሴ አገር ጥሎ ሲኮበልል፤ የእሱ ብጤ የሆነ ሰዉ ደግሞ ዘር ብሎ ባንዳ ቢሆን ብዙም አስገራሚ እንዳልነበር የሚገነዘቡ ሰዎች ዛሬም ይኖራሉ። በዚያን ጊዜም ቢሆን የአፄ ኃይሌ ሥላሴን ለኩብለላ መሄድ የተቃወሙ የአገር ተወላጆችና የውጪ ሰዎች ለምሳሌ እንደ ማርካስ ጋርቬ የመሰሉ *“... Haile Sellasie, who fled to London, as a great coward who ran away from his country”* ያለው የመኖራቸዉን ያህል፤ የእሱ ደጋፊ የሆኑ ደግሞ ንጉሱ ለድጋፍ ፍለጋ የሄዱ ስለሆነ እንደክፉ ነገር ሊቆጠርበት አይገባም ብለዉ የሚሞግቱም አልጠፉም። ንጉሡም በዓለም ማህበር ፊት የጣሊያንን ወረራ በማውገዝ ተመሳሳዩ ወረራ በናንተ ላይ ቢሆንስ በማለት የሥነ ልቦና ተፅዕኖ ለማድረግ ከመነሳሳቱ ውጭ እንግሊዞች ወራሪውን ጣሊያንን እንዲወጋላቸው ያስማሙት ወይም የተስማሙበት ሁኔታ አልነበረም። ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያን ወደ ቀይ ባህር መረማመጃ ለማድረግ ሦስቱ አገሮች ፤ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ያሰዩትን ፍላጎት ጥሰው በፈንሳይ ግፊት ጣሊያን ኢትዮጵያን ማስወረር እንግሊዝን አነሳስቶ ከንጉሱ ጎን እንዲትቀም ሳያደርግ አልቀረም።

ከሸዋ በስተደቡብ የሚገኙ ሕዝቦች ግን ከወረረዉ የጣሊያን ጦር ጋር ለማበራቸዉ ቅኝ አገዛዝን ከነፃነት መርጠው ወይም በባንዳነት ለማደር ሳይሆን የተለየ የራሳቸዉ ምክንያት ነበራቸዉ። ከላይ እንደተጠቀሰዉ ከምኒልክ ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓይነት የመሬት ይዞታ ስሪት እንደነበሩ ተወስቷል። ከመሬት ጋር በተያያዘም የንብረት ባለቤትነት መነፈግ ብቻ

ሳይሆን የሰዉ ልጅ ስብዕናዉ ራሱ በጣም ዝቅ ያለበትና ከሰዉነት የወጣበት ጊዜ ቢኖር በፊውዳላዊ የኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን ላይ ነበር። ልዑል ራስ እምሩ ኃይሌ ሥላሴ በመፅሐፋቸዉ ገጽ 117 ላይ "ወላይታ፣ ጎፋ፣ ካፍቾ፣ ጋሞ በሚባሉት አገሮች ሌሎችም በዚያ ወገን አሉ፤ አፄ ምኒልክ አገሩን ሳይዙት ሳያቀኑት ጀምሮ መሬት በየባላባቱ ገዥነት ጊዜ አንዳንዱን ክፍል ወገን ባሪያ እያሉ እርስ በርስ እያጋቡ እንደከብት ሁሉ እያራቡ ለራሳቸዉም ያሰሯቸዋል፤ ለወደዱትም ይሰጧቸዉ፤ ይሸጧቸዉም ነበር" በማለት ከገለፁ በኋላ፤ በዚሁ መፅሐፍ "ያንጊዜም የኢጣሊያ ሹማምንት ፕሮፓጋንዳ ደህና አድርገን ከጥንት በተሻለ አኳኋን እናስተዳድራሃለን፤ አርፈህ በፀጥታና በሠላም ተቀመጥ" እያሉ በያለበት ወሬያቸዉን ይነዙ ነበር። … "በኦሮሞ ሕዝብና ባማራዉም አገር የነባሩ ወገን አንዳንዶችም መኳንንት ፈቃዳቸዉን [የጣሊያንን] እየተቀበሉ የሚታዘዟቸዉ ብዙ ነበሩ" (ገፅ 283) በማለት የባንዳነትን አሊያም ከወራሪዉ የጣሊያን ጦር ጋር የማበርን መሰረታዊ መንስኤ በባንዳነት ለማደር ከነበራቸዉ ፍላጎት የመነጨ እንዳልነበረ ገልጸዋል።

ይህ ብቻም አልነበረም፤ የደቡቡ ክፍል ሕዝብ የምኒልክም ሆነ የኃይሌ ሥላሴ አገዛዝን ከመጥላቱ የተነሳ ጣሊያንን የሚወጋ የአርበኛዉ እንቅስቃሴ እንዲበረታታ ያደረገዉ ጥረት አልነበረም። አገዛዙ እንደመረራቸዉም ልዑል ራስ እምሩ እንዳሉት "ያንጊዜም እንደምናየዉ ምንም ዕርዳታ ከዉጭም ሆነ ከግቢም የሚጠቀም አልነበረም፤ የኦሮሞ ሕዝብ ፈፅሞ ከኛ ሐሳብ እርቆ፤ የሚጠባበቀዉም የኢጣሊያንን ጦር እስኪጠጋለት ነበር" (ገጽ 286) "… የኦሮሞዉ ሕዝብ ሁሉ ባለፍንባቸዉ አገሮች ላይ የነበሩት ያማራ ግዛት የሰለቻቸዉ ከኛ ጋር የተባበሩ አልነበሩም፤ … ከጣሊያን ጋር እየተላላኩ ወዳገራቸዉ መድረሻዉን ቀን ይጠባበቁ ነበር፤ (ገጽ 293) … አንዳንዱም ባላገር ኦሮሞ እደኑ ዉስጥ እየተደበቀ ጠመንጃ እየተኮሰ ጥቂት የሞቱ፣ የቆሰሉ ነበሩ" (ገጽ 295) በማለት በንጉሱ ወይም በነፍጠኛ አገዛዝ ላይ ያሳደሩትን የጥላቻ ልክ በመጥቀስ ምስክርነታቸዉን ሰጥተዋል። ሲጠቃለል፤ ይህ ሁሉ የፈረንጇን

ቅኝ አገዛዝ ፈለጋ ወይም ባንዳነት ተመርጦ ሳይሆን ያማራ አገዛዝ ያስመረራቸው መሆኑን ያሳያል። እዚህ ላይ ወራሪ ጣሊያኖች ለደቡብ ሕዝብ የዋሉት ውለታ ቢጠቀስ የመሬት ስሪቱን ከኋላቀር ፊዉዳላዊ አስተዳደር ማላቀቅና ሕብረተሰቡን በቀላሉ ሊያናገኝ የሚችል መንገድ፣ ድልድይ፣ ትምህርት ቤት እና የሕብረትሰቡን ማህበራዊ ሕይወት ማሻሻል የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰዱ ነው። ነገር ግን ኃይሌ ሥላሴ ወደ ሥልጣን ሲመለስ ያንን ኋላቀር የፊዉዳል ሥርአት መልሶ ሕዝቡ ላይ በመጫኑ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የማይወደውን የጣሊያንን ቅኝ አገዛዝ ከንጉሱ አስብልጦ እንዲወድ አስገድዶታል።

ዛሬ የጣሊያን ወረራ ብሎም ቅኝ አገዛዝ ትርፍና ኪሳራን ለማስላት የሚያስችል ጊዜና ዕድል አለ ወይም የለም? የሚለዉን እሰጥ አገባ ወደ ጎን ትተን የጣሊያን ወረራ ብሎም ቅኝ አገዛዝ ኤርትራን ጨምሮ በኢትዮጵያ ዉስጥ የቆሰቆሰዉን የፖለቲካና የፓርቲ ፖለቲካ አንደምታ ማየቱ የተሻለ እንደሆነ ለማስታወስ መሆኑን ለማስገንዝብ እወዳለሁ። በጣሊያን ወረራና በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ምክንያት ኤርትራዊያን ዜጎች ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፋብሪካ ግንባታ በተሻለ ሁኔታ የኤኮኖሚ መነቃቃትና በተለይም ተጠቃሚ የሚያደርጋቸዉን ለአዉሮፓዊ ፖለቲካ ተሳትፎ ቀደምት ተጋላጭ ነበሩ ለማለት ይቻላል። ይህንን ለማጣጣል የሚሹ አንዳንድ ኃይሎች በኤርትራ የቅኝ ገዥዎች ተፅዕኖ ፓስታ ለመቀቀልና አበላል ለማወቅ ከማስቻል በዘለለ፤ ከሌላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ለፓርቲ ፖለቲካ የቅድሚያ ተጋላጭነት አልሰጣቸዉም የሚለዉን ተራ አባባል ወደጎን ይሉታል። ነገር ግን እዉነታዉ ቅኝ ገዥዎቹ ጣሊያኖች ከአቋቋሟቸዉ ፋብሪካዎች ጋር ተያይዞ፤ በኤርትራ የቢሮክራሲዉ መስፋፋትና የሠራተኛ ማህበራት መቋቋም፤ በኋላ በተራዉ ኢትዮጵያዊ ላይ የራሱን ተፅዕኖ እንደፈጠረ የሚያስረዳዉ፤ የቅኝ አገዛዝ በኤርትራ ውስጥ የፈጠረው ተፅዕኖ የኤርትራዊያኑን የፖለቲካ ዓይነ ጥላ ሳይከፍት አልቀረም ቢባል ተገቢ ይሆናል። ማለትም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽንም ሆነ በመዋሃድ ከተቀላቀለች በኋላ በዚያ አከባቢ የነበረዉ የፖለቲካ ብዥታ ወደ መሀል

ኢትዮጵያም ሳይስፋፋ እንዳልቀረ መገመት አያስቸግርም። ምክንያቱም በቅኝ አገዛዝ ጊዜ ላይ በተመሰረተ መነቃቃት ምክንያት አሃዳዊነትን የሚቃወሙ ሰዎች ጀብሃ በሚባለዉ ነፃ አዉጪ ድርጅት ሥር ከ1951 ጀምሮ በመሰባሰብ በ1953 የተኮሱት የመጀመሪያ ጥይት ለነፃነት ትግል የጀመሩት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ይታወቃል። ኃይሌ ሥላሴ ደግሞ ኤርትራንና ፌዴራላዊ አስተዳደሯን እንደ አደገኛ ምሳሌ ይመለከት የነበረው ከዚሁ በተፈጠረው ፖለቲካዊ መነቃቃት የተነሳ ይመስላል። እንግዲህ በአንድ የፖለቲካ ማህበር ሥር ለመሰባሰብ መንስኤ ምክንያቱ የሚለያይ ቢሆንም፤ ለሚሰባሰቡበት ዓላማ የሕሊናዊ ሁኔታ (የፖለቲካ ፓርቲ እንኳን ባይሆን መዳረሻ የሚሆኑ የሠራተኛና ሙያ ማህበራት መኖር) መጎልበት በቀዳሚነት እንደሚያሻዉና አንድ ወሳኝ ሚናም እንዳለዉ ማሰብ ይቻላል። በኤርትራ የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ደግሞ ይህንን ቅድመ ሁኔታ ያመቻቸ ይመስላል።

ከዚህ በኋላ ነዉ የኤርትራ ጥያቄ እራሱ በኢትዮጵያ ልሂቃን ዘንድ እንደ አንዱ የአቋም መዉሰጃ ቅድመ ጉዳይ ሆኖ ብቅ ማለት የጀመረዉ። ከዚህ ጽሑፍ ዓላማ ጋር ሲስተያይ ግን የአዉሮፓ አገሮች የቅኝ አገዛዝ ፖለቲካ ተቀባይነት አለዉ ወይም የለዉም በሚለዉ ላይ ያተኮረ ክርክር ለማንሳት ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አካል (Ethiopian body politics) ዉስጥ የኤርትራ ፖለቲካ መነቃቃት ሁኔታ ጥሎት ያለፈዉ አሻራ ቀላል እንዳልሆነ ለመዳሰስ ተፈለጎ ነዉ። በአጭሩ ሲጠቃለል ደግሞ አንድ ኃይል በኢትዮጵያ ገዥዎች ፖለቲካ ላይ ለመነሳት ቢፈልግ የሚነሳበትን ኃይሉን ከዉስጥ እና ከዉጪ ጭምር ተጠቅሞ መነሳት እንዳለበት የወቅቱ ጠቋሚ ክስተት ነዉ ማለት ያስደፍራል። ስለሆነም በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካም ሆነ ንጉሳዊዉን የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ለማዳከም የሚችሉ አካላትን በመፍጠር እሳቤ ዉስጥ የቅኝ አገዛዝ የተጫወተዉ ሚና ቀላል እንዳልነበረ ግንዛቤ ሊያስጨብጠን ይችላል።

## የሠራተኞች እንቅስቃሴ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለተከሰቱት የመንግስት ሥርአት ለውጦች የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ከየወቅቱ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የደረሰበት የአደረጃጀት ደረጃ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የተጠበቀዉን ያክል ባይሆንም የበኩሉን ድርሻ እንደነበረዉ ይታወቃል። በተለይም የካፒታል ክምችት መፈጠርና ለሠራተኛ መደብ ማቆጥቆጥ፤ ከ1950ዎቹ በኋላ የተፈጠሩ የእንዱስትሪዎች መቋቋም የራሱ ቦታ ያለው ሲሆን፤ የአፍሪካ ከቅኝ አገዛዝ መላቀቅና ሌሎች አፍሪካዊያን ወዳጆች ወደ አዲስ አበባ መምጣትና በግልፅና በስዉር የልምድ ልዉዉጥ ማድረግ ለኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ መነሳሳት አስተዋጽኦ እንዳደረገ ሁሉ፤ የሠራተኛዉ መደብም ከተራ ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ጥያቄ ባሻገር የፖለቲካ ንቃቱ የዓይነት ለውጥ አድርጎ የንጉሱን አልጋ በመነቅነቅ የሥልጣን ተጋሪነት ጥያቄዉን መሰንዘር የቻለዉ ከተጠቀሰዉ ጊዜ በኋላ እንደነበር የድርጊት ሰነዶች ይናገራሉ። በፓርቲ ፖለቲካ አመሠራረትና የሥልጣን ጥያቄ ላይም ለአጭር ጊዜም ቢሆን የሠራተኛዉ መደብ ያሳየዉ ተሳትፎ ጉልህ እንደነበርም ይታወቃል።

ሜይ አንድ የዓለም ወዛደሮች/ሠራተኞች ቀን በተቀረዉ ዓለም ዉስጥ እንደሆነ ሁሉ በኢትዮጵያም ከደርግ አስተዳደር ጋር ጀምሮ ሲከበር ቆይቷል። መከበሩ ክፋት ባይኖረዉም፤ እነማን ናቸዉ የሚያከብሩት? የሚያገባቸዉ ናቸዉ ወይስ በባለቤቶቹ ስም የሚያጠናብሩ ጮሌዎች ናቸዉ? የሚለዉ ጥያቄ ለኔም ሆነ ጥቂት ለማይባሉ ሰዎች መልስ ለማግኘት ገና ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ። ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም መሠረታዊ ዓላማውን በጥልቀት ይወቀው አይውቀው በርግጠኛነት መናገር ባይቻልም ሜይ ዴይን የሚያከብረዉ ለሶሻሊዝምና ሶሻሊስቶች ታማኝነቱን ለማሳየት ሲል ላቡ ጠብ እስከሚል ድረስ ለረጅም ሰዓታት አብዮት አደባባይ ቁሞ በመደስኮር ያከብራል። የእሱ ጊዜ ያህል ባይሆንም በዓሉ በጥቂት የኢህአዴግ/ብልፅግና ፓርቲ/ቡድን አባላት ዘንድም በሚያመቻቸው ሁኔታ ሲከበር ይስተዋላል።

ወደኋላ ተመልሰን ከታሪክ አንፃር ጨልፈን ስንመለከት የሠራተኞች ሕልዉና የተጀመረዉ ከቢዝነስ እና እንዱስትሪ መስፋፋት ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታወቃል። ይህም በአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ላይ የተመረኮዘ ነበር። የሥራ አከባቢና የኑሮ ሁኔታ አለመመቻቸት እየከፋ ሲሄድ፤ የሠራተኞች እንቅስቃሴም የራሱን ቅርጽና ይዘት እየያዘ ይፈጠራል። ከሥራ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች፤ ሥራ ማቆምና ሥራ ማቀዝቀዝ (strike and freeze) ሲሆኑ በዚሁ ሥራን የማቆምና የማቀዝቀዝ ምክንያት ሥራን እስከ መዝጋት የሚያደርሱና ሌላዉንም ሕብረተሰብ ክፍል ሊያሳትፍ የሚችል ግጭቶች ድረስ ሊከሰቱ ይችላሉ።

በ18ኛዉ መቶ ዓመት አጋማሽ በኋላ የተነሳዉ የእንዱስትሪ አብዮትና በተለይም ደግሞ የሶሻሊስት ሥርአት ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የሠራተኞች በጋራ መነሳሳት ከአዝጋሚ ጉዞ ወደ እመርታ ለዉጥ የተሸጋገረበት ዘመን ነበር። ይህም የምርትና የአመራረት ዓይነትን በመቀየር፤ በሕብረተሰቡ ዉስጥ ሠራተኛ/ወዛደር የተባለዉን አዲስ የሕብረተሰብ መደብ ፈጠረ። ይህ መደብ ዕዉቀትና ጉልበቱን በጥሩ ዋጋ ለጥሩ የሥራ ሁኔታ ለሚገዛዉ እየሸጠ እራሱንና ቤተሰቡን ማስተዳደሩን የሚሻ መደብ ነዉ። ምቹ የሆነ የሥራ ሁኔታ ሳይኖር ሲቀር ከአጋሩ አርሶ አደር ጋር እንቅስቃሴ የሚያደርግ ወይም ተቃዉሞ የሚያሰማ መደብ ነዉ። ተቃዉሞዉም ወቅታዊ ጥቅም ከማስከበር ባሻገር በወዛደራዊ ዓለም አቀፍዊነት የሚደገፍ ከሆነ እስከ ሥልጣን ጥያቄ የሚያደርስ ይሆናል።

ከ1936 በፊት በኢትዮጵያ ስለሠራተኞች ሕልዉና የሚታወቅ ነገር ብዙም ያልነበረ ቢሆንም፤ በዚሁ ጊዜ በንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥር የፋብሪካዎች አዋጅ ወጥቷል። ከዚያ በኋላ ብዙም የቁጥርም ሆነ የዓይነት ለዉጥ ሳይታይበት ቆይቶ፤ በ1948 በተሻሻለዉ የንጉሱ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47 መሠረት “ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በማንኛዉ የሥራ ሁኔታ ዉስጥ መሳተፍና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ማህበር መመስረት ይችላል” የሚል

ተደነገገ።

በአዋጁ ላይ ተመርኩዞ የ1952ቱ የፍትሐብሔር ሕግ ደግሞ የመደራጀት ነፃነትን ጨምሮ አነስተኛ የሥራ ሁኔታ ማቋቋምና ተቀጥሮ የመስራት ደንብን አካቶ ይፋ ሆነ። ነገር ግን ሕገ መንግስቱም ሆነ የፍትብሔር ሕጉ፤ ሠራተኞች በምን ዓይነት ሁኔታ ከአሰሪ ጋር እንደሚደራደሩ (አገሪቱ ከነበረችበት የዕድገት ደረጃ አንፃር ባይጠበቅም) ያለዉ ነገር አልነበረም። ከአራት ዓመታት በኋላ ግን ለዚሁ አፈፃፀም ሲባል በ1956 ዓም ለአሰሪዉ ያደላ ደንብ ወጥቷል። ይህ ደንብ እስከ 1968 ዓም ሥራ ላይ ቆይቶ ከ1966 እስከ 1968 የተከሰተዉ የአገዛዝ ለዉጥና ሶሻሊስታዊ የርዕዮተ ዓለም ለውጥን ተከትሎ ለሠራተኞች ያደላ ሌላ አዋጅ ወጣ።

አንባቢዎቼ እንዲረዱኝ የማሳስበዉ የትኛዉ አዋጅ መቼና የትኛዉ አዋጅ በየትኛዉ እንደተተካ ለመግለጽ ሳይሆን ከ1936 ዓም ጀምሮ ከሥራ ሁኔታ መሻሻል ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሱና ፖለቲካዊ መልክ የያዙ የኢትዮጵያ ሠራተኞችን እንቅስቃሴ ለማሳየት ተፈልጎ ነዉ። በዚሁ ሁኔታ አመቺ ሁኔታዎችን ያገኘዉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች መሰባበሰብ የተጀመረዉ ከኢትዮ ጂቡቲ የባቡር ሐዲድ ሥራ መጀመር ጋር የነበረ ሲሆን፤ ከዚያ ቀደም ሲል ግን ቁጥራቸዉ ይህን ያህል ነዉ የማይባል በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች፣ በቡና ቤቶችና በሆቴል ቤቶች አከባቢ የተወሰኑ የሠራተኞች ክምችት በነበሩባቸዉ አከባቢዎች ነበሩ። ከኢትዮ ጂቡቲ የምድር ባቡር መከፈት ጋር የተጀመረዉ የዚህ የሠራተኞች ስብስብ አቅመ ደካማ የመሆን ጉዳይ፤ ከደካማ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ መግባት ጋር የተያያዘ የነበር ቢሆንም እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን ኤርትራን መረማመጃ አድርጎ የገባዉ የጣሊያን ወረሪ ጦር ለመንገድና የከተማ ቤቶች ሥራ የተጠቀመዉ በመደቡ የተደራጀዉን የሠራተኛ መደብ ወይም በአንድ ወይም በተወሰነ አከባቢ ከተሰባሰበዉ የሠራተኛ ስብስብ ይልቅ ብዙም ከማሳዉ ወይም ከቀዬዉ ያልተነጠለዉንና መነጠልም የማይፈልገዉን የገጠሩን ሕብረተሰብ ክፍል ይጠቀም ነበር። በዚህ መሠረትም እስከ 1950ዎቹ ድረስ በኢትዮጵያ የነበረው የሠራተኛ መደብ

የሚባለዉ የራሱን መደብ በሚገልፅ ዓይነት ሁኔታ ሳይሆን ኋላቀር የሆነዉን የአገሬዉን ሕዝብ አምሳያ ሆኖ ነበር። ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ለመደቡ ስለመቆሙ ከዚያ ሁኔታ የተለየ ያሳየዉ የዓይነት ለዉጥ ለማየት አድካሚ የሆነ ፊለጋ ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ አይቀርም።

ውስን የሆነዉ የእንዱስትሪና የእርሻ ክፍለ ኤኮኖሚዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ ማንሰራራት የጀመሩት ከ1950ዎቹ አጋማሽ በኋላ በፈጠሩት የጥቅም ግንኙነት የሠራተኛ መደብና የመደቡ የጥቅም ማስከበር እንቅስቃሴም የራሱን ቅርፅ መያዝ ጀመረ ለማለት ይቻላል። የእንቅስቃሴዉ ገጽታም በውስንና ምስጢራዊ በሆነ ሁኔታ በተለይም ከማህበራዊ ንቃተ ሕሊና እና እርስ በርስ ከመረዳዳት የዘለለ አልነበረም። በሌላም በኩል ንጉስ ኃይሌ ሥላሴ ራሱ ሕግ በሚሰጥበት ጊዜ በአደረገው ንግግር ውስጥ "... የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎች አገር ሕዝቦች ተለይቶ በመኖሩ ታላቁ የዘሬው ሥልጣኔ የሚሰጠውን ጥቅም ለማግኘት ሳይችል በመቆየቱ ..." ብሎ እንደመሰከረውና በተክል ፃዲቅ መኩሪያ መጽሐፍ እንደተጠቀሰው፤ ኢትዮጵያዊያን እምብዛም በውጭ ዜጎች ዘንድ ያልታወቀው የኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔታ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ መቋቋም የተነሳ፤ የኢትዮጵያ ሠራተኞች የሥራ ሁኔታም ለአፄ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት በጥያቄነት መቅረብ የጀመረዉ ከዚህ ከዉጪ አገር ሰዎች ጋር በተፈጠረዉ ግላዊና ቡድናዊ ግንኙነቶች ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይገለፃል። በዚህ የተነሳም አንዳንድ ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸዉ የውጭ ዜጎች አፄ ኃይሌ ሥላሴ የራሱን ዜጎች መብት ዝቅ እያደረገ፤ እንዴትስ ቢያደርግ ነዉ ፀረ ቅኝ አገዛዝ እና ፀረ ዘረኛ ተልዕኮ ያነገበዉን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽህፈት ቤትን በአገሩ ዉስጥ የሚያስተናግደዉ? የሚል ተጠይቃዊ ሐሳብ ያነሱ እንደነበረ ታዉቋል። ይህንንም ግብረ መልስ ለመስጠት ወይም ጠያቂዎቹን ለመሸንገል በሚመስል መልኩ የ1953ቱን የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ እንዲወጣ ያደረገዉ። በዚህ አዋጅ በመታገዝም እስከ1956 ድረስ ወደ ሃምሳ የሚጠጉ የሠራተኛ ማህበራት በአገሪቱ ዉስጥ ሊመሰረቱ ችለዉ ነበር።

እነዚህ የሠራተኛ ማህበራት ተሰባስበዉ የሠራተኛ ማህበራት ኮንፌደሬሽን ከማቋቋማቸዉም በላይ የዓለም የሠራተኞች ማህበራት ፌዴሬሽን ተመልካች አባል እሰከመሆን ደረጃ ደርሰዋል። ቢሆንም ግን እስከዚህ ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሠራተኞች የኑሮ ሁኔታ በቅኝ ተገዥ ጎረቤት አገር ጂቡቲ በምድር ባቡር ዉስጥ ከሚሰሩ ሠራተኞች ያነሰ ከመሆኑም በላይ፤ ሠራተኞቹም ይህንኑ ሕይወታቸዉን የሚለዉጥ ጥያቄ ለማንሳት ወይም ለማቅረብ አንዳች ብቃት አልነበራቸዉም። የያን ጊዜዉ ብቃት ማነስ እስከ ሃያ አንደኛዉ መቶ ዓመት ድረስ ቀጥሎ፤ ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ እያሸለበ ያለ በሚመስል መልኩ፤ የሠራተኞች አርስቶክራቶች የነገሱበት መሆኑ በተጨባጭነት ይታያል። ለምሳሌም ያህል የአገሪቱ ባለሀብቶች ከገዥዉ ኢሊት ጋር የወገኑ ወይም እነሱዉ ራሳቸዉ የጥቅም ተካፋዮች ስለሆኑ፤ ሙያተኞችን የሚቀጥሩበት አነስተኛ የክፍያ ምጣኔ (minimum wage standard) ተደንግጎ ባለመኖሩና ይህንንም የመነጋገርያ አጀንዳ አድርጎ የሚያነሳ አደረጃጀት ባለመኖሩ በአገሪቱ ዉስጥ ያለዉ የኑሮ ሁኔታ በአንድ ጫፍ በጣም የናጠጠ ሀብታምና በሌላ ጫፍ ደግሞ በጣም የደኸዬ ድሃ ሠራተኛ፤ ሁለት ሊተሳሰቡ የማይችሉና የጋራ አገር ቢኖራቸዉም የጋራ እሴት የሌላቸዉ ዜጎች የተፈጠሩበት፤ ወይም የአንዱ ሕልዉና ለሌላዉ ጨርሶ አሳሳቢ ያልሆነ ዜጎች በአገሪቱ ዉስጥ የሚኖሩ የሚመስልበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነዉ። የሠራተኛዉ መደብ ተጠናክሮ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ ሁለቱን ተቃራኒ ጫፎች፤ ማለትም በአሰሪና ሠራተኛ መሀከል የሚታየዉን የኑሮ መራራቅ በተወሰነ ደረጃ ማጣጣም እንኳን ቢቀር ማቀራረብ በተቻለ ነበር ለማለት ነዉ። “እንደእዉነቱ ከሆነ የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ተብሎ ስም የበዛበት ኃይል የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ በመኢሶን ወዝአደርነትና በኢሕአፓ ላብ አደርነት መካከል ያለዉን ልዩነት ሳያዉቅና ተራ ጥቅሙንም ማስከበር አቅቶት፤ መጀመሪያ የደርግ አሁን ቆይቶ ደግሞ የኢህአዴግ መጫወቻ የሆነ የምስኪኖች ስብስብ መሆኑን መረዳት አያቅትም።” በማለት ዶ/ር መረራ ጉዲና የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ዛሬ ድረስ የት ቦታ ላይ እንዳለ አስቀምጧል። በሌላም በኩል አደገ

የተባለዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ አስተማማኝ ደረጃ ላይ ስለመድረሱ ገና አጠያያቂ ቢሆንም፤ ሠራተኛዉ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮዉን ለመሸፈን ሲል ዉድድር አይሉት ምቀኝነት አንዱ ሌላዉን ጥሎ ለማለፍ የሚደረገዉ ማፈናቀል አይጣል የሚባል ሲሆን፤ ይህም ሊፈጠር የቻለዉ ለጋራ ጥቅም በጋራ የሚያስተባብራቸዉ የራሳቸዉ የሠራተኛም ሆነ የሙያ ማህበር ወይም ሊያግዛቸው የሚችል አደረጃጀት ስለሌላቸዉ ነዉ። በአገርና ዓለም አቀፍ ሕጎች ላይ ተመስርቶ የሠራተኛዉን ኤኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ጠንካራ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት ቢኖሩ ኖሮ፤ ደም የመምጠጥ ያህል አሰርቶ የማይከፍለዉ ባለሀብት አደብ ይገዛና ሠራተኛዉም የሚገባዉን ጥቅም ያገኛል ማለት ነዉ። ላቅ ባለ ሁኔታ ደግሞ ጠንካራ የሠራተኛ ማህበር ቢኖር የሕገ መንግስታዊ መብቶች መሸራረፍ ከመቀነሱም በላይ ባለሀብቱ ራሱ በጠመንጃ አፈሙዝ ሥልጣን ላይ ወጥቶ ከሚጠምዝዝ ኃይል ይልቅ ለአገሪቱ ሕገ መንግስት መከታ የሚሆን መንግስት እንዲፈጠር ጭምር ያስገድድ ነበር ተብሎ ይታመናል። ጠንካራ የሠራተኛ ማህበር መኖር ለጠንካራ ሕገ መንግስታዊ ሥርአት መፈጠርና መጠበቅ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል። አነሰ እንኳን ቢባል ሰብአዊ መብታቸዉ የተጠበቀ ዜጎች እንዲፈጠሩ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት የሚያበረክቱት አርአያነት ሰፊ ነዉ። የጠንካራ ማህበራትን አስተዋጽኦ ዘርዝሮ መጨረስ ባይቻልም፤ በዜጎች መሀከል የሚፈጠሩ ያልተመጣጠነ የኑሮ ሁኔታን ለመቀነስ ከፍ ያለ እገዛ ማድረግ እንደሚችሉ አንድና ሁለት የለዉም።

እንግዲህ እስከ 1950ዎቹ መጨረሻ ድረስ ከመናኛ ጥቅማ ጥቅሞች ጥያቄ ባሻገር የኢትዮጵያ ሠራተኞች እንቅስቃሴ አልነበረም እንኳን ባይባል በጣም አነስተኛ ነበር ለማለት ይቻላል። ነገር ግን በ1960 የተመሠረተዉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን መቋቋምና ከዓለም የሠራተኞች ማህበራት ፌደሬሽን ጋር የጀመረዉ ግንኙነት በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ዉስጥ የሚያደርገዉን ተሳትፎ አጎልብቶታል። በተለይም ከ1960 እስከ1965 የነበረዉ ጊዜ (ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላም ታይቶ በማይታወቅበት ሁኔታ) በአንድ ወቅት

የውጪ አገሮች ትምህርትና ግንኙነት የነበራቸው ወጣቶች በአሳደሩበት አዎንታዊ ተፅዕኖ ምክንያት የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ከራሱ መደብ ባሻገር ለሌሎች የመደብ አጋሮቹ ሊናገርና ሊደመጥ የቻለ የሕብረተሰብ ክፍል ለመሆን ችሎ ነበር። ይህም ሊታገዝ የቻለዉ ከዚያ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ የፖለቲካ ሥልጣን መጠየቅ የሚችሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች (በውጭ አገር ቢመሰረቱም) በአጠቃላይ በአገሪቱም ሆነ በተለይ በሠራተኛ መሀከል እንደገቡቱ የመላዉ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የተቋቋሙበትና ከዚህ ከሠራተኛ መደብ ጋር የተደባለቁበት ጊዜ ነበሩ።

ምንም እንኳን የእነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች መሠረት (በኋላ በዝርዝር እንደምናየዉ) በዉጭ አገሮች የነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ቀጣይ ቢሆኑም፤ በስድሳዎቹ ለተከሰቱ ቀዉሶች ፖለቲካዊ መልክ ግፋ ቢልም የሥልጣን ጥያቄ እንዲያቅፍ አስገድደዉ የሠራተኛዉን መደብ ሊያንቀሳቅሱ የቻሉ ናቸዉ። ምንም እንኳን ኢሕአፓ የተባለዉ የፖለቲካ ማህበር መንግስት” የማቋቋም ጥያቄን ከ1966ቱ አብዮት መነሻ ጋር አያይዞ እስከሚያነሳና በዘላቂነትም የሠራተኛዉ መደብ የፓርቲ ፖለቲካ ጨዋታ (የሥልጣን ጥያቄ) ዉስጥ እንዲሰለፍና የራሱን ተጨማሪ ሚና እንዲጫወት ከማድረጉ በፊት የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ያደረገዉ አስተዋጽኦ የጎላ አልነበረም። ምክንያቱ ደግሞ በአገሪቱ ዉስጥ የተንሰራፋዉ ድህነትና መሃይምነት በግንባር ቀደምትነት ያጠቃ የነበረዉ ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረዉን ሠራተኞችና ቤተሰቡን ስለሆነ፤ የሠራተኛዉ መደብ ከዕለት የራሱንና የቤተሰቡን ኑሮ ከመድፈን ባሻገር ስለፖለቲካ ሚናዉ ሊያስብ የሚችልበት አጋጣሚዉ አልነበረም። እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ ደግሞ የሠራተኛዉ መደብ የኢትዮጵያ ፊዉዳል ሥርአት ፖለቲካ መስመር ተላቅቀዉ በነፃነት እንዲራመዱ ስላልተፈቀደላቸዉ፤ አስቀድመዉ የነቁቱ ለስደት የተዳረጉ እንዳሉ ሲታወቅ፤ ተተኪዎቹ ደግሞ የሠራተኞች አርስቶክራቶች ሆነዉ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት” እያሉ ቀርተዋል። የሠራተኛዉ መደብ የመሪነት ሚናም ከ1980ዎቹ ጀምሮ ከሶሻሊስት ሥርዓት (እንደሥርዓት ማክተም ወይም መቀዛቀዝ ጋር)

ያከተመ ሆኗል። ቢሆንም ግን በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞከረዉ እስከ 1960ዎቹ ድረስ የሠራተኛዉ መደብ የተጫወተዉ ሚና የጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ ተፅዕኖ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል ግምት የሚሰጠዉ አልነበረም።

**የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ፡**

ከ19ኛዉ መቶ ዓመት በፊትም ሆነ በኋላ ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ሲወጣና ሲወርድ የነበረዉ ዛሬ ላይ ሆነን የምንገነዘባቸዉም ሆነ የምናዉቃቸዉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሕዝብ ተወካይ ለመሆን በግለሰቦችና ቡድኖች መሀከል የሚደረግ ፉክክር አልነበረም። ነበረ እንኳን ቢባል ለሥልጣን በሚደረገዉ እሽቅድምድም ዉስጥ በግለሰቦች መሀከል የተደረገ መሿኮትና ከንብረት መዉደም እስከ ሕይወት መጥፋት የደረሰ ወቅቶች ነበሩ። ለምሳሌም ቴዎድሮስ የየጁ ሥርወ መንግስት የሆነዉን የራስ ዓሊን አገዛዝ ከሥልጣን ለማስወገድ ጅምላ ጭፍጨፋ አካሂዷል። አፄ ዮሐንስ በቴዎድሮስና በተክለ ጊዮርግስ ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት ከእንግሊዙ ጦር አዛዥ ከናፒየር ጋር አሳፋሪ መሞዳሞድን ፈጽሟል። ምንሊክ ዮሐንስ እንዲሞት ሸፍጥ ፈጽሟል። እያሱ የተወገደዉ ሰበቡ ብዙ ሆኖ በተፈጸመበት የቤተ መንግስት ኩዴታ ነበር። ኃይሌ ሥላሴ በቀጠራቸው ወታደሮች ከመወገዱም በላይ ሲሞት መቃብሩ በደርጉ ሊቀ መንበር የግል ጉዳይ መጠቀሚያ ቤት አከባቢ ነው። ደርግ በተራው የተወገደው ነፋስ እንደመታው ጉም ተበታትኖ ነው። የዚህ መጽሐፍ 2ኛ ዕትም እየተዘጋጀ ባለበት ጊዜ የመዤንግሩ ቃሊቻ ተንብዮታል እንደሚባለው የወያኔ/ኢህአዴግ ቡድን መንግስትም የተወሰነ ቀሪ ክፍሉን ፊንፊኔ ላይ ትቶ እሱም እንደጉም ተበትኗል። ዲሞክራሲያዊ የሕዝብ ዉክልና ከቃላት ሳያልፍ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እነሆ 21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ ደርሷል። ቀጣዩ ጊዜ ለኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኛነት መናገር ቢያቅተንም ሥልጣን ላይ ካለዉ ቡድናዊ አምባገነናዊ ሥርአት የተነሳ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ግን በልቤ ሙሉነት መናገር ይቻላል።

ቴዎድሮስን ለመጣል በተደረገዉ ትግል ዉስጥም የወርቂት፣ የመስተዋት፣ የተክለ ጊዮርግስና የዮሐንስ ድርሻ ብዙ ቢሆንም፤ ዮሐንስ ከእንግሊዙ ጀኔራል ናፒየር ጋር በፈጠረዉ የተሻለ ግንኙነት የዮሐንስ ቡድን አሸናፊ ሆኖ ሊወጣ ችሏል። አንዱ ቡድን በሌላዉ ላይ የበላይነትን አግኝቶ ለመዉጣት በተደረገዉ ግብግብ፤ ደም አፋሳሽ እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም፤ ለአንዱ ቡድን ያደላና በተቃራኒ ላይ የሚገኘዉን ቡድን ለመበደል ወገንተኝነት የተንፀባረቀበት ትግል ነበር ለማለት ይቻላል። በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ገዥ ክፍሎችን በአጽንኦት ስንምለከት (አሁንም ተክለ ጊዮርጊሰና ዮሐንስን ሳይጨምር)፤ ቡድናቸዉ የበላይነትን ተጎናጽፎ እንዲወጣ ለማስቻል፤ ከአፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ ሥርወ ሰለሞን የተባለዉን ትውፊት እየጎተቱና የፊውዳል ሥርዓት እያራመዱ እስከ አፄ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት ድረስ ዘልቀዋል። ከልዩነታቸዉ ይልቅ አንድነታቸዉ የበለጠ የሚጎላዉ የፊዉዳል ነገስታት መጠነኛ ልዩነት ነበራቸዉ እንኳን ቢባል በአጭር የተቀጨው የልጅ ኢያሱ አገዛዝ ዘመን መሠረታዊ ሕግ ነክ ጉዳዮች መሻሻልና ኃይሌ ሥላሴ ደግሞ አገዛዙን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ማለትም እስከ 1920ዎቹ መጨረሻ ድረስ ሕገ መንግስታዊ ሽፋን ለማሰጠትና ለማዘመን የወሰነበትና ከውጪ መንግስታት ጋር ያደረገዉ ግንኙነት የሚጠቀስ ይሆናል። አፄ ምኒልክ አጎራባች ሕዝቦችን ወርሮ ቅኝ ግዛቱ ቢያደርግም ዘመናዊ ትምህርት፣ ትራንስፖርት፣ መገናኛ፣ ሕክምና፣ ወዘተ ማስፋፋቱ፤ ዛሬም ድረስ ሊካዱ የማይችሉና በቅርስነት ያሉ ምስክሮች ናቸዉ። እነሱም በተራቸው ቢያንስ ከተወረረው ደቡብ ግዛቶች የምግብ ዋስትና በማግኘታቸው የተደሰቱት የልጅ ልጆቹ ዛሬም ለዚያ ውለታው ሲባልም የሴሜቲክ ወይም የአበሻ ልጆች ተብለዉ የሚታወቁት ይኸዉ እስከዛሬ ድረስ ለዉለታዉ በስሙ እያመለኩ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

በምኒልክ የተጀመሩ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና መንግስታዊ አገልግሎቶች በተለይም የትምህርት ማዕከላት መስፋፋት፤ በአፄ ኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በተለይም በመጀመሪያዎቹ የነጋሲነት ወቅት ላይ

የሚጠበቀውን ያህል ቀጣይነት ሊያሳዩ ካለመቻላቸዉም በላይ፤ የዚህ ነጋሲ ትልቁ ችግርም አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ሊመሩ የሚችሉ ከዘር ሐረጉና የደም ትስስሩ ዉጭ ሌላ ባዕድ ወይም የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዳይገቡበትና ከዉስጥም ማዉጣት አለመቻላቸዉ የአገሪቱ ዕድገት ቁልቁል እንዲሆን አስገድዶት እንደነበረ እናስታዉሳለን። ፀረ አፓርታይድ ታጋዩና ለሽምቅ ውጊያ ሥልጠና ወደ አዲስ አበባ ዘልቆ የነበረዉ ኒልሴን ማንዴላ (1994፡ 349) የወቅቱ የኃይሌ ሥላሴን መንግስት ከጠበቀዉ በታች ወርዶ ያገኘ መሆኑን በ *Long Walk To Freedom* በሚለዉ መጽሐፉ *"Contemporary Ethiopia was not a model when it came to democracy, either. There were no political parties, no popular organs of government, no separation of powers, only the emperor, who was supreme." በማለት ተችቶታል።* በጣም አሳዛኙ ነገሩ ደግሞ ማንዴላ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ የነቀፈዉ ያልሰለጠነ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አመራር ከ50 ዓመታት በኋላም ቢሆን (እኔም ልጨምርበትና)፤ ሕዝባዊ ቅቡልነት ያለው የመንግስት ተቋማት (*popular organs of government)* አልተገነቡም፣ በመንግስት አካላት (ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ) መሀከል የሥልጣን ክፍፍል የለም (አለ ቢባል እንኳን አንድም እንደሚጠበቅ ወይም ትርጉም ያለው አይደለም)፣ ዴሞክራሲ የለም፣ የውስን ሰዎች ወይም ቡድኖች ወሳኝነት ብቻ ጎልቶ የሚንፀባረቅበት ነው። ይህንን እንደለውጥ የሚመለከቱ ካሉ ከኃይሌ ሥለሴ የአንድ ሰዉ ፈላጭ ቆራጭነት (aristocracy) ወደ የጥቂት ግለሰቦች ቡድን (oligarchy) ከመለወጡ በስተቀር ዛሬም ድረስ በመሠረታዊነት ለሕዝቡ ሕይወት ዋስትና የሚሆን የኢትዮጵያ ፖለቲካ የተሻለ የሚባል የአመራር ለዉጥ አላሳየም። ማለትም ተቋማዊነት ያለው አሳታፊ የፖለቲካ አመራር አልተፈጠረም ነዉ።

አፄ ኃይሌ ሥላሴ የአዋጁ አገላለፅ ኃላፊነት አለብኝ ከሚል ሰዉ የወጣ ባይመስልም፤ የባሪያ ንግድን በአዋጅ ማስወገዱና ይህም በዓለም መንግስታት ፊት ቆሞ መናገር ያስቻለዉን ያህል፤ ልክ እንደ ንጉስ ምኒልክ በመሬት ይዞታ ምክንያት ሕብረተሰቡ በሙሉ የባለመሬት ባሮች

ያደረገዉን የመሬት ይዞታ ስሪት ለማስተካከል አንዳች ሙከራ ባለማድረጉ የኢትዮጵያ ግብርና ምርታማነት እንዳያድግ ትልቅ እንቅፋት ሆኖበት ሰንብቷል። የተቆላ እህል ቢዘራበት ያበቅላል የሚባል ለም መሬት አለን እየተባለ እስከ 21ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ኢትዮጵያዊያን የምግብ እህል ተመፅዋች ሆነን እየኖርን ነው። አንዳርጋቸዉ አሰግድ ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሐፉ ገጽ 109 ላይ ይህ ለዉጥን አለመሻት የፊውዳል ገዥ አባላትና ንጉሱን ምን ላይ እንደጣላቸዉ እንደሚከተለዉ አስቀምጧል። "የንጉሴ ነገስቱ የገዥ መደቦች የመሬት ይዞታና የባለመሬት-ጭሰኛ ግንኙነት ጥያቄዎችን ተቀብለዉ አንዲት ጋት ፈቀቅ ለማድረግ ባለመፈለጋቸዉ ከለውጡ ጥያቄ አንፃር ስንመለከታቸዉ የራሳቸዉን አስከፊ ዉድቀትና መቃብር ሲያዘጋጁና ሲቆፍሩ የኖሩ ነበሩ" ብሏል።

እንደትግሉ ጥንካሬና ጥልቀት ሊያጥር ወይም ሊረዝም ይችላል እንጂ የሕዝቦች እንቅስቃሴ የመጠን ለዉጥ ተጠራቅሞ ወደ ዓይነት ለውጥ መሸጋገሩ አይቀሬ እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ከሕብረተሰቡ አብራክ የሆኑ የተማሪዉ፣ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ወዘተ ያደረጉት እንቅስቃሴ ተጠራቅሞ ሕልዉናዉ ከመሬት ይዞታ ስሪት ጋር የተያያዘዉን የኃይሌ ሥላሴን የፊውዳል ሥርዓት እንዲወድቅ አድርጓል።

በመሠረቱ፤ በስርአተ ንግሱ ውስጥ የመጠን ለውጥ እንኳን ባለማሳየቱና ንጉሱ እስከ ሚጃጅ ድረስ ሥልጣን ላይ ሙጭጭ በማለቱ፣ የመሬት ይዞታ አለመሻሻልና የድህነት መንሰራፋት በውጫዊ ሁኔታዎች ታግዞ በአስከተሉት ቀዉስ የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ሊወድቅ ችሏል። የኃይሌ ሥላሴ መንግስት መዉደቅ ማለት ደግሞ የሥርወ ሰለሞን ዘር መንግስት መዉደቅ፤ በተለይም የፊዉዳል ሥልተ ምርት የመጨረሻ ግብአተ መሬቱ የተፈጸመበት ነበር። በኃይሌ ሥላሴ መንግስት ዘመን የመጨረሻ አከባቢ ሕዝብን መርቶ ለድል የሚያበቃ የፖለቲካ ፓርቲ ባይኖርም፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ የሆነ የፓርቲ ፖለቲካ ቅርጹን ይዞ ብቅ ማለት የጀመረበት ወቅትም (epoch) ይኼዉ የኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ለመሆኑ መካድ አይቻልም። ከዚህ በኋላም በዘር ሐረግ እየተሳሳቡ ሲሿሿሙ

የነበሩ የፊዉዳል አገዛዝ ዘመን የሥልጣን ዝዉዉርና ውርስ በኃይሌ ሥላሴ ላይ ማክተሙ አንድ ቢሆንም፤ ነገር ግን በተጠበቀው ሁኔታ ስኬታማ ባይሆንም፤ አዲስ አስተሳሰብ የሆነዉ የፓርቲ ፖለቲካ ቅርፅ ይዞ ብቅ ያለበት ጊዜ ነበር። ቀጥሎ ባለው ምዕራፍ ላይ በስፋት የምንመለከት ይሆናል።

## ምዕራፍ ሁለት፡ **የወታደራዊ ደርግ አነሳስና ሊዳፈን የነበረው የፓርቲ ፖለቲካ ጥንስስ**

የሕግ የበላይነትን ለማስፈንና ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ መሆኑን ለማረጋገጥ የረጅም ጊዜ ትግልና ከፍተኛ የሕይወት ዋጋ ከሚያስከፍለዉ ዉስጥ ለሰው ልጅ ዕድገትና ሥልጣኔ ዝግ የሆነውን የፊውዳል ሥርዓትን ለማስወገድ የሚካሄደዉ ትግል ዕልህ አስጨራሽ ነው። ትግሉ ደግሞ ፈርጀ ብዙ ማለትም ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ድንቁርናን ጭምር መዋጋት ሲሆን፤ የፊውዳል ሥርዓቱን ማስወገድ ማለት የፊዉዳል ሥርአትን እንደ ሥርአት የአምላክን ተልዕኮ ፈፃሚ የሃይማኖት ሥርአት ጋር የተተበተበ ስለሆነ የአፈና መዋቅሩን አሽንፎ ለመሻገር ከፍተኛ ትግል ይጠይቃል፤ ተተኪ ሕዝባዊ ሥርዓት መፍጠሩ ራሱ ከዚህ ያላነሰ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነዉ። ከዚህም የተነሳ ነዉ ምንም እንኳን ከ1966 መጨረሻ ላይ ጀምሮ የፊውዳል ሥርዓት መሠረት የሆነው የመሬት ይዞታ ስሪት ከኢትዮጵያ ቢወገድም ያንን የፊውዳል ሥርዓት የተካዉ ሥርዓት ደግሞ (ወደፊት በዝርዝር የምንመለከት ይሆናል) የባሰዉኑ አፋኝና የዜጎችን ሕይወት የበላና የትውልድ ክፍተት *(generation gap)* ጭምር የፈጠረ አስቸጋሪ የነበረ የወታደራዊ አገዛዝ ሥርአት ነዉ። ለዚህም ነዉ አንድን ሥርዓት መለወጥ ብቻ ሳይሆን ምትኩን መፈለግ ወይም ማግኘትም ያንኑ ያህል ወይም የበለጠ አስቸጋሪ ይሆናል የሚባለዉ። “ማፍረስ ቀላል ባይሆንም መገንባት ደግሞ የበለጠ ከባድ ነዉ” የሚለዉ ሐረግ ከኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ዉድቀት በኋላ በደርግ መንሰራፋት አከባቢ አብዮታዊ መድረክ በሚል በመገናኛ ብዙሃን በተደጋጋሚ ይነገር የነበረው ቃል የሥራውን አስቸጋሪነት ገላጭ ለማድረግ ነው። የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሊያልቅ ሩብ ያህል ሲቀር መሠረቱ የተናጋው የኢትዮጵያ ፊውዳል ሥርአት መልኩን እየቀያየረ እስከ ሃያ አንደኛው ሩብ ምዕተ ዓመት ድረስ ኢትዮጵያዊያን ልንላቀቀው አለመቻላችን የፊውዳል ሥርአት ምን ያህል መጣጭ ዋግምት እንደሆነ ያመለክታል።

የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ሕልዉናዉን እየገዘገዘ የመጣዉን ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ለመቆጣጠርና ብሎም ለማፈን ንጉሱ ያለ የሌለ ኃይሉን የተጠቀመ ቢሆንም የሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ረሃብ፣ የነዳጅ ዋጋ መጨመርና የኑሮ ሁኔታ መመሰቃቀል፣ የታክሲ ሾፌሮችና የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ በአጠቃላይም ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ሁኔታዎች በመደማመር የንጉሱን መዉደቅ ሲያፋጥኑት፤ ሥርአቱን ሊታደገዉ የሚችል የዉስጥም ሆነ የዉጭ ኃይል ብቅ አላለም። እንዳዉም የሥርዓቱ ታማኝ የነበረዉ የመለዮ ለባሹ ሠራዊት በየክፍለ ጦሩ እያመጸ የደመወዝ ጭማሪና በዳይ አለቆቹ ከሥልጣን እንዲነሱለት የሚያቀርበዉ ጥያቄ እየጨመረ እንዲሄድ አደረገዉ። የደጉ ቀን አጋር ናቸው የተባሉ የውጪ ኃይላት፤ አሜሪካና እንግሊዝ ጭምር ሥርአቱን ቀርቶ የንጉሱን ሕይወት እንኳን ሊታደጉ አልፈቀዱም።

የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ሠራዊት ከ1960ዎቹ ንቅናቄ የተቀላቀለዉ በጣም ዘገይቶ ብቻ ሳይሆን ሊነጋጋ ሲል በጨለመበት ሰዓት ላይ ነዉ። ይህም ሊሆን የቻለዉ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ከተቀረጸበት የሕዝባዊ ወገናዊነት የለሽነት አደረጃጀት የተነሳ አብዛኛዉን ጊዜ የወጣበትን ሕዝብ ችግር ከመፍታት የበለጠ፤ ደመወዝ ለሚከፍለዉ መንግስት ወይም የመንግስት መሪ ታማኝነቱን ስለሚገልፅ ነበር። ነገሩን በግልፅ ለማስቀመጥ ያህል መለዮ ለባሹ ብዙም የትምህርት ዝግጅት ስላልነበረዉና አርቆ የማየት ችሎታዉም ከካምፑ ባሻገር እምብዛም ስላልነበረ ወይም ስለማይሆን፤ የአገዛዙ መሪ ከተነካ ሕገ መንግስቱና የአገሪቱ ሉዐላዊነት የመፈራረስ ዕድል ያጋጥማል ከማለትም አልፎ፤ ሰማይና ምድርም ይገለባበጣሉ የሚል ስሜት ሊይዝ የሚችል ኃይል ስለሚሆን ነዉ። “ሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ” የሚለዉን ተረት በግንባር ቀደምትነት ያነገበዉ የመለዮ ለባሹ ክፍል ነዉ ቢባል አጋኖ የተነገረ አይመስለኝም። ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ ኃይል ያለበት ክፍል በተለይም የደህንነትና መለዮ ለባሽ ክፍል ከሕዝባዊ የለዉጥ ፍላጎት ጋር መሄዱ ጨርሶ የለም ባይባልም አዝጋሚ እና ኋላቀር ይሆናል፤ አጋጣሚዉ ከተመቻቸ ግን ወደ ዲሞክራሲያዊ ጎዳና የመሳቡ ዕድል አነስተኛ ቢሆንም

አደረጃጀቱና ቁሳዊ አቅሙ በተሻለ ደረጃ ስለሚገኝ ወደ ሥልጣን ለመቅረብ ፈጣንና የአጥቢያ አርበኛ ባለድል ይሆናል። ስለሆነም የመለዮ ለባሹ ክፍል ከሕዝባዊ የገበሬዎች፣ የተማሪዎችና የተማረዉ የከተሜ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ጋር ከመራመድ ይልቅ ወደ ማፈን፤ ከፍ ሲልም ከማዳፈን ሥራ በላይ ቀጥታ በሕዝብ ልጆች ላይ ይተኩስ እንደነበር የኢትዮጵያ የቅርብ ዓመታት ታሪክ ነዉ። ነገር ግን ከወቅቱ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ሁኔታዎች አስገዳጅነት የተነሳ በተለሳለሰና ለንጉሱ ታማኝነቱን እየገለጸ፤ ደርግ በሦስት እርከን የተከፈለ ከጊዜ አንፃር ረጅም ጊዜ የወሰደና ዘገምተኛ የሚባል አብዮታዊ እርምጃ በመዉሰድ ወደ ሥልጣን የሚያደርገዉን ጉዞ ጀመረ። እነዚህ አዝጋሚ የተባሉ አብዮታዊ እርምጃዎችም፡-

1. ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹን ለመፍታት የቅርብ አዛዦቹን በቁጥጥር ሥር ማዋልና እነዚያን ለማስፈታት የተንቀሳቀሰዉን የበላይ አካል ጨምሮ በቁጥጥር ሥር በማዋል የበታቾቹ ሲጠጡ የከረሙትን ቆሻሻ ዉሃ እስከ ማጠጣት የደረሰ፣
2. የእንዳልካቸዉ መኮንን ካቢኔን ለመታደግና ዕድሜ ለማራዘም በአየር ኃይሉ አባል ኮሎኔል ዓለምዘዉድ ሥር የተቋቋመዉንና የሠራዊቱን ትግል ለማስተባበር፤ በዉነቱ ግን ለማዳፈን የተቋቋመዉን ኮሚቴ በማስወገድ፣ እና

3. ከየካቲት 21፣ 1966 ዓም ጀምሮ መሰባሰብ የጀመረው የእምቢተኛ ወታደሮች ስብስብ ግስጋሴውን ቀጥሎ፤ ሰኔ 3፣ 1966 የተቋቋመዉ የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የሕዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ማቋቋም መቻሉ ከላይ ከተጠቀሰዉ ጋር ተዳምሮ የደርግ የመጀመሪያዉ ጥንስስ ቅርስ ሊባል የሚችል የተደራጀ እርምጃዎች መውሰዱ ናቸዉ።

እዚህ ላይ አንድ ሊታወቅ የሚገባ ነገር ቢኖር በአብዛኛው በትምህርት ቤቶች በተለይም በዩኒቬርሲቲዎች አከባቢ ስንቀሳቀስ የነበረው ፀረ ፊውዳል የትግል እንቅስቃሴ አንድም የንጉሱ ጠባቂ የሚባለው ወታደር መቀላቀሉ ሲሆን በሌላም በኩል በተማረው ክፍል አከባቢ ተወስኖ

የነበረው የትግል እንቅስቃሴ በተለይ ከነቀምቴው የየካቲቱ 1965ቱ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ስብሰባ ዉሳኔ ወደኋላ ላይ አፍ እንጂ ጆሮ በሌላቸው ጉልበተኛ ወታደሮች መነጠቁ ነዉ። ስለሆነም፤ ከየካቲት 66 ጀምሮ ሕዝባዊ ፀረ ፊውዳል ትግሉ ደጋፊና ተቃዋሚ እያፈራ መጥቶ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓም ላይ ከንጉሱ ከሥልጣን መውረድና የደርግ በሥልጣን ላይ መደላደል ጋር የኢትዮጵያዊያን የዴሞክራሲያዊ መንግስት ማቋቋም ሕልም ሌላ ተጨማሪ ትግል ማድረግ እና መስዋዕትነት መክፈል ወደሚጠይቅ ተላለፈ።

በሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተቀጣጠለዉ የ1965/66 የለዉጥ ፍላጎት በውስን መልኩም ቢሆን የሁለት ሕቡዕ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ተሳትፎ ታክሎበት የኃይሌ ሥላሴን መንግስት በመጣል ወታደራዊ ደርግ ብዙም አስቸጋሪ ባልሆነ ሁኔታ ወደ ሥልጣን እንዲያዘግምና መስከረም 2 ቀን 1967 ንጉሱን ከሥልጣን ሊያወርድ ችሏል። የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት ሲል ደርግ በዚያዉ ዓመት ከኤኮኖሚ ጥያቄዎች በመለስ የሚከተሉትን የፖለቲካ እርምጃዎች ወስዷል። የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ታወጀ፤ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ለአንዴና መጨረሻ ጊዜ ግብአተ መሬቱ ተበሰረ፤ የኢትዮጵያ ሪፑብሊክ እንደሚታወጅ ተገለጸ። ነገር ግን ከድጡ ወደ ማጡ ሆነና ደርግ ንጉሱን ከመንበሩ ባስወገድበት ቅፅበት የፀረ ዲሞክራሲ አፈናዉ ጅምር የሆነዉን ሠላማዊ ሰልፍ ማድረግም ሆነ የተቃዉሞ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደማይቻል ክልከላም አወጀ።

ከላይ ጠቆም እንዳደረኩትና ወደ ኋላ ተመልሶም የደርጉ አባላት ተዋጽኦ ቢመረመር ከጦሩ መሀከል ተመልምለው የተላኩት በየክፍለ ጦራቸውም ቢሆን በባህርይያቸዉ ቅቡልነት ያልነበራቸዉ መሀከለኛ መኮንኖች ሲሆኑ፤ ለአቤቱታ ወይም ለተቃዉሞ እንጉሱ ፊት እንዲቀርቡም የተደረገዉ በተለመደዉ አጉል ድፍረታቸዉ እንዲጋፈጡና ንጉሱ የሚወስዱት እርምጃ ቢኖር በዚያዉ ቢያልቅላቸዉም “ዕዳቸዉ ገብስ

ነዉ” ከሚል እሳቤ የተነሳ እንደነበረ በኋላ ላይ እየወጡ ያሉ ማስታወሻዎች ይመሰክራሉ። ሀብታሙ አለባቸዉ የቄሳር እንባ ብሎ በፃፈዉና የደርግ አባላትን ብቃት በገለጸበት መፅሐፉ ገጽ 15 ላይ “ደርጉ በርካታ የበታች ሹሞችን ይዟል፤ የትምህርት ቤት ደጅ ያልረገጡም ሞልተዉበታል” ብሏል። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሰከነ የፖለቲካ ዓላማ አራምደዉ ሕዝብንና አገርን የሚያክል አመራር ለመስጠት ብቃት ይኖራቸዋል ብሎ መጠበቅም ያስቸግራል፤ ችግር እንኳን ቢገጥማቸዉ ለሚቀይሱት አቅጣጫ ምርጫቸዉ የሚያደርጉት ጭካኔን መፈጸም እንደሆነ ከወዲሁ መናገር ይቻላል። ከንጉሱ ቤተ መንግስት አከባቢም ይገጥማቸዋል ተብሎ የተጠበቀው ሁኔታ ግን እንደተጠበቀዉ ሊሆን አልቻለም።

በንፅፅር ሲታይም ከኃይሌ ሥላሴ መውደቅ በኋላ የሕዝቡ ሐሳብ በሁለት የተከፈለ ይመስላል፤ አንድም ሕዝባዊዉ ንቅናቄ ጎልብቶ በወቅቱ ከተከሰተዉ የኑሮ መመሰቃቀል የሚያላቅቀው ከሆነ ምንም ዓይነት ሥርዓት ቢመጣ ለመቀበል ደስታቸዉ ነበር። ሁለተኛም በዓለም ላይ ተራማጅ የሚባሉ አስተሳሰቦች እየሰረጹ የመጡበት ጊዜ በመሆኑና ሕዝቡም እነዚያን ተራማጅ አስተሳሰቦች ይመኝ ስለነበረ እንደደርግ ዓይነቱ የዘቀጠ የፖለቲካ ሥርዓት ይከተላል የሚል ግንዛቤ አልነበረም። እንዲያዉም “ኢትዮጵያዊ ሶሻሊዝም” ሲታወጅ እና <ኢትዮጵያ ትቅደም> የሚባለዉ መፈክር ሲቀነቀን የተሻለች ኢትዮጵያን ለማየት የሚፈጀዉ ጊዜ አጭር እንደሚሆን ተገምቶ ነበር። በተለይም ሰኔ 26 ቀን 1966 አስተባባሪ ኮሚቴዉ መመሪያዬ <ኢትዮጵያ ትቅደም> ነዉ ማለቱና፤ ይህንኑ ቀርቦ ለተሸመደመደዉ ንጉስ ማስረዳቱ ሕዝብን ወደ መስመሩ እየሣበ ነበር ለማለት ይቻላል።

ነገር ግን የደርግ መነሳሳትም ሆነ የ1966 ሕዝባዊ አብዮት ለኢትዮጵያ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሩ ግጥምጥሞሽ አልነበረም። በአንድ በኩል ሕዝቡን በማንኛዉም ስልት መርቶ ለሕዝባዊ ሥልጣን የሚያበቃ ሥር የሰደደ ተቀባይነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ እንዳልነበር ሲታወቅ፤

ተፈጥረዉ ከነበሩት ዉስጥ መኢሶን እና ኢሕአፓ ቢሆኑም፤ በኃይሌ ሥላሴ ሥርዓት ላይ ለመዉሰድ የነደፉት እርምጃ ቢኖርም፤ ከየተመሰረቱበት የዉጭ አገሮች ወደ አገር ቤት ሲመለሱ የጠበቃቸዉ መንግስት ግን ደካማ ጎኑን የሚያዉቁት የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ሳይሆን፤ <ኢትዮጵያ ትቅደም> ከሚለዉ መፈክር ውጭ ምን ዓይነት ሥርዓት ማራመድ እንዳለባቸዉ በቅጡ ያልተረዱና ለመግለፅም የማይመቹ የ120 የወታደሮች ስብስብ ርዕሰ ብሔርነትን ነበር። ስለሆነም የፖለቲካ ድርጅቶቹ በትልማቸው መሠረት የየራሳቸው አባላት ሥልጣን እስከሚይዙ ድረስ አንድም ደርግን ደግፈዉ ወይም ተቃዉመው ሰልፋቸውን መምራት እንደነበረባቸዉ አድርገዉ የተነሳሱ ነበሩ። በኃይሌ ሥለሴ የሥልጣን ዘመን መጨረሻ ላይ፤ ምንም እንኳን የመኢሶን እና ኢሕአፓ የጥናት ቡድኖች አገር ዉስጥ ቢኖሩም፤ ይደረጉ የነበሩ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች በራሳቸዉ በሕቡዕ ድርጅቶቹ ክልል ዉስጥ ከማብቃቱ ላይ ያተኮሩ ከመሆኑ በስተቀር፤ ምንም ዓይነት ከሕዝብ መሀከል ዘልቆ የገባ የድርጅት ትስስር ስላልነበራቸዉ፤ አብዮቱ ሲመጣ ብቻ ሳይሆን አብዮቱ የቆየዉን ያህልም ቆይቶ ሕዝቡን ለወታደራዊ አምባገነንነት አጋልጦ ከመስጠት ሌላ የተሻለ ምርጫ አላቀረቡም። ስለሆነም፤ ከሰለሞናዊ ሥርወ መንግስት ጋር ትስስር አለኝ የሚለዉ የፊዉዳል ሥርአት መዉደቅ ወዲህ ለፓርቲ ፖለቲካ መከሰት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆኑትንና በ1966ቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ዉስጥ የጎላ ሚና የነበራቸዉ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ መኢሶን እና ኢሕአፓን አነሳሳቸዉንና ክስመታቸዉን በተናጠል ለማሳየት እጥራለሁ።

እንደ ሀብታሙ አለባቸው አገላለጽ በርካታ የበታች ሹሞችንና የተወሰኑ መካከለኛ መኮንኖችን የያዘው ደርጉ ለዚያውም አንዳንዶች የትምህርት ቤት ደጅ ያልረገጡ የሞሉበትን ይዞ ከተለያዩ የአገሪቱ የጦር ክፍሎች የተሰባሰበዉ የወታደር ተወካዮች አዲስ አበባ በሚገኘዉ የአራተኛዉ ክፍለ ጦር በመሰባሰብ የከተማዋን መገናኛዎች በቁጥጥር ሥር አዉሎ ያነሳቸዉ ቀጥሎ የተመለከቱት ጥያቄዎች በተወሰኑ ደረጃም ቢሆን የሕዝብን ድጋፍ አስገኝተውለታል። እንደ አንዳርጋቸዉ አሰገድ አገላለፅ

የአራተኛዉ ክፍለ ጦር ስብስብ ያነሳቸዉ አማላይ ጥያቄዎች፤ ዉሎ ሲያድር ግን አሳሳች የሆኑ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ።

- ✓ “የጽሑፍ ነፃነት እንዲኖር፣
- ✓ የስብሰባና የሰላማዊ ሰልፍ ነፃነቶች እንዲፈቀዱ፣
- ✓ የፖለቲካ ፓርቲን የመመስረትና ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመረጣቸዉ አስተዳዳሪዎች እንዲኖሩ፣
- ✓ መሬት ላራሹ እንዲሰጥ፣
- ✓ የሠራተኞችና የአሰሪዎች ሕጎች እንዲሻሻሉ፣
- ✓ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣ ነፃ የትምህርት ዕድል ለሁሉም እንዲሰጥ፣ በገበያ ዋጋ ላይ በቂ ቁጥጥር እንዲደረግ፣
- ✓ የሕዝብን ንብረትና ገንዘብ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የዘረፉት ባለሥልጣኖች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣
- ✓ የወታደርና የሌሎችም ሠራተኞች ደመወዝ ከጊዜዉ የገበያ ሁኔታ ጋር ተነፃፅሮ እንዲጨመር፣
- ✓ ከሠላማዊዉ ሕዝብና ከወታደሩ ክፍል የተዉጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ከሥራ ላይ መዋላቸዉን እንዲቆጣጠር” (አንዳርጋቸዉ፡ 129) የሚሉ ይገኙበታል።

በርግጥም ከፊውዳል የኢትዮጵያ የሕዝቦች እስር ቤት ለመዉጣት አሰፍስፎ ተነስቶ ለነበረ ሕዝብ፤ እነዚህ ጥያቄዎች የወቅቱ ጊዜና ሁኔታ ላይ ሆነዉ ሲመለከቱት ሕዝባዊ ገጽታ የነበራቸዉ፤ ዉሎ አድሮ ግን ቃልና ተግባር ካለመጣጣማቸዉ በስተቀር አማላይ መልዕክቶች እንደነበሩት መካድ አይቻልም። ከጥቂቶች በስተቀር ከመደበኛ ትምህርት ርቀዉ የቆዩና ከወታደራዊ ሳይንስም ቢሆን ቅርበት ያልነበሩት የወታደር አባላት የታጨቁበት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሄደበት አቅጣጫ አርኪ ያልነበረ ቢሆንም፤ ንጉሱን ከሥልጣን ማዉረድ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ የነጋሲ ዘር የሚባለዉ ለመጨረሻ ጊዜ የተቋረጠ መሆኑን ማብሰሩ ብቻውን የፈረንሳይ አርስቶክራቶችን ከሥልጣን ከአስወገደዉ የ1789ኙ የፈረንሳይ አብዮት ያልተናነሰ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ባህሩ ዘዉዴ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው (2007፡ 246) መስከረም 2፣

1967 “በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ በርዝመቱም ሆነ ሀገሪቱ ባየችዉ ለዉጥ ብዙም ወደር የማይገኝለትን የንጉስ ዘመን ማክተም ብቻ የምታመላክት ሳይሆን ሥረ መሠረቱ ከንጉስ ሰለሞንና ንግስት ሳባ ጋር የሚያጣቅሰዉን “ሰለሞናዊ” ሥርወ መንግስት ፍፃሜም ጭምር ነዉ።” ብለዋል። በዚያ ላይ የየካቲት 25 ቀን 1967 የመሬት አዋጅ ታክሎበት የባላባትና የጭሰኛ ግንኙነትን ያቋረጠና የፊዉዳል ሥልተ ምርትን አከርካሪ የሰበረ ስለሆነ ለደርግ አባላት ቅቡልነትን ያጎናፀፈ አንድ ቅርስ (legacy) ሊታይ የሚችል እርምጃ ነዉ።

ከዚሁ ጋር በተጓዳኝነት ሊታይ የሚገባው ነገር ቢኖር ዓለም አቀፍ የአገሮች ሁኔታን በቅርብ ገምግመው የሚያውቁት የፊውዳል ሥርአትን መገላገል ራሱ አንድ ድል መሆኑን አስምረው ገልጸውታል። ምክንያቱም፤ ፊውዳሊዝም ውስጣዊና ውጫዊ አስቸጋሪ ባህርያት ያሉበት በመሆኑ ነው። ከውስጣዊ ሁኔታ አንፃር የፊውዳል ሥርአት የራሱ የሆነ ንጉስ የመሰለ አገር በቀል አስተዳደር ቢኖረውም ለዕውቀትና ዕድገት ክፍት አለመሆኑ እጅግ በጣም አሰቸጋሪ ነው። ከውጫዊ ሁኔታ አንፃር ደግሞ ያለበትን አገር የዝግ አገር ሕዝብ በማድረግ ከዓለም ሕብረተሰብ ድብቅ በማድረግ ይታወቃል። ቢከፈት እንኳን በሃይማኖት ገመድ የተበተበ ይሆናል። ለዚህ ደግሞ የኃይለ ሥላሴን የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴርን ፋይል ቁጥር 146/48ቱን የሥራ ማስታወሻ መመልከቱ በቂ ነው። በዚህ ሚኒስቴር ውስጥ የተሰናዳው ዕቅድ እንደሚያስረዳው በሁሉም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ እንዲከናወኑ የተፈለጉ ሥራዎች ሁሉ ቢያንስ የዲያቆናትን ይሁንታና ወሳኝነት የሚፈልግ አድርጎታል። በሌላም በኩል ከውጫዊ ሁኔታዎች አንፃር ወረራን በመፍራት ወይም በመከላከል ስም ሁሉንም የውጪ አገር ዜጋንና ቴክኖሎጂ አመጣሽ ሥራዎችን በጥርጣሬ ይመለከታል። ስለሆነም፤ የ1967ቱ የኢትዮጵያ የመሬት አዋጅ ከነዚህ የፊውዳል ችግሮች ባይገላግል እንኳን መንገድ ያሳየ ነበር ለማለት ይቻላል።

የካቲት 21 ቀን 1966 ደርግ ያነሳቸዉ ወርቃማ ጥያቄዎች ነበሩ ቢባልም፤

ሰኔ 21 ቀን 1966 ደርግ ነኝ ብሎ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ፤ ምናልባትም ሻለቃ አጥናፉ አባተ የራሱን ሂሳዊ ግምገማ ከማድረጉ በቀር፤ ደርግ እንደ ቡድን ወይም የደርግ አባላት እንደ ግለሰብ የተመረጠዉን የፖለቲካ መስመርን አስመልክቶ ሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርግስን ከመሳሰሉ ወደ ውጪ አገር ኮብላይ የደርግ አባላትና ከኢህአዴግ ቃሊቲ እስር ቤት እስከሚወጡ ድረስ የሆነውን ሁሉ ዞር ብሎ የገመገመ ወይም ለማስታወስ የሞከረ አንድም የደርግ አባል አልነበረም። ስለዚህም፤ ሕዝቡ የፊውዳሉን ሥርዓት ለማስወገድ ከከፈለዉ መስዋዕትነተ የበለጠ፤ የሕዝቡን ጩኸት የቀማዉን ደርግን ለማስወገድና የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑን ለማረጋገጥ የከፈለዉ ተጨማሪ ሁለንትናዊ መስዋዕትነት ሰፊና ጥልቅ ስለሆነ፤ ከላይ የፊዉዳል ሥርአት ከማስወገድ በበለጠ አዲሱን በቦታዉ ላይ ለመገንባት ብዙ መስዋዕትነትን ይጠይቃል ያልኩት ይህንኑ ግምት ዉስጥ በማስገባት ነዉ። ምክንያቱም፤ ለሕዝብ ይገባሉ የተባሉ መብቶች አልተተገበሩም፤ ንጉሱ እንዲያቋቁም የተጠየቀዉ ችግር ፈቺ ኮሚቴም ቢሆን በደርጉም አልተቋቋመም፤ የተቋቋመዉም እንኳን ቢሆን ሽባ ሆኖ የቀረ ነበር። በመሆኑም "የፖለቲካ ፓርቲን የመመስረትና ሕዝቡ በዲሞክራቲክ መንገድ በመረጣቸዉ አስተዳዳሪዎች እንዲኖሩ" የተመኘዉ ምኞት ገና ከሽሉ የጨነገፈ ሲሆን፤ በወታደራዊ ጡንቻ ሥር እንዲቆይ ተደርጓል። ያ ውርስ ዛሬም በ21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ ሳይቀር የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመረጣቸዉ ተወካዮች እንዳይተዳደሩ የሰማይ ያህል እንድርቅ የተደረገው በዚያን ጊዜ በተጣለ መሠረት ላይ ሆኖ እንደሆነ ግልፅ ነው።

ከላይ እንደጠቀስኩት ለደርግ ሥልጣን መደላደል አስተዋጽኦ ከአደረጉት ዉስጥ የካቲት 21 ቀን 1966 ለንጉሱ ያቀረቧቸዉና የሕዝብን ሥነ ልቦና የኮረኮሩበት የፕሮፓጋንዳ ሥራ እና መስከረም 2 ቀን 1967 ንጉሱን ከሥልጣን ማዉረድ፤ ከማውረዱ በዋዜማው የንጉሱ ውሻ በጮማ ሥጋ ሲትጫወት የወሎ ሕዝብ ተርቦ ልጅ የሞተች እናቷን ጡት ሲትጠባ የእንግሊዛዊውን ዮናታን ድንብልብይን ፊልም ማሳየቱ፣ የካቲት 25 ቀን 1967 የመሬት አዋጅና ይህንኑ እንዲያስፈጽሙ ከአስረኛ ክፍል ጀምሮ

ያሉ ወጣት ተማሪዎችን ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ማሰማራቱ ዉስጣዊ ሁኔታዎች ሲሆኑ፤ ዓለም አቀፍ የሶሻሊስት ንቅናቄዎች፣ ብሔራዊ የአርነት ግንባሮች በሰፊዉ መንቀሳቀስና ደርግም ራሱን የዚሁ አካል አድርጎ ማየቱ ዉጫዊ ግፊቶች እገዛ ያደረጉለት ናቸዉ። ሕዝባዊ ንቅናቄዉ ብዙም ባልተረጋጋበት ሁኔታ ዉስጥ እያለ፤ የሱማሊያ ወረራ መከሰትና ይህንኑ ወረራ ለማጠፍ በግዥ የተፈለገዉ የአሜሪካን መንግስት የጦር መሳሪያ ሽያጭ ክልከላ ጉዳይ በእሳቱ ላይ ነዳጅ በመጨመር ለደርግ ማበጥና ማፈንገጥ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አድርጓል።

በሌላም በኩል ለደርግ ተጨማሪ መደላደልን የፈጠረዉ በአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ዉስጥ የታችኛዉ የሕብረተሰብ ክፍል ላለመገዛት ያሳየዉ መነሳሳት ብቻ ሳይሆን ገዥዉ የኃይሌ ሥላሴ መንግስት እራሱ በመፋለሱ ምክንያት እንደቀድሞዉ ለመግዛት አለመቻል ትልቁን ሚና የተጫወተ ነበር። ይህ በኃይል በሚወገዱ ሥርዓቶች ሁሉ ዘንድ የቅርጽ ልዩነት ብቻ ኖሮት ተደጋግሞ የሚታይ ሲሆን፤ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ተደራጅቶ የወጣዉ የንጉሱ መለዮ ለባሽ በወታደራዊ አቋም፣ በዕዝ ሰንሰለት ግንኙነት፣ የራሱ የሆነ የመገናኛ ሰንሰለት ያለዉና ትጥቅንም ከተወሰነ በጄት ጋር ስለነበረዉ፤ የሰሜኑ ከደቡቡ፣ የምስራቁ ከምዕራቡ ጋር የመነጋገርና የመሰሳሰብ ዕድሉ ሰፊ ስለሆነ ቀዳሚ ጉልበት ፈጥሮለታል።

ሌላዉ ደርግን ሣቢ እንዲሆን ያስቻለዉ ምንጩ በወቅቱ በበቂ ሁኔታ ያልተብራራ <የኢትዮጵያ ትቅደም> ዓላማ ጉዳይ ነዉ። ኢትዮጵያዊያን ከነችግሮቿም ቢሆን ኢትዮጵያን የሚወዱ የመኖራቸዉን ያህል፤ ኢትዮጵያን የሚወዱ የሚያስመስሉም እንዳሉ ይታመናል። በርግጠኛነት ይወዳሉ ብሎ መግለፅ የሚያስቸግረዉ ላይኛዉ የገዥዎች ቡድንና ትንሽ ጥሪት የያዙ ሰዎች ወይ ጨርሶ ኢትዮጵያን አይወዱም ወይም ደግሞ የሚወዱት ትንሽ ከፍለዉ ብዙ የትርፍ ትርፍ ማግኘት የሚችሉ ብቻ ሲሆኑ ታችኛው የሕብረተሰብ ክፍል ግን የኢትዮጵያ ሰንድቅ ዓላማ ቀን ሙሉ ሲወጣና ሲወርድ ቢውል ከቆሙበት ቦታ ንቅንቅ የማይሉ ነበር።

ከገዥዎች ወገን ግን እስከዚህ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያን የሚወድ አንድም ሰዉ አልነበረም ወይም የለም ባይባልም እንኳን የአገሪቱ ገዥዎች ኢትዮጵያን የሚወዱት በራሳቸዉ ምኞት ልኬት ብቻ ነበር/ነዉ። የገዥዎቹ ቡድን ኢትዮጵያን የማይወዱ መሆኑ መገለጫው ኢትዮጵያ የምትባል አገር አዳምና ሔዋን ተመልሰው ወደ ምድር ቢመጡ እነሱ ሲፈጠሩ የነበረች አገር እንደዚያው እንደነበረች ሆና እነሱን ባልጠበቀች ነበር እያሉ ሲያሾፉ ይደመጣሉ። ድህነትና መሃይምነትም ባልተንሰራፉባት ነበር ብዬ መናገር ስለፈለኩም ነዉ። ሕዝቡ ግፉን መሸከም ሲያቅተዉና ፊቱን ሲያዞርባቸዉ፤ ንጉስ ኃይለ ሥላሴ ወርደውና በቮክስ መኪና ተጭነው በጉዞ ላይ ሳሉ "ኢትዮጵያ ይህን ያህል በድዬሻለሁ ወይ" ብለው ቀላምደው እንደነበር ተሰምቷል። ውሎ ሲያድርም የኃይሌ ሥላሴን መንግስት በአቆርቃዥነት ሲከስስ የነበረው መንግስቱ ኃይለማሪያምም ሕዝብን በአፈና ሥር ሲገዛ ከቆየ በኋላ ወደ ፍርጠጣው አከባቢ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ወርቅ ተነጥፎለት ፋንዲያ ነዉ ይላል" ብሎ ጋጠወጥ አነጋገር ሰንዝሯል። በርግጠኛነት መናገር የሚቻለዉ ግን እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን ሲገዙ የነበሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወርቅ ያነጠፈ መሪ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ሆዱን ሞልቶ እንዲመገብ ያስቻለ መሪ አለመኖሩን የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ በቂ ምስክር ነው።

<ኢትዮጵያ ትቅደም> የሚለዉና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሕዝብን ከደርግ ዓላማ ጎን እንዲሰለፍ ያደረገዉና ብዙዎች የደርግ አባላት ራሳቸዉ ባልተዘጋጁበት የአብዮት ማዕበል ዉስጥ ገብተዉ ሲናጡ፤ መንግስቱ ኃይለማሪያ እንደመፈክርም አድርጎ በመወርወሩ እፎይታን እንደፈጠረላቸዉ የሚናገሩ የታሪክ ሰዎች አሉ። ነገር ግን <ኢትዮጵያ ትቅደም> የሚለዉ ሐረግ የተቋጨዉ ከሃምሳ ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ ተንሰራፍቶ በቆየዉና ባለማፈርም ንግስናዉን ለልጆቹ ለማስተላለፍ ያልፈለገዉ ንጉስ ዘመን ውስጥ የተፈጠረ ሐረግ ነበር። ኢትዮጵያ ትቅደምን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠረዉ የ ደቅማስ መጽሐፍ ደራሲ የመቶ አለቃ ታምሩ መኮንን በ1962 ነበር። እንደመቶ አለቃ ታምሩ

መኮንን አገላለፅ “ዶቅማስ›› ማለት የአራዳ ልጆች ቁም ነገርን እያዋዙ መልዕክት ለማስተላለፍ ያወጡት ስም ሲሆን ትርጉሙም “መቅሰፍቱ” ማለታቸዉ ነዉ። ወጣቶቹ ቃሉን ከምን እንደወረሱ ያወቀ የለም፤ ብቻ መቅሰፍቱ ለማለት ያወጡለት አማርኛ መሆኑ ተረጋግጧል” ይላል የመቶ አለቃ ታምሩ መኮንን። በተጨማሪም “በሁላችን አእምሮ የሚላወሰዉ <የኢትዮጵያ ትቅደም> የስሜት ነበልባል በለዘብታ እፍ-ፍ-ፍ የሚል ነዉ።” ብሎ ጽፏል። የመቶ አለቃ ታምሩ መኮንን ዶቅማስ “ከሰዉ በላይ ሥልጣን ባለዉ ኃይል ታዝዞ አንድ መንፈስ የሀገሪቱን ባለፀጋዎች እንዲያራቁት የተላከ ነዉ ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምኗል” (ገጽ 5) በማለት በተዘዋዋሪ መንገድ የፀሐፄን ንጉስ ሙሰኛነት ለመግለፅ በተባ ብዕሩ የገለጸበት ነው። እንግዲህ፤ መንግስቱ ኃይለማርያም ከመቶ አለቃ ታምሩ መኮንን ዶቅማስ መጽሐፍ ኮርጆ የተጠቀመበት ኢትዮጵያ ትቅደም መፈክር ቀላል በማይባል ሁኔታ ሕዝቡ ከጎኑ እንዲቆም ዕድል ፈጥሮለታል።

በሌላም በኩል ታህሳስ 12 ቀን 1967 የታወጀው ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም (national democratic revolution program) ለደርግ ሥልጣን ላይ ተደላድሎ መቆየት ተጨማሪ አስተዋጽኦ ያደረገዉ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በዉስጡ የያዘ ስለነበር ነዉ። አንድም የአገሪቱ የዕድገት አቅጣጫ የወቅቱን የፖለቲካ ትኩሳት ወደሚጠይቀው ወደ ሶሻሊዝም የሚያሸጋግር ዲሞክራሲያዊ አብዮት የቀየሰ እንደሆነና በዋናነት ግን ደርግን ሥልጣን ላይ ለማቆየት አቋራጭ መንገድ የዘየደበት መመሪያ ነበር። እንደ ወዝሊጉ መስራችና መሪ ዶ/ር ሰናይ ልኬ የመሳሰሉ ምሁራን በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ንድፍ ላይ መሠረታዊ የሚባል ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን፤ ዶ/ር ሰናይም ለራሱ ዓላማ ስከት ሲል በሁለት ባላ ላይ ተንጠላጥሎ በደርግ ዉስጥና በራሱ ድርጅት ዉስጥ ለተወሰነ ጊዜ ለመንሸራሸር ችሎ ነበር። እንደ ዶክተር ሰናይ ልኬ ምክር ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የፖለቲካ ፓርቲዎችን መቋቋም የሚፈቅድ ስለሆነ፤ “መለዮ ለባሹም የራሱን ድርጅት የማይመሰርቱበት ምክንያት የለም” በማለት ለሻለቃ መንግስቱ ምክር

የሰጠበትና በአደረጃጀትም የቀረበበት ጊዜ ነበር፡፡ እንደ አንዳርጋቸዉ አሰግድ (2002፡ 362) አገላለጽ “የዶ/ር ሰናይ ልኬ ስሌት፤ ሻለቃ መንግስቱ በሚፈጥሩት ድርጅት ዉስጥ የራሱን የወዝሊግ አባሎች በመሰግሰግ <አብዮታዊ ሰደድን> ለመቆጣጠርና እንዲያም ሲል ለሥልጣን ለመቅረብ እችላለሁ የሚል ነበር” ካለ በኋላ በመቀጠል “ሻለቃ መንግስቱም የዋዛ ሰው አልነበሩምና በአንድ ወገን ከወዝሊግ ጋር በመሆን ሰደድን ማጠናከር ሲያያዙ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መረባቸዉን በሠራዊቱና በሹመት ባስጠጉአቸዉ ሹማምንት አከባቢ ዘርግቷል፡፡ ይህም ለጥር 1969ኙ የተራማጆች ህብረት ኮሚቴ በኋላም የኢትዮጵያ ማርክሰዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች ህብረት (ኢማሌዲህ) እስከማቋቋም አደረሳቸዉ፡፡ የኢማሌዲህ መቋቋም የሻለቃ መንግስቱን <ደርግ> የመቧጠጫ ጥፍር አጠናከረ” ይላል አንዳርጋቸዉ አሰግድ፡፡

ምንም እንኳን ከ1967 እስከ 1969 ባለዉ ጊዜ መካከል በተለይም ደርግ ገና በሥልጣኑ ባልተደላደለበት ጊዜ ዉስጥ ሁኔታዎች ለፖለቲካ ድርጅቶች መነሳሳት ማገዙ እና ሊጠቀሱ የሚችሉ ያለፉበት ችግሮች ብዙ ቢሆኑም፤ በዚህ ክፍል ሥር ለማንሳት የተፈለገዉ የደርግን ከ120 የወታደሮች ስብስብ ወደ ፖለቲካ (ፓርቲ) ማቋቋምና ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማሪያምን ደግሞ ማንም ዜጋ አንገቱን ቀና አድርጎ የማያየዉ አምባገነን ያደረገዉን ሁኔታዎች መፈጠሩን ነቅሶ ለማሳየት ብቻ ነዉ፡፡ የደርግ መሪ፣ ርዕሰ ብሔሩ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የኢማሌዲህ ማዕከል፣ የአረንጓዴ ዘመቻ ሰብሳቢ መንግስቱ ኃይለማሪያም ከደርግነት ተነስቶ ወደፊት በምትመሠረተዉና መለዮ ለባሹ ሥልጣኑን ከሕዝብ ለተመረጡ አስተዳዳሪዎች አስረክበዉ ወደየጦር ካምፖቻቸው የማይመለሱበትን ሥልት ያመቻቸለትና የመንግስቱ ኃይለማሪያም ጉዞ ተጠናክሮ የወጣዉ ከዚህ ጊዜ በኋላ ነበር ለማለት ተፈልጎ ነዉ፡፡ ይህ ነዉ እንግዲህ “የፖለቲካ ፓርቲን የመመስረትና ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመረጣቸዉ አስተዳዳሪዎች እንዲኖሩ” የሚለዉ ቅድመ መስከረም 2፣ 1967 ወርቃማ ጥያቄዎች፤ እንደጥያቄም እንደሐሳብም ሕዝቡ እያየ ከእይታ ውጭ እንዲሰወርበት የተደረገዉ፡፡ በሌላ አገላለፅ ያ

ወቅት የፖለቲካ ፓርቲ ምስረታ ጥንስስ ወደ መዳፈን ያመራበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል።

በዚህም አለ በዚያ፤ የደርግ የፀረ ዲሞክራሲያዊነት ገጽታ የጀመረዉ ንጉሱ ከሥልጣን ከመዉረዱ በፊት ሐምሌ 2፣ 1966 ዓም "ለሁኬት ፈጣሪዎች፣ ሥራ ለሚያቆሙና ሰላማዊ ሰልፎችን ለሚያዘጋጁ ሰዎች ከዛሬ ጀምሮ ለሚደረገዉ አሳፋሪ ተግባር የጠነከረ ዕርምጃ የሚወስድ መሆኑን ከገለጸበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ።" በማለት አንዳርጋቸዉ፡ እንደገለፀው፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አስተዳዳሪዎችም፣ አሳሪዎችም፣ ገዳዮችም፣ ሕግም፣ ዳኛም እነሱ ደርጎች ብቻ ሆነዉ ተሰየሙ። ፓርቲዎች በኃይሌ ሥላሴ ሥርአት ዉስጥ ቢጸነሱም በደርግ አገዛዝ ዘመን በሕዝብ መሀከል ስለገቡት የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ አነሳስና ዕድገት ዉስጥ በይፋም ሆነ በሕቡዕ ምን ሚና እንደነበራቸዉና እንዴት እንደ ተዳፈኑ ቀጥሎ ባሉት መስመሮች እንመለከታለን።

ከዚህ አስቀድሞ ግን ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ለመገንባት የፓርቲዎች ሚና፣ ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ዓይነቶችና ተቋማዊ አደረጃጀቶች የተወሰነ ዳሰሳ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደ ሮበርት ሚሼል ገለፃ (2001፡ 297) የፓርቲ ፖለቲካ ጥናትና ትንተና አንድ ራሱን ችሎ የተቋጨ ሳይሆን በማህበራዊ፣ በፍልስፍናዊ፣ ሳይኮሎጂ እና በታሪክ ዲስፒን መሀከል ያርፋል። በማህበራዊ ዘርፉ የሰውን ማህበራዊ ትስስር ሲያገናኝ በሳይኮሎጂ ዘርፉ ደግሞ የሰውን ስሜት የሚኮሮኩሩና ለአንዱ ቡድን ድጋፍን ሲያጎናፅፉ ለሌላው ቅሬታን ማንፀባረቂያ መድረክ ያመቻቻል። መቻቻልን የሚገነዘብ ሥልጡን አካሄድ ከሌለ በስተቀር አጥፊና ጠፊ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚፈጠሩበት ነው።

የፓርቲ ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች፤ ሌሎችም ተቋማት፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ ማህበራዊ ቡድኖች፣ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት፤ ሁሉም የመንግስትና የሕዝብ አገናኝነት ሚናን ይጫወታሉ። ፓርቲዎች የየራሳቸው የፖሊሲ አቅጣጫ፣ የፖለቲካ

ፕሮግራም፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች ኖሮአቸው፤ በዚህ የአገናኝነት ሚና ውስጥ ሲያልፉ ከውስጥና ከውጭ የሚገጥሙአቸው የመተማመንና የጥርጣሬ አመለካከት ችግሮች ይገጥሟቸዋል። ከውስጥም ሆነ ከውጭ እርካታ የሚሰማቸው ሲረኩና ተስፋ ሲጥሉበት በተቃራኒው ግን ዕምነት የማይጥሉበትና ካለፈው አገዛዝ የማይሻል ሆኖ ሲያገኙት ወይም አካሄዱ ዘገምተኛ ሲሆንባቸው በሰላማዊ ትግል ከማውገዝ እስከ በጦር መሳሪያ መፋለም ደረጃ ይደርሳሉ።

በፓርቲ ፖለቲካ እና በፓርቲ ጉዳይ ይኼን ያህል ከተባባልን በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የተሰባሰቡና የተደራጁ እና ተመሳሳይ ዓላማ የሚጋሩ ሰዎች የጋራ ግባቸው ላይ ለመድረስ አባሎቻቸውን ቢያንስ በምክር ቤት ደረጃ ለማስመረጥ ጥረት ያደርጋሉ። አምባገነንነት በሰፈነባቸው ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገሮች ውስጥ መተግበር ይህን ያህል ቀላል ባይሆንም፤ ለዓላማቸው ስኬት ሕዝብን ከውስጥና ከውጭ በዙሪያቸው ያንቀሳቅሳሉ።

የፓርቲ ሥርአት በሁለት ዓይነት፤ የባለብዙ ፓርቲዎች እና የሁለት ፓርቲዎች ሥርአት ተብለው ይከፈላሉ። በአንድ ግለሰብ ወይም በአንድ ቡድን ወይም በአንድ ንጉስ የሚመራ መንግስት ባለአንድ ፓርቲ ተባለ አልተባለ ስለብዝሃነት ወይም ሁለትነት አንስቶ ማውያየቱ ብዙም ፋይዳ ስለሌለው አልፈዋለሁ። በፓርላሜንታዊ እና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር የሚገዙ አገሮች ውስጥ የባለብዙ ፓርቲዎች ሥርአት ይተገብራሉ። የመንግስት ወይም የሥራ አስፈፃሚ አካል አመሰራረታቸውን አብዛኛውን ወይም በተመጣጠነ የመንግስት አመሰራረት ሥርአት ያደርጉታል። በሌላም በኩል በአንዳንድ በሰለጠኑና በኤኮኖሚ በዳበሩ ሀገሮች፤ እንደአሜሪካና እንግሊዝ በመሳሰሉ አገሮች ውስጥ ባለሁለት የፓርቲ አመራር ሥርአት ይጠቀማሉ። የመንግስት ሥልጣንም በሁለቱ ፓርቲዎች ፍርቅርቆሽ ወይም ጥምር መንግስት የመመስረት ልምድ አላቸው። ነገር ግን አንድ ቅንጣት ፓርቲ ባሉባቸው አገሮች ውስጥ አንድም ምርጫ

ባለመኖሩ፤ ቢኖርም ደግሞ ፓርቲውንና መንግስትን በጥምረት የያዙት ስለሚጸኑበት ሥርአቱ አምባገነናዊ ስለሚሆን እንደ አንድ የፓርቲ ሥርአት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። ከዚህ በታች እንደምንመለከተው የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥርአት በቅርፅ የባለብዙ ፓርቲዎች ሥርአት ይምሰል እንጂ ከሚከተሉት አንዱ ሌላውን ጠልፎ ከመጣልና ላለፉት ሰላሳ በላይ ዓመታት ደግሞ የአውራ ፓርቲነት ፈሊጥ የተነሳ የአንድ ቅንጣት ፓርቲ ሥርአት ነው። ተጠቃለሎ ሲታይ ደግሞ ከደርግ አገዛዝ እስከ ብልፅግና ፓርቲ ድረስ ያለው ሥርአት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በማስመሰል የቅንጣት ወይም የአዉራ ፓርተነት ሥርአት ነዉ።

## መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ/መኢሶን

ለፖለቲካ ፓርቲዎች መመስረትም ሆነ ለማንኛዉም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መፈጠር የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች በተሟላ ሁኔታ መኖር አስፈላጊ መሆኑን የመስኩ ባለሙያዎች ፅፈዉ ያስነበቡን መሆኑ ፀሓይ የሞቀዉ ዕዉነት ነዉ። የኢትዮጵያ ዜጎችን ሸብቦ የያዘዉ የፊውዳል አገዛዝ ከከመረበት የግፍ ብዛት የተነሳ፤ ምስኪን ዜጎች በቃን ያሉበት ሁኔታ እየበለጸገ ሲመጣ፤ እንዲሁም በተገኘዉ ጠባብ ቀዳዳ ተጠቅመዉ ለትምህርት ወደ ውጪ አገራት የወጡ ወጣት ዜጎች፤ በተለይም ወደ አሜሪካና አዉሮፓ የሄዱት ወጣቶች ቀስመዉ የሚመለሱት የሌላዉ ዓለም ሕዝቦች በነፃነት መኖርና እየጎለበተ የመጣዉን የፓርቲ ዲሞክራሲ ለመመልከት በመቻላቸዉ፤ እግረ መንገዳቸዉንም ይህ የፓርቲ ፖለቲካ በአገር ቤትም ጭሱ ጨሶ እሳቱ እንዲነድ መሰናዶ ማድረጋቸዉ አልቀረም።

በዚሁ መነሻ ሕብረ ብሔራዊና ሁሉን አቀፍ የአገሪቱ ጉዳይ ላይ የተነጋገረዉና በኢትዮጵያ ደረጃም የመጀመሪያ ነዉ የተባለዉ በውጪ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ሐምሌ 1960 በምዕራብ ጀርመን ሐምቡርግ ከተማ ተሰባስበዉና የመጀመሪያ ጉባኤ አድርገዉ፤ በዚያኑ ወቅት ላይ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ/መኢሶን ተመሠረተ።

ከመኢሶን የመጀመሪያ ጉባኤ ተሳታፊዎችና መስራቾች ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፣ ኃይሌ ፊዳ፣ ዶ/ር ከድር መሀመድ፣ ሂሩይ ተድላ፣ ዶ/ር ተፈራ ሁንዴ፣ ዶ/ር ከበደ መንገሻ፣ ሐጎስ ገብረየሱስ፣ ዳንኤል ታደሰ፣ ግርማ በሻህ እና ዳንኤል አደሬ እንደሚገኙበት አንዳርጋቸዉ አሰግድ ከፃፉት መጽሐፍና ከሌሎችም ሰነዶች ለማወቅ ይቻላል። እዚህ ላይ የመጀመሪያ ጉባኤ በሚባልበት ወቅት እነዚህ ሰዎች የመኢሶንን የመጀመጀሪያ ጉባኤ ማካሄዳቸዉን እንጂ ከዚያ ጊዜ በፊት ጀምሮ በአዉሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ስብስብ ላይ ከ1956 ጀምሮ የፖለቲካ ለውጥ ፍላጎት ስሜት መሠረቱን እየጣለ የመጣ ክስተት ነበር። እነዚያ ተጠቃሾች ምንም እንኳን የፊዉዳል ኢትዮጵያ ልጆች ቢሆኑም በውጪ አገሮች ቆይታቸዉ ወቅት ዓለም አቀፍ የፀረ ቅኝ አገዛዝና በምዕራባዊያን ዘንድ እየጎለበተ የመጣዉ የፓርቲ ዲሞክራሲ መስፋፋት በቡድንም ይሁን በያንዳንዳቸው የተናጠል ሕይወት ዉስጥ የፓርቲ ፖለቲካ አመራር አዎንታዊ ተጽዕኖ ሳያሳርፍባቸዉ እንዳልቀረ መገመት ይቻላል።

ምንም እንኳን በአሜሪካና አዉሮፓ ቆይታ የነበራቸዉ ወጣቶች ያገር ቤቱ ኋላቀር የፊዉዳል የፖለቲካ ስሜት ብዙም ያልተላቀቃቸዉ የዚያ ትዉልድ ወጣቶች በተለይም መኢሶንን የመሠረቱት በ1960 ቢሆንም የድርጊት መርሐ ግብሩን ቀርጸዉ ለማዉጣት ረጅም ጊዜ ፈጅቶባቸዋል። ከጊዜ መሮጥና ከሰዉ የድርጊት መርሐ ግብር ለመቅረፅ መንቀርፈፍ ጋር ሲስተያይ ጉድ የሚያስብል ሆኖ፤ ዳተኛው መኢሶን መርሐ ግብሩን ቀርጾ እያወጣ እያለ የ1965/66 በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ማዕበሎች እንደ ድንገተኛ ጎርፍ ከኋላ በኩል የደረሱበት እንደሆነ ይገለጻል። ቢሆንም ግን በንቅናቄዉ የመጀመሪያ ፕሮግራም ዉስጥ በአገራችን ሥሩን በሰደደ በአንዱ ችግር ላይ በማተኮር መኢሶን "ብሔሮች የራሳቸዉን ዕድል በራሳቸዉ ለመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸዉ መብት የታወቀ ይሆናል" በማለት ያስቀመጠ የመጀመሪያ ድርጅት እሱ እንደነበር ይነገራል።

በዚህም መሠረት የ1965/66 ሕዝባዊ ንቅናቄ ሲጋጋም ብዙ የመኢሶን

መስራቾችና አባላት ወደ አገር ቤት ተመልሰዉ በመምህርነትና በተለያዩ የመንግስት ሥራዎች ላይ ተሰማርተዉ እንደነበረ ይታወቃል። ነገር ግን ከንቅናቄዉ መርሐ ግብር መዘገየት የተነሳ ይሁን፤ አሊያም ከኃይሌ ሥላሴ መንግስት የአፈና መዋቅር ተሸሽገዉ መቆየታቸዉ ሕዝብን ለሥልጣን በማብቃት ሥራ ላይ ወደኋላ እንዲቀሩ ተገድደዋል። ሕዝባዊ እንቅስቃሴዉንም ለመምራት የሚያስችል ጠንካራ የአደረጃጀት ዝግጅትም ብዙ እንዳልነበራቸዉ በኋላ ላይ ከአጋጣማቸዉና መወጣት ካልቻሉት በተለይም ለደርግ ስልታዊ ድጋፍ ብሎ የሄደበት አኳኋን ጠቃሚ እንዳልነበር ብዙ ጸሐፍት ገልጸዋል።

እንግዲህ እንደታክቲክም ይሁን እንደስትራቴጂ መኢሶን የተከተለዉ ለደርግ ስልታዊ ድጋፍ እየሰጡ የትግል ስልት እንዴት እንደአልያዘለት በቀጣይ መስመሮች ማየት ይቻላል። የመኢሶን የትግል ስልት ካልያዘበት ምክንያቶች አንዱ አፋኝ የሆኑ መንግስታት ባሉበት አገሮች ዉስጥ እንደመሳሪያ አድርገዉ የሚጠቀሙበት አንዱና ትልቁ ስልት ሕዝቡ እንዳይማር ወይም እንዳያዉቅ፣ እንዳይነቃነቅ የሚያደርግ ሲሆን የተሻለ የትምህርት እርከን ላይ የደረሱ ዜጎች እንኳን ድንገት ቢያጋጥሙ ወደ ዳር ይወረወራሉ፣ ይታፈናሉ፣ ደብዛብቸዉንም ለማጥፋትና አደገኛ የሚባሉ ዕርምጃዎች ሁሉ ይወስዱባቸዋል። በተጨማሪም ሕዝቡ የሥጋትና የፍርሃት ፖለቲካ እንዲላበስና አንዱ ሲጎዳ ሌላዉ ለኔም አይቀርልኝም ወይም “ጎመን በጤና” በማለት ከትግል እንቅስቃሴ ተቆጥቦና ተሸብቦ ዕድሉን እያማረረ ኑሮዉን እንዲገፋ ስለሚያስገድዱት ነዉ። ነገር ግን መኢሶን ወደ መጨረሻዉ አከባቢ የገዥዉ የኃይሌ ሥላሴ ቡድን ክፋት ሲበዛበት “የሰብአዊ መፍትኄ ኮሚቴ” ብሎ በ1965 ዓም ራሱን በተዘዋዋሪ መንገድ ይፋ አወጥቷል። ይህ ወቅት ግን ኢትዮጵያ ለውጥን አርግዛ የወሊድ ቀኗን እየቆጠረች ያለችበት ጊዜ እንደነበርና እንዳዉም ቀኗን ቆጥራ የጨረሰች ወቅት ላይ ደርሶ ነበር። ይህ ማለት ደግሞ መኢሶን ትግሉን እንደመምራት ቀርቶ ጭራዉን እንኳን ሳይይዝ ከኋላ በመከተል ላይ እንደነበረ ያመለክታል። መኢሶን ሕዝባዊዉን ንቅናቄ ለመምራት የነበረዉ አቅምና ዝግጅት እጅግ አነስተኛ እንደነበር፤ ወይም

ጨርሶም አልነበረም የሚባልበት ደረጃ ላይ ነበር። ሌላዉ ቀርቶ የንቅናቄዉን ሕልውና በመግለፅና ባለመግለፅ መካከል የነበረዉ ክርክር ራሱ ረጅም ጊዜ የፈጀበት ነበር። በተጨማሪም ይኼዉ ንቅናቄ የኃይሌ ሥላሴ መንግስት የፀጥታ ኃይልን ከመጠን በላይ አጋንኖና አግዝፎ ይመለከት እንደነበረና የሚፈራም ስለነበር ትግሉን በስዉር ለመቀጠል የሚልፈልግ ኃይል የሚመስል ዓይነት እንደነበር ይገለፃል።

ይህ እንዳለ ሆኖ የ1966 ሕዝባዊ ንቅናቄ ለሕዝቡም ለመኢሶንም እንግዳ ደራሽ ስለሆነባቸዉ የመንግስት ሥልጣን አያያዝ ላይ ሕዝቡን ከማስተባበር ይልቅ አውሮፓ በነበረበት ወቅት ላይ ሲያነሳዉ ወደነበረዉ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት” ወደ ማቋቋም ያጋደለ ነበር። ኢሕአፓም ቢሆን ይህንኑ ጥያቄ ከመጀመሪያ ጀምሮ ሲያነሳ የነበረ ስለሆነ፤ የሁለቱ የፖለቲካ ማህበራት የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ጥያቄን ለመመለስ አግባቢ አቋም የያዙ ይመስል ነበር። ከዚህ ጋር ሊታሰብ የሚችለዉ የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት የማቋቋም ጥያቄዉ ራሱ ከመነሻዉ የመኢሶን ራሱን ችሎ መንግስት የማቋቋም የአቅም ብቃት አናሳነት እንዳለበት በትክክል ያመለከተ ነበር የሚሉ ታዛቢዎችም ቀላል አይደሉም። ከዚህ ከጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት መፈክር የተነሳ መኢሶን አንድም ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግስት ሆኖ መቋቋሙን ሳያስታዉል ሌላ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት መጠየቁ የራሱን ዓላማ አለማጠናከር ብቻ ሳይሆን እራሱን ጠልፎ በደርግ እግር ሥር እንዲወድቅ ያደረገ አንድ አቢይ ጉዳይ ነበር። ይህ ብቻም አይደለም፤ መስከረም 2/1967 ዓም ንጉሱን ከሥልጣን እንዳወረደ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማፈን መግለጫ በመስጠት የአፈና ዕርምጃ ከወሰደው ደርግ ጋር እንዴት አድርጎ በስልታዊ ድጋፍ ለመስራት እንዳቀደ ሲታሰብ አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል።

በሌላም በኩል መኢሶን የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ጥያቄዉን ቀጥሎበትም ቢሆን፤ የደርግን መሠረት ለመሸርሸር የመንግስት መዋቅርን ሁሉ ባሉት አባላቱ ለመሙላት ያደረገዉ ጥረት

አልተሳካለትም፤ ግን ሕልሙ ቀላል አልነበረም። ተስፋዬ መኮንን ይድረስ ለባለታሪኩ ብሎ በፃፈዉ መፅሐፍ ገጽ 196 ላይ "ከዚህም ቀደም ሲል ስለመኖሩ የማይታወቀዉ መኢሶን በአጭር ጊዜ ዉስጥ በኢትዮጵያ መንግስት ቢሮክራሲያዊ መዋቅር ዉስጥ ለመግባትና ቁልፍ የፖለቲካ አመራር ቦታን በመያዝ፤ በደብዳቤና በስልክ ትዕዛዝ በመስጠት ቁልፍ የሥራ ቦታዎችን በአባላቱ አስያዘ" ብሏል። ነገር ግን ምንም ያህል አባላቱን በመንግስት ቢሮክራሲ ዉስጥ ቢሰገስግም ወደ ሥልጣን ለመቅረብ ያደርግ በነበረዉ እንቅስቃሴ ዉስጥ አሰስ ገሰሱንም ሁሉ ስለሰበሰበ፤ ለሥልጣን የሚያበቁት እየመሰለዉ ያደረገዉ እንቅስቃሴ ገና ከመጀመሪያዉ ምስረታው ጀምሮ ከሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች እያፈገፈገ ከመጣዉና እንግዳ ደራሹ ደርግ ጋር እንዲቃቃርና እንዲንገዳገድ አስገድዶት እንደነበር ሊያዉቅ የቻለዉ በጣም ዘገይቶ ነበር።

በ1966/67 ከተጠናወተው የመንገዳገድ ጉዞ ብዙም ሳያንሰራራና በሕዝብ ዉስጥ መሠረቱን ሳይጥል የደርግን የቀይ ሽብር ተልዕኮ ለመፈጸም የተገደደዉ መኢሶን እራሱም በይፋና በድብቁ የደርጉ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኖ በ1969 አከተመለት። በተለይም በመሰሪና ክህደት አካሄዱ የሚታወቀው ተስፋዬ መኮንን ከላይ በተመለከተዉ መፅሐፉ ላይ እንዳሰፈረዉ ‹‹በቀዉጢዉ ቀን ለአንድ ሰዓት ቆመዉ የማይዋጉለትን አድርባዮችን መሰብሰብን ሥራዬ ብሎ የተያያዘዉ›› መኢሶን የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ አንዱን ምዕራፍ ለውድቀት ዳረገ በማለት ተችቶታል። ሆኖም ግን ተስፋዬ መኮንን ራሱ ማሌሪድን እንደ ትንሽ ቆሎ ይዞ ወደ ደርጉ አሻሮ ሰደድ የተጠጋ እንጂ ይህንን ያህል መኢሶንን የሚያስተች አስተዋጽኦ አልነበረውም።

አመራር አባሉ አበራ የማነአብ በ1984 የሠላም ኮንፈረንስ ላይ ለመገኘት አዲስ አበባ መጥቶ በወያኔ ባለሥልጣናት ለረጅም ዓመታት ታስሮ ከመውጣቱ በስተቀር፤ ይህ መጽሐፍ ለ2ኛ ጊዜ ከመታተሙ በፊት በተለይ ከመጋቢት 2010 ጀምሮ ከተፈጠረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ ጋር

ሌሎች ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አገር ቤት ሲመለሱ መኢሶን (መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ) እንኳን ድርጅትን ስሙንም በቅርስነት ይዞ ወደ አገር ቤት የተመለሰ ግለሰብ አባል አልተከሰተም። በአገር ቤት የቀሩና የደርግን እስራትና የተለያዩ ሰቀቆ የቀመሱ የመኢሶን አባላት ግን በተለይ ከ1981 በኋላ የተሻለ የፖለቲካ አማራጭ ለሕዝብ ያቀረቡና ቀላል የማይባል መስዋዕትነትን የከፈሉ እንዳሉ የማይካድ ነው።

## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ/ኢሕአፓ

የኢትዮጵያ አየር መንገድን አይሮፕላንን ጠልፎ ወደ ሱዳን የገባዉና በብርሃነ መስቀል ረዳ ይመራ የነበረዉ ቡድን ወደ አልጀሪያ አቅንቶ የአልጅሪያ ቡድን በመባል ራሱን አስተዋውቆ የፖለቲካ ድርጅትነቱን መሠረት ጥሏል። በሐምሌ ወር 1960 በሐምቡርግ ከተማ የተመሠረተዉ መኢሶንም የአባላቱን ቁጥር ለማሳዳግም ሆነ የትግል አድማሱን ለማስፋት እነዚያን የአልጀርስ ቡድን ለማግኘት ልዑኩን ወደ አልጀሪያ ይልክ እንደነበር አንዳርጋቸዉ አሰግድ ቢገልፅም፤ ነገር ግን እስከ 1964ቱ የፓርሱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጉባኤ ድረስ ማለት ነዉ፤ መኢሶን ስለመኖሩ አልጀሪያ ለሚገኙት ወጣቶች የተገለጸ ነገር እንዳልነበርና እነሱም በተራቸዉ ስለመኢሶን የሚያዉቁት ነገር አለመኖሩን የሚገልጸዉ ተስፋዬ መኮንን፤ በሌላም በኩል ይላል "… የመኢሶን መሪ የነበረዉ ኃይሌ ፊዳ ኢሕአፓን ከምንመስርተዉ ዉስጥ አልጀሪያ የነበሩትን ተመላልሶ በመገናኘት ካደረጋቸዉ የሐሳብ ልውውጦች … ለመረዳት መቻሉ ይገመታል" (ገጽ 92) በማለት ከግምት ያላለፈ መረጃ ሰጥቷል። በ1960 መኢሶን ስለመመስረቱ ከሰሚ ሰሚ ሰማሁ የሚለዉ ተስፋዬ መኮንን እነሱ ግን በ1964 በበርሊን ከተማ ኢሕአፓን መስርተዉ በ1965 ደግሞ በተከታታይ የተሰባሰቡት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጠቅላላ ጊዜያቸዉን ለዚያ ድርጅት [ኢሕአፓ] መጠናከር ያዋሉ መሆኑን ገልጿል። ምንም እንኳን ተስፋዬ መኮንን ኢሕአፓ የተመሰረተዉ በ1964 በርሊን ላይ ነበር ብልም የኢሕአፓ መስራች ጥንስስ የተነሳዉ በ1963 ከአልጀሪያዉ ቡድን Revolutionary Organization for the

Liberazation of Ethiopia/ROLE ከተሰኘ የፖለቲካ ቡድን እንደነበረ ሌሎች ማስረጃዎች ጨምረዉ ያመለክታሉ። ተስፋዬ መኮንንም ሆነ ሌሎች ግለሰቦች የመኢሶንን የምስረታ ጊዜ በትክክል ባይገልጹም፤ እንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ ሕልውና መካካድ የኢትዮጵያዊያን በተለይም የሐበሾቹ ሽፍጥ ስለሆነ ብዙም ላያስገርም ይችላል።

የኢሕአፓ ዓላማ ‹‹የብሔሮች ራስን በራስ ማስተዳደር እስከመገንጠል ድረስ መቀበል›› እና የሽግግር አካል የሚመስለውን በሕቡዕ ‹‹ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ›› አማካይነት ‹‹ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት›› አቋቁሞ በዚህ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አማካይነት ‹የመሬት ላራሹን› አዋጅ መተግበር ይገባናል የሚል ሲሆን፤ ይህንን ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የትግል ስልቱም የፊዉዳል ሥርአቱን የሚያስወግድ የትጥቅ ትግል አሁኑኑ መጀመር አለበት የሚል ነበር። እዚህ ላይ ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎው የሚቋቋመው በትጥቅ ትግሉ ነፃ በወጡት አከባቢዎች ነው።

ኢሕአፓ በ1964 በበርሊን ከተመሰረተ በኋላ ንጉሱን የማስወገድ ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የፓርቲዉን የሥራ አካላት በሦስት መንገዶች እንዳሰማራና የመጀመሪያዉ የፓርቲዉ አካል ቀድሞዉኑ በአገር ቤት የነበረና የማደራጀት ተግባሩን በስፋት እንዲያያዝ፣ ሁለተኛዉ የፓርቲዉ አካል በውጪ አገሮች ሆኖ የዲፕሎማሲ ሥራዉን እንዲያከናዉንና ሦስተኛዉ የፓርቲዉ አካል በወታደራዊ ክህሎት ሰልጥኖና ታጥቆ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ዉስጥ በመሰማራት የፖለቲካ፣ የፕሮፓጋንዳ፣ የድርጅታዊና የወታደራዊ ሁሉ አቀፍ የትግል ተልዕኮ የተሰጠዉ ክፍል እንደነበረ ተገልጿል።

ነገር ግን፤ በመጀመሪያ ደረጃ በ1964 የተመሰረተዉ ኢሕአፓ በ1965 ላይ ‹‹በአገር ቤት የነበሩ›› አባላቱ ሲል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም ከአዲስ አበባ ሕዝብ ቁጥር አንፃር (ለዚያዉም አገር ቤት ዉስጥ አባላት ነበሩ ከተባለ) የአባላቱ ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም ለማለት ይቻላል። ሌላዉ በአጠቃላይ በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የተደራጁ የተማሪዎች ማህበሮች፤ በተለይም ከነዚሁ የመነጨት

የመኢሶንና የኢሕአፓ አባላት እንታገላለን ብለዉ የሚንቀሳቅሱት የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ሆኖ ሳለ፤ ያ መንግስት ደግሞ በተለይ በ1965 በተዳከመበት ደረጃ ላይ እያለ ኢህአፓ በቂ መረጃ ሳይዝ ወይም ከነበረበት ሁኔታ አንፃር የነበረዉን ወቅታዊ ሁኔታ በመገምገም የትግል ስልት መቀየስ ሲገባው፤ ያንን አለማድረግና ሰልጣኝ አባላትን መልምሎ ለወታደራዊ ክህሎት ሥልጠና ወደ ሶሪያ መላክ መሠረታዊ የመነሻ ሐሳብ ድክመት በግልፅ ይታይበት እንደነበረበት እንረዳለን። ምክንያቱም "ኢትዮጵያ በ1960ዎቹ የነበረችበት ሁኔታ ከብዙ የኤኮኖሚ ውጥረት የተነሳ ወደ መለስተኛ ዝቅጠት እየተጓዘች የነበረች" እና ሌላዉ ቢቀር አገር ዉስጥ ያለዉ እንቅስቃሴ ለውጥ አፋፍ ላይ መድረሱን ግንዛቤ መወሰድ ነበረበት። በሌላም በኩል የኢሕአፓ ሁሉ አቀፍ ተልዕኮ የተሰጠዉ ታጣቂ ክፍል ሶሪያ ዉስጥ በፍልስጤም ኃይሎች ሰልጥኖ የ1965 ሕዝባዊ ንቅናቄ ተጋግሞ፤ መስከረም 2፣ 1967 ንጉሱን ከሥልጣን ሲያስወግድ፤ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ቢያስቸግርና የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የፖለቲካ አቅጣጫ ጥርት ብሎ ባይታወቅም፤ ነገር ግን አንድ የሚታወቅ ነገር ቢኖር ግን የነጋሲ ዘር ከኢትዮጵያ ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተወግዶ ሌላ ኃይል ሥልጣን የያዘበት ወቅት ላይ ደርሶ እንደሆነ ዓለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎች ተቀባብለው ያወሩትን ወሬ በማንኛውም ክፍልና ቦታ ላይ የሚገኝ የኢህአፓ አመራር ለማወቅ የግድ ሰይጣንን መቀለብ የሚያስፈልግ አልነበረም።

ለማንኛዉም የኢህአፓ ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገዉ ግስጋሴ የተመሰቃቀለ ቢሆንም፤ የኢሕአፓ ታጣቂ አካል ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለመቀላቀል ግስጋሴ በሚያደርግበት ወቅት ላይ ከሁለት አቅጣጫዎች ችግር ገጥሞታል። በመጀመሪያ የኃይሌ ሥላሴ የአገዛዝ ሥርዓት በ1967 ተወግዶ ደርግ ሥልጣን ይዟል። በተከታይም ከኃይሌ ሥላሴ መንግስት ማክተም በኋላ ሊኖር ስለሚችለዉ መንግስት ከአዉሮፓ ጀምሮ ከኢሕአፓ ጋር ተቃርኖ ዉስጥ የገባዉ መኢሶን፤ ከደርግ ጋር ጉድኘት ፈጥሮ ጠብቆታል። በ"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አሁኑኑ" ምትክ በ"ነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ምስረታ ጥያቄ ላይ ጫፍና ጫፍ የሆኑት መኢሶን እና ኢሕአፓ የተፋጠጡበት ጊዜም እንደነበረ ይታወቃል። ከአብዮቱ ፍንዳታ

በቀጠለም ሌላዉ የተቃርኖ አጥንት መኢሶን ደርግ ያወጀዉ የመሬት አዋጅ ሕዝባዊ ነዉ ሲል በጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ አማካይነት የሚታወጅ ነው የሚለው ኢሕአፓ ግን የፋሽስት ፅልመት የነገሰበትና አብዮቱ የተቀለበሰበት ዕለት ነዉ በማለት የኮነነበት ጊዜ ላይ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ በኢሕአፓ እሳቤ መሠረት በጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ አማካይነት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ተቋቁሞ፤ በዚህ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አማካይነት የመሬት ላራሹ አዋጅ መዉጣት ነበረበትና ነዉ ይላል። በሌላም በኩል በአገር ቤት የሚገኘዉ ኢሕአፓ ከደርግና መኢሶን ጋር ያደረገዉ መላተም አልበቃ ብሎ፤ ኢሕአፓ ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ መሃል አገር በሚያደርገዉ ግስጋሴ ዉስጥ የኤርትራ ነፃነት ግንባር/ጀበሃና ተጋድሎ ሀርነት ትግራይ/ተሀት ጋር በኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት የመርህ ጥያቄ ላይ አቋም እንዲወስድ ያስገደዱት ዓይነት ችግር ለኢህአፓ በቀላሉ ሊያልፉት የሚችሉት እንቅፋት አልነበረም።

ሶሪያ ዉስጥ ሥልጠናዉን ጨርሶ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ወደ ደቡብ የመን በመሄድ በፈጣን ጀልባ ተሳፍሮ በሱዳን ጠረፍ በኩል የገባዉ የኢሕአፓ ታጣቂ አካል በኤርትራ በረሃዎች ዉስጥ ምንም የቋጠረዉ የድርጅት ሕዋስ ሳይኖር በበረሃ ንዳድ የሞቱ ሁለት አባላቱን (ቢንያም አዳነ እና መሀመድ (የአባ ጅፋር እህት ልጅ) ቀብሮ የተረፉትን በመያዝ፤ በ1953 ዓም በተቋቋመዉና መሠረት የያዘዉ የኤርትራ ነፃ አዉጪ ግንባር ቁጥጥር ሥር ወደነበረዉ የሳህል በረሃ ገቡ። በዚህ ቦታ የገጠማቸዉ ሁለቱ ፈተናዎች የሳህል በረሃን ንዳድ መቋቋም አለመቻልና የኤርትራን ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ሥር መላቀቅ ከመርህ አንፃር መቀበል፤ ካልሆነም መጥፊያቸዉ እንደሆነ መቀበል (ሁለቱን የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ ችግሮችን) መቋቋምና መልስ መስጠት ነበረባቸዉ። ያራመደዉ የፖለቲካ ዓላማ ምን ይሁን ምን ገና ለገና ወደ ትግል ዓለም ሳይገባ የኢሕአፓ አባላት እንዲከፍሉት የተገደዱት መስዋዕትነት በጣም አሳዛኝና ገና የትግል ጅምር ላይ ላለ ድርጅት እጅግ ፈታኝ ነበር። በተለይም የኤርትራ ግዛት ሕዝብን ባካተተ መልኩ የሚታገሉለት ትግል ጅምር ላይ ከኢኤልኤፍ የገጠማቸዉ ፈተና ሊጋፉት ከሚሄዱበት የጠላት ጎራ ጋር ሲነፃፀር

በከፍተኛ ደረጃ የሚያዳክማቸዉ ነበር፡፡

ሌላዉ የ1965/66 የኢሕአፓ ችግር ከላይ ያስቀምጥኳቸዉ ሦስቱ አካላቶቹ ያለመናበብ ነበር፡፡ ሦስቱም አካላት የተመሠረቱት አፄ ኃይሌ ሥላሴ በሥልጣን እያለ ነበር፡፡ የንጉሱ ሥልጣን እየተዳከመ ሲሄድና እስከነ አካቴዉም በ1967 ሲንኮታኮት፤ በተለይ አገር ቤት ነበረ የተባለዉ የኢህአፓ አስኳል ከኢትዮጵያ ውጪ ለነበሩት ሁለቱ አካላት፤ በተለይም ደግሞ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ከነበቂ ምክንያት ማወቅ የነበረበት ታጣቂዉ አካል ከሶሪያ ሰልጥኖ፣ የመን ድረስ ተጓጉዞ፣ በሱዳን አድርጎ፣ ኤርትራ በረሃ እስከሚገባና በረሃማዉ ተፈጥሮና ጀብሃ ሠራሽ ችግሮች እስኪገጥሙት ድረስ ምንም መረጃ አልነበረዉም ማለት ድርጅቱ ለትግል በሚያደርገዉ እንቅስቃሴ ላይ ቀላል የማይባል ሳንካ ፈጥሮበታል፡፡

የኤርትራ ነፃነት ግንባር (ጀብሃ) ለኤርትራ ነፃነት ትግል ማድረግ የጀመረዉ በ1953 ሆኖ ሳለ፤ ከአስር ዓመት በኋላ የተመሠረተዉ ኢሕአፓ ከጀብሃ የሚፈልገዉንና ለጀብሃ የሚሰጠዉን የፖለቲካ ፋይዳ በወጉ ሳይረዱ የጀብሃን ድጋፍ አገኛለሁ ብሎ የኤርትራን በረሃ ለማቋረጥ ጉዞ መጀመር፤ የሦስቱ የኢሕአፓ አካላት ጨርሶ መረጃ አልተለዋወጡም፤ ወይም መረጃዉ የሚገኘዉ በአንድ ሰዉ እጅ ወይም በጥቂት ግለሰቦች እጅ ለዚያም ለኤርትራ ቡድን ቅድሚያ ተልዕኮ በተሰጣቸዉ ሰዎች እጅ እንደነበረ ያሳያል፡፡ ለምሳሌም ያህል “ብርሃነ መስቀል ረዳ በነሓሴ 1964 … በኤርትራ ተማሪዎች አጠቃላይ ማህበር 2ኛ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ያስወሰነዉ አንዱ “የኢትዮጵያ ተማሪዎችና አብዮታዊ ምሁራን የኤርትራ ሕዝብን ትግልና የነፃ መንግስት የማቋቋም ትግልን ሙሉ በሙሉ የሚደግፉት መሆናቸዉን” (ገፅ 98) ተናግሮ እንደነበረ፤ አንዳርጋቸዉ አሰግድ በመፅሐፉ ላይ ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ተስፋዬ መኮንን እራሱ እንደገለጸዉ “በኢኤልኤፍ አመራርና በእነአቶ ኢሳያስ መሀከል ከላይ ከተገለጡት ከስልትና የአቀራረብ ልዩነት ሌላ የግብ ጉዳይ በሆነዉ በኤርትራ መገንጠል ጥያቄ ላይ ልዩነት አልነበረም” (ገፅ 113) ሲል በግልጽ አስቀምጧል፡፡ አምባገነንና ጨቋኝ የሆኑ መንግስታትን ለመፋለም

የተደራጀ አንድ የፖለቲካ አካል ቀርቶ የግል ጉዞ ለማድረግ የሚነሳሳ ግለሰብ እንኳን የመረጃን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ሳይረዳ ወይም በቂ የሆነ መረጃ ሳያገኝ ጉዞ ማድረጉ ተገቢ እንዳልነበርና ኢሕአፓ ተሳስቶ የአባላቱን ሕይወት ብሎም ዘላቂ ትግሉን ለጀብሃ/ሻዕቢያ አሳልፎ መስጠቱ ያሳዝናል። ላቅ ሲልም ለኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ስርፀትም የዉድቀት ምሳሌ ሆኗል።

ለማንኛዉም ኤርትራ የሚባል ምድር ለስድሳ ዓመታት በጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ሥር፣ ለአስር ዓመታት ደግሞ በእንግሊዝ ወታደራዊ የበላይ ጠባቂነት አስተዳደር ሥር የቆየች ግዛት ሆና ከአዉሮፓ ቅኝ ገዥዎች ያንን ዓይነት ፖለቲካ ተስተምረዉ መልሰዉ በአፍሪካዊዉ ኢሕአፓ ላይ መስራታቸዉ ፖለቲካን በየዋህነት መስራት የሚቻል ቢሆንም የዋህነቱ የብዙ ሰዉ ሕይወትን እስከ መገበር መሆን እንዳልነበረበት ኢሕአፓን ያጋጠመዉ ችግር ለሌላዉ ማስጠንቀቂያ ደወል ሊሆን  የሚችል ነዉ። በጀብሃም ሆነ በሻዕቢያ አስተያየት “ኤርትራ ቀድሞዉኑ ከኢትዮጵያ ጋር ትስስር ያልነበረዉና በሌላም በኩል በዉጫሌ ዉል መሠረት ምኒልክ ኤርትራን ለጣሊያን የሸጠ ስለሆነ፤ የኤርትራ ነፃነት ትግል ከተጀመረ በኋላ እንደገና ጠቅልሎ ለመያዝ መሞከር፤ ሌላ የቅኝ መግዛት እሳቤ ስለሆነ ለኤርትራ ነፃነት ይገባታል ብለዉ በረሃ ገብተዉ ትግል የጀመሩ መሆናቸዉን የኢሕአፓ ሰዎች ገና አዉሮፓ ሳሉ የሚያዉቁት ወይም ሊያዉቁት የሚገባ ጉዳይ ነበር።

እንግዲህ ኢሕአፓ ከኤርትራ በረሃ የወጣዉ ቀደም ሲል የሚያዉቀዉም ሆነ የማያዉቀዉ አባሉ፤ የኤርትራ ጉዳይን አስመልክቶ ሊታጠፍ የማይችል ግዴታን፤ ማለትም የኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት ንድፈ ሐሳብ ዕዉቅናን በመስጠትና በመቀበል ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ ትግራይ ምድር ይገባል። ይህ ጉዞ ለኢሕአፓ የኤርትራን ምድር እንደ ኢትዮጵያ ምድር ቆጥሮ መርገጥ ራሱ ሚያዚያ ወር 1967 ላይ የመጨረሻው ሳይሆንም አልቀረም። ይህ ታጣቂ አካል ትግራይ ግዛት አሲምባ ሲገባ በመሳሪያ ኃይልም ሆነ በሞራል የላሸቀ ከመሆኑም በላይ፤

በቡሃ ላይ ቆረቆር እንደሚባለዉ በብርሃነ መስቀል ረዳ አምባገነናዊ ዉሳኔዎች ምክንያት ሰፊ አለመግባባቶች በአባላቱ መሀከል ተፈጥሮ እንደነበረ ከተስፋዬ መኮንን መጽሐፍ ለማወቅ ይቻላል። የሐሳብ አለመግባባቱ እየሰፋ በመምጣቱ ምክንያት የብርሃነ መስቀል ረዳ ቡድን አባላት እንቅልፍ እንደተኙ፤ ጫና የበዛባቸዉ የኢሕአፓ ታጣቂ አካል አባላት (እነ ተስፋዬ መኮንን) በትግራይ ግዛት ዛላ አንበሳ በሚባለዉ በኩል ሌሊት ተለይቷአቸዉ በአስመራ አድርገዉ ወደ አዲስ አበባ ማቅናታቸዉና ለወታደራዊዉ መንግስት (ደርግ) እጅ መስጠታቸዉ ይታወቃል።

ከዛላ አንበሳ በኋላ ለደርግ እጅ የሰጡት የኢሕአፓ አባላት ተቀንሰዉ፤ ቀደም ሲል ከ1964 ጀምሮ የቋጠረዉን የትጥቅ ትግሉን ለማስቀጠል ዓላማ የነበራቸዉ ሌሎች አባላት በሁለት አቅጣጫ በመክፈል በገጠርና በከተማ እያፈራረቁ በተለይ በከተማ ዉስጥ በተጠናከረ ሁኔታ የትጥቅ ትግሉን ማቀጣጠሉን እናያለን። በከተማ የነበረዉ የኢሕአፓ የትጥቅ ትግል ‹ደርግስት› ወይም ‹ፊድስት› ናቸዉ በሚላቸዉ የመኢሶን አባላት ላይ በገዳይ ቡድኖቹ አማካይነት ዕርምጃ መዉሰድ መጀመርና ለዚህም ‹ነጭ ሽበርተኛ› የሚል ስም እንዳሰጠዉ ታሪክ የመዘገበዉ ነዉ። (ስለቀይ እና ነጭ ሽብሮቹ ቀጥሎ ባለው አርእስት እናያለን)

ኢሕአፓ የትግል ስልቱን ወደ ከተማ ባዞረበት ጊዜ የሥልጠናና የቁስለኛዉ ማግለያ አምባ አድርጎት የተቀመጠዉ የአሲምባዉ ቡድን ተግባር አልባ ሆኖ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ የተደረገ ሲሆን፤ አስከፊነቱ ደግሞ የአሲምባዉ ቡድን ተግባር አልባ ሆኖ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን፤ የሻዕቢያን ዓላማ ያለማወላወል የተቀበለዉና የራሱም ዓላማ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ የትግራይ ሪፑብሊክን ለመመስረት ላለመዉ ለተጋድሎ ሀርነት ትግራይ (ተሀት) በኋላ ላይ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ/ማሌሊት አማካይነት ወደ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት ለተሸጋገረዉ ቡድን ጥቃት መጋለጡ ነዉ። በዚህም የተነሳ “የኢሕአፓ ጦር በትግራይ ላይ ተመትቶ ብትንትኑ ይወጣል። … ከፊሉ በኤርትራ በኩል አድርጎ ለስደት ወደ ውጪ

ይወጣል። ከፊሉ ወደ ሰሜን ጎንደር ያመራል። ከፊሉ ወደ ወሎ ይገባል። ወደ ወሎ የገባዉ በገበሬዎች ከበባ ተይዞ ለደርግ ተሰጠ። ወሎን ተሻግሮ ወደ ሸዋ የገባዉ መሪዉን ብርሃነ መስቀል ረዳን ጨምሮ፤ በደርግ ቁጥጥር ሥር ውለዉ መገደላቸዉ ይገለፃል።" ይላል ተስፋዬ መኮንን።

በጣም አሳዛኙ ግን በነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ ጣር ዉስጥ የነበረዉ የኢሕአፓ ጦር እዚያዉ አሲምባ ተራራ ዉስጥ ከከተማ የደርግ ቀይ ሽብር ሸሽተዉ የመጡትንና የኢሕአፓን ዉስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲ ጥንካሬ የሞገቱት ወጣት አባላት ‹‹አንጃ ፈጠራችሁ በመባል ቁም ስቅላቸዉን እንዲያዩና እንዲገደሉም መደረጋቸዉን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ <u>የነፃነት ጎህ ሲቀድ</u>፤ በሚለዉ መፅሐፍ ገጽ 7 ላይ "በወታደራዊ ልምምድ ላይ በነበርንበት ጊዜም የልምምዱ ቦታ አከባቢ በሰራዊቱ የደህንነት አባላት የሚታዘዝ እስር ቤት እንደነበረ ሰማሁ። በዚህ እስር ቤት በተለያየ ምክንያት የታሰሩ የሰራዊቱ አባሎች እንደነበሩና በእነኚህ እስረኞች ላይ ሰቆቃ ይደርስ እንደነበር ስንሰማ በብዙዎቻችን ላይ በተለይ ከከተማ በመጣነዉ አባላት ላይ ከፍተኛ ግራ መጋባት ተፈጠረ።" በማለት አምርሮ ገልጿል።

ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በፀረ ደርግ አቋሙ ለመንገዳገድ የቃጣዉ የኢህአፓ ቡድን በሕወሓት ተገፍቶ ጎንደር ሲገባ፤ እሱም ከጊዜያት በኋላ ተሀት/ሕወሓት ሲያባርረዉ ጎንደር አርማጨሆ በረሃ ገብቶ የመሞቻ ቀኑን ሲጠብቅ፤ ለጊዜዉ የማን ዘዴ እንደሆነ ባይታወቅም፤ በሕዳር ወር 1972 ስብሰባ ላይ ተቀመጦ ለነበረዉ የሕወሓት ማዕካላዊ ኮሚቴ እጁን በቡድን ሰጥቷል። በዚያዉም ከቀድሞዉ ኢሕአፓ ይልቅ አዲስ ስም ‹የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ›/ኢህዲን በሚል ስም ሕወሓትን ተቀላቅሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር/ኢህአዴግ የተባለዉን ጃንጥላ (ግንባር) በ1979 መስርተዋል። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የብአዴን/ኢህዲን 35ኛ የምስረታ በዓል ለማክበር መግለጫዎች በሚሰጡበት ጊዜ ሰንድቅ የተሰኘ የግል ጋዜጣ በ11ኛ ዓመት ቁጥር 527 ረቡዕ ጥቅምት 03፣ 2008 ዕትሙ ይዞ የወጣዉ

በማሳጠር እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

መግለጫዉ የቀረበዉ ታጋይ ሃባር (ተሾመ እሼቱ) ከሚባል የቀድሞ ኢሕአፓ ለአዲስ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ አስተሳሰብ የተሰለፉ መሆኑን የጋዜጣዉ ዘጋቢ ገልጿል። “ከኢሕአፓ መፈራረስ በኋላ በአዲስ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ አስተሳሰብ የተሰለፉ ኃይሎች ወደ ትግራይ ማፈግፈጋቸዉ ይታወሳል።” ካለ በኋላ ሃባር እነዚያ ኃይሎች ምን ዓይነት ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እንዳነገቱና ቢያንስ እነማን እንደሚመሯቸዉ ባይገለፅም፤ ታጋይ ሃባር እንደሚገልጸዉ፤ “በኛ በኩል በርካታ የጦር መሳሪያዎች እና የሰራዊት አባሎች የነበረን ሲሆን በአንፃሩ ሊቀበል የመጣዉ የሕወሓት ዩኒት በጣም ትንሽ ነበሩ። . . . ቀጥለን የተጓዝነዉ በአድዋ አዉራጃ ፃሂ በተባለ ሥፍራ ሲሆን በዚህ ቦታ አብዛኛዉ የሕወሓት አመራሮች ስልጠና ዉስጥ ነበሩ። በወቅቱም የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ነበር። በሥፍራዉም ላይ አባይን፣ ክንፈን፣ መለስን፣ እነተወልዴን አገኘናቸዉ። . . . በጣም በርካታ ዉይይቶችን አደረግን። … ወደ አብዬ አዲ በመመለስ ድርጅት ምስረታ ዉስጥ ገባን።” ከሐምሌ 22፣ 1972 እስከ ህዳር 11፣ 1973 በ37 ተሳታፊዎች ኢህዲንን እንደመሠረቱ በዚሁ ጋዜጣ ላይ ተገልጿል። ከኢትዮጵያ ውጪ ቀርቶ በ1964 የተመደበበትን ዲፕሎማሲያዊ ሥራ እየሰራሁ ነዉ የሚለዉን የኢሕአፓ አካል ሳይጨምር የኢሕአፓ ዕጣ ፋንታ በታሪክ እንደ አዲስ ክስተት ሊመዘገብ በሚችል መልኩ በተናጠል ሳይሆን በቡድን ለሕወሓት እጅ የሰጠ ምርኮኛ ሆኖ ተደመደመ። በዚህ አጋጣሚ ሃባር (ተሾመ እሼቱ) የኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያ ድርጅትንም አመሰራረት በዚያው ጋዜጣዊ መግለጫ ውስጥ ነጎሮናል። በዚሁ መሠረት በሃባር መግለጫ መሠረት “በኢህዲን ዉስጥ ይታገሉ የነበሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች የኦሮሞን አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ለማደራጀት እንቅስቃሴና ዉይይት የጀመሩት ከኢህዲን ጉባኤ በኋላ እንደነበር ፍንጭ ሰጥቷል። ከዚያም በኢህዲን ድርጅታዊ ጉባኤ በማዕካላዊ ኮሚቴ አባልነት ተመርጠዉ ይሰሩ የነበሩ ሦስት ጓዶችን ጨምሮ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ ተመድበዉ ይታገሉ ከነበሩበት መካከል በድምሩ ከ30 በላይ የኢህዲን ታጋዮች የኦሮሞ ህዝብ

አታጋይ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት የመመስረት ዓላማ ተቀብለዉ ሐምሌ ወር 1981 ዓም መጨረሻና ነሐሴ 1981 መጀመሪያ ላይ አዲስ ድርጅት ሊመስርቱ ከኢህዲን በይፋ ተሰናበቱ፡፡” ይላል፡፡ በዚህ መግለጫ ዉስጥ ጥያቄ የሚያስነሱ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም፤ የኦህዴድ ምስረታ ላለፉት 24 ዓመታት ኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ዳራ ነዉ ሲባል ከቆየ በኋላ ትግራይ ክልል አዴት ሆነ፤ እንደ ሃባር መግለጫ ደግሞ የኦህዴድ ምስረታ ከአዴትም ተንበን ግረዉሪ አከባቢ መሆኑን ነግሮናል፡፡ በሌላም በኩል ለኢህዲን ምስረታ የተቀመጡት 37 አባላት ከሆኑ ሰባቱ ብቻ ኦሮሞ ከሆኑ የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት/ኦህዴድ የተመሠረተዉ በሕዝብ መሀከል ሰፊ መሠረት በሌላቸዉ ሰባት ሰዎች ብቻ ለዚያዉም ምርኮኛ በነበሩ ሰዎች ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

እዉነቱ ግን የአሁኑ ኢህዲን የቀድሞዉ ኢሕአፓ ያለምንም ማወላወል የደርግን መንግስት ለመጣል ቂም ቋጥረዉ በተነሱት ምዕራባዊያን የሚረዳዉን የሕወሓትን ጡጫ መቋቋም ባለመቻሉ፤ በቡድን በመሆን ለሕወሓት እጅ የሰጠ ምርኮኛ ድርጅት እንጂ ከሕወሓት ጋር በእኩልነት በመቆም *(on equal footing)* ኢህአዴግን የመሠረቱ አልነበሩም፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ የሕወሓት የቅርብ ወዳጅ ከነበረ ፖል ቢ ሄንዝ (2007፡181) ጋር ሲወያይ ሞራልን በማይነካ መልኩ የገለጸዉ ሲተረጎም “ኢህዲን የሕወሓት ፍጡር ባይሆንም እንደ ሕወሓት በደንብ የተደራጀ አይደለም” ብሏል፡፡ በዚህ መሠረትም በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ እስከዛሬ ድረስ የታሪክ ጥቀርሻዉን ይዞ በመዳዝ ላይ ያለ ድርጅት ቢኖር አንዱ ኢሕአፓ ነዉ፡፡ ከኢሕአፓ መማር የሚቻል ነገር ቢኖር የመረጃ አልባነቱ፣ ጥናት ላይ ያልተሞረኮዘ የፖለቲካ አቋም መዉሰዱና ጉዞዉንም ሆነ ውድቀቱን ዘር ብሎ መገምገም ያልቻለ፣ ከዚህ በኋላም ይገመግማል ተብሎ የማይጠበቅ፣ እና በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ ዉስጥ በመሞትም ሆነ በመግደል ወንጀል ዉስጥ ከደርግና መኢሶን ጋር ወንጀልን በመጋራት በኢትዮጵያ የትውልድ ክፍተት በመፍጠር የሚታወቅ፤ ቀጥታ እንኳን ባይሆን ታሪክ ራሱን ይደግማል በሚባለው የመጠላለፍ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ (ዮሐንስ በቴዎድሮስና

ተክለ ጊዮርግስ ላይ፣ ምንሊክ በዮሐንስ ላይ፣ ኃይሌ ሥላሴ በእያሱ ላይ) ያደረጉትን ዓይነት መጠላለፍ ፈጽሞ ኢህአፓም ጥልቅ ጠባሳ ጥሎ ያለፈ ድርጅት ነበር ቢባል የተጋነነ አይደለም። ይህ መጽሐፍ ለ2ኛ ጊዜ ሊታተም በሚዘጋጅበት፤ በተለይም ከመጋቢት 2010 ዓም ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ ኢሕአፓም አዛውንት አባላቱን ይዞ እና የተወሰኑ ሰዎችን ጨምሮ ወደ ፊንፊኔ/አዲስ አበባ ተመልሷል። ብሔረተኝነት በገነነበት የዛሬዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢህአፓ የቀድሞ ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ አማካይነት የሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ተልዕኮውን የ1960ዎቹ መጨረሻ አከባቢ የአሲምባው ጩሎ ሰልጣኝ የነበረውን ለኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ መሪ ለሆነው ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ አስረክቦ እራሱ ሶሻል ዴሞክራሲ የሚለውን እንደሚያራምድ 6ኛ አጠቃላይ ምርጫ ቅስቃሳ ላይ አሳውቋል።

## ቀይና ነጭ ሽብሮቹ እና ተልዐኮዉን መወጣት የማይችል ፓርቲ ምስረታ

የኢትዮጵያ ሽብሮች ሁለት ቀለም ነበራቸዉ፤ ቀይና ነጭ። ሁለት የፖለቲካ ሥልጣን ያልነበራቸው ድርጅቶች፤ መኢሶን እና ኢሕአፓ እና ሥልጣን ያለው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ (ጉልቤ መንግስት) በሽብሮቹ የሚታወቁ ናቸዉ። ኢሕአፓ በነጭ ሽብር፤ ደርግና መኢሶን በቀይ ሽብር ይታወቃሉ። እንደ የሰማዕታት ድምፅ መጽሔት (1999፡ 7) መረጃ መሠረት “በአዲስ አበባ ዉስጥ በቀይ ሽብር ዘመቻ ያለቁትና በይፋ የሚታወቁት ወንድምና እህቶቻችን ሃምሳ አራት ሺህ ይሆናሉ።” የተፈናቀሉትና የተሰደዱት ቁጥር ምን ያህል እንደሆኑ የተባለ ነገር የለም። በተወሰኑ ጊዜያት ዉስጥ ከአንድ ትዉልድ 54 ሺህ ዜጎችን፤ ለዚያዉም ደግሞ ወጣትና አምራች ዜጎችን ማጣት ምን ያህል ዘግናኝ እንደሆነ ሲታሰብ የሕሊና ዕረፍት ይነሳል። ለዛሬ የአፍሪካ ኋላቀርነት እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀሰው በባሪያ ፍንገላ 320 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከሃያ ሚሊዮን የሚበልጥ ወጣት አፍሪካዊያን ከአህጉሩ በመጋዛቸው አምራችና ሊራባ የሚችል የሰው ኃይል በመጥፋቱ ለአፍሪካ ኋላቀርነት እንደ አንድ ምሳሌ ሆኖ ይጠቀሳል። በተመሳሰይ ሁኔታም ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ

ውስጥ 54 ሺህ ዜጎች በኢትዮጵያ በመገደላቸው፣ በመሰደዳቸዉና ሕይወታቸዉ በመመሰቃቀሉ የትዉልድ ዕድገት ተስተጓጉለዋል ቢባል የተጋነነ አይሆንም።

የቀይና ነጭ ሽብሮች መሠረታዊ መነሻ የስታሊን በትር የሚሉት ዓይነት ፈሊጥ ሳይሆን አይቀርም። ስታሊን የቦልሸቪክ ፓርቲ ተቀናቃኝ የሆኑትን የሩሲያ ዜጎችን ከምደረ ሩሲያ ያጠፋበት ስልት ነበር። ሩሲያዊዉ የቦልቪሽክ መሪ ቪላዲሚር ዑሊያኖቭ ሌኒን እአአ በ1924 ሲሞት ሥልጣኑን ያለብዙ ተቀናቃኝ የተረከበዉ የስታሊን ስም ሲነሳ ጎልቶ የሰው አእምሮ ውስጥ የሚመጣው ከሀገርና ፓርቲ መሪነቱ በበለጠ ከሽብርና ከአምባገነናዊ አገዛዙ ጋር የተቆራኘው ቀይ በትሩ ነዉ። የስታሊን መርህ የተጀመረዉ ለአንድ ፓርቲ አመራር *(monolithic party or dominant party leadership)* እና ለግሉ ሥልጣን በተዋጋበት ጊዜ የቋጠረዉ ጭካኔ ነበር። እንደቀድሞዎቹም ሆነ ዛሬዎቹ የአንድ ብቻ ፓርቲ አገዛዝ አቀንቃኞች የመጀመሪያ የስታሊን ዉግዘቱ ያነጣጠረዉ በሊበራሊዝም ላይ ነዉ። ያለምክንያት አልነበረም፤ ሊበራሊዝም ከዲሞክራሲ ጋር የሚሄድ መሆኑን የሚረዱ የአምባገነንነትን መስመር የሚከተሉ ሁሉ በሊበራል ንድፈ ሐሳብ ላይ የሆነ ቅጥያ በማድረግ ያጥላሉታል። ስታሊን ሊበራሊዝምን የበሰበሰ ሥርአት (moribund) ነዉ ብሎ አምርሮ ከመናገሩም በላይ ከተቃዋሚዎችም ሆነ ከዜጎች ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተገናኝቶ መወያየትንና ለቅራኔ አፈታት ጀርባዉን የሰጠ ብቻ ሳይሆን፤ የተለየ ሐሳብ ለያዘ ፓርቲ ፖሊሲ መንሸራሸር ዕድል መስጠትን እርም በማለቱ የስታሊን ሁሉ ችግር መፍቻ ሽብር ማካሄድ፤ ቀይ በትሩን መሰንዘር ብቻ ነበር። ያለምንም ጥርጥር መንግስቱ ኃይለማሪያምም ሆነ የዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ነጭም ሆነ ቀይ ሽብር አራማጆች የዚህን ሩሲያዊ ፈለግ ተከትለዋል፤ ዛሬም ቢሆን ኒዮ ሊበራለዝም እያሉ ፀረ ሊበራል አቋም የሚያራምዱ ሁሉ፤ በዚህ መስመር ላይ በሚከፈቱት የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ በአዉራ ፓርቲነት ወይም በሌላ፤ በብዙ መንገዶች አምባገነንነትንና ሽብርን የሚያራምዱ ናቸዉ።

በኢትዮጵያ የዚህ ዓይነት ሽብር የተጀመረበትን ጊዜና ሁኔታ ወደኋላ ተመልሶ ለማየት ጊዜና ትዕግስትን ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ ማወቅን ይጠይቃል። ሆዴ ሰፊነት ደብዝዞ፣ የመተሳሰብና ወገናዊነት ባህል ጨፍግጎ፣ የጠላትነት ስሜት መግነን፤ በተለይም ቅን ልቦና ጠፍቶ ድንቁርናና ጋጠወጥነት *(ignorance and arrogance) ሰፍኖ*፣ ልዩነትን በዉይይት አለመፍታት በአገር ሀብት በተለይም በሰዉ ሀብት ላይ ሊያደርስ የሚችለዉን አደጋ ለማወቅ አለመጣር፤ የፖለቲካ ልዩነትን በጦር መሳሪያ ለመፍታት ማጋደል ወደ ጀብደኝነት ይገፋፋል። የዚህ ዓይነት ችግር የተከሰተባቸዉ አገሮች ይቆጠሩ ቢባል ኢትዮጵያ አገራችን ከስታሊን ሩሲያ ቀጥሎ የመጀመሪያዉን ረድፍ ከሚይዙ አገሮች አንዷ እንደምትሆን ሳይታለም የተፈታ ነዉ።

የኢትዮጵያ ታሪክ ነዉ የሚባለዉን ከተለያዩ ሽብሮች ጋር ለአፍታ ያህል ወደኋላ ተመልሰን በዓይነ ሕሊናችን ብንመለከት፤ አፄ ቴዎድሮስ ተቀናቀኞቼ ናቸዉ ያላቸዉን ሁሉ እጅና እግር በመቁረጥ፣ ከገደል በመወርወርና ነጬን ደግሞ መያዣ አድርጎ ይዞ የግድያ ቀን ሲቆጥርላቸዉና ተዝናንቶ ለመግዛት የነበረዉ ሕልም ባይጨናገፍበት ኖሮ፤ ለአስራ ሦስት ዓመታት ሥልጣን ላይ በቆየባቸው ጊዜያት ዉስጥ የወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥርን በተለይም የወሎ ኦሮሞ ሕዝብ ቁጥርን በምን ያህል ያጠፋ እንደነበረ መገመት ይቻላል። በተመሳሳይም አፄ ዮሐንስ አዋጅ አወጣ፤ “ወይ ተጠመቅ፣ አሊያም አገሬን ልቀቅ” አለ። አፄ ምኒልክ የደቡቡን፤ የዛሬዉ የአገሬዉን ሕዝቦች በውጊያ ከአሸነፋቸዉ በኋላ ዕርቅ አውርድ ብሎ ጠራቸዉና ለሰው ምርጫ ሰጠ:: ምርጫዉም በጣትና በሰዉ መሀከል ማንን ትመርጣላችሁ? የሚል ሲሆን ጣት ማለት በተለመደዉ የኦሮሞ ሥርአት በሚመረጥ የገዳ ልማዳዊ ዲሞክራሲያዊ መተዳደር ሲሆን ሰዉ ማለት ደግሞ በንጉስ መተዳደር ማለት ነበር። በተለይም የኦሮሞዉ ወገን በለመዱት የገዳ ሥርዓት መሠረት መተዳደር መስሏቸዉ ድምፃቸዉን ለምርጫ ከሰጡ በኋላ የጭካኔ ዕርምጃ ተወሰደባቸዉ፤ እጅና እግራቸዉ፣ ጡትና ብልት ሲቆረጥ የሰዉ ጬኼት እንኳን እንዳይሰማ ነጋሪት እያስጎሰመ፤ እጅና እግራቸዉን፣ ጡትና

ብልታቸዉን አስቆረጠ። የዚህን ዓይነት አርማኔያዊ ድርጊት ሰለባዎች ማስታወሻ ሐዉልት ማንም ሰዉ ተነስቶ ኦሮሚያ ክልል፣ አርሲ ዞን፣ ኢቴያ ወረዳ፣ አኖሌ *(Anoolee)* ቀበሌ ወይም ጨለንቆ ሂዶ ማየት ይችላል። አፈሩን ለመቆፈር ብዙም ጉልበት ሳያባክን በተለያየ የዕድሜ ክልል ላይ የነበሩ ሰዎች ለመጨፍጨፋቸዉና በጅምላ ለመቀበራቸዉ የተለያየ መጠን ያላቸዉ አጥንቶች በመመልከት የምኒልክ ዘመን ጭካኔ ብቻ ሳይሆን፤ መታሰቢያ ሐዉልቱ ለምን ተሰራ ብለዉ ለሚቃወሙ የዛሬ ሰዉ ግብዝነትን ጭምር አነፃፅሮ ሊታዘብ ይችላል።

አፄ ኃይሌ ሥላሴ የኦሮሞ ልጅ አንገት ቀና እንዳይል በመጫ ቱላማ መረዳጃና ልማት ማህበር ሥር የተደራጁ ብርቅዬ የኦሮሞ ልጆችን አረደ። ደርግ ታሪካዊ አደራን ተቀብዬ የያዝኩትን ሥልጣን ተጋፋችሁ፣ መንግስት ለመጣል ሸፈታችሁ በማለት በከፊሉ ላይ ‹‹የፍየል ወጠጤ›› ሲዘፍንባቸዉ፤ አብዛኛዉ ወጣቱን ደግሞ የቀይ ሽብር ሰለባ ሲያደርግ ወላጅና ቤተሰብ ተወላጁን ቀብሮ እርሙን በወግ እንኳን እንዳይወጣ በማድረግ ተወዳዳሪ የሌለዉ ጭካኔዉን አሳይቷል። ሕወሓት/ኢህአዴግ ደግሞ በጠመንጃ አፈሙዝ የያዘውን ሥልጣን በማሽሞንሞን ሕገ መንግስታዊ ሥርዓት ያለዉ መንግስት ለመጣል አስባችኋል ‹‹ሽብርተኞች ናችሁ›› ከማለቱም ሌላ ከሕፃን እስከ አዛዉንት እስር ቤት በማጎር አሰቃይቶ በመግደል የኢትዮጵያ ታሪክ ከግጭትና ከጦርነት ታሪክ እንዳይወጣ በስልት ቀጠለበት። የ1997 ምርጫን ተከትሎ በተከሰተዉ ግጭት በጥቂት ሰዓታት ዉስጥ በተቃዋሚዎች ሠላማዊ ሰልፍ በማሳበብ የተፈፀመዉ ጭፍጨፋም ሆነ፣ የሲዳማ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የተወሰደዉ እርምጃና የጋምቤላ አኟኮች ላይ የተፈጸመዉ ግድያ ነጭ ወይም ቀይ የሚል ቀለም አይሰጠዉ እንጂ የዚያዉ ድርጊት ቀጣይ አካል ናቸዉ ቢባል የጥላቻ ፖለቲካ ማራመድ ሳይሆን ግልፅ እዉነት መናገር ነዉ።

አሳዛኙ ነገር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ቀይና ነጭ ሽብሮቹ ብቻ ሳይሆን ዛሬም በሃያ አንደኛዉ መቶ ዓመት ዉስጥ የመደማመጥና የመግባባት

ፖለቲካ የሚባል ጨርሶ አልተፈጠረም። ማንም በቀና መንፈስ ቢያስበዉ የተጨቆነዉን የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ የጭቆና መዳፍ ለማላቀቅ ተልመን ነበር ያሉት የድርጅት ኃይሎች፤ መኢሶንና ኢሕአፓ ገና ከፍጥርጥራቸዉም ጀምሮ ላይስማሙ ተስማምተዉ ብረት የተማዘዙ የነበሩ ሲሆን ደርግ ደግሞ መንግስታዊ ኃላፊነቱን ዘንግቶ ዱላ አቀባይ የእብድ ገላጋይ ነበር ለማለት ይቻላል።

ሽብርን ከታሪክ አንፃር ቆንጥሬን ለማየት ቢያስፈልግ፤ የኢሕአፓ የመጀመሪያ ሽብር ጠንሳሽ ይሆናል ተብሎ የሚገመተዉ በሊቪያዊዉ ቼ ጉቬራና ፈረንሳዩ ሬጅሳ ዴብሬይ የነደፉት ፋኖአዊ የትግል ስልት ሲሆን፤ በዚህ የትግል ስልትም ‹‹የትጥቅ ትግል አሁኑኑ መጀመር አለበት›› የሚልና መኢሶን በበኩሉ ‹‹የትጥቅ ትግሉን ከንቃተ ሕሊና መዳበር፣ ከድርጅታዊ ጥንካሬና ከሰፊ የፖለቲካና የፕሮፓጋንዳ ሥራዎች በፊት ማስቀደም የመጨረሻ መጨረሻ ፖለቲካን ለጠመንጃ ተገዥ ማድረግ ይሆናል›› ባይ ነበር። መኢሶን ኢሕአፓን በፋኖነት ሲከስስ ኢሕአፓ በበኩሉ መኢሶንን በአድርባይነት ከሷል። ስለፋኖአዊና አድርባይነት ፅንሰ ሐሳቦች በትንሹም ቢሆን ለአንባቢያን ማስጨበጥ ጠቃሚ ስለሆነ፤ ከተለያዩ ጽሑፎች ያገኘሁትን ለዚህ ጽሑፍ በሚመች አኳኋን በማሳጠር ተጠቅሜአለሁ።

*ፋኖአዊ (focoism) ታጋዮች ‹‹… አብዮታዊ ሁኔታን ከተጨባጩ የኤኮኖሚና የፖለቲካ አቋም ጋር ግንኙነት እንደሌለዉ ይቆጥሩታል። ሰዎች በቆራጥነት* ከታገሉ የተጨባጩን ሁኔታ ሕግጋት በመጣስ ሥር ነቀል የሕብረተሰብ ለዉጥ ሊያካሂዱ ይችላሉ›› ባይ ናቸዉ ፎኮይስቶች። በመኢሶን አረዳድ ደግሞ ጠመንጃ ነካሾች ማለት ነዉ።

*“የፎኮኢዝም ተከታዮች በሕዝብ ከመተማመን ይልቅ የደፈጣ ዉጊያ የሚጀምሩበትን ቦታ ለተገን ያመቻል አያመቸም ብሎ በጥንቃቄ መምረጥን ከፍተኛ ዋጋ ይሰጡታል። ለደፈጣ ዉጊያዉም የሚመርጡት ተራራማ ወይም ጥቅጥቅ ያለ ደን ያለበትን አከባቢ ነዉ።” ፋኖአዊ*

*የትግል ስልት የተቀየሰዉ በአርጀንትናዊ የሕክምና ሰዉ ቼ ጉቬራ ሲሆን፤ ፈረንሳዊዉ ፈላስፋ ጂን ፖል ሳርቴ ይህንን ሰዉ፣ ቼ ጉቬራን ማለት ነዉ፤ "የዘመናችን ሙሉ ሰዉ" ብሎ ይጠራዋል። ቼ ጉቬራ ጥቅምት 9፣ 1967 በሊቪያ ዉስጥ ቢገደልም የሱ ፈለግ ተከታዮች በየአገሩ ተፈጥረዋል፤ ኢትዮጵያዊዉ ኢሕአፓን የመሳሰሉ ማለት ነዉ።*

*አደርባይነት (opportunism):- ኢሕአፓ መኢሶንን የሚከሰስበት አቋም ነዉ። ተስፋዬ መኮንን ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሐፉ ገጽ 99 ላይ "በፋኖአዊነት ከስሶን የነበረዉ መኢሶን ዛሬም ከተጠናተዉ ዋና የመነሻ በሽታ ከአድርባይነት የተላቀቀ አይመስልም።" ሲል፤ ሌላዉ የመኢሶን ሰዉ ለመሆኑ ከመፅሐፉ የሚታወቀዉ አንዳርጋቸዉ አሰግድ "መኢሶን ለደርጉ ሒሳዊ ድጋፉን የሚሰጠዉ ከውጪና በተለይም የገጠርን መሬት አዋጅ በሥራ ለመተርጎም በሚደረገዉ ትግል አንፃር ነበር::" (ገጽ 223) ሲል መኢሶን ብልጥ እንጂ አድርባይ አለመሆኑን ሲከላከል ይታያል።*

*መኢሶን ከነጭርሱም ፓርቲ መሆኑን የሚጠራጠሩትና ለደርግ አጎብዳጅ የሆነ ድርጅት ብቻ መሆኑን የሚያስረግጡት ተቀናቃኞቹ የኢሕአፓ ሰዎች፤ መኢሶን በመንግስት ምስረታ ላይ ከሚወስደዉ አቋም በመነሳት ነዉ። መኢሶን እንደሚያምነዉ የመንግስት ምስረታ ሂደቱም ከታች ቀበሌ ጀምሮ እየተገነቡ የሚመጡ ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎዎች በመጨረሻ የሚቋጥሩት ነዉ ብለዉ ያምናሉ። ከዚህ በበለጠ ግን መኢሶኖች ብዙም አመርቂ አመራር ባልሰጡበት ሕዝባዊ ትግል ዉስጥ ‹‹የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ሕዝብ ያሸንፋል›› ይላሉ ብለዉ ያብጠለጥሏቸዋል። የአድርባይነት መገለጫ አንዱ ፓርቲዉ ቢሰራም ባይሰራም አስመሳይ የፓርቲ ፕሮፓጋንዳ መርጨትን ሥራዬ ብሎ መያያዝን መምረጡ ነዉ። ይኸዉም ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የሚያመራዉ መንገድ በሠላማዊ የምርጫ ውድድር ቢሆን የሚመረጥ ቢሆንም፤ ነገር ግን በዚህ እንደማይወሰንና የመሳሪያ ትግል አስፈላጊነት ሊኖር እንደሚችል ግንዛቤ የሚያደርግ የትግል ስልት እንደሆነ ያምናል። ገዥዉ ክፍል ሕገ መንግስታዊ ሥርዓትን ተከትሎ በሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት አምኖ የሚቀበል ከሆነ የተለየ ምርጫ አይኖርም፤ ወይም አያስፈልግም። ነገር ግን ይህ የማይሆን ከሆነ*

*የመሰሪያ ትግል መምረጡ አይቀረ ይሆናል፤ ነገር ግን ለመሰሪያ ትግል የተደረገ ቅድመ ዝግጅት ሳይኖር ሁለቱንም (ሠላማዊና የመሰሪያ ትግልን) ማማረጥ አድርባይነት ነዉ በማለት የመኢሶንን የትግል ታክቲክ ያጣጥላሉ፡፡*

*በሌላም በኩል መኢሶን የመንግስት ምስረታዉን በደርግ እግር ሥር ተኩኖ በጣም ቀላል በሆነ ሁኔታ የሚያሳካዉ ዓይነት አስመስሎ ማካሄዱ "ላም አለኝ በሰማይ" የማለት ያህል ነዉ ይሉታል፡፡ ይህንንም አንዳርጋቸዉ አሰግድ እንዳስቀመጠዉ ከሆነ "የሰፊዉ ሕዝብ ትግል ተደራጅቶና ገፍቶ አብዮታዊና ሕዝባዊ ግንባሩ እንደተቋቋመ፤ በትግሉ ዉስጥ የተሳተፉት የግንባሩ አባል ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸዉ ምልምሎች መካከል ሕዝቡ በሙሉ ነፃና ምስጢራዊ በሆነ ምርጫ እንደራሴዎቹን መርጦ፤ የመንግስቱን ከፍተኛ ሥልጣን ወደሚይዘዉ አብዮታዊ ሕዝባዊ ሸንጎ ይልካል፡፡ የሕዝቡ እንዴራሴዎች አጥንተዉ ባፀደቁት ሕገ መንግስት መሠረት የመንግስት መዋቅሮች፣ ዘርፎችና የሥልጣን ክፍፍሎች ተወስነዉ፤ በወዝደሩ ፓርቲ መሪነት ሕዝባዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፑብሊክ ይቋቋማል" (ገፅ 403) በማለት ዉሉ የማይታወቀዉን ተምኔታዊነትን ይደረድራል ይሉታል፡፡ ነገር ግን እጁ ወንጀል ካለበት ደርግ ጋር ያንን ሰፊ ጊዜና ትዕግስት የሚጠይቀዉን የመንግስት ምስረታ ሥራ አካሂዳለሁ ብሎ ማለም በርግጥም ጭልጥ ያለ አድርባይነት ነዉ ሳይሉ አላለፉም፡፡*

እንግዲህ ላይ ላዩን ሲመለከቱት የጊዜ ርዝማኔ ካልሆነ በስተቀር መኢሶንና ኢሕአፓ ሁለቱም የትጥቅ ትግልን የሚደግፉ ነበሩ፡፡ ልዩነት መስሎ የሚታየዉ መኢሶን ፋኖአዊ የትግል ስልትን እቃወማለሁ ሲል፤ ኢሕአፓ ደግሞ ትግል ዉስጥ ገብቶ የትጥቅ ትግልን ዳር ዳር ማለት አጎብዳጅነት ወይም አድርባይነት ነዉ በማለት ይኮንናል፡፡ በዚህም አቋማቸዉ አንዱ ሌላዉን ድል ነሽ እና ድል ተነሺ ተደራርገዉ ይገማመቱ ነበር፡፡ አንዱ ወደሌላ መምጣትና እጅ ለእጅ ለመያያዝ የመጣጣር ሁኔታ ባለመፈጠሩ የትግል ዘይቤአቸዉ ነጭና ቀይ ሽብር በሚል ወንጀል መጠፋፋት ሆኖ ተጠናቀቀ፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና (2006፡ 74) <u>የኢትዮጵያ ፖለቲካ</u>

ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች በሚለዉ መፅሐፉ የመኢሶንና የኢሕአፓ መጠፋፋትን ምርር ባለ ሁኔታ ሲገልጽ "የአንድ ለጋ ወጣት ብሩህ አእምሮ ለእርስ በርስ የመጠፋፋት ፖለቲካ ከመጠቀም በላይ ምን የሚያሳዝን ነገር ይኖራል?" በማለት የግርምት ጥያቄ አስቀምጧል።

ዘነበ ፈለቀ ደግሞ ነበር በሚለዉ መፅሐፉ ገጽ 265 ላይ "በእዉነተኛዉ ፍትህና በታሪክ ፊት ሁላችንም በእኩል የምንጠየቅበትና፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጋራ ይቅርታ የምንጠይቅበት፤ ዛሬ ላይ ቁሜን መሆን አልነበረበትም ብለን በፀፀት የምናስታዉሰዉ የወንድማማቾች ደም በጎዳና ላይ ፈስሶ ሀገራችንን ጎዳን፤ በፖለቲካ መስመራችን ከኋላችን ቁመዉ ‹በለዉ› እያሉ ሲያስተኩሱን የነበሩ ባዕዳን በዉድቀታችን ሳቁብን፣ በትንሽነታችንም ብሔራዊ ጥቅማችንን ሳይቀር አሳልፈን እንድንሰጥ አስገደዱን" ብሏል። ነበር ከሚለዉ መጽሐፍ ይዘት ስንነሳ፤ ይህ ሰዉ በደርግ አባልነት ወይም በደርግ ጽ/ቤት ዉስጥ ሁነኛ ቦታ እንደነበረዉ ጽሑፉ የሚያሳበቅበት ሲሆን፤ ጽሑፉ ‹‹የአዛኝ ቅቤ አንጓች›› ዓይነት ነዉ። ያሳዘነዉ ያስመስልበታል ያልኩበት ምክንያትም ይኸዉ ደራሲ በዚያዉ መፅሐፍ ገጽ 217 ላይ "በፖለቲካ ማዕበል ዉስጥ የሚገኘዉ የሕብረተሰብ ክፍል ስሜታዊ በመሆኑ ለሚናገርም ሆነ ለሚያደርገዉ የጎሊና ዳኛ አልነበረዉም" ብሎ የአጉል ይቅር ቡሉኝ ሐሳብ ሲያቀርብ ስለሚስተዋል ነዉ።

ስለቀይ ሽብር ሲነሳ ስለመንግስቱ ኃይለማርያምና የደርግ አባላቱ የግድያ ስልት መነሳቱ እንደሆነ ይታወቃል። እንዲህ ዓይነት ጭካኔ የተመላበት ተግባር እንዲሁም የአንድን ሰዉ የሐሳብ ልዩነት ያለማክበር ዝንባሌ ምንጬ ፍርሃት እንደሆነ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች የሚናገሩ መሆኑ ሳይገለፅ መዝለል አስፈላጊ አይመስለኝም። በአንድም ሆነ በሌላ የመኢሶን አዝጋሚ የጉዞ ስልት፤ የኢሕአፓ ጠመንጃ ነካሽነት፣ የሕዝቡ ለፖለቲካ ትግል ያለዉ ተጋላጭነት አናሳ መሆን፤ ሦስቱ ተዳምረዉ የመጠንም ሆነ የዓይነት ለዉጥ እያሳየ የመጣዉን ሕዝባዊ ንቅናቄ ድርጅት አልባ አድርገዉ በማቆየት አብዮቱን <ግብታዊ> በተሰኘዉ

ቃል የታጀበ አብዮት እንዲሆን አድርገዉ መንበረ ሥልጣኑን ለሰዉ ሕይወት ኃላፊነት ለማይሰማዉ ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አሳልፎ የሰጠ ሆኖ አልፏል።

የቂም ቁርሾዉ የቱ ጋ እንደሆነ ተሰምሮበት ሊታወስ የሚገባዉ አንድ ነገር ቢኖር፤ መኢሶንና ኢሕአፓ ከአገር ዉጪ በምስረታ ላይ በነበሩበት ጊዜ የቋጠሩት ቂም በቀል መኢሶን ወታደሩን ተጠግቶ ኢሕአፓን እንዲወጋ አስቻለዉ፤ ኢሕአፓም ያገኘዉን መሳሪያ ሁሉ በመጠቀም የዓላማዉ ጠላቶች ናቸዉ ባላቸዉ የደርግና መኢሶን አባላት ላይ አነጣጠረ። በመሠረታዊነት ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር ቀይ ሽብር ሲወገዝ ደርግና መኢሶንን መወንጀል፣ ያንኑ ያህልም ነጭ ሽብር ሲኮነን ኢሕአፓ ብቻዉን የተወገዘ የሚመስላቸዉ ሰዎች ይኖራሉ። ሁለቱም ፅንፎች ትክክል አልነበሩም፣ አይደሉምም። ምክንያቱም፤ ሁለቱም የአገራችን የኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ጠባሳ ስለነበሩ፤ ልንማማርበት ከምናነሳቸዉ በስተቀር፤ ከሁለቱም ወገን አንዳቸዉ ጠቅሟል የሚያስብላቸዉ ቅንጣት የሚታክል ሚዛን የሚያነሳ አስተዋጽኦ የላቸዉም።

የአፄ ኃይሌ ሥላሴን የአፈና ፖሊሲ ሲያስፈጽሙ የነበሩ ወታደሮች ግብታዊ (የፖለቲካ ድርጅት አልባ) ባሉት አብዮት ሥልጣን ላይ ወጡ። ሥልጣናቸዉንም ለማጠናከር የመጀመሪያ ምርጫቸዉ ፖሊሱንና የደህንነት ክፍሉን እጃቸዉ አስገብተዉ የሁሉ ነገራቸዉ ዋስትና ጠመንጃዉን አደረጉት። ይህንን መንደርደሪያ ያመጣሁት ለቀይ እና ነጭ ሽብሮቹ የትኛዉ ቀዳሚ ተጠያቂ ነበር? የትኛዉ ተከታይ ነበር የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲያመች ነዉ።

ስያሜዉ የኋላ ጊዜ ላይ ይምጣ እንጂ በኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ዉስጥ <ቀይ ሽብር> ቀዳሚ ድርጊት ነበር ለማለት ይቻላል። ነገሩ እንዲህ ቢታይ ግልፅ ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ስካን ተደርጎ የተቀመጠዉ የመንግስቱ ኃይለማሪያም ግድያ እንዲፈፀም ማዘዣ መሠረት ደርግ ስድሳዎቹን የኃይሌ ሥላሴ ሹማምንት ያለምንም ፍርድ በፖለቲካ

ዉሳኔ፤ ሕዳር 15፣ 1967 ፈጀ። (መንግስቱ ኃይለማርያም የንጉሱ ባለሥልጣናት እንዲገደሉ የፃፈውን ደብዳቤ ከተያያዘው አባሪ ይመልከቱ) በቀጣይም የደርግ አባላቱ የራሳቸዉ ቁና ይሞላ ዘንድ ለማሸነፍ ሲሉ ሁለት ከፍተኛና በኢትዮጵያ ወታደራዊ አመራር ዉስጥ ስመጥር የሆኑ መኮንኖችን በተለያየ ጊዜ ጋብዘዉ መሪያቸዉ አደረጓቸዉ። እነሱም የደርጉ ሊቃነመናብርት የነበሩትን ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ከንጉሱ ባለሥልጣኖች ጋር እና ብርጋዲየር ጀኔራል ተፈሪ በንቲን ደግሞ በማስከተል በማን አለብኝነት ገደሏቸዉ። ቀስ በቀስም ሌሎች የደርጉ አባላት የነበሩትን ሻለቃ አጥናፉ አባተን፣ ሻምበሎች ዓለማየሁ ኃይሌንና ሞገስን ቁርስ አደረግናቸዉ አሉ። ለዚህ ነዉ ስያሜዉ በኋላ ይምጣ እንጂ ቀይ ሽብር፤ ደርግ ሥልጣን ላይ ወጥቶ ከትንሽ ጊዜ በኋላ የጀመረዉና ከደም ጥማት የተነሳ ሊላቀቅም ያልቻለዉ ነዉ። ምንም ዓይነት ምክንያት ሊቀርብለት አይችልም፤ በተቋቋመ ሕግ እና በሕጋዊ ተቋም፣ እንዲሁም በቂ ጊዜ ተወስዶ ያልተዳኘ ፖለቲካዊ ዕርምጃ ምንም ዓይነት ቀለም ይሰጠዉ፤ ሽብር ነዉና ደርግ ቀይ ሽብርን ከነጭ ሽብር ቀድሞ ጀምሮታል ለማለት የሚቻለዉ።

እዚህም ላይ ከደርግ ጋር የፈርጅኩት የመኢሶን ሚና የቱ ጋ በተጨባጭም ከደርግ ጎን ቆሞ የቀይ ሽብሩ ተዋናይ እንደሆነ መግለፅ አስፈላጊ ነዉ። አባባሉን መሬት ለማስረገጥ ያህል የራሱ የመኢሶን አባል የነበረዉና ከላይ የተመለከተዉን መፅሐፍ የፃፈዉ አንዳርጋቸዉ አሰግድ "መኢሶን ከመጀመሪያ ጀምሮ የአፄ ኃይሌ ሥላሴን የፀጥታ ኃይል ይፈራ እንደነበረ ሁሉ፤ ከዚያ ባልተለየ ሁኔታ ደርግ ጥፋት ሲያደርግ በገንቢ ሂስ ማረም፣ አድሃሪ ኃይሎች በደርጉ ላይ ሲነሱ ከደርጉ ጎን በመሰለፍ መታገል፤ ይህ ነዉ የማንኛዉም ተራማጅ የሕዝብ ወገን አቋም" (ገጽ 165) በማለቱ መኢሶን ከርዕዮተ ዓለም አንፃር ሲታይ አድርባይነት እና ከታሪክ አንፃር ሲታይ ደግሞ የቀይ ሽብር አራማጅ ወይም ደጋፊ ወንጀለኛ ነበር ሊያስብለዉ የሚችለዉ። ከፊውዳል ፖለቲካ አንፃር ደግሞ መኢሶን ደርግን ተገን አድርጎ ኢሕአፓን ጠልፎ የጣለ ሴረኛ ድርጅት ነበር።
ኢሕአፓም ቢሆን ሲያራምደዉ ከነበረዉ አቋምና ከመኢሶን ጋር

ከተጋባዉ ቂመኛነት የተነሳ የሽብሩ አንዱ ተወናይ ነበር የሚያስብለዉ። ለማስረጃም ያህል የኢህአፓ ታጣቂ አካሉ አባል የነበረዉ ተስፋዬ መኮንን የአዉሮፓዉን የተማሪዎች ማህበር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሲወስድና ሙሉ ጊዜያቸዉን ለትግሉ ዓላማ ሰዉተናል ሲል "ከዚያን ጊዜ በኋላ በመሀከላችን ሊኖር ይገባ የነበር ሰብአዊ ግንኙነቶች ሁሉ ተቋርጠዉ በጠላትነት መተያየት ተጀመረ" (ገጽ 93) ይላል። በዚህም መሠረት በዉጭ አገር የተጠነሰሰዉ የሰለጠነ ፖለቲካ መምራት አለመቻላቸዉ ዉሎ ሲያድር ደግሞ ወደ አገር ቤት መጥቶ ትግላቸዉን ወደ ደም መፋሰስ እንዲያነጣጥሩ አድርጓቸዋል።

በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የተፈጠረዉ በጠላትነት የመተያየት ግንኙነት ‹‹ሥልጣንን ከሻሞ አገኘሁ›› ከሚለዉ ደርግ የሰለጠነ የፖለቲካ ግንኙነት ወይም አመራር ሊመጣ አይችልም፤ መንግስት ሊሰማዉ የሚችለዉን ኃላፊነት ማምጣት አይችልም የሚሉት ወገኖች ቢኖሩ አላዋቂ አያስብላቸዉም። ዲሞክራሲ ባልዳበረበትና ኋላቀር ፊዉዳላዊ የጎርጥ የመተያየት ፖለቲካ በሚካሄድበት ሕብረተሰቦች መካከል የሰለጠነ የፖለቲካ ግንኙነትን ከጀርባ ማንሾካሾክ የበለጠ ይመረጣል። ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሰዎች ከገንቢ ዓላማ ዉጪ ማንሾካሾክን ይጠቀሙበታል፤ አሊያም ወደመግደል፣ ማሰር፣ ከአገርና ከሥራ ማባረር፣ ስም ለማጠልሸት ይጠቀሙበታል እንጂ ልዩነታቸዉን የሕዝብ ዉሳኔ ወደ መሻት አይወስዱም። እንዲያዉም የሕዝብን ዉሳኔ ቀምተዉ የታሪክም የድርጊትም ተጠያቂ ይሆናሉ። በዚሁ ደርግና መኢሶን ኢሕአፓን ተጠያቂ ሲያደርጉ፤ ኢሕአፓም በተራዉ ደርግና መኢሶንን ተጠያቂ ያደርጋል። የተገኘ ዉጤት ስሌት ዉስጥ ቢገባ ግን አንድ ትዉልድ የሚሆን የኢትዮጵያ ዜጎች ሞተዉ፣ ታስረዉ፣ ከአገር ተሰደዉ፣ በሽተኛና ፈሪ ሆነዉ፣ አገሪቱ ዛሬ ድረስ የተማሩና የሚሰሩ ሰዎች ያለ እያለች እንዲትቀር (zero-sum game) አድርጓታል።

እንግዲህ ሁኔታዎች ከቃላት በበለጠ በድርጊት ይገለፃሉና የሽብሮቹ ስያሜ የመንግስት ኃላፊነቱን ተረድቶ ባለመወጣት የተጀመረ ነበር

ብንል፤ ከስም አሰጣጥና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንዳርጋቸዉ አሰግድ (1998፡ 420-21) እንደጠቀሰዉ “ቀይ ሽብር የኢሕአፓን አመራር የግድያን ወንጅልን ለመቋቋም የተወሰደ እርምጃ የተገለጸለበት ቃል ሲሆን፤ ነጭ ሽብር በመባል የሚታወቀዉ ደግሞ የኢሕአፓ አመራር የሶሻል አብዮት የግድያ ሂደት፣ የከተማ ትጥቅ ትግልን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመርኩዘን አስፈላጊነቱን አምነን የጀመርነዉ ነዉ።” በማለት የሰጡትን ትርጉም ይመስላል። ለዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ ግን ነጭም ሆነ ቀይ ሽብር የሰለጠነ ፖለቲካ ለማራመድ አለመቻል የፈጠረዉ ኋላቀር የእርስ በርስ ግድያ ነዉ ከማለት በስተቀር ብዙ ትንታኔ የሚያሻዉ ነገር አይደለም።በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ የሽብር ነገር የት እንደሚያበቃ መናገር የሚያስቸግር ሲሆን፤ ቅርፅን ብቻ በመለወጥ ሕወሓት/ኢህአዴግ ያራመደውን ሽብር ሁለትን አስምልክቶ ደግሞ በምዕራፍ ሦስት ዉስጥ እንመለከታለን።

ለማጠቃለል ያህል፤ የሰማዕታት ሐዉልት ግንባታ ማህበር ለቀይ ሽብር ሰለባዎች ሐዉልት አቁሞላቸዋል። ሐዉልቱ በሽብሮቹ ምክንያት የተፈጠረዉን የትውልድ ክፍተት መነሻ ምን እንደሆነ ለተተኪዉ ትውልድ ሊያስረዳም ሞክሯል። የሐዉልቱ ግንባታ ማህበር መልዕክትም (1999፡ 4) “አንደኛ ዓላማዉ ለሰማዕታቱ መታሰቢያ የሚሆን “ይበቃል” የተሰኘ ሐዉልት ማቆምና አጽማቸዉን በክብር ማሳረፍ ሲሆን፤ ሁለተኛዉ ደግሞ ጭፍጨፋዉ መቼም እንዳይደገም የመቻቻል ፖለቲካ ይሰፍን ዘንድ ገንቢ መልዕክት ማስተላለፍ ነዉ።” ብሏል። አባባሉ እንደአባባል ትክክል ቢሆንም እንዳይደገም የተባለዉ ጭፍጨፋ በ1997 በኢትዮጵያ ዉስጥ በተደረገዉ ምርጫና ከዚያ በኋላም ባሉት ተከታታይ ጊዜያት የሕዝብ ድምፅ ተቀልብሶ ጭፍጨፋዉም ተደግሞ በ1999 ላይ የታተመዉ የሰማዕታት ድምፅ ያለፈዉን ሽብር እንዳይደገም ብሎ መፃፉ ለዚህኛዉ ሽብር ደግሞ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሎ እንደማለፍ የሚቆጠር ነዉ። አልበቃም እንጂ የሽብሮቹ ነገር በዚያዉ ቢያበቃና የሰለጠነ ፖለቲካ ማራመድ ቢቻል የሁሉም ሰዉ የልብ ቁስል በጠገገ ነበር እላለሁ። በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ የመጀመሪያዎቹ ባለቀለም ሽብሮች

ጉዳይ ያለኝ ግንዛቤ ይኼዉ ነዉ፡፡

የቀይ እና ነጭ ሽብር ፅንሰ ሐሳቦች ፍተሻ እዚሁ ላይ ገታ ላድርግና ወደ መሠረታዊ አርእስተ ጉዳይ ስለፓርቲ ፖለቲካ ተመልሰን ዛሬም ድረስ ካልተላቀቅነው የፓርቲ-መንግስት መዋቅር ጥመርታ ችግሮች ማለትም ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ/ሰደድ እስከ ኢሠፓ/የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ/ኢህዲሪ መንግስት ምስረታና አወዳደቅ ምልከታ እንሄዳለን፡፡

የአፄ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት ከዉስጣዊና ዉጫዊ ችግሮች የተነሳ ሕዝባዊ ንቅናቄዎቹን ሊቋቋም ባለመቻል፤ በተለይም ከ1960ዎቹ ወዲህ በሕዝባዊ ማዕበል እየተናጠ በመሄዱ፤ ነገር ግን ሕሊናዊ ሁኔታዎች ማለትም የሕብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና አለመጎልበትና ሕዝብን በዓላማ ሥር አስተባብሮ ሥልጣንን የሚረከብ የፖለቲካ አደረጃጀት ኢትዮጵያ ዉስጥ ባለመኖሩ፤ ‹‹ሥልጣን ሻሞ›› ሆኖ ነበር ያለዉና ዘገምተኛ አብዮት ሲመራ የቆየው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፤ ከመስከረም 2 ቀን 1967 ጀምሮ የ120 ሰዎች ርዕሰ ብሔር/መስተዳድር ሆኖ መንበረ ሥልጣኑን መረከቡን ገልጫለሁ፡፡ በመቀጠልም በውጭ አገሮች የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች መኢሶን እና ኢሕአፓ የየበኩላቸዉን ቢያኔ በመስጠትና ሌሎችም ኢሊቶች በግልም ሆነ በቡድን ተሰባስበዉ ሕዝባዊዉን እንቅስቃሴ ለማገዝም ሆነ ለመቀናቀን ወደ አገር ቤት እንደገቡም ተገጿል፡፡

ወደ አገር ቤት መመለሳቸው ብቻ ሳይሆን ገና ከውጪ ጀምሮ መኢሶንና ኢሕአፓ ድርጅታዊ መሠረታቸዉን ብዙም ሳያጠናክሩ መቆራቆስ መጀመራቸዉን በዚህ ጽሑፍ ሌላ ክፍል ላይ አመላክቻለሁ፡፡ አንዳንድ ነገሮቻቸዉን በጥልቀት ለማመላከት ያመቸ ዘንድ በ1960 ጀርመን ሐምቡርግ የተመሠረተዉ መኢሶንና በ1964 እዚያዉ ጀርመን በርሊን የተመሠረተዉ ኢሕአፓ የ1966ቱን ሕዝባዊ አብዮት ለመቀላቀል ከየአቅጣጫዎች ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ቢሆንም፤ ከ1965ቱ በአዉሮፓ

ተማሪዎች ስብሰባ ወቅት የቆሰቆሱት ቁርሾ እራሳቸዉን ተራ በተራ አሳልፈዉ ለደርግ ዕርድ እንዲሰጡ አድርጓቸዉ እንደነበረ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መጠፋፋት *(elimination)* በሚባለዉ የሸፍጥ ፖለቲካ ደርግና መኢሶን ተጋግዘዉ ኢሕአፓን እንደጠመዱት ሁሉ፤ የወራት ዕድሜ የጊዜ ልዩነትን በማድረግ መኢሶንም ከ1969 ጀምሮ ከደርጉ ፓርቲ በተደረገበት ጫና ከአብዮቱ መድረክ ተወገደ፡፡

እዚህ ላይ ኤሊቶቹ ተራ በተራ ከፖለቲካዉ መድረክ መንሸራተታቸዉ ለታሪክ ሳይሆን ለትምህርታዊነቱም ሲባል የመኢሶንና የኢሕአፓ መሠረታዊ ቅራኔ *(bone of contention)* ከየትና በምን ሁኔታ እንደተከሰተ ዜጎችን መጠነኛ ግንዛቤ ይጨብጡ ዘንድ ሥረ ነገሩ የታሪክ ይሁን ወደ ሥልጣን በሚደረገዉ ጉዞ ላይ የተከተሉት የታክቲክ ምርጫ አዋጭ እንዳልነበረ፤ በሌላም በኩል ለቀለም ትምህርት ከቆዩባቸዉ የሰለጠነዉ የምዕራቡ ዓለም የቀዱት የፖለቲካ አካሄድን በእንጥፍጣፊ ደረጃም ቢሆን ያልተገናዘቡት መሆኑን ከማስረዳቱም ሌላ፤ ነገር ግን የተወለዱበት ፊውዳላዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ምንም ያልተላቀቃቸዉ መሆኑን የዛሬዉ ወጣት መገንዘብና መጠየፍ እንዳለበት በግልፅ ሊነገር አንደሚገባ መታወቅ አለበት፡፡ ምክንያቱ ለዉጥ መምጣት እንዳለበት ስናስብ ያለፈዉ ስህተት ወይም ጥፋት የተመሰረተዉ ምን ላይ እንደሆነ፣ የዛሬ ድክመት ምን እንደሚመስል ማመላከትና የወደፊት ራዕይን ለመቀየስ እንደሚያግዝ ይታመናልና ነው፡፡

በርሊን ላይ በተደረገዉ ስብሰባ ላይ በብሔር ጥያቄ ዙሪያ ከመርህ ዉይይት ጎን ለጎን ኢሕአፓን የሚመስርቱ ተሳታፊዎች ‹‹ፀረ ዘውድ ትግሉ የሚጀምረዉ ዛሬ ነዉ›› ሲሉ፤ ቀደም ሲል ሀምቡርግ ዉስጥ መኢሶንን የመሠረቱት የመኢሶንን አቋም የሚያንፀባርቁ ‹‹ንቃት፣ ድርጅት፣ ትጥቅ›› እያሉ ይሰብኩ እንደነበርና ይኸዉ ውሎ ሲያድር እርስ በርስ የሚያገዳድል የቅራኔ ምንጭ *(bone of contention)* ሆኖ መዝለቁ እጅግ የሚያሳዝን ነው፡፡ ይህንን አቋማቸዉን በዉጪ ባለዉም ሆነ በሕብረተሰቡ መሀከል ሳያንሸራሽሩና አንድ ስምምነት ላይ ሳይደረሱ የ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት ስለፈነዳ በቦሌም ሆነ በኤርትራ በኩል ወደ

ኢትዮጵያ የገቡት የመኢሶንና የኢሕአፓ አባላት ቁርቋሶአቸዉን በቀጣይነት ገፉበት።

አገር ዉስጥ ከገቡም በኋላ ዉስብስብ የቅራኔ ምንጮች እንደተፈጠሩባቸዉ ታሪካቸዉ ያወሳል። ይኸዉም የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ሆነዉ ድምፃቸዉን ከፍ አድርገዉ የጮሁለትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የነበሩ የተማሪዉ መሪዎች ሕይወታቸዉን ጭምር መስዋዕት ያደረጉበት ‹‹የመሬት ላራሹ›› አዋጅ በደርግ ሲታወጅ፤ የአዋጁን አፈፃፀም በተመለከተ መኢሶን ሂሳዊ ድጋፍ እያደረጉ ‹‹ከደርግ ጋር መስራት ይቻላል›› ብሎ የመሬት አዋጁን ለማስፈፀም እግሬ መንገዱንም የደርግን ሥልጣን ለመጋራት ከአዉሮፓና ከሌላም ክፍለ ዓለም ያሰባሰባቸዉ አባላቱንና ከአገር ዉስጥም ያቀፋቸዉን አባላትና ደጋፊዎች በግብርና ሚኒስቴር እና በሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ዉስጥ በመሰግሰግ፤ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጀምሮ ወረዳ ድረስ ሲያስገባ፤ ቀደም ሲል ከኢሕአፓ ጋር ይጋሩት የነበረዉን ‹‹የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት›› ምስረታ መፈክርን ሳይቀር ትዝብት ላይ በሚጥል መልኩ መኢሶን እርግፍ አድርጎ ተወዉ።

በተቃራኒዉ ኢሕአፓ ለደርግ ያለውን ጥላቻ በማግዘፍ ማለትም ደርግ የፈጸመው ከሆነ "የመሬት አዋጁ ፋሽስዚምን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚያነግስ" ስለሆነ፤ ይህንን ለማስፈጸምም ሆነ መሠረታዊ ትምህርት ለማስተማር በ*ዕድገት በሕብረት የዕዉቀትና የሥራ ዘመቻ* ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሄዱ የዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና ሌሎችም ዜጎች ዘመቻዉን ጥለዉ እንዲወጡ ወስኖ ጥሪ ሲያደርግ፤ የመሬት አዋጁን መኮነን ብቻ ሳይሆን ከደርግ ጋርም መስራት እንደማይቻልና በትጥቅ ትግል ጊዜያዊ ሕዝባዊ ሸንጎ ማቋቋም በሱም አማካይነት ‹‹ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት›› ሊያቋቁም የሚችልበትን ስልት በጠመንጃ አፈሙዝ ጭምር እንደሚጠቀም በመግለፅ እርምጃም እንደሚወስድ በማስታወቅ ከመኢሶንና ደርግ ጋር የነበረዉን ቅራኔ አሰፋዉ። በጣም በሚያሳዝንና በወረደ መልኩ ደግሞ በወቅቱ የየትኛውንም የኢትዮጵያ

ሕብረተሰብ ሊገልፅ እንደሚችል ባልተገለጸ ቅላፄ የፊደል ልዩነት “እናሸንፋለን” የሚሉት በደርግ ደጋፊነት “እናቸንፋለን” የሚሉቱ ደግሞ በኢሕአፓ ደጋፊነት በመፈራረጅ የአቋም ልዩነት መገለጫ እንዲሆን ተደርጎ ዜጎች እርስ በርስ ሊገዳደሉበት ችለዋል።

ሥልጣን ሻሞ ከሆነችበት ሜዳ ላይ አገኘኋት ያለዉ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ቢገጥሙትም ያጣጣመዉ የንጉሱ አልጋ ከእጇ እንዳታመልጥ ኢሕአፓን በመኢሶን፤ መኢሶንን ደግሞ በሌሎች ድርጅቶች ማጥራት ጀመረ። በተለይም በ1969 የሶማሊያ መንግስት ጦር አብዛኛዉን ምስራቃዊ የአገሪቱን ክፍል ይዞ ለመሀል አገር ሲንደረደር፤ ኢሕአፓ ደግሞ “አምስተኛ ረድፈኝነት” በሚለው የትግል ስልት አብዮቱን በመቃወም በመኢሶንና ሌሎች ድርጅቶች ካድሬዎች ላይ ይተኩስ ነበር ተብሎ ተከሷል። ይህ አጋጣሚ የደርግ የፖለቲካ አቅጣጫ ወዴት እንደሆነ በውል ባልተረዱት የሕብረተሰብ ክፍል አከባቢ በኢሕአፓ ላይ ምህረት የለሽ ጥላቻ እንዲደርስበት ሲያደርግ፤ ኢህአፓም ባለ በሌለ ኃይል እንዲመታ ጫና የተፈጠረበት ጊዜም ነበር ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም፤ የሶማሊያ መንግስት ወረራ ድንበር ቆርሶ መዉሰድ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕልዉና ጭምር እስከመፈታተን የደረሰ ነበር። በተለይ ዛሬ ሱማሌ ክልል ተብሎ የሚታወቀውን ተሻግሮ ዛሬ ኦሮሚያ ክልል ተብሎ የሚታወቀዉን ክልል ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች ከምስራቅ አፍሪካ ካርታ ላይ ለማጥፋትና ከታላቋ ሶማሊያ ጋር ለመቀላቀል ያደረገዉ መንደርደር በቀላሉ የሚመለስ አይመስልም ነበር።

ከሱማሊያ ወራሪ ጦር መደምሰስ ጋራ ኢሕአፓም ተመትቶ ከከተማ ወደ ገጠር በማፈገፈጉ የልብ ልብ የተሰማዉ ደርግ ሥልጣኑ እንዲያብጥ ከማድረጉም በላይ ያለማንም ተቀናቃኝ በሚባል መልኩ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ዓለም አቀፍ ፋሽን የሆነዉን የፓርቲ ምስረታ እንቅስቃሴ ዉስጥ ዉስጡን መንግስቱ ኃይለማሪያም ከነዶ/ር ሠናይ ልኬ ጋር ሲቋጥር ሲፈታ የቆየበትን የፖለቲካ ሸፍጥ ይፋ በማዉጣትና በአሸናፊነት መቀጠል የሚለዉ ሕልሙ አገረሸበት። በዚህም የደርግ አባላት የፖለቲካ

ፓርቲ ጥንስስ የሆነዉ አብዮታዊ ሰደድ በወዝሊግ አጋዥነት መሠረት እንደተጣለ የተመዘገቡ ታሪኮቹ ያወሳሉ። እዚህ ጋ የደርግ-ሰደድ የፖለቲካ ድርጅት ምስረታ ላይ የዶ/ር ሠናይ ልኬ ስምና ዝና በሰፊዉ አብሮ ስለሚነሳ የተወሰኑ ማስረጃዎችን መፈተሹ ተገቢ ይሆናል።

ዶ/ር ሠናይ ልኬ የተማረዉ በአሜሪካን አገር ሆኖ በትምህርት ላይ በነበረበት ጊዜ ከመኢሶን መስራች አባላት ጋር ቀላል የማይባል ግንኙነት እንደነበረዉና እንዳዉም ከመኢሶን ዓላማ አንፃር የኃይሌ ሥላሴን የዘዉድ ሥርዓቱን ለማስወገድ አገር ዉስጥ መግባት የፈለገዉ በቦሌ ሳይሆን የጦር መሳሪያን አንግቦ በባሌ በኩል ነበር። እግር ጥሎት እንዲሁ ወይም የመኢሶን የትግል ታክቲክ ለዉጥ እንደሆነ አይታወቅም በቦሌ ገብቶ ኑሮዉን ቢሾፍቱ የምግብ ጤና ምርምር እንስቲትዩት አደረገ። ከሰዉነት አቋሙ ወይም ከስፖርት ወዳድነቱ ሰፋ ካለም ፓርቲ የማደራጀቱን ፍላጎት ይዞ የተነሳ ሊሆን ይችላል፤ ቢሾፍቱ ከሚገኘዉ የአየር ኃይል አባላት ጋር በሰፊዉ እንደተዋወቀ አንዳንድ የጽሑፍ ማስረጃዎች ይገልፃሉ።

አነጋጋሪዉ ነገር ግን፤ ዶ/ር ሠናይ ልኬ ትግሉን ለማፋጠን አስቦም እንደሆነ አይታወቅም፣ ወይም እንደሚጠረጠረዉ የሥልጣን ጥማት በዉስጡ ቋጥሮ እንደሆነ፣ ይዞት የገባዉን መኢሶንን ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎ እነ ሻምበል ሸዋንዳኝ በለጠን ጨምሮ ብዙ ወታደሮች የተሳተፉበት ወዝሊግ የተባለዉን ድርጅት በ1964 መስርቶ በኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ከፈጣሪ በላይ ‹‹ኃይሌ ሥላሴ ይሙት›› ካለ እሳት ሊጋባ ያለዉን ሕፃን እንኳን የማይታደገዉን ሠራዊት፤ በዚህ ወዝሊግ በሚባለዉ ድርጅት ዉስጥ መመልመሉ አስገራሚ ነዉ ሊባል ይችላል። ይህንንም ያደረገዉ ተስፋዬ መኮንን እንደሚለዉ "ዶ/ር ሠናይ ልኬ ገና ጠዋት … በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዉስጥ የለዉጥ መሳሪያ ሕዝቡ ሳይሆን የወታደሩ ክፍል ነዉ" የሚል ድብቅ አቋም ይዞ እንደነበረ በመጽሐፉ ገጽ 202 ላይ ይገልጻል። እዚህ ላይ በወቅቱ ከዶ/ር ሠናይ ልኬም ሆነ ከወዝሊግ ወጣ ያሉም ቢሆኑም፤ እንዲሁም ዛሬ ላይ ሆነን

ስንገመግም የተወሰነ ስህተት ያለበት መሆኑን ብንረዳም፤ የወታደሩ የላዕይ ላዕይ ክፍል ፈጣን ንቃት ከሚያንሰዉ በስተቀር ድርጅትና ትጥቅ እንዳለዉና ለዉጥ ለማምጣት ያለዉ ዕድል ሰፊ መሆኑ ይነገራል። ነገር ግን ጊዜዉን ጠብቆ ከተደረሰበት ግንዛቤ አንፃር ወታደሩ የያዘዉ ድርጅትም ሆነ ትጥቅ የራሱ የወታደሩ ሳይሆን የገዥዉ አባላት የሆኑ የአለቆቹ መሆኑን አልተረዳም ነበር። ምክንያቱም፤ ገዥዎቹና አለቆቹ ትጥቁንም መቀማትና ድርጅቱንም መበተን፤ እሱንና ቤተሰቡን ማስራብ እንደሚችሉ ግንዛቤ ካለማድረግ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ሌላዉ ወታደሩ ራሱ ከሕዝብ አብራክ የወጣ መሆኑ ከሚነገርበት አካሄድ አንፃር የተሳሳተ ግንዛቤ መያዝ ነዉ። አዎን! እዉነትም ወታደሩ ከሕዝብ አብራክ የወጣ ነዉ፤ ነገር ግን ከሕዝብ አብራክ የወጣ በመሆኑ የሕዝብ ወገን ነዉ ብሎ መደምደሙ ስሜታዊና ራስን መሸወድ እንደሆነ ዶ/ር ሠናይ ልኬ አልተረዳም ነበር። በሌላም በኩል ዶ/ሩ የሥልጣን ጥማት የነበረበት መሆኑን አንዳርጋቸዉ አሰግድ እንደሚከተለዉ ገልጾታል። ‹‹ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዕወጃ በኋላ “መለዮ ለባሾች የራሳቸዉን ድርጅት የማይመስርቱበት ምክንያት የለም” በማለት ለሻለቃ መንግስቱ ምክር የሰጠበትና በአደረጃጀትም የቀረበበት ዶ/ር ሠናይ ልኬ ነበር” ካለ በኋላ በመቀጠልም “የዶ/ር ሠናይ ስሌት፤ ሻለቃ መንግስቱ በሚፈጥሩት ድርጅት ዉስጥ የራሱን [የወዝሊግ] አባሎች በመሰግሰግ፤ [አብዮታዊ ሰደድን] ለመቆጣጠርና እንዲያም ሲል ለሥልጣን ለመቅረብ እችላለሁ የሚል ነበር›› (ገጽ 362) በማለት የዶ/ር ሠናይ ልኬ የሥልጣን ጥማት ምን ያህል ጥልቅ አንደሆነ ገልጿል። እንዲያዉም ንዑስ የደርግ አባላት በሚባለዉ ስብስብ ዉስጥ በዶ/ር ሠናይ ልኬ የተመለመሉ ቀላል ቁጥር ያልሆነ የወዝሊግ አባላት የሆኑ ወታደሮች እንደነበሩበት ተገልጿል።

ይህ በዚህ እንዳለ የዶ/ር ሠናይ ልኬ ከደርጉ መሪ ጋር መሞዳሞድ የቆየበት አገር የአሜሪካውን የዲሞክራሲ ልምድ ያላጋራ ሲሆን፤ እንዲያውም ከመስከረም 2፣ 1967 በኋላ፤ ከደርግ ሥልጣን መቆናጠጥ በኋላ መጠነኛ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ታይቷል ቢባል እንኳን የአዲስ

ዘመን ጋዜጣ ለነገር ይሁን ለበጎ ጉዳይ፤ አስተናግዶት የነበረዉ <የአብዮት መድረክ> የተሰኘዉ አምድ በዲሞክራሲ መብቶች፣ በብሔር ጥያቄ፣ በመንግስትና በመንግስት ሥልጣን አያያዝ እንዲሁም በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ይደረግ የነበረዉ ሰፊና ይፋ ክርክሮች በስተቀር ለመተንፈስ እንኳን ዕድል የሰጠበት ጊዜ አልነበረም። ከፍ ሲልም አንድም የፖለቲካ ድርጅቶቹ ከሚያራምዱት የፖለቲካ አቋም የተነሳ፤ በሌላም በኩል ከደርግ አፈና የተነሳ በወቅቱ የነበሩ ድርጅቶች ሊታረቁ በማይችሉ በሁለት ተቃራኒ ጎራዎች መከፈላቸዉ ተረጋገጠ። ሻዕቢያና ሕወሓት በጀመሩት ጥምረት ለኤርትራና ትግራይ ነፃነት ጦር መስበቃቸዉን ተከትሎ፤ ኢሕአፓም ገና ከጠዋቱ ለሻዕቢያ ከፈረመዉ ‹‹የኤርትራ የኢትዮጵያ የቅኝ ግዛትነት›› ፍጥምጥም መላቀቅ ባለመቻሉ የነሱን ጎራ ተቀላቀለ። ምናልባት እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር ኢሕአፓ ለትጥቅ ትግሉ ሰሜኑን የአገሪቱን ክፍል የመረጠ በመሆኑና ሻዕቢያና ሕወሓት ደግሞ መሠረታቸዉን የጣሉበት እዚያው አከባቢ ስለሆነ፤ ከነዚያ ድርጅቶች ጋር ቅራኔ ወይም ግጭት ዉስጥ ላለመግባት የኤርትራን ጥያቄ መቀበሉና ወደዚያ ጎራም መቀላቀሉ ከታክቲክ አንፃር ትክክል ሊመስል ይችላል። ሆኖም ግን ሻዕቢያ ከመጀመሪያ ጀምሮ ሕወሓት ደግሞ በተከታይነት ኢትዮጵያዊነት ምንም የማይመስላቸዉ (ምንም እንኳን ሕወሓት ወደኋላ ላይ የአቋም ለዉጥ አድርጌያለሁ ብልም)፤ ኢሕአፓ የታክቲክም ሆነ የስትራቴጂ መቀየስ ላይ ችግር ነበረበት ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም፤ ዘላቂ የአገር ጉዳይን ለታክቲክ ብሎ ለሌላ አካል ጥቅም አሳልፎ መስጠት ተገቢም ተመራጭም አይደለምና ነዉ። ሁለተኛዉን ጎራ የያዙት ደግሞ በኋላ ላይ መጠሪያቸዉን የለጠፉ ደርግ/ሰደድ፣ ወዝሊግ እና ማሌሪድ ናቸዉ። እነዚህ ሁሉም በአንድ ላይ ከተመቸ በደርግ/ሰደድ ኃይል የሚዋጡ፤ ካልሆነም ተራቸዉን ጠብቀዉ እንደኢሕአፓ እንዲመቱ ተራ የተያዘላቸዉ ድርጅቶች እንደነበሩ ውሎ አድሮ ከደረሰባቸዉ የመመታት ዕጣ ፋንታ ለመረዳት ተችሏል።

እንግዲህ የነዚህ ድርጅቶች ሕልዉና ያልጣመዉ ደርግ በወዝሊግ እና ሰደድ ግፊት የህብረት ኮሚቴ በማቋቋም የካቲት 18 ቀን 1969 የጋራ

መግለጫ በማዉጣትና ሐምሌ 12 ቀን 1969 መተዳደሪያ ደንብ አጽድቀዉ፤ በዚህም የኢትዮጵያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች ህብረት/ኢማሌድህ ተመሠረተ። መስራቾቹም የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል/ኢጭአት፣ መኢሶን፣ ወዝሊግ፣ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሽናዊ ድርጅት/ማሌሪድ እና አብዮታዊ ሰደድ ናቸዉ። ከኢጭአትና ከመኢሶን በስተቀር ሁሉም ብዙ የሰፋ ታሪክ የሌላቸዉና አንዳንዶቹ እንዲያዉም ከመኢሶን ወይም ከኢሕአፓ ተሰፈንጣሪ ስብስቦች የነበሩባቸዉ ናቸዉ።

ከዶ/ር ሰናይ ልኬ እና መንግስቱ ኃይለማርያም መቀራረብ የተነሳ ወዝሊግ እና ሰደድ አንድም ሁለትም ናቸዉ ብሎ መናገር ይቻላል። ምክንያቱ ደግሞ ዶ/ር ሠናይ ልኬ የፖለቲካ ድርጅት መፈልፈያ ማሽን (incubator) ያለዉ ይመስል አሜሪካ ውስጥ ከጀመረው ከመኢሶን ምስረታ እስከ ወዝ ሊግና አብዮታዊ ሰደድ ምስረታ ውስጥ እጁን የከተተ ሰው ነበር። በሌላም በኩል ‹‹መሸጥን የለመደ እናቱን ያስማማል›› እንደሚባለዉ ተረት ከመኢሶን ወደ ወዝሊግ፣ ከወዝሊግ አብዮታዊ ሰደድ የተባለዉን ድርጅት አመሰራረት ላይ ለሻለቃ መንግስቱ ምክር ሰጪ እና ሥልጣን ለመጋራት ፈላጊ ሰዉ እንደነበረ ይታወቃል። አብዮታዊ ሰደድ በታህሳስ ወር 1969 ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያምን፣ ለገሠ አስፋዉና ታምራት ፈረደን ይዞ ብቅ ያለ ድርጅት ነዉ ቢባልም፤ አብዮታዊ ሰደድ አዲስ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን ደርግ እራሱ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ዶ/ር ሠናይ ልኬን በመሳሪያነት ተጠቅሞ ለመሄድ የወጣለት የዳቦ ስም እንጂ የተለየ ታሪክ የሚፃፍለት ድርጅት አይደለም።

ኢማሌድህን ከመሠረቱት አንዱ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል/ኢጭአት ከ1966 አብዮት ፍንዳታ በኋላ የተመሠረተ እንደነበር ቢገለጽም፤ የፖለቲካ አቋማቸዉ የብሔረሰቦች መጨቆን ላይ ትኩረት ሲያደርጉ የነበሩ ምሁራን የተሰባሰቡበትና ምናልባትም በ1950ዎቹ መጨረሻ አከባቢ የብሔር ነፃነት ትግል ድርጅትን ይዘው የተነሱ ሰዎች

የነበሩበት ነው። የዚህን ድርጅት የመመስረቻ ጊዜን ከ1966 ወዲህ ብሎ መደምደም በቂ አይሆንም። ነገር ግን ለኦሮሞ ነፃነት ትግል የጀመረዉ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ የሕቡዕ ድርጅቱን ተልዕኮ የሚወጡና በኢትዮጵያ ተማሪዎችና ወጣቶች ትግል ዉስጥ ስማቸዉ በጉልህ የሚጠራ እነ ባሮ ቱምሳ፣ ዘገየ አስፋዉና አሰፋ ጩቦ የመሳሰሉ ሰዎች ይገኙበታልና ነዉ። ከአስተዋጽኦ አንፃርም ዘገየ አስፋዉ በ1967 የወጣዉን የመሬት አዋጅ በማዘጋጀት ጉልህ ሚና የተጫወቱ፤ ከ1966 አብዮት ፍንዳታ በፊትም ከኦሮሞ የነፃነት ግንባር ጋር የተገናኘ የትግል ልምድ እርሾ የነበራቸዉ ናቸው።

ስለኢጭአት ከኢማሌድህ መወገድ ስናነሳ በጥቂቱም ቢሆን በወቅቱ ስለነበሩት የኦሮሞ ታጋዮች ማንሳቱም የግድ ሳይለን አይቀርም የሚል እሳቤ ይኖረኛል። በኢጭአት አመራር ዉስጥና በኦሮሞ የትግል ታሪክ በተለይም በኦሮሞ ነፃነት ግንባር ታሪክ ዉስጥ እንደ አርአያ የሚቆጠረዉ ባሮ ቱምሳ በመረዳጃ ማህበርነት በ1955 በተመሠረተዉና የኦሮሞን የብሔርተኝነት ንቅናቄን ከፍ ባደረገዉ የመጫና ቱላማ መረዳጃ ማህበር አባል ከመሆኑም በተጨማሪ፤ የአሃዳዊነት አስተዳደር ሥርአት ሥር በሰደደበት አገር ዉስጥ የብሔር ፌዴራለዝምን ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበ በሳል ምሁር ከመሆኑም በተጨማሪ፤ የታላቁ ስሜ ጥር ሃይማኖት መሪና ብሔረተኛ የቄስ ጉዲና ቱምሳ ወንድም በመሆኑ፤ እንደዚያ በተቀነባበረ ሁኔታ መገደሉና ኢጭአትም ከኢማሌድህ አባልነት መወገዱ የኢጭአት ታሪክ እንዲሁ አጭር አለመሆኑን ያመላክታል።

ከተነሳ አይቀር የባሮ ቱምሳን ማንነት ለመግለፅና የተገደለበትን ምክንያት ለመዳሰስ ቢያስፈልግ ጥቂት የታሪክ ማስረጃዎችን ከባህር የመጭለፍ ያህል አድርጎ ማሳየት ይቻላል። ይኸዉም ባሮ ቱምሳ ከ1964 እስከ 1965 ለሦስት ዓመታት ያህል የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ተማሪዎች ፕሬዝዳንት በመሆን ያገለገለ ነበር። በ1966 በዚያ በአፍላ እንቅስቃሴ ወቅት በአዲስ አበባ የሚገኙ ዩኒቬርሲቲዎች ህብረት ዋና ፀሐፊ ሆኖ ከማገልገሉም በተጨማሪ እስከዛሬም ድረስ ለማድረግ ያልተሳካዉን ወይም ሊሳካ

የማይሞከረውን የኦሮሞ ተማሪዎች፣ ወታደሮችና የፓርላማ አባላትና ምሁራን በመሀከላቸዉ ትብብር በመፍጠር የኦሮሞ ብሔርተኝነት ድርጅት እንዲፈጥሩ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተ ሰዉ ነበረ። የፀረ ፊዉዳል ትግል እንዲጎለብት ግንባር ቀደም ሚና የተጫወተዉ ባሮ ቱምሳ በአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ዉስጥ ጭቆናን የሚቃወም ጋዜጣ "Voice Against Tyrrany" የሚል ማሳተም ችሏል። ላቅ ባለ ደረጃም የሳባ ፊደላት ለአፋን ኦሮሞ ቋንቋ አጻጻፍ የማይመች መሆኑ ቀደም ብሎ የታወቀ ቢሆንም፤ ለአፋን ኦሮሞ ሰዋሰዉና ጽሑፍ የሚመች ፊደል ለመቅረፅ በተደረገዉ ትግል ዉስጥ ከወንድምየዉ ጉዲና ቱምሳ ጋር በመሆን ወጣቶችን እስከ ውጭ አገር ልኮ ለማሰልጠን ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ ሰው ነዉ። የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን መሠረት ለመጣል በተጠራዉ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ ከተገኙት የኦሮሞ ልጆች ዉስጥ ባሮ ቱምሳ ቀዳሚ እንደነበረ ይታወቃል።

ከ1966ቱ አብዮት ፍንዳታ በኋላም ባሮ ቱምሳ የኃይሌ ሥላሴ መንግስት ባለሥልጣኖች ወንጀሎችን ለመመርመር በደርግ በተቋቋመዉ አጣሪ ኮሚሽን ዉስጥ አባል የነበረ ቢሆንም፤ የደርግ አጀማመርና ጉዞ ከወዲሁ ያላማረዉ ባሮ ቱምሳ፤ አጋር ከሆኑና አሰፋ ጨቦ ከመሳሰሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ወገኖች ጋር ኢጭአት (የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል) የተባለዉን ድርጅት በሕጋዊ መድረክ ያቋቋመ ሰዉ ነበር። በከልቻ ኦሮሞ ተብሎ ይታወቅ የነበረዉን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ልሳን የሆነዉን መሠረት የጣለ ባሮ ቱምሳ መሆኑ ሲታወቅ፤ ይህ ሰዉ ዜጎቹን ነፃነት ለማጎናጸፍ ምን ያህል ብሩህ አእምሮ እንደነበረዉ የዛሬዉ ወጣት አንድ አፍታ ተመልሶ ዓርማዉን ሊያነሳ የሚገባ ሰዉ ነዉ። እንዴዚህ ያለና ሌሎችንም አንፀባራቂ ታሪክ ያላቸዉን ሰዎች በግድያ፣ በእስራት ወይም በሌላ ሰበብ ከመድረክ ለማጥፋት ምቀኞች፤ የማይቧጥጡት ቋጥኝ፣ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ የትናንትና ብቻ ሳይሆን የዛሬም ዕውነታ ጭምር እንደሆነ በተግባር የታየ ድርጊት ነዉ።

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት/ማሌሪድ ለኢማሌድህ ምስረታ

አባልነት የበቃዉ ከተለያዩ ድርጅቶች፤ በተለይም ከኢሕአፓና መኢሶን መልስ ተንጠባጥበዉ ከተገኙት ግለሰቦች በ1968 የተገኘ ድርጅት ነዉ ለማለት ይቻላል። ከብርሃነ መስቀል ረዳ ጋር የቆሙ የኢሕአፓ አባላትን እንደተኙ ሌሊት ተለይቶ ከዛላ አንበሳ የተሰወረዉ የእነ ተስፋዬ መኮንን ቡድን፤ አስመራ ገብቶ እራሱን አዲስ አበባ ላይ እንዳገኘ ይታወቃል። አዲስ አበባ ዉስጥ ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ‹‹ያዳቆነ ሰይጣን›› የሆነበት ተስፋዬ መኮንን ሌላ ፓርቲ መስርቶ ወደ ሥልጣን የሚያደርገዉን ጉዞ ለማመቻቸት ከተለያዩ የጥናት ክበቦች ጋር ዉይይት ሲያደርግ ቆይቶ ከላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ ማሌሪድ ተመሠረተ።

በአካል ካሉት ዜጎች ለማረጋገጥ እንደሚቻለዉ ተስፋዬ መኮንን ያሰባሰባቸዉ የማሌሪድ አባላት አንድም ከኢሕአፓ አሊያም ከመኢሶን አንፃር የነበሩትን እያባበለ መዉሰድ እንጂ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ትምህርት ወይም በሌላ አሰልጥኖ የፈጠራቸዉ ሰዎች እንዳልነበሩ ይታወቃል። ለምሳሌም የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ እና በወቅቱ አብረን የነበርን ወጣቶች ገና ከዕድገት በሕብረት የዕዉቀትና ሥራ ዘመቻ መልስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እያለን፤ ለፖለቲካ ንቃተ ሕሊናም ከመኢሶን ጋር እያሟሟቅን ሳለን ነበር የኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ተወላጅ የነበረዉ ድቤኩሉ ላቀዉ የተባለዉና በኋላ በደርግ ቀይ ሽብር የተገደለዉ የአንድ አውራጃ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ከፍተኛ ካድሬ ሆኖ ከጂማ ወደ መቱ ይሄዳል። ይኼው ሰው እኔን ጨምሮ ሌሎች አባሎችንም ይመለምላል።

ከድቤኩሉ ላቀዉ መገደል በኋላ አዲሶቹ የማሌሪድ ተመልማዮች ግራ ተጋብተን እያለ፤ አሁን በሕይወት የሌለዉ ፍቃዱ ሻረዉ የሚባልና፤ በአሁን ጊዜ የት እንዳለ ከማላዉቀዉ እስራኤል መገርሳ ከሚባል ወጣት ጋር ወደ ኢሉባቦር ተመድበዉ መጡ። እነሱም የመጀመሪያዉ ታሪካቸዉ ከኢሕአፓ መልስ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ከመኢሶን እንደነበረ ወደኋላ ላይ ልንረዳ ችለናል። ከእነሱ ጋርም ውስን እንቅስቃሴ ስናደርግ ቆይቶ ፍቃዱ ከክፍለ ሀገሩ የደርግ ተወካዮች ጋር ባለመስማማት በ1970 አከባቢ

ሥፍራዉን ሲለቅ፤ እስራኤል መገርሳ የአንድ አዉራጃ ከፍተኛ ካድሬ ሆኖ ሲሰራ ከቆየ በኋላ፤ በዚሁ ክፍል ሥር የምናነሳቸዉ ከመኢሶን ፍርጠጣ የተመለሱት ካድሬዎች በወዝሊግ-ሰደድ ዘንድ መታመንን ለማግኘት ሲሉ ምንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ የማይሉት ማለትም አሰቃይተው እስከ መግደል የሚሄዱ ሰዎች እስራኤል መገርሳንም ሆነ ሌሎች የማሌሪድ አባላትን መከራቸዉን ስላበሉአቸዉ፤ እስራኤል መገርሳ አከባቢዉን ብቻ ሳይሆን አገሪቱንም ጥሎ እንደኮበለለ ወሬ ተሰምቷል። ስለዚህ እኔም ሆንኩ ሌሎች የማሌሪድ አባላትና ካድሬዎች አስተባባሪም ሆነ ተከላካይ ሳይኖረን የመኢሶን ምልስ የወዝሊግ- ሰደድ የወረዳና አውራጃ ከፍተኛ ካድሬዎችና አስተዳዳሪዎች መጫወቻ ሆነን ቆይተን የኢሠፓአኮ መቋቋምን ተከትሎ ለሥልጠና የካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ቤት መግባት በውስን ደረጃ ፋታ ሰጠን ወይም በኋላ በምገልጸዉ ዓይነት ሁኔታ በየቦታ ለሚገኙና የኢሠፓአኮን አመራር ለተቆጣጠሩት ሲቪል ለለበሱ የሰደድ ወታደሮችና አደገኛነታቸዉ ለከፋ ሰዎች ተላልፈን ተሰጠን።

የላይኛዉ የማሌሪድ አመራር እንደ ኢሕአፓ ተደራጅቶ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል የሚያልም ሳይሆን እንደ መኢሶንም ‹‹የሐቀኛ ኢትዮጵያዊያኖችን ድክመት በመጠቆም የሚታረሙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስብ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ለማዳበር በሚደረገዉ ትግል ዉስጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚጥር›› ብሎ ራሱን የካበ፤ በአብዛኛዉ አቋሙ ግን ከአድርባይነት ጋር የተቆራኘ፤ ኮሎኔል መንግስቱን ለማስደሰትም እያሰበ፤ ይህንንም በስልት ለመፈጸም የሚፈልግ ድርጅት እንደነበረ ይታወቃል።

የማሌሪድ አስተዋጽኦ አንድ ተብሎ የሚጠቀስ ነገር ቢኖር ኢማሌድህ ሲቋቋም መሪዉ ተስፋዬ መኮንን እራሱ እንደገለጸዉ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን ፀሐፊ ሆኖ የጽ/ቤቱን አሰራርና የወጪ ገንዘብ አያያዝ ሥነ ሥርዓት እንዲይዝ መጣጣሩን፤ እሱም ቢሆን፤ ጽ/ቤቱን በሞኖፖል ይዘዉ በነበሩት መኢሶንና ከመኢሶን በኋላ ደግሞ ለመያዝ

ክንዳቸዉን አፈርጥመዉ ከመጡት የወዝሊግ-ሰደድ ኃይሎች ቅቡልነትን ያላገኘ ነበር። በደርጉ/ሰደድ ለገሠ አስፋዉና እራሳቸዉን ለወዝሊግ-ሰደድ በርካሽ ዋጋ ከሸጡ የማሌሪድ አመራር አባላት መሰሪ ሴራ፤ ድርጅቱም ተሽመደመደ። ሌላዉ የማሌሪድ አስተዋጽኦ ይሆናል የሚባለዉ አንድ ፓርቲን ለማቋቋም ከየድርጅቶቹ በኮታ በተዉጣጡ አባላት ማዕከል ለመመስረት ተስፋዬ መኮንን ያቀረበዉ ሐሳብ ሲሆን፤ እሱም ገና መራመድ ሳይጀምር ተቀልብሶ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ቀደም ሲል ከዶክተር ሠናይ ልኬ ጋር በጀመረዉ የፓርቲ ጠቅላይነት በግለሰብነቱ የፓርቲ ምስረታዉ ማዕከል እንዲሆን ተወስኖ ተስፋዬ መኮንን እራሱ የተጠመደበትና ለእስርም የተዳረገበት ጊዜ ነዉ። በዚህ የተነሳ በማኩረፉም የማሌሪድ መሪ ተይዞ ወደ እስር ቤት ተወረወረ፤ ተስፋዬ መኮንን እራሱ ቀላል ሰዉ ስላልነበረ የተለመደዉን ስልት ተጠቅሞ ከእስር ቤት እንደወጣ በአምባሳደርነት ተሹሞ ወደዉጪ አገር ሄደ። የማሌሪድ ዕጣ ፋንታም የደርግ ጡቻ ከደረሰባቸዉ ኢሕአፓና መኢሶን ቀድሞ አከተመ። ከዚያ በኋላ የኢሕአፓም ሆነ የመኢሶን ያህል ወሬዉም ተመልሶ ሊሰማ ያልቻለ ብቻ ሳይሆን ማሌሪድ እንደተወለደ የሞተ የአስር ዓመት ድርጅት ነው ተብሎ መቃብሩ ላይ የሚፃፍለት ድርጅት ሆኖ ያከተመለት ነው።

መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብሎ የኢማሌድህ አንዱ መስራች አባል የሆነዉ መኢሶን ‹‹የትግል ስልት ለዉጥ›› በማለት ከነሐሴ 14 ቀን 1969 ጀምሮ ከደርጉም ከኢማሌድህም ተለየ። “ምክንያቱ ከኃጥያቱ ይከፋል” እንደሚባለዉ ተረት ዓይነት ሆኖ መኢሶን መንግስቱ ኃይለማሪያምን አብዮታዊ መሪ እንዳላለዉ ሁሉ፤ ከደርጉ የተለየበትን ሁኔታ የገለፀዉ ደግሞ “ከደርጉ ጋር ጊዜያዊ ትብብር የተደረገዉ በመሠረቱ የዲሞክራሲያዊ መብቶችን ከደርጉ ለመንጠቅ እንጂ ለአንድ መንግስቱ ኃይለማሪያም ማዕከልነት አገልጋይና መሳሪያ ለመሆን አልነበረም” በማለት ነዉ። እንግዲህ ለኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ/ኢሠፓ ምስረታ መነሻ የሆነዉ የኢማሌድህ ዕጣ ፋንታ በዚህ ከተጠቃለለ በኋላ፤ የደርጉ አብዮታዊ ሰደድ ዉርስ በአደረጋቸዉ ካድሬዎች ታጭቆ የኢትዮጵያ

ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽንን/ኢሠፓአኮን ወደ መመስረት ገባ። ዶ/ር መረራ ጉዲና ከላይ በተጠቀሰዉ መጽሐፉ ገጽ 68 ላይ አብዮታዊ ሰደድ “ከኢሕአፓ፣ ከመኢሶን፣ ከወዝሊግ፣ ከማሌሪድ፣ ከኢጭአት (ከሁሉም ማለት ይቻላል) አስገድዶ በመዉረስ ብቸኛና ያበጠ ገዥ ፓርቲ ሆኗል።” በማለት አስቀምጧል። በርግጥም የሰደድ አባላት በቤተመንግስትና በመለዮ ለባሾች አከባቢ የተወሰኑ ነበሩ ተብለዉ ከሚጠቀሱት በተጨማሪ፤ ከመኢሶን እና ኢሕአፓ የተመለሱ የቀይና ነጭ ሽበር ግርሻ (saddachoo) ያለባቸዉ አዋኪዎች የተኮለኮሉበት እንደነበር መግለፅ ዕዉነቱን እንጂ እንደ ዘለፋ የሚቆጠር አይሆንም።

ጭንጋፍ የደርግ የፓርቲ ምስረታ ጉዞን ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለመጨረስ የትም ሊደርስ እንደማይችል በጉልህ ይታዩ የነበሩ ክስተቶች ነበሩ። ከተለያዩ አቅጣጫዎች በተነሱበት የነፃ አዉጪዎች የዉጊያ ኃይልና በኢትዮጵያ ሕዝብ የዝምታ የትግል ስልት ደርግ/ሰደድ ኃይላቸዉ እየተዳከመ በመሄዱ መጠነኛ እፎይታ ተገኘ ቢባል እንጂ የኢሠፓአኮ መቋቋም ትርፉ ችግር ሆኖ ለትግሉም ሆነ ለአገሪቱ ዕድገት ያስገኘዉ አንዳች ጠቀሜታ አልነበረም። በሌላዉ ዓለም እንደሆነዉ ሁሉ አምባገነኖችና ፋሽስቶች የአገዛዝ ዕድሜያቸዉን ለማራዘም ሲሉ አንዱን በብዙሃን ላይ ለብዙ ጊዜ ሲያበረታቱ ይቆዩና የሚፈልጉት ነገር ተመቻችቶላቸዉ ሲያገኙት፤ ያ በብዙሃን ላይ ወንጀል ሲፈጽም የቆየዉንና ከሕዝብ ጋር ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ ዉስጥ የገባው ሕዝብ ይቅር የማይለዉ ወንጀል መፈጸሙን በድፍረት ሲገልጹለት፤ በስተመጨሻዉ በእሱም ላይ አስከፊ የሚባል እርምጃ ሊወሰድ ሲል እግሬ አውጭኝ ብለው ይፈረጥጣሉ።

ኢሕአፓ የኢማሌድህ አባል እንዳይሆን መኢሶን የበኩሉን ተፅዕኖ ካደረገና በተጨማሪም ደግሞ ኢማሌድህ በተመሰረተበትና ትግሉ የመስከን ባህርይ ያሳያል ተብሎ በሚጠበቅበት ጊዜ ከመጋቢት እስከ ነሐሴ 1969 ከአምስት ወራት የጊዜ ቆይታ በኋላ መኢሶን በራሱ መረጃ መርምሮ አገኘሁ በሚባል ሽፍጥ የኢሕአፓ ነፍስ ገዳዮች ናቸዉ ባላቸዉ

ላይ የቀይ ሽብር እርምጃ ካስወሰደ በኋላ ሲፈርጥጥ፤ መኢሶን በፖለቲካ በኩል ሕገ ወጥነትን፣ ከፖለቲካ አንፃር ደግሞ አናርኪስትነትን የተላበሰ በደርግ በኩል ደግሞ የመንግስት ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት ያለመቻልና የመምራት ጉድለት እንደነበረ በግልጽ ያሳየ ድርጊት ነበር ለማለት ይቻላል። መኢሶን ደርግን ለማስደሰትም ሆነ የተፈጥሮ ጠላቱ ያደረገዉን ኢሕአፓን ካጠፋ በኋላ፤ በተራዉ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ዉስጥ በደርግ ድራሹ ሊጠፋ ችሏል። መኢሶን ለሌላ አካል አጥልቆ ሲቆፍር በቆየዉ ጉድጓድ ዉስጥ ገብቶ ዳግም ላይወጣ እዚያዉ ተደመደመበት። ሌላዉ ቢቀር ‹‹ኢትዮጵያዊ ልማድ ወይም ባህል›› የሚባለዉን የከንፈር መጠጣ እዝን እንኳን ለመኢሶን ያሳየዉ ሰው አልነበረም።

ደርግ የሥልጣን ዕድሜዉን ለማራዘም እንደሚፈልግ ገና ንጉሱን ከዙፋን ከማዉረዱ በፊት ጀምሮ እንደነበረ የሚያሳብቁበት ሁኔታዎች እንደነበሩ ከላይ መግለጼ ይታወሳል። በዚሁ መሠረት መኢሶን ተወግዶ የዓመት ዕድሜ እንኳን ሳይቆጠር ‹‹ሰርገህ ገብተህብኛል›› በማለት በወዝሊግ ላይ ሰደድ እራሱ ወንጅሎ እራሱ በወሰደዉ እርምጃ የአብዮቱ ኃይሎች ነን የሚሉት ወገኖች እንደገና ተባልተዉ አለቁ። ስለሆነም፤ ከሐምሌ 8 ቀን 1971 እስከ ሕዳር ወር 1972 ድረስ ኮሎኔል መንግስቱን ማዕከል አድርጎ ከኢማሌድህ ወደ ኢሠፓአኮ በተደረገዉ ሽግግር ዉስጥ የቀሩት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ምናልባት ለወሬ ነጋሪነት በሚባል ሁኔታ ጥቂት የማሌሪድና የወዝሊግ ግለሰብ አባላት ካልሆኑ በስተቀር፤ አብዮታዊ ሰደድ እና አብዮታዊ ሰደድ ብቻ ነበሩ። በዚህም በአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ውስጥ በስውር ብቅ ያለው የፓርቲ ፖለቲካ በደርግ ውስጥ በቀይ ሽብርና ተመሳሳይ ጥልፍልፎች ቀጭጮ አረፈው።

በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ ዉስጥ የኢማሌድህ ተልዕኮ የቱ ጋ እንደተጀመረና የቱ ጋ እንደተፈፀመ አይታወቅም ነበር ቢባል ግርምታን አይፈጥርም። ምክንያቱን ከአባል ድርጅቶቹ በኮታ ፓርቲ ይመሠረታል ተብሎ ሲጠበቅ መንግስቱ ኃይለማሪያም ከየት መጣ ሳይባል ጣልቃ

ገብቶ የፓርቲ ምስረታዉ ማዕከል ሆኖ ሁለቱንም የመንግስትና የፖለቲካ አካላት መዋቅርን አጣምሮ በመያዝ የታለመው የኢማሌድህ ውል እንዲጠፋ አድርጓል። እንግዲህ ኢማሌድህ ራሱ ወደ ፓርቲ ሊሸጋገር ወይም ፓርቲ ሊያደራጅ እንደሆነ ለማስረዳት አለመቻል ቢያስወቅሰኝም እንደማያስወነጅለኝ እርግጠኛ ነኝ። ለማንኛዉም ግን ኢማሌድህ ያደረገዉ ነገር ቢኖር ከማሌሪድ ወይም ከመሪዉ ተስፋዬ መኮንን እና ከሁሉም ድርጅቶች በኮታ ለማቋቋም የተጠነሰሰዉ ሐሳብ ከሽፎ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም አንድ ግለሰብ የፓርቲ መስራች ድርጅት ማዕከል ሆኖ ኢትዮጵያን የሚመራ ፓርቲ ለመመስረት አንድ ኮሚሽን ማለትም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) ሕዳር 12 ቀን 1972 በአዋጅ ተቋቋመ። የዚህ አዋጅ መዉጣት በራሱ የተለየ ትርጉም ያለዉ ባይሆንም ቀደም ሲል ተጀምሮ የነበረዉን ጥብቅ ማዕከላዊነትን ይበልጥ ያጠበቀ፣ የብዙሃን ፓርቲ ጥንስስ እንዲኮሰምን ብሎም ጨርሶ እንዲጠፋ ላቅ ካለም ኢትዮጵያ የምትባል አገር የተለያዩ ልጆቿን የልዩነት ሐሳብ አስባስባ ማስተናገድ ወይም መጠቀም የማትችል አገር መሆኗን የደመደመ ነበር።

በኢሠፓአኮ የምስረታ ሂደት ዉስጥ ደርግ ከሁለት አቅጣጫ ሰንጢቃ እንጨት ዉስጥ የገባ ዓይነት ነበር። በአንድ በኩል በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ጦርነት የተባባሰበትና ከኢማሌድህ እስከ ኢሠፓአኮ ያለዉ በካድሬዎች መካከል የነበረዉ ግንኙነት ራሱ መናቆር የነገሰበት ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ ዉስጥ የቀድሞ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና በሥሩ ያቀፋቸዉ ሠራተኞችና ካድሬዎች ከሥራቸዉ የበለጠ በመንደራቸዉና በየመሸታ ቤቱ ተሰባስበዉ በወሬ ተጠምደዉ እንዲቆዩ ሲደረግ፤ የደርግ አባላቱ ገደብ የለሽ ሥልጣን ተጨምሮላቸዉ ‹ጓድ እገሌ/እገሊት የኢሠፓአኮ አባል የዚያ ክፍለ ሀገር ኢሠፓአኮ ተጠሪና የዚያ ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ፣ የክፍሉ የአብዮትና ምርት ዘመቻ አስተባባሪ› እየተባለ ሲሿሿሙ መኪናቸዉ ገበያ መሀከል ሲያልፍ ሳይቀር ፍጥነቱን ሳይቀንስ የሚነጎድበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዉ እንደነበረ እናስታዉሳለን። በተለይም ከኢሠፓአኮ የመጀመሪያ ጉባኤ በኋላ ልክ መንግስቱ ኃይለማሪያም

በአገር አቀፍ ደረጃ የፓርቲ ምስረታዉ ማዕከል እንደሆነ ሁሉ፤ የየክፍለ ሀገሩ የመጀመሪያ ጉባኤ ተሳታፊዎችም እራሳቸዉን የየመጡበት ክፍለ ሀገር ማዕከል አድርገዉ ራሳቸውን ክበዉ በማስቀመጥ የሰዉን ፍዳ አራዝመው የሰዉን ዕድሜ ያሳጠሩበት ጊዜ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

እንደ ፖለቲካ ድርጅት ከሕዳር 1972 ዓም ወዲህ እራሱን በክፍለ ሀገር ደረጃ ማጠናከር፣ ሊኖረዉ ለሚፈልገዉ የሰዉ ኃይል ሥልጠና መስጠትና እግረ መንገዱንም ጭዳ የሚሆኑ ወይም የሚወገዱ ሰዎችን ቀለል ካለም በማራቅ ከበድም የሚል ከሆነ ሰበብ አሰባብ ፈልጎ አብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ/አዘአኮ በሚባል ከተለያዩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች በተዉጣጣ ኮሚቴ ዉሳኔ በማሳሰር ሥራ የበዛበት ነበር፡፡ የጠላት ብዛትን በሐሳብ ብልጫ በቁጥር ለመቀነስ አስበዉም እንደሆነ ወይም በቀዉጢ ወቅት ሊጠቀምባቸዉ አስበዉ እንዲሁ አይታወቅም፤ ቀድሞ በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሥር በተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ሥር ይንቀሳቀሱ የነበሩና ታፔላ ተለጥፎላቸዉ በአዘአኮ ተፈርዶባቸዉ እስር ቤት የነበሩ ሳይቀሩ ተሰብስበዉ ከታህሳስ 1973 ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ሥልጠና በየካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ቤት በማስገባት እስከ ሰኔ ወር 1973 አሰልጥኖ በተለያዩ የመንግስት ድርጅቶች ዉስጥ የኢሠፓአኮ ተጠሪዎችና ፓርቲ መስራች አስኳል አድርጎ መድቧል፡፡

እነዚህ የኢሠፓአኮ አስኳል የሚባሉ ተመዳቢዎች ያጋጠማቸዉ ችግር ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ እንዲያዉም የኢሠፓአኮ ጉዳይ ማስፈፀም ቀርቶ ሕልዉናቸዉ ራሱ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ ገብቶ እንደነበረ ዛሬም ሕያዉ ምስክሮች ሆነዉ የሚገኙ አሉ፡፡ አንዳንዶች ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ ቀጥታ ወደ አገሪቱ ዋና መዲናና ትልልቅ ከተሞች ለመጀመሪያ ጊዜ የወጡ በመሆናቸዉ፤ ብዙም ሳይቆዩ የያዙት ጥሪት አልቆባቸዉ የአባልነት ደብተራቸዉን እያሳዩ በረንዳ አዳሪዎች እንዲሆኑ ተገደዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ በትምህርት ደረጃቸዉ ገና ከአንደኛ ደረጃ ወይም ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች በላይ ሳይሆኑ ወይም ከዲያቆንነት ሳይወጡ፤ በተወለዱበት ሕብረተሰብ ዉስጥ ሆነዉ ደርግን እንዲያገለግሉ ታስበዉ

ተመልምለዉ የነበሩት፤ በአንድ ጊዜ ምንም በማያዉቁት የከተማ ኑሮና የከተማ ነዋሪዎች መሀከል ሲገቡ ውሉ የጠፋ ሊቃቂት ሆነዉ ሰማይ ምድሩ ዞሮባቸዉ እንኳንስ ማዕከል ሆነዉ ኢሠፓአኮን ማደራጀት ቀርቶ እራሳቸዉ አደራጅ ፈላጊዎች እንደነበሩ አስታዉሳለሁ።

ቀላል ቁጥር የማይባለዉን ካድሬ ደግሞ ሌላ ያጋጠማቸዉ ጉዳይ ነበር። ይኸዉም በኢሕአፓ ተቀርፀዉ በደርግ ዲሞትፎር አንገታቸዉን የደፉ እሳት የላሱ የኢሕአፓ ሰዎች የኢሠፓአኮ አደራጆቹን በጥያቄ ሲያጣድፏቸዉ፤ ስለማያዉቁት ነገር የማያዉቁትንም ሆነ ከነሱ የበለጠ የሚያዉቁትን ለማስተማር የመጡ ስለሆነ ፍጥጫ ዉስጥ ገቡ። ሌሎችም ከየተመደቡበት ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ቀና አቀባበል ያላገኙ ነበሩ። አንዳንድ የሥራ ኃላፊዎች ወር አልፎ ደመወዝ ለመክፈል እንኳን በአደራጆቹ ስም የተያዘ በጀት እንደሌላቸዉና ከነሱ ዕዉቀት ዉጪ የተመደቡባቸዉ ስለሆነ፤ የተላከላቸዉን ሰዉ ያህል መቀበል እንደማይፈቅዱ ቁጣ በተቀላቀለበት ስሜት ሲናገሩ፤ አብዮቱም ሆነ የኢሠፓአኮ ሥርፀት ገና ያልተጀመረ መሆኑንና እንዲያዉም አንዳንድ በታ ላይ ገና ሳይጀመር ያበቃለት ሁኔታ መሆኑን ያሳይ ነበር። በጣም አሳዛኙ ነገር ደግሞ አስፈላጊ ሁኔታዎችን አስቀድሞ እንዲያመቻች የተመደበዉ የአዉራጃና የአዲስ አበባ የቀጣና ኢሠፓአኮ ጽ/ቤቶች ማን የት እንደተመደበ፣ ወይም ምን ለመስራት እንደታሰበ የማያዉቁ እንደነበሩ ዛሬም ትዝታዉ ያልጠፋቸዉ ሰዎች ይኖራሉ። ከዚህ ሁሉ ድክመት ጋር ኢሠፓአኮ በጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም ማዕከልነት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን የሚያደራጅ ተብሎ በተለይም የኮሚሽኑ ጽ/ቤቶች የአሰራር ዝርክርክነት ታክሎበት፤ አንዳች የረባ ነገር ሊመጣ እንደማይችል በግልፅ ያሳይ ነበር። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ/ኢሠፓ አደረጃጀቶችን የገጠሙት ችግሮች እንደተጠቀሱ ሆነዉ፤ በዚሁ አደረጃጀት ዉስጥ አንዱ የታሰበዉ ሕዝባዊ ማህበራትን፣ የወጣትና የሴቶች ማህበራትን፣ እንዲሁም የሙያና የሠራተኛ ማህበራትን በአዲስ መልክ በፓርቲዉ አምሳያ አጠናክሮ ማደራጀት አንዱ ቅድመ ግዴታ መሆኑ ነበረ።

የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትን፣ የገበሬ ማህበራትን፣ የወጣትና ሴቶች ማህበራትን፣ ሰበነክ ማህበራትን፣ የሙያ ማህበራትና የሠራተኛ ማህበራትን ጠቅላላ አባላት እየሰበሰቡ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታና የኢሠፓአኮን ተልዕኮ በማስረዳት መሪዎቻቸዉን እንዲመርጡ ብለን ካስተማርን በኋላ፤ እነሱ ፈልገዉ የሚመርጡትን አስቀርተን፤ እኛ በድርጅታዊ ሥራ የምንመርጥላቸዉን አሳልፈን ለተላክንበት የፓርቲ አካል (ኢሠፓአኮ/ኢሠፓ) ሪፖርት እናቀርባለን። ይህ ሁሉ የዉይይት ክበብ የሚባለዉ ላይ ሳይቀር ተፈፃሚ ነበር። ትልቁ ችግር የሚፈጠረዉ በድርጅታዊ ሥራ እንዲመረጥ የተባለዉ ሰዉ ከመራጮች በሚፈጠረዉ ተቃዉሞ ወይም ጉምጉምታ አሊያም ከአስመራጩ ካድሬ ፍላጎት ማጣት የተነሳ ሳይመረጥ የቀረ እንደሆነ ነዉ። ይገጥማል የሚባለዉ ችግርም አንደኛ እንዲመረጥ የተባለዉ ሰዉ መሠረቱን የጣለዉ ከቀጣናዉ ወይም ከፍ ብለዉ ካሉት የኢሠፓአኮ ባለሥልጣናት ጋር በጓደኛነት ወይም በቤተዘመድ ግንኙነት ስለሚኖረዉ አልፎ ተርፎም በአብዮቱ ሂደት ዉስጥ በኢሕአፓ ወይም መኢሶን ላይ በተወሰደዉ ዕርምጃ ዉስጥ እጁ ላይ የደም ወንጀል ያለበት ይሆንና ሞራል ሊሰጠዉ ታስቦ አንድ ቦታ ላይ ተወሽቆ ገቢ እያገኘ እንዲኖር በመፈለጉ፤ ድርጅታዊ ሥራ ተሰጥቶት እንዲያስመርጥ፤ ነገር ግን ድርጅታዊ ሥራዉን ያልተወጣ ካድሬን የኢሕአፓ ወይም የመኢሶን ርዝራዥ አድርጎ ማስወንጀል ለነሱ ቀላል ሥራ ነበር። አንዳንዱ ደግሞ መከራ ታይቶ ተመርጠሃል ተብሎ ማስታወቂያ ላይ ስሙ ተለጥፎ የተሰማዉን ስሜት ሲገልፅ ቅሬታን ለመግለፅ ፊቱን አስረዝሞ ይቀርባል። ምን እንደነካዉ ሲጠየቅ የተፃፈልኝ ድምፅ ብዛት ያንሳል ብሎ በሣቅ ፍርስ የሚያደርግ ስሞታ ይናገራል። በዚሁ የተነሳም ለአቤቱታ እስከሚግባባቸዉ የበላይ ባለሥልጣኖች ቤት ወይም ቢሮ ድረስ ይሄዳል።

መቼስ ምርጫ ማለት አይቀርምና ምርጫ በሚደረግበት ወቅት ላይ ብቻ ሳይሆን የዉይይት ክበቦች ሲሰበሰቡ ጭምር ማዕከል የተባሉ ካድሬዎች በእያንዳንዱ ሰዉ እንቅስቃሴ ላይ ክትትል ያደርጋሉ። አሰስ ገሰሱንም

ወዲያዉኑ ሪፖርት ያደርጋሉ። አንድ ጊዜ የሆነዉን ልንገራችሁ። ባልታወቀ ምክንያት አንዲት ልጅ ዉይይት ክበብ ስብሰባ ላይ ቁጭ ብላ መጠነኛ የጩሄት ድምፅ ታሰማለች። ተሳታፊዎች በነገሩ ተደንቀዉ በሳቅ ይታፈኑና ዉይይቱ ሊቀጥል ባለመቻሉ የሻይ ዕረፍት ተብሎ ለትንሽ ጊዜ ይቋረጣል። ሰላሳ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ በስልክ ትፈለጋለህ ተባልኩ። ሄጄ መልሼ ደዉዬ ሳነጋግር የቀጣናዉ ኃላፊ የዉይይት ክበብ አንዱ ቡድን መቋረጡ ሪፖርት እንደደረሰዉና በአስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃ እንድወስድ ያዘኛል። አባላቱ ወደ መሰብሰቢያ ቦታቸው እንዲመለሱና ልጂቱ የሆነዉን ነገር እንዲትነግረን ጠየቅናት። እሷም በሰጠችው ቃል ከአየሩ ሁኔታ መጫጫን እንደሆነ አላወቀችም፤ ትንሽ እንቅልፍ እንደተጫጫናትና በእንቅልፍ ልቧም አንድ ቀንድ ያላት ላም ሊትወጋት እንደመጣችባትና ከላሚቱ ለመሸሽ ሲትል የሆነ ድምፅ እንዳሰማችና ድምፅ ማሰማቷንም በሻይ ዕረፍቱ ላይ ጓደኞቿ እንደነገሯት ግልፅ አድርጋ ነግራን ነገሩ በዚሁ ተቋጨ።

ሌላዉ ችግር የሚከሰተዉ ድርጅታዊ ሥራዉን ከሰጠዉ ሰዉ አከባቢ ነዉ። የብዙሃን ማህበራት ምርጫ ተከናዉኖ ሳያልቅ፤ በድርጅታዊ ሥራ ስሙ የተሰጠዉ ሰዉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ይኑረዉ አይኑረዉ ምንም ግንዛቤ መዉሰድ ሳያስፈልግ፤ የበላይ አካል ብሎ ለሚጠራዉ ሪፖርቱን ስለሚልክ የድምፅ ብዛቱ እንኳን ሳይቀር ተዛብቶ እንዲገኝ አይፈቀድም። እኔ በነበርኩበት የአዲስ አበባ ከተማ ቀጣና ሦስት ኢሠፓአኮ ጽ/ቤት ተብሎ በሚታወቀዉ ሥር በዚህ በድርጅታዊ ሥራ ሰዉን የማስመረጥና ሰዉን ሥልጣን ላይ የማስቀመጥ ገደብ የሌለበት የቀጣና ሦስቱ ኃላፊ የመቶ አለቃ ገስጥ ተጫኔ ነበር። ገስጥ ተጫኔ የደርጉ የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ፀሐፊ የነበረና በጨካኝነቱ ከመንግስቱ ኃይለማሪያ ይቀጥላል የሚባለዉ የሃምሳ አለቃ ለገሰ አስፋዉ የቅርብ ጓደኛ እንደነበረ ይነገርለታል። ዋናዉ ጉዳይ ገስጥ ተጫኔ ድርጅታዊ ሥራ ሰጥቶ ሳይፈፀም ቀረ ማለት የቁም ስቅል ማየት ነዉ። ድርጅታዊ ሥራዉን ያልተወጣዉን ካድሬ መሳሪያ አንስተዉ ደርግን ከሚቃወሙት ጋር ይፈርጃል። ቢያንስ ከአንድ በላይ ሰላዮች

ይመደብበታል።

የኢሠፓ መመስረቻ ጉባኤዎች በሚካሄድበት ጊዜ ድርጅታዊ ሥራን ያልተወጣ አባል ከጉባኤዉ እንዲገለል ያስደርጋል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ዉስጥ ከድርጅታዊ ሥራዎች ጣጣ ስላልወጣንና ልንወጣም የምንችል ስላልመሰለኝ ሁለት ነገሮችን ሊመርቅላቸሁ። አንድ ጊዜ መሠረታዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ እንዲመረጥ አሁንም ከመቶ አለቃ ገስጥ ተጫነ ድርጅታዊ ሥራ ይሰጣል። እንዲመረጡ የተፈለጉት ሠራተኞች አብዛኛቸዉን ሕዝብ የሚፈቅዳቸዉ ሆነዉ ሳለ፤ ቀሪዎቹ ሁለት ሰዎች ግን ጨርሶ ተቀባይነት የሌላቸዉ መሆኑን ስለአመንኩበት በሌሎች ሰዎች ተኳኋቸዉ። አንዱ ኃይሉ ይርዳዉ የሚባልና ነዋሪነቱ ከፍተኛ 14 ቀበሌ 22 የሆነና ከቀይ ሽብር ጋርም ንኪኪ አለዉ ስለሚባል አልተቀበልኩትም። ሁለተኛዉ ደግሞ ፀጋዉ ወሌ የተባለና የካሳ ገብሬ ሚስት ወንድም ሲሆን፤ ይኸ ሰዉ እንኳን የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ተመራጭ ሊሆን ይቅርና መደበኛ ሥራዉንም በአግባቡ ተወጥቶ የማያዉቅ ሰዉ ስለሆነ ስሙ እንዲሰረዝ ሆነ። ሁለቱንም በራሴ ኃላፊነት ሰረዝኳቸዉ። ሰማይና ምድር ቀዉጢ ሆኑ፤ የቀጣናዉ ተጠሪ ሪፖርቱን ላለመቀበል ሲያንገራግር በመሃል ላይ የሆነ አጋጣሚ ሲፈጠር ሪፖርቱን ጠረጴዛዉ ላይ ትቼለት ሄድኩ። ዝም ተብሎ የቀረ ሳይሆን ወደ ፓርቲዉ ዲስፒሊንና ቁጥጥር ኮሚቴ ተመርቶ በመጠባበቅ ላይ እያለሁ፤ የዲስፒልንና ቁጥጥር ኮሚሽኑ ሰብሳቢ ከሕወሓት ጋር ግንኙነት እንዳለዉ ተጠርጥሮ በመያዙ የኔዉ ጉዳይም ውሃ ጠጥቶ እዚያው ሊቀር ቻለ እንጂ ጉድ ሳይፈላብኝ አይቀርልኝም ነበር።

አስገራሚ ነገር የተከሰተዉ ሌላ ጊዜ ነዉ። ያ ያቋቋምኩት መሠረታዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ብር 90 ሺህ የሚያወጣ ነዉ የተባለ የደረቀ ኖራ ተገዝቶ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን መጋዘን መግባቱ ጥቆማ ደረሰዉ። ሲጣራ ጥቆማዉ ዕዉነት ሆኖ በመገኘቱ ተጣርቶ ዉጤቱ ቀጥታ ለብሔራዊ ሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ ይቀርባል። ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ የኮንስትራክሽን ሚኒስትሩ ካሳ ገብሬ ‹‹ይኸዉ ልጆቼ

የተከሰሱበት ሰነድ›› በማለት በሠራተኞች ስብሰባ ላይ ያንን መሠረታዊ የሠርቶ አደር ቁጥጥር ኮሚቴ የመረመረዉን ሰነድ ዋናዉን ኮፒ አምጥቶ ያሳይና ሐሞታችን ፈስሶ የዛሬዉ ኢሠፓአኮን ብቻ ሳይሆን ባለንበት ቦታ ላይ ሆነን የመጪዉ ጊዜ ኢሠፓን አወዳደቅ ከወዲሁ ለማየት ችለን ዝም አለን። በዚሁ ሰበብ የኮሚቴዉ ፀሐፊ እና ምርመራውን መርቶ የነበረ ሰዉ፤ አቶ ሙላቱ ገመቹ የዛሬ የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ከሥራ እንዲባረር ተደረገ።

‹‹ሐቀኛ፣ ኮሚኒስቱና አብዮታዊ መሪያችን›› በሚባሉ ሐረጎች የታጀበዉና ጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም ማዕከል የሆነበት አሠፓአኮ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲን መስርቶ፤ የዚህ ፓርቲ ምስረታ የታጀበዉ (ሹማምንቱ ቁርጥ ቆርጠዋል፣ ውስኪ ተራጭተዋል፣ ጠጅ እየጠጡ ደፍተዋል) ድባቡ ግን በሳቅ በፈገግታ ሳይሆን ማንም ሊያነበዉ ባልቻለዉ የሕዝብ ዝምታና ሐዘን፣ በአማፂያን ውጊያ መፋፋምና የሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ክፉኛ በድርቅና በረሃብ በተመታበትና በአገር ዉስጥ የተስፋ ጭላንጭል በማይታይበት ሁኔታ ዉስጥ ነበር። ኢሠፓም እንደአመራር ሰጪ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ከተመሰረተ በኋላ መንግስቱ ኃይለማሪያምም ሆነ የሰደድ አባላቱ ያሳስባቸዉ የገባዉ ከ1967 ጀምሮ ለአስራ አንድ ዓመታት የአንድን አገር ሕዝብ በአዋጅ (decree) ሲገዙ የቆዩበትን አሰራር መልክ ለመቀየርና ለአምባገነናዊ አገዛዛቸዉ ሕጋዊ ሽፋን ለማጎናፀፍ ሲሉ፤ ከ1978 ጀምሮ ዝግጅት ሲደረግበት ቆይቶ በ1979 የኢሕዲሪ ሕገ መንግስት ታወጀ። ሕገ መንግስቱም በአንቀፅ 6/2 ላይ ኢሠፓ የአገሪቱና የሕብረተሰቡ ዕድገት ብቸኛ አመራር ሰጭ ፓርቲ መሆኑን የገለጸበትና በአገሪቱ የአንድ ፓርቲ አገዛዝን ሥርዓት በማስፈን የብዙሃን ፓርቲ ሕልምና የዲሞክራሲ ተስፋን በድቅድቀ ጨለማ ዉስጥ ከቶ ብቅ አለ።

ይህ እንዳለ ሆኖ በኢሠፓ እና ኢሕዲሪ ምስረታ ዉስጥ ያጋጣሙ አንዳንድ ነገሮችን ወደኋላ ተመልሶ ማሳየት ግድ ይለኛል። ይኸዉም ወግ አይቀርምና የኢሕዲሪ ሕገ መንግስት በሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ ፀደቀ

ለማለት ሲባል ካድሬዎች ብቻቸዉን እያነበነቡ፤ ሕዝቡ አስተያየት እንዲሰጡበት ተቆጥሮ አለፈ ተባለ። የብሔራዊ ሸንጎ አባላት ምርጫ ከመካሄዱ አስቀድሞ ልክ ኢሠፓ ሲቋቋም እንደነበረ ዓይነት የዉይይት ክበባትን ጨምሮ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር፣ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፣ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት፣ ወዘተ ከኢሕዲሪ ሕገ መንግስት ጋር እንዲመሳሰሉ ምርጫ እንዲካሄድ ተደረገ።

በድርጅታዊ ሥራ ምርጫ ማካሄዱ ለዚያ ወቅት አዲስ ነገር ባይሆንም፤ ግን ይህ ምርጫ የራሱ የሆነ አስቂኝ ገጽታ እንደነበረዉ ለመግለፅ እወዳለሁ። የብሔራዊ ሸንጎ ተወዳዳሪዎች በያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ሦስት ሦስት እንዲሆኑ ተደረገ። የምርጫ ምልክታቸዉም ከላይ ወደታች ዝሆን፣ አንበሳና ጎሽ ናቸዉ። እኔ በአስመራጭ ካድሬነት በተመደብኩበት ለወረዳ 19 ምርጫ  ጣቢያ የተመደቡት ‹ዕጩዎች› አቶ ጣምያለዉ እሸቴ፣ አቶ ሽፈራዉ አድማሴ እና አቶ አብርሃም መንበሩ የሚሰኙ ነበሩ። ምርጫ ተብዬዉ አንድ ሳምንት ያህል ጊዜ ሲቀር ዕጩዎችን በማስተዋወቅ ፕሮግራም መሀከል አንድ አዲስ ነገር ይከሰታል። ይኸዉም ወረዳ 14 ኮሎኔል መንግስቱ የሚወዳደርበት ወረዳ የእሱ ተወዳዳሪ ዕጩ ራሱን እንዲያስተዋዉቅ ወደ መድረክ ሲጋበዝ፤ ስለራሱ ሳይሆን ኮሎኔሉ ራሱ ሊታዘበዉ በሚችልበት ሁኔታ ዓይነት ይባላል፤ ስለኮሎኔል መንግስቱ ከዘበዘበ በኋላ ከጓዱ ጋር ለመወዳደር ብቃቱን ስለሌለዉ በራሱ ፈቃድ ከዉድድሩ እንደወጣ ይናገራል። ዕጩዎችን የማስተዋወቁ ሥራ ፕሮግራም ሁሉም በታዎች ላይ በአንድ ቀን ከተከናወነ በኋላ፤ የመንግስቱ ኃይለማሪያም ብቸኛ ተወዳዳሪ መሆን በፈጠረዉ ክስተት በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ ባለዝሆን ምልክቶቹ ዕጩዎች ብቻ እንዲቀሩና ሌሎቹ እንዲለቁ ስለተፈለገ ከቀጣና 3ቱ የኢሠፓ ተጠሪ እና የድርጅታዊ ሥራዎች ዋና ኤክስፐርት ገስጥ ተጫነ ሁለቱ የወረዳ 19 ዕጩዎች በራሳቸዉ ፈቃድ እንዲለቁ የሚል ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ይሰጣል። በኔ ወረዳ ባለአንበሳ ምልክቱ አቶ ሽፈራዉ አድማሴ ብዙም አላንገራገሩም፤ ወይም ስሜትም አልሰጣቸዉምና ወዲያዉኑ ለመልቀቅ ተስማሙ። ባለጎሹ አብርሃም መንበሩ ግን ‹‹ቀድሞም ዕጩ ተወዳዳሪ

የሆንኩት በራሴ ተነሳሽነት ሳይሆን እራሱ ጓድ ገስጥ ጠርቶኝ ተወዳዳሪ ነህ ስላለኝ፤ ሕዝብ ፊት ቀርቤ ከተዋወቅሁ በኋላ፤ አሁን በራሴ ፈቃድ ብዬ ከዉድድር ለመዉጣት በተዘጋጀዉ ፎርም ላይ ፈርሜ የምጠይቅበት ምክንያት የለምና ሲትፈልግ አንተዉ ሰርዘዉ ወይም ጓድ ገስጥ እራሱ ይወስን›› ብሎ አሻፈረኝ አለ። እዉነቱን ለመናገር አቶ አብርሃም መንበሩ በግል ባህርዩ የመሸታ ቤት ደንበኛ ከመሆኑ ዉጭ ከሦስቱም ተወዳዳሪዎች የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያለዉ ሰዉ በመሆኑ፤ የውሃ አወሳሰዱ ከገደብ የሚያልፍና አንዳንድ ጊዜ የቆሻሻ ቱቦ ውስጥ ተጠልሎ ስለሚገኝ፤ ነገር ግን ሰውን የሚጎዳ ባህርይ ስለሌለው በሕዝብ መሀከል የነበረዉ ቀረበታም ደህና ነዉ የሚባል በመሆኑ፤ በተወሰነ ደረጃም ስለምንግባባ ከቀጣና በመጣዉ ፎርም ላይ ፈርሞ ከዉድድር ተብዬዉ በመዉጣቱ ቀሪ ፕሮግራሙ እንዲቀጥል ሆነ።

አስቂኝ ያልኩት ነገር ያጋጣመዉ ከሕዝብ ጋር ማስተዋወቅ የተካሄደ ዕለት ባለዝሆን ምልክቱ ተወዳዳሪ ሲያኮርፍ አየሁትና የሚሄድበት መኪና ዉስጥ ገብቶ ሳለ፤ ለመሰናበት እጄን ስሰነዝር ‹‹ታሪኬን አሳንሰህ ለሕዝብ አቀረብክ›› ብሎ አረፈዉ። በኋላ ወደቀጣና ሄዶ ይኸንኑ ሪፖርት አድርጎ ኖሮ ምን እንደቀረበት ሲጠየቅ ‹‹በቀይ ሽብር›› እርምጃ ዉስጥ ሰፊ ተሳትፎ አድርጎ እያለ፤ ይህንኑ ጎላ አድርጎ አለመግለፅ መሆኑ ተነገረኝ። በዚህም አለ በዚያ ብቻውን ተወዳድሮ በሙሉ ድምፅ ተመረጠ ተባለና የብሔራዊ ሸንጎ አባል ሆነ። ከዚያ በኋላ ለብቻም ሆነ በሕዝብ መሀከል ሳንገናኝ የደርግ ሥርአት ቀን ዳግም ላይነጋ መሸ።

ይኸዉ ፓርቲ ከግንቦት ወር 1981 ተሞክሮ ከነበረዉ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ የሕዝብ ጥያቄ የብዙሃን ፓርቲ ጥያቄ ነዉ ስለተባለ ብቻ ከግንዛቤ ማጣት ይሁን ከማጨናበር ፍላጎት እንደሆነ አይታወቅም፤ መለስተኛ የአመለካከት ልዩነት ያላቸው ዜጎች ጭምር የሚሳተፉበት የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ተመሠረተ። የደርጉ ምክትል ሊቀ መንበር ሻለቃ አጥናፉ አባተ አቅርበው የነበሩትን የቅይጥ ኤኮኖሚ ፖሊሲንም ተግባራዊ ለማድረግ የወሰነ ቢሆንም ከወሬ ባለፈ

ምንም ያደረገዉ እንቅስቃሴ ሳይኖር በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት/ኢሕአዴግ) የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር መሪነት ከግንቦት 1983 ዓም ጀምሮ ሰደድ/ኢሠፓ/ደርግ (ፓርቲና መንግስት ተጣምረዉ የሚሠሩበት) አንድም፣ ሁለትም፣ ሦስትም የሆኑበት የፖለቲካ አገዛዝ ከሥልጣን ተወገደ። ከዚያስ ወዲህ በፓርቲ ፖለቲካ አጀንዳችን የተፈለገዉ ነገር መጥቶ እንደሆን እታች ባለዉ ክፍል የብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎችን አስቀድሞ በማንሳት እንመለከታለን።

## ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች

ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎች መሠረታዊ መነሻቸዉ በምንም ዓይነት እይታ፤ የቅንጦት ወይም የሥልጣን ጥማት ወይም ከአመለካከት ጥበት ሳይሆን የነፃነት ተፋላሚዎቹ የየመጡበት የሕብረተሰብ ክፍል የጭቆና ሁኔታ አንገሽግሿቸዉና የእግር እሳት ሆኖባቸው የሚነሱ ናቸዉ። ብረት አንስቶ ዱር ለዱር መንከራተት ከአገር አገር መዞር፣ አሳቻ ሁኔታ ሲያገኙ መግደልና ከተያዙም ደግሞ መገደል ወይም ጀርባቸውን መገረፍና መተልተል፣ አነሰ ሲባል ደግሞ መታሰር እንዳለ እያወቁ፤ ለሕይወታቸዉ ሳይሳሱ ቁርጥ ያለ አቋም በመያዝ የምንወክለዉ ሕዝብ ነፃነት እስካልተጎናፀፈና መብቱ እስካልተጠበቀ ድረስ ሌላ ምርጫ የለም በማለት የሚታገሉ ናቸዉ። እነዚህ ብሔራዊ የነፃነት ተፋላሚዎች ሕዝባቸዉን ዝንተ ዓለም ከሚገዛዉ ክፉ ጠላት (sidii hamaa) ማላቀቅ ነዉ እንጂ ቅንጦት የሚለዉ ቃል ለነሱ ቦታ የለዉም ብቻ ሳይሆን፤ ጊዜያዊ የሰዉነት አቋማቸዉን አይተዉ ይህ ታጋይ ደልቶት የሚኖር ነዉ ብሎ ማሰቡ ራሱ የማይገባ ነው። ምክንያቱም፤ ምንም ያህል መብላቱ ወይም መጠጣቱ ሳይሆን ሞቱ እንኳን ቢመጣ የቤተሰቡ (የቤተዘመዱ) ዓይንና የአገሩ አፈር ሽታ እየናፈቀዉ ላይመለስ አንድያ ሕይወቱን ለቆመለት ዓላማ ይሰዋል። ለብሔራዊ አርነት የሚዋጉ ንቅናቄዎች መሳሪያ ስለያዙ ወይም ስላገኙ ብቻ ወደ ዱር የሚሄዱ አይደለም። እንዲያዉም ጦርነት በቀጥታ ከሚያጠፋዉ ንብረት ባልተናነሰ ሁኔታ የጦርነት ስሜት መኖሩ ራሱ በአከባቢዉ ወይም በአገሩ ላይ በሚኖሩ

ሰዎች ላይ የሚፈጥረዉን ሥነ ልቦናዊ ጭንቀትና በረጅም ጊዜ ዉስጥ ደግሞ አገሪቱን የሚያስከፍለዉ ኤኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ዋጋ በጣም ውድ መሆኑን እየተገነዘቡም ቢሆን የሚገቡበት ነዉ። ታላቁ የዓለማችን የነፃነት ተፋላሚ የሆነዉ ኒልሰን ማንደላ (1994፡ 304) *LONG WALK TO FREEDOM* በሚለዉ ግለ ሕይወት መጽሐፉ ውስጥ ሰዎች ለምን አመፅን እንደሚመርጡ ሲገልፅ (ሰው መኖር የምሻውን ሕይወት የመኖር መብቱን ከተነፈገ፤ ሕገ ወጥ ከመሆን ሌላ ምርጫ የለውም) *"… when a man is denied the right to live the life he believes in, he has no choice, but to become an outlaw."* ብሎ ሲደመድም፤ ዶ/ር ጌታቸዉ ጅጊ (2014፡ 163) <u>*BU'A BA'II QABSOO UMMATA OROMOO*</u> ብሎ በፃፈዉ መጽሐፉ ዉስጥ ሰዎችን ወደ ነፃነት ትግል የሚገፋፋ ጉዳይ ምን እንደሆነ ሲገልጽ *"Sabni bilisummaa hinqabne seena hinqabu. Seena qaba yoo jedhellee, seena itti boonu utuu hinta'iin, seena itti qaana'u ta'a."* ተዛማጅ ትርጉሙም *"ነፃነት የሌለው ማህበረሰብ ታሪክ የለውም። ታሪክ አለው እንኳን ቢባል የሚኮራበት ታሪክ ሳይሆን የሚያፍርበት ታሪክ ይሆናል"* ብሏል። እንግዲህ የነፃነት ጊዜው መርዘምም ሆነ ማጠር ሁኔታዎች የሚወስኑት ቢሆንም የነፃነት ንቅናቄዎች ብረት የሚያነሱት ሕዝቦቻቸውን ከአሳፋሪ ታሪክ ለማላቀቅ እንደሆነ ልንገነዘብ እንችላለን። በፈለገው ስልት ሥልጣን ይያዝ፤ ሥልጣን ላይ ያለው መንግስት የሰውን መብት የማያከብርና ነፃነቱን የማያከብር ከሆነ፤ እነዚህንኑ ለማስወገድ ደረጃቸው ይለያይ እንጂ ከማኩረፍ እስከ ብረት ማንሳቱ መሄድ የማይቀር ነገር ነው።

የብሔር ጥያቄ፣ የመሬት ላራሹ ጥያቄ፣ የዲሞክራሲ ጥያቄ እና ሌሎችም የመብትና የነፃነት ጥያቄዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ በወጉ ባለመመለሳቸዉ፤ ዱር ቤቴ ብለዉ የወጡና የሚወጡ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች ብዙ ስለሆኑ፤ ብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች የተማረዉና በንዑስ ከበርቴነት የሚመደበዉ ወይም ያፈነገጠው የሕብረተሰብ ክፍል ፍላጎት ብቻ ሳይሆን፤ ብዙ ሰዎች የተለያየ ሐሳብ ቢያራምዱም፤ ለነፃነት ንቅናቄዎች ግን እነሱ የመጡበት ሕብረተሰብ የተማረረበት ሕይወትና ችግር መከራ

ማለቂያዉ መቼ ይሆን ብለዉ የሚጨነቁና ለዚህም መፍትኼ ለማግኘት ሕይወታቸዉን ጭምር መስዋዕት ለማድረግ ቆርጠዉ የተነሱ ሰዎች ስብስብ ነው። ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎችና አመራራቸዉ ለግል ቅንጦት አስበዉ ቢሆን ኖሮ፤ ራሳቸዉን በርካሽ ዋጋ ለቅኝ ገዥዎች፣ ለአምባገነኖችና ለጨቋኞች እየሸጡ ወይም እየሸቀጡ ቅንጡ ኑሮ መኖር እንደሚችሉ ሳይገነዘቡ የሚቀሩ አይደለም። የአልጠግብ ባይ አምባገነንነት ማለቂያዉ ስለማይታወቅ እሮሮዉ ከሕዝቡም አልፎ ንዑስ ከበርቴ የተባለዉን የሕብረተሰብ ክፍል ስለአሰመረረ፤ ትግሉ ማለቂያ የሌለዉ መስሎ ቢታይም "ታጋይ ቢሞትም ትግል አይሞትም" እያሉ የአርነት ንቅናቄ ፊታወራሪዎች ትግሉን ይቀባበሉታል። ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎችን አምባገነኖች በተወሰነ ደረጃ ለተወሰነ ጊዜ ቢያዳፍኑት እንጂ ጨርሶ ሊያጠፉአቸው የማይቻላቸዉ ናቸው። ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎችን ማጥፋት የሚችለዉ ሕዝባዊ ዲሞክራሲን፣ ነፃነትን ማስፈንና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር የሚችልና ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሚሰማው አስተዳደራዊ ሥርአት ሲደራጅ ብቻ ነዉ። ይህ አጠቃላይ እዉነታ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ በፊት ጀምሮ ዛሬ ድረስ ገጽታዉን ብቻ እየቀያየረ በመቀጠል ላይ ሲሆን፤ ከወቅታዊ የሕወሓት ወይም ወንበሩን ከወረሰው ብልፅግና ፓ ር ቲ አቋም አንፃር የመንግስት ሥርአቱ ተመሰረተ የሚባለዉ ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝም እንደሆነ ስለሚገለጽ፤ እንደወትሮዉ የአርነት ንቅናቄዎቹ ቁጥር አይብዛ እንጂ ብሔር ተኮር የሆኑ (የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ/አብንን ሳይጨምር) ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች ዛሬም ቢሆን አጠቃላይ ሕዝቡም ሆኑ የአርነት ንቅናቄዎች በወቅቱ አመራር ባለመርካታቸዉ በሠላማዊ ስልትም ሆነ ብረት ማንሳታቸዉ እየቀጠለ ስለሆነና በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ የሚያሳርፉት ተፅዕኖም ሆነ የሚጫወቱት ሚና የጎላ ስለሆነ፤ የተወሰኑ የአርነት ንቅናቄዎችን አንስተን እያንዳንዳቸው ለምን ያንን የትግል ስልት እንደመረጡና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ምን ምን ችግሮች እንዳሉባቸዉ እንመለከታለን።

ከዚያ በፊት ግን ብሔር ምንድን ነዉ? ለሚል ጥያቄ ጥቂት ሐሳቦችና

ስለኢትዮጵያ ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄዎች ብለን ማንሳቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ <u>የኦሮሞ ጉዳይ እና የኢትዮጵያ ብያኔ</u> መጽሐፍ ፀሐፊ ሰለሞን ስዩም (2007፡ 28) ከተለያዩ ምሁራን ስራዎች ወስዶ በንፅፅር እንደፃፈዉ "ብሔር ማለት መንግስት ያለዉ ሕዝብ ነዉ" ካለ በኋላ "ብሔር የራሱ መንግስት ሳይኖረዉም ሆነ አንድነትና ብሔረ-መንግስት ባልፈጠሩ ብሔሮች ዘንድም በርግጠኝነት ሊኖር ይችላል፡፡" በማለት የፅንሰ ሐሳቡን ሁለት ገጽታዎች መንግስት ያለው ብሔር ወይም ሕዝብና ራሱን የቻለ መንግስት ሳይኖረውም በአንድ አገር ውስጥ ወይም በአንድ መንግስት ሥር ብዙ ብሔሮች ሊኖሩ እንደሚችል ግንዛቤን ያስጨብጣል፡፡ ሊዘለል የማይችል ነገር ቢኖር ግን ብሔርተኝነት አንድ ነፃ አገር ለመመስረት የሚደረግ መንደርደሪያ መሆኑ ሊዘነጋ የማይችል ቢሆንም የየራሳቸውን ብሔረ መንግስት ሳይፈጥሩ፤ ለምሳሌ በሕንድ፣ በናይጀሪያ፣ በኢትዮጵያ አገራዊ ጥላ ሥር የሚኖሩ የባለብዙ ብሔሮች አገሮች ዘንድም ብዙ ብሔራዊ ማንነቶች ማለትም የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች፣ ወዘተ ያሏቸው ብሔሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡

ወጣ አድርገንም እንመልከት! በአንድ ሉዐላዊ አገር ውስጥ አንድና ከአንድ በላይ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚሁ አንድ ሉዐላዊ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች በአጠቃላይ ወይም በአንዱ ብሔር ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ብሔሮች ላይ ተለይቶ በአንዱ ወይም ሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ላይ ጭቆና ሊፈጸም ይችላል፡፡ ጭቆናዉ ጭቆና ከሚባለዉ ቃል ተሻግሮ መንግስታዊ አስተዳደሩ የብሔሩን ወይም የብሔሮችን የሕልዉና መገለጫዎች ማለትም የሕዝቡን አሰፋፈርና የርስ በርስ ግንኙነት፣ ቋንቋና ባህላቸውን፣ የአስተዳደር ሥርአትና የአምልኮ ተቋማቸውን ጭምር ለማጥፋት የሚፈታተን ሆኖ ከተገኘና ተጨቋኝ ብሔሩ ደግሞ ላለመጥፋት ሲል የዚያ ብሔር የተወሰነ ቡድን አባላት ብረት አንስተው ወገኖቹን የመከላከል ኃላፊነትና አስፈላጊነት አማራጭ የሌለዉ መሆኑ ከታመነበት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ብሔሮች ውስጥ ለአርነት ንቅናቄ መነሳሳት ጅምር ስለሚሆን የእንዴዚህ ዓይነት ክስተት መኖር በማንኛዉም መስፈርት ወንጀለኛ፤ በዘመኑ አጠራር

ደግሞ አሸባሪ ሊያሰኝ የሚችል አንዳችም ምክንያት አይኖረዉም። ምክንያቱ ደግሞ በጣም አጭርና ግልፅ ነዉ። ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ብሔሮች ፍትህን ሕጋዊ ነኝ ከሚለዉ አካል፤ ከፍ ሲልም መንግስት ከሚባለው ተቋም ከተነፈጉ፤ ፍትህን ፈለጋ ወደ ሌላ መድረክ፤ ማለትም ከጠመንጃ አፈሙዝ ለማግኘት ማማተር ግድ ይላቸዋል። በሌላ አባባል ከላይ እንደተመለከተው ሰው መኖር የምሻውን ሕይወት በሕጋዊ ሁኔታ የመኖር መብቱን ከተነፈገ፤ ሥልጣን ላይ ባለው መንግስት ሕገ ወጥ ነው የሚባለውን ከመሆን ሌላ ምርጫ አይኖውም ማለት ነው። የሰዉ ልጅን ከሌሎች እንስሳት ለየት የሚያደርገዉ ነገር ቢኖር "ከዘላለም ባርነት ያንድ ቀን ነፃነት" ምርጫዉ ስለሚሆንና በነፃነት ለመኖር ሲል ፍትህን ፈለጋ የትየለለ የሚባለውን መንገድ መሄድ ግድ እንደሚሆንበት መገመት ይቻላል። ዶ/ር ታየ ንጉሴ የሚባል ብዕረኛ ቅዳሜ ሰኔ 6 ቀን 2007 በወጣዉ ኢትዮ-ምህዳር በተሰኘ የግል ጋዜጣ ላይ "በዓለም ዙሪያ እስከዛሬ ድረስ የተከሰቱና ከማንነት ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ግጭቶችና ጅምላ ጭፍጨፋዎች ያለምንም ልዩነት ሊከሰቱ የቻሉት፤ የያዘዉን የፖለቲካ ሥልጣን ለመልቀቅ በማይፈልገዉና በበርካታ ችግሮች ዙሪያዉን ተከብቦ በመንገታገት ላይ በሚገኝ ፓርቲ አማካኝነት በሚነዛዉ መጠነ ሰፊ እና ተከታታይነት ባለዉ ሥነ ልቦናዊና ስሜት ቀስቃሽ ዘመቻ ሳቢያ ነዉ" በማለት የፃፈዉ ከዚህ በታች ለማነሳቸዉ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች መነሻ ብቻ ሰይሆን አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ለሚገኙና ወደፊትም ለሚከሰቱ ንቅናቄዎች በቂ ተጠቃሽ ምክንያት መሆኑን ስለሚያረጋግጥልኝ ነው።

ሰፋ አድርገን ስናይ ለአርነት ንቅናቄዎች መነሻ የሚሆነው የአምባገነኖችና የቅኝ ገዥዎች የጭቆና ዓይነት በፖለቲካ ወይም በኤኮኖሚ የበላይነትን በመያዝ ብቻ የሚወሰን አለመሆኑ ነው። ሁለንተናዊ (holistic or package) ነዉ። ማለትም የፖለቲካ የበላይነቱን የያዘዉ አገዛዝ የኤኮኖሚ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የታሪክ፣ የሥነ ልቦና፣ የትምህርት፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የቴአትር (የቴውኔት)፣ ወዘተ የበላይነትን ያለ ጥርጥር ይቆጣጠራል። የተገዛው፣ የተወረረው፣ የተጨቆነዉ ሕብረተሰብ

መጨቆኑ ሳያንሰዉ እንደ አሜሪካ ቀይ ሕንዶች፣ እንደ አውስትራሊያ አቦርጂኖች ሕልዉናቸዉ ራሱ ሊጠፋ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ እንዲገባ ይደረጋል። ቅኝ ተገዥው አምርቶ ሕይወቱን ሊመራ ከሚችልበት አከባቢ በግልፅና በስልት እንዲፈናቀል ይደረጋል። ቤተሰቡ እንዲራብ ይደረጋል። ወይ እራሱ ወይ ተተኪ ትውልዱ እራሱን የሚገልጽበትን ባህል፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ ትስስሩን እንዲረሳ ወይም እንዲጠላ ይደረጋል። የኢትዮጵያ ብሔሮችም የተዘረዘሩ የጭቆና ዓይነቶች ገፈት ቀማሾች እንደነበሩና ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች እስር ቤት እስከ መባል የደረሰች አገር ነች። እንግዲህ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ ሕዝቦቻቸዉን አሰልፈዉ ለነፃነት የተንቀሳቀሱና ዛሬም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ የአርነት ንቅናቄዎችም በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ የተጫወቱት ሚና ቀላል ባለመሆኑ፤ ቀጥሎ ባለዉ ክፍል ዉስጥ እንዲታዩ ተፈልጓል። እነዚህ የነፃነት ተፋላሚዎች ተብለዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚጠቀሱት ብዙ ቢሆንም፤ ከመረጃ ዕጥረት የተነሳ፤ በዚህ ጽሑፍ ዉስጥ ሦስቱን ብቻ፤ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ እና ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት ብቻ የሚነሱ ይሆናሉ። በተለይ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይን በዚህ ክፍል ከነፃነት ንቅናቄነቱ አንፃር እና ቀጥሎ ባለዉ ምዕራፍና ክፍል ዉስጥ ደግሞ በገዥነቱ በማከናወን ላይ ካለዉ ገጽታ አንፃር ለያይቼ እንዲታይ አደርጋለሁ። ይህም ያለምክንያት አይደለም፤ ሕወሓት እንደነፃነት ታጋይ፤ በተለይ አምባገነናዊዉን ደርግን ተፋልሞ ሥልጣንን ተቆናጥጧል። በትረ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ደግሞ ከቀደምቶቹ አምባገነን ገዥዎች የተለየ ነገር ወይም ምን የተሻለ ነገር ሰርቷል? ምን ይቀረዋል? የሚለዉን ከአጀንዳው ጋር አያይዤ አነሳለሁ።

ከአርነት ንቅናቄዎች ጋርም የሰው ስጋት ምን ይመስላል የሚለውን ማንሳትም አስፈላጊ ይሆናል። ከ1984 ዓም ጀምሮ ሕገ መንግስት ተቀርጾለት ኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ የሚገኘውንና ቋንቋን መሠረት ያደረገውን የብሔር አደረጃጀት አንዳንዶች የአገር አንድነት አፍራሽ፣ ጎሰኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ዘረኝነት፣ አሸባሪነት፣ ዘውገነት፣ ወዘተ ነው ብለው ይፈርጃሉ። መፈረጅ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ አንድነት አፍራሽ እንደሆነ

አስምረው ይኮንናሉ። አንዳንዶች ደግሞ ስሜታቸውን መቆጣጠር እስኪያቃታቸው ድረስ እየሄዱ በቀጣይነትም ብሔር/ብሔረሰቦች በአብሮነት ወይም በጉርብትና የመኖራቸውን ዕድል እንኳን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ የጠላትነት ቃላቸውን ያዥጎደጉዳሉ። ከእነዚህ ፈራጆች አንዳንዶች በተለይ ኦሮሞ የሚለውን ብሔር ስም ሲሰሙ ዓይናቸውን የሚጨፍኑና ሆዳቸውን የሚያቀለሽልሻቸው ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ የሚዲያ ባለሙያ ነኝ ባዮች፣ ፓርቲዎች፣ ወዘተ አሉ። አልፎ ተርፎም የኦሮሞን ጨምሮ በብሔር የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች (ፓርቲዎች) ሕግ ተደንግጎባቸው እንዲፈርሱ አምርረው የሚጠይቁ አለፍ ሲልም ግፊት የሚያደርጉ አሉ። ለመሆኑ እንዲዚህ ዓይነት የብሔር አደረጃጀት በታሪክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ክስተት ነውን? አጀንዳውስ እንዴት ይተነተናል? እንዴትስ ይተገበራል? ከብሔር አደረጃጀት ተቃውሞ ሌላ ከበስተጀርባው ምን ይዘት ይኖረዋል? ዕውነትስ ብሔረተኝነት ዘረኛና አገር አፍራሽ ነውን? ቀጥሎ የምንመለከታቸው ይሆናል።

ከትርጉም እንጀምር፤ *“Nationalism is the desire to achieve political independence especially by a country under foreign control or by a people with a separate identity and culture, but state of their own.”* ይህ ከእንካርታ 2009 የተወሰደ ነው። የራሴ ተዛማጅ ትርጉሙም *“ብሔርተኝነት በተለይ በባዕድ ቁጥጥር ሥር የሚገኝ አገር ሕዝብ የፖለቲካ ነፃነት ለማግኘት የሚያሳየው ፍላጎት ወይም ከሌላው የተለየ የራሳቸው ማንነትና ባህል ኖሮአቸው ነፃነትን የሚሹ ነው።”* የሚል ይሆናል። የፖለቲካ ነፃነትን ለማግኘት ብሔር የሚባል ደረጃ ድረስ መሄድ አስፈላጊ ቢሆንም፤ የዕድገት ደረጃቸው ብሔር ደረጃ ላይ ባይደርስም፤ የሚቀራረቡ ነገዶች ወይም ጎሳዎች አቅማቸውን አጎልብተው ጠላታችን ነው ከሚሉት ብሔር የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከል ተባብረው መንግስት እስከ ማቋቋም ደረጃ ይደርሳሉ።

እንካርታ ይቀጥላል። *“The human population on the globe is divided into several thousand national groups, people who speak the same language or dialect and share common customs as well as common*

*history ... these national groups share a common national identity, and sometimes they share a common religious background."* ተዛማጅ ትርጉሙም "በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ወይም ተመሳሳይ የአነጋገር ዘይቤ ያላቸው የዓለም ቡድኖች፣ ሕዝቦችና ተመሳሳይ ማንነትና የጋራ ታሪክ ያላቸው ሕዝቦች ተመሳሳይ ማንነትና አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ የሃይማኖትና የኋላ ታሪክ የሚጋሩ" ይሆናሉ። *ኦክስፎርርድ አድቫንሲድ ለርነርስ ድክሽነሪ:* Nationalism-The desire by a group of people who share the same race, culture, language, etc to form an indepenedent country በማለት አስፍሮ ይገኛል። የቅርብ ትርጉሙም ብሔርተኝነት ተመሳሳይ ዘር፣ ባህል፣ ቋንቋ የሚጋሩ ሕዝቦች ነፃ ሀገር ለመመስረት የሚያሳዩት ፍላጎት ነው። (ትርጉም የራሴ)

ሰለሞን ስዩም ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ገጽ 34 ላይ ሃል የሚባል ጸሐፊን ዋቢ በማድረግ "ብሔረተኝነት እውነተኛም ይሁን የፈጠራ፤ በራሱ ብሔር ቅድምና ማመን ነው"- The belief in the primacy of a particular nation, real or constructed." ይላል።

ውብሸት ሙላት ፅጌ አንቀጽ 39 የራስን ዕድል በራስ መወሰን (2007፡ 30) ብሎ በፃፈው መጽሐፉ ውስጥ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት ጀምሮ ወደኋላ እነ ሌኒን እስከ ነበሩበት ጊዜ ድረስ ያለውን የብሔር፣ የብሔረሰብ እና የሕዝብ ፅንሰ ሐሳቦች ላይ ሰፊ ትንተና ሰጥቷል። በዚሁ መሠረትም በሕገ መንግስቱ ለሦስቱም ተመሳሳይ ትርጉም እንደተሰጠና "ሰፋ ያለ የጋራ ፀባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑና የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖሩ ናቸው" ይላል። ይኼው ፀሐፍ ስለብሔር ለየት ባለ ሁኔታ በተለይ ማርክሳዊ ትንተናን ዋቢ አድርጎ ሲገልፅ "ብሔር በታሪክ ሂደታ የተሰባሰቡ ቋሚነት ያለው የሰዎች ማህበረሰብ/ስብስብ ነው። በአንድ መልክአ ምድራዊ ክልል ውስጥ የሚኖሩ፣ በኤኮኖሚያዊ

ግንኙነት የተሳሰሩ፣ በአንድ ቋንቋ የሚጠቀሙ፣ በጋራ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የወል ሥነ-ልቦናዊ ገጽታዎችና ባህላዊ አመለካከቶች ያሉት ነው።” በማለት ጽፏል።

ፓወር ፖለቲክስ (1964፡55) ብሎ የፃፈው ጆርጅ ሸዋርዚንበርገር “Stalin’s Marxism and the National Question (1913) … defined a nation “a historically evolved stable community of language, territory, economic life, and psychological make-up manifested in a community of culture.” ብሏል። እነዚህን ትንተናዎች በቅርበት ስንመለከት ብሔርተኝነት ባለፈው ታሪክና ከወቅታዊ ሕይወት ጋር በተያያዘ ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ጭምር በማሰብ ልብን የሚያሞቅ ነፍስ ያለው መንፈሳዊ መርህ ያለው ነው ለማለት ይቻላል።

ሁሉም ገላጮች ብሔሮች ራሳቸውን በቻሉ አገራዊ ክልል እና ከሌሎች ጋር በጋራ አገር ውስጥ ሊኖሩ ስለመቻላቸው እንጂ ስለብሔርም ሆነ ስለብሔርተኝነት ትንተና ከሰጡት ሁሉ ውስጥ አንዳቸውም ሁሉም ብሔርተኝነት ጎሰኛ፣ ጎጠኛ፣ ዘውገኛ፣ ዘረኛ፣ አሸባሪ፣ አገር አፍራሽ ነው አላሉም። ብሔረተኝነት የግድ የራሱ መንግስት መኖርንም ይፈልጋል አላሉም። ይህንን አስመልክቶ ሰለሞን ስዩም ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ገጽ 28 ላይ “ብሔር የራሱ መንግስት ሳይኖረውም ሆነ አንድነትና ብሔረ መንግስት ባልፈጠሩ መንግስታት ዘንድም በርግጠኝነት ሊኖር ይችላል” ይላል። በመሆኑም በኢትዮጵያ በተከሰተ የፖለቲካ መለዋወጥና የብሔረተኝነት ጥያቄ ገንኖ ወይም ጎልቶ መውጣት ምክንያት ብሔረተኞች በአገር አፍራሽነት መፈረጅ ወይም መከሰስ አልነበረባቸውም ማለት ነው። የዚህ ዓይነት ስጋት ምንጮች ከሦስት አቅጣጫዎች ይሆናል። አንዱ ስጋት ከብሔርተኝነት ጋር የሚነሱና በሰዎች ላይ ስጋትን የሚፈጥሩ የፖለቲካ አመለካከቶች እንደ ፋሽስዚም የመሳሰሉ አቋሞች ሊከሰቱ ይችላሉ የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የሌላውን ብሔር ወይም ሕዝብ ሰውን ጨምሮ የተፈጥሮ ፀጋ የሚዘርፉ ኃይሎች ዘረፋቸው እንዳይቋረጥባቸው የራሳቸውንና እንወክላለን የሚሉትን

ቡድን ጥቅም እንዳይቋርጥባቸው በራሳቸው ከሚፈጥሩት ስጋት እና ሦስተኛው ደግሞ ያለባቸው የማንነት ቀውስ ስለሚያሳስባቸው ነው። ተጠቃልሎ ሲታይ ግን ብሔር ሁሉ አደገኛ ብሔረተኝነትን፣ ዘር ሁሉ ዘረኝነትን፣ ፋሽስዝምን፣ ናዚዝምን፣ አክራሪነትን፣ ጽንፈኝነትን፣ አይሁዳዊነትን፣ ወዘተ የማያስከትሉ መሆናቸውን በአግባቡ ካለመረዳት የተነሳ ነው።

ስለፋሽሰዝም አስፈሪነትና አስጊነት እንካርታ ድክሽነሪ 2009 እንደሚከተለው ያስነብባል። “Fascism rejects liberal ideas such as freedom and individual rights, and often presses for the destruction of elections, legislatures, and other elements of democracy.” የፋሽስዝም የፖለቲካ አቋምም “Fascism- any movement, ideology, or attitude that favors dictatorial government centeralized control of private enterprises, repression of all opposition, and extreme nationalism.” ይላል። እነዚህን የመሳሰሉትና ሊበራል ሐሳቦችን የማያስተናግዱ አቋሞችና የሰውን ነፃነት የሚያፍኑ ፀረ ዴሞክራሲ አመለካከቶች በማስፈናቸው፤ እነዚያ አምባገነኖች እራሳቸው በሚፈጥሩት የሥነ ልቦና ችግር ምክንያት ብሔረተኝነትን አምርረው ይፈራሉ፤ ይጠላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም በኢትዮጵያ የሚገኙ ነፃና የተለየ ሐሳብን የማያስተናግዱ ኃይሎች በራሳቸው ድክመት ስለተጨናገፈው ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ግንባታ ወይም አገረ መንግስት ግንባታ የበለጠ ተዳክሞ ጨርሶም እንዳይፈርስ ሲሉ ራሳቸውን ዘወትር ከሥጋት ጋር ያቆያሉ። እንዲያውም የኦሮሞንም ሆነ የሌላውን ብሔር ብሔረሰቦችን ብሔራዊ ማንነት ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነት አደጋ እንደሆነ በግልፅ ይናገራሉ። በተለይ የኦሮሞን ብሔረተኝነት የሚሰጉበት ብዙ ምክንያቶች አሏቸው። ከሚያስጨንቃቸው ውስጥም ከኦሮሚያ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ጀምሮ በተለይም የኦሮሞና ኦሮምያ ሀብት ካልፈሰሰበት በስተቀር ኢትዮጵያዊ መንግስትም ሆነ አንድነት ስለመቆሙ እምነት የሌላቸው እንደሆነ፤ ወቅታዊው የፌዴራል አወቃቀር ደግሞ ቀጣይ የብሔር

ብሔረሰቦችን ሉዐላዊነት እንደሚያበስር ጭምር አድርገው ያሳስባቸዋል። ነገር ግን መዝገበ ቃላቱ በሚገልፁት ዓይነት ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ብሔራዊ አደረጃጀት ወይም ብሔረተኝነት ከሐበሾች ምቀኝነት የተነሳ የትስስሩ ገመድ እየተበጣጠሰ ካልሄደ በስተቀር የፋሽስዝምና የናዚዝም ባሕርይ እየያዘ አይሄድም ቢባል የተሳሳተ አይሆንም። ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችም ይኼንን አይፈቅድም።

ከሚባለውና ከሚፈራው ዘረኝነት ጉዳይ ለመላቀቅ አካዳሚው የሚሰጠውን ትርጉም አዛምዶ ማየት ይጠቅማል። ኦክስፎርድ ድክሽነሪ ዘረኝነትን፣ Racism the unfair treatment of people who belong to different race, [to which it shows] violent behavior towards them. ጀምስ ቦግስ የተባለ ጸሐፊም Racism and the Class Struggle p.147 በተባለው መጽሐፉ ላይ "Racism is the systematized oppression by one race on another" በማለት አስቀምጧል። ተግባራዊ ዘረኝነትን የገለጸው Long Walk to Freedom የተባለው የማንዴላ መጽሐፍ ሲሆን እሱም "Apartheid means apartness and it represented the codification in one oppressive system of all the laws and regulations that had kept Africans in an inferior position to whites for centuries." ይላል። በተመሳሳይ ሁኔታ ብሔር ብሔረሰቦችን አሳንሶ ከሚመለከተው ሐበሻዊ አሃዳዊነት (አንድ ባንድራ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ አገር፣ ወዘተ ከሚለው ክፉ ዳዊ ራሳቸውን ለይተው (deconstruct) አድርገው የማይመለከቱ ሕብራዊ የኢትዮጵያዊያንን ስብስብ (conglomeration) ጨርሶ አያስቡትም ባይባል እንኳን ራሳቸውን መጠየቅም ሆነ ከራሳቸው ጋር መታገል የማይሹ ናቸው። የአካዳሚና የድርጊት ትርጉሞቹ ተጠቃልለው ሲታዩ አንዳቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ ከቆየም ሆነ ከወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር ሲተያይ የተከሰቱት ብሔራዊ አደረጃጀቶችን ዘረኛና አገር አፍራሽ መሆኑን አያሳዩም። ልንከድው የማንችለው ነገር ቢኖር ግን ተወራሪው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በማንነታቸው ዝቅ ተደርገው የተጠሩበት አዋራጅ ስሞች ሲታሰብ ጠሪዎቹን ነፍጠኞችና የነፍጠኛ ትውልድን እንዴት

አድርጎ ዘረኛ እንዳላስበላቸው የሚገርምና የሚደንቅ ነገር መሆኑ ነው። ወይም የዛሬዎቹ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ያለፈውን ግፍ አውስተው ባለመፈተሻቸውና ባለማውገዛቸው ከሞራል ተጠያቂነት እንደማያድናቸው አለማሰባቸው የሚያስገምታቸው ነው።

እንግዲህ ይህ ካልሆነና ብሔረተኝነት በሌሎች የማይገለጽ ከሆነና በተቃራኒው የሕዝብን የተፈጥሮ ፀጋ የሚዘርፉ ኃይሎች ዘረፋቸው እንዳይቋረጥባቸው ሲሉ ይፈጠራል ብለው ከሰጉ ደግሞ ያልታሰበውን ስጋት ፈጥረው ዘራቸው ከምድረ ገጽ እንደጠፋ ወይም ሊጠፋ እንደሆነ አድርገው ብሔሮችና ድርጅቶቻቸው ላይ ያልተገባ ውንጀላ የሚያካሂዱ ከሆነ አሃዳዊነትን ለአንድነት ተፈላጊ አድርገው ስለተመኙት ብቻ ከየትም ሊመጣ አይችልም። ተጠይቃዊ ሐሳብ ብናነሳ ደግሞ ይህ አሃዳዊነት በብሔረሰቦች ላይ የሚመጣ ነው ወይስ ለነሱ የሚመጣ ነው የሚል ይሆናል። ከመዝገበ ቃላት ትንታኔ ስንነሳ ዘረኝነት ከራሱ ዘር ውጪ ባሉ ሁሉም ሕዝቦች ላይ የተሳሳተ አስተሳሰብ መያዝ ነው። (Racism- a prejudiced against all people who belong to other races.) ብሔሩ ያፈለገ ይሁን ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በቀለም፣ በዘር፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግባቸው፤ ሁሉንም አቀፍ እና በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተ "አንድ ሰው አንድ ድምፅ" በሚል ዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ ተመስርቶ ሕዝብ በሚመርጣቸው ተወካዮች መተዳደር አለባቸው የተባለውን በዘረኝነትና አገር አፍራሽ የሚያደርጉ ከሆነ፤ መተማመንን ሊፈጥር የምችልበትን ሁኔታ ማሰቡ ይከብዳል። መተማመንና መተሳሰብ ቀርቶ ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ ጉልበተኞች ሥልጣን ላይ የሚፈናጠጡ ከሆነ ብሔረተኝነት ጎልብቶ ለብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎች መብቃታቸው እንደማይቀር እየፈሩም ሆነ እየጠሉ ከሚያስተናግዱት ስጋት መላቀቅ አይቻልም። ገንቢ ያልሆነ አቋም ይዘው ሰላምና ዕድገትም ስለተመኙት ብቻ ይኖራል ብሎ መጠበቅም ያስቸግራል።

አእምሮአችንን ሰፋ አድርገን ለየት ባለ ሁኔታ ስናይ ደግሞ ኢትዮጵያ

ውስጥ የዘረኝነት ስሜት ጭርሱንም የለም ብሎ መደምደምም ያስቸግራል። እንደአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉና ከታች ባለው የኢትዮጵያዊያን ትስስር ደንቃራዎች በሚለው አርእስት ሥር የሚዘረዘሩ ቢሆንም የተዛባ የሕዝቦች ታሪክ፣ በእምነት ተቋማት ላይ ስለሚፈጸሙ ደባዎች፣ በብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ላይ የሚፈጸሙ አድልዎአዊ አመለካከቶች ላልተፈለገ ልዩነት ከፍ ሲልም ለዘርኝነት በር ከፋቾች ናቸው። በተጨማሪም የኔ ወይም የኛ ጎሳ/ዘር ይበልጣል፣ የእሱ/የእነሱ ጎሳ/ዘር ያንሳል የሚባለውና ቢያንስ ሰዎች እኩል መፈጠራቸውን ከቃል በዘለለ በተግባር የማያሳዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ባሉበት አገር ውስጥ የተዛባ ወይም ኢፍትሓዊ የሆነ የሀብት ክፍፍልን ጨምሮ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ሲፈጠር ያ የሚፈሩት የጎሳ/የዘር ችግሮች መኖራቸው አይቀረ ይሆናል። የእኩልነት መብትም ሆነ ፍትሓዊነት ከቀጨጨ ደግሞ አገራዊ ስሜትም ይኮስምናል። ኋላቀር በሆነ ሁኔታ አንዱ ለሌላው ያልተገባ ስም መለጠፍ የትም የማያደርስ የሥነ ልቦና ዉቅር ይፈጥርና ዳፋው ለአገር ይተርፋል። በዚህም መሠረት ምንጫቸው በውል ተለይቶ ባልታቀው የኦሮሞ የዘር ምንጩ ማዳጋስካር ተብሎ መፃፉና የሐበሻ ወይም የአማራው ደግሞ ከንግስት ሳባ እና ቀዳማዊ ምንሊክ ጋር አያይዞ የዐረቡ የመን መሆኑ የሚነገረው የተዛባ የሕዝቦች ታሪክ መሆኑ አንድና ሁለት የለውም። ይህ ብቻ አይደለም ሐበሾች ለደቡብ ሕዝቦች ሲሰጡ የነበሩ ወራዳ መጠሪያዎች፤ ለምሳሌ ኦሮሞን ጋላ፣ ወላይታን ወላሞ፣ ሲዳማን ሲዳሞ፣ ሐዲያን ጉደላ፣ የምን ጃንጃሮ፣ ቤኒሻንጉልን ሻንቅላ፣ ሌሎችም እንዲህ እያሉ መጥራትና የዛሬ ትውልዳቸው ጭምር የቦታ ስሞችን ክልሎች በተስማሙበት ስሞች ላለመጥራት አሻፈረኝ ማለታቸው ራሱ ለዘረኝነት መነሻ አይሆንም የሚል ካለ ያ ሰው ወይም ቡድን ወይም ፖለቲከኛ ለኢትዮጵያዊያን አብሮነት አንዳች ደንታ እንደሌለውና ለሚከሰቱት የልዩነት ችግሮች ተጠያቂ መሆን ሲገባው ነገሩን ወደ ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝሙ ማላከክና ምስረታቸው ረጅም ጊዜ የሆነውን ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎችን ለአገራዊ አንድነት ፀር እንደሆኑ አድርጎ ያልተገባ ነገር ውስጥ ማስገባት፤ የአገራችንን ችግር መፍቻ ጊዜ ከማራዘም ውጭ የዘር ልዩነቱን ስለኮነኑት ብቻ እየታየ ያለውን የልዩነት

ችግሮችን ወዲያውኑ የሚያስቆም አይሆንም። ሲጠቃለል፤ ዘረኝነት እንዲጠፋ አዎንታዊ የሆነ ሥራ መስራት እንጂ የመንግስት ሥልጣን ይዞ ወይም የመንግስት ሥልጣን የያዙትን ተገን አድርጎ የጥላቻ ቅስቀሳ ማካሄድና ብሔረተኛ ዜጎችን መግደልም ሆነ አስሮ ማንገላታት እንዲሁም ድርጅቶቻቸውን ለማፍረስ መጣጣር አንዳች ፋይዳ አይኖረውም።

ከዚህ ከብሔር/ብሔረሰብ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በስጋት ከሚናጡት ሦስተኛዎቹ አካላት ውስጥ የማንነት ቀውስ (identity crisis) ያለባቸው ግለሰቦች ናቸው። የማንነት ቀውስ የሚከሰተው በመዋለድ ሂደት ውስጥ ከሚፈጠር ያልተጠበቀ ግንኙነትና በጥቅም ትስስር ራስን አሳልፎ ከመስጠት ነው። መዋለድን ብናነሳ አባት ከዳር አገር (ብሔር) ሆኖ እናት ከመሀል ወይም የተገላብጦሹም ዕውነት ነው፣ በሌላም በኩል አባት ቋሚ ቤተሰብ እያለው ወደ መንደር ወይም ከተማ በመመላለስ የራሱ ማንነት ከሚገለጥበት የደም ትስስር ውጪ ከሆነች ሴት ልጅ/ልጆች ቢወለዱ (በአንዳንድ አከባቢዎች የደንበኛ ልጅ ወይም የውሽማ ልጅ ወይም ድቃላም የሚባለው ዓይነቱ ሲያጋጥም) የማንነት ቀውስ ሊፈጠር ወይም ሊታይ ይችላል። እነዚህ የደንበኛ ልጆች ከስም አሰያየም ጀምሮ ሲነገራቸው የሚሰነበተው ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ሥነ ልቦና ወዘተ ከጉድኝቱ የአንዱን የሚደብቅ ወይም የሚያጥላላ ከሆነ ተወላጆቹ በተለይ የደንበኛ ልጆች የሚባሉት ለማንነት ቀውስ እንደሚጋለጡ ጥርጥር የለውም። አንዳንዶች እንዲያውም የአባታቸው ስም ቀርቶ የአጎታቸው/የሽማቸው (የእናታቸው ወንድም) ስም ይነገራቸዋል። ይህ የማንነት ቀውስ በብዙ ቦታዎች ላይ የሚከሰት ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ ግን የሐበሻ ገዥዎችን መሠረት አድርገው የተንቀሳቀሱት ዜጎች ከሐበሻ ውጭ የሚገኙ ማንነቶችን ለማዳከምና ለማጥላላት የሚፈጥሩት ችግር ቀላል አይደለም። ከተለያዩ ማንነቶች ስለተወለዱ የማንነት ቀውስ ይፈጠራል ብሎ መደምደምም አስቸጋሪ ቢሆንም በሁለቱ ወላጆች መሀከል የተዛባ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ ግን የሚፈጠረው የማንነት ቀውስ የገነነ ይሆናል። ሌላው የማንነት ቀውስ የሚፈጠረው “አሳዳጊ የበደለው” የሚባል ዓይነት ነው። ምንም ያህል

አባትና እናት ከአንድ ማንነት ቢወለዱም ወላጆች ተወላጆቻቸውን በራሳቸው ማንነት ዙሪያ አንጸው ካላሳደጓቸው ልጆቹ ድቃላ የማንነት ቀውስ (hybrid) ውስጥ ይገቡና መመለሻቸው ብዙ ያስከፍላል። ይህ ክስተት የሚኖረው በከተሞችና በውጪ አገሮች አካባቢው በሚኖሩ ወገኖች ዘንድ ሲሆን፤ ይህም ሊሆን የሚችለው አከባቢው ራሱ በሚፈጥርባቸው ተፅዕኖ ምክንያት (environmental influence) በትውልዱ ላይ የማንነት ቀውስ ይፈጠራል።

ከዚህ ጋር አደገኛ የማንነት ቀውስ የሚሆነው ሰዎች ከማንም ይወለዱ ከማንም ሰዎቹ የሀብትና የንዋይ ጥቅም ተገዥ ሆነው ወገናቸውን የሚክዱ ከሆነ ውጤቱም አደገኛ ይሆናል። ሁለቱም ኃይሎች የሕዝቦችን የነፃነትና የመብት ትግሎችን ዓላማ በትክክል እያወቁ በጥቅም ስለተገዙ ብቻ ተቃዋሚዎቻቸውን በተለይም የብሔር ማንነት የሚያነሱትን እንደ አንድነት አጥፊ አድርገው ይቆጥራሉ። በጥቅም የተገዙና የማንነት ቀውስ ያጠቃቸው ሰዎች ከማንም ብሔር ይመንጩ ጉዳያቸው ሳያደርጉት ሰውን በተለያየ ሁኔታ ያንገላታሉ፤ "ደም የጠማቸው" ተብለውም ይታወቃሉ። ጀምስ ቡትንግ የሚባል ፀሐፊ ስለ አዶልፍ ሂትለር በፃፈው መጽሐፍ ገጽ 111 ላይ "… once a man has tasted blood he never loses his appetite for it." የቅርብ ትርጉሙም፣ አንዴ ደም የቀመሰ ሰው በምንም ዓይነት ያንን ጥማቱን አይጥልም ነው። ተጠቃልሎ ሲታይ፤ የማንነት ቀውስ ያለባቸው ሰዎች ቀድመው ሌላውን ዘረኛ በማለት ድብቅ ሰው ሰራሽ የዘረኝነት ስሜታቸውን ለራሳቸውም ሆነ ለማንም በማይበጅ ሁኔታና ስልት ይገልጹታል።

በምንሊክ ማቅናት ወቅት ከአውሮፓ ወደ አፍሪካ እና ሌሎች ክፍለ ዓለማት የፈለሰዉ የዳበረ ካፒታሊስት ኤኮኖሚ ዓይነት ኢትዮጵያ ዉስጥ አለመኖሩ የታወቀ ቢሆንም ኋላቀር የሆነዉ የአበሻ ነፍጥ ተሸካሚዎች አገዛዝ በፖለቲካ አደረጃጀታቸው ያነሰና ተበታትነው ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችን፤ ነገር ግን ከአቅኚዎቻቸው የተሻለ ነዉ የሚባል ባህላዊ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የነበራቸዉን ሕዝቦች ከአዉሮፓ አገሮች

በተገኘዉ የጦር መሳሪያ አሸንፈው መያዛቸውና ተወራሪዎቹ የዕድገት ሂደታቸዉን ሳይጨርሱ ወደኋላ እንዲመለሱ መደረጋቸውን ሸምጥጠው በመካድ ቅኝ አገዛዝ ሊሰኝ ስለመቻሉ የሚጠራጠሩ ብቻ ሳይሆን የሚክዱ ብዙ ናቸዉ። እንዲያዉም እንደ አሰፋ ጫቦ የመሳሰሉት ተወራሪዎቹ የደቡብ ሕዝቦች ቅኝ ተገዙ ሳይሆን እንዲቀኑና እንዲሰለጥኑ የተደረጉ ስለሆነ፤ ስለቅኝ አገዛዝ የማታዉቁ ካልሆነ በስተቀር ሰሜነኞቹ አበሾች ደቡቦች ሕዝቦችን ቅኝ አደረጉ ብላችሁ ባታወሩ ይሻላል የሚል ምክር አዘል ግሳፄ የሚያደርጉ የአሃዳዊነት ቡድኖች ቀላል ቁጥር የላቸዉም። ነገር ግን በኤኮኖሚ ያልዳበሩ የሰሜን ኢትዮጵያ ገዥዎች የደቡቦችን ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ኑሮ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወዘተ ላይ ጫና ስላላሳረፉ የዳበረ ካፒታሊዝም የፈጠረዉ ዓይነት ቅኝ አገዛዝ አይደለም ለማለት ይዳዳቸዋል። ቅኝ አገዛዝ ነዉ ከማለት በላይ ሌላ ስም ፍለጋ ሄዶ ዳቦ ማስቆረስ አስፈላጊ አይደለም ብለዉ በተቃራኒዉ የሚደመጡ ወገኖችም እንዳሉ መዘንጋት አይቻልም። ሁሉን አቀፍ የቅኝ ገዥዎች ድርጊቶች ማለትም የሰውና የቦታ ስሞች ተቀይረዋል፣ የአምልኮ ሥፍራዎች ተወስደዋል፣ የብሔር ተወላጆች ከነባር ባህላቸውና ቋንቋቸው ተነጥለዋል፣ ልጆቻቸው ቢማሩ እንኳን ተገቢ ሥፍራ እንዳያገኙ ተደርገዋል። ስለሆነም የቀለም ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ቅኝ አገዛዝ የሚወስደውን የአገዛዝ ፓኬጅ ሁሉ በኢትዮጵያ የደቡብ ሕዝቦች ላይ ፈጽመዋል።

ለማንኛዉም የዳበረ የአዉሮፓዉም ሆነ ኋላቀሩ የአፍሪካ፤ ሁለቱንም ሊያመሳስል የሚችለዉ፤ ቅኝ አገዛዝ ማለት ያንድ አገር ሥርአት የተወራሪ ሌላ አገር ሥርአት በቁጥጥር ሥር ማድረግ ነዉ። ቅኝ ገዥዎች የራሳቸዉን ሰዎች ወደ ቅኝ ተገዥዎች በመላክ ቅኝ ተገዥዉን ሕዝብ ይገዛሉ። አሊያም ከቅኝ ተገዥዎች የተወሰኑትን በማላመድና በወገኖቻቸው ላይ በመመደብ ይገዛሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ምንም እንኳን የዳበረ ኤኮኖሚ ባይኖራቸዉም፤ በነበራቸዉ የፖለቲካ ብልጠትና የበላይነት፤ አበሾች ነፍጥ የያዙ ታጣቂዎችን (ነፍጠኞችን) በመላክ የደቡብ ሕዝቦችን ገዝተዋልና ሌላ መጠሪያ ያስፈልጋቸዉ እንደሆን ወይም ለማግኘት

ካልተፈለገ በስተቀር ቅኝ ገዥዎች ናቸዉ ቢባሉ የአዉሮፓ ዓይነቱ ካልመጣ ወይም ሰዎቹ ነጭ ካልሆኑ በስተቀር ቅኝ አገዛዝ አይደለም የሚያሰኝ አይደለም። ይህንን ሁሉ ችግር የሚያስከትል የአገዛዝ ሥርአት፤ ቅኝ አገዛዝ ነዉ መባሉ፤ ላለፈዉ ታሪክም ሆነ ላሁኑ ወንጀል ግልፅነትን ለማስቀመጥ ካልሆነ በስተቀር ለኢትዮጵያዊያን አብሮነት እንቅፋት ሊሆን አይችልም ብሎ መደምደም ሲቻል፤ የብሔሮች ራስን በራስ ማስተዳደርን የአገር አንድነት አፍራሽና ዘረኝነት ነው በማለት እነዚያው የምኒልክ ደቀ መዝሙሮች ዛሬም ይሞግታሉ። ለማንኛዉም ለብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ድርጅቶች ማቆጥቆጥ መነሻ ምክንያቶች ምን እንደሆኑና ከፍ ሲል ዛሬ ለኢትዮጵያ መፍረስ እንደሰበብ ስለሚኮነነው ብሔራዊ ፌዴራሊዝም በቦታው ላይ እንፈትሻለን። አሁን ስለብሔራዊ አርነት ነቅናቄዎች እነሆ!

## የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ

የዚህ ነፃነት ግንባር አባላት የኢትዮጵያ ሱማሌ ወይም ኦጋዴንያ ተብለዉ የሚታወቁ ናቸዉ። የዚህ ድርጅት አንዱ ታሪካዊ መነሻ የኢትዮጵያ ገዥዎችን ፀረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ለመጣል ቢሆንም፤ በስተጀርባው በኩል ግን የቅኝ ገዥዎች ተመሳሳይ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ያላቸዉን ሕዝቦች በሁለትና ከዚያም በላይ በሆኑ ቦታዎች ላይ ክፍፍልን ለመቀልበስና የኦጋዴን ብሔራዊ ንቅናቄም የሚኖሩበትን አከባቢ ከእናት ምድር (mainland) ሱማሊያ አገር ጋር ለመቀላቀል የሚያደርጉት ትግል ነዉ። የአፍሪካ ቅኝ ገዥዎች (የአበሻዉ ምኒልክን ጨምሮ) ከ1884ቱ የበርሊን ጉባኤ የአፍሪካ ቅርሚት በኋላ የፈጸሙትን ወንጀል ዴቪድ ላምብ የሚባለዉ “The Africans” ብሎ በፃፈዉና ነቢዩ እያሱ “አፍሪካና አምባገነን መሪዋ›› ብሎ በተረጎመዉ መፅሐፍ ገፅ 134 ላይ እንደምነበበዉ ቅኝ ገዥዎች ‹‹ብሔረሰቦች የበዙባትን አፍሪካ ባህላዊ ተመሳሳይነት ያልጠበቀና ለዚህም ግድ ያላደረገ ክፍፍል በማድረግ አንድ ቋንቋ የሚናገሩትን ብሔረሰቦች ለሁለትና ለሦስት ከፋፍሎ በተለያዩ አገሮች በታተኗቸዉ። ለምዕተ ዓመታት በቋንቋ ተመሳሳይነት በጋራ ቅርስና ታሪክ ተሳስረዉ የኖሩትን ሕዝቦች በመለያየት ለትዉልዶች

የሚተርፍ ችግር ፈጠሩ።” ብሏል። በዚህም መሠረት የሶማሊያ ሕዝብ ቢያንስ አራት ቦታዎች ላይ ማለትም በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በጂቡቲና በራሱ በሶማሊያ እንዲበጣጠቅ ተደርጓል። ተመሳሳይ ችግሮች በብዙ የአፍሪካ አገሮች መሀከል ቢኖርም አንዳንዶቹ በስምምነት፣ ሌሎች ደግሞ በነፃነት መፍትኼ እንዲያገኙ ተደርጓል። የኦጋዴንያ ክልል ጉዳይ ግን በዲሞክራሲያዊ አግባብ ይሁን በነፃነት መፍትኼ ያግኝ ገና ተለይቶ ከሚታወቅበት ደረጃ ላይ አልደረሰም፤ ወይም እንደተንጠለጠለ ይገኛል።

ሕዝቦች ለነፃነት በሚያደርጉት ትግል ወቅትም ሆነ ይፋዊ ነፃነታቸዉን ከተቀዳጁም በኋላ የሚከተሉትን የዕድገት ትልም ወይም ፖሊሲ እንዲያሳኩ ሊያሰባስባቸዉ የሚችል አታጋይ ድርጅት ይፈጥራሉ። በተለይ በአፍሪካ ዉስጥ በቅኝ አገዛዝ ጊዜ የነበረዉን ዓለም አቀፍ የየአገሮች ድንበሮችን መቀያየር ከሚያስከትለዉ ችግር ስጋት ለመዳን ሲባል፤ ይህንኑ ለመከላከል በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሥር የተለያዩ ድንጋጌዎች እንዲደነገጉ ቢደረግም፤ የነፃነት ትግሎች መኖርን ማስቀረት ግን አልተቻለም። ለማስቀረት ያልተቻለበት ምክንያቱ ደግሞ በጣም ቀላል ነዉ፤ ከቅኝ ገዥዎች ቀጥለው ሥልጣን የተቆናጠጡት አፍሪካዊያን መሪዎች ከቅኝ ገዥ ጌቶች በባሰ ሁኔታ ሕዝቦችን ከሰብአዊ ርህራሄ ዉጭ መግዛታቸው ነዉ። ስለሆነም አንድ ዓይነት ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ኖሮት በብዙ ቦታዎች የተቆራረጡትን ማስተዳደር አልቻሉም። የተከፉት ደግሞ ምርጫ ሲያጡ ወይም ምርጫቸዉ በጉልበተኞች ውድቅ ሲደረግባቸዉ ብረት ይዘዉ ዱር ቤቴ ማለትን ይመረጣሉ። የኦጋዴንያዉ ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ታሪክም ከዚሁ የተለየ አይደለም።

ይህ ብቻም አይደለም፤ የነፃነት ትግል የሚያደርጉት ድርጅቶች ብረት ለማንሳታቸዉ የሚያቀርቡት ምክንያት፤ የእኔ ነው የሚሉት ሕዝብ ፍትሓዊ የልማትና የዕድገት ተጠቃሚ እንዳልሆነ አስምረዉ ይገልፃሉ። ይህም በገዥዎች አድሎአዊ አመራር የተነሳ የሚወክሉት ሕዝብ በአገሪቱ ልማትም ሆነ የሀብት ክፍፍል ዉስጥ ተገቢዉን ፍትሓዊ ድርሻ

አለማግኘት መሆኑን አበክረዉ ይናገራሉ። አግላይ የሆነ የአስተዳደር ዘይቤ መፈጠርና በተለይም የገዥዉ ክፍል የአገዛዝ ሁኔታ ከባህላዊዉ የዚያ የተጨቆነዉ ሕዝብ አስተዳደር አንሶ የሚገኝ ከሆነና፣ ከዚህም የተነሳ የሕዝብ ቅሬታ እየጨመረ ሲሄድ፣ መፍትኼ የማግኘት ተስፋዉም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሟጠጠ ሲሄድ፤ አገዛዙን ቢማጠኑትም ሆነ ቢገፉት መሻሻልን የማያመጣ ከሆነ፤ ሲብስባቸዉም ቢታገሉት ውጤት የማያገኙ ከሆነ፤ የመጨረሻ አማራጭ ወደ ሆነዉ የነፃነት ትግል የተወሰነ የሕብረተሰባቸዉን ክፍል በማሳማን የትጥቅ ትግል መጀመር አስፈላጊ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። በዚሁ መሠረት በኢትዮጵያ ዉስጥ በሱማሌ ክልል ብቻ ሳይሆን በማንኛዉም አከባቢ የሚገኙ ሕዝቦች ከሌላዉ ዓለም ሕዝብ ባነሰ ሁኔታ ከልማት ወደኋላ የቀሩ ናቸዉ። ስለዚህ የሚጠይቁት ጥያቄ የፍትህ ጥያቄ ሆኖ እያለ የሚሰማን አጥተናል ብለዉ ብረት አንስተዉ ዱር ቤቴ ማለት ከጀመሩ ጊዜዉ እየገፋ ሄዷል። ስለሆነም የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ነሐሴ ወር 1970 ተመሠርቶ፤ ጥምር ዓላማ ማለትም ሰሚ ከተገኘ በትልቋ ኢትዮጵያ ውስጥ ለፍትሓዊ ልማት መታገል ካልተቻለም ደግሞ ለሕዝቡ ነፃነት ተከታታይ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስታትን በመፋለም እስከ 2010 ዓም የቆየ  የነፃነት ድርጅት ነዉ።

አንድ ሊደበቅ የማይችል ነገር ቢኖር ግን የኦጋዴን ብሔራዊ የነፃነት ግንባር ለራሱ ሕዝብ መብት የሚቀርበው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚንቃሳቀሱ የአርነት ግንባሮች ወይም ድርጅቶች ይልቅ የሁለት ጎጀዎች ምኞተኛ ሆኖ ወደ ሶማሊያ መንግስት ያደላ እንደነበር ይገለፃል። ይህ በመሆኑም በተለይ ከኦሮሞ የነፃነት ግንባር ጋር ለራሱም ሆነ ከዋናው ሶማሊያ መንግስት ከቀጠለው የመሬት ጥያቄ (irredentism- a policy advocating the restoration of a territory to a country of formerly belonging to it) በማንገቡ የረባ የጋራ የትግል እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዳልቻለ ይነገራል። ይህ በኦሮምያ ላይ የሚቀርበው የመሬት ጥያቄ ነገር ከ2010 በኋላ ሳይቀር አገርሽቶና የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ሕልውና ለማጥፋት ሕዝብን ማጥፋት ተብሎ በኦህዴድ በተወሰደው ፋሽስታዊ

ዕርምጃ በሱማሌ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጆችን እስከ ማፈናቀል ደርሷል። ከ2010 ዓም በኋላ የኦጋዴን ብሔራዊ አርነት ንቅናቄ የክልሉ ገዥ ፓርቲ መሆን ብቻ ሳይሆን፤ ዘላቂ ወዳጅም ሆነ ጠላት የለም የሚለውን አባባል ዕውነት በሚያስብል ሁኔታ የፌዴራል መንግስቱን ሥልጣን ለመዘወር ከኢህአዴግ ወደ ብልፅግና ፓርቲ የስም ለውጥ ካደረገው ፓርቲ ጋር ሆኖ አገር በማስተዳደር ላይ ይገኛል። ከተጠቀሰው 2010 ዓም በፊት በነበረው ጊዜ ውስጥ የድርጅቱ አባላትና ሕዝቡ ያየው መከራ ቀላል እንዳልነበር በወያኔ/ኢህአዴግ ሥር በጅግጅጋ እስር ቤት ውስጥ በመፀዳጃ ቱቦ ላይ፣ በመሬት ሥር እና ከዱር አውሬዎች ጋር ታስረው ያዩት መከራ ሲታሰብ እውነትም የአርነት ንቅናቄዎች ገና ከቤታቸውም ሆነ ከመንደራቸው ሲወጡ ምን ዓይነት ቃል ኪዳን ለፈጣሪያቸው፣ ለሕዝባቸው እና ለራሳቸው እንደሚገቡ ለማመን የሚያስቸግር፤ ነገር ግን ዕውነት የሆነ ቃል ኪዳን እንደሆነ የሚያስረዳ አሻራ አለ። ምንም እንኳን በኦጋዴን ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄ አመራር ውስጥ የግል ጥቅም ግጭት የተፈጠረባቸው እንዳሉ እየታየ ቢሆንም፤ ሶማሌዎች አንድ የማይሸረሸር እሴት እንዳላቸው ይነገራል። ይኼውም ለግልም ሆነ ለማህበረሰቡ የሚገባ ጥቅም መጠየቅ ከጀመሩ አንዴ ጊዜ ቢከለከሉ እንኳን አንድ መቶ አንድ ጊዜ ከመጠየቅም ሆነ ከመታገል እንደማይመለሱ ባህላዊ ቅርሳቸው እንደሆነ ሕዝቡን በቅርብ የሚያውቁ ሰዎች ስናገሩ ይደመጣል።

## የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ

“ለመሆኑ ኦሮሞ ደግሞ ምን ተቸገርኩ ብሎ ነዉ ሊገንጠል የሚለዉ?” ሲል ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የተናገረውን የለበጣ ንግግርን ሳስታዉስ ትንሽም ቢሆን ያስፈግጋል። የኦሮሞ ሕዝብ ችግር እንደሌላዉ ሕዝብ፣ ማለትም እንደ ሲዳማዉ፣ እንደ ወላይታዉ፣ እንደ ከንባታዉ፣ እንደ ሐዲያዉ፣ እንደ ኑዌሩ፣ እንደ አኙዋኩ፣ እንደ ቤኒሻንጉሌዉ፣ እንደ ትግሬዉ፣ እንደ ቀሪዎቹ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ችግር መሆኑ ተዘንግቶ የለበጣ ጥያቄ ተነስቶ በመንግስቱ ኃይለማርያም ሲጠየቅ

የመጀመሪያም ላይሆን ይችላል። ዛሬም ላይ ሆነን ወደፊትና ወደኋላ አድርገን ስንመለከት የኦሮሞ ሕዝብ ችግር ከአማራዉና ከትግሬዉ ችግር ጋር ተመሳሳይ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። እንደ ሕዝብ ችግር በሚታይበት ጊዜ ግን የኦሮሞና የሀበሻ ሕዝቦች (አማራና ትግሬ ማለቴ ነዉ) ችግር ተመሳሳይ ይሆናል። እንደ አገዛዝ ከሆነ ግን የሐበሻው ጉዳይ ሲገለልና ወደ ዳር ሲገፋ ከኖረው የኦሮሞ ተወላጆች ችግር የተለየ እንደሆነ ጥያቄ የለውም። ወደ ኋላ ተመልሰን ብንመለከት የአማራና የትግሬ ገበሬ ቢያንስ በመሬት ይዞታ ስሪቱ ውስጥ ከኦሮሞው የመሬት ስሪት ልዩነት ነበረው። ስለሆነም፤ የአማራው ገበሬ የኦሮሞ ገበሬ በተበደለበት ሁኔታ አልተበደለም። በሌላም በኩል የአማራና የትግሬ ገዥዎች እየተፈራረቁም ቢሆን ሌሎች ሕዝቦችን ገዝተዋል። ኦሮሞ ግን የሐበሻ ገዥዎች ሥርአት ውስጥ ከማንበጫረቅ በዘለለ በራሱ ሥርአት ኢትዮጵያን አልገዛም። የገቡትም ቢሆኑ የበታችነት ሥነ ልቦና እየተሰማቸው ከራሳቸው ባሻገር ሕዝባቸውን ሳይጠቅሙ እንደፍጥምጥማቸው ተሰናብተዋል። ስለሆነም የኦሮሞን የፖለቲካ ጉዳይ ከአማራዉና ትግሬዉ ተለይቶ መታየቱን የግድ የሚያደርገዉ እስከ ዛሬም የዘለቀውና በኦሮሞ ላይ ከተጋረጠዉ የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ የማግለል ችግር (marginalization) እና እስከ ዛሬም ቢሆን የኦሮሞ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ወደ ዳር ከመገፋት (cornering) ጋር የመነጨ ስለሆነ ነዉ።

ሌላም የለበጣ ንግግር አለ፤ በኃይሌ ሥላሴም ሆነ በደርግ ጊዜ በሥልጣን ላይ እንኳን ባይሆን በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች በአመራር ላይ እንደ ነበሩና ኦሮሞ የአገዛዙ አካል እንደነበረ አልፎ አልፎ ይደመጣል። በኦሮሞ ሕዝብ ሕልዉና ላይ ለማላገጥ ሲፈልጉ የዚህን የኦሮሞ ተወላጆች በአገዛዝ ሥርአቱ ውስጥ መሳተፍ ልክ የአፍሪካ አገሮች የባንድራ ነፃነታቸዉን ከማግኘታቸዉ በፊት የነበሩ መንግስታት የአዉሮፓ ቅኝ ገዥዎች ሎንዶንና ፓርስ ላይ ተቀምጠዉ የሚገዙበት የአፍሪካዊያን አገዛዝ ዓይነትን እየተገበሩ መሆኑ ተረስቶ፤ የኦሮሞ ሕዝብ በአገዛዙ ውስጥ እንደተሳተፈ መቁጠር በሕዝቦች ሕሊናና ሕልውና ላይ ማላገጥ እንደሆነ እያወቁ አያውቁም። የኦሮሞ ተወላጆች በብዛት በአመራር ላይ ቢኖሩ

እንኳን እነዚያ ኦሮሞዎች ለኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም የቆሙ ሳይሆን በኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም ላይ ቆመው ከባዕድ ጋር የተዋሃዱ (assimilandos) ወይም ኦሮሞን የከዱ ሰዎች (traitors) ነበሩ። ወይም ሌላውን ሕዝብ ለማስገበር ከምንሊክ ጋር ያበሩ እንደ የጂማው አባ ጅፋር፣ የሌቃው ኩምሳ ሞረዳን እና ሌቃ ቀለሙ ጆቴ ቱሉ፣ ጎበና ዳጪ፣ ቁሴ ድናግዴ፣ ባልቻ ሣፎ ዓይነት የነበሩትንና በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ በመጥፎ ምሳሌ የሚጠሩትን በመውሰድ ይሆናል። ዛሬም ከዚያ ያልተለዩና በኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም ላይ የቆሙ ከሃዲ የኦሮሞ ተወላጆች በአመራር ላይ እንዳሉ መለየት የማይችሉ ሰዎች ስለመኖራቸው ችግር የሚሆንባቸው አሉ። እዚህ ላይ ስለክህደትና ታማኝነት የተለያየ ግንዛቤዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ከማንኛዉም ማህበረሰብ ግንዛቤ አንፃር ማን በምን ጉዳይ ከሃዲ ሆነ በሚለዉ ጥያቄ አንፃር የሚሰጠዉ መልስም እንደዚያው የሚለያይና አወዛጋቢ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ እየተወሰደ፤ ነገር ግን አንድ የማያወዛግብ ነገር ቢኖር አሚጣ የወለደችዉን እናቱን አሳልፎ ለጠላት ካራ የሚሰጥ ሰዉ ካለ እሱ/እሷ ሰው ያለምንም ማወላወል ከሃዲ ነዉ/ነች። ኦሮሞ ሆነዉ በመንግስት ባለሥልጣንነት መስራታቸዉ ወንጀል ባይሆንም፤ ነገሩ ሥራዉን እየሰሩ ለኦሮሚያ እርድ ለጠላት ካራ ያቀበሉ ሰዎች ከሃዲዎች ተባሉ እንጂ የኦሮሞ ሕዝብ የሚገባዉን እንዲያገኝ አላደረጉም፤ በዚህ ምክንያት ቢወቀሱም ሆነ ቢወገዙ ምክንያታዊ ነው። አንድ ወቅት ላይ ሕወሓት ከኦነግ በተሻለ ለኦሮሞ ሕዝብ ይቀርባል ብሎ የተናገረው የኦፒዲኦ ሰው አባዱላ ገመዳ የከሃዲዎች ምሳሌ ከመባል ምንም የሚያስቀረው ነገር አይኖርም። ይህንን ግለሰብ አስመልክቶ ሰለሞን ስዩም የኢህአዴግ ፍፃሜ (2005፡ 182) ብሎ በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ “የኦነግ የምን ጊዜም ጠላት የሆኑት አባዱላ ገመዳ ከ[ሕወሓት] ተሿሚዎች በማፈንገጥ ወይም በማሴር እምብዛም የሚጠረጠር አልነበሩም።” በማለት ስለከሃድነቱ አስረግጦ ጽፏል። በመሆኑም የኦሮሞ ተወላጅ በመሆናቸውና በመንግስት ሥልጣን ወንበር ላይ መውጣታቸው ተመዝኖ የግለሰብን ሥልጣን ከሥርአት ጋር ሳያገናዝቡ ኦሮሞ እንደሕዝብ የሥልጣን ተጋሪ እንደሆኑ መግለፅ አደናጋሪዎች ቢሆኑ እንጂ ዕውነታን የማይገልጹ ናቸው።

ኦሮምያ ኢትዮጵያ ተብላ በዓለም ካርታ ላይ በምትታወቅ አገር ዉስጥ የሚገኝ አንድ ክልል ሲሆን፤ ተወላጁ ኦሮሞ ደግሞ በሀገሪቱ በቁጥር ትልቁ ብሔር ነዉ። እንደ አንዳንድ መንግስታዊ ወይም ይፋዊ ባልሆኑ መረጃዎች ኦሮሞ ከአገሪቱ ሕዝብ 45.5 በመቶ ይሸፍናል። ከመፅሐፍ ቅዱስ ገለፃ አንፃር ኦሮሞ የኩሽ ሕዝብ ዘር ግንድ አንዱ ቅርንጫፍ ነዉ። ሔል ሊንዲስ ፅፎት ማሞ ዉድነህ ከተረጎመዉ የ መጨዉ ጊዜ መፅሐፍ ገፅ 81 ላይ ‹‹በዕብራይስጥ ቋንቋ "ኩሽ" የሚለዉ መጠሪያ [በኋላ ላይ] ኢትዮጵያ ለምትባለዉ ሀገር የተሰጠ ትርጉም ነዉ። ኩሽ ማለት ደግሞ የኖህ የልጁ ልጅ የካም ልጅ ነዉ" በማለት የዘር ግንዱን ሲያስቀምጥ፤ ታቦር ዋሚም ከላይ በተጠቀሰዉ የራሱ መፅሐፉ ገፅ 8 ላይ ‹‹የኦሮሞ ሕዝብ ትልቁ የኩሽ ሕዝቦች ቅርንጫፍ›› በማለት ዋቢ በማስቀመጥ አስነብቦናል።

ኦሮሞ በአፄ ቴዎድሮስ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ገዳ በመባል የሚታወቅ ባህላዊ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር የነበረዉና አፋን ኦሮሞም ከመግባቢያ ቋንቋነት ባሻገር በሥራ ቋንቋነትም ሲጠቀም የነበረ ሕዝብ ነዉ። ይህ የቋንቋ መጠቀም ከ1847 ጀምሮ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ በጣሊያን ወረራ ወቅት የሥራ ቋንቋ ሆኖ ለትንሽ ጊዜ አገልግሎት ከሰጠ በኋላ፤ በኃይሌ ሥላሴ ከሸሸት መልስ ጋር ቋንቋዉ አገልግሎት እንዳይሰጥ ከመደረጉም በላይ የኦሮሞ ዜጎች ሕልዉናም ራሱ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ ገብቶ እንደነበርና በ1983 በማንሰራራት በክልል ደረጃ ሥራ ላይ በጽሑፍ የዋለ የሕዝብ ቋንቋ ነዉ። እዚህ ላይ ቀድሞስ አፋን ኦሮሞን ከመጠቀም የታገደበት ጊዜ አልነበረም እያሉ እንደማላገጥ የሚዳዳቸው ሰዎች መኖራቸው ነው። ለነዚህ ደግሞ መልሱ አምሃ ዳኘው ተሰማ አንደርሰንን ዋቢ አድርጎ እንደጠቀሰው … ብሔረኝነትን የሚፈጥረው ማንኛውም ቋንቋ ሳይሆን ለህትመት የበቃ እና በህትመት አማካይነት በስፋት የተሰራጨ ቋንቋ ነው።" በማለት መልስ ሰጥቷል። መባሉ ስለታወቀና ከራሱ ብሔር አባላት ሌላ ሌሎች ሰፊ ተጠቃሚዎች እንዳሉት እየታወቀ አፋን ኦሮሞ ለህትመት እንዳይበቃ እና ለህትመት ከበቃም በኋላ

ለህትመት የተጠቀመበት በተለምዶ የላቲን ፊደላት ከሚባለው ጋር ተያይዞ በስፋት እንዲጥላላ በመደረጉ የአፋን ኦሮሞ ህትመት በስፋት እንዳይሰራጭ በቀጥታና በስልት እንዲዳፈን ተደርጓል።

ኦሮሞ በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገ አከባቢ የሚኖር ሕዝብ ሲሆን፤ ከደረሰበት የተዛባ አስተዳደር የተነሳ እስከዛሬ ድረስ ደሄይቶ የሚኖር ሕዝብ ነዉ። በአጭር አገላለጽ ኦሮሞ ማለት ሀብታም አገር ያለዉ ሞላጫ ድሃ እንዲሆን የተደረገ ሕዝብ ነው ቢባል ያለበትን ሁኔታ ሊገልፅ ይችላል። ልድገመውና ከደረሰበት የተዛባ አስተዳደር የተነሳ የኦሮሞ ድህነቱ የሀብት ብቻ ሳይሆን ከሚደረግበት ጫና የተነሳ የአእምሮም ድሃ እንዲሆን ተገድዷል። ኦሮሞ ገዳ ተብሎ በሚታወቀዉና በዕድሜ ላይ በተመሠረተ ባህላዊ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ይተዳደር የነበረ ሕዝብ ሲሆን፤ ይህ ባህላዊ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደሩ ከባዕዳን ገዥዎች ከደረሰበት ጫና የተነሳ ወደ በለፀገ ዘመናዊ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዳያድግ የተደረገ አገርኛ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ራሱ ማንነቱን እንዲረሳ ብሎም እንዲጠላ የተገደደ ሕዝብ ነዉ። ይህ ብቻም አይደለም፤ የኦሮሞ ሕዝብ በቁጥር ብዛት ያለው ሕዝብ ከፍተኛ ሆኖ በዓለም ላይ ከደቡብ አፍሪካ የነጭ ዘረኝነት አገዛዝ (አፓርታይድ) ነፃነቱን ከጠየቀው ጥቁር ሕዝብ ቀጥሎ መብቱን በቁጥር አናሳ ከሆነው የሐበሻ ገዥዎች እየጠየቀ የኖረ ሕዝብ ነው።

ከዚህ ጋር ሊታይ የሚገባ ነገር ቢኖር አንድ ሕዝብ በመፍለስም ሆነ በኃይል በመስፋፋት የሚሰፍርባቸዉ አከባቢዎች ይኖራል። ለምሳሌ የዛሬ የተባበረ አሜሪካ የሚባለው አከባቢ ቀይ ሕንዶች የሚባሉ ሕዝቦች ይኖሩበት እንደነበርና እንግሊዞች ያፈናቀሏቸውና የራሳቸውን ዜጎች ያሰፈሩባቸው ቦታ ማለትም የዛሬው የነጮች ግዛት አውስትራሊያ አቦርጂኒስ ይባሉ የነበሩ ነባር ጥቁር ሕዝቦች ይኖሩበት እንደነበር የሚታወቅ ነው። አዲሱ ነዋሪ ወይም መጤው ያንን አከባቢ ብቻዉን ወይም ከሌላዉ ጋር በሚፈጥሩት መስተጋብር ይጠቀሙበታል። የኦሮሞ ሕዝብ ዛሬ ኢትዮጵያ ተብላ በምትታወቅ አገር ዉስጥ ከላይ በተጠቀሰው

ሁኔታ ማዕከላዊዉን ሥፍራ በመያዝ በመኖር ላይ የሚገኝ ሕዝብ ነዉ። ‹በታላቋ› ኢትዮጵያ ዉስጥ የኦሮሞ ሕዝብ ተመችቶት እየኖረ ነዉ ወይስ አይደለም ለማለት ደግሞ ለዚህ የሚመጥን መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ቢሆንም (ለዚያዉም በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሥራ ለመስራት ሕጋዊና ተቋዋማዊ ሁኔታዎች የሚፈቀዱ ከሆነ)፤ ሕይወት ለኦሮሞ ሕዝብ ያልተመቸና ይኼዉ ይስተካከል ዘንድ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የኦሮሞ ሕዝብን በማሳተፍ በመታገል ላይ የቆየውና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ሕዝቡ የሚደግፈዉ ድርጅት አንዱ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ተቋቁሞ ከትጥቅ እስከ ሠላማዊ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው።

ኢትዮጵያ በዕድገት የዓለም ጭራ መሆኗ አብዛኛዉ ሕዝቦቿ የሚስማሙበት ቢሆንም፤ በኦሮሞና ሌሎች የደቡብ ሕዝቦች ላይ ስለሚደርሰዉ ጭቆና ሲነሳ የጭቆናዉ ምንነት ላይ የሚሰጠዉ መልስ ቁርጠኝነት ራሱ ይለያያል። ለኋላቀርነቱ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የአበሾች ቅኝ አገዛዝ እንደሆነ አጥብቀው የሚከራከሩ የመኖራቸውን ያህል ከዚሁ በተቃራኒ ደግሞ ለጦር መሳሪያ ሸመታ ወደ አውሮፓ ኃይሎች የተጠጋው የአበሻ ቅኝ አገዛዝ ራሱ ኋላቀርና ጥገኛ ቅኝ አገዛዝ ከመሆኑ ውጭ እስከ ዛሬም ቢሆን የዳበረ አስተዳደር ማስፈን ያልቻለ አገዛዝ እንደሆነ ጥርጣሬ እንደሌላቸዉ አስረግጠዉ የሚገልጹ አሉ። ምንም ተባለ ምን በዚሁ የአበሻ ጥገኛ ቅኝ አገዛዝ የተመረረ የኦሮሞ ሕዝብ ኤሊት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ በመባል የሚታወቀዉን ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ በ1962/63 (በነ መገርሳ በሪ፣ አቦማ ምትኩ፣ ሙሄ አብዶ፣ ሌንጮ ለታ፣ ገላሳ ድልቦ፣ ዲማ ኖጎ፣ ኢብሳ ጉተማ፣ አባቢያ፣ ኤሌሞ ቂልጡ፣ እና ሌሎች በስም ያላስታወስኳቸው) በማቋቋም ማዕከላዊዉን የኢትዮጵያ መንግስት መፋለም ከጀመሩ እነሆ ዛሬ ወደ አምስት አስርተ ዓመታት ተቆጥሯል። ከኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም የለበጣ አነጋገር ጀምሮ እስከ ተራ የሚባል ዜጋና ቁንጮ ባለሥልጣን ደረጃ ድረስ ስለኦሮሞ ሕዝብ የነፃነት ትግል መስማትም ሆነ መናገር የማይወዱ አምባገነኖች ቢኖሩም፤ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ  የራሱ የሆነ ጉልህ ሥፍራ ያለዉና

ይህንን ከኢትዮጵያ ግዙፍ የሆነ ሕዝብ እወክላለሁ ስለሚለዉ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄ ከታሪክ አንፃር ምን ሰርቷል፣ ምንስ ይቀረዋል ብሎ ከመመዘን ሳይሆን፤ ይዞ የተነሳዉ ዓላማ ምንድን ነዉ? በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ በጥንካሬውም ሆነ በድክመቱ ምን ሚና ተጫውቷል የሚለዉን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊና ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ለኦሮሞ ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄ መቀጣጠል የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ እንዳልሆነ ብዙ መሠረታዊ ድርጅቶችን ወደኋላ ተመልሶ ለማንሳት ያህል፤ እ.አ.አ በ1969 የመን አገር በጃራ አባገዳ (Jaarraa Abbaa Gadaa) የተቋቋመዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ አዉጪ ግንባር (Ethiopia National Liberation Front)፣ እ.አ.አ በ1973 በምዕራብ ሐረርጌ በደሳ ወረዳ ዉስጥ በኤሌሞ ቂልጡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተተኮሰዉ አንድ ጥይት፣ የሐረሩ አፍራን ቃሎ ከያኒ ወጣቶች እንቅስቃሴ፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት በመጫ ኦሮሞዎች ተነስቶ የነበረዉ የምዕራብ ኦሮሚያ ፌዴሬሽንና ከ1956 ጀምሮ ደግሞ በሥር ነቀል አደረጃጀቱ የሚታወቀዉን የመጫ ቱላማ መረዳጃና ልማት ማህበር የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡ በተለይም ስለኦሮሞ ብሔርና ስለብሔራዊ ንቅናቄዉ መነሳት ካለበትም በመጀመሪያ መነሳት ያለበት ጉዳይ ስለዚሁ ማህበራዊ ተቋም፤ ስለመጫና ቱላማ የመረዳጃና ልማት ማህበር ታሪክ መሆን እንዳለበት ብዙ የኦሮሞ ተወላጆች የሚስማሙበት ሲሆን፤ የዚህን ድርጅት ሚና ቀንጨብ አድርጎ እንኳን ሳይጠቀስ ማለፍ፤ ስለኦሮሞ ሕዝብ ትግል የሚነሳዉ ሐሳብ ሙሉዕ ሊሆን እንደማይችል ያሰምሩበታል፡፡ ፕሮፌሰር መሐማድ ሐሴን “Being and Becoming Oromo በተባለው ስብስብ መጽሐፍ (1996፡ 74) ላይ “… the Metcha-Tulama Association … championed the political, social, cultural, educational and health improvements, and political rights of the Oromo people and symbolized the collective will and determination of the Oromo to assert their unity, and human diginity.” በማለት ለማህበሩ የሚመጥን ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በማንኛዉም ሕብረተሰብ ዘንድ ትግል ቆስቋሽ አካል እንደሚኖር ሁሉ የኦሮሞ ሕዝብን ከድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ የኦሮሞ ሕዝብን በልማት ዙሪያ ለማሰባስብ እግረ መንገዱንም ለብሔር ማንነቱ ግንባታ መሠረት ለመጣል እንዲሁም የትግል ስልቱንም ከፍ ለማድረግ ከተቋቋሙት ድርጅቶች ዉስጥ በ1956 የተቋቋመዉ የመጫ ቱላማ የመረዳጃና ልማት ማህበር ግንባር ቀደሙና ሚናዉም የላቀ ማህበራዊ ድርጅት ነው። የመጫና ቱላማ የመረዳጃና ልማት ማህበር ዓላማዎች ናቸዉ ተብለዉ የተጠቀሱትን ለማስፈፀም እስከ የዛሬዉ የአዲስ አበባ ዩኒቬርስቲ ድረስ በመስፋፋት መሠረተ ሰፊ እንቅስቃሴ ሊፈጥር ችሎም ነበር። በዚህ በተፈጠረዉ በመጫ ቱላማ መረዳጃ ማህበር ዉስጥ የኦሮሞን የብሔርተኝነት ንቃት ከፍ የሚያደርጉ የኦሮሞ ዜጎች እየጎለበቱ መጡ። የመጫ ቱላማ የልማትና የመረዳጃ ማህበር የራስ አገዝ ተራድኦ ዓላማን አንግቦ የተቋቋመ ቢሆንም ውሎ ሲያድር ግን እንቅስቃሴዉ የኦሮሞ ብሔረተኝነትን መሠረት የጣለ ነው። የዛሬን አያደርገውና እንደ ሌንጮ ለታ አገላለፅ ከሆነ ደግሞ "የመጫ ቱላማ ማህበር የኦሮሞ ወጣቶችን ከውርደት ነፃ የሚወጡበትን አማራጭ እንዲያስቡ" ያስተማራቸዉ ድርጅት እንደሆነ ገልጿል። ሞቲ ቢያ (1996/1998፡ 81) ደግሞ "ይህ ጀኔራል ታደሰ ብሩ በታላቅ ጀግንነት እስከ መስዋዕትነት ድረስ የመሩት ማህበር ለኦሮሞ ሕዝብ ትግል ብሔራዊ ንቃት መዳበር ታላቅ ሚና ተጫዉቷል።" በማለት ምስክርነቱን አስፍሯል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ከ1956 ወዲህ የተቋቋሙት የኢትዮጵያ መንግስታት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የጥቃት እርምጃ ለመዉሰድ ሲያልሙ የመጀመሪያ በትራቸዉ የሚያርፈው በመጫና ቱላማ ማህበርና በአመራር አባላቱ ላይ ነበር/ነው። ለአብነትም የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ወደ አዳማ መዛወሩን በመቃወም ሕዝባዊ የተቃዉሞ ስብሰባ ባስተባበሩ የማህበሩ አመራርና አባላት ላይ (የዚህን መጽሐፍ ደራሲ ላይ ጭምር) ዕድሜና ፆታን ሳይለይ በኢህአዴግ መንግስት የድብደባና የእስራት እርምጃ ተወስዶባቸዋል፤ ማህበሩም ዳግም እንዳይንቀሳቀስ ፈቃድ ተከልክሏል፣ ንብረቱም በዚሁ መንግስት ተዘርፏል።

ሌላ ጉዳይ፤ ኢትዮጵያዊያን ከተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች የተሰባሰቡ መሆናቸውን እያወቁ የሚያደበሰብሱት አንዳንድ የአበሻ ኤሊቶች በኦሮሞ ስም የተደራጀውን የኦሮሞን ድርጅት ስም ለማጠልሸት ሲሉ የመጫ ቱላማ የልማትና መረዳጃ ማህበርን እንዳለ ወደ ኦነግነት የተለወጠ አድርገዉ የሚገምቱ ቢሆንም፤ ነገር ግን በማንኛዉም ቦታ እንደሚደረግ ሁሉ ምጡቅ የመጫ ቱላማ የልማትና መረዳጃ ማህበር አባላት የነበሩ ማህበሩን ከለላ በማድረግ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን መመስረታቸው ወይም መቀላቀላቸው አይካድም። በመጫ ቱላማ የልማትና መረዳጃ ማህበር ላይ የተንደረደረዉ የኦሮሞ ሕዝብ ብሔራዊ የነፃነት ትግል እንቅስቃሴ በማይናወጥ መሠረት ላይ ያቆመዉ ከዚሁ ማህበር መጥቀው የወጡ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) አባላት መሆኑን ማንም ሊፍቀዉ የማይችል የታሪክ ሐቅ ነዉ።

ኦነግ ብዙ የኦሮሞ ልሂቃን የተሰባሰቡባቸው የኢትዮጵያ አርነት ግንባር፣ የባሌ ኦሮሞ ንቅናቄ፣ የአፍራን ቃሎ አርቲስቶች እንቅስቃሴ፣ የአርሲ ኦሮሞ መስዋዕትነት ነፀብራቅ፣ የመጫ ቱላማ የመረዳጃና የልማት ማህበርና የተማሪዎች ንቅናቄ በአጠቃላይም የሁሉም የኦሮሞ ሕዝብ የብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች መቋጫ ብቻም ሳይሆን ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ አገር ለማድረግ የተነሳ የኦሮሞ ሕዝብ ድርጅት ነበር ቢባል የተጋነነ አይመስለኝም። መሐመድ ሐሴን ከላይ በተጠቀሰው መፅሐፍ ገፅ 77 ላይ የዛሬውን ራስን በራስ ማስተዳደር እና ኢትዮጵያን በጋራ ማስተዳደር የሚመስለውን ፌዴራላዊ አስተዳደርን በሚያንፀባርቅ መልኩ "… the major objective of the Oromo national struggle is the establishment of Democratic Republic of Oromia and stresses the importance of the voluntary unity of the people of Ethiopia and the Horn of Africa. The OLF reflects the political maturity of the Oromo national movement." በማለት ጽፏል።

የዚህን ድርጅት ከምስረታው ለማጥፋት የተነሳው አፋኙ የንጉስ ኃይሌ

ሥላሴ መንግስት በተለይም በጣሊያን ወረራ ወቅትና ከጣሊያን ወረራ በኋላ የኦሮሞ ሕዝብን የለዉጥ ፍላጎት በማጤን በኦሮሞ የለዉጥ ፈላጊ መሪዎች ላይ ክንዱን ለማፈርጠም ያላደረገዉ ነገር አልነበረም። ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል የኦሮሞ ተወላጆች ከፍተኛ ትምህርት እንዳይማሩ፤ ቢማሩም እንኳን ከስድስተኛ ክፍል በላይ እንዳያልፉ፣ የኦሮሞ ዜጎች ለሹመት እንዳይታጩ፣ በተለይም በወታደራዊ መስክ ከፍተኛ የመኮንንነት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ ተወስኖባቸዉ እንደነበረ ይታወሳል። አንዳርጋቸዉ አሰግድ እንደገለጸዉ በ"1963 የአፄ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት የኦሮሞን እንቅስቃሴ ለማፈን በኦሮሞ ታጋዮች ላይ ከፍተኛ የጭቆና እርምጃዎችን የፈፀመበት ዘመን እንደነበርና በተለይም ሕዳር 4 ቀን 1963 የሐረር አካዳሚ [የ1ኛ ኮርስ] ምሩቅ [እና የሐረር መምህራን ማሰልጠኛ በሕግ የመጀመሪያ ድግሪ ምሩቅ] የነበረዉ የመቶ አለቃ ማሞ መዘምርን በ1959 "በሲኒማ አምፒየር ላይ ቦምብ ጥለሃል፤ ከጀኔራል ታደሰ ብሩ ጋር መንግስትን ለመገልበጥ አስረሃል" የሚል ክስ ከመሰረተባቸዉ በኋላ የሞት ቅጣት ተወስኖባቸዉ በስቅላት የገደለበትን ሁኔታ ታሪክ ያስታዉሳል። በመጫና ቱላማ አባልነታቸዉ በገሙጎፋ ቡልቂ በምትባል ከተማ በእስር ላይ ቆይተዉ የነበሩት አቶ ሰይፉ ተሰማም መስከረም 16 ቀን 1964 በታሰሩበት ክፍል ዉስጥ ‹‹ባልታወቀ ምክንያት›› ሞተዉ ተገኙ ተባለ። አቶ ኃይለማሪያም ገመዳ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት በእስር ላይ እንዳሉ በተፈፀመባቸዉ ድብደባ ሕይወታቸዉ አለፈ። አቶ ተመስገን ኃይሌ የተባሉትም ታጋይ ‹‹ሕይወቱን አጠፋ›› ተብሎ ተነገረ።" (ገጽ 117) በማለት የታሪክ ማስረጃ በማጣቀስ የኦነግን እንቅስቃሴ ለማዳካም የተደረገውን የነፍስ ግድያ ወንጀል አንዳርጋቸው አሰግድ አስቀምጧል።

ይህም አልበቃ ብሎ በዚሁ በኃይሌ ሥላሴ ሥርአት አፋን ኦሮሞ በማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ውስጥ እንዳይነገር የተከለከለበትና እታች እስካለዉ የመንግስት መስሪያ ቤት መዋቅር ድረስ አፋን ኦሮሞ ብቻ መናገርና መስማት የሚችል ሰዉ ሳይወድ በግዱ፤ ለዚያዉም ፍትህ ለማይገኝበት ጉዳይ ተጨማሪ ገንዘቡን ከፍሎ አስተርጓሚ መግዛት

ይገደድ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ብቻም ሳይሆን ቀደም ሲል የአፄ ምኒልክን ወደ ኦሮሞ አገር መስፋፋት ለማገዝ ከሩሲያ ንጉስ ኒኮላስ ተልኮ መጥቶ የነበረዉ እስክንድር ቡላቶቪች ከእንጦጦ እስከ ባሮ ብሎ ከፃፈዉና ዶ/ር አምባቸዉ ከበደ ወደ አማርኛ ከተረጎመዉ መፅሐፍ (ገጽ 124) ላይ ስለኦሮሞ ሕዝብ ጠባይ ሲፅፍ “የኦሮሞ ዋና መለያ ነፃነቱን የሚወድና ራሱን ችሎ ለመኖር የሚጥር መሆኑ ነዉ። ኦሮሞ ራሱን ችሎ ለመኖር የሚወድ ቢሆንም ነፃነቱ እስካልተነካበት ድረስ ለአባ ወራዎች፣ ለጎሳ ሽማግሌዎችና ለባህሉ ትልቅ አክብሮት አለዉ።” በማለት ኦሮሞ ማን እንደሆነ እማኝነቱን ሰጥቷል። እንግዲህ የአበሻ ገዥዎች ይህንን የራሱን ጠባይ የሚወደዉን የኦሮሞን ሕዝብ ጎዱት፤ ቀዬዉ ላይ መስዋዕትነት እንዲከፍል አስገደዱት። በገዛ የተፈጥሮ ሀብቱ በደጃፉ ላይ እንዲገደል የተገደደዉ የኦሮሞ ልጅ በየአቅጣጫዉ ሊንቀሳቀስ ግድ ሆነበት። ለብሔራዊ ማንነቱ የተንቀሳቀሰውን ይህንን ትልቅ ሕዝብ ሞራሉን ለመንካትና ለማኮሰስ ሲባልም ጠባብ አሉት። ኦነግም የተመሰረተው በዚህ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ግድ ይላል።

እንኳንስ ሰው ለማዳ ተደርገዉ የሚኖሩ የቤት እንስሳት የሆኑና በደሜ ነፍስ ምግባቸዉንና ማረፊያቸዉን በሠላም የሚፈልጉ ድመትና ዉሻ እንኳ ቢሆኑ አንድ ሰዉ በአንድ ክፍል ዉስጥ አስገብቶ የሚገርፋቸዉ ከሆነ፤ መገረፋቸዉ ከሚችሉት በላይ ሲሆንባቸዉ ጥፍራቸዉን ለመቧጠጨ፣ ክራንቻቸዉን ለመንከሻ እንደሚጠቀሙበትና ከዚያ ሲወጡ ቤቱን ጥለዉ እንደሚፈረጥጡና ደሜ ነፍስ ፍላጎታቸዉ አስገድዷቸዉ ወደ ቤቱ ቢመለሱም፤ ገራፊዉን ዘወትር ከመጠራጠር ለአፍታም ያህል አይዘናጉም። ሰብአዊ ሰዉ ከሆነ ደግሞ ሊቋጥር የሚችለዉን ቂም በቀል፣ ሊወሰድ የሚችለዉን የበቀል እርምጃ (በሰዉ ልጅ ሕሊናዊ ሚዛን በይቅርታ ካልታለፈ በስተቀር)፤ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን ጠብቆ ምን ሊከሰት እንደሚችል መገመት የማይችል ሰብአዊ ፍጡር ቢኖር፤ ያ ሰዉ ወይም ማህበረሰብ ስለሰብአዊነቱ ጥርጣሬ ቢገባን አይፈረድም። ስለሆነም፤ በዚሁ የተነሳ ከኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ ክብደት

በመነሳት የኦሮሞ ብሔረተኞች ለብሔሩ ንቅናቄ (ለኦነግ) የሚመጥነዉን መልክ ሊሰጡት ችለዋል። መረራ ጉዲና (2003፡ 22) ለዶክተሬት ድግሪ ማሟያ በፃፈዉ ጽሑፍ ላይ *“When the political leaders of an ethnic movement make demands to that effect, the ethnic movement therefore by definitions becomes a nationalist movement.”* የሕዝብ ጥያቄና የፖለቲካ ንቅናቄ መነሻ ተያያዥነት ያላቸው እንደሆነ አመላካች መሆኑን ገልጿል። የኦሮሞ ነፃነት ግንባርም መነሻ ሐሳብም ከዚህ የተለየ አይሆንም።

በምስራቅ አፍሪካ አከባቢ ላይ ስለኦሮሞ ሕዝብ የሚያሳስባቸዉ ሦስት አገሮች ቢኖሩም፤ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ይሆናሉ። የሶማሌ መንግስት “ለመገንባት ለሚያልሟት ታላቋ ሶማሊያ በሚሊዮናት የሚቆጠረው የኦሮሞ ሕዝብ [እና መሬት] እንደ ጥሬ ዕቃ ይታያቸው ነበር” ብሏል ሰለሞን ስዩም ከላይ በተገለጸው መጽሐፉ። ሶማሊያ የኦሮሞን መሬት ለመያዝ በግልፅና በስዉር ከሚያደርጋቸዉ ደባዎች ዉስጥ በኦሮሞ ሕዝብ ስም ያደራጀቻቸዉ ኦሮሞ አቦ ነፃነት ግንባር የመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅት የመሳሰሉ ሲሆን፤ ይባስ ብለዉ በ1969 የሶማሊያዉ መሪ ዚያድ ባሬ ኢትዮጵያን በመውረሩ በሁለቱ ዝሆኖች መሀከል በተደረገዉ ፍልሚያ ክፉኛ የተጎዳዉ የኦሮሞ ሕዝብ ነዉ። ከዚያ ቀደም ብሎም የኦሮሞን ዓላማ አንግበዉ ለነፃነት ትግሉ ችቦ ለመለኮስ የተንቀሳቀሱ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ታጋዮች ማንነታቸዉን በሃይማኖት እንዲለዩ ከሱማሊያ መንግስት ዕውቅና ያላቸው ሽፍቶች የተጠየቁትም፤ ሁሉም የኦሮሞን የነፃነት ዓላማ ያነገቡ ስለመሆናቸዉ እንጂ ሌላዉ ከዚሁ ጋር ወይም ከኦሮሞነት በኋላ የሚመለስ መሆኑን እቅጩን ስለተናገሩ፤ በዚሁ በዚያድ ባሬ ስዉር እጅ ለወሬ ነጋሪ እንኳን እንዳይተርፉ ተደርገዉ ተጨፍጭፈዉ በአንድ ጉድጓድ እንዲቀበሩ የተደረጉት ከዚሁ ከሱማሌ መንግስት ተቀጥላ ጥያቄ የተነሳ ነው። በዚሁ ምክንያትም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ለተወሰኑ ዓመታት ያለ ሁነኛ መሪዎች ወይም በሁለት ከፍተኛ መሪዎች ብቻ እንዲንቀሳቀስ ተገድዶ እንደነበር የኦሮሞ ሕዝብ በቁጭት የሚያስታዉሰዉ ጉዳይ ነዉ። የኦሮሞን ችግር

በአንክሮ ሲመለከቱት ደግሞ በኦሮሞ አከባቢ የሚገኙ ጎረቤት ሕዝቦች ሳይቀሩ የኦሮሞን የተፈጥሮ ሀብት ቀምተዉ ለመዉሰድ ወይም ገደብ የለሽ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም ከሚያድርባቸው ስግብግብ ፍላጎት የተነሳ፤ ኦሮሞ ምንም አጋዥ ሳይኖረዉ ለሃምሰ ዓመታት ያህል ብቻዉን እንዲታገል የተፈረደበት ሕዝብ ሲሆን፤ ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄውም በብዙ ችግሮች ውስጥ በማለፉ በምሳሌነት ተጠቃሽ ነዉ። ስለሆነም በ1962 ተቋቋመ ተብሎ የሚነገርለት ድርጅት፤ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፤ ከአቋሙ የኦሮሞ ሕዝብን ነፃነት ለማጎናፀፍ ብሎም ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ (decolonization of Oromia and democratization of Ethiopia) ለማድረግ ነዉ ቢባልም፤ በቀጣይነት ከሚገለጽ ከውስጥና ከውጮ በገጠሙት ችግሮች የተነሳ እንዲህ እንደተፈለገው በአጭር ጊዜ ሊሆንለት አልቻለም። ይኼውም፤ በቅደም ተከተል ሲያስቀምጡት ኦሮሞን ከቅኝ አገዛዝ ማላቀቅና ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ የሚለው የኦነግ ሐሳብ ራሱ እንደ ሐሳብ በሐበሻ ተወላጆች ዘንድም ሆነ በኦሮሞ ተወላጆች ዘንድ ሳይቀር የራሱ ችግር ያለበት ሆኖ ቆይቷል። ዛሬም ቢሆን በቀላሉ ልላቀቅ የምችል አይመስልም።

የኦሮሞ ክልል የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ግዛት መሆን ጥቅም ቢኖረዉም ከጥቅሙ ጉዳቱ ሳያመዝንበት አልቀረም። ኦሮሚያ በዉስጡ የሚገኙትና በዙሪያ የከበቡት ብሔር ብሔረሰቦች በኦሮሞ የመዋጥ ወይም የመበተን ሥጋት እንደሚያድርባቸዉ በርካሽ ዋጋ ራሳቸዉን የሸጡ ኤሊቶቻቸዉ የሚሰጧቸዉን የተሳሳተ መረጃ እየሰሙ፤ ከዕለታት በአንዱ ቀን በኦሮሞ ሕዝብ የመጠቃት አደጋ ይደርስብናል፣ ከፍ ሲልም የኦሮሞ ሕዝብ የራሱን ዕድል እንዲወስን ዕድል ከተሰጠው ይህ ሕዝብ የሚወስነው የራሱ ዕድል ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ብሔር ብሔረሰቦች ዕጣ ፋንታ ይሆናል የሚል ሥጋት አድሮባቸዉ፤ እራሳቸዉንም በሥጋት ዉስጥ ከትተዉ ለራሳቸዉም ሆነ ለኦሮሞም ሠላም የነሱበት ጊዜ ቀላል አይደለም። ለምሳሌ፤ ዩሱፍ ያሲን የተባለ ፀሐፊ ኢትዮጵያዊነት፤ አሰባሳቢ ማንነት በአንድ አገር ልጅነት በተባለ መጽሐፉ ገጽ 255 ላይ "… የኦሮሞ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት

ኦሮሞው፤ እንደ አንድ ስብስብ የራሱን የወደፊት ዕድል ብቻ አይደለም የሚወስነው። እግረ መንገዱን የበርካታ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ዕጣ ፋንታም ጭምር ነው የሚወስነው።" ያለው አንዳንዱ ውስጥ ለውስጥ በለበጣ ይነገር የነበረውን የኦሮሞ ብሔር ተገንጥሎ ኢትዮጵያን ያፈርሳል የሚሉትን ሟርት በመጽሐፍ ደረጃ አሳትሞ አርድቷል። ከ2010 ዓም ወዲህ ደግሞ በኢትዮጵያ በተፈጠረው የፖለቲካ መለዋወጥ ሁኔታ የተነሳ በኦነግ እና ኦፌኮ መሀከል እያቆጠቆጠ የመጣውን መስማማትና ወደ አገር ቤት የተመለሱ የኦሮሞ ኤሊቶች ወደ ኦሮሞ ድርጅቶች መሳሳብን በክፉ ዓይን የተመለከቱት ጥቂት ሰዎች ጤንነት አልተሰማቸውም። እንዲህ እንዲህም እያደረጉ በኦሮሞ ብሔረተኝነት (እሱም በሙሉ መገለጫው ካለ) እና በኢትዮጵያ አንድነት መሀከል እየተጠራጠሩ እንዲኖር ያደርጋሉ። ተፈራም አልተፈራ፤ ተፈለገም አልተፈለገ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ማዕከል ከሐበሾች (አማራ፣ ትግሬና ኤርትራ) ተፅዕኖ ወጥቶ ኦሮሚያ እየሆነ መምጣቱ ዕውነትና አይቀሬ እየሆነ መሆኑን መካድ አይቻልም። የኢትዮጵያን የሀገረ መንግስት ግንባታ ለማጠናቀቅም ሆነ እንደ አዲስ ለማስጀመር ማዕከሉ ኦሮምያ የሆነው በተገቢ ሁኔታ መገንባት ካልተቻለ ዳር የነበሩት ሁሉ ጎረበት አገር ሆነው እንደሚቀሩ ሳይታለም የተፈታ ነው።

የኦሮምያ የኢትዮጵያ አማካይ ሥፍራ ላይ መሆን ጥሩ አጋጣሚ ቢሆንም በሌላም በኩል የኦሮሞ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ወጣ ገባ (enclave/exclave) ስለሆነና ከራሱ ክልል የመሬት ጥበት የተነሳ የኦሮሞ ፍቅር የሌለዉ የጎረቤት ብሔር/ብሔረሰብ ኤሊት ሁሉ፤ ኦሮሞ አንድ ቀን ሊተናኮለንና ኢትዮጵያዊ አንድነት ሊያጠፋ ይችላል ብለው የሚሰጉ እንዳሉ ይገመታል። ከሁሉ በላይ ግን ሀብት ለማፍራትም ሆነ በተፈጠረዉ ሀብት ለመዝናናት ሲፈልጉ እነዚያ አሳሳች የጎረቤት ሕዝቦች ኤሊቶች ኦሮሚያ ዉስጥ ማረፍ፣ ማለፍና የተፈጠረዉን ሀብት በቋሚነት ለማስቀመጥ ወይም ለመጠቀም ሁሉም አለኝታ የሚያደርጉት የኢትዮጵያ ማዕከላዊ አስተዳደር ያለበት ኦሮሚያን ስለሆነ፤ የኦሮሞ ሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ የኦሮሞ ሕዝብ አፌ ቀላጤ (mouth piece)

ነኝ የሚለዉን ኦነግን የመገንጠል ዓላማ ያራምዳል በማለት አምርረዉ በመወንጀል ያጥላላሉ። በዚህ ብቻም ሳይወሰኑ ስለኦሮሞ ማንነቱ የሚያነሳ ኢትዮጵያዊ ሲያጋጥም በኦነግነትና በሽብርተኛነት በመፈረጅ ወደ እስር ቤት ቀለል ካደረጉለትም ወደ ጥግ ይገፉታል። የአበሻ ገዥዎች የአገዛዝ ዘይቤያቸዉ እንዳለ ሆኖ፤ ኦሮሞ የሆኑ፤ ነገር ግን ኦሮሞን በርካሽ ዋጋ የሚሸጡ አቀባባይ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ሳይቀሩ፤ ኦነግ ታግሎ የኦሮሞ መብትን ካስከበረ፤ የኦሮሞ ሀብትን (የሰዉ ሀብትን ጭምር) በርካሽ ዋጋ መሸጥም ሆነ መግዛት ስለሚቀርባቸዉ በኦነግ አሳብበዉ ኦሮሞ ጠል *(OLF and Oromo phobia)* ስሜት እንዲዳብር ያደርጋሉ። ስለዚህ በእነዚህ ችግሮች ምክንያት ኦነግ የቆመለት ዓላማ ላይ እንዳይደርስ ሆኖ እንዲቆይ የተፈረደበት ድርጅት ከመሆኑም በላይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ዳግም የመበታተን አደጋ የተጋረጠበት የፖለቲካ ድርጅት እንዲሆን ተደርጓል። በዚህ ደግሞ ከላይ እንደተገለጠዉ ሶማሊያን ጨምሮ ሌሎች የውጪ መንግስታትም ተሰትፈዉበታል።

የሩቁን ትተን የቅርቡን ዓመታት እንኳን ብናነሳ፤ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግን በስም እንጂ እንደ አንድ ድርጅት ስለአለመኖሩ የሚናገሩ የሕወሓት አገዛዝ አባላት፤ ኦነግ አለ እንኳን ቢባል አራትና አምስት ቦታ ስለመከፋፈሉ መረጃዎች እያላቸዉ፤ ነገር ግን በዚህ ግንባር ስም በመወንጀል ስፍር ቁጥር የሌላቸዉ የኦሮሞ ተወላጆች እስር ቤት እንዲታጎሩ አድርገዋል። ሙያተኛ ምስክሮች (professional witness) ተብለው የሚታወቁና በገንዘብ የተገዙና ስማቸዉን የሚቀያይሩ የሐሰት ምስክሮችን አስመስክረውባቸዋል። ከጥላቻ ወይም ከአድሎአዊ (prejudiced) አመለካከት አንፃር ሳይሆን ሥነ ምግባር በተላበሰ ሁኔታ ቢመለከቱት የኦሮሞ ተወጆችን በተመለከተ የፍትህ ሥርአቱ ሳይቀር በፖለቲካ ተጠምዝዞ ፈርዶባቸዋል። ፀረ- አፓርታይድ ታጋዩ ኒልሰን ማንዴላ የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግሬስ መሪ በነበረበት ጊዜ፤ ከሥራ ቤት የመዋል አመፃ አድርገዉ በነበረበት ወቅት ፍርድ ቤቱ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ከእስር ነፃ ያደረጋቸዉን ምሳሌ በመውሰድ፤ ከጥላቻ ነፃ በሆነ ሁኔታ የወቅቱ የደቡብ አፍሪካን የነጭ ዘረኛ መንግስትን ከገለጸበት

ሁኔታ የኢትዮጵያው ፍርድ ቤት ከሱ ያነሰ ነዉ የማለት ያህል እንደሆነ፤ ማንዴላ (1994፡ 308) *"The court system was perhaps the only place in South Africa where an African could possibly receive a fair hearing and where the rule of law might still apply."* ብሎ ስለዘረኛዉ መንግስት ፍትህ አካል አቋም ምስክርነቱን ገልጿል። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህንን ዓይነት የፍትህ ተቋም ማየት ባለመቻሉ ዜጎች በተለይም የኦሮሞ ተወላጆች በአንድ የብሔር ድርጅት በኦነግ ስም እየተከሰሱ ፍዳቸውን እንዲቆጥሩ ተደርገዋል።

ተከሳሾች የኦነግ አመራር አባል፣ ሴል አባል ወይስ ሕዋስ አባል፤ የሁሉም ወይም የአንዱ አባል መሆናቸዉ በውል ሳይገለፅ፤ በተከሳሾቹ መታሰር ምክንያት በሕይወታቸዉ፣ በኑሮአቸዉ፣ በጤናቸዉና በቤተሰባቸዉ ላይ በምንም ዓይነት መለኪያ ሊገመት የማይችል መጎሳቆል ከመደረሱም በላይ፤ ሌሎች የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችም ውሎ ቢያድር እንጂ የነሱም ዕጣ ፈንታ ከዚሁ እንደማይወጣ የሥነ ልቦና ሥጋት እንዲያድርባቸዉ ተደርጓል። ከዚህ ባለፈም ሕይወታቸዉን ያጡና ዛሬም ድረስ በእስር ቤት የሚሰቃዩ የኦሮሞ ተወላጆች ቁጥርን መናገር ያስቸግራል። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ (1998፡ 105) "ኦነግ ናቸዉ ተብለዉ የተጠረጠሩ በርካታ ግለሰቦች ይኸዉ ከ8 ዓመት በላይ ያለፍርድ በወህኒ ቤት ይሰቃያሉ" በማለት እማኝነቱን ሰጥቷል። ሰለሞን ስዩም (2007፡ 70) ደግሞ "ዓለማችን ስንት ዓይነት ተቃራኒ ሁኔቶችን አቅፋለች! ቻይና፣ ነብር ያደነ ሰዉ በሞት የሚቀጣባት ሀገር ናት፤ የህወሓቷ ኢትዮጵያ ግን ኦሮሞ አዳኞችን ትሸልማለች። በነቀሉት ጥፍር፣ በሰበሩት እግር፣ ባፈረጡት ዓይን፣ ከጥቅም ውጭ ባደረጉት ጭንቅላት ልክ ዕድገት የሚያገኙ ህወሓቶችና ተባባሪዎቻቸዉ የሞሉባት ምድር ኢትዮጵያ።" በማለት ንፅፅራዊ አስተያየቱን አስቀምጧል። ይህ መጽሐፍ ለ2ኛ ጊዜ ለዕትም በሚዘጋጅበት ጊዜ ላይ ሳይቀር የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግሬስ (ኦፌኮ) ከፍተኛ አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ተወንጅለው ወደ እስር ቤት ተወርውረው ይገኛሉ። ከነሱም ውስጥ የሰሜን ሸዋው ኦፌኮ ኮሚቴ ምክትል አስተባባሪ ወጣት ደጀኔ ግርማ ሁሪሳ በእስር ላይ እያለ የእግሮቹ

አውራ ጣት ጥፍሮች በፒንሳ ተነቅለዋል። ይህ ሁሉ የወንጀል ድርጊት የሚፈጸመው የኦሮሞ ድርጅቶችን ሕልውና ለማጥፋት ከፍ ሲልም የኦሮሞ ብሔር ሕዝብን የነፃነት ታጋዮችን አንገት ለማስደፋት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። በ2009 ዓም የኦሮሞ ተወላጆች በአርሰዲ እሬቻ ክብረ በዓል ላይ በመንግስት ኃይል ጭስ ተለቆባቸው የሞቱትን ዜጎች ከምንም ያልቆጠረው የኢፌዲሪ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ባለሥልጣን አዲሱ ገብረ እግዚአብሔር (ዶ/ር) ሳይቀር ሰለባዎቹ ተረጋግጠው ሞቱ ብሎ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀረበውና እንደ ውለታ ተቆጥሮለት እሱም መንግስትን፣ ሕዝብና አገርን ወክሎ በውጪ አገር 'አምባሳደርነት' መሾሙ የኢትዮጵያ ነገር መቼ የኦሮሞ ተወላጆችን ከማሳዘን እንደሚወጣ ያሳስባል።

በአርእስቱ ላይ ወደ አነሳሁት ኦነግ ልመለሳችሁና ኦሮሞ ላይ ከኢትዮጵያ ገዥዎች በኩል የሚደርስበት ተፅዕኖ እንዳለ ሆኖ፤ በሌላም በኩል የኦሮሞን ሕዝብ መብት ለማስከበር እታገላለሁ የሚለዉ ኦነግ እራሱ ቀላል ነዉ የማይባል ድርጅታዊ የዉስጥ ድክመት ያለበት ነዉ። ኦነግ ቢኖርም ባይኖርም አሌክሳንደር ቡላቶቪች እንደፃፈዉ "የኦሮሞ ሰዉ በነፃነት መኖርን ስለሚመርጥ" እና ከተቻለ ደግሞ ዴሞክራሲያዊነትን በተጎናጸፈች በታላቋ ኢትዮጵያ ዉስጥ፤ ካልተቻለም ነፃ ኦሮሚያን ለማየት ካለዉ ፍላጎት (ለዚያውም ከምኞት ያላለፈ ፍላጎት) የተነሳ ብቻ ኦሮሞ ጠል የሐበሻ ሰዎችና ሌሎችም በውስጡም ሆነ በዙሪያው የተሰግሰጉ አመኬላዎች በዓይነ ቁራኛ ይጠብቁታል። ባለአገሩን አፈናቅለው ሀብቱን መበጥበጣቸው ሳያንሳቸው ያለአንዳች ሐፍረት ኦሮሞ ጠባብ ነው ይሉታል።

የኦነግን የመንግስት ሥልጣን ተሳትፎን በተመለከተ የ1983/84ቱ ሽግግር መንግስት ዉስጥ የቆየዉ ዓመት ላልሞላ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል። ጊዜዉ በጣም አጭር ቢሆንም፤ የኦሮሞ ኤሊቶች ጎልተው ይገኙበት የነበረው መኢሶን ከደርግ ጋር በነበረበት የመጀመሪያዉ ዓመታት ላይ ከአደረገዉ እንቅስቃሴ በላይ ኦነግ በመንግስት ቢሮክራሲ ዉስጥ

በነበረዉ ጥቂት ተሳትፎ ያከናወነዉ ሥራና በሕዝብ መሀከል የፈጠረዉ መነሳሳት ቀላል እንዳልነበር ዛሬ ድረስ የሚታዩ አሻራዎች ምስክር ናቸው። ይህ ብቻም አይደለም፤ ኦነግ ከ1983-84 በሽግግር መንግስቱ ውስጥ በመሳተፉ የጠቀመው ነገር ቢኖር ኦነግ ራሱ በተበታተነ ሁኔታና በውጪ አገሮች ሲያካሄድ የነበረውን እንቅስቃሴ ወደ አንድ ማዕከል ወደ አገር ቤት ለማሰባሰብ መቻሉ ነው። በአጭሩ ነፃነት ወዳዱ የኦሮሞ ሕዝብና ተራርቀው ይኖሩ የነበሩ የኦሮሞ ታጋዮች በቅርብ እየተያዩ ሊወያዩ መቻላቸው ኦነግ ውጤታማ እንዲሆን አስችሎታል። የኦሮሞ ሕዝብም ከላይ እንደተጠቀሰዉ ካለዉ የነፃነት ፍላጎት አንፃር የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጭምር ወደኋላ መመለስ ከማይቻልበት ንቃት ላይ አድርሶት እንደነበር ዛሬም በገሃድ የሚታይ ነዉ። የቀደምት ኦሮሞ ታጋዮች ማሞ መዘምር፣ ጀኔራል ታደሰ ብሩ፣ ኮሎኔል ዓለሙ ቅጤሳ፣ ዶ/ር ሞጋ ፍሪሳ፣ ከበደ ፍሪሳ፣ ዋቆ ጉቱ፣ ሐጂ ቢፍቱ፣ ኃይለማርያም ገመዳ፣ ወዘተ በደማቸዉና ነፍሳቸዉ ያቀጣጠሉትን የሕዝብ ትግል በዚያች አጭር ጊዜ ዉስጥ ኦነግ እንዲጎመራ አድርጓል። ነገር ግን በሁኔታዎች አስገዳጅነት ከሽግግር መንግስቱ የወጣዉ ኦነግ በሁሉም አቅጣጫዎች፤ በአገር ዉስጥ እና ከአገር ዉጪ ማለት ነዉ፤ በሚጠበቀው ደረጃ ዉጤታማ ሊሆን አልቻለም። ለምን ዉጤታማ እንዳልሆነ በዚሁ ንዑስ አርእስት ሥር የማነሳው ቢሆንም የኦነግን ከሽግግር መንግስት መዉጣት ከመርህ አንፃር ምን ሊመስል እንደሚችል በቅድሚያ ማስቀመጡ አስፈላጊ ይሆናል።

በመሠረቱ ኦነግ ወደ ሽግግር መንግስት የገባዉ በወቅቱ ተዋናዮች ግብዣና ከውጪ ኃይላት በተደረገበት ጫናና በአበሾች መሰሪ ፖለቲካ ግፊት እንጂ በራሱ አካሄድ ተነቃንቆና ተዘጋጅቶበት እንዳልነበረ ይነገራል። ላለመዘጋጀቱም ጎጆ የቀለሰበት የራሱ ችግር በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ሆኖ፤ እንዲያዉም ለንደን ላይ ተደርጎ ከነበረዉ ስብስባ በኋላ አዲስ አበባ እንዲገባ በአሜሪካን የዉጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ የተፈቀደለት ኦነግ ሳይሆን ኢህአዴግ ነበር። ቃል በቃል እንኳን ባይሆን የአሜሪካዉ ዲፕሎማት የተናገረዉ “ሠላምና ሥርዓትን

ለማስፈን ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንድገባ ተፈቅዶለታል" *(The EPRDF is allowed to enter Addis Ababa to settle peace and order)* የሚል ነበር። ይህ ማለት ለኦነግ ያልተፈቀደ ወይም በለንደኑ ኮንፌሬንስ ዉስጥ የኦነግ ሚና አነስተኛ ወይም የሌለ መሆኑን ሲያመላክት፤ በሌላም በኩል የሱዳንን ምድር ኢህአዴግ እንደፈለገ እንዲጠቀም የፈቀደዉ የሱዳን መንግስት የሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ዕጣ ፋንታ ብዙም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ውስጥ ኦነግን ደግሞ በአገራችሁ ዉስጥ የተመቻቸ ሁኔታ ስላለ ከአገሬ ውጡ የሚል ማሳሰቢያ እንደተሰጠው በወቅቱ በስብሰባው ላይ የነበሩ የኦነግ አባላት የሚሰጡት መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኦነግ ከሽግግር መንግስት መውጣት ትክክል ነበር ወይስ አልነበር? የሚል ጥያቄ ቢነሳ የየራሳቸውን መልስ የሚሰጡ ሰዎች ቢኖሩም እንደዚህ ፀሐፊ ግንዘቤ ግን ወደ ጠርዝ የመግፋት ፖለቲካ *(brinksmanship)* ወይም የማስፈራራት ፖለቲካ (doorsisuu) ምን እንደሆነ የሚያዉቁት በትክክል ይገነዘቡታል ብዬ አምናለሁ። ወደ ጥግ የመግፋት ወይም የማስፈራራት ፖለቲካ የሚፈጸመዉ አንድ ድርጅት በሌላዉ ኪሳራ ማግኘት የሚፈልገዉ ነገር ሲኖር ነው። የጥቅሙ ባለመብት የሆነው ድርጅት ወይም ከጥቅሙ በሕጋዊ መንገድ ተካፋይ መሆን የሚገባው ድርጅት ወደ ጫፍ ተገፍቶ ወደ አምባዉ ለመመለስ ግን ከአቅሙም በላይ፣ ብሎም ከፍላጎቱም ውጭ የሆነ ግዴታ ሲጫንበትና ያ ጫና የተደረገበት ድርጅት ጫናውን ከተቀበለ አንገቱን ደፍቶ ሊኖር፤ ካልተቀበለ ግን ከአምባው ላይ ተገፍትሮ እንዲወድቅና የመሰበር ዕድል ሁሉ እንዲገጥመው የሚገደድበት አካሄድ ነው። ኦነግን በ1984 የገጠመዉ ይኸዉ ዕጣ ፋንታ ነዉ። ኦነግ በመድረኩ ላይ ለመቆየት አንድም የሕወሓት/ኢህአዴግን የፖለቲካ አካሄድ (ለዚያውም በምርኮ የተመሰረተውን የኦህዴድን አካሄድ) አምኖ መቀበልና መዳዝ መቻል ነበረበት፤ አሊያም ደግሞ የዘለቄታዉን ዓላማ ሳይሸጥ ትግሉን ሀ ብሎ ከትቢያ መጀመር እንዲችል ከሽግግር ሥርአቱ መዉጣትን መምረጥ ነበረበት። ኦነግ ሁለተኛዉን ምርጫዉ፣ ማለትም ከሽግግር ሥርአቱ

መውጣቱን ምርጫው አደረገ። ኦነግ ያንን ባያደርግ ኖሮ በኦነግ አመራር ሥር ወይም በሆነ ሁኔታ የኦሮሞ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ መወሰን ቢችል፣ የኦሮሞ ምድር ከምኒልክ ጊዜ ባልተናነሰ ሁኔታ በደም አበላ ይታጠባል፣ አሁን ያለዉ የኢትዮጵያ ካርታም ትርጉም ያጣል በማለት ሥጋት የነበረባቸዉና እስከዛሬም ሥጋቱ ያልለቀቃቸዉ የአበሻ ቀኝ አክራሪ ኤሊቶችና ነጭ ደጋፊዎቻቸዉ ጭምር ሥጋት እንዳለ በየጊዜዉ ከሚደረገዉ እንቅስቃሴና ከሚናገሩት መረዳት ይቻላል።

ኦነግ ከሽግግር መንግስቱ መውጣት ብቻም ሳይሆን ቆይቶም ቢሆን ትግሉ በኦነግ ቀደምት መሪዎቹም ጭምር የተፈለገውን አመራር ሳያገኝ የቆየ ሲሆን፣ ለዚህ ለኦነግ ዓላማ ስኬት ማጣት ኦነግ ራሱ ሁለት አለም አቀፍ ሁኔታዎችን መገመገም እንደነበረበት፤ መገምገም ባለመቻሉም በቀጣይነት ብዙ ዋጋ እንዳስከፈለው ለማየት ችለናል። ከነዚህም አንዱ አሜሪካኖች ለፈጠሩት ድርጅትም ሆነ ወጪ ላደረጉበት ድርጅት ሟቾች መሆናቸዉንና ወዳጅነታቸዉም ስለሚያስጨንቃቸዉ፤ በአፍሪካ ውስጥ ንጉስ ኃይሌ ሥላሴን፣ ጂን ቤደል ቦካሳን የመሳሰሉ የድሃ ደም መጣጮችን ይዘዉ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እንደተጓዙ ሁሉ፤ ዛሬም በፀረ ሽብር ሰልፍ ሥር የሚይዟቸዉን እንደ ሕወሓት/ኢህአዴግ የመሳሰሉትን ኃይሎች ከመንከባከብ እንደማይመለሱ ኦነግ ከጥርጣሬ በላይ ማወቅ ነበረበት። ከዚህ ጋርም ለራሳቸው እንጂ ለሌሎች ኃይሎች ቋሚነት የሌለው የአሜሪካኖች አቋም ሲገመገም፤ ዛሬም በዓለም ሕዝብ ፊት ነዉርና ውጉዝ የሆነዉን የጅራፍ ግርፍ ቅጣት የሚቀጣ የሳዉዲ ዓረቢያ መንግስት በሰብአዊ ፍጡራን ላይ እየፈጸመ ያለዉን ወንጀል አሜሪካኖች እያዩ፤ ከሳዉዲ ንጉሳዊያን ጋር ምንም ዓይነት ቅራኔ ላለመፍጠርም ሆነ የይስሙላ ተቃዉሞ ድምፅ እንኳን ለማሰማት የማይፈቅዱ መሆናቸውን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም ሕወሓት/ኢህአዴግን ከቀኛቸው ማድረጋቸው የማይቀር መሆኑን ኦነጎች አሁንም ከግምት በላይ ማወቅ ነበረባቸው። ከዚያዉ ከመካከለኛዉ ምስራቅ ሳንወጣ የእስራኤል መንግስት በፍልስጤማዊያን ላይ የሚወስደዉን የግፍ እርምጃ እያዩ፤ የግልብጦሽ ተበዳዮቹ ፍልስጤማዊያን ይቅርታ

እንዲጠይቁና ከእስራኤል ጋር ዕርቅ እንዲፈጥሩ ግፊት እንደሚያደርጉባቸው ከማንም የተሰወረ ባለመሆኑ ጥንቃቄ መወሰድ የነበረበት ሁኔታ እንደነበር ኦነጎች ማወቅ ነበረባቸው። አሜሪካኖች ሁሉንም የሚያደርጉት የራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም ትንሽ እንኳን እንዳይሸራረፍባቸው ካላቸዉ ጽኑ ፍላጎት አንፃር ነዉ። በዚህም መሠረት አሜሪካዊያን ብዙ ወጪ አወጥተዉ ጥቅማቸዉን የሚነካ ኃይል ሲፈጠር የሚታዘዝላቸዉን ኃይል በየቦታዉ ስለሚያስቀምጡ ለኦነግም ሆነ ሌላ ድርጅት ግድ እንደሌላቸዉና ለሕወሓት እንደሚያደሉ ኦነጎች ወታደሮቻቸውን ካምፕ ሲያስገቡ ጭምር ልብ ማለት ነበረባቸዉ።

ኦነግ ከሽግግር መንግስት ሲገፈተር የተሰራዉ ድራማ በሲ.አይ.ኤ ደራሲነትና አቀነባባሪነት እንዲሁም በኤርትራ ኃይሎች እርምጃ ወሳጅነት፤ የኦነግ ተዋጊዎች መሳሪያቸዉን አስቀመጠዉ ካምፕ እንዲገቡና ከዚያም ካምፑን ለቅቀዉ ወጥተዋል በማለት ባዶ እጁን በቀረዉ ሠራዊት ላይ የተፈፀመዉን የጅምላ ጭፍጨፍ ሲታይ የኦነግ ከሽግግር መንግስቱ ተገፍትሮ መሄዱ (የኦነግ የውስጥ አሠራርና ግንኙነት ክምር ድክመቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ) ትክክል ነበር የሚል ግንዛቤ ይሰጣል። ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት በደርግ መዉደቂያ አከባቢ ሎንዶን ላይ በተደረገዉ ድርድር ዉስጥ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር እንደ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ግንባር ቀደም ወይም መሳ ለመሳ ተደራዳሪ እንዳልነበረ ተወስቷል። ከዋናዎቹ የሕወሓት አጋዥ አገሮች ከአሜሪካና እንግሊዝ መንግስታትና ከሻዕቢያ ጋር የነበረዉ ግንኙነት እንዳያማ ጥራዉ ከማለት ያላለፈ ነበር ማለት ይቻላል።

የራሱ በሆነ መንገድ ፍተሻ የሚያስፈልገው ቢሆንም ኦነግ በራሱ አባላት፣ በሐበሻ ገዥዎች እና በጎረቤት ተቀናቃኞች ተደጋጋሚ ክህደት ተፈጽሞበታል። የዚያድ ባሬ መንግስት ያሰማራቸው ሽፍቶች በነ መገርሳ በሪ ይመራ የነበረውን የኦነግ መስራች መሪዎችን ያለወሬ ነጋሪ ፈጅቷቸዋል። ሻዕቢያ እና ወያኔ እንደልባቸው ሱዳን ግዛት ውስጥ ስንቀሳቀሱ እንደነበር እየታወቀ ኦነግ በሱዳን ማዕከላዊ መንግስትም ሆነ

በደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ሠራዊት ጫና ተፈፅሞበታል፤ በቀጣይነትም በ1983 ኦነግ ባልተጠራበት የሎንዶን ስምምነት ውስጥ ሰለባ እንዲሆን ሱዳኖች ኦነግ አገራቸውን ለቅቆ እንዲወጣና ለጥቃት እንዲጋለጡ አድርገዋል። በ1983 ኦነግ ወታደሮቹን ያለምንም መተማመኛ ወይም በሽፍጠኛ መሪዎቹ አሳሳችነት ካምፕ እንዲያስገባ ያንድ ወገን የበላይነት ያየለበት ስምምነት (lopsided) ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። ኦነግ ወታደሮቹን በካምፕ ለማስቀመጥ ከሕወሓት ጋር ሲስማማ ይህንን ስምምነት መተግበሩን እንዲቆጣጠሩ ከተመደቡት ዉስጥ የሻዕቢያ ወታደሮች አንዱ ነበር። “ጌታም ለሥጋዉ አደላ” እንደሚባለዉ ዓይነት ሆነና ሕወሓትና ሻዕቢያ በመተባበር ኦነግን አታልለዉ ወታደሮቹ ካምፕ እንዲገቡ አደረጉ። የኦነግ ወታደሮች ካምፕ ከገቡ በኋላ ለረሃብና ወረርሽኝ በሽታ ተጋለጡ። የኦነግ ሠራዊት ባዶ እጁ መሆኑን ከአረጋገጡ በኋላ ተኮሱበትና እንደ ሱማሌዉ ሽፍቶች በጅምላ መቃብር ቀበሯቸዉ። ነገር ግን የኦነግን ሠራዊት ፍቅር ከኦሮሞ ሕዝብ ልብ ውስጥ ፍቀው ማውጣት ወይም መግደል ባለመቻሉ ሠራዊቱ በራሱና በቄሮ መልክ ተደራጅቶ ተከሰተ። መጨረሻው የቱ ጋ እንደሆነ ያልታወቀው የሻዕቢያው ሽፍጥ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ በ2010 ዓም ሌላ ገጽታን ተላብሶ ኦነግ እና መሪዎቹን ካገሩ እንዲወጡ አደረጉ። የኦነግ አመራሮችም ሆኑ ወታደሮች ለ1983ቱ የሽግግሩ መንግስት ማሳረጊያ ጭዳ እንደሆኑ ሁሉ ፍጹም ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ እንኳን ባይሆንም ለ2010 ዓም ሽግግርም አመራሩ ጭዳ እንዲሆን ክህደት ተፈጽሞበታል። በዚሁም እንደፍልስጤማዊው እናት የኦሮሞም እናት ሰቆቃ እንዲቀጥል ተደረገ። ከዚህ ሁኔታ እና ቀደም ሲል ከነበሩት ሁኔታዎችን መነሻ በማድረግ የኦሮሞ ፖለቲከኞች የአበሻ ፖለቲከኞችን ማመን ጭንቅ ቢሆንባቸዉ ማንም በኦነግ አባላት ላይ አይፈርድም። ዛሬ አንድ ኦነግ ሳይሆን የተበጣጠቀ ኦነግ ሆኖ እያለም የኦሮሞ ሕዝብና ሌሎች በሠላም የሚታገሉ የኦሮሞ ፓርቲዎች ለሚያነሱት ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ ስውር የኦነግ ታፔላ ተለጥፎባቸዉ ሕገ ወጥ እርምጃ የሚወሰድባቸዉ የኦሮሞ ተወላጆች ቁጥር ቀላል አይደለም። ነገር ግን አበሾች ከኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት መከበር ጥያቄ የበለጠ፤ የክልሉ ያልተነካ

ድልብ ጥሬ ሀብትና ለም መሬት ያሳስባቸዋል፣ የኦሮሞ ሕዝብ ሀብት ሳይኖር ኢትዮጵያ ሊትኖር እንደማትችል፤ መኖር ቢትችል እንኳን ውጣ ውረዱ እንደሚከፋ የሐበሻ ኤሊቶች ልቦና በትክክል ያውቀዋል።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባርም ሆነ ሌሎች አምሳያ የኦሮሞ ድርጅቶች ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን የኢምፓየር ግዛት ይሏታል። *ኢምፓየር ማለት ቀደም ሲል ራሳቸዉን ችለዉ ይኖሩ የነበሩ ነፃ ሕዝቦችን ወይም አገሮች በሌላ ባዕድ ኃይል የምንበረከኩበት አገዛዝ ማለት ነዉ።* ይህ አገዛዝ ደግሞ የሰለባ ሕዝቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ የሚያጠፋ ሲሆን ለዕውቀት ወይም ሥልጣኔ ዝግ ነው። ኦነግ ይህንን ሥርአት በሚታገልበት ጊዜ ባዕድ የሆኑ ሰዎች ቀርተዉ ኦሮሞ የሆኑ ሰዎች ሳይቀሩ በቀላሉ የማይረዱለት ችግሮች ነበሩበት። ከላይ እንደተገለጸዉ አንዱ የኦሮሞ ሕዝብ ችግር የኦሮሚያ አንፃራዊ መገኛ በኢትዮጵያ ኢምፓየር ማዕከላዊ ግዛት መሀከል ላይ መሆኑንና ኢትዮጵያን ለመግዛት የሚፈልግ ሁሉ በመጀመሪያ የኦሮሞን ተወላጆችና ድርጅቶች ሞራል ሰብሮ መግዛት እንደሚፈልጉ ያልተፃፈ ሕግ መኖሩን እንደ ሃይማኖታዊ ቀኖና የማይስቱት ነገር እንደሆነና ቢስቱት እንኳን ቅስፈቱ ወይም የሚያስከፍለው ዋጋ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የሚገነዘቡት ነዉ።

ሌላዉ ለኦሮሞ ሕዝብና ድርጅቶቹ አስቸጋሪ ነገር የሆነዉ የኦሮሞን ባህላዊ ዲሞክራሲያዊ የገዳ አስተዳደር ሥርአት ለጥንቱም ሆነ ለዛሬዉ የአበሻ ልጆች አለመዋጡ ነዉ። እንዲያዉም ባህላዊውን የገዳ ሥርአት ተከትሎ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሰፈነ የብዙኃን አስተዳደር መስፈንና የአናሳዎች መብት መከበር በሚባል መርህ መሠረት ከተተገበረ በኦሮሞ ደጋፊዎች ድምፅ እንዋጣለን የሚል ስጋት አንገታቸዉ ድረስ በመዝለቁ የአናሳ ብሔሮች ኢሊቶች ሁሌም እንደ ሰጉ እንዳሉ ከላይ አሳይቻለሁ። በማንኛዉም መመዘኛ ብዙኃን አናሳዎችን ይጨናሉ እንኳን ቢባል ዲሞክራሲዉ ራሱ ከሚፈጥረዉ ጫና ውጭ ዲሞክራሲ የአናሳዎችን መብትና ፍላጎት የሚያስከብር መሆኑን መገንዘብ ግድ ይላቸዋል። ከዚህም ሌላ ዲሞክራሲዉ ራሱ ከላይ የተጠቀሰዉ ሥጋት

እንዳይኖር የሕዝቦችና ዜጎች መብት እንዳይነካ በመንግስት አካላቱ መሀከል ቁጥጥር ማድረግ የሚችል (check and balance) እንዲኖር የሚያደርግ ተቋም መኖር ግድ ስለሚለው በራስ ላይ ስጋትን ፈጥሮ መጠላለፍን መፍጠሩ ተፈላጊ አይደለም። የሚቋቋመው ሕግ ጠንካራ ተቋም ካለው አንድ ብሔር ቁጥሩ በዛ ወይም አናሳ ሆነ ተብሎ ስጋት አይኖርም፤ ስጋቱ ከተፈጠረም ደግሞ አነስተኛ ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

ይህ ሁሉ ተፈታታኝ ነገሮች በተለይ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ እንዳለ በመረዳት፤ ከሽግግር መንግስቱ የወጣዉን ኦነግ ካለበት ድክመት አንፃር በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ በአገር ዉስጥና ከአገር ውጪ በሚለዉ። በአገሪቱ ከፍተኛዉ የሕግ አውጪ አካል ማለትም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአገር ውጪ ሁለት ድርጅቶችን (አልቃይዳና አልሸባብ)፣ ሌሎች ሦስት ድርጅቶችን ከአገር ዉስጥ (ኦነግ፣ ግንቦት 7 እና ኦብነግን) አሸባሪ ድርጅቶች ናቸዉ ብሎ መፈረጅና በአካል የማዉቃቸዉና ብሔራቸዉ ኦሮሞ የሆኑ ብዙ የኦሮሞ ማህበረሰብ አባላት የሆኑ ዜጎች በዚሁ ድርጅት ስም እየተወነጀሉ ወህኒ ቤት ሲታጎሩ ለማየት በመቻሉና እንዳዉም የወህኒ ቤቱ ይፋዊ የመግባቢያ ቋንቋ አፋን ኦሮሞ ሆኗል እስከመባል የደረሰ ነዉ በሚለዉ ላይ በመንተራስ ነዉ። በዚህም ያገር ቤቱ ኦሮሞ ኦነግ ላለመባል ካደረበት ፍርሃት የተነሳ መብቱን መጠየቅ እስከ አለመቻል ሲሄድ፤ በሥራው አከባቢም ኪሳራ እስከሚያስተናግድ ድረስ ገንዘብህን አምጣ ሲባል እሱ ራሱ ፈርሞ ወጪ በማድረግ ወስዶ ለማስረከብ በመገደዱ በአፈራዉ ሀብት ላይ ማዘዙን እንኳን የፈራበት ሲሆን፤ በተለይ ከ1997 ምርጫ በኋላ የገቸዉ ኢህአዴግ አባላት በተለይም በሚኒስትር ግርማ አማካይነት የኦሮሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዳይደገፉ ለኦሮሞ ባለሀብቶች የሰጧቸዉ ማስጠንቀቂያ የባለሀብቶቹን ቆሌ ስለተገፈፈ መብትን መጠየቅ ራሱ አሸባሪ ኦነግ እንደሚያሰኝ አምነው ሰንብተዋል።

በውጪ አገሮች ያለዉ የኦነግ ኃይል ከአገርና ከወገን ርቆ ስለሚገኝ ያን

ያህል የተመቻቸ የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ ባይሆንም፤ እንዲሁም አገር ቤት ካሉት የበለጠ ብዙ የገንዘብና የጊዜ ወጪ የሚጠይቃቸዉ ቢሆንም፤ ከትልቁ ችግር ማለትም በመንግስት የፀጥታ ኃይል የመዋከባቸዉ አደጋ አናሳ ነዉ። ነገር ግን የኦነግ የውጪዉ አካል ቀላል በማይባሉ የመርህ ጉዳዮች ላይ ሰፊ የሆነ መለያየት አድርጎ የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ከማስተባበር ይልቅ እራሱም ሌላ አስተባበሪ አስፈልጎት እንደነበር ሲሰጡ ከነበሩት ተራጋጭ የጋራም ሆነ የግል መግለጫዎች ስለምናዳምጥ ነዉ። በፖለቲካው ዓለም በአንድ ነገር ላይ ልዩነት መፍጠር እንዳለ ሆኖ አንድ የማይካድ ሐቅ ቢኖር ደግሞ የመርህ ጉዳይ ከማነታረክም አልፎ ሊያለያይና ጦር ሊያማዝዝ እንደሚችል እገነዘባለሁ። ሩቅ አገሮችን ሳንነካ ጀብሃና ሻዕቢያ፣ ቀጥሎም ሻዕቢያና የኡስማን ሳላህ ሳቤህ ቡድን፣ ተሀትና ማሌሊት የተለያዩበትንና ያደረጉትን ደም አፈሳሽ የጦርነት ሁኔታ እንደምሳሌ ይታወሰናል። ነገር ግን ‹‹እየየም ሲዳላ ነዉ›› የሚባለዉን የአማራዎች ተረት ለኦሮሞ ሕዝብ አይሰራም ያለ ማን እንደሆነ ባይገባኝም ኦነጎች ተረቱ ለሌላ ሰው መስሏቸው ወደ ራሳቸዉ አዙረዉ አልተረዱትም። በመሆኑም በአስመራ በነበሩ የኦነግ አመራሮች መሀከል ይከሰቱ የነበሩ የመናቆር ችግሮች ከመብዛታቸው የተነሳ በሌላ ቡድን የተፈረጀ የኦነግ አባል ቤተሰብ አስከሬን ቀብር አጥቶ ሀኪም ቤት ውስጥ ሊበሰብስ ወይም አጉል ቦታ ላይ ሊጣል እንደነበረ እየቆዩ ከሚወጡ መረጃዎች ማወቅ ተችሏል።

ኦሮሞ በአፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ እጅና እግሩ እየተቆረጠ ከገደል እንደሚወረወር፣ በአፄ ዮሐንስ ካልተጠመክ በስተቀር አገሬን ለቅቀህ ውጣ እንዳልተባለ፣ በአፄ ምኒልክ አገዛዝ ብልትና ጡት፣ እጅና እግር እንደተቆረጠ ሁሉ፤ ዛሬም ውድ የሆኑ ልጆቹ እንደ ኢሉባቦራዎቹ ሐጂ ከማል ሙሳ (ሙቱ) እና ቀነኣ ጉታ (ሱጴ)፣ እንደ ወጣቱ ኤብሳ አዱኛ፣ እንደ የአምቦዉ የተከበሩ አዛዉንት ደራራ ከፈኒ፣ እንደመዳ ወላቡና የሙቱ ዩኒቬርሲቲ ተማሪዎች፣ የምዕራብ ሸዋ ወጣቶች፣ እንደነቀምቴ አምስቱ ወጣት ጓደኛሞች እና ሌሎችም ዜጎች በገዛ ቀዬያቸዉ እየተገደሉ እንደሆነ ለአፍታም ተዘንግቶ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቀዳሚ ሆኖ

ከሰዉ ሕይወት በልጦ ኦነጎችን እንዴት አድርጎ እንዳናቆረ አይገባኝም። ኦነግ አራት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ቦታ ላይ ተከፋፍሏል ሲባል ምን ለመጨመር ወይም ለመቀነስ እንደሆነ ግልፅ ማድረግ የሚችል ሰዉ ወይም ድርጅት ቢኖር ጥሩ ቢሆንም፤ ከሌለም ደግሞ እገሌ ክርስትያን ነዉ እገሌ ደግሞ ሙስሊም ነዉ ብለን አንለያይም ብለዉ ሸንጋ በሚባል የሶማሊያ ምድር ተገድለው በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የመጀመሪያ መሪዎች፤ አይቻልም እንጂ ቢቻልና አንድ ጊዜ ቀና ብለዉ ምን እያደረጋችሁና እየሆናችሁ ነው ብለዉ ቢጠይቋቸዉ፤ ማን ምን መልስ እንደሚሰጥና ለመስጠቱስ ቃሉ ራሱ ይገኝ እንደሆነ የሚያሳስብ ይመስለኛል።

ከሸንጋ ሰማዕታት መታሰቢያ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ተጨማሪ ጉዳይ ይኖራል። ይኼውም ሸንጋ ውስጥ ተገድለው በአንድ ጉድጓድ ስለተቀበሩት የኦነግ አመራሮችን ስናስብ በየዓመቱ አፕሪል 15 የመታሰቢያ ሻማ ይለኮሳል። የመታሰቢያ ሻማ መለኮሱ ክፋት ባይኖረውምና ሰማዕቱ ሲታሰቡም ስለወደፊቱ ትግል ቁርጠኛነትን ማሳያና እግረ መንገዳችንንም ቃል ኪዳን ማደሻ ሥነ ሥርአት እንደሆነ ስለሚታሰብ ነው። ከዚህ ጋር አብሮ መታሰብ ያለበት ነገር ቢኖር ከዚያ ወዲህም ቢሆን ስንት የኦሮሞ ታጋዮች በምን ዓይነት ሁኔታ እነማን እንደታፈኑና እንደተገደሉ የነፃነትና የመብት ትግሉ እንዴት እንደተዳፈነ በጥልቀት ሊፈተሸ ይገባል። በተለይ በኦነግ አመራሮችና በአጠቃላይም በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የተፈፀሙ ጥቂት የጉዳት ምሳሌዎችን እናንሳ ቢባል በደርጉ መጋቢ የሃምሳ አለቃ ንጉሴ ፋንታ አስተባባሪነት ቀለም ወለጋ ውስጥ በምስጥ መግደያ መርዝ ስለተገደሉት ስድስት ወይም ሰባት የኦነግ አባላት፣ ለሕዝብ ነፃነትና መብት ብሎ ዱር ቤቴ ያለው ለገሠ ወጊ ስለተገደለበት ሁኔታ እንዲሁም አሁን ባለንበት ጊዜም ቢሆንም የኦሮሞ ሕዝብን ነፃነትና መብት ለመናኛ ጥቅም አሳልፈን አንሸጥም ያሉ የኦሮሞ ታጋዮችና ወገኖች ቤተሰቦቻቸውን በትነውና ሕይወታቸውን ጭምር የሚያስቀጥፉ፣ ደማቸውን የሚያፈሱ፣ አጥንት የተሰበሩ፣ ኑሮአቸው የተመሰቃቀለና የግላቸው ቅምጥል ኑሮ ስለማያሳስባቸው

ግለሰቦች አንዳንድ ነገር ሳይባል መታለፍ የለበትም። ይህ ግምት ውስጥ ገብቶ ነው የሸንጋ ሰማዕታትን ሻማ ለኩሶ ማሰብ የተሟላ የሚያደርገው።

ወደ ተነሳሁበት ዋና ርዕስ ልመለስና የኦነግ ሰዎችን ክፍፍል ብልጠት ወይም ሞኝነት እንበለዉ ምን እንደሆነ ለመለየትና ለግንዛቤም ይረዳ ዘንድ፤ ምናልባት አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ያህል ወደኋላ ተመልሰን እናስብ ቢባል፤ የሆሮ ጉዱሩዉን ጀግና አብሼ ገርባንና ቀድሞ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) አባልና የወቅቱ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) መስራችና መሪ የሆኑትን ሌንጮ ለታን እናነፃፅራለን። በነገራችን ላይ ንፅፅር ለማድረግ የጊዜ፣ የቦታና የሁኔታ ግጥምጥሞሾችን ግምት ውስጥ አስገብቶ ካላሰቡ በስተቀር ሊያሳስት ይችላል። ወይም ሊነፃፀሩ የማይችሉ እሴቶችን ወደ ማነፃፀር እንዲሄዱ ያስገድዳል። የኔ ንፅፅር የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ጉዳዮች አይፋለስብኝም እላለሁ።

ሌንጮ ለታን ያነሳሁት ስለቀለሉኝ ሳይሆን የፖለቲካ ስብዕናቸዉ ከብዙዎቹ ሰዎች ጎልቶ ለረጅም ጊዜ ሲታይ የቆየ ስለሆነ ነዉ። ታሪኩና ኩነቱ እንዲህ ነው። አብሼ ገርባ የጎጃሙን ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ጦር መዉጫ መግቢያ አሳጥቶት ያባረረ የኦሮሞ ጀግና ነበር። አሸናፊነቱ ከተረጋገጠለት በኋላ የአበሻን መሰሪ ፖለቲካ ባለማገናዘቡ ለዕርቅ ተብሎ ሲጋበዝ እሽታዉን በማሳየት ብቻ ሳይሆን ኦሮሞ አንድን ተቀናቃኙን አንዴ ካሸነፈ በኋላ፤ ነገር ማመኻኸክ አይሆንለትምና አብሼ ገርባም ለተባለዉ ዕርቅ ፈቃደኛ ሆኖ ቀጠሮ ቦታ ላይ ይቀርባል። በዚህ ዕርቅ ዉስጥ ለራሱም ጥቅም ሲባል ሚና የተጫወተዉ ቀዲዳ ወነቤ የተባለዉ የዚያዉ አከባቢ የጅማ ገነቲ ኦሮሞ ነዉ። ቀዲዳ ወነቤ እንደገመተዉ ተቀናቃኙ አብሼ ገርባ ቢደመሰስ እና አንድ ቀን አብሼ ገርባ ከሚያሳርፍበት ጠንካራ ክንድ እፎይታን እንደሚያገኝ በመገመት፤ አልፎ ተርፎም የመልከ ጥፉዉን አብሼ ገርባን ቆንጅዬ ሚስት ቀዲዳ ወነቤ የራሱ ሊያደርጋት ማሰቡ ነዉ። “አለመማር ክፉ አለመመልከት ወንድሙን ይገድላል ሚስቱን ለማግባት” እንደተባለዉ ተረት፤ ቀዲዳ ወነቤ የአበሻን የሸፍጥ ፖለቲካ ባለማገናዘብ አብሼ ገርባ ላይ አስሯል።

በተስማሙት ሳይሆን ባልተነጋገሩበት ሁኔታ አብሼ ገርባ ለዕርቅ ሄዶ፤ ነገር ግን እጁን እንደሰጠ ተቆጥሮበት ነጋሪት ተጎስሞበት በምርኮ ተይዞ፤ ደብረ ማርቆስ ላይ እጁን አኝኮ ይሞታል፡፡ የንጉስ ተክለ ሃይማኖት ሚስት መተረቻም ከመሆንም አልተረፈም፡፡ አብሼ ገርባን አሳልፎ በመስጠቱ ቀዲዳ ወነቤ የተጠቀመዉ አንድም ነገር አልነበረም፡፡ ውሎ ሲያድር በጎጃሙ ተክለ ሃይማኖት መሆኑ ቀረ እንጂ ጀግናው አብሼ ገርባ ባለመኖሩ የኦሮሞ መሬት በምኒልክ ጦር ከመወረር አላመለጠም፡፡

ጀግናዉ አብሼ ገርባ የጦር አባሎቹን እንኳን በውግ ሳያደራጅና በእጃቸዉ የሚገኘዉን መሳሪያ እንኳን ለዕርቅ ብለዉ እንዳይጠቀሙበት ተደርገዉ እጃቸዉን እንደሰጡ ተቆጥሮባቸዋል፡፡ ነገርን ነገር ያነሳልና አብሼ ገርባ በዚያ ዘመን በአስራ ዘጠነኛዉ መቶ ዓመት ላይ ተሞኝቶ ነበር ብንል፤ በዚህ በ21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ ሌንጮ ለታ ምን ሆኖ ነዉ ወይም ምን ይገኛል ብሎ ነዉ ምንም ጠብ ለማይል የአበሻ ፖለቲካ እናት ድርጅቱን ኦነግን አዳክሞ ወይም ክዶ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር/ኦዲኤፍ መሰረትኩ ብሎ ሰተት ብሎ ፊንፊኔ ገብቶ እጅ የሰጠዉ? ምንስ የተገኘ ነገር ይኖር ይሆን? ይህ ድርጊት ሲጨመርም ሆነ ሲቀነስ ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ በጭቆና ቀንበር ሥር ለቆየዉና አሁንም በገዛ ቀዬዉ ለሚገደለዉ የኦሮሞ ተወላጅ የፈየደዉ አንዳችም ነገር የለም፡፡ ደግነቱ ሌንጮ ለታ እጅ በመስጠቱ እንደአበሼ ገርባ የእጁን ጣት ስለመብላቱ የተሰማ ነገር እንደሌለና ረብጣ የአሜሪካ ዶላር እያለ እጁን እንደማይበላም በእርገጠኛነት መናገር ይቻላል፤ ምክንያቱም ሌንጮ ለታ ብልጥ እንጂ የአብሼ ገርባ ዓይነት ጀግና ላይሆን ይችላልና ነው፡፡

አለክሳንደር ቡላቶቪች ጽፎ ዶክተር አምባቸዉ ከበደ ከተረጎመዉ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ዉስጥ በአስቆጭነቱ የሚጠቀሰዉ “አምስት ሚሊዮን የሚሆነዉ ጥሩ መሬት የያዘዉና በሁሉም ቦታ በአንድ ቋንቋ የሚናገረዉ የኦሮሞ ሕዝብ በአንድነት ቢቆም አለጥርጥር ታላቅ ኃይል ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በመሀከላቸዉ ያለዉ የመለያየት ስሜት ይህ ዓይነቱ ሕብረት ዕዉን እንዳይሆን አድርጎት ነበር፡፡” (ገፅ 130) ብሎ

የፃፈው ዕውነትም ያስቆጫል። “ባለቤት ያቀለለዉን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለዉም።” ይባልስ የለ! ምንም ሆነ ምን በብሔር ንቅናቄ ውስጥ የግላቸውን ጠባብ ዓላማ የሚያራምዱ ግለሰቦችና ተሰፈንጣሪዎች መኖራቸው የሚያጋጥም ቢሆንም የሕብረተሰባቸውን ችግር ለመፍታት የሚቋቋሙት ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች፤ ኦነግን የመሳሰሉ ደግሞ ስሸመደመዱ ማየት ያሳዝናል። ፀረ አፓርታይዱ የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ በአፋኙ የዘረኞች አገዛዝ አገር ውስጥ ረጅም ጊዜ በሕዝቡ መሀከል ሊኖር የቻለውና የነፃነት ትግሉን ሊመራ የቻለው ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ስለነበረው ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም ኦነግን የመሳሰሉ የአርነት ንቅናቄ ድርጅቶች ይህን ያህል ዕድሜ የመኖራቸው ምስጢርም ያን ያህል የተደበቀ ነገር ኖሮ ሳይሆን አንግቶ የተነሳው ሕዝባዊ ዓላማ እንደሆነ ጥርጣሬ የለውም። ነገር ግን በዓለም ላይ የፖለቲካ ንግድም ሆነ ክህደት፤ በጣም በወረደ ቃል እንግለጸው ከተባለ ደግሞ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የፖለቲካ ሽርሙጥና ከተፈጸመባቸው ድርጅቶች ውስጥ ኦነግ አንዱ እንደሆነ ቢገለጽ ከዕውነት የራቀ አይሆንም።

ከዚሁ ከኦነግ ጉዳይ ሳንወጣ ሁለት ነገሮች ኦነግ ደካማ ሆኖ እንዲቆይ አስገድደውታል። አንዱና ዋናው የኦሮሞ ጠላት የሆኑ ሁሉ የኦሮሞን ዓላማና ፍላጎት ለመጠምዘዝ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እስከ ማፈሰስ ሄደው የኦሮሞ ተወላጅን ይገዛሉ። በዚህም፤ ጥንት የነበረው ኦሮሞ አይዋሸምና ኦሮሞ የሰው ሐቅ አይወስድም፤ የራሱንም አይሰጥም የሚባለው አባባል ጊዜ ያለፈበት ብቻ ሳይሆን ያረጀ ያፈጀ ሆኖ የኦሮሞ ወጣት ትውልድ ከትግል እንዲዘናጉ አድርጓል። ባልቻ ሣፎ፣ ቁሴ ድናግዴ፣ ኩምሳ ሞረዳ፣ አባ ጅፋር ለምንሊክ፤ ጃጋማ ኬሎ፣ መስፍን ስለሺ ጆቴ፣ ለኃይሌ ሥላሴ፤ እነ ተካ ቱሉ፣ ለማ ጉተማ፣ ደበላ ዲንሳ፣ ለመንግስቱ ኃይለማርያም አድረው ኦሮሞን ያስጎዱ ስለነበሩ አባባሉ ከድሮም ጀምሮ አልሰራም፤ ዛሬም አይሰራም። ዛሬም የኦነግን የትግል አቅጣጫ ክደው የወያኔን ወንበር ለተረከበው የኢህአዴግ አዲስ አበባ ቀሪ ክፍል ያደሩት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች የኦሮሞን ሕዝብ ለማስጎዳትና መናኛ ጥቅም ለማግኘት እንደሆነ ለማወቅ ማስጠንቆል የሚያስፈልግ አይሆንም። የሌንጬ ለታን

ከመለስ ዜናዊ ጋር መሞዳሞድ የተመለከተው ገላሳ ድልቦ ዝም ብሎ ሌንጮን ከኦነግ ለማባረር መነሳሳት ሌንጮ ማነው የሚለውን ጥያቄና ከሱ ጋር ያሉትስ እነማን ናቸው ብሎ አለማሰብ ክፍተት ነበረበት። ይኼው መገፋታተር ውሎ አድሮ በገላሳ ድልቦ ላይም አነሳስቶ ዳውድ ኢብሳ ወደ ኦነግ አመራር እንዲመጣ መንገድ አመቻቸ። ወደ ኦነግ ሥልጣን የመጣው ዳውድ ኢብሳ ግን እንደፈለጉት የሚጠመዝዙት ዓይነት ሰው ሆኖ አለመገኘቱ ሳያሳስባቸው አልቀረም። በሌሎች አገሮችም ሆነ ኤርትራ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ በኦነግ አመራሮች መሀከል ምን ያህል ቂም ቋጥረው እንደቆዩ በዝርዝር ባናውቅም፤ ከ2010 ዓም ጀምሮ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ ከነድክመቱም ቢሆን ኦነግ ወደ አገር ቤት ሲመለስ፤ በነፃነት ወዳዱ የኦሮሞ ሕዝብ የተደረገለት አቀባበል የሕወሓት/ኢህአዴግን ፊንፊኔ/አዲስ አበባ ቀረ ክፍል ሳያሳስብም ሆነ ሳያስደነግጥ አልቀረም። ኦነግ ወደ አገር ቤት ከተመለሰ በኋላ ያስተናገደው የሕወሓት/ኢህአዴግ ርዝራዦችን ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን ቂም ቋጥረው አንድም የኦነግ አመራርን ለመቆጣጠር አሊያም ደግሞ ኦነግ ማንሰራራት በማይችልበት ሁኔታ አከርካሪውን ለማስመታት ያደቡ የቀድሞ የኦነግ አመራር አባሎችን ለመቋቋም ጭምር ነው። በዚህ መነሻም ለወደፊት፤ ኦነግንም ሆነ ሌሎች የኦሮሞ የነፃነት ታጋይ ድርጅቶችን የሚጠብቅ ውጣ ውረድ ቀላል እንደማይሆን ይጠበቃል።

በኦሮሞ ብሔር ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን ደባ ለማየት ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጉዳይ ወጣ ባለ ሁኔታ ስለኦሮሞ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን - ስለሌሎች የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅቶች አቋም፣ ስለኦሮሞ ተወላጆች ብሔራዊ ማንነት (ብሔረተኝነት) ግንባታ ዕውቀትና ቁርጠኝነት ማነስን አንስቶ እንዲሁም ስለኦሮሞ ወታደራዊ መኮንኖች የኦሮሞነታቸው ብሔራዊ ንቃተ ሕሊና ማነስን አንስቶ አብሮ መመልከቱ ጠቃሚና አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም፤ ኦሮሞ መብቱን እንዲያስከብር ከማስቻልና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚገባውን ቦታ ለማግኘት እንዲበቃ አደረጃጀቱን ማጠናከርና ብሔራዊ ማንነቱ

እንድጠናከር የማድረግ ሥራውም ሆነ ድክመትን ለአንድ ኦነግ ብቻ የሚተው ሥራ አይደለም። መጋራት የሚገባቸው ሌሎች የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ስላሉ ነው። ዕውነት እንናገር ከተባለ፤ እንደበቅ ቢባል እንኳን የማይሞከር፤ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ከኃይሌ ሥላሴ የጨለማ ዘመን አገዛዝ ጀምሮ ደርግን ጨምሮ እስከ አፋኙና ዘራፊው የወያኔ መንግስት ድረስ በአካልም ሆነ በመንፈስ የኦሮሞ ሕዝብን የፖለቲካ ነፃነት ትግል ዓይነ ጥላ የገለጠ ድርጅት መሆኑን መካድ አይቻልም። ነገር ግን ሊዘለል የማይችልና ከሚታይበት ጉድለት ውስጥ አንዱ በኦነግ የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ የነፃነት ትግሉ እስካሁን ድረስ በወታደራዊ ሙያ በሰለጡኑ መኮንኖች ወይም ሙያተኞች አለመመራቱ አንዱ ነው። ምናልባት እነ ጀነራል ከማል ገልቹ፣ ጀነራል ኃይሉ ጎንፋ፣ የመሳሰሉ አሉ/ነበሩ ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ለኦሮሞ ሕዝብ የሚገባውን ቦታ አላመቻቹም ወይም ኦሮምያ ምን እንደሚያስፈልጋት እራሳቸውም አላወቁም። በደርግ መንግስት ውስጥ የነበሩ የኤርትራ ወታደራዊ መኮንኖች ለሻዕቢያ ሲያብሩ፣ ወታደር ትግሬዎች ለሕወሓት ከመረጃ እስከ መሳሪያና ገንዘብ ማቀበል ሲሰሩ፤ አማራዎቹ እነ ተፈራ ማሞ፣ አለበል አማረ፣ አሳምነው ፅጌ፣ ወዘተ ለአማራ ሕዝብ መብት ሲሞግቱ፤ የኦሮሞ መኮንኖች የኦሮሞን ሕዝብ መብት ማስከበር እሳቤ በመቶ አለቃ ማሞ መዘምር፣ ብ/ጀነራል ታደሰ ብሩ፣ ኮሎኔል ዓለሙ ቅጤሳ፣ እና ሌሎች ቀደምቶች ላይ ብቻ ያበቃ ይመስላል፤ ምክንያቱም ከነሱ ወዲህ ጎልቶ የወጣ ወታደራዊ መኮንን የለም። ምንም እንኳን ከሰላሳ ዓመታት ወዲህ ጀኔራሎቹ እነ ኃይሉ ጎንፋ፣ ከማል ገልቹ፣ የመሳሰሉት የኦሮሞ ወታደራዊ መኮንኖች ኦነግን ቢቀላቀሉም ለገዥዎች አድረው ኦነግን ለማፍረስ ስለመንቀሳቀሳቸው እንጂ ለኦሮሞ ሕዝብ መብትና ነፃነት አስተዋጽኦ በማድረግ አይታወቁም። ለዚህም ይመስላል የኦነግ የነፃነት ትግል፤ ሕዝባዊ ትግል ስለመሆኑ አንዳች ጥርጣሬ ባይኖርም፤ ትግሉ በወጣቶች ብቻ በመመራቱና የወታደራዊ ሳይንስ አመራር በማነሱ በዓላማው የስኬት ጊዜ ላይ ተፅዕኖ ሳያሳርፍ እንዳልቀረ ይገመታል። የኦሮሞ ወታደራዊ መኮንኖችን አስተዋጽኦ አናሳነት በሕወሓት መኮንኖች ምሳሌ

ጋር አነፃጥሮ ማንሳት ይቻላል። ይኼውም ምንም ያህል አስቀድሞ ከመለስ ዜናዊ ጋር ተጣልተው ከሕወሓት የተለዩ ቢሆንም የትግራይ ሕዝብ ትግል ፈልጎናል ባሉበት ጊዜ ውስጥ እነ ስዬ አብርሃ፣ ጀነራል ፃዲቃን ገ/ትንሳይ እና የመሳሰሉት የሞቀውን የአሜሪካን አገር ኑሮ ጥለው የትግራይን ሕዝብ ትግል ለመምራት ነው ገስግሰዉ አገር ቤት የገቡት።

ለኦሮሞ ሕዝብ ትግል መቀንጨር ብዙዎች የኦሮሞ የፖለቲካ አዋቂዎችም ሆኑ አላዋቂዎች ከኦሮሞ ውጭ ባሉት ኃይሎች ላይ ጣታቸውን ይቀስራሉ። እኛ እራሳችን እውስጡ ስላለን ወደ ውስጣችን በቁርጠኝነት ስለማንመለከት ነው እንጂ ችግሩ የኦሮሞ አዋቂዎች ነን በሚሉ ላይ ያመዝናል። በቁርጠኝነት የሚታገል አንድ የኦሮሞ ሰው ከተገኘ ደግሞ በዚህም በዚያም ተብሎ እንዲወገድ ወይም እንዲያነክስ ይደረጋል። የኦሮሞ ሕዝብን ትግል ተረድተውና የሚኖሩበትን የተወሰነ ኑሮን ጥለው ትግል የገቡ፤ ትግል በመግባታቸውም እነሱም ሆኑ ቤተሰቦቻቸው የሚበሉትን፣ የሚለብሱትን፣ የሚኖሩበትን ቤት ሲያጡ፤ ሌሎች ግን ለትግሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ አድርገው የትግል እንቅስቃሴውን ካለማገዛቸውም በላይ ሁለት ቀናት የማያድር ድል በቀበሌ ወይም በወረዳ ደረጃ ሲመዘገብ ግን ተሰባስበው የድል ብስራት ዴስኳሪዎች እነሱ ይሆናሉ። ከሁሉ እንቆቅልሽ የሚሆነውና ብታምኑም ባታምኑም በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ ለኦሮሞም ሆነ ለሌላው መብት መከበር የሚታገሉ ቢያሸንፉ ቀድመው የሚሰለፉ፤ መሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሞተው እንኳን ቢያልቁ አንዳንድ የኦሮሞ ኤሊቶችና ባለሀብቶች እነርሱ ተርፈው እነሱና ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቻቸው ሌላ ዓለም ፈጥረው የሚቀጩት ወይም የሚዝናኑበት ይመስላቸዋል። ይኼ ስለሚመስላቸውም ነው ብቅ ጥልቅን የሚያዘወትሩት።

ሌላውን ሌላ ጊዜ የምንመለስበት ሆኖ ከዚህ ከተያዘው ከኦነግ የድክመት ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሱና በተለያዩ ጊዜያት ስለተጋረጠበት ችግር ማውሳት ይመረጣል። የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ለኳሾች በተለይ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የተንቀሳቀሱት እዚያው ምስራቅ አከባቢ ከነበሩት ጋር

ሲቀላቀሉ ስለተፈጠረው ችግር አንድ ማሳያ ማንሳት ይቻላል። የኦሮሞ ታጋዮች ወደ ምስራቁ የኦሮምያ አካባቢ የተንቀሳቀሱበት ሁለት ምክንያቶች እንደነበሯቸው መገመት ይቻላል። አንደኛው ምስራቃዊያኑ ኦሮሞዎች አስቀድመው የተሻለ የማንነት ንቃት አዳብረው ስለሆነ ለትግሉ ሲሉ ከሌላ የኦሮሞ አከባቢ መጥተው የተጠለሏቸውን ወገኖቻቸውን አሳልፈው አይሰጡም የሚል ዕምነት በልባቸው ሰንቀዋል። ሁለተኛው ደግሞ የሱማሌ መንግስት ከኢትዮጵያ በተለይም ከዛሬ ኦሮምያ ክልል የሚያቀርበውን የመሬት የይገባኛል ጥያቄን ዘንግተው እ.አ.አ በ1961 ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጣውና ወዲያውኑ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመሬት የይገባኛል ጥያቄ ምክንያት አታካሮ ውስጥ የገባውን የሱማሌ መንግስት ድንበር አቋርጠው ለሚመጡ ፀረ-ኢትዮጵያ መንግስት አቋም ይዞ ለሚመጣ ኃይል የመውጫና የመግቢያ ኬላ አይነፍገንም የሚል ተስፋ አድሮባቸውም ይሆናል።

እንደተባለውም በመጀመሪያ ዕሳቤ ምክንያት ወደ ምስራቁ ኦሮምያ የተጓዘው የትግል ችቦ አብሪዎች ጥሩም መጥፎም አጋጣሚ ጠብቋቸዋል። ጥሩ አጋጣሚ የነበረው በአከባቢው ይንቀሳቀስ የነበረውና በጃራ አባገዳ ይመራ የነበረው ግንባር ለኦሮሞ ነፃነት ቡድንና ሕዝቡ ተቀብለውታል። መጥፎው ደግሞ ምንጩ ምዕራብ ሆኖ ከመሀል አገር የተንቀሳቀሰው ቡድን ትምህርት ቀመስና ያነበበ ነው የሚባለው ኃይል ከጦረኛ ጃራ አባገዳ ቡድን ጋር ሲቀላቀል በሥልጣን ተጋፊነት ሳይጠረጠር አልቀረም። ከአንዳንድ ምንጮች ለመረዳት እንደተቻለው ጃራ አባገዳ ምንም እንኳን ፀረ-ፊውዳል የትግል ዓላማው የጠነከረ ቢሆንም ከመሃል አገር የሄደውን ቡድን በሥልጣን ተቀናቃኝነት ሳይጠረጥረው አልቀረም። ማን ምን እንደተናገረ ወይም ምን እንደሰራ በግልፅ የታወቀ ነገር ባይኖርም የሥልጣን ተጋፊነት ሳይፈጠር እንዳልቀረ ይነገራል። ስለሆነም፤ ሁለቱ ቡድኖች ከመሰባሰብና ከመቀላቀል ይልቅ የመበታተን ዕድሉ ሰፊ ሆኖ ተከሰተ።

በቡሃ ላይ ቆሮቆር ይሉ ዓይነት ተረት ሆነና በቂ ዝግጅት አድርጎና ሥራ

ተከፋፍሎ ወደ ትግል ያልገባው የኦነግ ጥንስስ ቡድን በባሮ ቱምሳ እና በበዶ ዳቻሳ መሞት አይሉት መገዳደል የባሰ ችግር ውስጥ ገባ። ባሮና በዶ ከ2ኛ ዓመት የዩኒቬርሲቲ ትምህርት ጀምሮ የመኻታ ክፍል ይጋሩ የነበሩና በከልቻ ይባል የነበረውን የኦነግ ልሣን አብረው ሲያዘጋጁ እንደነበረ አባጫላ ለታ መስክረዋል። ነገር ግን አሰቀድሞ ትግል ሜዳ ገብቶ ያገኙት በዶ ዳቻሳ ዱሮ የሚያውቁት ዓይነት እንዳልሆነ፤ “Dirree dhaqee Badhoon ani arge isan dur beeku natti ta’uu dide” በማለት አባጫላ ለታ (2022፡ 81) ገልጿል።

ሁለቱም ለትግሉ መሠረት መያዝ ያስፈልጉ እንደነበረና በተለይም ባሮ ቱምሳ ከፊትም መርቶ ከኋላም ሆኖ አንቀሳቅሶ መስራትም ሆነ ማሰራት የበለጠ ተሰጥኦ እንደነበረው ብዙ የተፃፉ ሰነዶች ይገልፃሉ። ባሮ ቱምሳን በዶ ዳቻሳ እንደገደለው አባጫላ ለታ (2022፡83) “Badhoon jara laman achitti dhiisee deemuuf ol ka’ee dhaabbatee dhukaasa itti bane.” ትርጉሙም በዶ ሁለቱን [ሌንጮና ባሮን] እዚያው ትቶ ለመሄድ ተነስቶ ቁሞ ተኩስ ከፈተባቸው ይላል። ነገር ግን የአባጫላ ለታ የዚህ ዐረፍተ ነገር ምስክርነት ከጥርጣሬ የሚያመልጥ አይሆንም። ምክንያቱም አባጫላም ሆነ ሌሎች አስቀድመው ከስብሰባው አከባቢ በመሄዳቸውና ተኩስ ሰምተው ዞር ብለው ሲመለከቱት ብቻ ባሮ የሆነ ጉድባ ላይ ወድቆ በማየታቸውና ሌንጮ በጫት ማሳ ውስጥ ስለመሮጡ እንጂ በዶ ተኩሶ ባሮን ስለመግደሉ አባጫላ ለታ እርግጠኛ ሆኖ አላስረዳም። የአባጫላ ጽሑፍ ባሮንና በዶን አቀያይሞ ለመገዳደል ያበቃቸው ጉዳይ ራሱ ምን እንደሆነ በውል ካለመግለጹም በላይ ማን መጀመሪያ እንደተኮሰ ወይም ሌላ ሰው ሁለቱን ስለመግደሉ ወይም ስላለመግደላቸው ዕቅጩን ለኦሮሞ ሕዝብ መንገር የሚችል አይደለም። ይህንን መግለፅ የሚችሉትና የነበረባቸውም አባጫላ ለታ ሳይሆን ሌንጮ ለታ ነው። ለማንኛም ለኔ ጉዳዬ የሆነው ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሩብ ምዕተ ዓመት ድረስ የኦሮሞ ምሁራን ለኢትዮጵያ ገዡዎች ለመመቻቸት እርስ በርስ መጋደላቸው እጅጉን የሚቆጭ ነገር መሆኑ ነው።

ወጣ ተብሎ ሲታሰብ በአፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ከራሱ ከኦሮሞ ጋር በተያያዘም ሆነ ከሌሎች ሶማሊያን ከመሳሰሉ ጎረቤት ሕዝቦች ከሚያሳርፉበት አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ እንደ ኦሮሚያ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች የተቋቋሙበት ወይም የተፈለፈሉበት፣ ከፍ ሲልም የኦሮሞን ሕዝብ ጥቅም የሚፈታተኑ ኃይሎች የተኮለኮሉበት ክልል የለም። ይህም የሆነው ያለ ምክንያት አይደለም። ከብዙ በጥቂቱ ምክንያቶች ውስጥ አንድም የኦሮሚያ ክልል የሀገሪቱ ማዕከል ያለበት ክልል በመሆኑና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም በብዙ አጋጣሚዎች ከዚሁ ማዕከል ከኦሮምያ በተለይም ከፊንፊኔ (ሸገር) ስለሚንቀሳቀሱ ነው። እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የፌዴራል መንግስቱም መቀመጫ ነው ይባል እንጂ ክልላቸው ከኦሮሚያ ማዕከልም ወጣ ያሉም ቢሆኑ ተንቀሳቃሽ ጽ/ቤታቸውን ብሪፍ ኬዝ ይዘው በማዕከል ደረጃ (የኦሮሚያን ጨምሮ) የሚያደረጉትን ሁሉንም እንቅስቃሴዎች ከዚሁ ከፊንፊኔ አድርገው ስለሚከታተሉ ወይም እንደየአቅማቸው ስለሚቆጣጠሩ፤ እነዚህ ብዛት ያላቸው ፓርቲዎች ፊንፊኔ ውስጥ እየተፈለፈሉ የኦሮሞ ድርጅቶችና ታጋዮች ላይ ተፅዕኖ መፍጠራቸው በቂ ምክንያት ነው ሊባል ይችላል። እነዚህ በፈለጉት አቅጣጫና ዓላማ ተደራጅተው በአዲስ አበባም ሆነ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱት ኃይሎች (ገዥው ፓርቲን ጨምሮ) የኦሮሞ ኢሊቶች ኃይል እንዲዳከም ከየራሳቸው ፓርቲ አልፈው ብዛት ያላቸው ስም እንጂ አባልና ሥራም የሌላቸውና በኦሮሞ ስም የሚንቀሳቀሱ ብዙ ፓርቲዎችን በማደራጀትና ከኦሮሞ ነፃነት ግንባርም በማስከበለል ለማምታቻነት እንዲያገለግሉ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል። ይህም ሊሆን የቻለዉ የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አካል ዉስጥ ተገቢዉን ቦታ ለመያዝ ስለሚመራዉ ትግል ኦነግ ከድርጅትም በላይ የኦሮሞ ሕዝብ የትግል መንፈስ ነዉ ብለዉ ስለሚያስቡ ነዉ።

የሌሎች በኦሮሞ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለጊዜው ትተን በኦሮሞ ሕዝብ ስም ተቋቁሞ በተለይም ከ1984 ዓመተ ልዴት ወዲህ በኦሮሞ ምሁራን ዘንድ የተከሰተውን የፖለቲካ ክፍተት ለመሙላት ስለተቋቋመውና የሰውን ስሜት ለመሳብ ስለተንቀሳቀሰው ፓርቲ -

ስለኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) ማንሳት ተገቢ ይሆናል። ከኦፌኮ መስራቾች አንዱ የነበረው የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግረስ (ኦሕኮ) በሕወሓት/ኢህአዴግ በተደረገበት ሸፍጥ ከውስጥ በተነሱ ፈንቃዮች የቀድሞ ስሙን፤ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮን) እስከ ማጣት ደርሶ ጽ/ቤቱንና ንብረቱን በመነጠቅ በኦህኮ ስም እንደገና ራሱን አደራጅቶ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ከሕወሓት/ኢህአዴግ ጥቃት መልሶ ነው ከኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር ሐምሌ 22/2004 ዓም በመቀላቀል የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) የተመሰረተው። ኦፌኮ ከተቋቋመ ረጅም ጊዜ የሆነው ቢሆንም በሰላማዊ ትግል ውስጥ የሚያጋጥሙትን ውስብስብ ችግሮች ያላወቁለት የኦሮሞ ተወላጆች ሳይቀሩ ከሩቅ ሆነው ኦፌኮን በዳተኛነቱ ያሙታል።

የሕዝብ አስተያየትን በሐሜት ደረጃ ብቻ ዝቅ አድርጎ አይቶ ወይም ሰምቶ ማለፍ ተገቢ አይሆንም። ዳተኛ ነው የተባለው ኦፌኮ በተለይ ከ2010 የኢህአዴግ ተሃድሶ ወዲህ የገባበት ቅርቃር ወይም በውንም የታየበት ዳኘኝነት በተለይም "የለማ ቲም" የሚባለው ቡድን ወደ ሥልጣን እንደመጣ አፍላ ሰሞን ፊታቸው ኦሮሞ ይመስላል፣ የለውጥ ኃይሉ ከሕዝብ ጎን የሚሰለፍ ከሆነ ከፊት ሆነን አናደናቅፋቸውም፣ ከኋላ ሆነን አንጎትታቸውም ከማለት ጀምሮ እስከ ተቋቋመው ጋዲሳ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ስብሰብ ድረስ ተሳትፎ ተደርጎ በክልል ደረጃ እንኳን ቢሆን ሥልጣን እንጋራለን" ተብሎ የነበረው እንደቀድሞው መኢሶን-ደርግ "ሂሳዊ ድጋፍ" ማድረግ ዓይነት በሽታ ተጋብቶብን ኦፌኮንም ሆነ አባላቱን ከፍ ሲልም የኦሮሞን ሕዝብ ዋጋ አስከፍሎናል። ገዥ ፓርቲ የሆነው የኢህአዴግ አዲስ አበባ ቀሪ ክፍል ስሙን ወደ ብልፅግና ፓርቲ ቀይሮ መግዛት ሲቀጥልና የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች መሰባሰብ ቢጀምሩም ዘለቄታ ሊኖረው አልቻለም። ዘለቄታ ሊኖረው ያልቻለበት ምክንያትም ገዥው ፓርቲ ወደ ሌሎች ክልሎች እየተመላለሰ ውይይት ሲያደርግና እርቅ ሲፈጥር ኦፌኮ እና ከመሳሰሉት የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ለመነጋገር እንኳን ተነሳሽነት የለውም።

አንድ ክብደት ያለው ጉዳይ ግን፤ ኦፌኮ እነዚህን የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ቢኖሩበትም በኦሮሞም ሆነ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ የቆዩም ሆነ ወቅታዊ ችግሮችን ለመፍታትና ብዛት ያላቸውን ችግሮች በመፍታት ዴሞክራሲዊት ኢትዮጵያን እንፍጠር በማለት አማካይ የፖለቲካ ሥፍራን በመያዝ የሰከነ ጥረት ያደረገ ፓርቲ ነው። በተለይም የነፍጠኛው ሥርአት አቀንቃኞች አንጋፋውን የኦሮሞ ሕዝብ ድርጅት የኦሮሞ ነፃነት ግንባርንም ሆነ የኦሮሞን ሕዝብ ወደ ጠርዝ ከመግፋት እንዲቆጠቡና የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚገባውን ሥፍራ እንዲይዝ ቀላል ያልሆነ ጥረት ያደረገ ፓርቲ ነው። በተጨማሪም ኦነግ የኦሮሞ ብሔር ሕዝብ የብሔራዊ ማንነቱ ግንዛቤን እንዳስጨበጠ ሁሉ ኦፌኮም የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ፖለቲካ እና ኤኮኖሚ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ቦታ በግልፅ ያመላከተ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የሰላም፣ ዴሞክራሲና ፍትሓዊ ተጠቃሚነትን ያስተማረ የነፃነት ንቅናቄ አካሄድን ያስተማረ ፓርቲ ነው። ኦፌኮ የሶሻል ዴሞክራሲ አመለካከትን በመምረጥ ከግራም ሆነ ከቀኝ ኃይሎች እንዲሁም ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚመጡበትን ጽንፈኝነትና አክራሪነትን በመቋቋም የተንቀሳቀሰ የፖለቲካ ድርጅት ነው። የሶሻል ዴሞክራሲ አመለካከትን በኢትዮጵያ ውስጥ በመምረጥ ኦፌኮ የመጀመሪያ ፓርቲ ባይሆንም የማያወላውል አቋም በመያዝ ኦፌኮ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት አንዱ ነው። በነገራችን ላይ ሶሻል ዴሞክራሲ አንድ ራሱን ችሎ የተቀመረ ርዕዮተ ዓለም ሳይሆን በአንድ በኩል የሊበራሊስቶችን የመንግስት ሚና ማኮሰስ በመግታት እና የገበያ መር ኤኮኖሚ አቋም ሕፀፆችን በመጠገን፤ በሌላም በኩል የሶሻሊስቶችን የውሸት ዴሞክራሲ ጭምብል በማስወለቅ **ፍትሓዊ ተጠቃሚነት** ጎልቶ እንዲወጣ የሚያደርግ አመለካከት ነው። እንደ ክርስቲያን ኬርል አገላለፅ "Social democracy is, … a conception of democracy at the heart of which stands equal freedom for all and which expresses the close connection between political and social emancipation." ነው። ከኦፌኮ አባላት ጀምሮ ስንቶቹ ይህንን መርህ በትክክል እንደተረዱት አይታወቅም እንጂ እኩል ነፃነት ለሁሉም በተለይ ደግሞ

ነፃነት ወይም አሳታፊነትን ለማስፈን የተለየ ሐሳብ ለሚያራምዱ ዕድል የሚሰጥ ፓርቲ ቢኖር አንዱ ኦፌኮ ነው።

የኦነግ-ኦፌኮ ጥምረት ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላም በኩል ስሙን በየጊዜው እየለዋወጠ ከሚገኘው ከገዥው ፓርቲ፤ (ኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ወይም ኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ) ወይም ብልፅግና ፓርቲ (ብፓ) ኦሮሚያ ቅርንጫፍ) እና ሌሎች በኦሮሞ ስም የተቋቋሙ ፓርቲዎች፤ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር፣ የመላ ኦሮሞ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ገዳ ሥርአት አራማጅ ፓርቲ (በቅርቡ ደግሞ ገዳ ብልሱማ በማለት ራሱን የሚጠራ)፣ ኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ፣ የሕወሓት ደንጡር የሆነዉ ኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ፣ ኦሮሞ ብሔራዊ ፓርቲ፣ የኦሮሞ አንድነት ነፃነት ግንባር፣ የኦሮሞ ነፃነት ፓርቲ፣ ኦሮሞ አቦ፣ የመላው ኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና ሌሎችም በኦሮሚያ ውስጥ የተፈለፈሉና በመናኛ ጥቅም እየተገዙ የኦሮሞ ሕዝብን የነፃነት ትግልን ሲያደናቅፉ ከኖሩ ጋር ኦፌኮ ያደረገው ትግልና አባላቱ የከፈሉትና እየከፈሉት ያሉት መስዋዕትነት ቀላል አይደለም።

በአገር ውስጥ ስንቀሳቀስ የነበረውን የኦፌኮን ስም ለማጠልሸት በቶለሳ ተስፋዬ የሚመራው የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ)፣ ገዳ ሥርአት አራማጅ ፓርቲ፣ የመላው ኦሮሞ ነፃነት ፓርቲ እና ሌሎች ኦሮሞን እንወክላለን የሚሉት፤ ከኦህዴድም ከፍ ብለው በሕወሓት/ኢህአዴግ እየተገዙ እነሱ ማሸነፍ ባለመቻላቸው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱት ምርጫዎች ሁሉ ዴሞክራሲያዊ እንደነበሩ የውሸት ምስክርነት የሰጡት እነዚህ ኃይሎች፤ በኦፌኮም ሆነ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ቢዝነስ ሰርተዋል። እነዚሁ የታሪክም ሆነ የሕዝብ ሸክሞች በኦነግ አባልነትና ደጋፊነት የተጠረጠሩና የኦፌኮ አባላትን በሽብርተኝነት እየወነጀሉ ወደ እስር ቤት እንዲጋዙና የእስር ቤቶች ቋንቋ ራሱ አፋን ኦሮሞ እንደሆን ያደረጉ፤ እንዲህ ለመሆኑም ኦሮሞ ባልሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ዜጎች እየተገለጸ እየሰሙ "ወንጀል ሰርተው እንጂ በፖለቲካ ምክንያት አንድም የታሰረ ሰው የለም" ያሉ የኦሮሞ መርገምቶች ናቸው። ከነዚህ ፓርቲዎች

አንዳንዶች በአንድ ሰው ወይም በጥቂት ሰዎች የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ዋና ሚናቸውም ለገዥው ፓርቲ ወሬ እያቀበሉ አገሪቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እንዳለ ለመናገር ስብሰባ አዳራሽ ቀድመው የሚገቡና የገዥውን ፓርቲ መሪዎችን በቂ ባልሆነ አፈፃፀም ለማመስገን የሚሽቀዳደሙ ናቸው። ሌሎችን ጨምሮ እነሱ በኦሮሞ ስም የተቋቋሙ ፓርቲዎች የፌዴራሊስት ኃይሎች በሚል ስም ተባድነው ለሕወሓት ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ ከ2012 መጨረሻ አከባቢ ጀምሮ የሕወሓት/ኢህአዴግን ወንበር ለተረከበው የብልፅግና ፓርቲ አነስ ባለ ዋጋ የተለመደ አገልግሎታቸውን ለተወሰነ ጊዜ ያበረከቱ፤ የፓርቲነት አገልግሎታቸዉ ሲያበቃ ደግሞ ለዉለታቸዉ ሲባል በግል በከፍተኛ አማካሪነት ተቀጥረዉ የሰሩ ናቸው። በተጠቀሱትና ብሔረተኞች ነን በሚሉትና በተለይም አገር ቤት ባሉት ወገኖች ኦፌኮ በበቂ ሁኔታ ስላልተረዳ እንቅስቃሴው ሁሉ ዘገምተኛ እንዲሆን ተገድዷል።

ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ከኦነግ ጋር ብቻ የተያያዘ ባይሆንም ሁለተኛው ስለኦሮሞ ሕዝብ መነጋገር የግድ የሚለው አብዛኛው የኦሮሞ ተወላጅ ገና ያላለቀለትንና እንዲያውም በሐበሾች ተፅዕኖ ሥር ለረጅም ጊዜ ስለቆየው ስለኦሮሞ ብሔራዊ ማንነቱ ግንባታ ያለውን ግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት በተለይ ኤሊቱና ባለሀብቱ ያላቸው ቁርጠኝነት አናሳ የመሆን ጉዳይ ነው። በርግጥ በምንሊክ የኃይል ወረራ ተገድዶ በኢትዮጵያ አገዛዝ ሥር የወደቀው የኦሮሞ ሕዝብ ከተባለው የምንሊክ ወረራ በፊት ኦሮሞ በሚገኝባቸው ቦታዎች ሁሉ እንድተዋወቅና አንድ ብሔራዊ ማንነት እንዲገነባ ያደረገበት ሁኔታ ስለሌለ የኦሮሞ ሕዝብ የራሱ የሆነ ብሔራዊ አንድነት በተሟላ ሁኔታ ገንብቶ እንዳልጨረሰ ይታወቃል። እንኳንስ ከምንሊክ ወረራ በፊትና በዚያን ወቅት ቀርቶ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜም በኃይሌ ሥላሴ የመንግስት አስተዳደር ውስጥ በቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ለመማር ከወለጋ የሚመጣ ወጣት ኦሮሞ ሌላ የሐረርጌ ኦሮሞ መኖሩን ወይ አያውቅም፤ ቢያውቅም ከሱ ጋር የኦሮሞነት የጠበቀ ብሔራዊ ትስስር ያለው አይመስለውም ነበር። ማለትም የኦሮሞ ብሔረተኝነት አንድም አላደገም ወይም ዕድገቱ

በኦሮሞነትና በሐበሻነት መሀከል የተሰናከለ ዘገምተኛ ነበር ለማለት ነው።

ስለኦሮሞ ሕዝብ ክፉ የሚያስቡት እንደሚናገሩት የኦሮሞ ሕዝብ ለክፍፍል የተጋለጠውና ለምንሊክ ወረራም የተመቸው በከፋፍሎ የመግዛት ዘይቤ ስለሆነ ብዙም የሚያሳስብ አይሆንም የሚሉ አሉ። ሸዋን የገዥው አባል ወይም ተባባሪ ያደረገው የምንሊክ ወራሪ ኃይል ወለጋንና ጂማን ወዳጅ አድርጎ በሌሎች ደቡብ እና ምዕራብ ሕዝቦች ላይ በማሰማራቱ እንደሆነ በቁጭት ይነገራል። የምንሊክን ወረራ ለመቋቋም የወለጋንና የጂማን ትብብር የጠየቁት የኢሉው አባቦራ (ጫሊ) ፋታንሳ እና የቡኖው ፍሪሳ አባወጋ ወዳጆቻችን ናቸው ከሚሏቸው ከጂማና ከወለጋዎቹ ገዥዎች ሳይደርሱላቸው ስለቀሩ በተለይ የኢሉው ሰው አስከሬኑ በወራሪው ኃይል ተቆራርጦ በዛሬዎቹ ሦስት ወረዳዎች ውስጥ እንዲበተን ተደርጓል። የዕድገት ደረጃው ስላልፈቀደ የአርሲው፣ የሸዋው፣ የኢሉው፣ የወለጋው፣ የሀረርጌው፣ ወዘተ ኦሮሞ ለብቻ ለብቻው ነው የተወቀጠው። ሲጠቃለል፤ የኦሮሞ ብሔራዊ አገርም ሆነ የኦሮሞ ብሔርተኝነት በማዕከላዊነት ሊገነባ አልቻለም ማለት ነው። የመጀመሪያ ሙከራ ተደረገ እንኳን ቢባል የምዕራብ ኦሮሞ ኮንፌዴረሽን በወለጋ ውስጥ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለአጭር ጊዜ የተከሰተው እና የመጫና ቱለማ ማህበር አርሲ ዴራ ላይ ኦሮሞን ሃይማኖትም ሆነ ሌላ ሊከፋፍል እንደማይችል ቃል ኪዳን የፈጠሩበት ናቸው።

በተበታተነም ሁኔታም ቢሆን ከመጠነኛ የአነጋገርና የአለባበስ ልዩነት በስተቀር ባለበት ቦታ ሁሉ ብሔራዊ ማንነቱን ጨርሶ ያልጣለው የኦሮሞ ሕዝብ ፈፅሞ የጋራ ማንነት እንደሌለውም ተቆጥሯል። ሰለሞን ስዩም ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ገጽ 7-8 ባህሉ ተፈላን ዋቢ በማድረግ "ቁጥረ-ብዙው የኦሮሞ ሕዝብ በጋራ ከሚኖረው ቋንቋ በተረፈ እምብዛም የጋራ ማንነት የሌለው የትንንሽ መንግስታት ስብስብ ነው፤ እርስ በርስ ለመዋጋትም የማያመነቱ ናቸው።" ብሎ የኦሮሞ ብሔረተኝነት ያለ ማደጉን ገልፆ ባህሉ ተፈላ የፃፈውን የማኮሰስ ጽሑፉን አስነብቧል። የባህሉ ተፈላ የማኮሰስ ጽሑፍ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን

ዕውነትነት እንዳለው ብንቀበል እንኳን የኦሮሞ ብሔረተኝነት ልክ እንደሌላዉ ሕዝብ ብሔርተኝነት ዕድገት ብዙ ዉስብስብ ሂደቶች ዉስጥ ማለፍ የግድ እንደሆነ ማወቅን ይጠይቃል።

አስገራሚው እሱ ያለፈው ጉዳት አይደለም። ዛሬም ቢሆን ብዙዎች የኦሮሞ ኤሊቶች ሕወሓት የኦሮሞ ብሔረተኝነትን ለማጨናገፍ በራሱ አምሳያ ቀርፆ ካሰማራው ከኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ምት ማገገም አለመቻሉና ጥቅሙን ማስጠበቅ ከሚችልበት ደረጃ ላይ አለመድረሱ ጉድ የሚያስብል መሆኑ ነው። ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ኢህአዴግ አገዛዝ ድረስ የቀጠለው የአበሻ ልጆች አገዛዝ ኦሮሞን በአካል ከመግደል ጀምሮ ዕውቀት እንዳያገኙና በአገኙት ዕውቀትም ተገቢ ሥፍራ ይዘው እንዳይሰሩ ጫና መፍጠራቸው፣ በተለይም ደግሞ የኦሮሞ ተወላጆች በተፈጥሮ ቋንቋቸው እንዳይጠቀሙ፣ ባህላቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ታሪካቸው፣ ልማዳቸው፣ ማህበራዊ መስተጋብራቸው እንዳይጎለብት ሕጋዊና ተቋማዊ ጫና ሁሉ ተደርጎባቸዋል። የሩቁን ትተን የቅርቡን የኢህአዴግ ዘመን ብናነሳ እንኳን የኦሮሞ ተወላጆች ከፍተኛ የመንግስት ሥልጣን ጋር እንዳይደርሱ ታስቦ በተሰራው ሁኔታ፤ በተለይ ኦነግ ከሽግግር መንግስቱ ተገፍቶ ከወጣ በኋላ እና ሠራዊቱ በአሜሪካና ኤርትራ ስትራቴጂ ነዳፊነት ካምፕ እንዲገባ ተደርጎ ባዶ እጁ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የተወሰደበት ገደብ የለሽ የመግደል፣ የማሰር፣ የማሳደድና የማጎሳቆል እርምጃ የኦሮሞ ብሔርተኝነትን ጨርሶ ባያጠፋም በብዙ ጊዜያት ወደኋላ እንድጎተት አድርጓል። ለግላቸው ጠባብ ዓላማ የቆሙ አንዳንድ የኦሮሞ ባለሀብቶች ደግሞ ወገኖቻቸውን አራቁተው በብርሃን ፍጥነት ያገኙትን አዱኛ ለወገኖቹ በርህራሄ ከመርዳትና ለነፃነት ታጋዮቹ ማጎልበቻ ከማዋል ይልቅ ለኦሮሞ ገዳዮች ይበትኑታል። የግለሰቦች ጉዳይ ቢመስልም በንዋይ ፍቅር ተሸንፈው ከአባቶቻቸውና እናቶቻቸው ገዳዮች ጋር የተፈጣጠሙም ብዙዎች ናቸው። ኦሮሞ አቃፊና አሳታፊ ነው የሚባለውና የማይለወጥ ተደርጎ የሚነዛው አባባልም (stereotype) በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ቀላል ያልሆነ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን አዙሮ ማየት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ ሳይከፋፈል ጠላቱን ይዋጋል የሚለው የጥንቱ የአባ ባህሬ ምስክርነት ቃል እንኳን ዛሬ የተዳከመና ያረጀ ተረት ከሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ምክንያቱም፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ ቀላል የማይባል ገንዘብ በማፍሰስ ባህርይውን እየለዋወጠ ዓላማውን የሚያስፈጽምለትን ኦህዴድን አደራጅቷል፤ ቀላል የማይባል ሀብት በመሰብሰብም የነፃነት ትግሉ ከግብ እንዳይደርስ ሰፊ የገንዘብ መጠን በማፍሰስ ራሳቸውን ሸጠው ሕዝብ ላይ ሸፍጥ የሚሰሩ ሰዎችን በዚህ ድርጅት አማካይነት አሰማርቷል፤ እጅ አንሰጥም የሚሉትን ወገኖች እስገድሏል፣ አሳስሯል፣ ከኑሮአቸው እንዲፈናቀሉም አድርጓል። ከዚህ ድርጅት መንሰራፋት በኋላ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው የሚባለው የአማርኛ ተረት ኦሮሞ ሰፈር ሳይገባ ኦሮሞ አቃፊ ነው የሚለው የጥንቱ ትርክትም በጥንቃቄ መፈተሽ ያለበት መሆኑ ግንዛቤ እንድውሰድ የግድ ይላል። አንዳንዶች በንዋይ እየተገዙ ከኦሮሞ ሕዝብ ፍላጎት ውጭ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሲቀፈቅፉ የሚኖሩ የኦሮሞ ሰዎችን ስመለከቱት ኦሮሞ ገና ያልሰለጠነና በቀላሉ ላይግባባ የሚችል ማህበረሰብ አድርገው እንዲገምቱ አስችሏቸዋል። እነዚያ በንዋይ የሚገዙ የኦሮሞ ተወላጆች በሐቀኛ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ እርምጃ ከማስወሰድ ውጭ እርምጃ ተወስዶባቸው ስለማያውቁ የነፃነትን ውድ ዋጋ አይረዱም። አልተራቡም፣ አልታረዙም፣ ድንጋይ ተንተርሰው ጉቶ ተደግፈው አላደሩም፣ አልታሰሩም፣ አልተገረፉም፣ የሞት ጥላ አላንጃበባቸውም። አንዳንዶች በስደት ቢኖሩ እንኳን በያሉባቸው አገሮች በታገይ ሕዝብ ዕርዳታ ስም ለዘመዶቻቸው የሀብት ኮረብታ ከመስራት ባለፈ መስዋዕት ለሚከፍሉ ወገኖቻቸው ክብር አልሰሩም፤ ሰሩ እንኳን ቢባል የሚጠበቀውን ያህል አይደለም። የኦሮሞ ሕዝብ እርስ በርስ መረዳዳትም ሆነ መተጋገል አሁንም ገና ቀሪ ሥራዎች እንደሚጠብቁት ነጋሪ የሚሻ አይመስለኝም።

የቄሮ/ቃሬ የትግል እንቅስቃሴ ለኦሮሞ የብሔረተኝነት ግንባታ ነፍስ የዘራበት ቢሆንም፤ ዛሬም ቢሆን ስንፍናን፣ ጥርጣሬንና ፍርሃትን አስወግደው ከትግል ግንባር ያልተሰለፉ የኦሮሞ ልጆች ገና ብዙ ናቸው ማለት ብቻ ሳይበቃ፤ እጅግ አንገብጋቢ የሚሆነው ደግሞ ከትግል ግንባር

ከተሰለፉት ብቻ ውጤትን መጠበቅ የኦሮሞ ኤሊቶችና ባለሀብቶች የቆየ በሽታ (ጋንግሪን) ሆኖ ይታያል። ዛሬ ተነስተን ዓለም ላይ መዘዋወር ብንችልና የኦሮሞ ብሔር አባላት ይህን ያህል ብዛት አለን እያሉ፤ ሰፋት ያለው ሀብትም አለን እያሉ፤ በጥቂቶች ተገዛን፣ ተበደልን፣ ሕልውናችን ፈተና ላይ ወደቀ ብለው የሚያማርሩት ለምን ይሆን ብለው ሌሎች ሰዎች እንቆቅልሽና ዕውነት የሚመስል ጥያቄ፤ በርግጥም ዕውነት የሆነ ጥያቄ ቢጠይቁንና ለጥያቄአቸው መልስ ቢኖረን እንኳን በመልሳችን ዙሪያ ጠያቂዎቻችንን ለማሳማን ቀላል የማይባል ጊዜ እንደሚፈጅብን የኦሮሞ ልጆች ጥልቅ ግንዛቤ ልኖረን ይገባል።

ከዚሁ ጋር ሌላም የሲቪል ምሁራን ኢሊቶቹ በሽታ አለ። ለኦሮሞ ሕዝብም ሆነ ለሌሎች ሕዝቦች የነፃነት ትግል አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ ብሔራዊ ስሜቶች ገንብቶና ሌሎች እሴቶች እንደ ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ሥዕል፣ ቅርሳ ቅርስ፣ የታሪክ ጥናት፣ ስለስፖርትና የሰውነት ማጎልመሻ ልምምዶች፣ ወዘተ አስመልክቶ የቀናትና ምሽቶች ፕሮግራሞች ተይዘላቸው በኦሮሞ ምሁራን ውይይት እየተደረገባቸው አይደለም። ብዙ የኦሮሞ ልጆች የንባብ ልምድ የላቸውም። በማንበብ መሠረታዊ ዕውቀት ካልተጨበጠ ደግሞ ስለመሠረታዊ ጉዳዮች ውይይት ሲነሳ በምክንያት ከመተማመን ይልቅ ወደ ኩርፊያ ማምራት ይሆናል። በጣም አሳዛኙ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ የኦሮሞ ምሁራን ጊዜ ጥሏቸው ስለሄደ ዳግም ተመልሰው ትግሉን ሊያገኙት ወይም ሊቀላቀሉት የማይችሉ ይመስላቸዋል። እንዲያውም አንዳንዶች ደግሞ ስለኦሮሞ ሕዝብ ብሔራዊ ማንነት ግንባታ ሲነሳ ሌሎች ሕዝቦችን ወይም አገርን የበታተኑና ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት መናጋት የሚጠየቁ ይመስላቸዋል። ስለሆነም፤ በመጫና ቱላማ የልማት ማህበርና በኦሮሞ የነፃነት ግንባር የተጀመረው የኦሮሞ ብሔራዊ የማንነት ግንባታ ቀሪ ሥራዎች አሁንም በስፋት እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። የኦሮሞ ተወላጆች ለራሳቸው ማንነትም ታማኝ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ሲጠቃለል፤ ለኦሮሞ ብሔራዊ ማንነት ታማኝ አለመሆን ማለት ፖለቲካውን በሐበሻ ሽፍጥ ከማስጠለፍ በስተቀር ሌላ ትርጉም

አይኖረውም።

በ1984 በኦነግ ከሽግግር መንግስት መገፋት የተዳፈነ የመሰለው የኦሮሞ ሕዝብ የማንነት (ብሔረተኝነት) ግንባታ ከ2005 ዓም ጀምሮ በአዲሱ ትውልድ ውስጥ በተከሰተው የቄሮ/ቃሬ ትግል ሊያንሰራራ ችሎ ነበር ብያለሁ። በቄሮ ግንባር ቀደምትነት የተቀጣጠለው ሕዝባዊ እምቢተኝነት በኢህአዴግ ላይ ጫናን ፈጥሮ የኢህአዴግ ኃይል በአዲስ አበባ እና መቀሌ መሀከል እንዲበታተንና እንዲቀንስ ተደርጓል። በውጤቱም በኃይል ተገፍትሮ ከሽግግር መንግስቱ የወጣው ኦነግ በ2011 ዓም የተመናመነ አመራሩን ይዞ ስለታጣቂ ኃይሉ ብዙም ሳይባል ወደ አገር ቤት ተመልሷል። ዛሬ ከተደረሰበት ዕድገት አንፃር ኦነግ ያሰባሰበው የኦሮሞነት ቅርስ ተሰባስቦ ከአንድ ቅንጣት ድርጅትነት በላይ በማደግ የኦሮሞ ሕዝብን ብሔራዊ ማንነት አንድ ላይ ያጋማደ ተጠቃሽ መንፈሳዊ ድርጅት ሆኗል። ነገር ግን "ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቄስስ አይለቅም" የሚባለው ዓይነት ተረት ሆነና በሠላማዊ መንገድ ታግሎ የኦሮሞ ሕዝብን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተገቢ ቦታ ለማስያዝ የተንቀሳቀሰው ኦነግ አሁንም በገዡ ፓርቲ መንግስት ጫና ከመንገጫገጭ አላመለጠም። በ2012 ዓም ወደ መጨረሻ አከባቢ ደግሞ የሕቡዕ ትግል ላይ እንደነበረ ጊዜ ሆኖ እንደገና ተፈረካክሷል። አንድ እንዲታወቅ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ግን ለኦነግ አገር ውስጥ ከገባ በኋላ እንደገና የመሰነጣጠቅ ምክንያቶች አንድም የሕወሓትን ወንበር የተረከበው ኦህዴድ መስከረም 5/2011 ዓም ወደ አገር ቤት የገባውንና ከተጠበቀው በላይ አቀባበል የተደረገለትን ኦነግን በሐበሻ ኤሊቶች ግፊት በክፉ ዓይን ማየትን አለመተው ነው። ሁለተኛውና ጎልቶ የታወቀው ግን ቀደም ሲል በግለሰቦች ጫና ከኦነግ ተገፍተናል የሚሉት ቀደምት የኦነግ አባላት ከተስፈኛ የወቅቱ የኦነግ አመራሮችና ኦነግን ለግል ጥቅማቸው መያዣ ከአደረጉ አዛውንት የቀድሞ ኦነጎች ጋር በመሆን የፈጠሩት አታካሮ አስቸጋሪነት ነው።

አዛውንቶቹ የቀድሞ ኦነጎች ከገዥው ፓርቲ ሰዎች ትዕዛዝ ተቀብለው

የሚያላዝኑት ነገር አለ። እሱም በኃይሌ ሥላሴ፣ በደርግም ሆነ በሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዞች ኦነግ አንድም ጥይት ሳይተኩስና አንድ ወረዳ ቀርቶ አንድ ነፃ ቀበሌ ሳይኖረው ዛሬ ከኢህአዴግ ወጥተው ዴሞክራሲያዊያን በሆኑ ታዳሽ የኢህአዴግ አባላት ወይም ብልፅግና ፓርቲን መገዳደራቸው እንደሚያሳዝናቸው በመግለፅ ኦነግን አምርረው ይኮንናሉ። ዛሬ ላይ ሆነን የምንረዳው መራር ዕውነት አለ። እሱም ኦነግ በተጠቀሱት አገዛዞች ውስጥ ውጤት ያላስመዘገበው እነዚሁ የኦነግ አዛውንቶች አንድም ትግሉን ለመምራት የሚጠበቅባቸዉና አሁን ግልፅ ወጥተው የትግሉ ጋሬጣ ሆነዉ እንደቆሙት ዓይነት ሁኔታ ሳይቆሙ በመቅረታቸውና እንዲያውም በዚያን ወቅት በነበራቸው የኦነግ አመራር ውስጥ አመራሩን በስውር ሲያሽመደምዱ ስለቆዩ እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃ አያሻውም። በአጭሩ፤ በወቅቱ የነበረው የመገናኛ ዘዴ ምቹ አለመሆንና ተበታትነው በአገር ቤትና በጎረቤት አገሮች የነበሩትን የኦነግ አመራሮችን በቀላሉ አገናኝቶ ትግሉን ለማስተባበር ብቃት እንዳልነበረው መጥቀስ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ትልቁ ችግር ግን እነዚያ አዛውንት አመራሮች ኦነግን ለድል የሚያበቃ አመራር ሲሰጡ እንዳልነበረ ወቅቱን ጠብቆ ግልፅ መሆኑ ነው። እነዚያ አዛውንቶች እንኳንስ ኦነግን ውጤታማ ሊያደርጉ ቀርቶ እራሳቸው ተከፋፍለው ተቀጥላ ኦነግ ወይም ሌላ ‘ዴሞክራሲያዊ ግንባር’ የሚሉትን ሲገነቡና ሲያፈርሱ የቆዩ ስለሆነ ማን ምን እንደነበረ ራሳቸውን አጋልጠዋል። ስለሆነም፤ ያለ ምንም ማጋነን ሕዝብ ያለው ኦነግ መሪ/መሪዎች እንዲያጣ ተደርጓል። ይህ ደግሞ ድንገተኛ ክስተት ሳይሆን ሆን ተብሎ የኦሮሞ ሕዝብን የነፃነት ጥማት እንዲሁም የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊነትን ለመጉዳት ታስቦበት የተሰራ ስልታዊ ሴራ ነው። ዝም ተብሎ ሲታሰብ ግን የኦሮሞ ነፃነት ግንባርንም ሆነ ሌላውንም ለሕዝብ እንቆማለን የሚሉ የሕዝብ ኃይሎችን ለማዳከም የሚሞክር መኖሩ ባይካድም፤ በደል የተጫነበትም ሆነ በተጫነበት በደል የተቆጣ ሕዝብን ከትግሉ አውድ አደብ ማስገዛት ይህን ያህል ቀላል ሆኖ እንደማይገኝ ከኦሮሞ ሕዝብና ኦነግ መስተጋብር መረዳት ይቻላል። ዛሬ በተደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንፃር የኦሮሞነት ኦሮሙማ ማንነት ከማንኛውም ሃይማኖት በላይ ያደገና ሰፊ መሠረት የገነባ መሆኑንና

ለዚህም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የተጫወተው ሚና ትልቅና እንዲህ በቀላሉ ሊቀለበስ የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት

የትግሬ ብሔር በአከባቢዉ ከሚገኙት የአፋር፣ የአማራ፣ የራያ አሰቦ እና ቅማንት ሕዝቦች ጋር ከሚፈጥሩት መስተጋብር በስተቀር እራሱን በቻለ ክልል ዉስጥ በኩታ ገጠምነት የሚኖር ነዉ፡፡ የኑሮ ሁኔታዉ ዉስን የእርሻና ከብት ርቢ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ተወላጆቹ በመላ ኢትዮጵያና በሌሎች ዓለማትን ተበታትነዉ በመስራት እርስ በርስ የመደጋገፍ ባህልን ያዳበሩ ናቸዉ፡፡ ከ1983 ወዲህ ደግሞ በተፈጠረላቸዉ ዕድልና እጁ በገባው ረብጣ ዕጣ ፈንታ ምክንያት የተወሰኑ የፋብሪካ ግንባተዎች አስገብቷል፡፡ አከባቢዉ ወቅትን ጠብቆ ከሚከሰት ተደጋጋሚ የአየር ንብረት መዛባት የተነሳ በማዕካላዊ መንግስት አስተዳደር ካልታገዘ በስተቀር የተፈጥሮ አከባቢዉ ለመገናኛም ሆነ ለእርሻ ምቹ ባለመደረጉ የሕዝቡን ደስተኛነት እንዳይሆን ዓይነት አድርጎ እንዲቆይ አስገድዶት ነበር፡፡

ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ግዛት የአስተዳደር ማዕከሉን በማፈራረቅ አንዴ በአማራ ሌላ ጊዜ ደግሞ በትግሬ ተወላጆች ሥር ይተዳደር እንደነበር እናስታዉሳለን፡፡ ከአፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ግን የመንግስት ማዕከል ከትግራይ እንድርቅ በመደረጉ የትግሬ ተወላጆች ኢትዮጵያን ወደ መግዛት ሥልጣን የሚመለሱበት ሁኔታ እንዲደብዝዝ ተደርጓል፡፡ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 271) እንደፃፉት “ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ የትግራይ ግዛት ባጠቃላይ፤ መኳንንቱ በተለይ፤ የፖለቲካ ማዕከላዊነት በማጣታቸዉ ምክንያት የተሰማቸዉ ቁጭት ሲሆን፤ በሃያኛዉ መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ በክፍለ ሀገሩ በተከሰተዉ ተደጋጋሚ ድርቅ ምክንያት የደረሰዉ የኤኮኖሚ ችግርም የበደል ስሜቱን [በማባባሱ]” ጥቂት የዩኒቬርስቲ ተማሪዎችና የአከባቢዉ ነዋሪዎች (የንጉሱ ፓርላማ አባል የነበረ አቶ አየለ ገሠሠ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ ስዩም መስፍን፣

አስግደ ገብረስላሴ፣ ቀለበት ታየ፣ ፀሐዬ አረፋአይኔ፣ አግአዚ ገሠሠ፣ ሙሉጌታ ሐጎስ፣ አምባዬ ወልደጊዮርግስና አማራው አብተው ታከለ፣ በኋላ ስብሃት ነጋም ተቀላቅሏል) ያንን ያጡትን ማዕካላዊ አስተዳደር በሚገኝበት አዲስ አበባ ድረስ በመምጣት መልሶ ለመጨበጥ እንኳን ባይችሉ ትግራይን ነፃ አድርገው ለመግዛት ወደ ግዛቲቱ ሽሬ አዉራጃ፣ ደደቢት ወደምትባል በረሃማ ወረዳ ገብተዉ ለመዋጋት (ጊዮርግስ ፊትለፊት ወደ ሀገር ፍቅር መውረጃ አንዲት ሻይ ቤት ውስጥ በመገናኘት) የካቲት 11፣ 1967 ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓትን መሠረቱ።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ትግራይን ጨምሮ ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች ማንም ሰዉ ባላሰበዉ ጊዜና ሁኔታ አንድም ከውጭ ኃይል ጋር አሊያም የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ በመግባት ጦርነት ዉስጥ ስለሚገቡ የሕዝቡ ምርታማነት እንዲቀንስ እየተደረገ የኖረበት ጊዜ ብዙ ነዉ። ከነዚህና ሌሎች ከታች በምንመለከታቸዉ ምክንያቶች የተነሳ የግዛቲቱ ወይም የክልሉ ወጣቶች በተለመደው ሁኔታ ለትግል ቢነሳሱ አበጀችሁ ሊባሉ የሚችሉበት ሁኔታ ነበር/አለ።

ሕወሓት የመንግስት መንበር የተቆናጠጠበት ደረጃ ጋር ከመድረሳችን በፊትም ሆነ ሕወሓት ራሱ ሕወሓት ከመባሉ በፊትም ረጅም ጊዜ የወሰደ ሁለት ደረጃዎችን ተራምዷል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ሌሎች ደረጃ ተማሪዎች እንደተመሰረተ የሚነገረው ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ/ማገብት እና ተጋድሎ ሀርነት ትግራይ/ተሀት የሚባሉ ድርጅቶችን ፈጥረዉና አባጣ ጎርባጣ መንገዶችን አልፈዉ ከዮሐንስ 4ኛ ወዲህ የተነጠቁትን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ አስተዳደር እስከ 2010 ዓም ድረስ በራሳቸዉ አምሳያ በቀረጹት ኦህዴድ እስከ ተነጠቁበት ጊዜ የቆዩበት ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸዉ። እንደማንኛዉም የሌላ አከባቢ ሕብረተሰብ ወጣቶች ለትግራይ ወጣቶችም ለአከባቢዉ የብሔርተኝነት ስሜት መፈጠርና መጎልበት አልፎ ተርፎም በአሸናፊነት የመንግስት ሥልጣን እስከ መያዝ ለመድረስ የቻሉበት ሣቢና ገፊ (push and pull factors) የሚባሉ ምክንያቶች ነበሩ።

የብሔር ንቅናቄዎች ከንጉስ ኃይሌ ሥላሴ ዘመን ማብቂያ በፊት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ናቸዉ። ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ለማድረግ ብረት አንስተዉ ትግል የጀመሩት የኤርትራ የአርነት ንቅናቄዎች (ጀብሃ እና ሻዕቢያ)፣ የሶማሌ አቦ ንቅናቄ፣ በዋቆ ጉቱ የተመራዉ የባሌ ኦሮሞ ገበሬዎች ንቅናቄ፣ የመጫና ቱላማ የልማትና መረዳጃ ማህበር፣ የወላይታ ሕዝብ ንቅናቄ፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣ ወዘተ በጥቂቱ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸዉ። አንዳንድ ጊዜ የሰከነና ፀረ ዘዉድ የትግል እንቅስቃሴ እንደነበረ የሚያሳየዉ “በ1963 በወላይታ አዉራጃ በሁምቦ ወረዳ እንደሆነዉ የተማሪዎችና ወጣት ጭሰኞች የጋራ ማህበር መስርተዉ በአንድነት ለመታገል” መነሳታቸዉን አንዳርጋቸዉ አሰግድ ከላይ በተጠቀሰዉ መፅሐፉ (ገፅ 110) ላይ ገልጿል።

የእነዚህ ህብራዊ የብሔር ንቅናቄዎች ነፀብራቅም ወደ ቀድሞዉ የቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ዩኒቬርስቲ ግቢ ዘልቆ ገብቶ ኖሮ ሕዳር 30 ቀን 1965 የተገደለዉና የብሔር ንቅናቄ ስሜት አቀጣጣይ የሆነዉ የዩኒቬርስቲዉ ተማሪ ዋለልኝ መኮንን ኢትዮጵያ ማለት የብዙ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ድምር ዉጤት እንጂ የገዥዉ ክፍል ብሔር ብቻ አለመሆኗን በአጽንኦት የገለፀበት ጊዜ ነበር። ይህ በሚገለፅበት ወቅት ላይ ከኤርትራና ትግራይ የመጡ ተማሪዎች ከኤርትራ ነፃነት ግንባር ጋር ባላቸዉ ቀዳሚ መረጃ ምክንያት እነ ዋለልኝ ላነሱት የብሔር ጥያቄ ጆሮአቸዉን ሳይሰጡ እንዳልቀረ ቢገመት በግምት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይመስልም።

ይህ ብቻም አይደለም፤ በ60ዎቹ መጀመሪያ ላይ በአዉሮፓና አሜሪካ የነበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በማህበራቸዉ አማካይነት “ስለኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መብት እስከምን” በሚለዉ ላይ ሰፊና ግልፅ ዉይይቶች ያደርጉ ነበር። በዚህም መሠረት ሐምሌ ወር 1963 በርሊን ላይ ተሰብስቦ የነበረዉ የተማሪዎቹ ማህበር የአዉሮፓ ቅርንጫፍ “የኢትዮጵያ የብሔረሰቦች መብት የማይደፈር መሆኑን፤ የራሳቸዉን ዕድል በራሳቸዉ የመወሰን መብታቸዉ እስከመገንጠል ድረስ” መሆኑ እና “መገንጠልን

የማይጨምር” እያሉ በመሀከላቸዉ ልዩነት በመፍጠር የዉሳኔ ሐሳቦች ላይ ክርክር ተደርጎ በተሰጠዉ ዉሳኔ ድምፅ መሠረትም “የብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል” እንደሚደርስ የሚያዉቀዉ የዉሳኔ ሐሳብ በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ብልጫን አግኝቶ አለፈ።” በማለት ተስፋዬ መኮንን፡ (ገፅ 97) ከላይ በተገለጸው መጽሐፉ ላይ ገልጿል።

ከወቅቱ እንቅስቃሴ ጋር አገናኝተን ብንመለከት ደግሞ ይህ ጊዜና ድርጊት ለትግራይ ወጣቶች እንቅስቃሴ መጀመር ሳቢ እንደነበር መገመት ይቻላል። በተለይም በስብሰባዉ ወቅት ሕልዉናዉን ያገኘዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ/ኢሕአፓ አመራር ዉስጥ ብዛታቸዉ ይህን ያህል ነዉ ባይባልም የትግራይ ተወላጆች እነ ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ ተስፋዬ ደበሳይ የመሳሰሉ ስለነበሩ፤ ስለብሔሮች መብት አጀንዳ ውይይት ላይ ጉልህ ሚና ሳይጫወቱ እንዳልቀረ ይገመታል። በተጨማሪም ሳቢ ምክንያቶች ናቸዉ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለዉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙ ወጣቶች አእምሮ ዉስጥ ገብቶ የነበረዉ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም አራማጆችና ከቅኝ አገዛዝ ሥር ለመላቀቅ ትግል ሲያደርጉ ለነበሩ ሕዝቦች ሲሰጥ የነበረዉ ዓለም አቀፋዊ የሞራል ድጋፍ አንዱ ሳቢ ነበር ለማለት ይቻላል። የሳቢነታቸዉ ደረጃ ይለያይ እንጂ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ለትግራይ ወጣቶች ትግራይን እንዲወክሉና <ነፃ> እንዲያወጡ ከመቋቋም ጎን ለጎን ቀዳሚና አንዱ ሳቢ ተብሎ ሊነገር የሚችለዉ የኤርትራው ሻዕቢያ ትግልና ለትግራይ ወጣቶች የሰጠዉ ሁለንትናዊ ድጋፍ ቀዳሚ ተጠቃሽ ነዉ።

ጀብሃን በፀረ ዲሞክራሲነት ወንጀሎ የተለየዉ የኢሳያስ አፈወርቂ ቡድን ኢፕአልኤፍን መስርቶ መንቀሳቀስ ሲጀምሩ፤ ኢራቅና ሶሪያ ዉስጥ የበላይነት ከነበረዉ ከበዓዝ ፓርቲ ጋር ሰፊ ግንኙነት አደረጉ። የበዓዝ ፓርቲ ደግሞ “የአረቡ ዓለም የመሬት ግዛቱን ኤርትራንም እንደሚጨምር በኦፊሴላዊዉ ካርታ ላይ አስቀምጦታል። … በዚሁ ሻዕቢያ ከደቡብ የመን ጋር በተራማጅነት ለሶሻሊዝም የቆመ በመምሰል

ግንኙነትን ይመሠርታል። በየመን አገናኝነት ከኩባ፣ ከሶቪዬትና ከምስራቅ አዉሮፓ አገሮች ጋር በተራማጅነት ስም እዉቂያን ያገኛል። በድብቅ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፍን ያገኛል። በደቡብ የመን በቻይናና በኩባ የሥልጠና ዕርዳታ ይደረግለታል። ከአረቡ ዓለም ዉስጥ ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ናቸዉ ይባሉ ከነበሩት ከሊቢያ የገንዘብ፣ የጦር መሳሪያና ምግብ፤ ከሶሪያና ከኢራቅ የጦር መሳሪያና የምግብ ዕርዳታን በማያቋርጥ ሁኔታ ያገኛል። ከፀረ ኢምፔሪያሊስትና ከፀረ ኮሎኒያሊስት እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት ይመሠርታል። የሞራል ድጋፍና አንዳንድ የፕሮፓጋንዳ መድረክ ይከፈትለታል። ይህ ሁሉ ይዳመርና ያካሂድ ከነበረዉ አሳሳች የውጪ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻው ጋር ተቀናጅቶ ተራማጅ መስሎ የመቅረብ ችሎታው በኢትዮጵያ የተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የማይናቅ ቁጥር የነበረዉ ለጋ የፖለቲካ አስተሳሰብ ደረጃ ላይ ያለውን አሳስቶ ለመማረክ ቻለ።" ይላል ተስፋዬ መኮንን በመጽሐፉ ገጽ 115-6 ላይ። ይህ የማቴሪያና ሞራል ድጋፍ ለትግራይ ወጣቶች መነሻ እርሾ ሆኖ ሳያነሳሳቸዉ እንዳልቀረ ከግምት በላይ ነዉ።

ይህ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሳበዉና በተለይም ደግሞ ለሻዕቢያ ገደብ የለሽ ድጋፍ ያሰባሰበዉ ክስተት፤ ለትግራይ ወጣቶችም እንደሚያካፋላቸው ቢያስቡና የትግራይ ሪፑቢሊክን ለመመስረት ተልመዉ የመገንጠል ንቅናቄ ቢያደርጉ አይፈርድባቸዉም። በተረፈ ደግሞ የትግራይን የመገንጠል ዓላማ አራማጆችና የሻዕቢያ መሪዎች ከትግራይ ወገኖቻቸዉ ጋር ያላቸዉ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የደም ትስስር ስላላቸዉ፤ ትግራዮቹ የሻዕቢያን ዓላማ ተከትለዉ መራመድ የውዴታ ግዴታ ቢሆንባቸዉ፤ በተለይም ደግሞ የትግራይ ወጣቶች በትግራይ ዉስጥ የሚያንቀሳቀሱት ትግል ለሻዕቢያ መመከቻ ግንብና የኢትዮጵያ ገዥዎች ጥይት ማብረጃ አንድ ተጨማሪ ቡድን ስለሚፈጥርላቸዉ፤ የኋላ ኋላ ይዘው የተነሱትን ዓላማ ማጠፋቸው ባይቀርም፤ ሻዕቢያዎቹ ወደ መገንጠል እንዲስቧቸዉ ቢያድርጉና በዚህ ስሜት ዉስጥ የገቡ የዩኒቬርስቲ ተማሪዎች ‹‹ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ/ማገብት›› ተብሎ የሚጠራዉን የፖለቲካ ቡድን፤ በተለይም

በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እዉቅና እንደመሠረቱ ነዉ ለመረዳት የምንችለዉ። ተስፋዬ መኮንን (ገፅ 145) እንደሚለዉ "ብዙዎች የማገብት አመራር አባላት ከፊል ውልደታቸዉ ከሀማሰን የነበሩና አንዳንዶቹም የአቶ ኢሳያስ የሥጋ ዘመዶች መሆናቸዉ ለግንኙነቱ መሰካት አይጫወቱ ሚና ተጫዉቷል።" ይላል። ይህ የደም ትስስር የዓላማ ትስስርን ከመፍጠሩም በላይ አንዱን የሻዕቢያ የኃይል መሪ <ወዲ ሙሴ> የተባለዉን ለማገብት ከማሰጠቱም ሌላ "… ተሀት የትግራይን ክፍለ ሀገር ለብቻዉ ነፃ የማድረግና የመቆጣጠር መብቱ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጦለታል። … የጦር መሳሪያ ሳይቋረጥ ከኋላዉ እንደሚጫንለትም ቃል ተገብቶለታል።" (ገጽ 147) ይላል ዉስጥ አዋቂዉ ተስፋዬ መኮንን።

ከዋናዉ እናት ድርጅት ማግበት ሥር በሻዕቢያ ቁጥጥር ሥር ወደሚገኘው በረሃ ተወስደዉ ሥልጠና የተሰጣቸዉ የማገብት አመራር አባላት በ1965 የድርጅታቸዉ ስም ከማግበት ወደ <ተጋድሎ ሀርነት ትግራይ/ተሀት> አዲስ ስም ተቀይሮላቸዉና የኤርትራ ጥያቄና ትግልም ፀረ ቅኝ አገዛዝ መሆኑን ተቀብለዉ፤ ሻዕቢያ ከላይ ከተጠቀሱት አካላት ያገኝ የነበረዉን ዕርዳታ በመቋደስ ለትግራይ ነፃነት የሚያደርጉት ትግል ተመርቆላቸዉ እንደተመለሱ እንረዳለን። የነፃነት ትግል የሚያካሂዱ ቡድኖች ሁሉ ለማለት ይቻላል ለትግላቸዉ መሰካት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን ግምት ዉስጥ ማስገባታቸዉ የግድ እንደሆነ ሁሉ፤ ወታደራዊ ድጋፍና ፔትሮ ዶላር ያገኘዉ ቀዳሚዉ ተሀትም ሆነ የዛሬዉ ሕወሓት የመረጡት ቦታ ወጣ ገባ የበዛበት ተራራማ ክልላቸዉ ለሽምቅ ዉጊያ ተመራጭ በመሆኑ እንደ አንዱ ሳቢ ምክንያት ተጠቅመዋል።

ለአንድ ቡድን የነፃነት ፈልሚያ ከሳቢ ምክንያቶችም ሌላ ገፊ ምክንያቶች እንደሚያመዝኑ የታወቀ ሲሆን፤ ለሕወሓትም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች በቀዳሚ ገፊ ምክንያትነት የሚጠቀሰዉ አፋኙ የአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ነዉ። አገዛዙ የተጨቆኑ ሕዝቦች አባላትን ብቻ ሳይሆን፤ በስተመጨረሻ አከባቢ የገቸዉ መደብ አባላት (ሮያል ፋሚሊ) የሆኑና

አእምሮአቸዉ ብሩህ የሆኑ እንደ ጥላሁን ግዛዉ የመሳሰሉትን ወገኖች ጭምር እንዲነሳሱ አድርጓል። ስለሆነም፤ የትግራይ ወጣቶችም ያንን አፋኝ ሥርዓት ለመዋጋት መነሳሳታቸዉ ትክክል ነበር ለማለት ይቻላል። ከዚህ ጋር ሌላዉ ለትግራይ ወጣቶች ገፊ ምክንያት ይሆናል ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለዉ በአበሾች (አማራና ትግሬ) መሀከል የሚደረግ የሥልጣን ፉክክር ቀጣይ አካል ነዉ። በጥንታዊ የሰው ልጅ እኩልነት ላይ የተመሰረተው የየጁ ሥርወ መንግስት ከ1847 ላይ በአፄ ቴዎድሮስ የጭካኔ እርምጃ ካበቃለት ወዲህ፤ አብዛኛዉን ጊዜ ሥልጣኑን የአማራዉ ወገን ይዞ የቆየ ሲሆን፤ የትግሬዉ ወገንም በተክለ ጊዮርግስ እና ዮሐንስ አራተኛ አማካይነት በተወሰኑ ጊዜያት የበላይነቱን ተረክበዉ ሲያስተዳድሩ እንደነበረ ይታወቃል። ከአማራዉ/ቅማንቴው አፄ ቴዎድሮስ ወደ ትግሬዉ ተክለጊዮርግስ፣ ከዚያም ወደ ዮሐንስ፣ እንደገና ተመልሶ ወደ አማራዉ ወገን አፄ ምኒልክ ሥልጣን ተንሸራሸሯል። ከላይ ጠቆም ለማድረግ እንደ ሞከርኩት አፄ ምኒልክ ሥልጣን መያዙ ብቻ ሳይሆን የመንግስቱን መቀመጫ ከሰሜኑ ትግራይ ወደ ደቡብ የአገሪቱ አቅጣጫ (ሸዋ) ቀይሮ ከተቀናቃኞቹ ትግሬዎች እንድርቅ አድርጓል። አፄ ኃይሌ ሥላሴ እና መንግስቱ ኃይለማሪያም በደም አማራ ባይሆኑም ከአስተዳደጋቸዉ ጀምሮ የአማራዉን ስታየል (assimilate) ተከትለዉ አገር የገዙ ስለሆነ፤ ወደ አማራዉ ስለሚቆጠርላቸዉ የትግሬዉ ወገን ወደ ሥልጣን የመመለስ ሕልም ሕወሓት እስከ መጣበትና ደርግን እስከ ገለበጠበት ጊዜ ድረስ የትግሬ ሥልጣን በ120 ዓመታት እንድርቅ ግድ ሆኖበት ነበር። ከዚህ የተነሳ ከሆነላቸዉ በአጠቃላዩ ኢትዮጵያ ላይ፤ ካልሆነም ደግሞ ትግራይን ለብቻ ነፃ አድርጎ የመግዛት አምሮታቸዉን ሊወጡ እንደሚችሉ ገምተዉ የግዛቱን ነፃ አዉጪ ድርጅት ያሰባሰቡት ነው ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ ለትግራይ ነፃነት ብረት አንስተዉ መቆማቸዉ ሳቢም ሆነ ገፊ ምክንያት ያልኩት አንዱ ይህ ሊሆን ይችላል። እንግዲህ፤ በሳቢም ሆነ ገፊ ምክንያቶች በትግራይ ኮረብታዎች መሀከል የትግራይ ነፃነት ትግልን ቋያ የለኮሰዉ ተሀት ከአፋኙ ንጉሳዊ አገዛዝ ጋር የጀመረዉ ትግል የ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት ጎርፍ ከአመጣዉ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጋርም ቀጥሎ የተጋፈጠ ነዉ።

ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ጋር ተቃርኖ ዉስጥ ገብተዉ ትግል የጀመሩት የፖለቲካ ቡድኖች፤ አብዛኛዉ ለማለት ይቻላል፤ አዲስ ከመጣዉ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጋርም በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃርኖ ዉስጥ መግባት አልነበረባቸዉም፣ እንዲያውም የደርግን ምንነት ሳያውቁ ነፍጥ በማንሳታቸው ደርግ የጨካኝነት ባህርይ እንዲላበስ አድርገዋል ብለው የሚኮንኑ ወገኖች አሉ። ነገር ግን፤ ተሀትን ጨምሮ ሌሎችም በዚያ ሁኔታ ዉስጥ እንዲገቡ ያስገደዳቸዉ በኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ዉስጥ የነበሩት ገፊ ምክንያቶች በደርግም በመቀጠላቸዉና በተለይም ደርግ ንጉሱን ከሥልጣን ከማዉረዱ በፊት ጀምሮ በይበልጥም ንጉሱ ከሥልጣን የወረደ ዕለት ያስነገረዉ አዋጅ አገሪቱን ከጨለማ ወደ ጨለማ ያሸጋገረ ነዉ ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም፤ በደርጉ መግለጫ መሠረት የተቃዉሞ ሰልፍ የሚያደርጉ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጡና የሚያስተባብሩ ወገኖች ሁሉ እርምጃ እንደሚወሰድባቸዉ በማስጠንቀቁ፤ የአገሪቱ ዜጎች ሕይወታቸዉን ጨምረዉ ሲታገሉለት የቆዩት የዲሞክራሲ እና የብሔር ብሔረሰቦች የመብት ጥያቄ ከደጡ ወደ ማጡ የገባበት ጊዜ ነበር። በአጭሩ ደርግ የፖለቲካ ተቃዉሞን ወይም የሐሳብ ልዩነትን ለማስተናገድ የሚያበቃ ዝግጅትም ሆነ ብቃት ስላልአልነበረዉ ተሀቶች ብረት አንስተዉ ደርግን መዋጋት መጀመራቸዉ ተገቢ ነበር።

በ1965 በረሃ የገባዉ ተሀትም ሆነ በ1967 የደርግን የዕድገት በሕብረት የዕዉቀትና የሥራ ዘመቻ ረግጦ ወደ ትግራይ ኮረብታዎች የገባዉ ሕወሓት ከአራት አካላት ጋር ተዋግቷል። አንድም የሻዕቢያን ዓላማ ለማስፈጸም ከጀብሃ ጋር፣ ሁለተኛም የራሱን የትግራይ የነፃነት ትግል እዉን ለማድረግ ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጋር፣ ሦስተኛ አሲምባ ሥር መሽጎ በሁለት ፍጹም ተፃራሪ በሆኑ አቋሞች ማለትም በኤርትራ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መዉጣትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት እታገላለሁ ከሚለዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ እና ከኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት ጋር ነበር። በተለይ ሕወሓት ከኢሕአፓ ጋር ያደረገዉ ጦርነት ደም አፋሳሽ ከመሆኑም በላይ ሕወሓት ከኃይሌ

ሥላሴ መንግስት ጋር የተዋጋዉና በደርግም የቀጠለበት ምክንያት ማንንም ኢትዮጵያዊ የማያሳትፍ በትክክልም ለትግራይ ነፃነት ብቻ መሆኑ በግልፅ ያሳብቅበት ነበር። ምንም እንኳን የሕወሓት ትግል አገር አቀፋዊ መልክ እንዲኖረዉ ተብሎ በቡድንም ሆነ በተናጠል የተያዙ ምርኮኞችን አደራጅቶ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር/ኢሕአዴግን ቢያቋቁምም ዲሞክራሲያዊነት የሌለዉ የሕወሓት ዓላማ በ2012 የራሳቸውን ክንፍ ይዘው ወደ መቀሌ እስከ አፈገፈጉ ድረስ የነፃ አውጪነት ባህርያቸው አልተላቀቃቸዉም።

ሕወሓት ኢዲህንን የወጋዉ የንጉሱ ርዝራዦች በመሆናቸዉ፣ ከጀብሃ ጋር የተዋጉት የሻዕቢያን የበላይነት ለማረጋገጥና ከኢሕአፓ ጋር የተዋጋዉ ደግሞ ኢሕአፓ ሕብረ ብሔራዊነትን አንግቦ ኢትዮጵያን ማዕከል አድርጎ ስለተንቀሳቀሰና ውሎ አድሮም ኢሕአፓ በለስ ቀንቶት ሸገር ቢገባ ተመልሶ ለተሀት/ሕወሓት ትግራይን ከኢትዮጵያ ማስገንጠልና ነፃ አገር የመሆን መብት ላይ ሠላም እንደማይሰጠዉ በመገንዘቡ ነዉ። ተሀት ደርግን ወግቶ ትግራይን ነፃ ከአወጣ በኋላ እመራበታለሁ ያለዉ መርህ የአልባኒያዉ ዓይነት የሶሻሊስት ማህበረሰብ፤ ለዚያዉም ከካፒታሊስቱም ሆነ ሶሻሊስቱ ጎራ ምንም ዓይነት ድጋፍ የማይፈልግና "ራስን መቻል" በሚለዉ የኢንቨር ሆጃ ዓይነት ሶሻሊዝም ያምን እንደነበር ይታወቃል። የአልባኒያዉ ዓይነት ሶሻሊስት ማህበረሰብ ግንባታ ማርሹ የቱ ጋ እንደተቀየረበት የማይታወቀዉ ሕወሓት፤ ግንቦት ወር 1983 የኢትዮጵያን መናገሻ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር የሚከተሉት ሌሎች ዋና ዋና ገፊና ሳቢ ምክንያቶች አግዘውታል።

የመጀመሪያዉ ሳቢ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ስልት ነዉ። ከብዙ ኢትዮጵያዊያን ጋር ደም የተቃባዉን የደርግ አስተዳደርን ለመጣል ሕዝቡ ‹ዝምታ› የሚባልን የትግል ስልት መርጧል። ዝምታ የሚባለዉ የትግል ስልት ወጤታማ ለመሆን ረጅም ጊዜ ወስዶ የሚያጎብጥ ስለሆነና ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ቢሆንም፤ ኢሠፓ ተመሠረተ ዝም ነዉ፤ ሕገ መንግስት ቆመላችሁ ዝም ነዉ፤ የኢሕዲሪ መንግስት ተመሠረተላችሁ

አሁንም ዝም ነዉ፤ ሻዕቢያና ወያኔ አገር ቆረሱ/አስቆረሱ ዝም ነዉ። በወጣትነቴ ጊዜ ያገር ቤት አዋቂዎች የሚነገሩን አስተማሪ ተረት ነበረ። “ሕዝብ ቢወድቅብህ ይሻላል ወይስ ተራራ ቢወድቅብህ” የሚል ሲጠየቅ ሞኝ የሆነ ሰዉ ሕዝብ ቢወድቅብኝ ይሻላል ሲል ብልህ ግን ተራራ ቢወድቅብኝ ይሻላል ብሎ ይመልሳል። ለምን ተብለዉ ሁለቱም ምክንያታቸዉን ቢጠየቁ ሞኙ ሕዝብ አይወድቅብኝም፤ ከወደቀብኝም ደግም ሲበቃዉ ይነሳል ሲል ብልሁ ተራራ ቢወድቅብኝ ሕዝብ ያነሳልኛል፤ ሕዝብ ቢወድቅብኝ ግን ማን ያነሳልኛል ብሎ ያብራራል። በርግጥም በአገራችን ባህል መሠረት ሕዝብ የወደቀበት ሰዉ የሚያነሳለትም ሆነ የሚነሳለት ባለመኖሩ ደርግን ሕዝብ በዝምታ ወደቀበትና የሚያነሳዉም ሆነ የሚያነሳለት ጠፍቶ ወደቀ። አጭርና ግልፅ ነዉና ሊማርበት ዝግጁ የሆነ ሰዉ ካለ ጥሩ መማሪያ ነዉ። ሌላዉ ቀርቶ ከላይ እንዳስቀምጥኩት በኢሠፓ ድርጅታዊ ሥራ የተሰላቸዉ ካድሬ ራሱ ደርግን ዞር ብሎ ለማየት ከመጠየፉም በላይ፤ እነሱም በዝምታ የደርግን መውደቂያ ቀን በጉጉት ከሚጠብቁት ግንባር ቀደም እንደነበሩ የዓይን እማኝ ነኝ።

ሁለተኛዉ ሕወሓትን የቀናዉ በለስ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሶሻሊዝም እንደ ዋና ሥርአት መዉደቅ ነዉ። ሶሻሊዝም እንደ ሥርዓት ሲወድቅ ዋልታና ማገር የነበረችዉ ሶቭዬት ሕብረት ሪፑብሊኮችም ተበተኑ። የደርግ የመሳሪያ ልመናም ሆነ ሸመታ ገበያ ተዘጋ። ምዕራባዊያን በተለይም ዩኤስኤ ደርግን ሲገዘግዙ የቤት ሥራቸዉን የሚቀበል ሰዉ ወይም ኃይል ፍለጋ ሂደት ዉስጥ ሕወሓት ዝግጁ ሆኖ ተገኘላቸዉ። ፖል ሄንዝና ሌሎችም የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ሕወሓትን ለማዘጋጀት ሲሉ መኖሪያቸዉን ሱዳንና ሱማሌ ከተሞችና የኤርትራና የትግራይ በረሃዎች አደረጉ። የሕወሓቱ መለስ ዜናዊ እና አሜሪካዊዉ ፖል ቢ ሄንዝ ኤፕሪል 3 እና 5፣ 1990 እንደቅድም ተከተላቸዉ ጠዋትና ከሰዓት በኋላ እራትን ጨምሮ ተከታትለዉ በአደረጉት ፍጥምጥም የሕወሓቱን መለስ ዜናዊ የአልባኒያዉን ዓይነት ሶሻሊዝም አስጥለዉ ወደ አዲስ አበባ የሚያደረገዉን ግስጋሴ አሳመሩለት።

ሦስተኛዉና ሕወሓትን የቀናዉ በለስ የደርግ መንግስት በጎረቤት አገሮች ዘንድ ቅቡልነት ማጣት ነዉ። በምስራቁ የአገሪቱ ክፍል ከሶማሊያ መንግስት ጋር የተዋጋዉ ደርግ ከደረሰበት የምጣኔ ሀብት ድቀት ሳያገግም፤ ሱዳን ምናልባት ወደፊት በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሚቋቋመዉ መንግስት የሚታገኘዉ መሬትና ገበያ እያጓጓት ሊሆን ይችላል፤ አንዳርጋቸዉ አሰግድ እንደገለጸዉ "ሱዳን ምድርና ድንበሯን [ለተቃዋሚዎች] እንዲጠቀሙበት ፈቀደችላቸዉ።" (ገጽ 270) ላለፉትም ሆነ ለሚመጡት ሁሉ ትምህርት ሊሆን የሚችል ነዉና አንድ ተቃዋሚ ኃይል መዉጫና መግቢያ (inlet and outlet) ካገኘ ቀሪዉን ሥራ መስራት ብዙም አይገደዉምና ሕወሓትም ሱዳን የለገሠችዉን ይህንን ዕድል ሰፋ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

አራተኛዉና ሕወሓትን በለስ የቀናዉ የውጪ ዕርዳታና ድጋፍ ማግኘት ነው። በተለይም ምዕራባዊያን አገሮች የሶሻሊዝምን መስፋፋትን ከገቱ (deter/contain) በኋላ ሊያሳስባቸዉ የሚችለዉ የተጽዕኖ አድማሳቸዉን (sphere of influence) ማስፋትና የሚቀናቀናቸዉና በተለይም እያቆጠቆጠ የመጣዉን የአሸባሪነት ምልክቶችን ለመጫን በራሳቸዉ አምሳያ የሚቀርጹት መንግስት ስለሚያስፈልጋቸዉ፤ ሕወሓትን አግኝተዋል። በዓለም ከሁሉም የተሻለ ነዉ የሚባለዉ የአሜሪካ ዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት አጠባበቅ እሴቶች በደርግ መንግስት በኢትዮጵያ ሊስፋፉ ባለመቻላቸዉ፤ የደርግ መንግስት እንዲወድቅ ምርጫ ብቻ ሳይሆን ብልጫ ሆኖ በመገኘቱ፤ ከጦር ሜዳ ነጥብ ጣቢያ ጀምሮ ፖል ሄንዝን (Paul B. Henz) የመሳሰሉት አማካሪዎች ሱዳን ዉስጥ በማስቀመጥ የሕወሓት ሰዎችን እንዲያሰለጥኑ ተደረገ። በለስ ቀና ማለት አንዱ ይኸዉ የሰለጠነ ሕዝብና የኃያል አገር አሰልጣኝ ማግኘት ነዉ።

አምስተኛዉ የሕወሓት በለስ ሰሜን ኢትዮጵያ ዉስጥ የገባዉ የድርቅና ረሃብ አደጋ ነዉ። በተለይም ደርግ 10ኛዉን ዓመት የአብዮት በዓልና ለኢሠፖ ምስረታ ሽር ጉድ ይል በነበረበት ጊዜ የሰሜኑ ወገኖቻችን ደግሞ

በጠኔ እየረገፉ ነበር፡፡ ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለ እየተደሰኮረ የመሀል ሀገር ባለሥልጣናት ጮማ ሲቆረጡ በዉስኪ ሲራጩ፣ የሴሰኝነታቸዉ ማርኪያ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ላይ ሲራኮቱ (የጂማዎቹን የክፍለ ሀገሩን የኢሠፓ ኮሚቴ አባላት ድሪያ ምሳሌ መዉሰድ ይቻላል)፤ ልክ አፄ ኃይሌ ሥላሴ 84ኛ የልዴት በዓሉን ያከብር እንደነበረ ጊዜ ሁሉ የሰሜኑ ኢትዮጵያ ወገኖች በረሃብና በበሽታ ይረግፉ ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር ሕወሓትን በሁለት በኩል በለስ ቀናዉ ማለት ይቻላል፡፡ ደርጉ ድርቁን መከላከል በሚል ፈሊጥ የተጎዱ ሰዎችን ባሉበት ቦታ ምንም ዓይነት ዕርዳታ እንዳይደርስላቸዉ በመከላከል፤ በደንብ ወዳልተዘጋጁ የሠፈራ ቦታዎች ሲወስድ ከወላጆቻቸዉ ወደ ገበያ ወይም ሱቅ የተላኩ ልጆችን ጭምር እያስገደደና እያፈሰ በመኪና አዳጉዞ ወሰዳቸዉ፡፡  አቅሙ የቻለዉ ከመኪና ላይ እየዘለለ በመዉረድ የሕወሓትን ሠራዊት በሰዉ ኃይል ሞላዉ፡፡ በለስ ቀና አይባልም ታዲያ?

ሌላዉ የሕወሓት ሰዎች በተራበዉ ወገናቸዉ ስም ከነቦብ ገልዶፍ ጋር በለመኑት ገንዘብ የጦር መሳሪያ ጥይት መግዛታቸዉ ነዉ፡፡ “እግዚአብሔር ያንዱን ጉሮሮ ሲዘጋ የሌላዉን ይከፍታል” ይባል የለ፤ በለስ ሲቀና እንዴዚህም አድርጎ ነዉ፡፡ የትግራይን ሕዝብ ጉሮሮ የዘጋው ድርቅ የሕወሓት ሰዎችን ጉሮሮ ከፍቷል፡፡ በትግራይ ሕዝብ ስም ከነ ቦብ ገልዶፍ ከሰበሰቡት ገንዘብ ጭምር የቡድኑን ጥቂት አባላትና የድርጅቱን የኤኮኖሚ የበላይነት አጎናጽፏል፡፡ በዉጭ ኃይሎች ገደብ የለሽ ዕርዳታ የአራት ኪሎውን  ቤተ መንግስት ከተቆጣጠሩም በኋላ በተገኘው ተጨማሪ ገንዘብ ማንም ቀና ብሎ እንዳያያቸው፤ ቢያያቸዉ ደግሞ እንዲተኮስባቸዉ ማዘዝ የሚችሉ የሕወሓት የንግድ ኢምፓየር ገንብተዋል፡፡

ስድስተኛዉ በለስ ሕወሓትን የቀናው የኢትዮጵያ ሠራዊት፤ በኋላ ላይ የደርግ ሠራዊት፣ የውጊያ ብቃት ማነስና በተለይም በጦር ሜዳም ሆነ በሕብረተሰቡ መሀከል የሚያሳየዉ የሥነ ሥርዓትና ሥነ ምግባር ጉድለት ነዉ፡፡ ከጦር ሜዳ ጀምሮ የሲቪል አስተዳደሩ ሳይቀር፤ ሁሉ ሥራ

በወታደሮች ተያዘ። ሁሉም ሥራ የጦር ሜዳዉን ጨምሮ የሚመራዉ በዕቅድ ሳይሆን በዘመቻ ሆነ። በወታደሩ ዉስጥ የፖለቲካ ኃላፊ ሆኖ የተመደበ ሰዉ፤ አስር አለቃዉ ማለት ነዉ የጦር መሪዉን ጀኔራል ማዘዝ ብቻ ሳይሆን ማዕረጉን አስገፍፎ እስከ ማስገደል የቻለበት ጊዜ ሆነ። ጠላት ነዉ የሚሉት የሚወጋቸዉ ሳያንስና ለዜጎች የሚገባዉ አክብሮት መስጠት ቀርቶ፤ እንደሰዉ መቁጠሩም ቀረ። ልክ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ዉስጥ እንደሚደመጠዉና የመንግስት መሪዎች አንድም በመፈንቅለ መንግስት ወይም በሽሚቅ ዉጊያ ሥልጣን ሲይዙ የራሳቸዉን ወታደር ወይም የብሔሩ ወይም የጎሳዉን ሰዉ እንደሚያስቀምጡ ሁሉ ‹‹ታማኙ፣ ኮሚኒስቱ፣ ሐቀኛዉ፣ ምናምንተዉ ጓድ መንግስቱ ኃይለማሪያም የሚል ብቻ የሚሾምበት፣ የሚሸለምበት ጊዜና ቦታ ሆኖ አረፈዉ። ሹመትና ሽልማት አለ ከተባለ ለመንግስቱና ለፖለቲካ ሥርዓቱ ታማኝ የሆነ ሰዉ እንጂ ለሕዝብ የሚገባዉ ታማኝነትና አክብሮት እንጦርጦስ ወረደ። ይህ ሁሉ መመሰቃቀል እያለ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ይሉ ዓይነት በ1981 የከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ስብስብ የሆነዉ ክፍል ያልተሳካ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ አደረገ። ከዚህ ጊዜ በኋላ የደርግን ዉድቀት ወያኔ ራሱ፤ ለራሱ ዝግጅት ሲል እየቆጠበ አከናወነዉ እንጂ ደርግ እንደ መንግስት፣ ኢሠፓም እንደ ፓርቲ ያበቃላቸዉ ጊዜ ነበር።

መንግስቱ ኃይለማርያምና ፓርቲዉ በሕዝብ ሳይመረጡ በሕዝብ የተመረጡ መንግስት አድርገዉ ራሳቸዉን በመካብ በሕዝብ መተፋታቸዉን በጣም በጣም ዘገይተዉ ነቁ ሳይሆን ባነኑ። የትም ሆነ የት ገዥዉን ክፍል ብቻ አስበልጦ ሕዝብን የሚያሳንስ የፖለቲካ ሥርዓት ጊዜ ይዉሰድ እንጂ አምባገነኑም ሠራዊቱም ተያይዘዉ እንደሚነጎዱ ከደርግ መማር የማይችል ቢኖር ለመማር ያልተፈጠረ ብቻ ነዉ። ይኼኛዉ በለስ ሕወሓትን ደህና አድርጎ ቀንቶታል። ምናልባት የማይዘለል ሐቅ ቢኖር የጦርነቱ ዕድሜ እየተራዘመ መሄዱና ከተቃዋሚዎችና ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ለሚቀርበዉ የመወያየትና የመግባባት ጥያቄ ጆሮ የሚሰጥ የሰከነ ፖለቲካዊ መፍትኼ መስጠት የሚችል አመራር

ባለመኖሩ፤ በወታደሩ ዘንድ የመሰላቸትና የመዳከም ምልክቶች በጉልህ ታይቷል። በወቅቱ የነበረው የሀገሪቱ ኤኮኖሚም አጠቃላይ የፖለቲካ ቀውሱን ሊሸከም የሚችል ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም፤ ዳር ድንበር እንዲከላከል የተላከው ወታደር የውሃ ኮዳው ሳይቀር እያስረከበ ወይም እየጣለ ወደ መሃል አገር ጎረፈ። አዛዦቻቸዉ ግን በኢህዲን፣ በኦህዴድ፣ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ እየተደራጁ በፈረሙት የሽያጭ ውል መሠረት የየራሳቸዉን ኑሮ ማመቻቸት ተያያዙ። ተራው ወታደር የጦርነት እሳት ውስጥ እየተማገደ መኮንኖቹ እዚያው እያሉም ቢሆን ከራሳቸውም ተርፈው የወታደሩን ስንቅ አሳልፎ በመሸጥና በመስጠት የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ጭምር ሚሊዮነር ሲያደርጉ ታይተዋል። አማፂያኑ ደግሞ አንድም እየተሽረሸረ በሚሄደው የሶሻሊስት ካምፕ እና ስፍር ቁጥር በሌለው የምዕራባዊያን ቁሳዊ እና ሰብአዊ ድጋፍ እየታገዙ ርዕሰ ብሔሩ መንግስቱ የሚኖሩበትን ከተማ እና ቤተመንግስት ከበባ ቀለበት ውስጥ እያስገባ ሲሄድ፤ የፓርቲው ሊቀ መንበር፣ የመንግስት ፕሬዚዳንት፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ወደ ዚምባቢዊ ተሰደደ።

ሰባተኛዉ በለስ የሕወሓት የሰዉ ኃይል አጠቃቀም ነዉ። በመጀመሪያ እዉስጡ የተከሰተዉን ግጭት መፍታት ያልቻለዉንና የእነ ተስፋዬ መኮንን ቡድን አስመራ፣ ከአስመራም አዲስ አበባ ሲገባ፤ በብርሃነ መስቀል ረዳ ይመራ የነበረዉና የኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት መርህን የተቀበለዉ የኢህአፓ ቡድን በወሎ አድርጎ ወደ አዲስ አበባ ሲጠጋ በገበሬ ማህበር የተመታዉና የጫካዉ የትጥቅ ትግሉ የማያዋጣ ሆኖ ሲገኝ፤ እስካሁን በማን መርህ ላይ እንደተመሰረተ የማይታወቀዉ የትጥቅ ትግሉን ወደ ከተማ በማዞሩ እየተንጠባጠበ ወደ አሲምባ የገባዉና ያለተልዕኮ፣ መሳሪያና ስንቅ የተቀመጠዉን የኢሕአፓን ጦር ሕወሓት አሳድዶ መታዉ። ኤርትራን ጨምሮ ለአንዷት ኢትዮጵያ ነፃነት እፋለማለሁ የሚለዉ የኢሕአፓ ግራ ክንፍ ተበታትኖ ሱዳንና አሜሪካን አገሮች ሲገቡ፤ የብርሃነ መስቀል ረዳን ዓላማ አንግቦ የነበረዉና በተለይም የኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት መርህ ሲያቀነቅን የነበረዉ ክንፍ

የሕወሓት ጡጫ ሲበዛበት ወደ ሰሜን ጎንደር አርማጨሆ በረሃ እና በለሳ ገብቶ የኢሕአፓን ካባ አዉልቆ <የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ኢህዲን> የሚለዉን ስም በመያዝ ለሕወሓት እጅ በመስጠት ከሰባት ዓመት ዝግጅት በኋላ አነስተኛ የደረጃ ማሻሻያ በማግኘት ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር/ኢሕአዴግ›› በመመስረት፤ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ቀላል የማይባል የሰዉ ኃይልና መሳሪያ አስገኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ሕወሓት መቼና የቱ ጋ የድርጊት መርሐ ግብሩን እንደቀየረ ባላዉቅም፤ ትግሉን ወደመሀል አገር ለማስፋፋት በቀየሰዉ ሐሳብ መሠረት ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ ጋር ለመፍጠር ያቀደዉ ወዳጅነት ስላልያዘለት ተማርከዉ በሻዕቢያና በሕወሓት ራሱ እስር ቤት የነበሩትን እንዲሁም ከኢሕአፓ የቡድን እጅ ሰጪዎች ጋር የደርግ ምርኮኛ የኦሮሞና አፋን ኦሮሞ የሚናገሩ የሌሎች ብሔሮች ምርኮኞች ካሉበት እስር ቤት በመሰብሰብ፤ ሰፊ የሕዝብ ብዛትና ሰፊ ለም መሬት ላይ የሠፈረዉን የኦሮሞ ሕዝብ ለመያዝ በአጭር ጊዜ ሥልጠና በመስጠት የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት/ኦሕዴድ የሚባለዉን ድርጅት መስርቶ ወደ ኦሮሚያ አከባቢዎች ገሰገሰ፡፡ በለስ ሲቀና በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሰዉ ኃይል ተገኝቶ ሥራ ላይ ይዉላል፡፡ ያላለለት ደግሞ እልፍ አእላፍ ሕዝብ ቢኖረዉም *(maxinoo cirrachaa)* የአሽዋ ጥቢኛ ይሆንበታል፤ ይበታተንበታል ማለት ነዉ፡፡

ስምንተኛዉ የሕወሓት በለስ ግዙፉ የአርሶ አደር ክፍል ነዉ፡፡ ደርግ የአርሶ አደሩን መደብ ከጭሰኝነት ያላቀኩት መደብ ነዉ ብሎ ሲመካበት የኖረና በእዉነትም ከኤርትራ ወሎ የገባዉን የኢሕአፓ ጦር የገደለዉን ገድሎ የእነ ብርሃነ መስቀል ረዳን ቡድን ደግሞ ማርኮ ለደርግ ያስረከበ፣ እስከ አዋሽ ድረስ የዘለቀዉን የዚያድ ባሬን ጦር ለማባረር ሦስት መቶ ሺህ ዘማች ሠራዊት ያቀረበ፣ የመሬት አዋጁን በመቃወምም ሆነ የዘዉድ አገዛዝን መልሶ ለመትከል ያሰፈሰፈዉን አኩራፊ ፊዉዳሎችን ይዞ ለደርግ ያስረከበ፣ የመኢሶን አባላት ገና እግራቸው ከሸዋ ሳይወጣ የተቆጣጠረ፣ እና የመሳሰሉትን የፈፀመዉ ይህ የገበሬ መደብ ስለሆነ ደርግ እንደ ግል ሀብቱ ቢመካበት ዉሸት የለበትም፡፡ የያነዉ ገንጣይ አስገንጣይ፤ የዛሬዉ

ባለመንግስት ፓርቲ ሕወሓት ደግሞ የአርሶ አደሩን ክፍል ማህበራዊ መሠረቴ (social base) ነዉ ብሎ ተመክቶበታል። እንደ እዉነቱ ከሆነ ግን አርሶ አደሩ ማህበራዊ መሠረቱ ሳይሆን የማይነጥፍ የገቢ ምንጩ ሆኖ እያገለገለ መሆኑ የንግድ ድርጅቶቹ ሳይቀሩ ይመሰክራሉ። የደርግ ሥርአት ምሬት ለአርሶ አደሩ አንገቱ ድረስ ደርሶ ቋቅ ብሎበት የነበረዉ አርሶ አደር፤ በመጀመሪያዉ አርሶ አደሩ እንደ ዋስትናዉ የሚቆጥረዉን ልጁን በዉትድርናና በሚሊሻነት ወስዶ ማለቂያ በሌለዉ ጦርነት ዉስጥ ማግዶበታል። በርግጥም ወላጆች ያጡት የሚጦራቸዉን ወጣት ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ወላጅ ከአቅሙ በላይ በሆነ ሁኔታ የልጅ ልጅ ለማሳደግም ተገድዶ ስለነበረ፤ የምሬቱ መጠን መለኪያ አልነበረዉም ቢባል የተጋነነ አይደለም። ሌላዉ የአርሶ አደሩ ችግር ዓመቱን ሙሉ ክረምት ከዝናብና ከብርድ፤ በጋ ከሐሩር ጋር ታግሎ ያመረተዉን እህል በትንሽ ዋጋ ለመንግስታዊ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት እንዲያስረከብ መገደዱና፤ በዉጤቱም የአርሶ አደሩ ኑሮና ሰዉነት እየቀጨጨ ሲሄድ የመንግስት ባለሥልጣናት በትንሽ ገንዘብ እህል መሸመት አስቻላቸዉ። ሦስተኛ የአርሶ አደር ችግር ማለቂያ የሌለዉ መዋጮ መክፈል ነዉ። ዓመታዊ ግብርን ሳይጨምር የእናት ሀገር ጥሪ፣ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ፣ የድርቅ መዋጮ፣ ለኢሠፓ ምስረታ፣ ወዘተ እየተባለ አፍንጫዉን ተሰንጎ እንዲከፍል ይደረጋል። ዛሬ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ እንደሆነዉ ዓይነት ማለት ነዉ። እነዚህ ሁሉ ተደማምረዉ አርሶ አደሩን ግራ ስላጋቡት ደርግን ልናወርድልህ ነዉ ላለዉ ሕወሓት፤ ይህንን ከፈጸምክልኝማ እኔ ከምቀምሰዉ ቀምሰህ፣ በደጄም በሠላም ማለፍ ትችላለህ ብሎ አስተናገደዉ። ‹‹ሺህም ቢታለብ ያዉ በገሌ ነዉ›› እንዳለችዉ ውሮ ሆነበት እንጂ አርሶ አደሩ ያለገደብ የሕወሓት በለስ እንድቀና ሆኖ አገልግሏል። ሁሉም በለሶችና ሌሎችም ተጨማምረዉ ግንቦት ወር 1983 መንግስቱ ኃይለማሪያምን በስደት ወደ ሐራሬ፤ ሕወሓትንና መለስ ዜናዊን ለፊንፊኔዉ የምኒልክ ቤተመንግስት ያበቁ ናቸዉ።

ሕወሓት ደርግን ጥሎ አዲስ አበባ ሲገባ፤ በኔ እይታ ማለት ነዉ፤ አራት

ኪሎ፣ አምስት ኪሎና ስድስት ኪሎ አከባቢ በአነስተኛ ቁጥር የተቃውሞ እንቅስቃሰ ካደረጉት ዉስን ሰዎች በስተቀር የጠበቀዉ ብዙም ተቃዉሞ አልነበረም። ምክንያቱ ደግሞ ቀላል ነዉ። በሃያ አንደኛዉ መቶ ዓመት ላይ ደርግን የገለበጠው ሕወሓት በራሱ ልክ ያሰፋዉን ጥብቆ አጥልቆና የዲሞክራሲ ካባ ደርቦ ከደርግ ባነሰ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ይቀርባል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ስለነበረ ነዉ። ከደርግ ያነሰ ኃላፊነት የሚሰማዉ መንግስት አይመጣም የሚል ግምት የነበራቸዉ ዜጎች ቀላል ቁጥር አልነበራቸዉም ማለት ነዉ። ነገር ግን ከደርግ ወይም ከኢሠፓ አባላት ያልሆኑ አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍል ሕወሓት/ኢህአዴግ አዲስ አበባ እንደገባ አደባባይ ወጥተዉ የተቃዉሞ ድምፅ ያሰሙትን ግለሰቦች ወይም ቡድኖችን ዛሬ ላይ ሆኖ ሲታዩ አድናቆት የሚቸራቸዉ ናቸዉ። ምክንያቱም፤ ሕወሓትም ልክ እንደ ደርግ የራሱን አምባገነንነት የሚገነባ እንጂ ዲሞክራሲያዊና የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነትን እንደማያራምድ በግልፅ ቋንቋ ገና ከጅምሩ መናገር በመቻላቸዉ ነዉ። ሕወሓት/ኢህአዴግ ከመከፈሉ በፊት እና ሥልጣን ላይ በቆየበት ዓመታት ውስጥ ለማረጋገጥ የተቻለዉም በርግጥም ሕወሓት ታላቅ ወንድሙ ደርግን ተመስሎ ምኒልክ ቤተመንግስት የገባ መሆኑ በመረዳታቸው ነዉ። እሱ ብቻም አይደለም ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ ከሕወሓት ተነጥሎ በተሃድሶ ስም የኢህአዴግ አዲስ አበባ ቀሪ ክፍል የብልፅግና ፓርቲም ከስትራቴጂ አንፃር ሲታይ አንድም ደርግን ሲቀጥልም ሕወሓትን ከመምሰል አላመለጠም። ምክንያቱም፤ ተፎካካሪ ሊሆኑ የሚችሉ ፓርቲዎችን (የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ እና የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን መጥቀስ ይቻላል) አንድም የደርግን የአንድ ፓርቲ አመራር ሲመርጥ፤ ሲቀጥልም የሕወሓት/ኢህአዴግን አውራ ፓርቲነት አመራር በማራመድና የዴሞክራሲ ጭንብል በመልበስ የይስሙላ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ አካሄድኩ በማለት ጊዜ እና ጉልበት ሲጨርስ ከርሟልና ነዉ።

**የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ፡-** በ1960ዎቹ በነዳጅ ዋጋ መናር፣ በስዊስ ቦይ መዘጋትና የኑሮ መናር፣ በአረቦችና እስራኤል ጦርነት፤ ወዘተ ምክንያት የተከሰተዉ የኤኮኖሚ ቀዉስ፤ እንዲሁም በሰሜኑ የኢትዮጵያ

ግዛቶች የተከሰተዉ የድርቅና የረሃብ አደጋ፣ እንዲሁም በዉስጥ አስተዳደር መዳደል፣ ሙሰኝነት እና የሀገሪቱ ዜጎች የዕዉቀት ዕድገት እየቀጨጨ መሄድ ተከማምረዉ ያረጀዉንና ያፈጀውን የኃይሌ ሥላሴ መንግሰት ሊሸከመዉ ከሚችለዉ በላይ ስለሆኑበት የሥርአቱ ግብአተ መሬት ሆነ፡፡ በአገር ዉስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች፤ ማለትም ሰለሞናዊም ሥርዌ መንግስትም ሆነ ሌላ ንጉሳዊ አገዛዝ ለአንዴና መጨረሻ ጊዜ ማክተሙና ዋነኛ የፊዉዳላዊ ሥልተ ምርት ግንኙነት መሠረት የሆነዉ የመሬት ስሪት መቀየሩ ናቸዉ፡፡

ነገር ግን ተንሰራፍቶ የቆየዉን የኃይሌ ሥላሴ መንግስት በሕዝባዊ ኃላፊነት ለመተካት የተዘጋጀ የፖለቲካ ኃይል ባለመኖሩና ተበታትነዉ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የገበሬ፣ የወታደሩና የወጣት ተማሪ ንቅናቄዎች የንጉሱ ዘዉድ አመራር እንዲወድቅ ከመመኘት ባሻገር ያንን ክፍተት የሚሞላ ኃይል ማዘጋጀት ቀርቶ አስፈላጊነቱን እንኳን በቅጡ የተረዱት ገና ዘገይተዉ፤ ለዚያዉም አዉሮፓ ዉስጥ መሠረታቸዉን በጣሉት በመኢሶንና በኢሕአፓ አማካይነት እንደነበሩ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የፊዉዳሉ ላዕላይ መዋቅር መግዛት ሲያቅተዉና መሠረታዊ አመራር መስጠት የሚችል የተዘጋጀ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ፤ የንጉሱ ጋሻ ጃግሬ ሆኖ ሲያገለግል የነበረዉና ከተለያዩ ወታደራዊ ክፍሎች የተዉጣጣው መለዮ ለባሽ ኃይል ሥልጣኑን ተቆናጠጠ፡፡

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የመሬት አዋጅ የመሳሰሉ ሕዝባዊነት ገፅታ የተላበሱ እርምጃዎችን ቢወስድም፤ ተጠቃሚዉ ሕብረተሰብ ነፃነት እንዲኖረዉና ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑን እንዲያስረግጥ ዕድሉን ስለነፈገ፤ ደርግ ንጉሱን አውርዶ የተረከበዉ አልጋዉን ብቻ ሳይሆን የፀረ ዲሞክራሲያዊነቱንም ባህርዩንም ጭምር የወረሰ ስለሆነ፤ የሥልጣን ዕድሜዉን አደላድሏል፡፡ ይህንን የሚቃወሙ ብሔራዊና ሕብረ ብሔራዊ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ተፈጥረዉ ስለተፋለሙት ከአስራ ሰባት ዓመታት ደም አፋሳሽ ጦርነቶች በኋላ በግንቦት 1983 ከውህዳኑ

የትግራይ ክልል በተንቀሳቀሰዉ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት መሪነትና በኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ኢህዲን እና ኦሮሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት/ኦህዴድ አሸናፊነት ከሥልጣን ተወገደ። ስለደርግ ሲወሳ ስለመዉደቁ ሳይሆን ስለአወዳደቁ በተለይም ምንም ዓይነት የሕዝብ ዉክልና ሳይኖረዉ ሥልጣን የያዘዉ በታሪክ በተጣለብኝ አደራ ነዉ እያለ አስራ ሰባት የግፍ ዓመታትን ከአስቆጠረ በኋላ፤ ምንም ዓይነት የሕዝብ ፍቅር ሳያተርፍ በጠመንጃ ከቆየበት ሥልጣን በጠመንጃ መወገዱ ብቻ ነዉ።

## ምዕራፍ ሦስት፡ ከሕወሓት/ኢህአዴግ እስከ ኢፌዲሪ መንግስት ምስረታ እና የፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት ተግዳሮቶች

በአፍሪካ ያንዱ ጎሳ አባላት ፍትህ ተዛባ ብለው ሥልጣን ላይ ባለዉ አካል ላይ ከአኮረፉ አንዱ የጎበዝ አለቃ የመሰለ የጎሳ አባላቱን አሰባስቦ ጥቂት አሮጌ ጠመንጃዎችን በመያዝ ዲሞክራሲና ፍትህን ለማምጣት ጫካ ገብቶ በለስ ቀንቶት ሥልጣን ከተቆናጠጠ፤ እሱ ራሱ ደግሞ በተራዉ ቤተ ዘመዶቹንና የጎሳ አባላቱን በዙሪያዉ አሰባስቦ ቀደምቶቹ ሲያደርጉ የነበረውን ሁሉ በማድረግ ወይም ትንሽ በማሻሻል ወይም የባሰ በማበላሸት ፍትህ ማዛባቱ ላይ ይሰማራል። በቀደመው መንግስት ተዛባ የተባለዉ ፍትህና የዲሞክራሲ እጦትም፤ ያ ቡድን ሥልጣን እስከሚይዝ ድረስ ብቻ ይራገብና ከዚያ በኋላ ሕዝቡም ዲሞክራሲዉም አስተዋሽ ሳይኖራቸዉ የግፍ አገዛዝና የሕዝብ ጉስቁልና ይቀጥላል። በአጭሩ በሕወሓትም የሆነዉ ይኸዉ ነዉ። የሕዝብ ነፃ አውጪ ነኝ ያለው ሕወሓት በለስ ቀንቶት የአዲስ አበባውን ሥልጣን ሲቆናጠጥ ቁጥር አንድ የሕዝብ ጨፍጫፊ ሆኖ አረፈዉ። የፓርቲ ፖለቲካ ዕድገትን የማዳፈን እንቅስቃሴውን ስልታዊ በሆነ ሁኔታ ከደርግ ትንሽ በማሻሻል ቀጠለ።

ሕወሓት/ኢህአዴግ በግንቦት ወር 1983 አምባገነናዊዉን ወታደራዊ ደርግን አስወግዶ ሥልጣን ከተቆናጠጠ ከሁለት ወራት ቆይታ በኋላ በትግሉ ዉስጥ (ከኦነግ በስተቀር) ምንም ሚና ያልነበራቸዉን የተለያዩ የብሔርና ሕብረ ብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም ተቋማት የተሳተፉበት የሠላም ኮንፈረንስ በመጥራት 87 መቀመጫዎች ያሉት የሽግግር ጊዜ መንግስት አቋቋመ። የሽግግር ጊዜ መንግስቱ ምክር ቤትና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነበሩት። የሽግግር ጊዜ መንግስት ይቋቋም እንጂ ውጤቱ ወደ ተሻለ ነገር የማያመሩ የተለያዩና የሚጋጩ ሐሳቦች ብቻ ሳይሆን ተቃቃሪ የሆኑ አንቀጾች፤ ለምሳሌም በዴሞክራሲ መብቶች በሚለዉ ዉስጥ የእምነት፣ ሐሳብን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ በሰላም የመሰብሰብና የመቃወም ነፃነት አለዉ፤ ከሚለዉ በማስከተል የሌሎችን ሕጋዊ መብቶች እስካልተጋፋ የሚለዉን በማስቀመጡ በአንድ ራስ ሁለት

ምላስ እንደሚሉት ዓይነት ሆኖበታል። የሽግግር ቻርተሩ፤ ፖለቲካን ለሚረዳ ሰዉ፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሰኔ 21/1966 ከሰጠዉ መብት ገዳቢ መግለጫ ጋር የሚመሳሰልና ከመጀመሪያዉ ሥጋት ፈጣሪ መሆኑ ሊጠቀስ የሚችል ነዉ። ምክንያቱም፤ እንዲህ ካልሆነ የሚባለዉ ቅድመ ሁኔታ ራሱ ጤናማ እና ነፃ የፓርቲ ፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይካሄድ ቅድመ ግዴታዊ ሕግ ወይም መመሪያ ብጤ የማስቀመጥ ያህል ሆኖ ስለሚቆጠር ነዉ። የሌሎችን መብት እስካልገደበ ድረስ የሚለው ቃል "አልበላህምን ምን አመጣው" እንደሚባለው ዓይነት ሁኔታ ማለት ይሆናልና ነው። ይህ ደግሞ ያለምንም ማጋነን ሕወሓት ልክ እንደ ደርግ ከራሱ ፓርቲ ውጪ የማንንም ተቃራኒ ወይም ተቃዋሚ ሐሳብ ወይም አመለካከት ላለማስተናገድ የወሰነበት ሁኔታ ዉስጥ እንደነበረ አመላካች ነው።

ሕወሓት ውሎ አድሮ የራሱን ችግር ይዞ ይከሰት እንጂ በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ ሥር ሰዶ የቆየዉን የብሔር ጥያቄ በፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ሥርአት ለመፍታት ያደረገዉ ጅምር እንደ ሐሳብነቱ ለመላው ሕዝቦች ለሁሉም ባይሆን ስለብሔሮች ችግሮች ሲያስቡ ለኖሩት የሚደገፍ ነዉ። የሽግግሩ ቻርተር ክፍል አንድ አንቀፅ ሁለት እንደሚለዉ "የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተረጋግጧል" የሚለውን ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በአንድ ድምፅ የተስማሙበት ነበር ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ባይቻልም በጎ በጎ የሚሸቱ አንቀፆች ነበሩበት። እንግዲህ ደርግም ሆነ ቀደምት አገዛዞች አንዳቸዉም ዲሞክራሲያዊ ባህርይ ያልተላበሱ ስለሆነና እንዲያውም ደርግ የተቋቋመ ሕግ ሳይኖረዉ በድንጋጌ (decree) ብቻ እየገዛ በቆየበት አገር ውስጥ፤ የሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን መያዝና የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማሳተፍ የሽግግር ጊዜ መንግስት ማቋቋም፤ ለተወሰነዉ የሕብረተሰብ ክፍል የጭቆና አገዛዝ የማክተሚያ ምልክት ተደርጎ ቢወሰድ ተሳሳትኩ ብሎ የሚያስቆጭ አልነበረም። ይህንን ግምት የወሰዱ ዜጎች ተሳስተዋል ማለት የማያስደፍረዉና ከአስር ዓመታት በላይ የተቋቋመ ሕግ ሳይኖረዉ በአዋጅና መግለጫ ብቻ በደርግ ሲገዛ የኖረዉ ሕዝብ፤ በሽግግር ወቅት

ቻርተር ትተዳደራለህ ሲባልና አልፎ ተርፎም፤ በዚያዉ ቻርተር ዉስጥ አገሪቱ የሚትተዳደርበትን ሕግ የሚቀርፅ ሕገ መንግስታዊ ኮሚሽን እንደሚቋቋም መገለፁ ተስፋ የሚጣልበት ዓይነት ሥርአት ይመስል ነበር፡፡

እንደተባለውም ሕገ መንግስታዊ ኮሚሽኑ በአቀረበዉ ሕገ መንግስት ውስጥ አገሪቱ በፌዴራላዊ የመንግስት ሥርአት እንደሚትተዳደርና ፌዴራላዊ ሥርአቱም በብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አሰፋፈርና ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል መባሉ፤ ከዚህ በላይም ለመግለፅ እንደተሞከረዉ ለአገሪቱ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ለአንድነቷም ጭምር አስጊ የሆነዉን የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄና ትግልን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መሻቱ ይበል የሚያሰኝ ነበር ተብሎ ቢገመት አይፈረድበትም፡፡ ነገር ግን በኋላ በዝርዝር እንደምናየዉ፤ ሲጀመርም የሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የዲሞክራሲ መዝገበ ቃላት ብቅ የሚለዉ ዲፕሎማቶችንና ዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን ለማማለል ብቻ ስለሆነ፤ ሥልጣን ላይ ለመዉጣት የሕዝብ ይሁንታ መፈለግ የሚለዉ የዲሞክራሲ መንገድ ይበልጥ ተዘጋ፡፡ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት እስካልሰረፀ ድረስ ደግሞ በሕገ መንግስት የተቀመጠዉ ፌዴራላዊ የመንግስት አስተዳደር ሥርአትም ሆነ የፓርቲ ፖለቲካ ተግባራዊ አይሆኑም ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ችግሮች አልተፈቱም፤ በኢትዮጵያዊያን መሀከል ተፈጥሮ የቆየዉ የትስስር ገመድም መላላቱና የሚፈለገው ትስስርም በተፈለገዉ ዓይነትና ፍጥነት ሊጓዝና የተፈለገዉን ዕድገት ሊያመጣ አለመቻሉ በግልፅ የሚታይ ነበር፡፡ እንኳንስ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ማጥበቅ ቀርቶ ለትስስሩ መላላት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶችንም በቅጡ አልተፈተሹም፡፡ ስለሆነም፤ የኢትዮጵያዊያን የመንታ መንገድ ጉዞ እንዲቀጥል ተገዷል፡፡ ብዙ ከበሮ የተመታለት ሕብረ ብሔር ፌዴራሊዝምም አልተሳካም፤ ያልተሳካበትን ምክንያቶች በሌሎች ቦታዎች ላይ የማነሳቸዉ ይሆናል፡፡

አጭርም ሆነ ረጅም ጊዜ ሆኖታል ተብሎ ከበሮ የሚመታለትና ደረት

የሚደለቅለት የኢትዮጵያዊያን አንድነት በርግጥም በዓለም ሕብረተሰብ ዘንድ የራሱ የሆነ አንደምታ ያለዉ ቢሆንም፤ አብዛኛዉ የአብሮነት ትስስሩ የውጪ ኃይልን ለመዉጋት ላይ የተመሠረተ የጦረኛነት ስሜት ካልሆነ በስተቀር በልማትና አንዱ የሌላዉን እሴት የማክበሩ ሂደት ላይ ወደ አልተገባና ወደ መናናቅ ያጋደለ ነበር/ነው። ይህም ሊሆን የቻለዉ ቀጥሎ ባለዉና በተለይ ገዥዎች ኃላፊነት ባለዉ ሁኔታ ፈትሸዉና ጎጂነት ያላቸውን አስተዳደር ጎጂነቱን አስረግጠዉ የእርምት እርምጃ ባለመዉሰዳቸዉ፤ ይተገበራል ተብሎ ሕገ መንግስት የተቀረጸለት ሕብረ ብሔራዊ የፌዴራል ሥርአትም ፈተና ገጥሞታል። ይህ ደግሞ መሠረታዊ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን፤ የኢትዮጵያዊያን ስብስብ ከየት ተነስቶ አሁን ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማመላከት ቀጥሎ ያሉትን ነጥቦች መመልከት ይቻላል።

ለኢትዮጵያዊያን ትስስር መላላት ችግሮች ናቸዉ ያልኩዋቸዉና ቀጥሎ የማነሳቸዉ ነጥቦች በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ ሰዎች የተነሱ ቢሆኑም በአብዛኛዉ ግን እንደ አይነኬ ተደርገዉ የሚደበቁ ወይም በማድበስበስ የሚታለፉ ስላሉ እዚህ ጋ በድፍረት መነሳቱ አስፈላጊ ነው። እነዚሁ አይነኬና ድብቅ የሆኑ ነገሮች የዘር አመጣጥ፣ የሃይማኖት ግንኙነትና ልዩነት፣ እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች ናቸዉ። እነዚህን በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የማነሳዉ በሁለት ምክንያቶች ነዉ። አንደኛዉ የኢትዮጵያዊያን ተሸፋፍኖ የቆየዉ የአብሮነት ችግር ምን እንደሆነ ለማሳየትና ሁለተኛም ኢህአዴግ በሕዝቦች መሀከል መተማመን እንዲጎለብት አድርጌአለሁ ከሚል ጋር ሁሉም ሰዉ እንኳን ባይባል አብዛኛዉን ያግባባ ነው ወይስ የሚለያይ ነው የሚለዉን ለመፍተሽ እንዲያግዝ ነው። የእነዚህ ጉዳዮች ፍተሻ የሰለጠነው ዓለም የሚመራበትን የአመለካከትና የፓርቲ ፖለቲካ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ዓይን ይከፍታል ብዬ በማሰብ ነው።

በመጀመሪያ፤ ከዘር አመጣጥ እንጀምርና ለመሆኑ በሰሜትኮችና ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች መሀከል የነበሩና ዛሬም ያሉ የልዩነትና ለትስስር

መላላት ደንቃራ የሚሆኑት የትኞቹ ናቸዉ? ተብለዉ ቢነሱና ካብ ለካብ ከመተያየት በዘለለ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም ፖለቲከኞች የሚባሉቱ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ብዙም ከቃላት ያልዘለለዉን የብሔር ጥያቄን ከሕዝቡ ፍላጎት አንፃር ተግባራዊ ሊያደርጉ ችለዉ ቢሆን ኖሮ የአብሮነት ጉዞው ሊሰምር በቻለ ነበር ብዬ አምናለሁ። በተዛማጅም፤ ከግዛት አንድነትና ከሕዝቦች አንድነት የትኛው ያሳስባል የሚል ጥያቄ ሊነሳና በስፋት ሊያነጋግር ያስፈልጋል። በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የግድ መምረጥ ቢያስፈልግ የግዛት አንድነት እንኳን ቢላላ፣ ጨርሶም ቢፈርስ ሕዝቦች ሊተሳሰቡ ይችላሉና የሕዝቦች ትስስር ይመረጣል ቢባል የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል። ስለሆነም፤ ከሕዝቦች አንድነት የግዛት አንድነትን አስበልጦ መምረጥ ጉዳቱ አንዳንድ ጊዜ ልዩነቱ የትየሌለ ሊሆን ይችላልና ቀድሞውንም ልዩነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ሕዝቦችን አንድ ሕዝብ፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ባንድራ፣ እያሉ ተጨንቆ ሰውን ማስጨነቅ ከኋላው በአንድነት ወይም በአሃዳዊነት ስም የሆድ ቁርጠታችንን መልሶ ለመቀስቀስ ያለመ ነው ሊባል በሚችል ሁኔታ የሕዝቦችን አንድነት የሚሸረሽር ሥራ ከመስራት የዘለለ አይሆንምና መቆጠቡ ተመራጭ ነው እላለሁ። ኢትዮጵያዊያን ከ1847 ከአፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ ጅምሮ እስከ 1952 የኤርትራ በፌዴሬሽን ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል ድረስ አንዳንድ ጊዜ በተፋጠነና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዝግታ የብዙ ሕዝቦች ስብሰብ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሃይማኖት፣ የዘር ግንድ፣ የአመጋገብ፣ የአነጋገር፣ የአለባበስ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የታሪክ፣ የአስተዳደር፣ ወዘተ በልዩነትም ሆነ በመተሳሰር አብረው ቆይተዋል። እንደ መላሹ አቋም ይለያያል እንጂ የልዩነት መጠኑ ሰፊ ነው። ለምሳሌ ከሃይማኖት አንፃር ብንመለከት ማክሰኞ የተመገበው ምግብ በሰውነቱ ውስጥ እየሰራ ያለ መሆኑን የሚረዳ ሰው ያንኑ ምግብ ረቡዕ ዕለት ይመገብ ቢባል አያደርገውም። ምክንያት፤ ማክሰኞ በልቶ ያንኑ ምግብ እሮብ ዕለት ይፆማልና ነው። እሮብ አለመመገቡ ብቻ ሳይሆን ሐሙስ ያንኑ ምግብ ሊመገብ እያሰፈሰፈ ረቡዕ ተመጋቢ ሌላን ሰው ሲኮንንም ይታያል። ተራ ሰው ይህንን ድርጊት መፈፀሙ ብዙም የሚባል ነገር ባይኖርም የሕዝቦችን እሴቶች በማክበርና በማስከበር

አስተዳድራለሁ ለሚል የፖለቲካ ፓርቲ መሪ/ዎች አያያዝ ያስቸግራል። ለምሳሌ፤ የከፋ እና የሞቻ ሕዝቦች ቆጮ በብዛት ይመገባሉ። ቆጮውን ደግሞ በወተት፣ በወተት ተዋጽኦና በሥጋ ይመገባሉ። የእነዚህ ሕዝቦች የቤት አያያዝና የንጽህና አጠባበቅ ዛሬ ከተሜ ነን፣ ሰልጥነናል ከሚሉት ጋር የሚስተካከልና የተሻለም ስለሆነ የሚናቁ አይደሉም። ታዲያ፤ እነዚህን ሰዎች ሮብ ጌታ የተከዳበት ዓርብ ደግሞ ጌታ የተሰቀለበት ቀናት ላይ የወተት ተዋጽኦና ሥጋ ይመገባሉ ብሎ አቃቂር ማውጣት እንዴት ይቻላል? እነዚህን ሕዝቦችስ በማግለል እንዴትስ በስሙ ፓርቲ ማቋቋምና መሪው መሆን ይቻላል? ከሕዝቦች እና አገር አንድነት ጋር ተያይዞ መመለስ ያለበት ነው።

እንግዲህ ካለፈው ታሪኮቻችን የተነሳ አንድ ለመሆን ባንችል እንኳን ለመቀራረብ አይነኬ የሚመስሉ ልዩነቶቻችን ማንሳትና ማንሸራሸር አስፈላጊ ይሆናል። ለመሆኑ ኢትዮጵያዊያን እነማን ናቸዉ? አበሾችስ? ኢትዮጵያዊነትንና አበሻነትን በተወራራሽነት መጠቀም የት ድረስ ይቻላል? የኢትዮጵያዊያን አንድነትና ልዩነት በፓርቲ ፖለቲካ ላይ ያሳደረዉና ሊያሳድር የሚችለዉ ተፅዕኖ አለ? ይህንንና ሌሎች የልዩነት ነጥቦችን ማንሳት አላዋቂም ሆነ በሕዝቦች መሀከል አላስፈላጊ ግጭት ወይም ጠብ ቀስቃሽ አያስብልም። በፌዴሬሽን ወይም በአሃዳዊ የመንግስት ቅርፅ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የሚፈለጉ ኃይሎች ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ልዩነትና አንድነት እንዲሁም አስተሳስሮት የሚያኖረዉን የፍቅርም ሆነ የኃይል አገዛዝን በሚገባ ያጤኑ መሆን ይኖርባቸዋል።

በዝርዝር እንመልከት! ኢትዮጵያዊያንን የሚለያየዉ ጉዳይ አንዱ የየመጡበት የዘር ግንድ ነዉ። እራሳችንን ካላታለልን በቀር፤ በኢትዮጵያ ዉስጥ ሁሉም ሰዉ ለማለት ይቻላል፤ ከላይ እንደ ገለፅኩትም፤ በጥቅም ጉዳይ ላይ ወደ ራሱ የዘር ግንድ ይጎትታል ማለት ብቻ ሳይሆን ማን ማንን ይወልዳል? ብሎ እስከ መጠያየቅ የሚደርሱ ናቸዉ። የሰሜን ኢትዮጵያ ሰው ስሙን ጠርቶ ያባቱን ስም የማይደግመውን ሰዉ፤

“ወንድሜ ነዉ/እህቴ ናት ተዋወቀዉ/ተዋዉቃት” ብሎ የተለየ ጥቅም እንዲያገኝለት ወይም እንድታገኝለት ያግዛል። ይኼ ነገር በኛ በኋላቀር አገር ብቻ ሳይወሰን፤ ሰለጠኑ በሚባሉ አገሮች ጭምር ለአንድ ፕሮጀክት ዕርዳታ ሲያደርጉ እንኳን፤ ያንን ፕሮጀክት የሚሰራዉ ወይም የሚቆጣጠረዉ የዚያ የዕርዳታ ሰጪ አገር ዜጋ እንዲሆን በስምምነት ፊርማቸዉ ውስጥ እንዲካተት ያደርጉታል። *(Tied aid project)* የሚባለዉ ዓይነት ማለት ነዉ። በአገራችን በኢትዮጵያም ይኼዉ ጉዳይ የተለመደ ብቻ ሳይሆን፤ ለዚያም ከሕዝብ በተሰበሰበ ግብር የሚሰራ ሥራን የሥራዉ የበላይ አካል የራሱን ወገን ወይም የራሱ የሆነ የደም ወይም የጥቅም ትስስር ያለዉ ሰዉ ካልተመደበ በስተቀር ሥራዉ ሊሰራ እንደማይችል፤ ቢሰራ እንኳን አቃቂር የሚወጣለት ዓይነት ይሆናል። ከፓርቲ ፖለቲካ አንፃር ሲታይ ደግሞ የአንድ ቤተሰብ አባላት ወይም በጥቅም የተቧደኑ ሰዎች የተሰባሰቡበት ሥርአት በናፓርቲዝምና ኦሊጋርኪ የሚባለዉ ነዉ። ጥቂት የአንድ ቤተሰብ አባላት ወይም በጥቅም የተሳሰሩ ሰዎች የተሰባሰቡበት ቡድን ማለት ነው። በትግራይ ክልል ልጅነት የተሰባሰቡ የሕወሓትን ቡድን ወይም ምርኮኞች የተሰባሰቡበት ኦህዴድንና ዘራፊ ዘመዶቻቸውን ምሳሌ ማድረግ ይቻላል።

ይህንን ጉዳይ መሬት ማስያዝ ያስፈልጋል። የአማራ ተወላጆች የበላይነትን ይዘው በነበሩበት በምንሊክ፣ በኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ጊዜያት ጤንነቱ ያልተጠበቀ ሰው (ዝሆነ እግር ወይም ግንድ እግር የሆኑ ሰዎች) ጭምር ከምስለኔ እስከ ጠቅላይ ግዛት ደረጃ ሾመው ጥቅሙን ይጠብቁለት ነበር። ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸዉን በራሳቸዉ ያስተዳድራሉ በተባለባት በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ደግሞ ሕወሓት/ኢህአዴግ የሁሉም ጉዳዮች የበላይነቱን ለማሳየት ሲል የሕወሓት አባላት የሆኑትን አነሰ ቢባል ደግሞ የትግራይ ተወላጅ የሆኑትን በየክልሎች በተቆጣጣሪነት እንዲመደቡ አድርጓል። ሎቪስ አላን (2002፡ 86) *Ethnic Federalism in a Dominant Party Democracy: The Ethiopian Experience 1991-2000* ብላ በአከናወነችዉ ጥናት ዉስጥ እንደጠቀሰችዉ *“… the EPRDF has*

*deployed party officials in the regions. In* 1999 all of the assigned advisers were TPLF cadres." *ብለ በስም* እየጠቀሰች የሕወሓት ካድሬዎችም ሰለሞን ተስፋዬ (ጢሞ) በኦሮሚያ ክልል፣ ህላዊ ዮሴፍ በአማራ ክልል፣ ቢተው በላይ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ ሣሙኤል ገብረማርያም በጋምቤላና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፣ ዘራይ አስገዶም በሶማሌና አፋር ክልሎች፣ ሙሉጌታ አለምሰገድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ማስቀመጡ፤ እነዚህ ግለሰቦች በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት ብዙ ሰዎች የተሻለ ነው የሚባል የትምህርት ዝግጅት ኖሯቸዉ ሳይሆን፤ በጥቅምና በዘር ግንድ ትስስራቸዉ ለመጠቃቀም ሲሉ ያደረጉት ነገር ብቻ ስለሆነ ነዉ። ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችና የሕወሓትን ጥቅም የሚያስጠብቁ ውሳኔዎች የሚሰጡት በነዚህ ግለሰቦች እዉቅና ብቻ ይሆናል። የኦሮምያን ክልል ትንሽ ለየት የሚያደርግ ነገር ቢኖር ደግሞ ከሕወሓት ካድሬ ሌላ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የሌሎች ብሔረሰቦች (ሕዳጣን) ተወላጆች አፋን ኦሮሞን በመቻላቸዉና ለገዥው ፓርቲ ታማኝ ከመሆናቸው የተነሳ ብቻ በክልሉ የአስፈፃሚነት ቁንጮ ቦታ ላይ እስከ መቀመጥ ደርሰዉ፤ በኦሮሞ ሕዝብ ሕይወት (ዕጣ ፋንታ) ላይ እስከ መወሰን የሚደርሱበት ጊዜና ሁኔታ መኖሩ ቀላል የሚባል በደል አይደለም። ይህ ሲባል ግን በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ የሚኖሩ የሌሎች ብሔረሰቦች ተወላጆች ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ የመስራት መብት የላቸዉም ወይም መስራት አይችሉም ለማለት ሳይሆን፤ የኦሮሞን ሕዝብ ጥቅም የሚጎዱ ፖሊሲ ነክ ዉሳኔዎችን በመስጠት በኦሮሞ ሕዝብ ሕይወትና ጥቅም ላይ መወሰን የሚያስችላቸዉን የፖለቲካ ሹመት ደረጃ መድረስ አልነበረባቸዉም ለማለት ተፈልጎ ነዉ።

እንደ ምኞት ሆኖ ኢትዮጵያዊነት የበላይነት ቢኖረዉ የሚመረጥ ነዉ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ከተገነባችበት ታሪካዊ ዳራ አንፃር ኦሮሞነትን፣ ትግሬነትን፣ አማራነትን፣ ሲዳማነትን፣ ኑዌርነትን፣ አኙዋክነትን፣ ጉሙዝነትን፣ አፋርነትን፣ ሱማሌነትን፣ ቅማንትነትን፣ ኑዌርነትን፣ ወዘተ በመደፍጠጥ መሆን እንደሌለበት ትዉልዴ አበሻ የሆኑ ዜጎች

አይቀበሉትም ብቻ ሳይሆን ትዝም አይላቸዉም። ትዝም አላቸው አላላቸው ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ከተለያዩ እምነታቸው፣ ባህላቸው፣ ቋንቋቸው፣ ልማዳቸውና ታሪካቸው ጋር የተሰባሰቡባት (conglomerated) ምድር መሆኗን ዕውቅና ካልሰጡ አጠፈታው ከቀላል እስከ ከፍተኛ ሊደርስ የሚችል አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነው።

በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል መሳሳብ ወይስ መጣረስ ያመዝናል ተብሎ ለሚነሳዉ ሐሳብ ቁርጥ ያለ አስተያየት መስጠት አስቸጋሪ ቢመስልም፤ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በመልካም ፈቃዳቸዉ በመርጡት መንግስት የተዳደሩበት ጊዜ እና ትስስራቸዉን ያጠበቁበት ጊዜ እስከ ዛሬ ስለአልተፈጠረና ይህንን ለመፍጠር ደግሞ ረጅም ጉዞና ጊዜ የሚወስድና ትዕግስት የተሞላበት መረጃ ላይ የተመሠረተ እዉነታ ተጣርቶ አንድ መቶ ዓመት ወይም ከዚያም በላይ የሆነዉን የኢትዮጵያዊያን አብሮነትን ማጣራት የራሱ ችግር ስለሚኖረዉ፤ በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የግጭትና የጦርነት ታሪክ ነዉ ማለት ግጭትና ጦርነት መቀስቀስ ሳይሆን የታሪኩን እዉነትነት መግለጽ፤ ከአሁን ወዲያም ሊያቃቅሩ ከሚችሉ ምክንያቶችና አካሄዶች ትምህርት ቀስሞ ማስተካከል መቻል ማለት ይሆናል ማለት ነዉና ሻካራ ግንኙነት ይፈጥራሉ በሚባሉት ላይ ትኩረት አድርጎ መፈተሹ ተገቢ ይሆናል።

ኢትዮጵያዊያንን የሚያጋጭና በዕድገታችን ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ የሚፈጥረዉ አንዱ የሀገረ መንግስት ግንባታው የሦስት ሺህ ዘመናት እና የአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት ታሪክ ወይም ትርክት ነዉ። በዚህ የጊዜ ግጭት መሀከል አንድ ሊያስማማን የሚችል ነጥብ አለ። ይኸዉም አንድ አገር (nation-state) በአንድ ጊዜ ተነስቶ ሊገነባ እንደማይቻል ግንዛቤ መያዙ ላይ ነዉ። በማስከተልም ሁለት ነገሮች ሊያስማሙን ይችላሉ፤ የጥንቷና የሦስት ሺህ ዘመኗ ኢትዮጵያ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ አለች። እንዲሁም የዛሬዋ ኢትዮጵያ አካሎች የሆኑት ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና

ሕዝቦች በሙሉ የጥንቷና የሦስት ሺህ ዘመኗ ኢትዮጵያ ዉስጥ አልነበሩም። በሌላም በኩል የዛሬዋ ኢትዮጵያ አካሎች የሆኑት ብሔር ብሔረሰቦች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ በቃል ይሁን እንጂ በማንም ሊደፈጠጥ ወይም ሊዘለል የማይችል የየራሳቸዉ ታሪክ የነበራቸውና ያላቸዉ ናቸው። ይህ አንድ ነገር ሆኖ፤ በሌላም በኩል የሩቅም ሆነ የቅርብ የኢትዮጵያ ታሪክ ግድ የማይሰጣቸዉ እንዲያዉም ታሪክ ተቀቅሎም ሆነ ተጠብሶ አይበላም የሚሉና ግድ የማይላቸዉ ዜጎች በመሀል ላይ ስለመኖራቸዉ መዘንጋት የለብንም። እነዚህ መሀል ሰፋሪ የሚመስሉ ዜጎች ሐሳብ ስለአገርም ሆነ ስለታሪክ ግድ የሌላቸዉ እንደሆነ አስመስሎ ዝም ተብሎ የሚጣልም አይሆንም። ምክንያቱም፤ እነዚህ የመሀል ሰዎች የጥንቱንም ሆነ የቅርቡን ታሪክ ብሎ ከማዉራት ይልቅ ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር ልክ እንደምዕራባዊያን አገሮች ለሁሉም ዜጎቿ ምቹ ማድረግን ወይም ለአዲስ ማህበረሰባዊ ኮንትራት (new social contract) ቅድሚያ የሚሰጡ ናቸዉ። በተወሰነ ደረጃ ተቀባይነት ቢኖራቸዉም፤ ነገር ግን አንድ የዘነጉት ነገር ቢኖር ታሪክን ለምን እንደምንማር ነዉ። ታሪክን የምንማረዉ በሦስት ምክንያቶች፤ የነበረዉን በጎም ሆነ ክፉ ነገሮችን እንደነበረ ለመረዳት፣ ያሁኑን ለመተርጎም እና (ምንም እንኳን የነገን መተንበይ የራሱ የሆኑ ችግሮች ቢኖሩትም) የወደፊቱን ኢትዮጵያ ግንባታ አቅጣጫ ለማሳየት ወይም ለመተንበይ ነዉ። ምክንያቱም፤ የኢትዮጵያዊያን ትስስር ለመጠንከርም ሆነ ለመላላት ታሪክ የራሱ የሆነ በጎና መጥፎ ሚና አለዉ ተብሎ ስለሚታመን ነዉ።

የጥንቷ ኢትዮጵያ ታሪክ አፍቃሪዎች የጥንት ኩሻዊያንን የእጅ ጥበብና የአስተዳደር ብልሃት አስተዋጽኦ ዕዉቅና የሚሰጡ ከሆነ ከሦስት ሺህ ዘመኗ ኢትዮጵያ በተወሰነም ደረጃ የሚጋሩት ታሪክ አለና ንትርኩም በተወሰነ ደረጃ እዚያ ላይ ሊቀንስ ወይም ሊያበቃ ይችላል። በሚገባ ሊሠመርበት የሚገባ ነገር ቢኖር ግን በአንድ ጂኦግራፊያዊ ክልል ወይም አገር ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የሚጋሩትም ሆነ የሚለያዩበት የታሪክ አጋጣሚዎች እንደሚኖሩ ነዉ። ለምሳሌ የዛሬዋ ኢትዮጵያ አሻራዎች

ከግብፅም ሆነ ከሱዳን ሕዝቦች ግዛት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል። ነገር ግን ታሪክ በሚያስተላልፈዉ ኩነትና የዛሬዉ ሕብረተሰብ መተሳሰቡ ላይ ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ አጥርቶ ዓለም ዛሬ ከደረሰበት የሰለጠነ ፖለቲካ አካሄድ ጋር ማጣጣምና ማየት አስፈላጊ ይሆናል። ምክንያቱም፤ ኢትዮጵያ ታሪኳ ለሁሉም ሕዝቦቿ እንዲሆን ተደርጎ ያልተፃፈ በመሆኑ ለሕዝቦቿ ትስስርም የማይቋጠርና የማይፈታ ቋጠሮ የሆነባት አገር ነችና ነዉ። የሕብረተሰብ ዕድገት የተለያየና የተጣጣመ መሆኑን የማይረዱ፤ ቢረዱም ዕውነቱን ለመናገር የማይደፍሩ የሐበሻ የታሪክ ፀሐፊዎች የደቡቡን ሕዝብ ታሪክ ሲጽፉ ከኋላው የመንደርደሪያ ታሪክ እንደ ሌለው አድርገው ይቀርጹታል። ታሪኩ የኋላ መንድርደሪያ የሌለው ሕዝብ ደግሞ ከጎኑ ካለው ሕዝብ ጋር እኩል ወደ ፊት የሚጠበቀውን ያህል ርቀት መዝለል ቀርቶ መራመድም አይችልም። በዚህም መሠረት የጥንት ኢትዮጵያዊያንን ከወሰድን ሰሜነኞቹ የአበሻ ገዥዎች ኦሮሞና ሌሎች የደቡብ ሕዝቦችን በአንድ ማዕከላዊ የመንግስት አስተዳደር ጥላ ሥር የሚያዉቁት ከምኒልክ ወረራ ወዲህ ነዉ። ከዚያ በፊትም ያውቁ ነበር ቢባል እንኳን የወሎና የራያ አሰቦ ኦሮሞዎችን እንጂ ከምኒልክ ወረራ ወዲህ የተጠቃለሉትን የአርሲ፣ የሐረር፣ የባሌ፣ የጂማ፣ የወለጋ፣ የኢሉባቦራ፤ ወይም የሲዳማ፣ የወላይታ፣ የከምባታ፣ የደራሼ፣ የሐዲያ፣ ወዘተ ሕዝቦችና መኖሪያ አከባቢያቸዉን አልነበረም። በሌላም በኩል አወቁ እንኳን ቢባል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስልጤ ነው ከሚባለው ከ"ግራኝ መሐመድ ኢብን አልጋዚ ወረራ" የሚሉት ጋር ተያይዞ ያለዉን ሊሆን ይችላል። ሊሆን ይችላል ያልኩበትም ምክንያት ራሱን የግራኝ መሀመድን ማንነት በትክክል ባለመግለፅ አንዴ ቱርካዊ፣ ሐረሪ፣ ሱማሌ፣ አዉሳ አድርገዉ ይገምቱ ስለነበረ ነዉ። ከምኒልክ ወረራ በፊት የአበሻ ንጉሶች የነበሩ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ ስለኦሮሞ የሚያዉቁት ሁለት ቅርንጫፍ የሆኑ ኦሮሞዎች የየጁና የራያና አሰቦ ሕዝቦችን ብቻ ነዉ። ስለሆነም፤ የጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ የሰሜነኞች ታሪክ ሲሆን የቅርቡ የኢትዮጵያ ታሪክ ደግሞ የደቡቡን ኢትዮጵያን ታሪክ ጨምሮ መሆን አለበት። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የኢትዮጵያን ታሪክ ካልተረዳን በስተቀር የኢትዮጵያ ታሪክ የሚባለው በሙሉ ለማዋሃድም

ሆነ ለመለየት የሚያስቸግር በስህተት የተደባለቀ የዘይትና የውሃ ቅይጥ ሆኖ እንዳነታረከም ይቀጥላል። ይኼ ደግሞ የሆነው ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሐበሻ ካልሆኑ ወይም ካልተባሉ በስተቀር ሞቴን እንገኛለን የሚሉ አስቸጋሪ ሰዎች ስላሉበት ነው።

እንግዲህ በመሠረታዊነት የሚያግባባን የታሪክ ግንዛቤ ሳይኖረን ሌላዉ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ትስስር ይዳብራል ማለት ያው የአገራችን ትስስር በጠመንጃ ወይም በጉልበት ይፈጠራል በማለት በቀድሞዉ ዓይነት ሁኔታ ከማሰብ በስተቀር የተለየ ነገር አይሆንም። የጉልበትና የጠመንጃ ነገር ደግሞ ኢትዮጵያን ከኋላቀርነትና ከተመጽዋችነት ሊታደጋት አልቻለም፤ ወደፊትም ይታደጋታል ተብሎ አይታሰብም። ተመፅዋችነትንና ዛሬ የሚያራርቁን ነገሮችን አስመልክቶ ማንም የማይመልሰው የኢትዮጵያን የታሪክ ፍራሽ ላይ መተኛት ነው። አንዳንድ ሀገሮች ጥቂት ዓመታት በሚባል ጊዜ ውስጥ ሕዋን መዳሰስ ሲችሉ፤ ኢትዮጵያ (ከአምስት ዓመት የጣሊያን ወረራ ሌላ) የሦስት ሺህ ዓመታት የመንግስትነት ዕድሜን ይዞ ዛሬ ተመፅዋች መሆኗ እንዳሳለፍነው ኑሮ ከምንኖር ባንኖር ይሻላል ቢባል አያስኮንንም። ይህ በታሪክ ላይ መተኛትና አለመግባባት የሚያሳርፈዉ ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ በፌዴሬሽንም ሆነ በአሃዳዊነት የኢትዮጵያን አንድነት ለማቆየት የሚፈልጉ ኃይሎች ሁሉ ከታሪክ አንፃር የኢትዮጵያ ሕዝቦችን የልዩነት መነሻ የቱ ላይ እንደሆነ ቢያንስ ካሉት አፈ ታሪክ መነሳትም ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌም፤ በባለሦስት ሺህ የኢትጵዮያ ታሪክ ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ታሪክ የንግስት ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝትና የንጉስ ሰለሞን መስተንግዶ ብሎም ቀዳማዊ ምንሊክን መውለድ ነው። የኢትዮጵያን የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ ከቀዳማዊ ምንሊክ ጋር እያጣቀሱ፤ በተገላብጦሽ ደግሞ ለኢትዮጵያ አንድነት ቀዳሚ የሆነውን የንግስ ምንጭ የሆነውን የቅማንትን ሕዝብ ምንነት ማኮሰስ አብሮትን የማይጋብዝ ፈተና ነው።

ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ከተፃፉ መፃሕፍት ለመረዳት እንደሚቻለዉ

የዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን ከሁለት የሰዉ ልጆች የዘር ሐረግ፤ ሴሜቲክ እና ኩሽቲክ የተዋቀሩ ናቸዉ። እንደ መፅሐፍ ቅዱስ መረጃ ምንጭነት ደግሞ ከምድራችን የውሃ ጥፋት በኋላ ተባዝተዉ ምድርን የሞሏት የኖህ ልጆች ሴም፣ ካም/ሐም እና ያፌት ነበሩ። የሴም የዘር ግንድ ሴሜቲክ ሲሆኑ የካም/ሐም የዘር ግንድ ከከነዓን ቀጥሎ ዛሬ ድረስ ያሉትን የሚጠሩበት ኩሽ አንዱ ነዉ።

የአባቱን በወይን ጠጅ ሰክሮ ራቁቱን መተኛት ለወንድሞቹ የተናገረዉ ካም/ሐም ልጁ ከነዓን የባሪያዎች ባሪያ እንዲሆን በአባቱ በኖኅ ተፈርዶበታል፤ ወይም ተረግሟል እንበል። ፊታቸውን ወደኋላ በማዞር የአባታቸዉን ራቁት የሸፈኑት ሴምና ያፌት ስለመመረቃቸዉ የተገለጸ ነገር ባይኖርም፤ (በቀና ሁኔታ ሲታይ ግን ካልተረገመ የተመረቀ ነውና) የከነዓን እርግማን ከከነዓን ይዝለል አይዝለል የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፤ ያቺ እርግማን ግን ለሴሜቲክና ለኩሽቲክ የዘር ግንድ ሕዝቦች መለያየት ወይም መናናቅ መነሻ መሠረት ሆና በተለይ በኢትዮጵያ ዉስጥ አገልግላለች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምንም እንኳን በሳይንስ የተደገፈ ነገር ባይኖርም የጠቆሩት ማለትም የኩሽ ዘር የሆኑ የተረገሙ ናቸዉ ተብሎ ስለሚገመት፤ በተለይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዉስጥ ያልተረገሙት የሴምና የያፌት የዘር ግንዶች ያልተረገምን ነን ብለዉ ስለሚያስቡ በሌሎች የዘር ግንድ ሕዝቦች ላይ የበላይነትን ለማሳየት የሚፍጨረጨሩበት ሁኔታ ስለመኖሩ አንድና ሁለት የለውም። እንዲያዉም አንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ሴማዊያን ስለጥቁርነታቸዉ እንዳይነሳባቸዉ ከመፈለጋቸዉም በላይ ጠይም እንጂ ጥቁር አይደለንም የሚል ፈሊጥ በመያዝ ከዚህ የተነሳም ከሌሎች ጥቁር አፍሪካዊያን ጋር እስከ መጣላትና ጥቁር አፍሪካዊያን ከቅኝ አገዛዝ ሲላቀቁና ነፃነት ሲያዉጁ ቀላል የማይባል ድጋፍ ያደረጉት ኢትዮጵያዊያን፤ ከነዚህ ወገኖች ማግኘት የሚገባቸዉን የአጠፈታ ክብርና ቦታ እንዳያገኙ እስከ ማድረግ ደርሷል። ለምሳሌም፤ ጽህፈት ቤቱ አዲስ አበባ ሆኖ፤ ፍራንኮ ፎንና አንግሎ ፎን የሚባሉትና በቋንቋ ላይ የተመሠረተዉ የክልል ክፍፍል ያላቸው ሲፈራረቁበት፤ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ሆነ ለአፍሪካ ሕብረት ፀሐፊነት ወይም ኮሚሽነርነት

የተመረጠ ወይም የተወዳደረ ኢትዮጵያዊ እስከ ዛሬ ድረስ የለም፤ ምናልባት የንጉሱ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትሮች የነበሩ ክፍሌ ወዳጆ እና ከተማ ይፍሩ በስተቀር።

ከዚሁ አርእስተ ጉዳይ ሳንወጣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለቦታው የሚነገረውን የዘር ፖለቲካ የሚባለውን የሚያፋልሰው በዓለም ላይ የሚገኙ የሰው ልጆች በሦስት ሰፋፊ ዓይነት የሰው ዘሮች- ካኮሳይድ (ነጮች)፣ ኒግሮይድ (ጥቁሮች) እና ሞንጎሎይድ (ብጫዎች) በመባል ይመደባሉ። እነዚህ የሰው ዘሮች በዓይንና ቆዳ ቀለም፣ በአፍንጫ አቀማመጥ፣ በከንፈር ስፋትና ጥበት፣ በግንባር አጥንት፣ በመሳሰሉት የሰውነት ክፍሎች ይለያያሉ። የቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት፣ ኤኮኖሚ፣ ሥነ ጥበብ፣ አመራረት፣ አመጋገብ፣ ወተፈ የሚባሉ ልዩነቶች በሰው ልጆች የተፈጥሮም ሆነ ማህበራዊ የዕድገት ሂደት ጋር የተፈጠሩ በአብዛኛው ማህበራዊ ክስተቶች ናቸው። ማህበራዊ ክስተቶች ደግሞ ከሚደረግባቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጫና የተነሳ ለመለወጥም ሆነ ለመጥፋት የተጋለጡ ናቸው። ይህ እስከሆነ ድረስ ከማንም የግልም ሆነ የቡድን ፍላጎት ውጭ በተፈጥሮም ይሁን በማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ማለትም በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶች ላይ ተንተርሰን ድብቅ ፍላጎት ከሌለ በስተቀር የሚታየውን የሰው ልጆችን ልዩነት ዘርና ዘረኝነትን በቅጡ ሳንለይ ለምን የጥፋቶች ሁሉ መነሻ እና መድረሻ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ግልፅ አይደለም። ስለሆነም ነው ልዩነትን ማስተናገድ የማይችል አንድነት በአፍንጫችን ይውጣ የሚሉ ዜጎች ቢኖሩ ዜግነታቸውም ጥርጣሬ ውስጥ መግባት የለበትም፤ አፍንጫቸውም መያዝ የለበትም ለማለት የፈለኩት።

*ሌላዉ አንዳንዶች በመለዋወጥ የሚጠቀሙበት አብሲኒያና አበሻ የሚባሉ ቃላትና ኢትዮጵያዊያንን ብዙም የማያጣጥሙትን የሚመለከት ነገር ነዉ።* እዚህ ላይ አንባቢያን ሊረዱልኝ የሚገባቸዉ ነገር ቢኖር አብሲኒያ የታሪካዊ አጠራር አገልግሎት ለዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ከመሰጠቱ በፊት፤ ሌሎችንም ኢትዮጵያዊያንን ሊያግባባ በሚችል ዓይነት ሁኔታ

አብሲኒያና አበሻ የዛሬዋም ሆነ የጥንቷ ኢትዮጵያ የሰሜን ግዛቶች አማራና ትግራይን ሊወክል ይችላል እንጂ ከዚያ ይሰፋል እንኳን ቢባል ከስልጤ፣ ከወለነ፣ ከአርጎባ፣ ከሐራሪና ከጉራጌ ሕዝቦች ውጭ ያሉትን ሊጨምር አይችልም ማለት ነዉ። እነዚህም ሴሜቲክ በመባል የሚታወቁ ሕዝቦች ናቸዉ። ስለሆነም አበሻ የሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ኢትዮጵያዊነታቸዉ የማያከራክረዉን ያህል፤ የኩሽ የሆኑ ዝርያዎችም ኢትዮጵያዊያን መሆናቸው ያንኑ ያህል ማከራከር አይገባም። በአጭሩ <u>ሁሉም ሐበሾች ኢትዮጵያዊያን ቢሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ግን ሐበሾች አይደሉም</u>። ሐበሾች አይደሉም ስለተባለ ደግሞ ፈረንጅ ናቸው ማለትም አይደለም። ወይም ሐበሻ ማለት ጥቁር የሆነውን ሁሉ ያጠቃልላል ማለት አይደለም። ከዚህ በዘለለ ደግሞ ታሪክ በምንልበት ጊዜ በሁሉ ዘንድ ባይሆንም በአብዛኛው ሕብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ታሪኩ ራሱ ቀጣይነት ያለውና የወዳጅነት፣ የወንድማማችነትና የነፃነት አንድነት ጎልቶ የሚንፀባረቅበት ታሪክ መሆን አለበት። ሲጠቃለልም፤ በሀገረ መንግስት ግንባታ አረዳድ መሠረት ዘመናዊት ኢትዮጵያ አሁን ባላት ቅርጿና ዓለም አቀፍ ሕጋዊነቷ በተሟላ ሁኔታ የተቋቋመችው የዛሬ መቶ ሃምሳ ዓመት ግድም ነው ተብሎ የአፄ ምንሊክ አፅም ሳይቀር ቢጠየቅ፤ ይህማ በኔው መሪነት የተከናወነ ስለሆነ፤ ታዲያ ምን የተሳሳተ ነገር አለው ብሎ መልሶ በአግራሞት እንደሚይጠይቅ መገመት ይቻላል። “ታሪክ ስንል ጠባቡን የፖለቲካ ሥልጣን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሕዝቦችን አሰፋፈር፣ የቋንቋዎችን ስርጭት፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ አወቃቀርን ያጠቃልላል” ይላል ኦላና ዞጋ በ<u>ግዝትና ግዞት</u> መጽሐፉ ገጽ 360 ላይ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን ዋቢ በማድረግ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ለፓርቲ ፖለቲካችን ተግዳሮት ከሆኑት አንዱ የሆነው የዘር ምንጭ የሚባለው ልዩነት ጉዳይ ይህን ያህል ግንዛቤ የሚፈጥር ከሆነ፤ በኢትዮጵያዊያን መሀከል የነበረና ጊዜ ጠብቆ ሊያቆጠቁጥ የሚችለዉን ሌላ ጉዳይ ብናነሳ የባህርይ ጉዳይ ተጠቃሽ ነዉ። የአማራዉን ንጉስ አፄ ምኒልክን ለመርዳት በቀይ መስቀል ስም

የመጣዉ ሩሲያዊ ቡላቶቪች ከላይ በተጠቀሰዉ መጽሐፍ ላይ እንደገለጸዉ ‹‹እንደአበሻ ጠባይ ብዙ ቅራኔዎች የተዋሃዱበት ሌላ ሕዝብ ማግኘት አስቸጋሪ ነዉ። የአበሻ ጠባይ ገደልና አለት፣ ተራራና ሜዳ፣ ቁርና ሐሩር የሚፈራረቅበትን የአገሩን [የኢትዮጵያን] ተፈጥሮ ይመስላል›› (ገፅ 137) ብሏል። ይህንን ሰፊ የልዩነትን ተፈጥሮ አስተካክሎ ኢትዮጵያዊ አብሮነትን መኖር ይቻላል አይቻልም መመለስ ያለባቸዉ ኦሮሞዎች ሳይሆኑ፤ ጥቂት የማይባሉ ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝምን አጥፍቶ የአሃዳዊነት አቀንቃኝ የአበሻ ኤሊቶች ናቸዉ።

ከአበሻ ባህርይ ጋር ይበልጥ የሚያሳዝነዉ ግን የአበሻ ገዥዎችን በመደገፍ የማንነት ቀውስ የሚያጠቃቸው ኦሮሞ የሆኑ ሰዎች የሚሰሩት ሥራ አስገራሚም አሳዛኝም መሆኑ ነዉ። አንስተዉ ራሳቸዉን አበሻ ከማድረጋቸዉም በላይ እነሱኑ ለመጫን የተቋጬ ሐበሻዊ ተንኮልን የሚረዱት አንድም በጣም ዘገይተዉ ይሆናል፤ ወይም በአላዋቂነታቸዉ እየሳቁ ይኖራሉ፤ ሲብስ ደግሞ  ማንነታቸውን ሳያውቁ የተፈጥሮ ሞት ይወስዳቸዋል፤ ወይ ደግሞ ሐበሻ ጌቶቻቸዉ ያጠፉአቸዋል። የደቡብ አፍሪካን ፀረ አፓርታይድ ንቅናቄን ለማዳከም የተሰለፉት ጥቂት ዘረኛ ነጮችና ለእነዚህ ዘረኛ ነጮች የሚሰልሉት ጥቁሮች እንደሚሉት *“... any effort by the black man to challenge the white man was foolhardly and doomed to failure; the white man was too smart and too strong”* ብለዉ የአድናቆት ፊልም እስከ መስራት የደረሱ ሲሆን፤ አይበገረዎቹ ጥቁሮችና ነጭ የነፃነት ደጋፊዎች *(it is possible)* ብለዉ በቃላትም በተግባርም መልስ የሰጡት ጊዜ የሚረሳ አይደለም። ስለዚህ ያገራችንም ችግር ልክ ደቡብ አፍሪካዊያን እንዳደረጉት፤ እየጎመዘዘም ቢሆን እየተጎነጬ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የግድ ሐበሻ ሳይሆኑ በዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊያን መሀከል ያለዉን ችግር ‹‹መፍታትና በፌዴራላዊነትም ሆነ በአሃዳዊት  ኢትዮጵያ ሥር መኖር ይቻላል›› ማለትን መቀበል አለባቸዉ ብቻ ሳይሆን ከስያሜ ጀምሮ ወላይታን ወላሞ፣ ሲዳማን ጀምጀም፣ የምን ጃንጃሮ፣ አዳማን ናዝሬት፣ ቢሾፍቱን ደብረ ዘይት፣ ጭሮን አሰቤ ተፈሪ፣ ሐዋሳን አዋሳ፣ ባቱን ዝዋይ፣ ጨቃላን ዝቋላ፣

ነቀምቴን ለቀምት፣ አርሲን አሩሲ፣ ኤጀሬን አዲስ ዓለም፣ ፊንፊኔን/ሸገርን አዲስ አበባ፣ ወዘተ ማለትን ለኢትዮጵያዊ አብሮነት ሲባል ማቆም አለባቸዉ። ይህ የማስገደድ ሳይሆን የአብሮነትን መስመር የሚያራምዱ ከሆነ የሰዉን ስሜት ጭምር መገንዘብና ማክበር ይጠበቅባቸዋል። በአንዱ ኪሳራ የሚዛቅ ትርፍ ዘለቄታ አይኖረዉምና።

የተቃራኒዎች አንድነት (unity of opposites) የሚለዉን በመስኩ ባለሙያዎች የቀረበዉን መርህ ግምት ዉስጥ በማስገባት፤ ኢትዮጵያዊያን በተለይም የአበሻ ሊህቃን አንድነትን የምንወደዉን ያህል ልዩነትንም መጥላት እንደሌለብን እየተረዳን ያለ ይመስለኛል። ልዩነት እንዳይነሳ መከላከል ማለት ላሉብን ችግሮች መፍትኼ ፍለጋ አንሄድም እንደማለት ነዉ። የዘርና የኢትዮጵያዊነትን አንድነትና ልዩነት ጉዳይን ከላይ በተባለው መሠረት እናጠቃልልና ሌላው በብዝሃነታችን ዉስጥ መስተናገድ ያለበት አንዱ ትልቁ ልዩነት የሃይማኖት ልዩነት እንደሆነ ስንቶቻችን እንደምንቀበል ማወቅ ያስቸግራል። ግን ስለሃይማኖት ጉዳይ ተግባሮቻችንን በመፈተሸ ልንደርስበት የሚቻል ስለሆነ ማስጨነቅ የለበትም። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ስለተፈጥሮ መብታቸዉም ሆነ ስለፖለቲካዊ ጉዳያቸዉ ሲያነሱ ከገዥዉ አካል የሚደርስባቸዉን ጡጫ ስለሚረዱ ወይም ስለሃይማኖት ጉዳዮች ያላቸዉ ተጋላጭነት (ኤክስፖዤር) አናሳ ስለሆነ፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሃይማኖት ልዩነት እምብዛም ለከፋ ግጭት የሚዳርግ ሆኖ አልወጣም። ከዚህ ቀደም ስላልወጣ ለወደፊትም አይወጣም ብሎ መደምደም ግን እንደ ሐሳብ እራሱ ችግር ያለበት ነው። እንዲያዉም አንዳንዱ የሃይማኖት ልዩነት ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ጉዳት እንዳደረሰ እና እያደረሰ እንደሆነ ካለበት የግንዛቤ አናሳነት ወይም እየተገነዘበም ልዩነቱንና ችግሩን ላለመግለፅ ሲል የራሱን ሃይማኖት ስም ጠርቶ ከሙስሊሙ ወይም ከክርስቲያኑ ማዕድ ቢቋደስ ኃጥአት የለዉም እያሉ ዝቅተኛ ግንዛቤን የሚፈጥሩ ዛሬም አሉ። ትናንትናና ዛሬ እንደዚህ ነዉ ማለት ነገም በዚሁ ይቀጥላል ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ መሆኑን ላሰምርበት ፈልጌ እንደሆነ እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ። በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት

እስልምናዉንም መጣል ያልወደደና የዮሐንስን ግድያ ደግሞ የፈራዉ ‹‹ወላህ ክርስቲያን ነኝ›› ያለዉ የመኖርና ያለመኖር ምርጫ መሀከል ተገብቶ የተባለ እንጂ የአሁኑ ዘመን ትዉልድ የሃይማኖቴን ስም ጠርቼ ሙስልሙ ከክርስትያኑ፣ ክርስትያኑም ከሙስልሙ ገበታ ለመቋደስ የሚዘይዱት ዓይነት ዘዴ አይሆንም። እንደዚያ ተወስዶ ብዙም ባይቀለድበት  የሚመረጥ ብቻ ሳይሆን፤ ሕብረተሰባችን ለንዲዚህ ዓይነት ችግር እንዳይጋለጥ የመከላከል መንገድ መቀየስና አለአስፈላጊዉ ቀልድም እንዳይደገም ከመጠለፍም ሆነ ከመጠርነፍ መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳሰብ ነዉ።

እንደሌላዉም አገር ሁሉ ሃይማኖትን የተመለከተ ችግር ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደነበረ ከታሪክ እናነባለን። አፄ ቴዎድሮስ ከሃይማኖት አንፃር ክርስቲያን ቢሆንም፤ እንደዚህ የሚባል ቤተክርስቲያን ገብቶ አስቀድሶ ነበር የሚባል ብዙ አላጋጠመኝም። የአፄ ዘርዓ ያዕቆብን ፈለግ የተከተለዉ አፄ ዮሐንስ ግን ያልተጠመቀ ሰዉ አገሩን ለቅቆ እንዲሄድ አዝዞ እንደነበር የተመዘገበ ታሪክ ነዉ። አፄ ምኒልክ መቼም ቢሆን የጦር ዘመቻዉን ሲያሳዉጅ ‹‹ማርያምን አልምርህም›› ይል እንደነበር ዛሬ ድረስ የምኒልክን ታሪክ የሚጠርቁ ሰዎች ያወራሉ። አፄ ኃይሌ ሥላሴ ‹‹ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ነች›› ብሎ ከመተረኩም በላይ ከሚኒስተር መስሪያ ቤቶቹ አንዱ የነበረው የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስተር <u>የሃይማኖት ማስፋፊያ ክፍል ሥራ</u> የሚሰራ አደራጅቶ ሲያሰራ እንደነበር ይታወቃል። በገቢ መዝገብ ቁጥር 146/48 ሰኔ 8/1948 ዓም በእጅ ተፅፎ ለንጉሱ እንደቀረበው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ <u>ማስታወሻ</u> ከሆነ ኢትዮጵያ ቀላል የማይባል የሙስሊም ሕዝብ እንዳላት እየታወቀና ምንም ዓይነት ግምት ሳይሰጣቸዉ “በመላ ኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስብከት እንዲስፋፋ ፕሮግራም የሚያዘጋጅ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን የሃይማኖት ሥርአትና ደንብ የሚያስፈጽም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሥራ የሚሰራ ክፍል” ተደራጅቷል።

በአፄዉ ዘመነ መንግስት የንጉሱ ልደትም ሆነ አንዳንድ ብሔራዊ በዓላት

የሚከበሩት መስጊድ ግቢ ተኪዶ ወይም በኦዳ ዛፍ ሥር ወይም መልካ ወርደዉ ሳይሆን (በጊዜዉ እነዚህን ማሰቡም ያስቸግርና ይከበድ ነበርና) ሙስሊሙም፣ ክርስቲያኑም፣ ዋቄፋታዉም በሰልፍ ሆኖ ቤተክርስቲያን እየሄደ ያከብራል። በሰልፉ ላይም የዚያ ወቅት የኢትዮጵያ ባንድራ (አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ) በመሃል ሆኖ ያንዱን የክርስቲያን መልአክ ወይም ቅዱስ ሥዕል (የጣኦት ሥዕል) ስካዉት ተብሎ በየትምህርት ቤቶች የሚቋቋም በአንድ ወይም ሁለት መምህራን የሚመራ የወጣቶች ስብስብ ይታጀብና ይከበራል። ይኸዉ ስካዉት ከሃይማኖት አንፃር ሌላም ሥራ ነበረበት። በትምህርት ቤቶች መግቢያ በራፍ ላይ ቁሞ ሙስሊም ሴቶች ሻሽ ፀጉራቸዉ ላይ አስረዉ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ይቀማ እንደነበር ጎሬ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ፣ አስተማሪ ወይም ሌላ ሠራተኛ የነበረ ሰዉ ያስታዉሳል። ለሻሹ ቅሚያ ይሰጥ የነበረዉ ምክንያት ሴቶቹ የፀጉራቸዉን ንጽህና መጠበቃቸዉን ለመቆጣጠር ነዉ ይባል እንደነበረ፤ ነገር ግን ያልተነገረዉና እዉነቱ ሙስሊም ሴቶች በሃይማኖታቸዉ ሥርዓት መሠረት እጃብ እንዳያደርጉ ወይም ሻሽ እንዳያስሩ ተፅዕኖ ለማሳረፍ እንደነበር ከቆየ ግንዛቤም ቢሆን አስታዉሳለሁ። እሱ ድርጊት ሳይጨመርም ሆነ ሳይቀነስ የኦርቶዶስ ሃይማኖት የበላይነት የፈጠረው ችግር ነበር። ስካውቶቹ በሙስልማን ላይ ተፅዕኖ እንዲያደርጉ የልብ ልብ የሰጣቸው "... ለአገሪቱ አንድነት ለመንግስቱ የፖለቲካ ትግልና ማህበራዊ ኑሮ አሰጊና አስፈሪ የሆነው ይህ የእስላም ሃይማኖት መስፋፋት ነው" ብሎ ለንጉሱ የቀረበው የ1948ቱ የኢትዮጵያ ን.ነ. መንግስት ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር መመሪያ ነው።

ከዚሁ ከሃይማኖት ጉዳይ ሳንወጣ ኢትዮጵያዊያን የአበሻ ኢሊቶችን ሲያሳስባቸዉ የቆየዉና ያለው የኢትዮጵያ አንድነት ችግር በተለይም የመገንጠል ጥያቄን አስመልክቶ አሁንም ልዩነትን እየተገነዘብን እንሂድ ከተባለ ለኤርትራ ቆለኛ ልጆች ወደ በረሃ መሄድና ለኤርትራ ነፃነት ጀብሃን ለማቋቋም መንቀሳቀስና ዱር ቤቴ ለማለት ያበቃቸው፤ መሠረቱን በአፄ

ምንሊክ ከአድዋ ጦርነት በኋላ ከጣሊያን ጋር የተፈራረመው የመረብ ምላሽ ስምምነት ነው ተብሎ በብዙ የኢትዮጵያ ኤሊቶች ሲነገር የቆየው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአፄ ኃይለ ሥላሴ የኤርትራ ፌዴሬሽንን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን፤ በዚሁ ንጉስ በኤርትራ ክፍለ ግዛት ላይ የተሾሙት ባለሥልጣናት ሙስሊማን የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባላት ላይ ሲያደርሱ በነበረዉ ግፍ ሙስሊማኑ በመገፋታቸዉና በመከፋታቸው እንደሆነ ታሪክ በማስረጃ አስደግፎ መዝግቦታል።

ደርግ ማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለም ያነገበ መንግስት ስለነበር የአንዱ ሃይማኖት በሌላዉ ሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ተፅዕኖ የማሳረፍ ዕድል በጣም አናሳ ከመሆኑም በላይ፤ የእስልምና ተከታይ ዜጎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እፎይታን ያገኙበት ጊዜ ነበር። ደርግ በኦርቶዶክሶች ላይ ተፅዕኖ አሳርፏል ቢባል እንኳን ታሪካዊነቱ የጎላ መሆኑን የሚያመላክተዉ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲሶ መሬት ከመንግስት ለመረከብ ከአፄ ይኩኖ አምላክ (1270-1314) ጋር የቅዱስ ቃል ኪዳን የዙፋን ስምምነት ጀምሮ እስከ አፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ፍፃሜ (1967) ድረስ ከሃይማኖት ተቋምነቱ ባሻገር በመደብ ጭቆናዉ ትንተና ዉስጥ ከመሬት ከበርቴ መደብ ጋር ተጣምሮ የአገሪቱን የመሬት ሥሪት ሥርዓት ውስጥ ሢሣ ተብሎ የሚታወቅ የመሬት ባለቤት እንደነበረችና በተለይ ከአማራ በስተደቡብ ባሉት ዜጎች ላይ ታደርስ የነበረዉ የኤኮኖሚ መጥማጭነትን ታሪክ የማይረሳ ብቻ ሳይሆን ታሪክም ሆነ ፈጣሪ ይቅር የማይሉት ድርጊት ነበር። ለንጉሱ እንደቀረበው የ1948ቱ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ማስታወሻ ደግሞ መጤ የሐበሻ ሰፋሪዎችን በደቡቡ ክፍል ለማቆየት ይቻል ዘንድ "በመንግስት ሥራ፣ በጸጥታ ጥበቃ፣ በአገር አገዛዝ፣ በፖሊስነት ወደነዚህ አገሮች (ወደ ተወራሪው ደቡብ ሕዝብ ማለት ነው) የሚሄዱት አማሮች በዚያ አገር ውስጥ ለመኖርና ለመቆየት ምክንያት እንዲኖራቸው **በጠፍነት የሚገኘውን የጋላ መሬት** በየአቅራቢያቸው እንደመንግስት ችሮታ መጠን እንዲያገኙ …" ያዛል። አስገራሚው ነገር ደግሞ ትናንት የሢሣ መሬት ባለቤት የነበረች ተዋህዶ ዛሬም የሕዝብን መሬት በመውረር

ጠበል ፈለቀ፣ ታቦት ወረደ በማለት ቤተክርስቲያን ትገነባለች፣ ማዘጋጃ ቤትን ወይም አስተዳደርን በመተካት የመቃብር ሥፍራን አከራይታ የማይነጥፍ ገቢ ታሰባስባለች፡፡

በሕወሓት/ኢህአዴግ የመንግስትና የሃይማኖት ግንኙነት አስተዳደር በመጠኑ ወሰብሰብ ያለ ይመስላል፡፡ ሕወሓት የአልባኒያዉን ዓይነት ኮምኒዝም እከተላለሁ ይል ስለነበረ፤ ስለሃይማኖቶች ጉዳይ ከደርግ ጋር የሚያመሳስለዉ ገፅታ ነበረዉ፡፡ ከድርጅቱ የፖለቲካ ፕሮግራም አንፃርም የተቀረፀዉ የ1987ቱ ሕገ መንግስትም ሃይማኖትና መንግስት የተለያዩ መሆናቸዉንና መንግስታዊ ሃይማኖትም ሆነ የሐይማኖት መንግስት አለመኖሩን ደንግጓል፡፡ ነገር ግን የእስልምና ሃይማኖትን በተመለከተ የተከተለዉ መስመር ከሕገ መንግስቱ ጋር የተጣጣመ አይደለም፡፡ ምክንያቱም፤ የሌሎች ሃይማኖቶች አባላት መሪዎቻቸዉን በየማመለኪያ ቤታቸዉ ዉስጥ ሲመርጡ ማን እንደተመረጠ እንኳን መስማት የምንችለዉ ከቅርብ ወዳጆቻችን ወይም በአንድ ይፋዊ ንግግር ማድረጊያ ላይ ወይም ከሠፈር ዉስጥ ከሚያገባቸዉ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ወሬዉ እዚያዉ በሃይማኖት ድርጅቱ ግቢ ዉስጥ የሚቆይ ሲሆን፤ በሕወሓት አገዛዝ ሥር ግን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የቀበሌ ካድሬ በተገኘበት ከሃይማኖት ተቋማቸዉ ውጭ ወጥተዉ መሪዎቻቸዉን እንዲመርጡ ተገድደዋል፡፡

እዚህ ላይ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 11(3) አንፃር መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም የሚለዉ አልተከበረም ለማለት እንጂ እስልምና በአመራሩ ወይም አስተዳደሩ ከሌላዉ ሃይማኖት በተሻለ ሁኔታ ዲሞክራሲያዊ ነዉ ወይም ይኼዉ ሃይማኖት ራሱ የሚያስፈራ ገጽታ አለዉ የለውም ለማለት ተፈልጎ አይደለም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እስልምናን ጨምሮ ሁሉንም ሃይማኖቶች ከተደራጁበትና ከሚከተሉት ቀኖናዎቻቸዉ ጋር ማስተያየት እንጂ ከመንግስት እርምጃዎች ጋር በማነፃፀር አንዳቸዉ ከሌላቸዉ የሚሻሉበትን ገጽታ ለመለየት ወይም

ለማሳየት አስፈላጊ ሆኖ አይደለም። የዚህ መፅሐፍ ተልዕኮም አይደለም። በአገራችን ኢትዮጵያ እንኳን ባይሆን በሌላዉ ዓለም በሃይማኖቶች ምክንያት ግጭቶች የሚነሱና ሰላማዊ ሰዎችን ለችግር እያጋለጡ መሆኑን እያየን ሲሆን፤ ዛሬ ላይ የሌላዉ ዓለም ችግር ኢትዮጵያ ዉስጥ ባይኖርም፤ መንግስት በሃይማኖት ጉዳዮች አያያዝ ላይ ጥንቃቄ የጎደለዉ ከሆነ እነዚያ በሌላው ዓለም የምናውቀው ችግር ላለመከሰቱ መተማመኛ የሚሰጥ ስለማይኖር መጠንቀቁ አስፈላጊ ነዉ። ቢያንስ፣ ቢያንስ ከሃይማኖት ነፃ የሆኑ ሰዎች በሃይማኖት ምክንያት ሕይወታቸዉ ላይዛባ ዋስትና ሊኖራቸዉ ይገባል።

የአበሻ ገዥዎች ሆን ብለዉ ሕዝብን ለመጉዳት የክርስትና ሃይማኖትን እንደመሳሪያ ለምን እንደሚጠቀሙበት አይታወቅም፤ ወይም ያንን ለምን እንዳደረጉ መናገር የሚችሉት እነሱ እራሳቸዉ ናቸዉ፤ ወይም ሊጠቀሙበት ያቆዩት ሰነዶቻቸው ነው። ምናልባትም እንደፈጣሪ ትዕዛዝ ሳይሆን እንደተቋም የሃይማኖት ተቋማቱ ስምምነት ስላለበት ነው። አሳዛኙ ነገር በኢትዮጵያ የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት እንቆምለታለን የሚሉት ፍጡራን ሲበደሉ አይተዉ እንዳላዩ መሆናቸዉ ወይም በደሉ ከአምላክ እንደ ታዘዘባቸዉና ስርየቱም ከዚያው ሊመጣላቸዉ እንደሚችል ሲያስተምሩ ተልዕኮአቸዉን በትክክል የተረዱና የሃይማኖታቸዉን ግዴታ በትክክል የተወጡ አይመስለኝም። ምክንያቱም፤ የመንፈስ አባቶች ነን የሚሉትና እናገለግላን የሚሏቸው ሕዝቦች በገዥዎች ሲበደሉ አይተዉ እንዳላዩ መሆኑን ፈጣሪ ከሚያዘዉ በተቃራኒ ስለሆነ ነዉ። ለአብነትም ዶክተር መረራ ጉዲና (ገፅ 11) ስለ1997 ምርጫን አስመልክቶ የዶክተር ብርሃኑ ነጋን ንግግር ጨምቆ ሲፅፍ “የኢትዮጵያ የሃይማኖት አባቶች የሞራል ብቃት የላችሁም፤ በተለይም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የአባቴም የኔም ሃይማኖት ነዉ። በዚህ ሃይማኖት በጣም አፍርበታለሁ። በደርግ ዘመን ግፌኞች በወጣቱ ደም መንገድ ሲያጥቡበት፣ ይህን እግዚአብሔር አይወድም ተው አላላችሁም። አሁንም ጉልበተኞች የሕዝብ ልጆች ደም ሲያፈሱ ተው ለማለት የሞራል ብቃት የሌላችሁ፤ አንድ ጠመንጃ ኖሮት አንድ ሰውን ያልገደለ ተቃዋሚን

ትከሳላችሁ” ብሎ ለተሰበሰቡት የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ፣ የእስልምና፣ ወዘተ የሃይማኖት መሪዎች በመዉቀስ የተናገረዉን በእማኝነት አስቀምጧል። ትኩረቱን በሃይማኖት ዙሪያ አድርጎ Leadership: Living and Serving ብሎ የፃፈዉ ለማ ደገፋ (2012፡ 51) ሕዝብን ማዕከል አድርገዉ የማይንቀሳቀሱ የሃይማኖት መሪዎችን አስመልክቶ “... a leader that fails to focus on people is a miscarriage.” ብሏል። ሕዝብን ያላማከለ አመራር ጭንጋፍ ነዉ ብሏል። ስለ ማርቲን ሉተር ኪንግ “ሕልም አለኝ” በሊሊ ፓተርሰን የተፃፈውና በወጋየሁ በለው ተገኘ የተተረጎመው መጽሐፍ ደግሞ “የሃይማኖት አባቶች ፈላስፎችና ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚጥሩ መሆን አለባቸው” በማለት ቢያስገነዝብም የኢትዮጵያ የሃይማኖት አባቶች በሚያሳዝን ዓይነት ሁኔታ ኢትዮጵያዊያንን ለመከላከልም ሆነ ለማዘመን ገና አልተፈጠሩም። ሲጠቃለል፤ የሃይማኖት ተቋማቱ አንድም በዉስጣቸዉ ሃይማኖታዊ ተልዕኮ የላቸዉም፤ ሰፋ ሲልም እያወቁ እናገለግላለን ከሚሉት ሕዝብ ጋር የማይወጡት ቅራኔ ዉስጥ የሚያስገባቸዉ መንገድ ተከትለዋል። ስለሆነም፤ አንድም በዉስጣቸዉ ቀጥሎም ከሕዝብ ጋር ልዩነት ሊፈጥርባቸዉ የሚችለዉን ድርጊቶች በሃይማኖት ተቋማቱም በመንግስትም የመፍትኼ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል እላለሁ። ምክንያቱም፤ በዚህ አገር የሃይማኖትም ሆነ የመንግስትን ሁሉን ነገር ተሸካሚ ሕዝብ ነዉና።

ከተነሳ አይቀር ስለሃይማኖት ሌላም ነጥብ አነሳለሁ። በሌላዉ ዓለም እንደሆነዉ ሁሉ በኢትዮጵያም ሁለት ዓይነት የሃይማኖት መቀበያ መንገዶች አሉ፤ በመወለድና በመቀበል ወይም በመጠመቅ ናቸዉ። (by birth or by conversion) በዋናነት የኩሽ ሕዝቦች የሆነዉ የዋቀፋና ሃይማኖት በመወለድ የሚከተሉት ሃይማኖት ቢሆንም ከኩሽ የዘር ቤተሰብ ያልሆነም ቢከተለዉ ችግር የሚፈጥር አይሆንም። በኢትዮጵያ የዋቀፋና ሃይማኖት ተከታዮች ብዙዎች ከኩሽ የዘር ግንድ የሚመጡ ሲሆኑ፤ ከነዚህም ዉስጥ የኦሮሞና የሲዳማ ሕዝቦች ተጠቃሽ ናቸዉ። ሌሎችም ይኖራሉ። እንደዋቀፋና ሃይማኖት ተከታዮች እምነት በዋቃ

(እግዚአብሔር) እና ዋቀፋታ መሀከል ሌላ የሚመለክበት ነገር ወይም የሚያማልድ ሌላ 'አምላክ' የለም። ዋቃ (እግዚአብሔር) ፈጣሪ፤ ዋቄፋታ ፍጡር ናቸዉ። ዋቃ አባት፣ እናት፣ አጎት፣ አክስት፣ ወንድም፣ እህት፣ አማት፣ ምራት፣ የሉትም። አይበላም አይጠጣም። አይራቆትም፣ አይለብስም። የሚኖረዉ ከፍጡራን ጋርና በዉስጣቸዉ (ልባቸዉ) ዉስጥ ነዉ። ከሰጠ ሰጠ፤ ከነሳም ነሳ። ሁሉንም ድርጊቱን በበጎነት መቀበል ነዉ። "ነገሩ ሁሉ ለበጎ ነዉ" እንደሚባለዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማለት ነዉ። እንደዋቀፋታ እምነት ዋቃ ከለሙኑት ይቅር ባይነቱ ወደር የለዉም። በኦሮሞ የሃይማኖቱ ተከታይ ሕዝብ ዘንድ ፍጡራንን መበደል ፈጣሪን የመበደል ያህል ነዉ። ኦሮሞ ሲበደል ለብቻው ወጥቶ ወይም የቤተሰቡን አባላት አስተኝቶ አንዳች ድምፅ ሳያሰማ ለፈጣሪው ይነግራል። በዋቀፋና እምነት ከፈጣሪ ዕውቀት ውጭ የሆነም ሆነ የሚሆን ነገር የለም። በአጭሩ የተፈጥሮ ሃይማኖት፣ ዋቀፋና (religion by birth) ይህንን ይመስላል። በነገራችን ላይ ሃይማኖት በመወለድ ያለዉ በዋቀፋናና በተከታዮቹ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ የአይሁድ እና የሕንዱ ሃይማኖቶችን ከተወላጆቹ ውጭ ማንም በዘፈቀደ የማይከተላቸዉና በመወለድ ብቻ የሚከተሉት ሃይማኖቶች ናቸው።

በብዝሃነት ዉስጥ ያለዉን ልዩነት እንደ ተፈጥሮአዊ ፀጋ የማይቀበሉ የአበሻ ተወላጆችና አሚቻዎቻቸው የዋቄፋና ሃይማኖትን አእምሮአቸዉ በትክክል እያወቀ ላለማወቅ ያንገራግራሉ። ዋቄፋታ ጎረቤታቸዉ እያለና ዓመታዊ የእረቻ በዓልም እየተከበረ ዋቀፋናን እያወቁ አያዉቁትም። እንዲያዉም አንዳንዱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የራሳቸዉን ቅዱስ የሌላዉን እርኩስ አምልኮ ይቆጥሩት ነበር። ለዚህ አቋማቸዉ ሁለት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ። አንዱ የራሳቸዉን ሃይማኖት የተፅዕኖ አድማስ ከፍ ለማድረግ ሲሆን፤ ዋነኛዉና ትልቁ ግን የደቡብ ሕዝቦችን ማንነትና ሃይማኖታቸዉን በማጠልሸት የዝርፊያቸዉን ዕድሜ ለማራዘም አስበዉ ነዉ። በማስረጃ ላስደግፍ! ከዮሐንስ "ያልተጠመቀ አገሬን ይልቀቅ" ግድያ እና ከምንሊክ የጦር ዘመቻ "ማርያምን አልምርህም" አፈና የተረፉት ሐበሻ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን በኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ደግሞ ለባሰ

ስልታዊ ጥቃት ተጋልጠው እንደነበር ከላይ የጠቀስኩትና ለንጉሱ ቀርቦ የነበረው የንጉሴ ነገስቱ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ማስታወሻ ያስረዳል። ማስታወሻው እንደሚለው “የኢትዮጵያ ንጉሴ ነገስት መንግስት ግዛት ሕዝብ በሶስት የሃይማኖት ግንድ እምነቱ የተከፈለና በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ አገር አረማዊ አዋማ የሚበዙበት ስለሆነ ለአገሪቱ አንድነት ለመንግስቱ የፖለቲካ ትግልና ማህበራዊ ኑሮ አስጊና አስፈሪ የሆነው ይህ የእስላም ሃይማኖት መስፋፋት ነው። [ስለሆነም] ለፀጥታ ዘበኛነት … የሚቀጠሩት ክርስቲያን፤ አማርኛ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ያላቸውና አማሮች እንዲሆኑ ስለሚያሻ ጥንቃቄ እንዲደረግ ያስፈልጋል” በማለት ንጉሱ ዜጎቼ በሚላቸው መሀከል ከፋፋይ ፖሊሲ ተከትሏል።

ሌላዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የሃይማኖት ዓይነት በመለወጥ ወይም በመቀበል (religion by conversion) የሚገኝ ነዉ ብያለሁ። በአገራችን እስልምናና ክርስትና ከብዙ ቅርንጫፎቻቸዉ ጋር በዚህ ይታወቃሉ። ክርስትና ከ4ኛዉ መቶ ዓመት ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባና እስልምናም በ7ኛዉ መቶ ዓመት እንደገባ ይነገራል። ከነዚያ ጊዜያት ወዲህ ኢትዮጵያዊያን እንደተመቻቸዉ ወይም እንደተገደዱ ከአንዱ ሐይማኖት ወደሌላ ሲቀያይሩ የቆዩና ዛሬም ሲቀያይሩ የሚታይ ክስተት ነዉ። አንዱ የቀድሞ ሃይማኖቱን ትቶ ወደ ሌላኛዉ ሃይማኖት ሲሄድ፤ የተቀበለዉ ወገን ሃይማኖት አሸናፊ የመሆን ስሜት ይሰማዋል። ተለዋጩ ሰዉ ራሱ አንድም የተለየ ጥቅም ለማግኘት አሊያም በሰማይ ቤት ልዩ ሥፍራ የሚይዝ እየመሰለዉ በንቃት ላይ ያልተመሠረተ በቤተዘመድ ወይም በሌላ ድርጅት ተፅዕኖ ሥር የሚፈጽመዉ በጣም ጥንቃቄ የጎደለው ነገረ ሥራ ነው። ቢሆንም ግን ኢትዮጵያዊያን እንደሌላው አፍሪካዊ ማንኛውም ሃይማኖት ከቅኝ ገዥዎች በግዴታ ያልተጫነባቸው መሆኑን በኩራት ይናገራሉ። ምንም ሆነ ምን የሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች የእምነትን ውስጣዊ አስገዳጅነት ወደ ጎን በመተው ተከታዮቻቸውም ሆኑ ሌሎች ወገኖች ሲበደሉ ዝም ብለው በማለፋቸው ከወቀሳ አልተረፉም።

ከዚሁ ከሃይማኖት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጠርቶ ያልወጣዉ ሃይማኖትና እምነት አንድም የሚሆኑበት ወይም የተለያዩ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዳለ ነዉ። በተለይ፤ በኢትዮጵያ ስለበዓላት አበዛዝ በኋላ የምንመለስበት ሆኖ፤ በነዚህ በዓል ቀናት የእንኳን አደረሳችሁ ምልዕክት፤ ሃይማኖትንና እምነትን ሲያምታታ ይዘወተራል። እንዲዚህ የተምታቱ ነገሮች ጠርቶ መዉጣት አለባቸዉ። አንድ ሰዉ ሃይማኖት ኖሮት ቀኖናዉን ሺህ ጊዜ ቢያነበንብም ትንሽ እንጥፍጣፊ እምነት በልቡ ዉስጥ ከሌለ ሃይማኖቱና እምነቱ የተለያዩበት ሲሆን፤ ከዚህ በተቃራኒዉ ግን ሃይማኖቱ በጠንካራ እምነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ፤ ስለሚበላውና ስለሚጠጣው ብቻ ሳይሆን ስለሚናገረው ጭምር በጣም ጠንቃቃ ከሆነ ሃይማኖቱም እምነቱም አንድ ናቸዉ። ቤኒቶ ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን እንዲወርና ምኒልክ ኦሮሞን እንዲጨፈጭፍ ምርቃት የሰጡት እንደቅደም ተከተላቸው የካቶሊክና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ግለሰቦች ከሃይማኖት በዘለለ ቅንጣት ታክል እምነት በውስጣቸዉ አልነበረም ለማለት ይቻላል። በባሪያ ሽያጭ ዘመን ወጣት ጋናዊያንን መመለሻ እስከ ሌለው (a point of no return) ወደ መርከብ መጫኛ ጫፍ ድረስ ሸኝተው ቅባ ቅዱስ አቅምሰው ወገኖቻቸውን በመሸጥ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ‘የሃይማኖት መሪዎች’ የሚባሉ ነበሩ። ዶ/ር አምባቸዉ ከበደ <u>በአፍሪካና አምባገነን መሪዎች</u> ትርጉም መጽሐፉ (1984፡ 139) ሃይማኖት ላይ ተመርኩዘው የሚፈጸሙ ጭፍጨፋዎችን አስመልክቶ እንደፃፈዉ “በአፍሪካ የክርስትያኖች ቁጥር የመብዛቱን ያህል የእምነታቸዉ ጥንካሬ ጥያቄ የሚያስከትለዉ ነዉ።” በማለት ሐሳቤን ያጠናክርልኛል። ይህ ብቻም አይደለም፤ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት አስተምሮአቸዉ ዕድገት ተኮር አለመሆኑን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም <u>አዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ</u> ተብሎ በተፃፈዉ መጽሐፋቸዉ ገጽ 31 ላይ “በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ማተኮራቸዉና የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የሚረዳ ዕዉቀትን ባለማስገኘታቸዉ፤ ትምህርታቸዉም አእምሮን ከማስፋት ይልቅ የሚያጠብ በመሆኑ ሊወቀሱና የመክሸፍ ምንጭ ሆነዋል” በማለት የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ለዕድገት

የተሟላ ተልዕኮ የሌላቸዉ ተቋማት እንደሆኑ አመልክተዋል።

እንግዲህ፤ ስለተፅዕኖና ቅራኔ በምናስብበት ጊዜ አገርን ማዕከል በአደረገ ሁኔታ ከአፍራሽነቱ ባሻገር ያሉብንን ችግሮች አብጠርጥረን ለመረዳት ካለን ግንዛቤ ጋር መሆን አለበት። ስለኢትዮጵያዊያን አብሮነት ስናስብ ደግሞ ከሆድና ቃላት ባሻገር ጥልቅ በሆነ ግንዛቤ ማሰብ እንደሚያስፈልገን ለአፍታም ቸል ማለት የለብንም። እዚህ ላይ ትልቅ ጥያቄ ሆኖ መነሳት ያለበት ኢትዮጵያዊያንን አንድ ላይ አስተሳስሮ ያቆየና አስተሳስሮ ሊያቆይ የሚችል የጋራ የሆነ ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ወይም እሴቶች ምንድን ነዉ/ናቸዉ? የሚል ነዉ። ተቃርኖስ? ታሪክ፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወይስ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት? እነዚህ እሴቶች ለፓርቲ ፖለቲካችንስ ምን ያህል ተግዳሮትን ፈጥረዋል ብለን በንፅፅር መመልከቱ ይበጃል።

ለፓርቲ ፖለቲካችን አለማደግ ተግዳሮት ናቸው የሚባሉትን ሰፋ አድርገን ስንመለከት፤ ትስስራችንም ሆነ ልዩነቶቻችን አንዱ ታሪክ ነዉ የምንል ከሆነ ተቃርኖው ያለው በባለሦስት ሺህ ዘመንና በባለአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት ታሪክ መሃከል ያለዉን ክርክር በአሸናፊና ተሸናፊ ወይም በዜሮ ድምር ፖለቲካ ሥነ ልቦና ሳይሆን ከጋራ ድል አድራጊነት አንፃር መታየት ይኖርበታል። ባህል ከሆነ የዘር ሐረጎቻችን እንደየመጡበትና እንደ አኗኗራችን ሁኔታ ሊያመሳስሉንም ላያመሳስሉንም የሚችሉ እሴቶች እንዳሉ እንረዳ። ሃይማኖት ያስተሳስረናል እንዳይባል ድብቅ ገጽታዎቹ ሳይገለጡ፤ በልዩነቱ ከሚጠቀሱት አገሮች ዉስጥ ቀዳሚዉን ተርታ የምንይዝ ይመስለኛል። ሌላዉ ቀርቶ ለፈጣሪ አደሩ የሚባሉ የሃይማኖት መሪዎች ሳይቀሩ መንፈሰ ጠንካራ ባለመሆናቸዉ ታማኝነታቸዉን ለአገሪቱ ገዥዎችና ለፋሽስት ኃይል ተንበርክከዉ ሕዝቦች እንዲገዙ ሰብከዉ እንደነበረ በትርክቱ ታሪካቸው ዉስጥ የተመዘገበ ነዉ። ስለዚህ ከማስተሳሰሩ ይልቅ በጥርጣሬ መሳተፉን የሚመርጡ ብዙዎች አሉ። የቋንቋ ልዩነታችን የብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች ቁጥር ያህል ነዉ ባይባልም ከግማሽ በላይ ነዉ። ለዚያውም ደግሞ የሐበሾቹ አማራ እና

ትግሬ ቋንቋዎች የበላይነት እንዲይዙ የቅኝ ገዥዎችን ዓይነት የሥነ ልቦና ተፅዕኖ ሲያሳርፉ ሌሎቹ ጠባብ ተብለው ይፈረጃሉ። ለይስሙላ የብሔር በሔረሰቦች ቋንቋዎች ይከበራሉ፣ እንዲበለፅጉም ይደረጋል በተባለበት አገር ውስጥ፤ እንደ ገመቹ መገርሳ (ዶ/ር) የቪድዮ አገላለፅ "ትግራይ ክልል ውስጥ በትግሪኛ፣ አማራ ክልል ውስጥ ደግሞ በአማርኛ ይዘመራል፣ ይዘፈናል፣ ይለቀሳል፣ ይቀደሳል። ወደ ደቡብ በተለይም ወደ ኦሮምያ ክልል ሲመጣ በአፋን ኦሮሞ እነዚያን ድርጊቶች መፈጸም ጠባብ ያስብላል።" ቋንቋን መሠረት ያደረገ ፀያፍ ፍረጃ ከላይ እንደተረዳነው ሆኖ፤ ሥነ ልቦናዊ አመለካከታችን ያስተሳስረናል እንዳንል ደግሞ አንዱ አስገባሪ ብዙሃኑ ገባር በሆኑበት አገር ዉስጥ ስለነበርን እንዴት ተደርጎ ተመሳሳይ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት እንዲኖረን እንደምንሻ ብናስብም መሠረቱ አልተገነባም። ቀድሞ አስገባሪዎች ያደረጉት እንደነበረ ሁሉ ዛሬም ድረስ የገዥዉ ፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ የሆነ ሰዉ ድምፁን ከፍ አድርጎ ቢያወራ ወሬዉ ሁሉ የአሸናፊነት ሥነ ልቦናዉና መንፈሱ ምን ያህል እንደደነደነ መገመት ይቻላል። ከዚህ ሰዉ ጋር ሁሉም ዜጎች የጋራ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት ይኖራቸዋል ብሎ መጠበቅ የማይመስል ነገር ነዉ። ምናልባት የኋላቀርነትና ረሃብተኛነት ሥነ ልቦና ያስተሳስረናል ካልተባለ በስተቀር፤ ይህ ነዉ ኩራታችን፣ ያን ያህል ነዉ መተሳሰባችን የምንለዉን ብናፈላልግ እስኪናገኝ ድረስ ብዙ ሊያደክመን ይችላልና ብንተወው ይመረጣል የሚሉ ዜጎች ይኖራሉ።

ከፓርቲ ፖለቲካ አንፃር ለአመለካከት ያለን መሠረታዊ ዕውቀትና አተጋባበራችን ለየቅል እየሆነ ስለተቸገርን አሁንም መተዉ ይመረጣል። አመለካከታችን ለአገርና ሀገረ መንግስት ግንባታ በሚያመች ሁኔታ ይቀረፅ ዘንድ ምሁራኖቻችን የሚያዉቁትን በማስተማር መልካም ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሆነዉ ለመገኘት ያላቸዉ ተነሳሽነት አናሳ ይሆናል፤ ወይም ለሆድ ጥቅም የተገዙ እየሆኑ ስለምንቸገር፤ የሐቀኛ ምሁር አልባ አገር ነን ባልልም ወኔ-ቢስና ሆድ አደር የሆኑት ምሁራን ለራሳችንም ለአገራችንም እንዳንሆን እንቅፋትነታቸዉ ዛሬም ቀላል አልሆነም። ጥቂት የማይባለው የተማረው ኢትዮጵያዊ ከፊውዳል አስተሳሰብ ሳይላቀቅና

የሰለጠነ ፖለቲካ ማራመድ እስካልቻለ ድረስ የብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ሕይወት ሊለወጥ አይችልም። በሌሎች አገሮች ሁሉ እንደሚሆነው ሁሉ የተወሰነው የኢትዮጵያ የተማረ የሚባለው የሕብረተሰብ ክፍል የዕድገት ሥርጭቱ በትልልቅ ከተሞች አከባቢ የተወሰነ ሲሆን፤ እሱም ከሕዝባዊ ወገንተኝነትና የሙያ ሥነ ምግባር ድህነት የተነሳ ኢ-ፍትሐዊ የሆኑ ሕጎች ሕዝብ ላይ ሲጫኑ አንድም ሳይቃወሙ በቸልተኝነት ያልፉታል ወይም በመናኛ ጥቅም በመደለል የሕዝብን መብትና ጥቅም አሳልፈው ለጥቂት የገዥ ቡድን አባላት በመስጠት ክፉ ምሳሌ (sinister role) ይጫወታሉ። በንጉሱ ጊዜ ፀሐዩ ንጉስ፣ በደርጉ ጊዜ ሐቀኛ እና ኮሚኒስቱ መሪ፣ በኢህአዴግ/ብልፅግና ጊዜ የአፍሪካ ዕንቁ መሪ/ኢትዮጵያዊ ሙሴ በማለት ያልተገባ ሙገሳ ያዥጎደጉዳሉ። ለሕዝብ ነፃነት የሚነድዱትን ፈቃደኞችን ግን በነገር ያንዳጥጣሉ። የአንድ አገር ሕዝብ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ቢያንስ በሦስቱ ወይም ከሦስት በላይ በሆኑ ነጥቦች ካልተስማማን ለአንድ ዓላማ ስለመቆማችን መተማመኛዉ ምን ሊሆን እንደሚችል ያነጋግራል። እንደ ጎረቤት አገር ሶማሊያ አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት ኖሮአቸዉ (የዉጪ ኃይሎች ተፅዕኖ እንዳለ ሆኖ)፤ የውጪ ሸር ተከላክሎ በሰለጠነ ሁኔታ የሚመራቸዉ ፓርቲ/መንግስት ላለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ሳይኖራቸዉ ተበታትነዉ ከመቅረታቸዉም በላይ የጉልበተኞች መሳሪያ መፈተሻና የወታደሮች ቁጥር ማቀናነሻ መድረክ ሆነዉ ቀርተዋል። ኢትዮጵያዊያን ለንደዚህ ዓይነት ችግር ላለመዳረጋቸዉ ዋስትና የሚሰጥ ማን እንደሆነ ማወቅ የሚችሉት ኢትዮጵያዊያን ወይስ ሌላ ኃያል አገር መሆኑን መወሰኑ ለጊዜዉ ሊያስቸግር ቢችልም፤ የፓርቲ ፖለቲካው የሕዝብ አስተዳደር በምርጫ ላይ እንጂ በጡንቻ ላይ የተመሠረተ ከሆነ የመንግስትና ሕዝብ ወይም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ ወደ አፍራሽነት ያደላል። ምክንያቱም፤ የማንንም ቀልቀሎ ማንም መሸከም አይፈልግም፤ አንዱ ፓርቲ ያወጣዉን ሕግ ያወጣዉ ፓርቲ እራሱ የማያከብር ከሆነ ሌላዉ የመሸከም ግዴታ አይኖርበትም።

**ከመመሳሰሉ በላቀ ሁኔታ ሰፊና ጥልቅ መሠረት ያለው የአገራችን**

**ሕዝቦች የልዩነት** ጉዳይ (የባህል፣ የታሪክ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የሥነ ልቦና) ብዙም ትኩረት ሳይሰጥበት አይነኬ ሆኖ በመቅረቱና ብዙዉን ጊዜ የግዴታ አንድነት በጫና የበለጠ ትኩረት እንዲያገኝ በመደረጉ፤ በሚደረጉ አንዳንድ ስብሰባዎች ላይ ሳይቀር ከስምምነት ሳይደረስ የሚወጣበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በ1994 ይመስለኛል ፒያሳ ብሔራዊ ሎቶሪ አዳራሽ ዉስጥ በተጠራዉ አንድ ስብሰባ ላይ ፕሮፌሴር መስፍን ወልደማሪያም ሐሳባቸዉን በአማርኛ ቋንቋ ለመግለፅ ፈልገዉ ይመስለኛል፤ ገና ሲጀምሩ "እንግዲህ ሁላችንም አበሾች ነን" ብለዉ ተናግረዉ ሳይጨርሱ ያጋጠማቸዉን የወጣቶች ጩኸት በቦታዉ የነበረ ሰዉ ያስታዉሳል። እሳቸዉና ደጋፊያዎቻቸዉ የሆኑ፤ በዚያን ጊዜም ሆነ ዛሬ በጎሳ ፖለቲካ የተለከፈ ወጣት ነዉ ያንን ያደረገዉ ብለዉ ይኮንኑ ይሆናል። የልዩነት፤ ለዚያዉም የአስከፊነቱ ገጽታ፤ እነሱ እንደሚገልጹት ልበልና የጎላ ልዩነት እንደነበረ አስረጂ ነበር። ነገር ግን ያንጊዜም ሆነ ዛሬ አበሻ ያልሆኑ ሰዎች፤ ዛሬም አበሻ አይደሉምና ሰዎች ያልሆኑትን እንዲሆኑ መገፋፋት ተራ ስድብ ነዉ፤ አለፍ ካለም ኢትዮጵያን አፍራሽ ወንጀል ይሆናል።

በሕዝብ አስተዳደር ዉስጥ ከዘር ግንድም ሆነ ከሃይማኖት አኳያ የሚከሰቱ ቅራኔዎችን መረዳትና በመቻቻል ማስተናገድ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስገነዝቡ ነገሮች ብዙ ሲሆኑ፤ በፓርቲ ፖለቲካ ላይ የሚሰሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ ከሃይማኖት ጋር ስለሚነሱ ችግሮች ለአፍታም ቢሆን ቸል ማለት እንደሌለባቸዉ፤ ዛሬ ኢትዮጵያችን ዉስጥ ቀርቶ ሰለጠኑ በሚባሉ የአሜሪካና የአዉሮፓ አገሮች ዉስጥ ሳይቀር እንዲዚህ ዓይነት ልዩነቶች ምን እየፈጠሩ እንደሆነ ከራስ ጋር ታግሎ አምኖ መቀበል የግድ ነው። እነዚህን የልዩነት ጉዳዮች ያነሳሁበት ምክንያት ዛሬ ሰለጠኑ በሚባሉት አገሮች ዉስጥ ጭምር ከላይ የተጠቀሱ ነገሮች የቅራኔ መነሻ ወይም የቆየ ቁርሾ መቀስቀሻ ሆነዉ ሕዝብን ከሕዝብ ያፋጃሉ፤ ቅርስና ሥልጣኔን እያወድሙ ይገኛሉ።

በሌላም በኩል ያለፍንባቸውን ሺህ ዓመታት ጊዜ ትተን ዛሬ በ21ኛው

መቶ ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያችን ውስጥ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለዓለሙ ጉዳዮች ብዙም ተጋላጭነት ሳይኖረን ሰለጡኑ የሚባሉ ሕዝቦች በየአገሮቻቸዉ ፋናቲክ (የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና ሌሎች አክራሪ አመለካከት) የሚባለዉን አኗኗር ዘይቤ ከተዉት ወይም ካለፉት ጊዜዉ ብዙ የሰነበተ ነው። ነገር ግን እነዚያ ሰለጡኑ የሚባሉ ሕዝቦች የጥቅም ግንኙነት ካላቸዉ አገሮች ጋር ሳይቀር ተያይዞ አክራሪ ወይም ተስፈንጣሪ ችግር የሚመጣባቸዉ ከሆነ የሚከተለዉ መዓት አደጋ ቀላል የሚባል አይደለም። የሰለጡኑ ሕዝቦች ፋናቲክ የሆነዉን አኗኗርና አሰራር የተዉት ወይም ያለፉት እንዲሁ ቀላል በሆነ ዘዴ እና ጥራቱ በዘቀጠ የትምህርት ዓይነቱ ሳይሆን የተሻለ ነው የሚባለውን ትምህርት ለሕዝቦቻቸዉ በማዳረስ ነዉ። ትምህርት ካልተስፋፋ የሰው ልጅ ኑሮ ከሌሎች እንስሳት የሚለየው በትንሽ ነገር ብቻ ይሆናል። ትምህርት ከተስፋፋና ሥልጣኔ ከሰረፀ ሰዉ ከእንስሳነት ሕይወት ይላቀቃል። አንድ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል፤ ምንም እንኳን በቀለም ላይ የተመሰረተዉ ከመናቆር እስከ መጋዳደላቸው እንዳለ ሆኖ አሜሪካኖች በእግዚአብሔር እንታመናል *(In God We Trust)* ወይም አሜሪካ ለዘላለም ትኑር ሲሉ ከመፅሐፍ ቅዱስ ወይም ከቁራን የቀዱት ሳይሆን፤ የጋራ ግንዛቤ ፈጥረዉ የጋራ እሴታቸዉ በማድረግ የሰለጠነ የሕይወት መመሪያ ስላደረጉት ነዉ።

እዚህ ላይ ማንም ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የፓርቲ ፖለቲካን የሚያራምድ ሰዉ ወይም ቡድን ከአንድነቱ ጎን ለጎን ለልዩነትም ቦታ መንፈግ የለበትም ማለቴ ሳይዘነጋ፤ የቅራኔ ምንጭ ከሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች ዉስጥ አንዳንዶችን በማጠናበር፣ ሌሎችን ደግሞ ባለማወቅ ኢትዮጵያዊነትንና አበሻነትን እየለዋወጡ ወይም እየቀላቀሉ መጠቀም የማንነት ቀዉስ ዉስጥ የሚያስገባ መሆኑን በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል። ሊታወቅ የሚገባ ነገር ቢኖር ግን ከፍላጎት ባለፈ መሆን ወይም ማድረግ ስለሚፈልጉት ነገር ነባራዊ ሁኔታን ቅድሚያ ሰጥተዉ መፈተሽና ማወቅ ይገባል። ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ኢትዮጵያዊ የዜግነት ስሜታችን ሊጎልብት የሚችለዉ የአበሻነት ካባ ስለለበስን ሳይሆን የወንድማማችነት/እህትማማችነት፣ ነፃነትና የወዳጅነት ሥነ ልቦና

በዉስጣችንና በመሀከላችን ሲሰርፅና የሥራ ወዳድነት እሴትና ባህርይን ገንብተን በጋራ በመስራት ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የምትሆን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት ስንችል ብቻ ነዉ። ካልሆነ ግን ማደግ የሚገባውን የራስን ፍልስፍና ትቶ ወይም ረስቶ የሌላውን አንጠልጥሎ መሄድ ለባርነት እንደሚዳርግ ሊሰመርበት ይገባል።

የቅርብ ጊዜያት ክስተትና የኢትዮጵያዊያን ልዩነት የሚያሳዩበት፤ እንዲሁም የፓርቲ ፖለቲካ እንቅስቃሴን ከሚገቱት አንዱ የምንተዳደርበት የመንግስት ቅርፅ ላይ የምናደርገዉ ልዩነት ነው። የአመላካከት ልዩነት የአንዱ ግለሰብ፣ ቡድን፣ ፓርቲ አመለካከት ሊሆን ይችላል እንጂ ብሔር/ብሔረሰብ ወይም ጎሳ/ዘር ተብሎ በአገር ጠላትነት በሚያስፈርጅ መልኩ መሆን የለበትም። ልዩነት እንኳን ቢኖር ፍትሓዊ ተጠቃሚነት ያልተመዘገበበት የአሃዳዊነትና የፌዴራላዊነት ደጋፊዎች ልዩነት ነዉ። ታሪክ ቀመስ ከሆነ መነሳት እንችላለን። ለምሳሌም አርስቶክራሲ እና አዉቶክራሲ የሆኑ የመንግስት ዓይነቶች በአብዛኛዉ አገሮች ለማለት ይቻላል፤ አሃዳዊ የመንግስት ቅርፅን ሲመርጡ፤ አንዳንድ ኦሊጋርኪና ሊቤራል የመንግስት ቅርፆች ደግሞ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅን ሲመርጡ ይታያሉ። እዚህ ላይ መጠንቀቅ የሚያስፈልገዉ አሃዳዊ የመንግስት ቅርፅን የሚመርጡ መንግስታት ወይም ፓርቲዎች ሁሉም ዴሞክራሲያዊያን አይደሉም፤ ወይም ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅን የሚመርጡ ደግሞ ሁሉም የግድ ዲሞክራሲያዊያን ናቸዉ ለማለት ተፈልጎ አይደለም። ፌዴራላዊ ሆነዉ አምባገነናዊ የመሆን አጋጣሚዉ እንዳለ ሁሉ አሃዳዊ ሆነዉ ዲሞክራሲያዊ የመሆን ወይም የዴሞክራሲ ባህርይ የሚላበሱ አገሮች የመላበሳቸው አጋጣሚዉም የዚያን ያህል ሰፊ ነዉ። በመሠረቱ ዲሞክራሲያዊ ወይም አምባገነናዊ መሆን አሃዳዊ ወይም ፌዴሬላዊ ሥርአት ለመከተል እንደቅድመ ሁኔታ ሊወሰዱላቸዉ የሚገቡ ነገሮችም አይደሉም። ከልዩነትም ሆነ ከአሃዳዊነት የሚመነጬት ችግሮች በአብዛኛዉ እነዚህ ሥርአቶች ስለተመረጡ ሳይሆን ከመሪዎቻቸዉ ብስለትና ቀናነት ማጣት በመነጨ ፍትሓዊና አሳታፊ ካለመሆን የተነሳ ነው። ምክንያቱም፤ በአሃዳዊነትም ሆነ በፌዴራላዊነት

ዉስጥ ቀናነት የሚጎድላቸዉ ሕሊናዎች በምንም ዓይነት መመዘኛ አርቆ አስተዋይ፣ አሳታፊና ዴሞክራሲያን ሊሆኑ አይችሉም፤ ዴሞክራሲያዊ ካልሆኑ ደግሞ የዜጎችን ሁለንትዊ ስብዕና ሊያረካ የሚችል ሥርአትም መገንባት አይችሉም።

ከታሪክም ሆነ ከተግባር እንደምናየዉ አሃዳዊ የመንግስት ቅርፅ ይከተሉ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግስታት በ1983 ካከተመላቸዉ በኋላ ብዙም ከአሃዳዊ ሥርአት ያልተለየዉ በተለይም በተግባር ራሱን በፌዴራላዊነት ሊከስት ያልታደለው ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅ በኢህአዴግ እንደ አንድ ምርጫ ቀርቧል። አሃዳዊ የአስተዳደር ቅርፅ ሰንሰለቱን ከላይ ጀምሮ እስከታች ድረስ በጂኦግራፊያዊ አከላለል የሚያስተዳድር ስለሆነ፤ ተመሳሳይ የሆኑ ሕዝቦች ሕዝባዊ ጉዳያቸዉ ምንም ያህል ተመሳሳይ ቢሆንም፤ አንድ ላይ አይሰተናገዱም። በተለይ በአገራችን ተግባራዊ ይደረጋል የተባለዉ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅ የአንድን ሕዝብ ጉዳይ (ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ መልካ ምድራዊ አኗኗር፣ ሥነ ልቦናዊ አመለካከት) ግምት ዉስጥ አስገብቶ ተመሳሳይ የሆኑ ሕዝቦች የልማትና የአስተዳደር ጉዳያቸዉ በአንድ የግንኙነት መስመር የሚስተናገዱበት ይሆናል ብቻ ሳይሆን የሕይወት ዋስትናም ይሆናቸዋል ተብሎም ስለታመነበት ነው። ላቮስ አላን (2002፡ 44) በጥናቷ ዉስጥ ስለፌዴራሊዝም ፋይዳ ሲትገልጽ "Federalism is a good way of sharing power; it gives the people opportunities to govern themselves and it could help to speed up the developmental and administrative efforts." ብላለች። በአሃዳዊነት ግን በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይነት ቅቡልነት የሌለዉ አንድነት ገንኖ የሚታይበት ስለሆነና አገሪቱ የግድ ማስተናገድ ያለባት ልዩነት (diversity) ይዋጣል፣ ወይም ሊስተናገድ አይችልም። የአንድ ብሔር እሴቱ ይኮስሳል፤ የሌላው ገንኖ ይወጣል። ከዚህም የተነሳ የጋራና የግል አስተዳደር (self and shared rules) የሚባሉ ቦታ ያጡና ያንድ ክልል ወይም ያንድ ክልል ሕዝብ የጥቂት ኤሊቶች ጠባብ ፍላጎት በሌላዉ ሕዝብ ጥቅምና ሕልውና ላይ ጫና ይፈጥራል። ዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ድልድል ወይም ክፍፍል ይዳፈናል። ስለሆነም ኢትዮጵያን በመሳሰሉ

አገሮች በተለይም የብሔር ብሔረሰብ እስር ቤት በሚባሉት አገሮች ዉስጥ ፌዴራሊዝም በአሀዳዊነት ሥር ላጋጠሙ የፖለቲካ በሽታዎች ፍቱን መድሃኒት ነዉ ተብሎ ይታመናል። ከዚህ የበለጠ ደግሞ የተለያዩ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና የመሳሰሉ ልዩነት ያላቸውን ሕዝቦችን ወርረዉ አንድ አገር፣ አንድ ባንዲራ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ሚስት፣ ወዘተ የሚባሉት ከማስገደድ ይልቅ በመደራደርና በስምምነት ላይ በተመሠረተ አኳኋን አገራዊ አንድነት ማስጠበቁ የበለጠ ተመራጭነት ይኖረዋል። ምክንያቱም፤ በልዩነት አንድነት የፈጠሩና የዕድገት ደረጃቸዉም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ አገሮች ብዛታቸዉ እየጨመረ በመሄድ ላይ መገኘቱ ለኢትዮጵያ ትምህርት ይሆናል።

በወረራ የተያዙና በጉልበት አንድነት ሥር ሲተዳደሩ የነበሩ ሕዝቦች (empire states) በአንድ አጋጣሚ ፌዴራሊዝምን ቢመርጡ ወይም እወክላቸዋለሁ የሚለው አንዱ የፖለቲካ ቡድን ፌዴራሊዝምን ስለመረጠ፤ በተቃራኒውም ቀድሞም ሆነ በወቅቱ የአሃዳዊነት የመንግስት ቅርፅን የመረጡ ቡድኖችና ግለሰቦች ደግሞ በፌዴራሊዝም ጦስ የሕዝቦችና የአገር አንድነት መላላት ብሎም መበታተን እንደሚፈጠር ሆኖ ሊያሳስባቸው ወይም ሊያስፈራቸው አያስፈልግም። በጥልቀት ሲታሰብ ግን አንድ የፖለቲካ ማህበር ወይም ፓርቲ አሃዳዊ ወይም ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅን መምረጡ በራሱ ችግር ሊሆን አይችልም። ይልቅስ ችግር የሚሆነዉ የተመረጠው ሥርአት ዲሞክራሲያዊ አለመሆን ጉዳይ ላይ ነዉ። ወይም የተመረጠው የአስተዳደር ዘይቤ አሃዳዊም ሆነ ፌዴራላዊ ትክክለኛ የመንግስት አመራር ከሌለ በስተቀር የሕዝብን ፍላጎት ማሟላት አይቻልም። ሊዘለል የማይችል ነገር ቢኖር ግን ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ሕብረ ብሔራዊ አገሮች ውስጥ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ ወዘተ እንዳይደፈጠጡም ሆነ ዕድገት እንዲኖራቸው ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ከአስፈላጊነትም በላይ ግዴታ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅ ከአሃዳዊነት

የሚመረጥበት ምክንያት ቢኖር፤ ብሔር ብሔረሰቦችን እስረኛ ሲያደርግ የነበረው ሥርአት አመዝኖ በአንድ በተወሰነ አጋጣሚ ወደ ኋላ የመመለስ የፖለቲካ ችግር እንኳን ቢከሰት ፌዴራሊዝሙ የማኩረፊያ ቀዳዳ ከፍ ሲልም የመገንጠል የማስፈራሪያ ክፍተትን ስለሚፈጥር ተመራጭ ይሆናል። ማስፈራሪያ ወይም ማኩረፊያ ያልኩትም አምባገነናዊ አስተዳደር እየገነገነ የሚሄድ ከሆነ ተገንጥሎ የራስን ነፃ መንግስት እስከ ማቋቋም የሚያደርስ ሕገ መንግስታዊ ድጋፍ እንዳለዉ ለማወጅ ያስችላል። በተመሳሳይ ሁኔታም ዴሞክራሲያዊነት የሚጎለብት ከሆነ ተመልሶ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርጹ ውስጥ የመታቀፍ ዕድሉም ያንኑ ያህል ሰፊ ነዉ። በኢትዮጵያ ደረጃ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርጽ የሚደገፈው ሕወሓት/ኢህአዴግ ስላመጣዉ ወይም ሌላዉ ስለደገፈዉ ወይም ስለተቃወመዉ ሳይሆን አሃዳዊነት ለረጅም ጊዜ በተግባር ተፈትኖ ወይም ለረጅም ጊዜ ተሞክሮ የወደቀና የሦስት ሺህ ዘመን ዕድሜ ያስቆጠረ ተብሎ ጩቤ የሚረገጥለትን የሀገረ መንግስት ግንባታ ለማጠናቀቅ እንኳን ብቃቱንም ሆነ አቅሙን የሌለው ሲሆን፤ ከዚያ ባልራቀ ሁኔታም ቋንቋን መሰረት ያደረገው የወቅቱ ፌዴራሊዝምም የሚነቀፈው ፌዴራሊዝሙ እራሱ እስካሁን ከተፃፈበት ወረቀት አልፎ ተግባራዊ ስላልተደረገ ለተቃውሞ ተጋልጦ ይገኛል። ስለሆነም፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ የመረጠዉ ፌዴራላዊ የመንግስት ቅርፅ አሃዳዊ ዓይነት የሆነ ፌዴራሊዝም ነዉ ለማለት ይቻላል፤ ወይም ብዙዎች የአገረው ምሁራን እንደሚስማሙበት ‹‹የዉሸት ፌዴራሊዝም›› (pseudo-federalism) ነዉ።

የብሔር ፌዴራሊዝምን ለመገንባት በዓለም ደረጃ ሲታይ ሕወሓት/ኢሕአዴግ የመጀመሪያ ፓርቲ እና የዘረኝነትን መሠረት የጣለ እንደሆነ አድርገው የሚከስሱ ወገኖች አሉ። ነገር ግን ቤልጅም፣ ሕንድ፣ ናይጀሪያና ካናዳ የብሔር ፌዴራሊዝምን በመገንባት የሚጠቀሱ ናቸዉ። በተለይም ሕንድ (indivisible union divisible federation) እና ካናዳ የገቡበትን ፌዴራላዊ ሕገ መንግስታዊ ኪዳናቸዉን ዴሞክራሲያዊ አድርገዉ ስለሰሩ የበለፀገ አገር ለመገንባት ችለዋል። በሕወሓት/ኢህአዴግ

የተመራዉ የፖለቲካ ስብስብ ነሐሴ 15 ቀን 1987 ይፋ በአደረገዉ ሕገ መንግስት ዉስጥ ፌዴራላዊ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓትና የብዙሃን ፓርቲ ዲሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችል አንቀጾች ቢታጨቁበትም ተግባራዊ ሥራዉ ላይ የለም። ከላይ የተጠቀሱትን የኢትዮጵያዊያን ችግሮች፤ ነገር ግን በመተሳሰብና በመቻቻል በየዋህ ፖለቲካ ከተያዘ ግን ሊፈታ የሚችል ልዩነቶችን እዚህ ላይ ገታ ላድርግና፤ የሕወሓት/ኢህአዴግ የፓርቲ ፖለቲካ ግንባታ ከፌዴራላዊ ሥርአት ምስረታ ጋር እንዴት እንደከሸፈ ቀጥሎ ባሉት መስመሮች ጨምቀን እንመለከታለን። ምክንያቱም ለአገሪቱ አንድነት፣ ለሕዝቦቹ ትስስርም ሆነ ለፌዴራላዊ የመንግስት ሥርአት ግንባታ አንዱ ተግዳሮት ስለሆነ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

የአንድን መንግስት ዲሞክራሲያዊነት ወይም ኢዲሞክራሲያዊነት ለመናገር የሚቻለዉ የመንግስቱን ቁልፍ የያዘዉ ፓርቲ ወይም ግለሰብ ከሚናገረዉ ብቻ ሳይሆን እመራበታለሁ ብሎ ካስቀመጠዉ ወይም ከሚያራምደው መርህ አንፃር የሚያደርጋቸዉን ወይም የሚተገብራቸዉን በተናጠልም ሆነ በጥምረት ጥናቶችን በማድረግ መግለጽ ይሆናል። ቢያንስ ለሃያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያን የመራው ሕወሓት/ኢህአዴግ እና ዛሬ ወንበሩን የተረከበው የብልፅግና ፓርቲ የመንግስት ሥርአቱ የሚመራዉ በፌዴሬሽን ነዉ ብሎ በሕገ መንግስት ደረጃ ቢደነግግምም በተደነገገዉ መሠረት ላለመሄዱና የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግር ሕወሓት/ኢህአዴግም ሆነ የብልፅግና ፓርቲ የሚያራምዱት አብዮታዊ ዴሞክራሲ መሆኑን ብዙ ምሳሌዎችን አንስቶ መግለጽ ይቻላል። ቀጣይ ባሉት አርእስቶች ሥር ስለአብዮታዊ ዴሞክራሲ በስፋት የምናይ መሆኑን እየገለፅኩ ለጊዜው ግን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ማለት የሕግም ሆነ የፖሊሲ አመራሮች ሁሉ በፓርቲ ደረጃ ተወስነው ወደ መንግስት የሚዘሩና በተግባር ደግሞ የተማከለ ነው። የሕወሓት/ኢህአዴጉ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ መንግስት አመራር ፌዴራሊዝሙን ራሱን በፓርቲ-መንግስት መዋቅር መሀከል ጠርንፎ ዴሞክራሲ አልባ ያደረገ ነው።

ፌዴራሊዝም ራሳቸዉን ችለዉ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ግዛቶች ካላቸዉ ሥልጣን ቆርሰዉ (የአገር መከላከል፣ የአገሪቱን ሸርፍ ማተምና ማስተዳደር፣ የውጪ ግንኙነቱን ሥራ መስራት፣ የውጪ ንግድ መምራትና ማከናወን፣ በክልሎች መሀከል የሚካሄድን ንግድ መምራት እና ሜጋ ፕሮጀክቶችን መገንባት) በጋራ ወይም በስምምነት ላቋቋሙት የላይኛዉ መንግስት (የፌዴራል መንግስት ማለት ነዉ) የሚያጋሩበት ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርአት ነዉ። እነዚህ የፌዴሬሽኑ አባል ግዛቶች ወይም ክልሎች ተብለዉ የሚታወቁት አካፍለዉ የሰጡት ሥልጣንም የሚታሰረዉ ተራ በሆነ የውል ስምምነት ሳይሆን መልክ ባለዉና ማንም በፈለገ ጊዜ በፈለገዉ ዓይነት ሁኔታ በሚጠቀምበት ወይም በሚጠመዝዘዉ ሳይሆን በሕዝቦች ቃል ኪዳን በሚባል በሕገ መንግስት ነዉ። ይህ የሚከወነው ምናልባት ከታች ወደላይ በሚገነቡ የፌዴራል ሥርአት ብቻ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ከላይ ወደታች የሚገነባዉም የፌዴራል ሥርአትም ቢሆን ከዚህ የሚለይበት ሁኔታ አይኖርም፤ ማለትም በዚሁ ሕገ መንግስታዊ ውል መታሰር ይኖርበታል። ኮሪ እና አብርሃም (1964፡ 158) የሚባሉ ፀሐፍት "A federal system is always a compromise between two distinct and sometimes conflicting sets of political forces." ብለዋል። ስለሆነም የፌዴራል ሥርአት የሚቋቋመዉ ሥርአቱ ከታች ወደ ላይና ከላይ ወደታች በሚቋቋምበት ጊዜ ሊነሱ የሚችሉ ድርድሮችን የሚያደርግና ግጭቶችን ማስታረቅ የሚችል እንዲሆን ታስቦ ነዉ በማለት እአአ በ1998 በኤኮኖሚክስ የዓለምን የኖቤል ሽልማት የተቀበለዉ አማርትያ ሴን፤ "Federalism provides room for diversity by offering a constitutionally guaranteed balance between shared rule and self rule." ማለቱን ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በዓል አከባበር የተሰናዳ መጽሔት አስነብቧል።

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ይገነባል ተብሎ የታለመዉ ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል በጥገኛ ኮሎኒ ጭቆና ወይም በአፄያዊ አገዛዝ (empire state) ሥር የነበሩ ብሔር ብሔረሰቦች አንድን ብሔር ለዚያዉም

አናሳ ቁጥር ያለዉ ሕዝብን በሚወክል ፓርቲ (ሕወሓት) አማካይነት ከላይ ወደታች የተገነባ ነዉ። ይህ በመሆኑ ከሁለት አቅጣጫዎች ችግር ገጥመዉታል። አንደኛዉ ኢህአዴግ የፌዴራል ሥርአትን በመምረጡ ለተጨቆኑት ብሔር ብሔረሰቦች ውለታ እንደዋለላቸዉ እየተቆጠረ፤ ትግበራዉን በማንኪያ እየቆነጠረ ይሰጣል። እየቆነጠረ ካልሰጠ በስተቀር ደግሞ እነዚህ ብሔሮች ራሳቸዉን ችለዉ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ራሳቸውን ከአስተዳደሩ (home rule/self rule) ከሕወሓት አገዛዝ ነፃ ስለሚያወጣቸዉ፤ ገና ከምስረታው አልሞ የተነሳላቸዉ ሕዝቦች (ትግራይ ማለት ነው) ተጠቃሚነትን ይቀንሳል የሚል ስጋት ያድርበታል። ስለሆነም፤ ራስን በራስ ማስተዳደር በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ መዋል አልተቻለም። በሌላም በኩል ኢትዮጵያን ከገነቡ ወይም የኢትዮጵያ አካል ከሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች የበለጠ በጠመንጃ አፈሙዝ የተገነባችዉ የኢትዮጵያ አንድነት የሚያሳስባቸዉ የሚያስመስሉ የአሃዳዊነት ሥርአት አቀንቃኞችም ይህንን የፌዴራል ሥርአት (እሱም ካለ) ይገዳደሩታል። ግጭትን ወይም ቅራኔን በዉይይት የመፍታት ባህል በለመገንባቱ የተነሳ የኤርትራን ነፃ አገር መሆን እንደ ምሳሌ በመውሰድ የሕወሓትን ሥራ በአፍራሽነት በተለይም የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 39ኝን የሞኮንኑ አሉ። አንቀጽ 39ኝን የሚኮንኑ ኃይሎች ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር፤ እንዲህ በቀላሉም ሊገነዘቡት የማይችሉት ነገር ቢኖር የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የሚለው መርህ ለዴሞክራሲያን ጭንቅ አለመሆኑን ነው። ምክንያቱም፤ አእምሮ ፈታሹን መርህ በጥልቀት ቢረዱ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ማምጣት ካልተቻለ መገንጠል የሚለው መርህ በሁለተኛ አማራጭነት ሥራ ላይ ልውል የሚችል መሆኑን ነው። ከጨለምተኛ ወገናዊነት በፀዳ እይታ ብንመለከት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የመጀመሪያ የፖለቲካ ፕሮግራም፤ አንደም የኦሮሞ ሕዝብን ከጥገኛ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ማዉጣት ወይም ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ የሚለዉን ይመክራል።

አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን፤ በተለይም አሃዳዊያን፤ ለኤርትራ መገንጠል ዝም ብሎ የጫጉላ ሽርሽር የሆነውን የሽግግር ሥርአቱንም ሆነ የሕገ

መንግስቱን አንቀፅ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ሁሉ ለሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችም መበታተንና ለኢትዮጵያ ሕልውና ማክተምም በር የከፈተ አድርገው ይኮንኑታል። በዚህ የተነሳም በየብሔራቸው የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማፍረስ አልመው ጎሰኛ፣ ጎጠኛ፣ ዘረኛ፣ ጠባብ ብሔረተኛ፣ ፅንፈኛ፣ አሸባሪ፣ ዘውገኛ፣ ፋሽስት፣ ናዚ፣ አፓርታይድ፣ ወዘተ እያሉ ሞራል በሚነካ ዓይነት ሁኔታ ሕወሓት/ኢህአዴግንና በዚያ መስመር የተደራጁ ኃይሎችን ሁሉ ያወግዛሉ። እነዚህ ለኢትዮጵያ አንድነት ጠበቃ ነን የሚሉ፣ ኢትዮጵያዊ የዜግነት የምስክር ወረቀት ለመስጠትም ሆነ ለመንሳት የሚዳዳቸው አሃዳዊያን ያልተረዱት ነገር ቢኖር መንግስት በቅርጹም በተግባሩም አሃዳዊም ሆነ ፌዴራላዊ በሆነ ሁኔታ <u>የሚከሰትና የሚከስም</u> ማህበራዊ ድርጅት መሆኑን አይገነዘቡም። በኢትዮጵያ ደግሞ ግዛታዊ (ኢምፓየራዊ) የኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት የመገንባት ሥራዎች ሳይሰኩ በመቅረታቸውና ዜጎች ደግሞ በሚደርስባቸው ገደብ የለሽ ጭቆና የተነሳ በየብሔራቸው በመጠቀቃስ የአርነት ንቅናቄዎች ሥር ተደራጅተው ቢያንስ ላለፉት ሃምሳና ስድሳ ዓመታት የኢትዮጵያ መንግስታትን አፍንጫ ሰንገው ይዘው እንደነበር የሚታወቅና ከነሱም ከሕወሓት/ኢህአዴግ ወገን የተሰለፉት በለስ ቀንቶአቸው አዲስ አበባን ተቆጣጥረው በቀረጹት ሕገ መንግስት ውስጥ አንቀፅ 39ኝን ማካተታቸው አሃዳዊያኑ ስመለከቱት በዓለም ላይ በቅርቡም ሆነ በሩቁ የትም ተከስቶ የማያውቅ፤ አዲስና የተለየ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተከሰተ መቁጠራቸው መወለድ፣ ማደግ፣ ማርጀትና መሞት ወይም መክሰም የሚለው የተፈጥሮ ሳይንስ የዕድገት ሂደት አልታያቸውም ወይም አይታያቸውም ማለት ይቻላል። ዕውነቱን ለመናገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ችግር የተፈጠረው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንቀፅ 39ን ተግባራዊ ስላደረጉ ሳይሆን በሕገ መንግስቱ የተቀመጡት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሕወሓት/ኢህአዴግ ስግብግብ ባህርይ የተነሳ በሕገ መንግስቱ መሠረት ባለመተግበራቸውም ሆነ ባለመከበራቸው ነው። እንደ ጆርጅ አንደርሰን “የመገንጠል ንቅናቄ አደጋ ብዙ ጊዜ ከፌዴራሊዝም ጋር ተያይዞ የሚነሳ ቢሆንም፤ በታሪክ እንደታየው የመገንጠል ንቅናቄ በበርካታ አሃዳዊ አገሮችም በብዛት

ሊከሰት ይችላል።” የሚለውን ምሁራዊ አስተያየት በሰለጠነ አቅል መቀበል ብቻ በቂ ይሆን ነበር።

ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ ተጋፊና ተደጋጋፊ የሆኑ ሐሳቦችን አንስቼ ለማሳየት ልሞክር። በርግጥ ሕወሓት/ኢህአዴግ ሕገ መንግስት ቀርፆ የኢትዮጵያን መንግስታዊ አስተዳደር በብሔር ብሔረሰብ አደረጃጀት ቋንቋ አዋቀረ እንጂ ለኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰብ ጥያቄ መነሳት የመጀመሪያ እንዳልሆነና የ1960ዎቹ የትግል ቸቦ ለኳሾች የትግላቸው አንዱ ማጠንጠኛ የብሔር ብሔረሰብ ጥያቄ እንደነበረ አይክዱትም። ኃይሌ ሥላሴን ከሥልጣን ያስወገደው ደርግ ራሱ የብሔር ብሔረሰብን ጉዳይ ቢያንስ ለአስር ዓመታት ይህል ቸላ ብሎ ከቆየ በኋላ ሊያልፈው እንደማይችል ሲረዳ በ1976 በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት “የብሔረሰቦችን ቁጥር፣ የየሕዝባቸውን ብዛትና ስርጭት ለማግኘት የሚያስችሉ መረጃዎች በቆጠራው ጊዜ እንዲሰበሰቡ አድርጓል” ሲሉ ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌታሁን ዴለቦ ከላይ በተገለጸው መጽሐፋቸው ውስጥ ገልፀዋል። ከዋለልኝ ቀደም ሲልም አውስትራላዊው ኦቶ ባወር በ1907 እና ሩሲያዊው ጆሴፍ ስታሊን በ1913 በብሔር ብሔረሰብ ጉዳይ ላይ ሰፊ ትንተና ሰጥተውበታል። ስለሆነም፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ ከ18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የተቀነቀነውን፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ1957 የዋለልኝ መኮንን ኢትዮጵያዊው ማነው አርትክል ጀምሮ ሲቀነቀን የኖረውንና ደርግም የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩት አቋቁሞ ለሕወሓት/ኢህአዴግ መንደርደሪያ ቦታ ያመቻቸውን ጉዳይ እሱ እንደ ጀመረው ተደርጎ ሕወሓት/ኢህአዴግን መወንጀሉ ይህን ያህል አስፈላጊ ነገር አልነበረም።

ከዚህ ጋር ሁለት ነገሮችን በንፅፅር ማየት ያስፈልጋል። አንደኛ ሕወሓት/ኢህአዴግ ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝሙን የመሬት ይገባኛል ጥያቄን በመሳሰሉ ጉዳዮች ሕዝቦች እንዳይናቁሩ አድርጎ ማከናወን ሲገባዉ ያንን ባለማድረጉ፤ ሁለተኛው ደግሞ በርግጥ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቋቸው፣ ባህላቸውና ስሜታቸው መደራጀት

ነባር ችግሮችን መነሻ በማድረግ ግልፅ የሆነ የአመለካከት፣ የግንዛቤ እና የተግባር ልዩነት ጭምር በሕዝቦች መሃከል እንዲከሰት መደረጉ የማይካድ ዕውነት ነው። ሕወሓት/ኢህአዴግ ከፈጸማቸው ወንጀሎች ውስጥ በፌዴራል ተብዬው ውስጥ ሲሰጥ የነበረው ትምህርትና ሥልጠና ሳይቀር ከጥራት ጉድለቱ በተጨማሪ የሃይማኖትና የፖለቲካ ኃይሎች እኩይ ድርጊቶችም አጠቃላይ የአገር ወይም የኢትዮጵያዊ ዜግነት ስሜት እንዲደበዝዝ አላደረገም አይባልም። በዚሁ ጊዜ ደግሞ አዲሶቹ ገዥ ሰሜነኞች የመሀልና የደቡብ ሕዝቦችን ከነባር መሬታቸው ማፈናቀል ብቻ ሳይሆን ሕገ መንግስታዊ መብት አለኝ ብሎ ዘረፋቸውን ቀና ብሎ የሚያይ የደቡብ ሰው ካገኙ ወይ ቀጥታ እራሳቸው ወይም በሕዝብ መሀከል በአስቀመጧቸው ጀሌዎቻቸው ሕይወቱን እስከ ማጥፋት ስለሚደርሱ፤ ደቡቦቹም በተራቸው ከተደራጁበት የቋንቋ፣ የባህል፣ ከባቢያዊ አደረጃጀት ሁኔታ የበለጠ የሌላ ብሔር ተወላጅ የሆነን ሰው በጥላቻ መንፈስ እንዲያዩ ስላደረገና በሸፍጥ ፖለቲካ የተካኑት አሃዳዊያኑ ደግሞ ነባሩን ችግር ወደ ጎን ትተው የችግሩን መነሻ የፌዴራል ሥርአቱ እንደሆነ አድርገው እንዲያስቡ ሳያስገድዳቸው አልቀረም። ስለሆነም፤ እንደ አመለካከት አሃዳዊ ሥርአትን መምረጥ መብት ቢሆንም ከሕወሓት/ኢህአዴግ ጥፋት ጋር አያይዞ ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝሙን መጥላት ወይም ማንቋሸሽ ግን ተገቢ አይሆንም። ይልቅ የወሰደው ጊዜ ተወስዶ የፖለቲካ ሥርአትን በሕዝብ ይሁንታ መለወጥ ወይም ማሻሻል የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት የግድ ይላል።

ሕወሓት አዲስ አበባን ከመቆጣጠሩና በሕገ መንግስቱ ውስጥ አንቀፅ 39ን ከመጨመሩ በፊት ጀምሮ ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር፣ የጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል፣ የአፋር፣ ወዘተ የአርነት ንቅናቄዎች ነበሩ። እነዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ የማትሆን ከሆነ የሚወክሉትን ሕዝብ ነፃነት ለማጎናጸፍ እስከ መገንጠል ድረስ ሲዋጉ የነበሩ ናቸው። ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር በተለያዩ ቅራኔዎች የተሞላችው ኢትዮጵያ፤ ቀድሞም በቅራኔዎቹ መፍረስ የጀመረችው ሀገር የሕገ መንግስት አንቀፅ

39ም ሆነ በብሔር ፓርቲ ሥር መደራጀት  ሰበብ ቢሆን እንጂ ለኤርትራ መገንጠልም ሆነ ለቀሪ ብሔር ብሔረሰቦች ዝግጅት ውስጥ መሆን ሲጠራቀሙ የመጡትን መጥፎ ክስተቶችን ሁሉ ሆን ብሎ አለመረዳት ወይም የመረዳት አቅምን ማሳነስ እኩይ አስተሳሰብ ከመሆን አይዘልም።

እነዚህን ትይንቶች መረዳት ቢቻልና ቢታሰብበት ለኢትዮጵያ አንድነት መነካት መንስኤ የሚሆነዉ ቋንቋን መሰረት ያደረገ ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝም ሳይሆን ፌዴራሊዝሙ ራሱ በታለመለትና በሕገ መንግስቱ በተቀመጠለት ሁኔታ በትክክል አለመተግበሩ ነው። የአማራ ብሔር ተወላጆች ጉራ ፈርዳ፣ ጎባ፣ ጎሬ፣ መተከል፣ ወዘተ እንዳይኖሩ መቆስቆስ ኢህአዴግ ሕዝቦችን ከፋፍሎ ለመግዛት ብቻ የተጠቀመበት ስልት ቀደም ሲል የነበረዉ ግጭት እንዲያገረሽና ለኢትዮጵያዊያን ትስስር ሕልዉና ስጋት ላይ እንዲወድቅ ከማድረጉም በላይ ለአሃዳዊነት ሥርአት አራማጆችና ለፊውዳል ሥርአት ናፋቂዎች ዓላማ ስኬት እንደ አንድ መከራከሪያ ነጥብ አድርገዉ እንዲጠቀሙበት አግዟል። የአሃዳዊነት አንድነት ኃይሎችም ቢሆኑ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት የሚያከብሩ ከሆነና ማንነቱ የተከበረለት ሰዉ ደግሞ ረጅም ጊዜ አብሮ የኖረ ወንድሙን ቀርቶ ሌላውንም የሚጠላበት አንዳች ምክንያት እንደማይኖር በመገመት፤ ኢትዮጵያዊ የሀገረ መንግስት ግንባታውን ከብሔር ተኮር ፌዴራሊዝሙ ሙሉ ጥቅሙና ክብሩ ጋር በፅኑ መሠረት ላይ መገንባት የተሻለ አስተሳሰብ ይዘው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይኼ ደግሞ መጀመሪያ ብሄሬ ቀጥሎ ኢትዮጵያዊነቴ እንደማለት ነዉ። እንደማሳያም የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የተባለውና ዘግይቶም ቢሆን በሕብረ ብሔራዊ ዓላማ የተቋቋመው ድርጅት ለብሔራዊ ፌዴራሊዝሙ ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት ይመስላል። ይኼም አሜሪካዊዉ ሮቤርት ኢ ሊ ካለዉ የተለየ አይደለም። የኢ ሊ የመጀመሪያ ታማኝነቱ ለክልሉ ለቬርጂኒያ እንጂ ለአሜሪካ አይደለም። ሚስተር ሊ **ለአሜሪካን ብሎ በቬርጂኒያ ላይ ሰይፍ አልመዝም** ነዉ ያለዉ። በተመሳሳይ አባባልም ለኢትዮጵያዊነት ብሎ በራሱ ብሔር ላይ ሰይፍ የሚመዝ ወይም ኮረት የሚወረውር አይኖርም እንደማለት ነዉ። አለሁ

የሚል ሰው ካለ ደግሞ እሱ ሰው ለራሱ ብሔርም ሆነ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊም ሆነ አሃዳዊ አንድነት የማይበጅ የማንነት ቀውስ ያለበት ሰው መሆኑ ነዉ፡፡ በሌላ አባባል ለመግለፅ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያዊነት የሚወስደው መንገድ እንደ ሀገረ መንግስት ግንባታው በብሔር ብሔረሰቦቿ በኩል ያልፋል እንጂ በኢትዮጵያ በኩል ወደ ብሔር ብሔረሰቦች አያልፍም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀላል ነው፤ ኢትዮጵያ በውዴታም ይሁን በግዴታ የተገነባችው የየራሳቸው ሰፊ የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የሥነ ልቦና አመለካከት፣ ወዘተ ልዩነት ባላቸው ብሔር ብሔረሰቦቿ ስለሆነ፤ ብሔር ብሔረሰቦች ቀዳሚ ናቸው፡፡ ይኼ ደግሞ የማንም ሀገር ወይም ሕዝብ ቅጂ ሳይሆን ብቸኛ የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርአት ግንባታ ነው፡፡ አሁንም ልብ ማለት ያለብን ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ በውዴታም ይሁን በግዴታ የየራሳቸው ሰፊ የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖት፣ የሥነ ልቦና አመለካከት፣ ወዘተ ልዩነት ባላቸው ብሔር ብሔረሰቦቿ የተገነባች ስለሆነ፤ የፌዴራሊዝም ግንባታችንም ያንኑ ያህል ልዩነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ጆርጅ አንደርሰን ጽፎት ፎረም ኦፍ ፌዴሬሽንስ የተባለ ዓለም አቀፍ የፓርላማዎች ስብስብ <u>የፌዴራል መንግስት አወቃቀር መነሻ ነጥቦች</u> (2001፡ 11) ብሎ ባዘጋጀው የአማርኛ ትርጉም ላይ እንደተገለጸው "እያንዳንዱ አገር አፈጣጠሩን እንዲሁም የግዛት ክልሉንና የፖለቲካ ለውጥ ሂደቱን በተመለከተ የየራሱ ታሪክ፣ ጦርነቶችንና አብዮቶችን የቅኝ አገዛዞችን፣ ሥርወ-መንግስታዊ ጋብቻዎችን፣ ዓለም አቀፍ ውሎችንና ሰላማዊ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደትን አካትቶ የያዙ ናቸው፡፡ [ስለሆነም]፤ … ፌዴራሊዝም የተመረጠው በአገሪቱ ባለው የቋንቋዎች፣ የሃይማኖቶችና የብሔረሰቦች ልዩነት የተነሳ፣ ምናልባትም በክልሎች መሀከል በሚኖር ጉልህ የኤኮኖሚ ልዩነት ምክንያት የተነሳ ያልተማከለ አስተዳደራዊ ስርአት እንዲፈጠር ለሚደረግ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ግፊት ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች የራስ ገዥ መብት እንዲሰጣቸው ግፊት የሚያደርጉት ክልሎች ቀደም ሲሉ የየራሳቸው የፖለቲካ ሕልውና የነበራቸው ሊሆኑ ይችላል፡፡" ይላል፡፡ ይህንን የመሳሰሉ የይሆናል ምክንያቶች እያለ ኢትዮጵያ ላይ የብሔር ብሔረሰብ ዘረኝነት መዓት እንደወረደባት አድርጎ

ማቅረብ ምናልባት ያልነበረን ወይም ሕልውናው አነስተኛ ደረጃ የሚገኘውን የዘር ልዩነት ጎልቶ እንዲወጣ የመቀስቀሻ ሞተር ሊሆን ይችላል።

ቀድሞም ቢሆን እንዳይሆን ሆነዉ በአንድ ቅርጫት የተጠቃለሉት የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ተፈንክቶ ቁጥራቸዉን ባይጨምር ኖሮ የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የተመሠረተዉ በዘጠኝ ክልሎች ነዉ። የፌዴራል ክልሎቹ የተደራጁበት ዝርዝር ደጋፊ መረጃዎች በሕገ መንግስቱ ላይ ይቀመጣሉ ተብሎ ባይጠበቅም፤ በይፋ ሲነገር የቆየዉ ቋንቋን መሠረት ያደረገ ነዉ። ነገር ግን የሕዝብ ብዛትንም ግምት ዉስጥ ማስገባት ነበረበት። ምክንያቱ፤ በብሔር/ብሔረሰብ ስም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው እንደ ሐረሪ ብሔረሰብ የመሳሰሉት ክልል መመስረት አልነበረባቸውምና ነው። The Ethiopian Population Profile: 1999 ብሎ የወጣዉ አንድ መፅሔት እአአ በ2015 [ከአከባቢው በፖለቲካ ውሳኔ የተጠቃለሉ የኦሮሞ ተወላጆችን ጨምሮ] የሐራሪ ሕዝብ ቁጥር 257000 ይሆናል የተባለዉ የክልል ደረጃ እንዲኖረዉ ሲደረግ፤ በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ ቁጥሩ ከዚህ በላይ የሚሆነዉ የሲዳማ ወይም የወላይታ ሕዝቦች የክልል ደረጃ እንዳያገኙ ተደርገዉ በአንድ የጅኦግራፊ ቅርጫት ዉስጥ እንዲካተቱ መደረጉ ጥያቄ ሊያስነሳ የቻለ ነዉ። ከዚህም በተጨማሪ በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ሁለት የከተማ አስተዳደሮች፤ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተጠሪነታቸዉ ለኦሮሚያ ክልል ሆነዉ የልዩ ዞን ደረጃ አስተዳደር ቢሰጣቸዉ የሚሻል ነበር እንጂ ኦሮሚያ ወይም ሌሎችም ክልሎች ማግኘት ያለባቸዉን ጥቅሞች እንዳያገኙ ለማድረግ ሲባል፤ በበለጠ ግን የኦሮሞ ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን ስጋት ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ሲባል፤ የፌዴራሊዝም አመሰራረት መርህ ጋር የሚጋጭ ሥራ በመስራት የከተማ አስተዳደሮቹ ተጠሪነት ለፌዴራሉ መንግስት ማድረጉ ሊገነባ የታሰበዉን የፌዴራል ሥርአትን ጉድለት ያመላክታል።

የፌዴራል ሥርአት ግንባታና የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲ ፈተና ከዉስጥና ከዉጮ፤ ማለትም ከሁለቱም አቅጣጫ የሚቀርቡለትን ፈተናዎች ማለፍ ያለበት ፓርቲ ነገሮችን በማዳፈን ሳይሆን በተግባር መመለስ መቻልን የሚጠይቁ ናቸዉ። የሊበራል ዲሞክራሲ ሥርአት የሚከተሉ መንግስታት አጥብቀዉ ከሚከተሉት ሁለት ነገሮች አንዱ ኮሪ እና አብርሃም (1964: 683) እንደሚሉት *"... liberal democratic government is expected to serve two principal related ends or purposes. First, democracy defined as government by, of, and for the people, seeks to ensure a close correspondence between what the people want and what the government does"* ይላል። እንዲህ ካልሆነና በዴሞክራሲ አልባነት የተገነባዉ የፌዴራል ሥርአት የውሸት ፌዴራሊዝም ሆኖ ያርፋል። ብሔር ተኮርም ሆነ ጂኦግራፊያዊ የፌዴራል ሥርአትን ያለዴሞክራሲ ማሰብ ራስን የማሞኘት ያህል ነው።

ኢህአዴግ በፌዴራሊዝም ግንባታው በተያያዥነት አሁንም ያላለፈውን የውስጥ ፈተናዎችን ጠለቅ አድርጎ መመልከቱ ጠቃሚ ነበር። በኢትዮጵያ የተማሪዎች የብሔር ጥያቄ እንቅስቃሴ ላይ ተመርኩዞ የተመሠረተዉ ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ/ማገብት ትግራይን ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ የጭቆና አገዛዝ ነፃ ለማዉጣት ተቋቁሞ እንደነበር ገልጫለሁ። ይኸዉ ማገብት የተባለዉ ድርጅት በአብዛኛዉ ሲንቀሳቀስ የነበረዉ በተማሪዎች አከባቢ እንደነበረና ከሻዕቢያ ባገኘዉ የሥልጠናና ሎጂስቲክስ ድጋፍ በኋላ ወደ ተጋድሎ ሀርነት ትግራይ/ተሀት መለወጡን ጠቅሻለሁ። ተሀት የነፃነት ንቅናቄ ሆኖ እያለ በዉስጡ በተፈጠረዉ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ/ማሌሊት በሚባል አንጃ ተቦርቡሮ እአአ በ1985 የአመራር ለውጥ ማድረግ ብቻ ሳይሆን መስራች አባላቱንም በማባረር የድርጅቱንም ስም ከተሀት ወደ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት እስከ መቀየር ደርሷል። ሆኖም ግን ማሌሊት ከተመሠረተ በኋላ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር ለትግራይ ሕዝብ ባህላዊና ኤኮኖሚያዊ ነፃነት መታገሉን እንደጀመረ ይገለፃል።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ከላይ በተገለጹት አጋዥና በለስ በቀናቸው ምክንያቶች

ሥልጣን እንደያዘ ከወሰዳቸዉ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ዕርምጃዎች አንዱ በተለይም በከተሞች አከባቢ ‹‹ሠላምና መረጋጋት›› የሚባል ኮሚቴ በማቋቋም አስተዳደራዊ ሥራዎችን ከመስራቱም ሌላ፤ የሥልጣን መሠረቱን ያመቻቸበት የሠላም ኮንፌሬንስ ብሎ ያካሄደዉ ድርጊት ነዉ። የሠላም ኮንፌሬንሱ በቀዳሚነት ያረጋገጠዉ የጫጉላ ሽርሽር የሆነውን የኤርትራን መገንጠል ነበር። በርግጥ ኮንፌሬንሱ የኤርትራን መገንጠል አረጋገጠ አላረጋገጠ የቢሮክራሲና የዲፕሎማሲ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የኤርትራ መንግስትነት የተረጋገጠዉ ከኮንፌሬንሱ መካሄድ በፊት የኤርትራ ሕዝባዊ ነፃነት ግንባር ኃይሎች አስመራ ላይ መንግስት ያቋቋሙ ጊዜ ስለነበረ፤ ኮንፌሬንሱ ቀጣይ ግንኙነትን አስመልክቶ የመልስ ግብዣ ከመሆን ያለፈ አልነበረም። ያ ኮንፌሬንስ ምናልባት በኋላ ላይ እየተነሳ የመጣዉን የወደብ ጉዳይና የኢትዮጵያ አፋሮች የሰፈሩባቸው ቦታዎች፤ በተለይም የአሰብ ወደብ ጉዳይን አንድ ነጥብ ባለማንሳቱ ቢወቀስ እንጂ፤ የሠላም ኮንፌሬንሱ ያደረገዉ አዲስ ነገር ቢኖር ለተበላዉ ዕቁብ የውል ፊርማ እንደማስቀመጥ የሚቆጠር ነዉ።

በኮንፌሬንሱ የተከናወኑት መሠረታዊ ጉዳዮች ዲሞክራሲያዊና ሁሉን አሳታፊ ባይሆኑም፤ ጦርነት ለሰለቸዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጊዜዉም ቢሆን እፎይታን የፈጠረና 87 መቀመጫዎች ያሉት የሽግግር ጊዜ ምክር ቤትና ሕግ በማቋቋም ሕወሓት/ኢህአዴግ በጠመንጃ የተጎናፀፈዉን አሸናፊነት ኮንፌረንሱ ዕዉቅና መስጠቱ ብቻ ነዉ። በኮንፌሬንሱ የተሳተፉ ድርጅቶችን በተመለከተ ደግሞ ሦስቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች (ሕወሓት፣ ኢህዲን፣ ኦህዴድ) እያንዳንዳቸዉ አስር አስር መቀመጫዎችንና በብርጋድየር ጀኔራል ዓለምእሸት ደግፌ ይመራ የነበረው ምርኮኛው የደርግ መኮንኖች አቋቋሙት የተባለዉ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢዴመአን) ሁለት ተወካዮች በመያዝ፣ ኦነግ አስራ ሁለት መቀመጫዎችን በመያዝ እና ሌሎች ለዚሁ ተብለዉ የተቋቋሙ የብሔር ድርጅቶች አንድ ግለሰብ ናቸዉ። የደርጉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ/ኢሠፓን ጨምሮ ሕብረ ብሔር የሆኑ እንደ ኢሕአፓና መኢሶን የመሳሰሉት ድርጅቶች

አልተሳተፉም። ላለመሳተፋቸዉም ሁለቱም ከሕወሓት ውጭ ያሉ ሰዎች የሚሰጡት ምክንያት ሕወሓት/ኢህአዴግ ከሚያራምደዉ የፖለቲካ አካሄድ አንፃር ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝምን ለማቋቋም ማቀዱን የማይደግፉ ሲሆን፤ ከዚህ ወጣ ባለ ሁኔታ ግን ሁለቱም ድርጅቶች መኢሶን ለደርግ በመወገንና ኢሕአፓ ደግሞ ወደ አሲምባ ተጠልሎ በነበረበት ወቅት ከሕወሓት ጋር በቋጠሩት የማይሽር ቂም በቀል የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ። ለዚህ ማረጋገጫ ደግሞ ከኮንፈረንሱ በኋላ በአገር ዉስጥ በተጠራዉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ አገር ቤት ያቀናዉ የመኢሶን አባል የነበረዉ አበራ የማነአብ ከመንገድ ተይዞ ለረጅም ዓመታት ዘብጥያ መወርወሩ ነበር። ላለመሳተፋቸው ዋና ምክንያት ግን ያልተፃፈው ወይም ያልተነገረው አግላይ የሆነው የሕወሓት/ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከመሆን እንደማያልፍ እሙን ነው። እንግዲህ፤ ለዚህ ኮንፈሬንስ ተብለዉ ከተፈጠሩት የብሔር ድርጅቶች ዉስጥ ከኮንፈረንሱ በኋላ የት እንደገቡ የማይታወቁ ድርጅቶች መኖራቸዉ ሲሆን፤ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በመገለባበጥ በሚታወቁት በመቶ አለቃ ግርማ ውልደጊዮርግስ (በኋላ ፕሬዚዳንት) እና አሁንም በኋላ የኦህዴዱ የሆነዉ ግርማ ብሩ የተመራዉ ድርጅት ወደ ሰማይ ይውጣ መሬት ቀድዶ ይግባ የታወቀ ነገር የለም።

የሕወሓት እጅ ሥራ የሽግግር ሥርአቱ ስለሆነው የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ)ን በሚመለከት ምስረታና እስከ ዛሬ ያለበትን ገጽታ በአጭሩ መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል። ሲጀመር፤ ኦህአዴድ እንዲመሰረት መንድርደሪያ የሆነው ሕወሓት የወቅቱ የኦሮሞ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይ የሆነውን ኦነግን ለመያዝ ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት በመቅረቱ ነው የሚሉ ሰነዶች አሉ። ያንን ክፍተት ለመሙላትም የሄደበት መንገድ ከራሱና ከሻዕቢያ ምርኮኛ የኦሮሞ ወታደሮችን ከያሉበት ቦታ በመሰብሰብ፤ በመጀመሪያ በኢህዲን ውስጥ፤ ቀጥሎም ራሳቸውን ችለው የፖለቲካ ድርጅት እንዲሆኑ አስቻለ። ሕወሓት ኦነግን ለማስኮብለል ወይም ጠርንፎ ለመያዝ የፈለገውና ይህም ሳይሳካ

በመቅረቱ ምርኮኛ የኦሮሞ ወታደሮችን ሰብስበ ፓርቲ ያቋቋመለት መሠረታዊ ምክንያት ልክ እንደ ቀደምቶቹ፤ ለምሳሌ ምንሊክ እነ ጎበና ዳጪን፣ ባልቻ ሣፎን ይዞ የኦሮሞን ሁለመና እንደሰበረ ሁሉ ሕወሓትም ኦሮምያ አከባቢ ገብቶ የኦሮሞን ሀብት ለመበጥበጥ መንገድ መሪ ድርጅት ስላስፈለገው ነው። በእርግጥም ኦህዴድ ከምስረታው ጀምሮ እስከ ሕወሓት አዲስ አበባ ቆይታ ማብቂያ ጊዜ ድረስ የተፈለገውን ወይም የሚጠበቅበትን ተልዕኮ ፈጽሟል። ከዚህ ጋር ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር በምርኮ ሥር የነበሩ ሰዎች (ኩማ ደመቅሳ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ሱለማን ደደፎ፣ ድሪባ አርቆ፣ ዮናታን ድቢሳ፣ ኢብራሂም መልካ፣ ባጫ ደበሌ፣ ዓለምእሸት ደግፌ፣ ዓለማየሁ አቶምሳ፣ ብርሃኑ ጁላ፣ የመሳሰሉት) ሕወሓት ፓርቲ ሲመሰረትላቸውና የኦሮሞ ሀብት ዝርፊያ ሥራ ላይ እስኪያሰማራቸው ድረስ፤ ከመጥፎ የኦሮሞ ልጅነታቸዉ ወደኋላ ያላሉበት ምክንያትም፤ በስም ተጠቃሽ ምርኮኞቹ እንደማንኛውም አገር ምርኮኛ ካሉበት የጉልበትና አይነኬ ሥራዎች ሊላቀቁ፤ ብሎም ከነበረባቸው የሥራና የኑሮ ጫና ሊተነፍሱ፤ እንዲሁም በግል ግንዛቤም የበታች ከመሆናቸው አንፃር ሲታይ እንኳን ፓርቲ ሌላም ከሱ ያነሰ ነገር ቢመሰረትላቸው አሜን ብለው የሚቀበሉና ከጫናው ለመገላገል የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ደርግን ደምስሶ መላ ሀገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ምርኮኞቹ የኦህአዴድ ፓርቲ መስራቾች ከፍተኛ ዘመቻ በማድረግ በክልል ደረጃ የኦህዴድ መንግስት በማቋቋም ሌሎች ዳግማዊ የኦሮምያ ምርኮኞችን አደራጅተዋል። እነዚያ ሁለተኛ ምርኮኞች አብዛኛዎቻቸው ለመስራትና ለመኖር ከመሰማራታቸው ውጭ ብዙዎች ምግባረ ብልሹ ከመሆናቸው የተነሳ ውሎ አድሮ ምን ይፈጠራል ብሎ ጥያቄ መጠየቅ የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው የነበሩ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ከነዚያ ሞራለ ቢሶች ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ ኦህዴድን የተቀላቀሉት ደግሞ መደራጀትን በመሠረታዊነቱ ቢቀበሉም፤ ዋና ዓላማቸው “የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም አብረህ ዝረፍ” የሚባለውን ተረት የተከተሉ ናቸው። ማህበራዊ ሜዲያዎችን ሁሉ በመክፈትና ከተማሩት

ሙያ ውጭ እስከ መውጣት ሄደው ሌሎች ያገኙትን ጥቅም አንተስ ለምን አታገኝም እያሉ የዋህ እና አቅመ ደካማ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆችን እጅ በመጠምዘዝ ወንጀል ውስጥ የነከሩ ናቸው። እነዚህ ተሰላፊዎች ከአንዳንድ ቀዳሚ ምርኮኛ ኦህዴድ ጋር በመጣመር ኮሚሽን ተቀባይ ሌቦች በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ ሌቦች በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የነባር ነዋሪዎችን ይዞታ ሁሉ በትንሽ ዋጋ ወይም ያለምንም ክፍያ በመረከብ ሰዎቹን ያለአንዳች ርህራሄ እያፈናቀሉ መሬታቸውን በመቸብቸብ በሀብት የደለቡ ናቸው። እነዚህ በጮሌነታቸው የሚታወቁበት ስልታቸው ተለዋዋጭ መሆኑና በስተመጨረሻም በመሬት ሽያጭ ኪሳቸው ሲሞላ የሚደበቁበትን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅትን ሁሉ አቋቁመው ሌላ ዘረፋ ውስጥ የገቡ ናቸው። በዚህም ሳይወሰኑ በተፈናቃይ ዜጎች ስም በሚሊዮኖች የሚቆጠር የሎቶሪ ዕጣ አዘጋጅተውና በግል ባንክ አማካይነት በመሸጥ ዕጣው ሳይወጣ ገንዘቡን ኪሳቸው የከተቱ ነፍስ በላ ወንበዴዎች ናቸው፡፡ አባይ ፀሐዬ የሚባል የሕወሓት ቀዳሚ አመራር ከነበሩት አንዱ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ ወንጀል የሠሩ፣ ኦሮሞን ያፈናቀሉና ተጠያቂም የሚሆኑት እነዚህ የኦህዴድ አባላት የሆኑ እንደሆነ ገልጿዋል።

የመጨረሻዎቹ የኦህዴድ ገጽታ ማደጎዎቹ ናቸው። እነሱም ከሁለት አቅጣጫ የተቀላቀሉ ናቸው። አንድም ከተወለዱበት ቤተሰብ ኑሮ ማነስ የተነሳ ከሕወሓት ካምፕ ተጠግተው የመላላክ ሥራ እየሰሩ ቡሌ እየተመገቡ የመማር ዕድልም አግኝተው ታማኝ ሆነው ያደጉ ናቸው። ማደጎዎቹና ብጤዎቻቸው አብዛኛዎቹ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጀምረው ክትትል እየተደረገባቸውና ፀረ ሕወሓት አቋም ያላቸውን ተማሪዎችንና መምህራንን የሚከታተሉና ፈተና ቀንቷቸው ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቢገቡም ሁለት ዓይነት ግሬዶች (የኮርስና የድርጅት) እየተሰጣቸው ተመርቀው የሚወጡ ናቸው። በተለይ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲወጡ በመደበኛ ትምህርት ሲ አግኝተው በድርጅት ኤ ማግኘትን ይመርጣሉ። ሥራ ቦታ ላይ ሲመደቡም የሚጠቀሙት ከመደበኛ ትምህርት ዉጤት በበለጠ በድርጅት ውጤት ነው።

በማምታት የተካኑ ስለሆነ፤ ማደጎዎቹ ከሁሉም የኦህዴድ ገጽታዎች የተውጣጡትን ይይዛል። በዚህ ቡድን ውስጥ ሀብት ያካበቱም ሆነ ያላካበቱ ይገኙበታል። ነገር ግን የፈላጊ ክፍያዎችን (finders fee) በመቀበል የቀድሞ ኦህዴዶችን ያደፈ እጅ ለማንፃት ሕጋዊና ሕገ ወጥ ሥራዎችን በመስራት፤ ሥነ ምግባር የጎደላቸውን ምሁራን በመግዛት ሕገ መንግስቱን ጭምር እስከ ማጠፍ ሲሄዱ ያለ የሌለ ኃይልን የሚጠቀሙ ናቸው። አስመሳይነታቸው ደግሞ በዴሞክራሲ ስም እየማሉ እና እየተገዘቱ የኦህዴድን እጅ የሚያነጹ እየመሰላቸው ብዙ ይለፋሉ፤ እነሱ ሥልጣን ላይ እስከ ቆዩ ድረስ የአገሪቱ አንድነትም ሆነ የሕዝቡ እሴቶች ደንታ የማይሰጣቸው አስመሳዮች ናቸው። ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሌላውን ሀብት እየዘረፉ የሌላውን ብሔር ምሁር ጭምር ከመግዛት የማይመለሱ ናቸው። የዳቦ ስማቸውም  የለማ ቡድን (ቲም ለማ) በመባል ይታወቃሉ።

ምንም እንኳን የሰኔ 1983ቱ ኮንፈረንስ የብዙ ፓርቲዎች ስብስብ ቢመስልም፤ ከሕወሓት የብሔር ድርጅቶችን መፍጠርና ዛሬ ድረስ እያሳደረ ካለዉ ጫና የተነሳ ኮንፈረንሱ የኢህአዴግ ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል። ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም የወቅቱ ኢህዲን ሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች ይወክላል ካልተባለ በስተቀር በወቅቱ በኢትዮጵያ ዉስጥ በሕዝብ ብዛት ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘዉን የአማራ ብሔርን የወከለ ድርጅት አልነበረም። ከዚህ ውጭ አስቂኝ በሚባል መልኩ የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ እንደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ይሁን ምኑም ሳይታወቅ በኮንፌሬንሱ ተወከለ መባሉ ነዉ።

የሽግግሩ ጊዜ ዕድሜ ያበቃል ተብሎ ታስቦ የነበረዉ በስድስት ወር ጊዜ ዉስጥ ይሆናል ቢባልም ለሌላ ስድስት ወር በመራዘሙ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የተባለዉ ‘ሕዝባዊ ምርጫ’ በሚያዚያ ወር 1984 ተካሄደ። ኦነግን ጨምሮ የሽግግር መንግስቱ ተሳታፊ የነበሩ የብሔር ድርጅቶች በሕወሓት/ኢህአዴግ መዋከባቸዉን በመግለፅ ከምርጫዉ ዉድድር ራሳቸዉን አግልለዋል። ብዙ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችም

ሕወሓት/ኢህአዴግ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን መፈናፈኛ በማሳጣት በምርጫዉ ዉስጥ በነፃነት እንዳይሳተፉ አድርጓቸዉ እንደነበረ ምስክርነታቸዉን ሰጥተዋል፡፡ ለሠላም ኮንፈረንሱም ሆነ ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት ሕወሓት/ኢህአዴግ በራሱ አምሳያ የቀረፃቸዉ ብዙ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ ሲያደርግ፤ አንድም ፓርቲ ተጠናክሮ ወጥቶ የሥልጣን ተጋሪ ወይም ተረካቢ እንዳይሆኑ ጫና ፈጥሯል፡፡ ኢህአዴግ ጫና ያደረገበትን ምክንያት ላቮስ አላን አንድ ባልታተመ ጥናቷ ዉስጥ አንድ ማንነቱ ያልተገለጸ የሕወሓት ባለሥልጣንን በመጥቀስ እንደገለጸችዉ *'We [the EPRDF] fought for 20 years, and it is not fair that any party born yesterday should compete with us. We will fight to keep the power.''* ብሏል ብላ ጽፋለች፡፡ ‹‹የሚቃወመንን ሁሉ እንደጎርፍ እናጠለቀልቃለን›› የሚለዉ የደርጉ መፈክርና ‹‹ሥልጣን ለማቆየት እንዋጋለን›› የሚለዉ የሕወሓቱ ባለሥልጣን አባባል ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይኖራቸዉ ወይም "ሥልጣንህን ከማጣት በላይ ውድቀት የለምና ሥልጣንህን ለማስጠበቅ የሚረዳህ እስከሆነ ድረስ ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ አትቦዝን" የሚለውን የኒኮሎ ማኪያቬሊን የጮካኔ አስተምሮ በመጠቀም የ1984ቱ ምርጫ የፓርቲዎችን ሕልዉና እያቀጨጨ ያንድ ቡድን ወይም ያንድ ግለሰብ አምባገነንነትን የገነባበት ጊዜ ነበር፡፡ <u>አምባገነንነት የአንድ ግለሰብ፣ ቡድን</u> <u>ወይም የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ሲሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሕልዉናና የተለየ አስተሳሰብን የማይቀበልና የተለየ አማራጭ እናራምድ የሚሉትን ሁሉ በጠላትነት ፈርጆ በመግደል፣ በማሰር፣ በማሳደድ፣ በማድሄየት የሚያጠፋ ነዉ፡፡</u> ፍጽም በተመሳሳይ መንገድ ባይሆንም ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደተባለው ሁሉ የኢህአዴግ አምሳያ የሆነው ብልፅግናም ኢህአዴግ በ1984 በሰራው ዓይነት ሁኔታ ሊገዳደሩ የሚችሉ የኦሮሞ ፓርቲዎችን (ኦፌኮ እና ኦነግን) አስቀድሞ ከጨዋታ ውጭ በማድረግ የ2013ቱን ምርጫ ተአማኒ አደርጋለሁ ብሎ ብቻውን ተወዳድሮ ብቻውን አሸንፏል፡፡

ምናልባት ከቀደምት ገዥዎች ሕወሓት/ኢህአዴግ ለየት የሚያደርገዉ

አምባገነንነቱን በብልጠት ፖለቲካ መሸፈን መቻሉ ነዉ። ይኼውም ኃይሌ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ነኝ ሲል፣ መንግስቱ ሃይለማሪያም ደግሞ የሕዝብን አደራ የተቀበለ ብቸኛ መሪ ብሎ ፓርቲው ሲያንቆለጳጵሰው፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ ግን በ1987 በፀደቀዉና ሥራ ላይ ባለዉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 29(1) መሠረት ማንኛዉም ሰዉ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለዉን አመለካከት ለመያዝ እንደሚችል በመደንገግ ዴሞክራሲያዊ ማስመሰሉ ነዉ። በተጨማሪም፤ የዴሞክራሲ ሂደቱን ያመቻቻሉ የተባሉ የተለያዩ መንግስታዊ የዴሞክራሲ ተቋማት ለይስሙላም ያህል ነፃና ገለልተኛ ናቸው የተባሉ እንደ ምርጫ ቦርድ የመሳሰሉ ተቋማት እንዲቋቋሙ መደረጋቸዉ ነዉ። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀፅ 102 የምርጫ ቦርድ፤ በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኛነት እንዲያካሂድ ከማንኛዉም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ እንደሚቋቋምና የቦርዱ አባላትም በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ ተብሎ ተደንግጓል።

በአገሪቱ የሚካሄዱ ምርጫዎችን ለመምራት እንዲችል በአዋጅ የተቋቋመዉ የምርጫ ቦርድም የፖለቲካ ፓርቲዎችን በበላይነት መቆጣተር የሚያስችለውን የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ወጥቶለታል። በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ እንደተጠቀሰዉ የምርጫ ቦርድና ሌሎች የዲሞክራሲና የፍትህ አካላት እንዲሁም መገናኛ ብዙሃን “ከማናቸዉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፅዕኖ በነፃና በገለልተኛነት ሕዝብን ማገልገል እንዳለባቸዉ” ያስገነዝባል። ይህ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ወደፊት ታሪክ የራሱን ፍርድ የሚሰጥ ቢሆንም ብዙዎች የዚህ መመሪያ አንቀጾች አንድም በቦርዱ ተጥሷል፤ ወይም ለገዥዉ ፓርቲ በሚያመች ሁኔታ ሥራ ላይ እንዲዉል ተደርጓል።

የምርጫ ቦርድ ገለልተኛነት ማጣት ጥያቄ ምልክት ዉስጥ መግባት የሚጀምረዉ ለፖለቲካ ፓርቲዎች መግለጫ ከመስጠት ጀምሮ ይሆናል።

ለምሳሌም ታህሳስ 3 ቀን 2006 የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለ2007ቱ ጠቅላላ ምርጫ ዝግጅት "የምርጫ አለመግባባት አፈታትና ቅድመ ማስጠንቀቂያ" በሚል ርዕስ ሥር ለአገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ አመራሮች በአዘጋጀዉ መግለጫ ላይ ስለምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት መግለጫ ሲሰጥ የምርጫ ቦርድ ሥራ አስኪያጅ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና ትንሽ እንኳን ይሉኝታ ሳይሰማዉ "አሁን በዓለም ላይ ከኢህአዴግ የሚበልጥ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ አለ ወይ?" ብሎ እየተደመመ ሲናገር ተደምጧል። እንደዚህ የሚናገር ሰዉ ያለበት አካል (ምርጫ ቦርድ) እንዴት ሆኖ ገለልተኛ ሊባልና ምርጫን የመሰለ ትልቅ ኃላፊነት የሚጣልበት ሊመራ እንደሚችል ጤነኛ አእምሮ ያለዉ ሰዉ ይፍረድ ብዬ ከማለፌ በፊት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ (1998፡ 394) ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ "በምንም ዓይነት ሁኔታ በዕዉቀትም፣ በልምድም፣ በባህርይም እንደዚህ ዓይነት አቢይ ተቋም [ምርጫ ቦርድን] እንዲመሩ ኃላፊነት የሚሰጣቸዉ ሰዎች፤ የኢህአዴግ ዓይነት ኃይል ተቋቁመዉ ለሕሊናቸዉ ያድራሉ ተብለዉ ሊገመቱ የሚችሉ ሰዎች አይደሉም" በማለት የምርጫ ቦርድ ሰዎችን ብቃት ጥያቄ ምልክት ዉስጥ በሚከት ዓይነት ሁኔታ ጽፏል። ለቦርዱ ሥራ አስኪያጅ ውለታም በውጪ አገር የመንግስት፣ የሀገርና የሕዝብ 'አምባሳደር' ሆኖ ተሹሟል። (ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የኢህአዴግን የ1997 ምርጫን አስመልክቶ ብዙ ትንተናዎችን ጽፏል። መሠረት ያደረገውም ቅንጅት የተባለውን የፓርቲዎች ስብስብን በመምራቱ ጭምር ስለሆነ፤ ስለዚሁ ቅንጅት በዚህ መጽሐፍ አንድ ቦታ ላይ እንደማነሳ ለአንባቢያን እገልፃለሁ።)

የምርጫ ቦርዱ ሰብሳቢ እንዲያ መናገሩና ሌሎችንም የቦርዱ አባላት ጨምሮ ገለልተኝነት ማጣቱን መግለጹ የሚመነጨዉ የምርጫ ቦርድ ተሿሚ ግለሰቦች ተመልምለዉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበዉ የሚሾሙት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ስለሆነና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስትርነቱ በተጨማሪ የገዥዉ ፓርቲ ሕወሓት/ኢህአዴግ መሪና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ፣ የአገሪቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የደህንነቱና የፖሊስ ተቋማት የበላይ ኃላፊ

ሲሆን፤ በሌላም በኩል ሦስቱ የመንግስት አካላት (ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሥራ አስፈጻሚ) አንዱ ሌላውን በማይቆጣጠርበት አገር ዉስጥ የሚኖሩ ስለሆነ፤ የምርጫ ቦርዱ ባለሥልጣናት ፍርሃት ቢያድርባቸውና ያለምንም ይሉኝታ ገዥውን ፓርቲ ቢያመሰግኑ አይፈረድባቸዉም። ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ፍርሃት ምን ሊያከትል እንደሚችል ለማ ደገፋ ከላይ በተጠቀሰዉ መጽሐፉ (2012፡ 119) *"Fear is one major obstacle that can easily drift us out of the way when we face challenges."* ብሏል። ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ ደግሞ እንደ ከብት ሐኪሙ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና ዓይነቱ ግለሰቦች ከሙያቸዉ ርቀዉ በሥራ ላይ የሚሰማሩ ከሆነና በተለይም የሙያ ሥነ ምግባር ያልተላበሱ ወይም የሙያ ሥነ ምግባራቸዉን አዉልቀዉ የሚጥሉ ከሆነ፤ ስለገለልተኛነታቸዉ ማሰቡ ጊዜና ጉልበት ከማባከን በዘለለ ብዙም አይፈይድም። ስለምርጫ ነፃ፣ ፍትሓዊና ተአማሚነት ስታሰብ የምርጫ ቦርድን አወቃቀር ከውስብስብ አደረጃጀቱ ነፃ የሚሆኑበትን አብሮ ማሰብ ያስፈልጋል።

ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የሚባለዉና የአገሪቱን የሠላም፣ የዲሞክራሲ፣ የሰብአዊነት ጥበቃና የልማት መሠረት ለመጣል የሚችል መንግስትን ለመመስረት የሚያግዝ ነዉ ብሎ መጠበቁ የፖለቲካ የዋህነት ይሆናል። ፖለቲካን በየዋህነት መስራት አይቻልም እያልኩ አይደለም፤ ምክንያቱም በሰጥቶ መቀበል ዉስጥ የፖለቲካ የዋህነት ሊኖር ስለሚችል ነዉ። ይህንንና በሌሎችም አፈፃፀም የምርጫ ቦርድ ከገለልተኝነት በተቃራኒ በመቆሙና ለሁሉም ዜጎች የሚመች የፖለቲካ ሥራ ባለመስራቱ የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ እንዲሽመደመድ በማድረጉ ዉስጥ ምን ሚና እና ምን ያህል ክፋት እንደተጫወተ ለመግለፅ ያህል ብቻ ነዉ እዚህ ላይ የገባዉ። እዚህ ላይ በዋናነት ሊሰመርበት የሚገባዉ ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ ምርጫ ሥራ ዉስጥ እዉነተኛና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ቢኖር ኖሮ የተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ወይም የምርጫ ታዛቢዎች የሚባል የሰዉ ኃይል መመደብ አስፈላጊ አይሆኑም፤ ወይም ይኑር እንኳን ቢባል ያንን ያህል

ሰፊ ቁጥር አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። በጣር የሚገኝ ገንዘብም ላይባክን ይችላል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ምርጫ ለሚመስል ነገር፤ በርግጥ ግን ምርጫ ላልሆነ ነገር፤ ግርግር ፈጥሮ የዚህችን ድሃ አገር ትንሽ ሀብት ማባከንም ባላስፈላገ ነበር። እንግዲህ ፌዴራላዊ የመንግስት ሥርአት እንዲቋቋምም ሆነ ዲሞክራሲ እንዲያብብ ሰፊ ሚና ይኖራቸዋል ተብለዉ ከተቋቋሙት የዴሞክራሲ ተቋማት ዉስጥ የምርጫ ቦርድ ዕጣ ፈንታ እንዲህ ሆኖ ካበቃለት፤ ሌሎቹ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት የሚቻል ስለሆነ፤ ይህንን እዚህ ላይ ቆም አድርጌ፤ የፓርቲ ፖለቲካን ያሽመደመዱና ሌሎች ለኢትዮጵያዊያን ፌዴራላዊ አንድነት ደንቃራ የሆኑ የሕወሓት/ኢህአዴግ እኩይ ድርጊቶችን በቀጣይነት አመለክታለሁ።

የአገራችንን የፓርቲ ፖለቲካ ካቀጨጩት ዉስጥ አንዱ የኢህአዴግ የአዉራ ፓርቲነት *(dominant party)*፣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ልማታዊ መንግስት የሚባሉ አደንቋሪ ፖለቲካዎች ናቸዉ። አደንቋሪ የሚያስብላቸው ደግሞ እኛ ከሌለን ሀገር ብሎ ነገር ሊኖር አይችልም ብለው የአህያ ተረት መደስኮራቸው ነው። ሕወሓት እንደምሳሌ አድርጎ የሚወስዳቸዉ በዓለም ላይ የአውራ ፓርቲ አመራርን የሚከተሉ አገሮች ብዙ ናቸዉ፤ ቻይና፣ ጃፓን፣ ሴንጋፖር፣ ሩሲያ፣ ኬንያ፣ ዚምባቡዌ፣ ዩጋንዳ፣ የመሳሰሉ አገሮች ጥቂቶች ናቸዉ። እነዚህ አገሮች አውራ የሚባሉ ፓርቲዎቻቸዉ የተቋቋሙበት ጊዜና ሁኔታ አሁን ኢትዮጵያ ካለችበት ጊዜና ሁኔታ ጋር ሲተያይ ለየቅል ናቸዉ። ለምሳሌ የጃፓን ፓርቲ የተቋቋመዉ የጃፓን ሚሊታሪዝም ከተደመሰሰ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ ሲሆን፤ እነሱም የጃፓን ሚሊታሪዝም የመራዉ ዓይነት ፓርቲ እንደገና በአገራቸዉ ዉስጥ ላለማየት ስለሚፈልጉ አሁን ሥልጣን ላይ ባለዉ ፓርቲ ብቻ እንዲኖሩ የሙጥኝ ያሉበት ነዉ። የጃፓንን አውራ ፓርቲ ከሌሎች አገሮች ለየት የሚያደርገዉ አባላቱ የአንድ ፓርቲ አገር ቢሆኑም መንግስት ለመምራት የሚወዳደሩት ግለሰብ የፓርቲ አባላቱ ግን ከፓርቲዉ ፖሊሲ እስከ መለየት ድረስ የሚያደርስና ሊያሰራቸዉ የሚችል፤ እንዲሁም በሕዝብ ዘንድ መሠረታዊ ሊሆን የሚችል የራሳቸዉን ፖሊሲ ቀርፀዉ በሚያቀርቡት የማህበረ ኤኮኖሚያዊ ዕድገት

ፖሊሲ መሠረት ይለያሉ። ማለትም የሚመረጡት መሪዎች የጃፓንን ሁለንትናዊ ዕድገት ማስመዝገብ የሚችሉ በተግባር የተመሰከረላቸዉ ናቸዉ። The Asian Aspiration (2020፡ 29) በማለት እነ Greg Mills በአዘጋጁት መፅሐፍ ውስጥ "Japan's industrialization was based on three key elements: a strong private sector, a supportive state and an ability to adapt and absorb outside influences, including technology, ideas, machines and capital." እሳቤዎች የጃፓን አውራ ፓርቲ መገለጫዎች ናቸው።

በጃፓን አገር የፓርቲ አባላቱ እከክልኝ ልከክልህ በሚል ፈሊጥ በሕዝብ ሀብት ላይ ፊጥ የማይሉ ስለሆነ ብቸኛ ወይም አውራ ፓርቲ ሆነው ለረጅም ጊዜ ሥልጣን ላይ እንዲቆዩ አስችሎአቸዋል። በኢህአዴጉ ኢትዮጵያ ግን የግል ክፍለ ኤኮኖሚው እንዲቆረቁዝ ይደረጋል፣ መንግስት አልሞ ድጋፍ ካለማድረጉም በላይ ሬድኤት ሰጪ አገሮችና ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ከሚያደርጉት እገዛ እንኳ ሳይቀር እየቆነጠሩ በግል የባንክ አካውንታቸው ያጠራቅማሉ፣ በተጨማሪም የውጪ ዕውቀትን፣ ቴክኖጂን፣ ማሽንና ካፒታልን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ላይ ዳተኛ ከመሆናቸውም በላይ የሀገርን ሀብት በመዝረፍ ላይ የተሰማሩ ሌቦች ይበዙባቸዋል። ስለሆነም፤ የጃፓን ዓይነት አውራ ፓርቲ ጋር አያነፃፅራቸውም። በነገራችን ላይ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ወደ ሥልጣን በመጣበት ወቅት ላይ የኢትዮጵያ እና የጃፓን የዕድገት ደረጃ ተመሳሳይ ደረጃ አከባቢ ላይ እንደነበረ አጥኚዎች ይገልፃሉ። ነገር ግን ልዩነት የተፈጠረው የኢትዮጵያ መሪዎች እንወደዋለን ለሚሉት ሕዝባቸው የሚጠበቅባቸውን ያህል አለመስራታቸው ትልቁ ችግር ሆኖ ስለቆየ ነው። በነገራችን ላይ ጃፓኖች አሃዳዊ የመንግስት አስተዳደር የሚከተሉ ቢሆንም ሥልጣንን ለየክፍለ ሀገራት ያከፋፈሉ ናቸው።

ሌላዋ ባለአውራ ፓርቲዋ ቻይና በዓለም በሁለተኛነት ጠንካራ የሚሰኝ ኤኮኖሚ የገነባች አገር ነች። ነገር ግን ቻይና በአገሯ ዉስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰብአዊነት የሚትሰጠዉ ቦታ ወይ ጨርሶ የለም፤ ወይም

ደግሞ እጅግ  በጣም አናሳ ነዉ። ዜጎችን ማዕከል የማያደርግ የኤኮኖሚ ፖሊሲና ዕድገት የገቸዉ ፓርቲ አባላትን ማዕከል ያደረገ ስለሆነ፤ ምሳሌነቱ ዛሬ ዓለም በደረሰበት የ21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ የቻይና ዓይነቱ አውራ ፓርቲ አመራር ምሳሌነት ተቀባይነቱ እጅግ እጅግ በጣም አናሳ ነው። ምክንያቱም፤ የዜጎችን መብት የማይጠብቅና ሰብአዊነትን ግምት ዉስጥ የማያስገባ በአውራ ፓርቲ የተመራ ዕድገት ምንም ያህል ዕድገት ይሁን፤ ምንም ያህል ድንጋይ በድንጋይ ላይ ቢቆለል፤ ዛሬ የዓለም ሕዝቦች ከደረሱበት የዲሞክራሲ ዕድገት ደረጃ ሰብአዊነት የሚጎድለዉን የቻይናምን ሆነ የኢትዮጵያን ዓይነት አውራ ፓርቲ አገዛዝ አይሹም።

ሴንጋፖር በአዉራ ፓርቲ የሚትመራ ሀገር ቢትሆንም ለዕድገታቸዉ ተጠቃሽ የሚሆነዉ የአዉራዉ ፓርቲያቸዉ ሚና ሳይሆን ከፍተኛዉን አስተዋጽኦ ያደረገዉ የደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮችን ከኮሚኒዝም መስፋፋት ለመከላከል እነ አሜሪካ የሰጡት ገደብየለሽ ሁሉን አቀፍ ዕርዳታ ነዉ። ሴንጋፖሮች የተሰጣቸዉን ሀብት ሁሉ ኪሳቸው ሳይከቱ ወይም ወደ ውጪ ባንኮች ሳያሸሹ ለአገራቸው ዕድገት በአግባቡ በመጠቀማቸዉ ዛሬ ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ሰንጋፖሮች የሚፈልጉትና መስራት ያለባቸውን ሥራዎች በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል። ሀገራቸውን ከድህነት ለማላቀቅ በመጀመሪያ ካፒታልና የግል እንቨስትመንት እንደሚያስፈልጋቸው ተረዱ። እነዚህን ከማፈላለግ ጋር ስለሚሠሩ ሥራዎች ቅደም ተከተል ለማውጣት ቻሉ። መሬትን ምርታማ ለማድረግ፣ የቤት ችግርን ለመፍታት፣ የሥራ ዕድልን መክፈት እና እንቨስትመንትን ለማስፋፋት ተበርታተው ተነሱ። ምናልባት፤ የኢህአዴግ ሰዎች ቢጠየቁ እኛም አድርገናል ይሉ ይሆናል። ላለማድረጋቸው ሰፊ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ የመሬት አስተዳደርን የሕዝብና የመንግስት ብለው የኢህአዴግ ፓርቲ አባላት ብቻ የሚቸበችቡት ማድረጋቸውን መስማት አንጀት የሚያቆስል ነው። የቤት ችግርን ለመፍታት ደሳሳ የድሃ ጎጆዎችን ማፍረስ እንጂ በቦታው ላይ የድሃ ሕዝቡን ዐቅም የሚመጥን የሚገነባ የለም። ሲብስ ደግሞ የተገነቡ ኮንዶን ቤቶች የግንባታ ጥራት ከማጣታቸው በላይ  የኢህአዴግ

ካድሬዎች እሱንም ብዙ ቁልፎችን በመረካከብ ይቸበችቡታል። በተከፈተው ትንንሽ የሥራ ዕድሎች ላይ አንድም የማይሰሩ ወይም የማያሰሩ ገጣባ ካድሬዎች ተመደቡ። እንሸስትመንት እንዳይበረታታ ቀማኛ ካድሬዎች ተመደቡ። ጥፋተኞች ተለይተዉ እንዳይጠየቁ ፍቱን መፍትኼው ሆኖ ያገኙት የዘረፉትን መከፋፈል ነው። ሌቦች ከስርቆት ጊዜ ይልቅ ሲከፋፈል ነዉ የሚጣሉት የሚባለዉን ንቅተው ተቆጣጥረውታል። ስለሆነም፤ ኢትዮጵያም እንደ ሰንጋፖር አልበለጸገችም፤ አውራ ፓርቲውም ከምኞት ሊያልፍ አልቻለም። ሰንጋፖሮች የልማት ዕቅዳቸውን ጀምረው ዛሬ ከደረሱበት የብልፅግና ደረጃ ለመድረስ ከ30 እስከ 33 ዓመታትን ብቻ ፈጅቶባቸዋል። የኛዋ የባለ 3000 የነፃነት ዘመኗን ጠብቃ የኖረች አገር ኢትዮጵያ ዜጎች ሆዳቸውን እየፎክቱ የሚያድሩባት ነች። ምናልባት በእጅ የሚሄደው የሕወሓት/ኢህአዴግ አውራ ፓርቲ ፖለቲካ የዜጎችን የድህነት ጊዜ ለማራዘም ካልሆነ በስተቀር ፋይዳ የለውም። በዚያዉ ማህበር ዉስጥ የነበረችና በየጊዜዉ በመፈንቅለ መንግስት የምትናጠዉ ታይላንድ የማህበሩ አባል፤ ያገኙትን ዕርዳታ ሁሉ በአግባቡ ባለመጠቀማቸዉ፤ ዕድገት እንኳን ቢኖራቸዉ ዛሬ ሴንጋፖር ከደረሰችበት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር እኩል አይደሉም። ምክንያቱ ደግሞ ዛሬ ኢትዮጵያችን ዉስጥ እየታየ እንዳለዉ ዓይነት ለአገር የተሰጣቸዉን ዕርዳታ የመንግስቱ ባለሥልጣናት የተለየ ጥቅም የሚያገኙበትን ድርጅቶች (favored firms) ውስጥ በመኖራቸዉና ይካበታል የሚባለው ሀብት በመመዝበሩ እንደ እስያ ታይገር ኢኮኖሚ ለማደግ ገና ሌላ ሦስት ሺህ ዘመን ሳይጠይቅ አይቀርም።

የኬንያና የዚምባቡዌ አውራ ፓርቲነት የተመሠረተው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል በሚደረግበት ወቅትና ሁኔታ ጋር ተያይዞ ነዉ። የእነዚህ ፓርቲዎች መሪዎች የነበሩና ዛሬም ሥልጣን ላይ ያሉት መሪዎች (የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ዕትም ከመዉጣቱ በፊት የነበሩት) የፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል መሪዎች የደም ግንኙነት ያላቸዉ ዜጎችና ሌሎች ፖለቲከኞች ነባሩን ታሪክ ተጠቅመዉ፤ የሥልጣን ምንጭ የሆነዉን ሕዝቦቻቸዉ አንገታቸዉን ቀና አድርገዉ እንዳያዩአቸዉ ያደረጉ ናቸዉ። ወይም ዩጋንዳን የሚገዛ ፓርቲን

የመሳሰሉ ፓርቲዎች ቀደምት አምባገነን መሪዎቻቸዉን በረጅም ጊዜ የትጥቅ ትግል ያስወገዱና የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትን የውለታ ክፍያ አድርገዉ ቅሚያ የፈፀሙ ናቸዉ። ስለሆነም፤ አንድ ሕዝባዊ አመፅ ወይም ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ከሥልጣን እስከሚያስወግዳቸዉ ድረስ ራሳቸዉን ከሕዝቡ በላይ የሥልጣን ምንጭና አድራጊ ፈጣሪ አድርገዉ ያስቀመጡ ናቸዉ። ምንም እንኳን ኬኒያ የአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚታጠብቅ አገር ቢትሆንም፤ አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመልክቱት ኢትዮጵያ ዛሬ ጎረቤት ኬንያ ከደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ኬንያ ቢያንስ ለሃያ ወይም ሰላሳ ዓመታት ቁማ ኢትዮጵያን መጠበቅ ይኖርባታል።

ዛሬ በ21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ የዓለም የፖለቲካና የግንኙነት ሁኔታ በጣም አጭርና የተቀራረበ (ሉላዊነት) በሰፈነበት ጊዜ ዉስጥና ባለአዉራ ፓርቲ መንግስታት ዉስጥ የሚከናወኑ ሥራዎች በግልፅ እየታወቀ፤ የሕወሓት/ኢህአዴግ አዉራ ፓርቲነት መለዮ ሁሉንም የአገሪቱን ዜጎች እንደማያስማማ ሊረዱ የሚችሉ ይመስለኛል። ምክንያቱም ሲዳማ፣ ኦሮሞ፣ ሐዲያ፣ ጋሙ፣ ካፍቾ፣ ሻክቾ፣ የመሳሰሉት ሕዝቦች ከአበሾች ወረራ በፊት ጀምሮ የየራሳቸው ልማዳዊ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ስለነበራቸዉ፤ እንደዚህ ዓይነት የቆየና የኋላ ታሪክ ያላቸዉ ሕዝቦች የአንድ ወይም የጥቂት አምባገነንነት አውራ ፓርቲ አገዛዝ ይጎረብጣቸዋል። ስለዚህም፤ የአውራ ፓርቲ ፖለቲካ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች በተለይም ባህላዊ እሴቶቻቸዉ ለተለያዩ የሕብረተሰብ ወገኖች አክብሮት ለሚሰጠዉ ከኦሮሞና ከደቡቡ ሕዝብ እሴቶች ጋር አይዘልቅም። ኦሮሞን ጨምሮ የሌሎች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች አመራር በሰው መብት ወይም እኩልነትን የሚያምን እሴት (egalitarian) ሲሆን የዚህ ተቃራኒ የሆነው የሐበሻ ዝሪያ ያላቸው ሴሜትኮች ደግሞ ደረጃን የጠበቀ ተዋረድ (hierarchical) የሆነ ነው። ሁለቱ እሴቶች ከመጣጣም ይልቅ የመራጋጥ ስሜት ይታይባቸዋል።

የሕወሓት/ኢህአዴግን የአውራ ፓርቲነት መስመር እየገዘፈ እንዲሄድ

ያደረጉት አምስት ዋና ዋና የሕወሓት/ኢህአዴግ መሠረታዊ ችግሮች ናቸዉ። እነዚህ ለፓርቲ ፖለቲካ መጫጨት በቀደምትነት ተጠቃሾች የሆኑት የሕወሓት በቁጥር አናሳ ከሆነ ሕዝብ መምጣት፣ ሙሰኝነት፣ ኪራይ ሰብሳቢነትና የመልካም አስተዳደር እጦት ናቸዉ። በአጭር አጭሩ እንመለከታለን።

ሳቢም ሆነ ገፊ ሁኔታ ሊባል ይችላል፤ ሕወሓት በአውራ ፓርቲ አካሄድ ላይ እንዲያተኩር የገፋፋዉ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር፤ በተለይም በተቀናቃኝነት ከፈረጃቸዉ የአማራና የኦሮሞ፣ መለስ ባለ ደረጃም ቢጠቀስ ከሲዳማና ወላይታ፣ እንዲሁም ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ የሚባለዉን የሕዝብ ቁጥር በመወከል ሥልጣን ላይ የተቀመጠ ነው። አነስተኛ ቁጥር ያላቸዉን ሕዝቦችን (minority) የሚወክሉ ፓርቲዎች ደግሞ በብዙሃን እንደሚዋጡ በመገመት ዘወትር በሥጋት ውስጥ ስለሚኖሩ በብዙሃን አስተዳደርና የጥቂቶች መብት መከበር (majority rule and minority rights respect) የሚለዉን የዴሞክራሲ መርህ እንደመርህ ቢቀበሉትም እውነት ነው ብለው በድርጊት ለማየት አይፈልጉም። በመሆኑም የአዉራ ፓርቲ ሕልዉናን ከወቅታዊ ሁኔታ ውጭ በሆነ ሁኔታ ሥራ ላይ ለማዋል የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ላቨስ አላን (2002: 9) ኦታዌን በመጥቀስ *"The TPLF was politically weak when it came to power, because it represented less ten percent of the population."* ብላ የፃፈችዉ ሐሳቤን ያጠናክርልኛል። ሕወሓት አራት ኪሎ ባለዉ ወንበር ላይ ቁጭ ካለም በኋላ እንኳን በ21ኛዉ መቶ ዓመት ላይ ሆኖ እና የዓለም የዲሞክራሲ ዕድገት ከደረሰበት ደረጃም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚጠይቀዉና በሚፈልገዉ መሠረት፤ ኢትዮጵያን እየገዛም ይሁን እያስተዳደረ፤ ዛሬም ቢሆን ሕወሓት በቁጥር አናሳ ከሆነው መምጣቱን በማሰብ ከትግራይ ነፃ አውጭነቱ፤ በሌላ አገላለፅም ከጦረኛነቱ ራሱን አላላቀቀም። ወይም በቅርብ ጊዜ ይላቀቃል ተብሎም ለመጠበቅ ደግሞ ምቹ ሁኔታ ላይ አይገኝም። ላለመቀየሩም አንድ አቢይ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ ከአናሳ የሕዝብ ቁጥር ካለዉ ብሔር የመጣ ስለሆነ፤ ከዕለታት አንድ ቀን የዴሞክራሲ ትግሉ እየጎለበተ ቢሄድ የሚያጓጉዘዉ

ኮተት አይኖርምና በየክልሉ የበተናቸዉንና መሰብሰብ የሚችላቸዉን ዜጎቹንና ሀብቱን ስብሰቦ ወደ  ትግራይ ለመግባት፤ ለዚህም የሚያበቃ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ እራሱ በፈጠራቸዉ ዴዴዎች (PDOs) ጋር የራሱን ሥራ እየሰራ መቆየት አስቦ ይሆናል። ሰለሞን ስዩም ስለነዚያ ዴዴዎች <u>በኢህአዴግ ፍፃሜ መጽሐፉ</u> (ገፅ 157) ሲፅፍ፤ ኦሮምያ አቋቸውን መግለፅ የማይችሉ፤ ነገር ግን በኮታ ብቻ የሚወከሉ ግዑዝ ፖለቲከኞች ይሞሏታል ያለው፤ ባለአዉራ ፓርቲ ሕወሓትን ተንከባካቢ ፓርቲዎች መኖራቸውን ለመግለፅ ፈልጎ ነው። እነዚያ የራሳቸዉ የፖለቲካ አጀንዳ የሌላቸዉ ዴዴዎች ክፋታቸው የራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ይዘዉ አለመቋቋማቸው ብቻ ሳይሆን ሕዝባዊ ትግል በሚመሩ ድርጅቶች ላይ የሌለ ጥላቻ በመፍጠር፣ የተለያዩ ስሞችን በመለጠፍ ለአናሳው ሕወሓት ሥራ ሲሉ ያሳድዷቸዋል፤ በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ ያደርጓቸዋል። ሌሎች ደግሞ በመናኛ ጥቅሞች ተደለልለዉ ፓርቲ መሠረትን በማለት ገዥዎቻቸዉ ምን እንደሚሏቸዉ እንኳን በወጉ ሳይረዱ፤ እንዲያዉም አይቻልም በማይባልበት ዓይነት ሁኔታና ቦታዎች ሁሉ እየገቡ ከሰብአዊነት ወደ እንስሳነት እየተቀየሩ የሐሳብ ልዩነት ያሳየዉን ዜጋ ሁሉ በጠላትነት ይፈርጃሉ። በዚህም መሠረት ለሕዝቦቻቸዉ ዴሞክራሲና ነፃነት የሚታገሉትን ዜጎች ሐሳባቸዉን በሐሳብ ማሸነፍ ስለማይችሉ በጥቅም በመደለል፣ በማሳሰር፣ ስማቸዉን በማጠልሸት፣ ከአገር በማሳደድ፣ እራሳቸዉንና ቤተሰቦቻቸዉን ለኤኮኖሚያዊ ችግር በማጋለጥ፣ ወዘተ ወንጀል በመፈጸም የገዥዉን ፓርቲ ፍላጎት ያሳካሉ። ላቨስ አላን (2002፡ 39) አሁንም በጥናቷ እንደገለጸችዉ *"The organizations that became members of the EPRDF were to a large extent created by the TPLF itself and did not initially have any popular base." መረራ ጉዲናም (2003፡123) ይህንኑ የአላንን ሐሳብ በሚያጠናክር ሁኔታ፤ ". . . PDOs are not locally and independently initiated political groups, but, TPLF created 'Peoples Democratic Organizations' for the control of non- Tigiryan ethnic groups of the country."* ብሏል። በኦሮሞ ብሔር ስም የተቋቋሙ ዴዴዎች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው እነሱ ከአቅም ማጣት የተነሳ ማሸነፍ አልቻሉም እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉት ምርጫዎች ሁሉ

ዴሞክራሲያዊ እንደነበሩና በወንጀል በመጠርጠራቸው እንጂ በፖለቲካ ሐሳብ ልዩነት ምክንያት አንድም የታሰረ ሰው እንደሌለ በማስረገጥ ያለምንም ሐፍረት የጋራ መግለጫ የሰጡ ናቸዉ።

ሕወሓት እነዚህን በበላይነት የሚቆጣጠራቸዉን ዴዴዎች በተሰጣቸዉ ትዕዛዝ መሠረት ማከናወናቸዉን የሚያረጋግጠዉና የአውራ ፓርቲነቱ ዓላማ ሥር መስደዱን የሚረዳዉ አምስት ለአንድ በሚባል የቁጥጥርና የጥርነፋ ሥራ በማሰራት ነዉ። ሕወሓት/ኢህአዴግ የማይቆጣጠረዉ የፖለቲካም ሆነ ሕዝባዊ ማህበር ቢኖር ሃርድ ኮር እያለ ያሳድዳል፤ ከአሸባሪነት ጎራ ይፈርጃል። ለቁጥጥራቸዉም የሚሰጡት ምክንያትና አንዳንዶች እንደሚያስወሩላቸዉ ሕወሓት/ኢህአዴግ አዉራ ፓርቲ እንዲሆን የገፋፋዉ ያለዉን የአገሪቱን የሰዉም ሆነ ሌላ ሀብት ሳይበታተን (ከኢህአዴግ የታክቲክ ብተና ወዲህ ደግሞ መደመር) ለአገር ግንባታ እንዲውል አስቦ ነዉ የሚሉ አሉ። ነገር ግን የአውራ ፓርቲነት አባዜዉ የሚመነጨዉ ከነባር ምንጩና አልፎበት ከመጣዉ ታሪኩ ይሆናል። ሕወሓት በትግሬ ግዛት በአሲምባ ተራራ ሥር የተጠለለዉን የኢሕአፓ ሠራዊት አሰድዶ መታና ርዝራዥ አካሉን ደግሞ ኢህዲን ብሎ ስም በመስጠት ዋጠዉ። የአዲስ አበባዉ ኮንፈረንስ ሲጠራ ሕብረ ብሔር ፓርቲዎችን በማስወገድ ኋላ ላይ ደግሞ በ1984ቱ የአካባቢ ምርጫ ጊዜ ደግሞ ሌሎችን የሱ ተቀጥላ ያልሆኑና የራሳቸው ነፃ ሐሳብ ያላቸውን በማዋከብ አስወገዳቸዉ። ከዚያ በኋላ ባሉት ጊዜያት ዉስጥ ተቃዋሚ ሆነዉ ለተመሠረቱት ፓርቲዎች በበላይነት የሚያዙባቸዉን የመንግስት መዋቅሮችን በመጠቀም ሠላም የነሷቸዉና አሁንም ከፍተኛ ጫና የሚፈጥሩባቸዉ ስለሆነ የሕወሓት/ኢህአዴግ የአዉራ ፓርቲነት ስሜት አብሮ ተወልዶ አብሮ ያደገ ክፉ ባህርይ ነዉ እንጂ በምንም ዓይነት መመዘኛ የሕዝብ ዓላማና ሰልፉ ሳይበታተን ለአገር ግንባታ ለማዋል የዘየደዉ ዘዴ አይደለም። ሲጠቃለል፤ አዉራ ፓርቲነት የተለያየ አመለካከት ያላቸዉን የኢትዮጵያ ሕዝቦችን በአገር ስሜት ማስተባበርና ማሳተፍ የማይችል ከሶሻሊዝም ወይም ከቻይናዉ አዲሱ ዴሞክራሲ የተቋጨ ነፃ ያልሆነ ዲቃላ አመለካከት ነዉ።

የሕወሓት/ኢህአዴግ የአውራ ፓርቲነት አባዜ ወንበሩን ከተረከበው የብልፅግና ፓርቲም ሊላቀቅ አልቻለም። ብልፅግናም እንደቀዳሚው ሕወሓት አንደኛ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉ ተገዥ ሊሆኑ የሚችሉ ፓርቲዎችን በማባበልና ያልተቀደሰ ትብብር በመፍጠር እየዋጣቸው ይገኛል። በተለይም ለሕዝብ ዓላማ ቃል ገባን በማለት ዞር ሲሉ ደግሞ በመናኛ ጥቅማ ጥቅም ሊገዙ የሚችሉትን እየገዛቸው ይገኛል። ሁለተኛና ትልቁ የገኘው ፓርቲ ወደ አውራ ፓርቲነት እየተሸጋገረ ያለው ምንም ዓይነት ሚና መጫወት የማይችለው ፓርላማው በሚያወጣው አዋጅ እንደ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በመሳሰሉ መሳሪያነት እየተጠቀመ የተለየና ነፃ አስተሳሰብ የሚያራምዱትን ፓርቲዎች አባላትን በተለይም የመንግስትና የግል ድርጅቶች ተቀጣሪዎች የሆኑትን በስልት በማዳከም ነው። የዚህ አዋጅ በተለይ ሁለት አንቀፆች የተቃዋሚ/ተፎካካሪ ፓርቲ አባላትን በተለይም የመንግስትና የግል ድርጅት ሠራተኞችን በኤኮኖሚ እንዲጎዱ በማድረግ ያንበረክካቸዋል። እንደ አዋጁ አንቀፅ 2(29) ትርጓሜ "የመንግስት ሰራተኛ ማለት በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው። ሆኖም ሚኒስትሮችን፣ ሚኒስትር ዴኤታዎችን እንዲሁም በተመሳሳይ ደረጃና ከዚያ በላይ የሆኑ የፌዴራልና የክልል የመንግስት ተሿሚዎችን የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤትንና በየደረጃው ያሉ የክልል ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላትን አይጨምርም።" በማለት ኮሮጆ በመገልበጥ የሥልጣን ወንበር የተቆናጠጡትን ባለሥልጣናት ነፃ ያደርጋል። ብልፅግና ፓርቲ ወደ አውራ ፓርቲነት የሚያደርገውን አካሄዱን ማመቻቸቱን በዚህ አንቀፅ ብቻ ሳይወሰን በዚያዉ አዋጅ አንቀፅ 33(1) ለ ምርጫ ተወዳዳሪም ሆነ ቤተሰቡ ወደ ምርጫ ውድድር ከገቡበት ቀን ጅምሮ የማይመገቡ ይመስል "የመንግስት ሰራተኛ በሕዝብ ምርጫ ለመወዳደር ተወዳዳሪ ሆኖ ሲቀርብ የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄድበት ወቅት እና ምርጫው በሚከናወንበት ጊዜ <u>ያለደመወዝ ፈቃድ</u> እንዲሰጠው ይደረጋል።" በማለት ኢ-ሰብአዊ ድንጋጌ ደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት በተቃዋሚ

ፓርቲ መስመር የተደራጁ የፓርቲ ሰዎች አንድም የተለየ መስመር እንዳይከተሉ፤ ከተከተሉም ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወክለው ለምርጫ ውድድር እንዳይቀርቡና ቢቀርቡ እንኳን በሚወዳደሩበት ጊዜ ደመወዝ የማይከፈላቸው ስለሆነ፤ የገዥው ፓርቲ አባላት ብቻ በአንቀፅ 2(29) መሰረት በተሰጣቸው ትርጉም ምክንያት ያለተቀናቃኝ አውራ ፓርቲ ሆነው ለመውጣት የዘየዱት ዘዴ ለመሆኑ ግልፅ ነው።

የሕወሓት/ኢህአዴግ ሌላዉ ችግር አብዮታዊ ዲሞክራሲ የተባለዉ አመለካከት ነዉ። አብዮታዊ ዴሞክረሲ ሲበዛ ሕወሓትን ላቋቋሙ አባሎቻቸው የወገነ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት በሚባለዉ ቃልም ሆነ ፅንሰ ሐሳብ በጣም የተሰላቹ ናቸዉ። በተለይ ደግሞ “አብዮት ልጆቿን ትበላለች” የሚባለዉን የደርግ አባባል ሕዝቡ ከቀይና ነጭ ሽብሮች ጋር በማያያዝ መጥፎ ትዝታ ስለአሳደረበት ምን ያህል እንደሚዘገንን መግለፅ ያስቸግራል። ለዚያዉም ደግሞ ለውጥን ላላመጣና ወደ አለፈዉ የደርግ አብዮታዊነት የሚያደላዉን አብዮታዊ ዲሞክራሲዊነትን ጭምር ባይሰማ ደስ ይለዋል። ሕወሓት/ኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ራሱን በቻለ ሁኔታ ሳይሆን ከሊበራል ዲሞክራሲ ጋር በንፅፅር ከማስቀመጥ በስተቀር አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም አልሰጡበትም። ሰለሞን ስዩም በፃፈዉ መጽሐፉ ገጽ 122 ላይ እንደጠቀሰው “የሕወሓት የአስተዳደር ቤተ-ሙከራ የሆነዉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ አንድም በፓርቲዉ ልሂቃን በደንብ አልተተነተነም፤ ሁለትም ለሕዝቡ ግልፅ የተደረገ ሐሳብ አይደለም። ከሕወሓት አብዮታዊ ዲሞክራሲ መረዳት የምንችለዉ አንድ ነገር ቢኖር ፍልስፍናዉ ከማኦ አዲሱ ዲሞክራሲ የተገኘ ስለመሆኑ ነዉ።” ብሏል። በጣም የረፈደበት ቢሆንም የሕወሓትን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ትርጉም ያፈላለገዉ ሀብታሙ ግርማ የተባለ በ<u>አዲስ አድማስ ጋዜጣ</u> የጥር 14 ቀን 2008 ዕትም ላይ እንደፃፈዉ “አብዮታዊ ዲሞክራሲ ከፊዉዳሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገዉ ሽግግር ፖለቲካዉ የሚመራበት አስተምህሮ ነዉ።” ብሏል። ይህ ደግሞ ለብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ከተሰጠው ትርጉም የራቀ አይደለም። ይህ አስተምሮ ሰው በሰው የሚበዘበዝበትን

የካፒታሊሰት የዕድገት ጎዳናን ወደ ጎን በመተው በፍላጎትና በችሎታ ላይ የተመሠረተ የሶሻሊሰት ኤኮኖሚ የሚገነባበት እንደሆነ በኤንግልስ የተቀረጹ መርሆችን መሠረት ያደረጉ ሰነዶች እንደሆነ ይገልፃሉ። ደርግም በ1968 ቀርፆ የተከተለዉ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከዚህ የተለየ አይደለም። ከዚህ ወጣ ካለም ሕወሓት አብዮታዊ ዲሞክራሲን የዳበረ የንድፈ ሐሳብ መሠረት ካለዉ ሊበራል ዲሞክራሲ ጋር በንፅፅር ያስቀምጣል። ማስቀመጡ በጎ ጎን ያለዉ ቢሆንም የሕወሓቱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ንፅፅር ራሱ ጉድለት ይታይበታል። እንደ የሀብታሙ ግርማ ጽሑፍም ደግሞ ለካስ ሕወሓት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በደርግ ተሞክሮ ወደ አልተሳካዉ ሶሻሊዝም የሚመልሰን ነዉ ብሎ ጥያቄ ያጭራል።

ከሚታይበት ጉድለትም ሌላ ሕወሓት/ኢህአዴግ ሊበራል ዲሞክራሲን ልክ እንደ 18ኛዉና 19ኛዉ መቶ ዓመቱ ዓይነቱ ወደኋላ መልሶ መንግስት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ቢዝነሱን ለግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ ብቻ መልቀቅ አለበት እንጂ በ21ኛ መቶኛ ክፍለ ዘመን ሊበራሊዝምን ኒዮ-ሊበራሊዝም ነዉ ብሎ በመተቸት አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለዚህ ፍቱን እንደሆነ ለማሳመን ይታትራል። ዛሬ የሕብረተሰቡ ዕድገት ከደረሰበት የ21ኛዉ መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ የሚገኘዉ ሊበራሊዝም ካለፈዉ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል ብሎ መተቸትና መጠበቅ አልፎ ተርፎም የዛሬዉ ሊበራሊዝም ኒዮ-ሊበራለዝም ነዉ ብሎ መፈረጅ ከጊዜም ሆነ ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አንፃር አስቸጋሪ ይሆናል። ምክንያቱም በለፀጉ በሚባሉ አሜሪካን በመሰለ አገር ዉስጥ በቅርቡ የተከሰተዉን የግል ድርጅቶችና የፋይናንስ ተቋማት ቀዉስን ለማስወገድ የቻሉት መንግስት የግል ቢዝነስ ጉዳይ ነዉ ብሎ ወደ ጎን ትቶ ሳይሆን ሰፊ የሆነ የድጎማና የማንሰራራት ሥራ ሰርቶ፤ በአጭሩ ጣልቃ ገብቶ በማቋቋም ነዉ። የቅርብ ጊዜ ድርጊት ስለሆነ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሊበራል ዲሞክራሲን ማጣጣል ሊሰራ አይችልም ወይም ተጨባጭ ሁኔታን ያላገነዘበ ይሆንበታል።

ኢህአዴግ ትኩረቱን በኤኮኖሚ ላይ በማተኮር እንደሚለዉ “አብዮታዊ

ዲሞክራሲ ብቃት ያለዉ የመፈፀም አቅምና ጉድለት ያለበትን ሴክተር እንዲሁም በግልፅ የሚታይ የገበያ ጉድለት የሌለባቸዉ መስኮች በባለሀብቶች የሚሰሩበትን ምቹ ሁኔታ መንግስት እየፈጠረ፤ በሌላም በኩል የገበያ ጉድለት ባለባቸዉ አከባቢዎች ይህንኑ ለመሸፈን የሚያስችል የተጠና ምርጥ ፖሊሲና ዕቅድ አስቀምጦ ከአጭር ጊዜ አኳያ ችግሩን ለማቃለል፤ በረጅሙ ጊዜ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ የሚያስችል የተመረጠ፤ ግን ሰፊ ሚና የሚኖረዉ ነው በማለት አብዮታዊ ዲሞክራሲዉን ይገልጣል፡፡ ሊበራሊዝምን ግን በደፈና የመንግስት ሚና ሊገታ ይገባል ይላል" ብሎ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የልማት መስመሮችና ስትራቴጂዎች (ለዉይይት የቀረበ) በተባለዉ መጽሔቱ በገፅ 8-9 ላይ በንፅፅር አስቀምጦ ይተቻል፡፡

በግልፅ የገበያ ጉድለት የሌለባቸዉ መስኮች በገበያና በባለሀብቶች መያዛቸዉ ባይከፋም፤ ነገር ግን አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ዉስጥ ካለችበት ኋላቀርነት የተነሳ በኤኮኖሚዉ መስክ ጉድለት የሌለባቸዉ መስኮችን ለይቶ ማግኘቱ አስቸጋሪ መሆኑ ነጋሪ የማያስፈልግ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የተጠና ምርጥ ፖሊሲና ዕቅድ አስቀምጦ ችግሩን ማቃለል የሚለዉ የሕወሓት/ኢህአዴግ አካሄድ የሚታመንም አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ከፍተኛ ችግር ካለባቸዉና የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሕይወት ከሚነኩ የሥራ መስኮች አንዱ የግብርናዉ ክፍለ ኤኮኖሚ ሲሆን፤ የዚህን ክፍለ ኤኮኖሚ ግብአቶች፤ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ማምረቻ የእጅ መሳሪያዎችን እንዲያቀርብ ኃላፊነት የተሰጠዉ ከሕወሓት/ኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች አንዱ ለሆነዉ ለአምባሰል የንግድ ሥራዎች (party firm) ስለሆነ፤ ላይ ላዩን ሲመለከቱት ገንቢ የሚመስል፤ ውሎ ሲያድር ግን የገዥዉ ፓርቲ ወገኖችና ገዥዉ ፓርቲ ራሱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የቀየሰ እንጂ የአገሪቱን ባለሀብቶችን የሚያሳትፍ አካሄድ አይደለም፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግ እስከ 1981 ድረስ የአልባኒያን ዓይነት ሶሻሊዝም ያራምድ እንደነበረና አብዮታዊ ዲሞክራሲዉ ደግሞ የዚያ ቅጥያ ነዉ እንዳይባልበት በአንድ ወቅት ‹‹ነጭ ካፒታሊዝምን›› እንደሚያራምዱ

ተደምጠዉ ነበር። የማርሽ ለውጡ የቱ ጋ እንደተደረገ ባይታወቅም የአዉራ ፓርቲነት ስሜቱ በፈጠረበት ሁኔታ የተነሳ ዲሞክራሲያዊ ነኝ ባዩ ሕወሓት/ኢህአዴግ፤ አብዮታዊም ዴሞክራሲያዊም ሊሆንም አልቻለም። የሚባለዉ ነገር ሁሉ ቢባልም ሕወሓት/ኢህአዴግ አብዮታዊም ዴሞክራሲያዊም አይደለም። ምክንያት አብዮታዊነት ምን ሊሰራ እንደሚችል የታሪክ ማጣቃሻ ስላለ ነዉ። ይኼዉም፤ ከ1789 እስከ1799 ለአስር ዓመታት የተካሄደዉ የፈረንሳይ አብዮት የፈረንሳይን ሕብረተሰብና የፈረንሳይን የፖለቲካ ሥርዓት የቀየረዉ በአብዮታዊነት ነዉ። ምንም እንኳን የአብዮቱን ድሎች በስተመጨረሻዉ ለናፖሊዮን ቢያስረክቡም፤ በአብዮቱ ጊዜ ፈረንሳይ ከፈላጭ ቆራጭ ፍጹማዊ ሞናርኪ ተላቅቃ ነፃነትና እኩልነት ወደ ሰፈነባት ሪፑብሊክ ያሸጋገረ አብዮት ነበር። ይህ አብዮት በፈረንሳይ ዉስጥ ብቻ ሳይወሰን በአዉሮፓ ሁሉ ጭምር የለዉጥ ምሳሌ ተደርጎ የተወሰደ ክስተት ነዉ።

በአስሩ የአብዮት ዓመታት ዉስጥ ፈረንሳይ ከ1789 በፊት የነበረዉን አሮጌ ሥርዓት ደመሰሰች፤ በቦታዉም ለፈረንሳዮች የሚመጥን ሥርዓት ገነባች። በፈረንሳይ አብዮት ወቅት የተለያዩ የመንግስት አመራሮች መቀያየር ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የመንግስት አመራር ከአራት ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ እንዳይዘልቅ የጊዜ ገደብ የተደረገበት ነዉ። በቆዩባቸዉ ጊዜያት ዉስጥ ግን የፈረንሳይን የፖለቲካ ሥርዓት ከመሠረቱ የሚለዉጡ ሥራዎችን ሰርተዋል። ከተሰሩት ሥራዎችም የሰዉን መብት የሚያስከብሩ ሕጎችና ሕገ መንግስት ቀርጸዋል። ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት የሚያገለግል የፖለቲካ ሥርአት ዘርግተዋል። ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ዉክልና እንዲኖር ሕጎችን ደንግገዋል፤ ተግባራዊም አድርገዋል። የፈረንሳይ አብዮት የለዉጥ አስፈላጊነት ምርጫ ግዴታ እንደሆነ በመቀበል፤ በምርጫ ለዉጥ ማምጣት የማይችሉ የመንግስት ባለሥልጣናትን ጭምር ያለማመንታት ከሥልጣናቸዉ አስወግዷል።

የ1917ቱ የሩሲያ አብዮት እስከሚያደበዝዘው ድረስ ፈረንሳይ ብቻ ሳትሆን የዓለምን ትኩረት የሳበ፤ የፈረንሳይ አብዮት በተለይም

አዉሮፓን ከፍጹማዊ ሞናርኪ ወደ ሪፑብሊክ የለወጠ አብዮት ነበረ። እንደዚህ ዓይነት አርአያነት ያለዉ አብዮት በኢትዮጵያ ቀርቶ በራሱ በሕወሓት ዉስጥ ባለመካሄዱ አብዮታዊ ሊያሰኘዉ የሚችል መመዘኛ አላሟላም። ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑ ደግሞ ብዙ ሐተታ መፃፍ ሳያስፈልግ ኢህአዴግ በ1997 (2005) እንከንየለሽ ምርጫ አካሄዳለሁ ብሎ ቢለፍፍም ሠራዊትና ካድሬዉን አሰልፎ የምርጫ ኮሮጆ ከማስገተት በቀር ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ለማየት አልቻልንም። የዲሞክራሲያዊነት አንዱና ትልቁ መገለጫ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሄድ ቢሆንም ኢህአዴግ ለዚህ ብቃት አላገኘም።

የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ባለቤቶችን ነን ለሚሉት ኢህአዴጋዊያን አብዮታዊያን አይደሉም የምንልበት ምክንያትም ከበቂ በላይ ሊባል በሚችል አኳኋን ሥርዓቱን መለወጥ ቀርቶ ራሳቸዉን ያልለወጡ ሰዎች ስለአብዮታዊነት ቢያወሩ የሚደነቅ ሰዉ አይኖርም። የቀድሞ አሮጌ ሥርአትን የለወጠው አዲስ ሥርአት ያ አሮጌ ሥርዐት ሲያደርገዉ የነበረዉን፤ ለምሳሌ ምርጫ ከደርጅታዊ አሰራር እንዳይወጣ ማድረግ የመሳሰሉትን የሚያደርግ ከሆነ፤ በሆነ ሁኔታ መለወጡ ብቻ ሳይሆን በተለወጠዉ ቦታ የተተካዉን ጭምር መመዘን ያስፈልጋል። ለውጥን አብዮታዊ ሊያሰኘዉ የሚችለዉ አሮጌዉን የፀረ ዴሞክራሲ ሥርአት ማፍረሱ ብቻ ሳይሆን በቦታዉም ተራማጅ በሆነና የሰዉን ልጅ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት የሚያስከብር ሥርአት በቦታዉ መገንባት የሚችል፣ ሕብረተሰባችንን ራሱን በዕዉቀትና በቴክኖሎጂ አበልጽጎ ካለበት ኋላቀርነት የሚያላቅቅ ከሆነ ብቻ ነዉ። ይህ በሌለበት ቦታ ደግሞ ሕወሓት/ኢህአዴግን አብዮታዊ የሚያሰኝ ባህርይ የለም። ኢህአዴግ ዲሞክራሲያዊ አለመሆኑን በምሳሌ ማስረዳት የበለጠ ተመራጭ ሆኖ አግኝቻለሁ። ደርግ ኢህዲሪን ሲያቋቁም በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ባለዉ ቅጥፈት የወትድርናዉን ኮፊያ ወደ ካምፕ ሲመልስ እራሱ በሕወሓት ተጠርጎ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ እዚያዉ አራት ኪሎ ቤተመንግስት ቆይቶ ነበር። አሁንም ሕወሓት ያንኑ የደርግ ድራማ እየደገመ ያለ ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ ዓይናችንን አስጨፍኖ እያሞኘን

ነዉ። ዊኪፔዲያ የተባለዉ ሴለክሽን በሕወሓት የሚመራዉን የኢትዮጵያን መንግስት ባሕርይ በአጭር አረፍተ ነገር ሲገልጽ *“Ethiopia is a hybrid of regime situated between a flawed democracy and authoritarian regime.”* ብሎታል። ስለሆነም የዲሞክራሲ ዋና መገለጫ የሆነዉ ነፃ ምርጫ ሳይኖር ኢህአዴግ ዲሞክራሲያዊ ነዉ የሚያሰኘዉ ባህርይ እንደሌለዉ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል። ከተለያዩ ንባቦች ለመረዳት እንደቻልኩት ደግሞ (ሕወሓት/ኢህአዴግ ሊኖረው የማይችል) ዴሞክራሲያዊ ሥርአት የሚከተሉትን መገለጫዎች ወይም ገጽታዎች አካትቶ የያዘ ነው።

- ሕግ አውጪ አካል በየጊዜው በሕዝብ የሚመረጥበት ሥርአት፣
- የንግግር፣ የመደራጀትና የሃይማኖት ነፃነቶች በሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሚያገለግሉበት፣
- ሁሉም ዜጎች የመንግስትና የመስተዳድር አካላት በየጊዜው በሕዝብ የሚመረጡበት፣
- ዘር፣ ፆታ፣ መደብና ሃይማኖት ሳይለይ ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው የተረጋገጠበት ማህበራዊ ሥርአት፣
- ማንኛውም ዜጋ በእኩልነት መምረጥና መመረጥ የሚችልበት ሥርአት፣
- እያንዳንዱ ዜጋ ያለምንም ተፅዕኖ ሰላማዊ ስብሰባ፣ ሰላማዊ ሰልፍና አቤቱታ የማቅረብ መብት የተጠበቀበት፣
- ከተፅዕኖ ነፃ የሆነና በሕግ ብቻ የሚመራ ፍርድ ቤት መኖር፣ እና የነፃ ፕሬስ መኖር ናቸው።

የእነዚህ መገለጫዎች ወይም ገጽታዎች መኖር ደግሞ የተለያዩ ሐሳቦችን ማስተናገድ፣ መቻቻልን መፍጠር እና ልዩነቶችን በሰላማዊ ውይይት መፍታትን እንደሚያጎናጽፍ በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች ያስረግጣሉ።

የሕወሓት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከተግባር የበለጠ የሥነ ልቡና ማስፈራራት አካሄዶ የመግዛት ዕድሜውን ሊያራዝም እንደሚፈልግ ኤርሚያስ ለገሰ <u>የመለስ ሊቃቂት</u> በተባለ መጽሐፉ የአቶ መለስን አባባል

በመጥቀስ እንደፃፈው "በኢትዮጵያ ምድር የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር መከተል የሕልውና ጥያቄ እንደሆነ፤ ኢትዮጵያ ይህንን መስመር ካልተከተለች የመበታተንና እና የእርስ በርስ እልቂት እንደሚያጋጥማት-የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ማህበራት፣ አብዮታዊ ድርጅቶችና ግለሰቦች) ልዩና መተኪያ የሌለው ሚና ሊጫወቱ ይገባል" ሲል ተናግሮ እንደነበር አስቀምጧል። የአባቱ ኢህአዴግ ልጅ የሆነዉ የብልፅግና ፓርቲም ሀገራዊ የለዉጥ እርምጃዎች (ገፅ56) ብሎ የካቲት 2012 ዓም የቀደምቱን ፈለግ በመከተል የሥነ ልቦና ቅስቀሳ በሚመስል መልኩ ሲያስፈራራ የሚከተለዉን ጽፎ እናገኛለን። "በሀገራችን የፖለቲካ ሪፎርም ለማምጣት ሲታሰብ በቀደምትነት ገዥዉ ፓርቲ ያለዉ ታሪካዊ፣ ወቅታዊና ሀገራዊ ሚና የሪፎርሙን ይዘትና አቅጣጫ በዋነኛነት ይወስናል። በዚህ ምክንያት ነዉ አሁን ባለዉ ነባራዊ ሁኔታ የድርጅታችን ዉድቀት የሀገር ዉድቀትን፤ የድርጀታችን መፈረካከስ የሀገር መፈረካከስን ይወልዳልየሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰዉ። ኢትዮጵያ አሁን ባላት የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ ገዥዉ ፓርቲን ያህል የፖለቲካ ድርጅት በኪሳራ ለማጣት የምትችልበት ትከሻ የላትም።" በማለት የገዥዉ ፓርቲ ሕልዉና ካከተመ የሀገርም ሆነ የሕዝብ ሕልዉና እንደሚያከትም በቀጥታ ነግረዉናል። ግን ግን በ1948 ዓም በተሻሻለዉ ሕገ መንግስታቸዉ አንቀፅ 4 ላይ የንጉሴ ነገስቱን የነጋሲ ዘር ክብር በድፍረት ለመንካት ደፍሮ የሚነሳ ማንም ሰዉ በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል ያሉት ተሽንቀጥሮ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ ምድር እና ሰማይ አለመገላባበጣቸዉን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ።

ሌላዉ ልማታዊ የሚባለዉ ፅንሰ ሐሳብ የኢህአዴግ ሌላዉ አስቸጋሪ ጎን ነዉ። ኢህአዴግ ልማታዊ ቢሆን ልማትን የሚጠላ አይኖርም። ነገር ግን ልማታዊነቱ ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግ አይደለም። ከደርግ መውደቅ ወዲህ መንገዶችና ፎቆች ተሰርተዋል፣ አዳዲስ መኪናዎች ወደ አገር ዉስጥ ገብተዋል። ሆዳቸዉ ወደፊት የተወጠረ ጥቂት የማይባል

ሰዎች ተፈጥረዋል፤ ነገር ግን ከሀብታሞች ገበታ የወዳደቁ ፍሪፋሪ ፊለጋ ቆሻሻ ገንዳ ላይ የሚራኮቱ ዜጎች የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲና በተባለች አዲስ አበባ ዉስጥ እያየን የኢህአዴግን መንግስት ልማታዊ መንግስትነትን መቀበሉ ይከብዳል።

ኢህአዴግ የሚመራዉ መንግስት ልማታዊ አለመሆኑን አንዳንድ መሠረታዊ ናቸዉ የሚባሉትን ነጥቦች ማንሳት ይቻላል። ከነዚህም አንደኛ ከፖሊሲ ቀረፃ እስከ ትግበራ ድረስ የሕዝብና የመንግስት ፍላጎት አለጣጣም ነዉ። ለምሳሌ በጂማና ኢሉ አባቦራ ዞኖች የሚገኘዉን የድንጋይ ከሰልና ዳላቲ ምዕራብ ወለጋ ዉስጥ የሚወጣዉ ዕብነ በረድ ጥሬ ዕቃ ከማጓጓዝ እዚያዉ ማቀናባበሪያ ፋብሪካ ተቋቁሞለት የአከባቢዉ ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነበረበት። ሁለተኛ ልማታዊ መንግስት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ መንግስት ሲሆን ሕዝብ ያልመረጠዉን መንግስት መቀበል አይገደድም። ሦስተኛ የልማታዊ መንግስት ልሂቃን አገራዊ ራዕይ የሚኖራቸዉ ናቸዉ። አገራዊ ራዕይ በምንልበት ጊዜ እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ ነጭና ጥቁር ተብሎ በቀለም ላይ የተመሠረተ ሕይወት ሳይሆን ሁሉም ባለቀለም አሜሪካዊያን በእኩልነት የሚኖሩባት አሜሪካን መፍጠር ሲሆን እነ ማንዴላ የዘር መድልዎ የሌለባት ደቡብ አፍሪካን ለመፍጠር ያደረጉት ዓይነት ትግል ነዉ። አራተኛዉ የልማታዊ መንግስት ባህርይ ቢሮክራሲዉ ከፖለቲካ ጫና ነፃ መሆን ነዉ። ከምልመላ እስከ ምደባና ደረጃ ዕድገት ድረስ የፓርቲ አባላት የታጨቁበት የመንግስት ቢሮክራሲ እንዴት አድርጎ ከገዥው ፓርቲ ተፅዕኖ ተላቅቆ ገለልተኛ አገልግሎት እንደሚሰጥና ልማታዊ መንግስት እንደሚያስብል ማሰቡ ራሱ ይከብዳል። አምስተኛዉ የልማታዊ መንግስት ባህርይ የፖለቲካ ሹመት በታ ብቃት ባላቸዉ ዜጎች መሞላት ሲኖርበት፤ የኢህአዴግን ዓላማ የተቀበለ ዘበኛም ቢሆን የሚኒስትርነትን በታ መያዝ ይችላል ማለት በግብር ከፋይ ሕዝብ ላይ የመቀለድ ያክል ነዉ። ምክንያቱም፤ ከዘበኛነት ሚኒስትር ለሆነዉ ሰዉ ደመወዝና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች የሚደረጉት በመጀመሪያ ከሕዝብ ከተሰበሰበ ግብር፣ በተጨማሪም በሕዝብ ስም ከሚወሰደዉ

ብድርና በዚሁ ሕዝብ ስም ከሚገኘዉ ዕርዳታ ነዉ። ስድስተኛዉ የልማታዊ መንግስት ባህርይ አመቺ የሆነ ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ግንኙነት መፍጠር ነዉ። ኢህአዴግ አለም አቀፍ ፀረ-አሸባሪነት ዘመቻ ዉስጥ የተሳተፈ ስለሆነ በዚህ መስክ የተሳካለት ይመስላል። ነገር ግን አይደለም። ምክንያቱም፤ ኃያላን መንግስታት የኢህአዴግን ደካማ ጎን በመረዳት ሊጠቀሙበት ስለአንቆለጳጴሱት ነዉ እንጂ ውሎ ሲያድር የቀደምት አምባገነኖች ዕጣ ፈንታ ሳይገጥመዉ አይቀርም። በጥልቀት ከተመለከቱት ደግሞ ዜጎች መብታቸው እየተረገጠ እንዲኖሩ የሚገደዱ ከሆነ ትንሽም ሆነ ትልቅ የሚባል የልማት ሥራ ተብሎ አያስፈልጋቸውም። ሕወሓት/ኢህአዴግ የሰውን ነፃነት የሚገድብ ድርጅት ስለሆነ ሰብአዊ ባለመሆኑ ልማታዊም ሊሆን አይችልም። ልማታዊ ነኝ ቢል እንኳን የሕወሓት/ኢህአዴግ ልማታዊ መንግስትነት ጣሪያውና ግድግዳው የውጪ ዕርዳታ ለማግኘት ወይም ለመውሰድ ነው።

አንዱ የሕወሓት/ኢህአዴግ ችግር ሙስና ነዉ። ሙስና የአገር ሀብትን ብቻ ሳይሆን የሰዉን አእምሮ ጭምር የሚሰልብ ስለሆነ በዕዉነት ሕወሓት/ኢህአዴግን የሚያስጨንቀዉ ከሆነ ያሳዝናል። ስለተጨነቁበትም መሰለኝ የኢህአዴግና የግንባሩ አባላት ጉባኤም ሆነ ስብሰባ በተካሄደ ቁጥር ሙስና እየተወገዘ፤ ይህ ወንጀል አስከፊና የግንባሩ ችግር መሆኑን ይገልፃሉ። ሙስና በነገሰበት አገር ዉስጥ ዲሞክራሲያዊ የፓርቲ ፖለቲካ በሁለት እግሩ ይቆማል ብሎ ማሰብ ከማስቸገሩም በላይ፤ ፀረ ሙስና የተባለ መንግስታዊ አካል ተቋቁሞለትም የፀረ ሙስና ትግሉ የሚያነጣጥርባቸዉ ቱባ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት የማይገፉት ተራራ እየሆኑ፤ ፀረ ሙስና የተባለዉ መንግስታዊ ድርጅት ብዙዉን ጊዜ አንገቱ ተይዞ ሳይንቀሳቀስ ውሎ እንደሚያድር ዉስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። የታደለው የኢትዮጵያ መንግስት ሙስና የተቋቋመለት አንድ መንግስታዊ ድርጅት ሳይበቃው ቀርቶ ከፍተኛ የብልፅግና ፓርቲ መንግስት አባላት ያሉበት ተደራቢ ብሔራዊና ክልላዊ ኮሚቴዎች ተቋቁሞለታል።

ሦስተኛ እትም ካምብሪጅ አድቫነሲድ ድክሽነሪ፤ ሙስናን ሕገ ወጥ፣

መጥፎ እና ታማኝነት የሌለው ባህርይ በተለይ በሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች የሚፈጸም ነው ይላል፡፡ ከመዝገበ ቃሉ አገላለፅ የምንረዳዉ ነገር ቢኖር ሙስና የሚከናወነዉ ታማኝነት በጎደላቸዉና የመንግስት ሥልጣን ላይ በተቀመጡ ብልሹ ባህርይ ባላቸው ሰዎች ነዉ፡፡ ሦስቱም የሙስና ወንጀሎች የንብረትም ሆነ የገንዘብ (የኤኮኖሚ)፣ የሥልጣን (የፖለቲካ) ሙስና እንዲሁም የቢሪክራሲ ሙስና የሚፈፀመሙት በተራ ሰዎች ሳይሆን ሥልጣን ባላቸዉ ሰዎች ነዉ፡፡ የባህርይ አለመታመን (dishonest behavior) ምንጩ በፖለቲካ አለመታመን ነዉ፡፡ የማይታመን ፖለቲካና ባህርይን ይዞ በሕዝብ አመራር ላይ tቀምጦ እንዴት ተደርጎ እንደሚቻል ሲታሰብ፤ በደህንነት፣ ፖሊስ፣ ጦር፣ ፍርድ ቤት፣ ምርጫ ቦርድ፣ ወዘተ ኃይሎች ካልታገዘ በስተቀር የማይሞከር ነዉ፡፡ አለመታመን የሚፈጠረዉ ሥነ ምግባር በጎደለዉ አካሄድ የህግ ምክር በሚሰጡ ባለሙያዎች፣ ሞራላቸዉ የላሸቀ ግልሰቦች ሥልጣን ላይ ሲወጡ፣ ብልሹ ምሁራን በሚያመነጩት አሳሳች የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ እንዲሁም ስለወደፊቱ ትውልድ ደንታ በሌላቸዉ የፖለቲካ መሪዎች የሚፈፀም ወንጀል ነዉ፡፡ ሙሰኛ ባለሥልጣናት በቢሮክራሲው ውስጥ ያላቸውን ጫና በመጠቀም የኤኮኖሚ ሙሰኞችን የሥራ ቦታ በመቀያየር ውስጣቸው ያደፈ ሰዎችን ነጭ ሸሚዝና ክራባት ያለብሳሉ፡፡ ዶክተር ፋሲል ናሆም እና ዛሬም የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ የተቀመጡና ተማሩ የሚባሉ ሰዎች ከኃይሌ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሕወሓት/ኢህአዴግ ድረስ ፀረ ዲሞክራሲ አቋምን ከሚያራምዱ ገዥዎች ጋር የሚሰለፉ የመኖራቸዉ ብቻ ሳይሆን በኃይሌ ሥላሴ ጊዜ የዩኒቬርስቲ ቻንሲለር፣ ፀረ ሕዝብ የደርግ ሕገ መንግስት አርቃቂና የሕወሓት ቁንጮ አመራር፣ አማካሪ፣ አምባሳደር ሆነዉ የዘለቁ ግለሰቦችና እንዲሁም እምነት የማይጣልባቸው እንደ የሙቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርግስ እና ሌሎችም ሰዎች የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር እስከመሆን የደረሱ ግለሰቦች ስለመኖራቸዉ መግለፅ እንደ አዲስ ነገር ታይቶ ባስያስገርምም፤ አጨበርባሪ ሰዎች ከሕዝብ ጫንቃ ላይ ሳይወርዱ የመኖራቸዉ ጥበብ (art of life) በጎ ቢሆን ኖሮ ስንቱ ሰዉ በተማረበት ያሰኛል፡፡

ሙሰኝነት የሕግ የበላይነት ስለመጣሱ አንድ ዓይነት መገለጫ ነዉ። ይህም የሚከሰተዉ በማጭበርበር፣ በጉቦና አድሎአዊነትን በመፈጸም ነዉ። በአድሎአዊነት (nepotism) ሥልጣንን የተቆናጠጡ ግለሰቦች ዘመዶቻቸዉን በሕግ ከሚገባቸዉ ዉጪ በሥራ ቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በገንዘብ ብድር፣ በጨረታ ሂደት፣ በግብር አሰባሰብ ወቅት፣ የላኪና አስመጪ ፈቃድ አሰጣጥ ወቅት፣ ወዘተ የሚጠቃቀሙበት ሲሆን፤ እነዚህ ሕገ ወጥ ድርጊቶች የሚሰሩ ዜጎችን ከሥራ ያገልላል ወይም የሚሰሩ ሰዎችን ሞራል የሚጎዳ ነዉ። ዜጎች በሙያቸዉ፣ በችሎታቸዉና በዜግነታቸዉ ጭምር እንዳይኮሩ ያደርጋቸዋል። ኢ-ፍትሐዊነት ነግሶ ዜጎች የሚገባቸዉን እንዳያገኙና አንገታቸዉን እየደፉ እንዲኖሩ ያስገድዳቸዋል። ሙስና በግዥና ጨረታ ወቅት በሚፈጸም ማጨበርበር ጥቂት ግለሰቦች ኪሳቸዉ ዉስጥ መግባት የማይችለዉን ወይም መግባት የሌለበት የሕዝብ ገንዘብ ወይም በመንግስት ካዝና ዉስጥ መግባት ወይም መቅረት ያለበት የሕዝብ አንጡራ ሀብት ወይም ዜጎች ኪስ ዉስጥ መቅረት ያለበት ገንዘብ ወደ ሙሰኞች ኪስ መክተት ነዉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ጉቦና ምልጃም ፍትህንና መልካም አስተዳደርን በማዳደል ቀላል የማይባል አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ። ሙስና የዕድገት ፀር መሆኑ አንድና ሁለት የሌለዉ ቢሆንም ታማኝነት ደግሞ ውድ ስለሆነ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊ ከሆኑ ርካሽ ሰዎች ይገኛል ተብሎም አይጠበቅም። ኢትዮጵያ ውስጥ ሙሰኝነት ለምንና እንዴት እንደተንሰራፋ <u>የተጠለፈው ትግል</u> (2011፡ 68) መጽሐፍ ደራሲ መድህን ስራጅ እንደገለፀው/እንደገለፀችው ከሆነ "ተጠያቅነትና ግልፅነት ማጣት፣ አነስተኛ የሆነ የዴሞክራሲ ባህል፣ የዜጎች ቀጥተኛ ተሳታፊ አለመሆን፣ ግልፅ የሆነ ህግጋትና ስልጣን አለመኖር፣ በዝቅተኛ ደረጃ ተቋማትን መቆጣጠር፣ ወንጀለኞች ላይ ቅጣት አለመጣል፣ ስልጣንና ሀብትን ጠቅልሎ መያዝ፣ ለአገራችን ከፍተኛ የሆነ ሙስና ካበረከቱት ውስጥ ከፍተኛ መሆናቸውን" አሳይቷል/ታለች። ወደ ኢህአዴግ "ፖለቲካ የሚመጡ ሰዎች በአቋራጭ ለመክበር የቆረጡ፣ ለራሳቸውም [ሆነ] ለሌሎችም ክብር የሌላቸው፣ ለመዋሸት፣ ለማታለል፣ ለመሸፈጥ፣ ለመወንጀል፣ ለመፍለጥ፣ ለመቁረጥ፣ ያሰቡ" ናቸው ይላል ሰለሞን ስዩም

በየኢህአዴግ ፍፃሜ መጽሐፉ ውስጥ። ሪክ ስታፕንሀርስት የተባለ አዘጋጅ Curbing Corruption ብሎ በአዘጋጀው የመግቢያ ጽሑፍ ውስጥ Corruption is the abuse of power, most often for personal gain or for the benefit of a group to which one owes allegiance. ብሏል።

በኢትዮጵያ ደረጃ ሙስና ሲጠራ ሕወሓት/ኢህአዴግ የመጀመሪያም የመጨረሻም ላይሆን ይችላል። ሙስና ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ሲሆን ዕድሜዉም የሕዝብን ተጠቃሚነት ከጫማቸዉ በታች አድርገዉ ከሚያስቡ ፖለቲከኞች ጋር የሚያያዝ እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን የባሰበት ጊዜ ቢኖር በዚህ በሕወሓት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን ዉስጥ ነዉ ቢባል አልተሳሳተም። አፍቃሬ ኢህአዴግ የሆነው ሪፖርተር የተባለ የግል ጋዜጣ በቅፅ 21 ቁጥር 1615 ዕትሙ ላይ የአገራችን የሙስና ችግር የደረሰበትን አስከፊ ደረጃ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዓሊ ሱሌማንን በመጥቀስ እንዳሰፈረው፤ “ፍትህን በገንዘብ የሚችበችቡ፣ የተሰጣቸዉን የሙያ ሥነ ምግባር ዘንግተዉ ዳኝነትና ፍትህን በአገር ልጅነት ወይም በብሔር ግንኙነት የሚሸጡና ለወሲብ ድርድር የሚያቀርቡ እንዳሉ ተነገረ።” በማለት ገዥዉ ፓርቲ በሙስና የተነሳ ያለበትን የውድቀት ደረጃ ፍንትዉ አድርጎ ገልጾታል። ለንፅፅር እንዲያመች ያህል ዛሬ ጥቂት የሕወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካ፣ የፖሊስ፣ የደህንነት፣ የመከላከያ፣ ሲቪል ባለሥልጣናትና ተጠቃሚዎቻቸዉ አፍርተዋል የሚባለዉን የዘረፋ ሀብት የደርግ ባለሥልጣናት የነበሩ ሁሉ በ17 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በድምር እንዳላፈሩ ዋቢ በማጣቃስ የሚናገሩ ሰዎች አሉ። የባለሥልጣናት ሀብት ምዝገባ በሚባለው የሸንገላ ሥራ ሂደት ውስጥ አንድ መሀከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ ባለሥልጣን “እስከ ሃምሳ ሚሊዮን የሚገመት ሀብት አለኝ” ብሎ ሲያስመዘግብ፤ እሱም ሆነ ቤተሰቡ አንድም ቀን ሳይመገቡ ሀብት ሲያጠራቅሙ የኖሩ ይመስላል። ምክንያቱም፤ ዓይነ ግቡ ቤት ገንብተውና ባልና ሚስቱ ለየብቻቸው ወደየሥራዎቻቸው የሚመላለሱበት መኪና ገዝተው ሙስና ከሌለበት በምንም ዓይነት ሁኔታ በአንድ የመንግስት መሀከለኛ የመንግስት ባለሥልጣን እጅ ሃምሳ ሚሊዮን ብር በጥቂት ጊዜ ዉስጥ ሊጠራቀም አይችልም።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ከሁለት አቅጣጫ ሀብት አለዉ፡፡ እንደ ገዥ ፓርቲ መዋቅራዊ ሰንሰለታቸው ከመንግስት መዋቅር ጋር የተጣመረ የፖለቲካ ድርጅት ስለሆነ በኢትዮጵያ መንግስት ካዝና ያዝበታል፡፡ በየእርከኑ የሚገኙ የመንግስትና የፓርቲዉ መሪዎች ድርብ ሚና (የመንግስትም የፓርቲም) መዘውር የያዙ ናቸዉ፡፡ ሌላዉ ከዚህ በመለስ ነዉ የማይባል በእንዳዉሜንት ስም ፓርቲዉ የሚያንቀሳቅሰዉ የኢንዳውሜንት ሀብት አለዉ፡፡ ሲፈልግ ደግሞ በስንት መከራ ከሚጠራቀመው የባንክ ተቀማጭ ብድር ይወስዳል፡፡ ውስጥ አዋቂው ኤርሚያስ ለገሰ በመጽሐፉ እንደገለጸው "አልመዳ ጨርቃጨርቅ የተመሰረተው በ470 ሚሊዮን ብር ሲሆን፤ ከዚህ ካፒታል ውስጥ 64 በመቶ ወይም 300 ሚሊዮን ብር የተገኘው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለ መያዣ በተሰጠው ብድር ነው፡፡" ይላል፡፡ ከንግድ ድርጅቶቹ በተገኘ ስፍር ቁጥር በሌለው ትርፍም የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴም ሆነ ዘላቂ የዴሞክራሲ ግንባታውን ዕድገት ያፍናል፡፡ ስለሆነም የአምባገነኖች ፖሊሲ አውጪዎችም ሆኑ አስፈፃሚዎች ሁሉም ነገር በእግራቸዉ ሥር እስከሆነ ድረስ በመንግስትና በሕዝብ ንብረት ላይ ሙስና ቢፈፅሙ ሃይ የሚላቸዉ ከየትም መምጣት አይችልም፡፡ ከ2010ሩ ሕዝባዊ ንቅናቄ ወዲህ ደግሞ የሕወሓት/ኢህአዴግ ሙሰኝነት በግልፅ ስለወጣና በሕግ ተጠያቂነት እየጎላ ሲመጣ አዲስ አበባ ላይ የቀረው የኢህአዴግ ክንፍ ከሕወሓት ጋር ሊጠየቁ የሚገባቸውን ሰዎች ለማትረፍ ሲል በብርሃን ፍጥነት ስሙን ከአህአዴግ ወደ ብልፅግና ፓርቲ ቀየረ፡፡ ያለምንም ማጋነን ከ1983 ወዲህ የሕዝብ ሀብት ከፓርቲ ሀብት ጋር ተቀላቅሏል፡፡ ሙሰኞች "የተገፋ ሕዝብ ሀብት ዘርፈዉ እራሳቸዉን እንደ ባለመብት ይቆጥራሉ" ይላል ዶክተር ጌታቸዉ ጅጊ ከላይ በተጠቀሰ መጽሐፉ ገጽ 93 ላይ፡፡ የሕወሓት/ኢህአዴግ የሀብት ምንጭ ብዙ ሊባሉ የሚችሉ ክስተቶችም ይኖራሉ፡፡ የመላዉ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማህበር/መኢገማ፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማህበር/አኢወማ፣ የአብየታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር/አኢሴማ ገንዘብና ንብረት ለመንግስት ወይም ለፓርቲ ይግባ ወይም የት እንደደረሰ ለሕዝቦች የተሰጠ ሪፖርት የለም፡፡ እዚህ ላይ የማንዘነጋዉ ነገር ቢኖር ፓርቲ ሀብት ሊኖረዉ ይችላል፡፡ ነገር ግን የተገኘዉ ሀብት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት የሚረግጥና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ፖለቲኮ ማህበራዊ ግንኙነት እስከ ማኮላሸት የሚያደርስ ሊሆን አይገባም። ሪክ ስታፔንሀርስት ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ (1999፡ 19) አለን ዶይንግን ዋቢ በማድረግ corrupt activities of public officials can destroy the potential effectiveness of all types of governmental programs, hinder development, and victimize individuals and groups. በማለት የሙስናን አስከፊ ገጽታ ጽፏል። ይህ አስከፊ ገጽታ ጥፋቱ በራሱ ሥርአት ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ለሚቀጥሉት ረጅም ዓመታት ውስጥ ከቀጣይ ትውልድ ኢትዮጵየዊያን ጫንቃ ላይ እንዲህ በቀላሉ የሚወርድ አይመስልም። ሕወሓት/ኢህአዴጎች የመቶ ዓመታት ጦርነትን ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥለን እንሄዳለን ብለው የዛቱትም በትክክል ልናይ የምንችለው ማባራ በሌለዉ በሙስና ድርጊታቸው ይመስላል።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ችግሬ ነዉ ብሎ የሚደሰኮረዉ፤ ነገር ግን በእርግጠኛነት የሱ ሳይሆን የሕዝብ ችግር ሆኖ እየዘለቀ ያለዉ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። ኪራይ ሰብሳቢነት በአብዛኛዉ ለማለት ይቻላል ሕግና ሕጋዊነትን ተገን በማድረግ የመንግስትን ወይም የሕዝብን ሀብት መቀራመት ነዉ። “ኪራይ ሰብሳቢነት … የገበያ መርህ ከሚያመቻቸው ሁኔታ ውጭ ያለአግባብ የፖለቲካ ድጋፎችን በመጠቀም ከገበያ ዋጋ ያልተገባ ትርፍ ወይም አብላጫ ጥቅም ማግኘት ማለት ነው።” ይላል ሰለሞን ስዩም በኢህአዴግ ፍፃሜ መጽሐፉ ገፅ 143 ላይ። ለምሳሌ የአክሲዮን ባለድርሻዎች ይወስኑ አይወስኑ አይታወቅም፤ የብልፅግና ፓርቲ በ2011/12 ከአዋሽ ባንክ ብቻ ሃያ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ተቀብሏል። ጠቅለል ባለ አገላለፅ ኪራይ ሰብሳቢነት ማለት ሰዎች (የተፈጥሮና ሕጋዊ ሰዎች ማለት ነዉ) የማይገባቸዉን ጥቅም ማግኘትና የተገኘዉም ሀብትም ለሕብረተሰቡ ምንም እሴት በማይጨምር ነገር ላይ ማዋል ማለት ነዉ። ኪራይ ሰብሳቢነት በስፋት ተንሰራፍቶ የሚገኘዉ በመንግስት መሥሪያ ቤት ዉስጥ ነዉ ቢባልም በሲቪክ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ድርጅቶች፣ በሠራተኛና ሙያ

ማህበራት፣ በዕድሮችና በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዉስጥ ሳይቀር ተንሰራፍቶ የሚገኝ ነዉ። ዜጎች አባል ላልሆኑበት ፓርቲ ወይም ድርጅት በተለይም ለገዥዉ ፓርቲ ዓመታዊ ክብረ በዓል፣ እንዳዉሜንት፣ ፋዉንዴሽን፣ የሙት መንፈስ መታሰቢያ ቀን፣ ወዘተ እየተባሉ የውዴታ ግዴታ በማለት የሚያዋጡት መዋጮ፤ በተለይም የግል ነን የሚሉት ባንኮች የብሔራዊ ባንክንም ሆነ የራሳቸዉ የዉስጥ መመሪያን ተገን በማድረግ የተለያዩ ሐሳብና አመለካከት ካላቸዉ ባለአክስዮኖች ፈቃድና ፍላጎት ውጭ አንስተው የሚሰጡት ችሮታ ምንም በሉት ምንም ወደ ኪራይ ሰብሳቢዎች ኪስ የገባ ነው። ሲከተልም፤ ለአገራችን ዴሞክራሲ መቀጨጭ አሉታዊ አስተዋጽኦ አድረገዋል። ይህ ብቻም አይደለም ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከት፣ እና ከሌሎችም ጉዳዮች በገለልተኛነት ተደራጅቶ ለሕጋዊ ተገልጋዮች ሁሉ ከወገንተኝነት በፀዳ ሁኔታ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ የተደራጀዉ የሲቪል አገልግሎት መስሪያ ቤትና ሠራተኛዉ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ የገዥዉ ፓርቲ አባል እንዲሆንና በአባልነቱም የሚጫንበትን ክፍያ እንዲፈፅም የሚገደድ ከሆነ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ።

ሙሰኝነትና ኪራይ ሰብሳቢነት አንድ ዓይነት አለመሆናቸዉ የታወቀ ቢሆንም የመመሳሰል ባህርይ አለባቸዉ። ኪራይ ሰብሳቢነት የመንግስትና የፓርቲ ፖሊሲን ተገን አድርጎ የሚከሰት ነው። በምሳሌ ለማስረዳትም ገንዘብ ከላይ ወደታች ወይም በተቃራኒዉ እንዲዘዋወር ለማስቻል መንግስት ሕግ የመደንገግና ፖሊሲ የማዉጣት ሥልጣን አለዉ። ወይም በቂ ምክንያት አለዉ/የለዉም የሚባለዉ እንዳለ ሆኖ፤ መንግስት ብድር የመስጠትና ዕዳ የመሰረዝ ሥልጣን አለዉ። ብዙዉን ጊዜ የዜጎች ኑሮ አለመመጣጠን የሚከሰተዉ መንግስት በተለያዩ ነገሮች በተለይም የኤኮኖሚ አስተዳደሩን አስመልክቶ ፖሊሲና ሕግ በሚያወጣበት ሂደት ዉስጥ ጀምሮ ነዉ። እሱም በተዛባ የመንግስት ፖሊሲ ምክንያት ሥልጣን ላይ ካለዉ ፓርቲ ጋር ውገና ያላቸዉ ወገኖች ጠንካራ ሆነዉ ሲወጡ በተቃራኒዉ ያሉት ደግሞ ደካማና ተጎጂ ሆነዉ ይቀራሉ። ጠንካሮቹ የፈለጉትን የመንግስት ፖሊሲ ሳይቀር ሲጠመዝዙና ሲለወጡ

ደካሞች ደግሞ የፖሊሲዉ ሰለባ ይሆናሉ።

አንድ አገር ኃላፊነት የሚሰማዉ መንግስት እስከሌለዉ ድረስ የላይኞቹ አስፈፃሚዎችና ወገኖቻቸዉ ሙሉ ክፍያ ወይም የተትረፈረፈ ክፍያ ያገኛሉ። በሌላም በኩል ለባለሥልጣኖቹ ገደብ የለሽ ሥልጣን የሚሰጥ መንግስት እስካለ ድረስ እነሱ በሙስናም ሆነ በኪራይ ሰብሳቢነት የሚቀበሉትን የሀብት መጠን የሚገባቸዉን ስጦታ እንዲወሰዱ ይቆጥራሉ እንጂ ሕዝብን አገለገሉ አላገለገሉ ማን ምን አደረገ የሚል ጠያቂ አይኖርባቸዉም። ባለሥልጣኖቹም እየቆዩ ሲሄዱ ዘረፋ እንኳን ቢፈጽሙ የዘረፉ ሳይሆን በተቀመጠላቸዉ 'ሕግ' መሠረት የሚገባቸዉን እንደወሰዱ ይቆጥራሉ እንጂ ጥፋት የፈጸሙም አይመስላቸዉም። በአቋራጭ የከበሩም ሆነ ሊከብሩ ያሰቡት ከራሳቸው ውጭ ለሌሎች ክብር የሌላቸውና ማንንም በፈለጉበት ቦታና ጊዜ ለመቁረጥም ለመፍለጥ ሃይ የሚላቸው የለም። ጆሴፍ ስትግሊዝ የተባለ የኤኮኖሚ ባለሙያና በቢል ክሊንተን አስተዳደር ጊዜ የሁዋይት ሀዉስ የኤኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረዉ (xvi) The Price of Inequality በሚለዉ መጽሐፉ ችግሩ ከፖሊሲ መሆኑን ሲያሰምርበት *"If no one is accountable, if no individual can be blamed for what has happened, it means that the problem lies in the economic and political system."* ብሎታል። ከዚህ ጋር የፖለቲካ ሥርአቱ ከመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት አማካይነት የሚሰጠው የድጋፍ ገንዘብ እንዴት እንደሚከፋፈልና ገንዘቡ በኪራይ ሰብሳቢነት ስልት ወደ ገዥው ፓርቲ ተመልሶ የፓርቲ ፖለቲካን እንደሚያቀጭጭ በዝርዝር ስለሚያስረዳ ቦርዱ ለ2014 ዓም ያስተላለፈውን መመሪያ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

1. በምርጫ ለሚሳተፉ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት 25 በመቶ፤ በዚህ ስሌት መሠረት ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ እኩል ያገኛሉ።
2. በምርጫ የሚሳተፉ ፓርቲዎች በሚያቀርቧቸው ዕጩዎች ላይ ተመስርተው 25 በመቶ ያገኛሉ። ገዥው ፓርቲ ብዙ ዕጩዎችን

ያቀረበ ስለሆነ ብዙ መቶኛ እንደሚያገኝ ሳይታለም የተፈታ ነው።

3. በምርጫ የሚሳተፉ ፓርቲዎች ለውድድር በሚያቀርቧቸው የሴት ዕጩዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ 25 በመቶ ያገኛሉ። ለገዥው ፓርቲ ያልወገኑ ፓርቲዎች ሴት አባላት በገዥ ፓርቲ ካድሬዎች ከአሁን አሁን ጥቃት ይደርስብናል ብለው በሚሰጉበት ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ድፍረት ቀርቶ ማንም ቀና ብሎ ሊያያቸው የማይደፍር የገዥው ፓርቲ ሴት ዕጩዎች ያለአንዳች ስጋት ስለሚሳተፉ የገንዝቡ ድልድልም ያንኑ ያህል ከፍተኛ ነው።
4. በፓርቲ የሴት አመራር አባላት ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል 15 በመቶ፤ የፖለቲካ ምህዳር በጠበበበትና ወንዶች እንኳን ብዛት ያላቸው አደጋዎችን በሚያንቀሳቅሱበት አገር ውስጥ ሴት አመራር አባላት ማግኘት ምን ያህል እንደሚያስቸግር የደረሰባቸው ስለሚያውቁ የሚከፋፈለውን ገንዘብ ከማግኘት በላይ የሴቶቻችን በሰላም ወጥተው በሰላም ወደ ቤት መመለስ ያስደስታል።
5. ፓርቲዎች ለምርጫ ውድድር በሚያቀርቧቸው አካል ጉዳተኛ ዕጩዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፋፈል 10 በመቶ ያገኛሉ። የመከራ ሌሊት ቶሎ አይነጋም እንደተባለው ጤነኛ አካል ያለው ሰው ሩጦ በማያመልጥበት አምባገንነት በነገሰበት አገር ውስጥ አካል ጉዳተኛን የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪ አድርጎ ማቅረብ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ የደረሰበት ይፈርዳል ብለን አልፈናል።
6. በፓርቲ የአካል ጉዳተኛ አመራር አባላት ተመስርቶ የሚከፋፈል አምስት በመቶ ይሰጣል። የዚህ ክፍፍል ችግርም ከአምስተኛ ተራ ቁጥር ጋር ይመሳሰላል።

ከ1-6 በተጠቀሱት መመዘኛዎች መሠረት (ለናሙና ያህል) በ2013 ዓም ምርጫ ዓመት የብልፅግና ፓርቲ ብር 22,699,501.65፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ብር 10,854,018.61፣ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) ብር 1,855,835.41፣ የቁጫ ሕዝብ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ቁሕዴፓ) ብር 615,163.85 እና የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) ብር 483,451.96 ሆኖ ተከፋፍሏል። እንዴዚህ ዓይነት

የተዛባ አከፋፈል ጆሴፍ ስትልግዚ እንደፃፈው ምንም ሳይሆን የኤኮኖሚና የፖለቲካ ሥርአቱ የሚፈጥረው ችግር ነው። ሕግና ሕጋዊነትን ተገን በማድረግ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አማካይነት ከመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ይከፋፈላል የተባለው የህዝብ ሀብት ተመልሶ ገዥው ፓርቲ እጅ እንዲገባና የሕዝብን ድምፅ ወሳኝነትን አዛብቷል።

ይኼ ኪራይ ሰብሳቢነት እንዴት እንደሚገን ከአገራችን የግብር አሰባሰብ አንፃር እንመልከት። ለዜጎች ጥቅም ሲባል መንግስት በሕግ በተቀመጠ አግባብ መሠረት የገቢ ግብር ይሰበስባል። የተቀመጠዉ ሕግ ሳይተገበር ከቀረ ወይም የገቢ አሰባበሰቡ አካሄድ አቅጣጫዉን ከሳተ መሠረታዊ የሕግ ጥሰት እንደተጠበቀ ሆኖ ኪራይ ሰብሳቢነት የሚባል ወንጀል አለ ማለት ይቻላል። ከ1997/2005 ምርጫ ወዲህ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግስትን በመጣስ ለክልሎች የተሰጠዉ ወይም በፌዴሬሽን የመንግስት አስተዳደር መርህ መሠረት መከናወን የሚገባዉ የግብር አሰባሰብ ወደ ፌዴራል ተጠሪነት እንዲዞር ተደርጓል። የፌዴራል መንግስት የፌዴራል አካላቱ በሚያካፍሉት በጀት ይተዳደራል እንጂ በክልሎች ሥልጣንና ኃላፊነት ዉስጥ መግባቱ የአገሪቱን ሕገ መንግስት መጣስ ነዉ። በገዥዉ ፓርቲ ሥር የሚገኘዉ የፌዴራል መንግስት የማይገባዉን ጥቅም ሊያገኝ ወይም ያገኘ ስለሆነ ያፈጠጠ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። በጥልቅ ምክንያታዊነት ለሚያምን ሰው ኪራይ ሰብሳቢነት የአገር ባለሀብቶችን፤ በማስከተልም ተጠቃሚ ዜጎችን ዘመናዊ ባሪያ የሚያደርግ ነው።

እንደሚባለው ሀብት ለማፍራት ሁለት መንገዶች አሉ። አንደኛዉ ሰርቶ ሀብት መፍጠር ሲሆን ሁለተኛዉ ሀብት መዝረፍ ነዉ። የተፈጠረ ሀብት ላብን አንጠፍጥፎ ስለሆነ በክብርና በተገቢዉ መንገድ ሥራ ላይ ይውላል። የተዘረፈ ሀብት ግን እየተደፋፋ አንዳች ሐዜነታ ሳይደረግለት መሸታ ቤቶች ሳይቀሩ ይበተንላቸዋል። ሀብት ሲዘረፍ ደግሞ የሚጎዱ አካላት (የሰዉ ሕይወት መጥፋት ጭምር) ይኖራሉ። በዚሁ መሠረት ኪራይ ሰብሳቢነት ብክነት ነዉ፤ የአገሪቱን ሀብት ለብክነት ይዳርጋል።

ምርታማነትን ይቀንሳል፣ ያገሪቱን ኤኮኖሚ ያሽመደምዳል። ኪራይ ሰብሳቢነት ደንበኛ የሚባሉና መከበር ያለባቸዉን ዜጎችን ክብር ያሳጣል። አገሪቱም ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዲታመራ ያደርጋል። ዕዉነት ይኮስስና ውሸት ይነግሳል። የኃይል ዕርምጃዎች በፖሊስ፣ በመከላከያ፣ በደህንነት ኃይሎች፣ በካድሬ፣ ደንብ አስከባሪ በሚባሉ ጭምር እየታገዘ ይወሰዳል። የዜጎች ሕይወት እንዲያዉ ምን ማድረግ ይቻላል ወደሚል ተስፋ ወደ መቁረጥና እርስ በርስ ወደ አለመተማመን ያመራል። ውሎ አድሮ ደግሞ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ።

አሁንም ልድገመውና ሰዎች ስለየሕግ የበላይነት ስለሚያነሱ ስለዚሁ ፅንሰ ሐሳብ በተገቢው ሁኔታ ስለመነሳቱና መብራራቱ ከጥርጣሬ በላይ ስጋት የሚገባቸው ብዙ ሰዎች ስለሚኖሩና ይህ ጉዳይ ለአገር ዕድገትም ሆነ አንድነት ደንቃራ መሆናቸው ስለማይቀር በአጭሩ ማሳየት አስፈላጊ ይሆናል። የሕግ የበላይነት ማለት የመንግስት ባለሥልጣናትን ጨምሮ ሁሉም ሰው አንድም ከሕግ በታች ናቸው ማለት ነው፤ ሁለትም በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ማመልከቱ ነው። ደስታ ዲንቃ ጎሴ፤ <u>መቋጫ ያጣው የኢትዮጵያዊያን የነፃነት ትግል</u> ብሎ በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ “የሕግ የበላይነት ሰዎች/ዜጎች/ ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውንና ከሕግ በላይ የሆነ ሰው ወይም አካል የሌለ መሆኑን የሚገልጽ ዴሞክራሲያዊና ሕገ መንግስታዊ መርህ ነው” ይልና ይኼው ጸሐፊ “የሕግ የበላይነት ተቃራኒ [ደግሞ] የሰው ወይም የገዥ ወይም የመንግስት የበላይነት ነው። የሰው ወይም የመንግስት የበላይነት ሲባል ደግሞ ሕግ ከመንግስት በታች መሆኑንና ለሕግ መገዛት ሳይሆን በሕግ መግዛትን ያመለክታል” በማለት ለሕግ የበላይነት መገዛትንና በሕግ መግዛት መሀክል ያለውን ልዩነት አሳይቷል። በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ ሲተገበር የነበረውን የሕግ የበላይነትና በሕግ መግዛት መሀከል የነበረውን ልዩነት ግልፅ ከመሆኑም በተጨማሪ እስከ ዛሬ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግስታት ዴሞክራሲን ከቃላት በላይ የማይተገብሩት፣ በአወጡት ሕገ መንግስትም ሆነ እናከብራለን ብለው የሚቀበሉትን ዓለም አቀፍ ሕግ ከመጠፍ የማይቆጥሩ አምባገነኖች ናቸው። የኢህአዴግ

ባለሥልጣናትም ሆኑ የኢህአዴግን ወንበር የተረከቡ የብልፅግና ፓርቲ አባላት ከሕግ በላይ መሆናቸው ወይም የሕግ የበላይነትን የማያከብሩ ለመሆናቸው የሐሳብ ልዩነት ያላቸው ዜጎችን ያለአንዳች ምክንያት ወይም ያለበቂ ምክንያት በተገኙበት ቦታ የዓይንህ ቀለም አላማረኝም በሚል ስሜት ብቻ ለማሰርም ሆነ ከእስር ቤት በማውጣት ለመግደል ጭምር 'ሙሉ መብት' ያላቸው መሆኑ ነው። ለምሳሌም የቡኖ በደሌ ዞን ዳጶ ወረዳ ነዋሪ የነበረው ከድሮ ብርሃኑ ከእናቱ ፊት መገደሉ፣ የሰሜን ሸዋ ኤጀሬ ወረዳ እና የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ኦፌኮ ኮሚቴዎች አስተባባሪዎች ፍርድ ቤት በነፃ ቢያሰናብታቸውም የገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና ፖሊሶች እስር ሥር ማቆየታቸው፣ የሰሜን ሸዋ ኦፌኮ ኮሚቴ ምክትል አስተባባሪ ወጣት ደጀነ ግርማ ሁሪሳ የሁለቱም እግሮቹ አውራ ጣት ጥፍሮች በፒንሳ መነቀላቸው፣ አዱኛ የተባለውና የዚያው ዞን የወረዳ ኮሚቴ አባል የሆነው ከእስር ቤት ተወስዶ መገደሉ፣ የምዕራብ ሸዋ ባኮ ወረዳ ኦፌኮ ኮሚቴ አባል መለሰ ጫላ ጎበና ከሚኖርበት ቤት በምሽት ተወስዶ መገደሉና  አስከሬኑ እንኳን የት እንደተጣለ አለመታወቁ፣ እንዲሁም፤ የምስራቅ ወለጋ ዞን ኦፌኮ ኮሚቴ አስተባባሪ ፍቃዱ አያና ፋጂ ከሥራ ቦታ ተወስዶ በነቀምቴ ደህንነት ጽ/ቤት ዉስጥ ለብቻዉ ታስሮ ከቆየ በኋላ የት እንዳደረሱት አለመታወቁና በሌሎችም ላይ የተፈፀሙ ግፎች የሕግ የበላይነት ላለመኖሩ አመላካች ነው። ከዚሁ በተቃራኒ ደግሞ ወንጀል የፈጸሙና ሕግ ፊት መቅረብ የነበረባቸው የመንግስት ባለሥልጣናት በነፃነት እንድንቀሳቀሱ በውስጠ ታዋቂነት የተፈቀደላቸው ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ለአገር አንዳች ጀብዱ የሰሩ ይመስል እንዲሁም ለተቃውሞ የወጡ ዜጎች ላይ ያስተኮሱና ያስገደሉ ባለሥልጣናት ደረታቸው በወርቅ መለበጡ፣ ለአንዳንዶች ደግሞ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ተቋቁሞላቸው ተጠቃሚ ሆነው ስንመለከታቸው፤ ባለሥልጣናቱ ከሕግ በላይ መሆናቸውንና የሕግ የበላይነት ጫማቸው ሥር መረገጡን ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ይህ ሁሉ የሕግ የበላይነት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን የሕግ የበላይነትን ያስከብራሉ ተብለው የሚጠበቁ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ተቋማት (የሰብአዊ መብት

ኮሚሽን፣ መከላከያ፣ ፖሊስ፣ የሕዝብ ደህንነት፣ ፍርድ ቤት፣ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ፣ አቃቤ ሕግ፣ ምርጫ ቦርድ፣ ወዘተ) አስፈፃሚው የመንግሰት አካል የዘፈቀደ እርምጃዎችን ዜጎች ላይ ሲወስድ ዝምታን መምረጣቸው የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣታቸው በሕግ መግዛት እንጂ የሕግ የበላይነት ማለትም የሕዝብ የበላይነትና የሕገ መንግስት የበላይነት አለመኖሩን አመለካች ነው። እንዴዚህ የሕግ የበላይነት የሚባል ሲጣስ የሦስት ሺህ ዘመናት ታሪክ አላቸው የሚባሉ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በሞት መንጋጋ ውስጥ እየተሸለኮሎኩ ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ሆነው ኑሮ መግፋታቸውን ያሳይል። ከዚሁ ጋር አንድ ሊዘለል የማይችል ነገር ቢኖር ተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝቦችም በአድርባይ ምሁራን እየተወናበዱ ከሕግ አክባሪነቱ የበለጠ ሕግ ፈሪነቱ እንዲያመዝን መደረጉ ነው። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ዝም ብለው በደመ ነፍስ ስመለከቱት የኢትዮጵያ ሕዝቦች መንግስትንና እግዚአብሔርን እኩል ያከብራሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መንግስት በሕዝብ ላይ ከሚለቀው የፍርሃት ድባብ የተነሳ መንግስትን ከእግዚአብሔር በላይ የሚፈሩ ዜጎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። ከዚህም የተነሳ የሕግ የበላይነት ማስከበር የሚለው ልፈፋ መሠረታዊ ትርጉሙን ከሳተ ሥርአትን ከፍትህ እንድናስቀድም የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው። ግብረ መልሱ ደግሞ ዜጎች በፍትህ ሥርአቱ ፊት ፍትህ የሚነፈጉና በፍርሃት ድባብ እንዲሸፈኑ የሚደረጉ ከሆነ ፍትህን ፊለጋ ከፍትህ ሥርአቱ ውጭ ወዳሉ ስልቶች ሊያማትሩ ይገደዳሉ። የነፃነት ቀንድል አብሪዎች እነ አብርሃም ልንከሊን እንደተናገሩት “ባሪያ መሆን የሚፈልግ ሰው እንደሌለ ሁሉ ራስን አንስቶ ጌታ ማድረግም ጨርሶ ተቀባይነት አይኖረውም።” ነገሩ እንደማይሆን ሆኖ ቀረ እንጂ ንጉስ ኃይለ ሥላሴም የሐምሌ 9/1923ቱን ሕገ መንግስት ሲያቆም ተናግሮ በነበረው ድስኩር ውስጥ “ሕግ ለሰው ከሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም። መከበርም፣ መጠቀምም፣ የሚገኙት በሕግ መተካከል የተነሳ ነው። ግፍና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው።” ብሏል። በዚያን ጊዜ እንዴዚያ ቢባልም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባሉት ጊዜያት ውስጥም በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት አለመከበሩን በዓይናችን እያየን ኖረናል።

ከላይ ከተጠቀሱት ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ማለትም ለአገር ዕድገትም ሆነ አንድነት ደንቃራ የሆኑ ነገሮችን ማየት ስንቀጥል ከፍርሃትና አድርባይነት ወጣ ባለ ሁኔታ ስለመከላከያ ኃይላችን በመደጋገም በግልፅ መነገር የሚገባና በፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ተቋሙ ሲያሳርፍ የቆየውን የማቀርብ ሐሳብ ይኖራል። እሱም ለፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት ለማገዝ ከማንኛውም ፓርቲ ወይም ቡድን ገለልተኛ ነኝ የሚለው የመከላከያ ኃይላችን ወደ ሩዋንዳ፣ ላይቤሪያ፣ ሱማሊያ ተጉዞ ሠላም አስከበርኩ የሚለው የመከላከያ ኃይላችን በፓርቲ ፖለቲካ ምክንያት የራሱ ዜጎች ደህንነት አደጋ ላይ በወደቀበት ጊዜ ስለ ሌሎች አሰበ ሲባል ጨርሶ የማይመስል ነገር ነው። የራሱን ሕዝብ ደህንነት የማያከብርና የማያስከብር ሠራዊት ምን ስለሆነ ነው ወይም እንዴት አድርጎ ነው የሌላውን አገር ሕዝብ ደህንነት አስከበርኩ ብሎ የሚኩራራው። እዚህ ላይ ኢህአዴግ ደርግን ገልብጦ የመከላከያ ተቋሙን ሲያፈርስ፤ ከነ ተቋሙ እያደገ መሄድ የነበረበትን የአንድ አገር ሠራዊትን እሴት ሁሉ አብሮ እንዳንኮታኮተ ቢገመት፤ ጉዳዩ ከተቋም መፍረስ ግምት በላይ ነው። "… ሠራዊቱ በአንድ ወቅት የኢህአዴግ መንትያ ፍጥረት ነበር" ብሎ የፃፈው ደግሞ በረከት ስሞን <u>በየሁለት ምርጫዎች ወግ</u> (ገጽ 119) መጽሐፉ ላይ ነው። በሌላም በኩል በየክልሎች የተደራጀው ልዩ ኃይል የሚባለው የሕግ የበላይነትን በመጣስ በሚወስዳቸው ያልተገቡ እርምጃዎች የተነሳ የኢትዮጵያን የመከላከያም ሆነ የፖሊስ ኃይልን ስም በማጉደፉ የተቋማቱን ዝና መልሶ ለመገንባት ቀላል የማይባል ዋጋ ማስከፈሉ አይቀርም። በአጭሩ፤ ኢ-ሕገ መንግስታዊ አደረጃጀት ያለው የየክልሎች ልዩ ኃይል የገዥው ፓርቲ ካድሬ፣ ካቢኔና ባለሥልጣናትን ወንበር ጠባቂ ካልሆኑ በስተቀር በምንም ዓይነት መስፈርት ሕዝባዊ ወገናዊነት አይኖራቸውም። ቀድሞውንም ቢሆን ርህራሄ የሌላቸው እንደ ሂትለር ትሩፐርስ፣ ሳዳም ሁሴን ሪፑቢሊካን ጋርድ፣ እንደ ጋዳፊ አማዞን ጋርድ፣ የመንግስቱ ኃይለማርያም ስፓርታ፣ እንደ መለስ ዘናዊ (ኃይለማርያም ደሳለኝ) አጋዚ፣ እንደ አብይ አህመድ ሬደበረት ዓይነቶች በምንም ዓይነት መስፈርት ሕዝባዊ ወገናዊነት ይኖራቸዋል ተብለው አይጠበቁም።

ስለኢህአዴጉ ኪራይ ሰብሳቢነት ብዙ ብዙ መከሰቻዎችን መፃፍ ቢቻልም ከግል ንግዱ አንፃር ደግሞ ተለዋዋጭና ሥርዓት የሌለዉ ግብይት (መግዛትና መሸጥ) ማካሄድ ለሀገር ዕድገትና አንድነት ደንቃራ ስለሆነ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። ምንም እንኳን በመንግስት መመሪያ ማዕቀፍ ዉስጥ ያለ ነዉ ቢባልም የባንኮች ከጣሪያ በላይ ትርፍና የአገልግሎት ክፍያ ማጋበስ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። በሌላም በኩል ሊመለስ እንደማይችል እየታወቀና ግልፅልነት የጎደለዉ ትርፋማነት እንዲሁም የማይመለስ የባንኮች ብድር አሰጣጥና ኮሚሽን መቀበል ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። በተለይ የንግድ ማህበረሰብን በተመለከተ ክፉ ጊዜን በመጠበቅ ወይም የተዛባ የመንግስት ፖሊሲን ከለላ በማድረግ ተጠቃሚን ለችግርና ለችጋር በሚያጋልጥ ሁኔታ ማትረፍ ኪራይ ሰብሳቢነትም ሌብነትም ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አንዱና ትልቁ የኪራይ ሰብሳቢነት መከሰቻና የዕድገት ፀር መሬት የማስተላለፍ ሥራ ነዉ። የአገራችን መንግስት መሬትን ከከተማና በከተማ አከባቢ ከሚገኙ ገበሬዎች እንዲሁም ከግል ባለይዞታዎች በጣም አነስተኛ በሚባል ክፍያ ወይም ያለምንም ክፍያ እየተረከበ ምንም እሴት ሳይጨምርበት ወይም ትንሽ እሴት ብቻ በመጨመር (የአገልግሎት መስጫ ተቋማትን ሳይገነባ ማለት ነው) በካሬ ሜትር በከፍተኛ ሂሳብ ለባለሀብት/እንቨስተር ያስተላልፋል። በጣም አሳዛኙ ደግሞ መሬት ላስረከበዉ ዜጋ ይከፈላል ከተባለዉ ካሳ ላይ እየተቆነጠረ ለባለመብቱ ይሰጣል። ዜጎችን ከመሬት እያፈናቀሉ ሀብት መሰብሰብ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ። ከፍ ተብሎ ሲታሰብም ዘር የማጥፋት ወንጀል ነዉ። አብዛኛው ሕብረተሰባችን መሬትን ከደምና አጥንቱ ጋር ያይዛል። ከመሬት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ቄለም ወለጋ ዞን ተረት የሚመሰል፤ ነገር ግን የምር ዕውነት የሆነና ለተተኪ ትውልድ መነገር ያለበት ዕውነት አለ። እሱም አፄ ምንሊክ አከባቢዉን እንዲወረረ ለአገሬዉ ሕዝብ ቀጠን ያለ ትዕዛዝ ያስተላልፋል። ትዕዛዙም የአንበሳ ደቦል ይዛችሁ ካላመጣችሁ በስተቀር መሬታችሁን ትቀማላችሁ የሚል ነበር። የአገሬዉ ሕዝብም መሬቱን ከሚያጣ የዱር አዉሬዉን ይዞ

ማቅረብ ምርጫዉ አድርጎ ለሕይወቱ ሳይሳሳ የዱር አዉሬዉን ይዞ ለንጉሱ አስረከበ። የስድስት ኪሎዉ ወይም የቀድሞዉ የቤተመንግስት አንበሳ (ከሁለቱ አንዱ) በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ተይዞ ለምንሊክ የተሰጠ ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሕዝብ ከዱር አዉሬና ከወራሪ ጋር ከሰዉነት ወጥቶ የዱር አዉሬ ባህርይ ከተላበሰዉ ሰው ጋር ታግሎና የሕይወት ዋጋ በከፈለበት መሬት ላይ የኢህአዴግ ኪራይ ሰብሳቢነት ተንሰራፋ።

ሌላዉ የኪራይ ሰብሳቢነት ክስተት የመንግስትን ንብረት ለመሸጥ የተዛባ የጨረታ ሥርዓት መከተል (wrong and disputable auction) ማካሄድ ነዉ። ሌላም ማንሳት ይቻላል፤ ከመንግስት ካዝና አወጥቶ ዕሴት ለማይፈጥር ሥራ ሽልማት ወይም ስጦታ መስጠት ሌላ ኪራይ ሰብሳቢነት ነዉ።

እነዚህና ሌሎችም የኪራይ ሰብሳቢነት ባህርያት በኢትዮጵያ ዉስጥ አሉ፤ በተለይም የገዥዉ ፓርቲ የኢህአዴግ እና የኢህአዴግ ወንበር ተረካቢ የብልፅግና ፓርቲ ካድሬዎችና ካቢኔዎች ዋና ባህርያት ናቸዉ። የትም ይሁን የት በኪራይ ሰብሳቢነት ጥቂቱና የላይኛዉ ወገን አጥቂ፤ ብዙኃኑ የታችኛዉ ህብረተሰብ ክፍል ተጠቂ ናቸዉ። ኪራይ ሰብሳቢነት ከፖለቲካ አንፃር መልካም አስተዳደርን፣ ከኢኮኖሚ አንፃር የገቢ መመጣጠንን፣ ከማህበራዊ ሕይወት አንፃር የመዋደድና የመከባበር ባህልን አመንምኖ ቦታ እንዳይኖራቸዉ ያደርጋል። ውጤቱም የማያባራ ግጭት ነው።

ስለኪራይ ሰብሳቢነት በተለይም ስለአገራችን ኪራይ ሰብሳቢነት ስናስብ የአገዛዝ ሥርዓቱ ከመሠረቱ ሲገነባ ሕዝባዊ ተቀባይነት ባለዉ ዲሞክራሲያዊ መንገድ ሳይሆን፤ ብቃት የሌላቸዉ ሰዎች እየተለቀሙ በሕዝብ ላይ የተጫኑ ስለሆነ፤ ታማኝነታቸዉን የሚያሳዩት አገልግሎታቸዉ ለሚገባዉና ለሚፈልግ ሕዝብ ሳይሆን፤ በዚህ እና በዚያም ብሎ ሥልጣን ላይ ላስቀመጣቸዉ ድርጅትና ባለሥልጣን ስለሆነ፤ ኪራይ ሰብሳቢነቱ ከዚያ ይጀምራል። ጆሴፍ ስትግልዚ (31-32) በተጠቀሰው መጽሐፉ *"... a political system that gives inordinate power to those at the top, and they have used that power not only*

*to limit the extent of redistribution but also to shape the rule of the game in their favor, and to extract from the public what can only be called large "gifts". Economists have name for these activities; … rent seeking."* ብሎታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሕወሓት/ኢህአዴግ በፕሮፓጋንዳ መጽሔቱ አዲስ ራዕይ ቅፅ 3 ቁጥር 3 (2002፡ 8) ላይ "ኢህአዴግ በምርጫ 2002 እጅግ አስገራሚ በሆነ አኳኋን ሊያሸንፍ የበቃበት አንድ መሠረታዊ ምክንያት ልማታዊ መስመራችን የኪራይ ሰብሳቢነት መስመርን በልማት ትግል መስክ በማሸነፍ ነዉ" በማለት በፎከረበት አንደበት በነሐሴ 2007 መቀሌ ላይ ባካሄደዉ ጉባኤ ደግሞ ዛሬም ኪራይ ሰብሳቢነት ችግሩ መሆኑን መግለጹ፤ በማኪያቬላዊ አነጋገር ማጨበርበር ከመሆኑም በላይ በዚሁ ገዥ ፓርቲ በሕዝብ ሀብት ላይ ወንጀል እየሰሩ ያሉ ሰዎች መኖራቸዉን፤ ነገር ግን ተሸፋፍኖ ለመኖር ዛሬም ያልተኙ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ዜጎችን ከኪራይ ሰብሳቢዎችም ሆነ ከማንኛዉም አደጋ የማይከላከልና የኑሮ ደረጃቸዉን ማሻሻል የማይችል አገዛዝ በራሱ ዜጎች መጠቃቱ አይቀረ ነዉ። አንደ Charles W. Kegley (1981:495) አገላለጽ *"No government is immune from attacks by its citizens for its inability to protect its population or improve its life."* በማለት የገለጸዉን ድርጊት፤ ትንቢት ተናጋሪው ዶክተር መረራ ጉዲና ደግሞ "የሚበላዉን ያጣ ሕዝብ መሪዎቹን ይበላል" ብሏል። ዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብታቸዉን የማስከበሩ ትግል አንድም ከምግባቸዉ እኩል ወይም የበለጠ ያሳስባቸዋል። ዜጎችን ለአደጋ ከሚያጋልጡና ዘመናዊ ባሪያ ከሚያደርጉ ድምፅ አልባ ጥቃቶች ዉስጥ አንዱ ኪራይ ሰብሳቢነት እንደሆነ በሰፊዉ ገልጫለሁ። የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮች ብዙ እና የተለያዩ ቢሆንም በዋናነት የመንግስት መዋቅር ቀዳሚ ሲሆን፤ በተለይም በሕዝብ ዘንድ ቅቡልነት የሌለዉና ተጠያቂነት የማይሰማዉ የመንግስት ዓይነት ከሆነ ዋና የኪራይ ሰብሳቢዎች ምንጭና የዚሁ ኪራይ ሰብሳቢነት ፖሊሲ አዉጪ ፓርቲ ስለሆነ፤ ጉባኤና ስብሰባ በጠሩ ቁጥር የተለየ አደጋ እንደሆነ አድርጎ መናገሩ ጉንጭ አልፋ ንግግር ከመሆን

የሚያልፍ አይሆንም።

ለኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት ደንቃራ ከሆኑት ውስጥ የሕወሓት/ኢህአዴግ በማዕከልም ሆነ በተዋረድ ባሉት መዋቅሮቹ አስከፊ ችግሮቼ ናቸዉ ከሚላቸዉ ዉስጥ አንዱ የመልካም አስተዳደር እጦት ነዉ። መልካም አስተዳደር ባልሰፈነበት ሕብረተሰብ ዉስጥ ፍትህ ይዛባል፣ በመንግስት ባለሥልጣናትና በሕብረተሰቡ መሀከል የበታችነትና የበላይነት ስሜት ይሰፍናል፣ ኤኮኖሚዉንም ማሳደግ አይቻልም። አገራችን ኢትዮጵያ የስው ሀብትን ጨምሮ ያላት ሀብት በሙሉ በተፈለገዉ ሁኔታ ሥራ ላይ ይውላል ማለትም አይቻልም። መልካም አስተዳደር ባልሰፈነበት የአገዛዝ ሥርአት ዉስጥ ሕዝብ የአገሩ ባለቤትነት እንዲሰማዉ ሳይሆን ባዕድነት የሚሰማዉ ስለሆነ፤ ገዥዉ ፓርቲ በሚያወጣዉ የልማት ፕሮግራም ዉስጥ አይሳተፍም፤ ቢሳተፍም ከልቡ ሳይሆን እየፈራ ይሆናል። ከመልካም አስተዳደር ጉድለትና ሙስና፣ ኪራይ ሰብሳቢነት መንሰራፋት የተነሳ ብዙዎች ሜጋ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው ጊዜና ወጪ እጥፍ ጊዜና ወጪ እየጠየቁ ተጠቃሚውን ሕዝብ ለእንግሊት ይዳርጋሉ፤ የባለሥልጣኖች ኪስ ደግሞ ይደልብበታል። በውጤቱም የአገራችን የፓርቲ ፖለቲካ ስልጡን አመራር ማጣትን ያሳያል።

በአንዳንድ መስሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ጭምር ከግለሰቦች የተዛባ የግል ባህርይ የተነሳ ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር በተዳደኘ ሁኔታ የመልካም አስተዳደር እጦትም አለ። ነገር ግን መሠረታዊ ጥያቄ መሆን ያለበት የሕወሓት/ኢህአዴግ የመልካም አስተዳደር እጦት በስርአቱ ውስጥ በስፋት የተንሰራፋ በመሆኑ በዚህ በመልካም አስተዳደር እጦት የተቸገረዉ ኢህአዴግ ነዉ ወይስ ሕዝቡ? ግንባሩ ከሆነ ብዙም ጩኸት ሳያስፈልገዉ መልካም አስተዳደርን በሚያዛቡ አባላቱና ካድሬዎቹ ላይ እርምጃ መዉሰድ ብቻ በቂ መሆኑን ብዙም አማካሪ አያስፈልገዉም። በመልካም አስተዳደር እጦት የተቸገሩት ሕዝቡ ከሆነና ያስቸገሩት ደግሞ የገዥዉ ፓርቲ ጠቅላላ አባላቱ ይሁን ውስን ክፍሉ፤ ሕዝብ ሳይመርጣቸዉ የሥልጣን ቁንጬ ላይ ከመቀመጥ እጅን መሰብሰብ

ይጠበቅባቸዋል፤ ወይም ፓርቲዉ ራሱ እንዳለ ሥልጣን መልቀቅ አለበት። ነገር ግን ሕወሓት/ኢህአዴግ የመልካም አስተዳደር እጦትን ከፖሊሲ አቅጣጫ ወይም ከአስፈፃሚዉ አካል ሳይሆን ብዙም አቅም በሌላቸዉ የበታች አካላት አባላቱ ላይ በማላከክ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ለመጥቀስም ከላይ የተጠቀሰው አዲስ ራዕይ (2002፡ 15) የተባለዉ የኢህአዴግ መጽሔት "በፍትህ አስተዳደር በተለይም በዝቅተኛ አመራር አካላት ዙሪያ ባለዉ የመልካም አስተዳደር ሁኔታ ልዩ ግምት መስጠት እንዳለብን አበክሮ አሳስበናል።" በማለት ጽፏል። ይህ ማለት ደግሞ የከፍተኛዉን አመራር አካል በዝቅተኛዉ አመራር አካል መስዋዕት ለማለፍ ፍላጎት ያለዉ ይመስላል። ሆኖም ግን የዓሳ ግማትን ተረት የተገነዘበ ሰዉ ይህንን ሴናሪዮ አይቀበልም። እንደ አዲስ ራዕይ መግለጫ የመልካም አስተዳደር ሁኔታን በተለይም በዝቅተኛ አመራር አካላት ላይ የሚያርፍ ቢሆንና ግምቱም ትክክል ነዉ ቢባል፤ የሸፍትነትና የሌብነት ስብእናን ይዞ እንዴት ተደርጎ የሕዝብ መሪ እንደሚኮን ማሰቡ ራሱ አስቸጋሪ ነዉ። ነገር ግን *"Crimes against humanity are not merely the responsibility of those who commit them, but also the responsibility of the highest government officials."* ብሎ አሜሪካዊዉ ጃክ ኬኔዲ (1995፡ 11) የፃፈዉንና ብዙ ሰዎች የሚቀበሉትን እዉነታ እንዴት ተደርጎ በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ወደ ታች ሊገፋ እንደሚችል ማሰቡ አስቸጋሪ ነዉ። በአብዮታዊ ዴሞክራሲና በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አመራራቸው የላይኛው አመራር ሳያውቅ የበታች አካል የሚሰራው አንዳች ሥራም ሆነ የሚፈፅመው ጥፋት አይኖርም። አልፎ አልፎ ይከሰታል እንኳን ቢባል የላይኞቹ የሚወስዱት የማስተካከያ እርምጃ የለም። ለሚሰሩት ወንጀል እንኳን ተጣጥመው እየሄዱ ያሉ እንደሆነ ማረጋገጫ ነው። ከ2012 ዓ.ል ወዲህ ደግሞ የኢህአዴግ የመልካም አስተዳደር ጉድለትን በክፍልፋይ ሲሰላ 2/3ኛ የሆነውን ነፃ በማድረግ ወይም ይቅርታ አድርገው እንደሆን በማይታወቅበት ሁኔታ ¼ኛ በሆነው ሕወሓት ላይ ይደፈድፋሉ። በርግጥም ሕወሓት እንደ ኢህአዴግ የበላይ ፓርቲ የተጠያቂነት አንበሳ ድርሻ ቢወስድም በምንም ዓይነት ሁኔታ 2/3ኛው የሆነውና አዲስ አበባን

ምሽግ ያደረገው ወንጃይ እጁ ነፃ አለመሆኑን መገንዘብ አለበት።

መልካም አስተዳደር ወይም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ከዉጤታማነትና ብቁነት የሰፋና የገዘፈ ፅንሰ ሐሳብ ሲሆን፤ ለአጠቃላይ የፖለቲካ ሥርአቱ የሚቆምና የዜጎችን ፖለቲካዊ እና ሰብአዊ መብቶች እና ነፃነቶች የሚያስከብርና ማንኛዉንም ዓይነት አድልዎ የማይቀበል ሂደት ነዉ። ግልፅነትና ተጠያቂነትም በሲቪል ሰርቪሱ ብቻ የማይታጠር በፖለቲካ አመራሩና ተቋማት ሊተገበር የሚገባዉ ቁልፍ ሚና አለዉ። መልካም አስተዳደር አሳታፊነትን፣ ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትን፣ የሕግ የበላይነትን፣ ዉጤታማነትን፣ ፍትሓዊነትን እና ስትራቴጂያዊ ባለራዕይነትን ጨብጦ መስራትን በአጠቃለለ ሁኔታ ይገለፃል። የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ከጥያቄም በላይ የሕልዉና ጉዳይ ነዉ ከተባለ ለይምሰል ወይም ለለበጣ (rhetoric) ሳይሆን መገለጫዎቹን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ቁርጠኛ ትግል በተለይም ከራስ ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል ማድረግን ጭምር ይጠይቃል። ትልቁና አስቸጋሪዉ ትግል የት የሚጀምር መሰላችሁ? ከራስ የሚጀምር መሆኑን ብዙ ሰዎች ሲናገሩ ይደመጣል። በመልካም አስተዳደር እጦት ከሕወሓት/ኢህአዴግ የበለጠ ተጎጂዎች ሕዝቡ ሲሆን፤ ምናልባት ከግንባሩ አባላት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሐቀኝነትና ሕዝባዊ ኃላፊነት የሚሰማቸዉ ግለሰቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይጠረጠርም። ነገር ግን ሕዝባዊ ኃላፊነት የሚሰማቸዉና ራሳቸዉን ነፃ ማዉጣት የሚችሉ ግለሰቦች መኖራቸዉ ቢታመንም ሥርአቱን መለወጥ እስካልቻሉ ድረስ ሥርአቱን ከተጠያቂነትና ራሳቸውም ከሕሊና ጉስቁልና ከመዳረግ አያድኑም።

የመልካም አስተዳደር እጦት ማለት ሕዝቡ ማግኘት ያለበትን ሕዝባዊ አገልግሎት አለማግኘት ወይም ኢትዮጵያዊያን እንደሰብአዊ ሰዉ የሚገባቸዉን የተፈጥሮም ሆነ በሕግ የተደነገገዉን ማጣታቸው ነዉ። ዜጎች በዜግነታቸዉ ማግኘት የሚገባቸዉን አገልግሎት ሳያገኙ ሲቀሩ፤ ላገኙት አገልግሎትም ከመጠን ያለፈ ክፍያ ሲጠየቁ፤ ወይም የሚፈለግባቸዉን የዜግነትና ሕጋዊ ግዴታ ለመወጣት ሲቀርቡ

የሚያስተናግዳቸዉ የመንግስት ተቀጣሪ ሰዉ ከቦታዉ ሲጠፋና ለተጨማሪ ወጪ ሲዳርጋቸዉ፤ ዜጎች ለከሰሱበትም ሆነ ለተከሰሱበት ጉዳይ ፍትህ ሲነፈጉ፤ ወይም በፖለቲካ አቋም ልዩነት የተነሳ ዜጎች በሐሰት ሲከሰሱና ሙያተኛ (ፕሮፌሽናል) ምስክሮች ወይም የመጋረጃ በስተጀርባ ምስክሮች እየተመደቡባቸዉ የረጅም ዓመታት እስር ወይም ዕድሜ ልክና ሞት ሲፈረድባቸዉ፣ ወይም ኢፍትሓዊ የፖለቲካ ብይን ሲበይንባቸዉ፣ ከዚህም የተነሳ ዜጎች የመኖር ሕልዉናቸዉ ጥያቄ ምልክት ዉስጥ ሲገባ፤ የመልካም አስተዳደር እጦት እንዳጋጠማቸዉ መታወቅ አለበት። ስለኢህአዴግ የመልካም አስተዳደር ጉድለት ብዙ ማለት የሚቻል ቢሆንም፤ ጠቅልል ባለ አገላለፅ ግን ቀደምት ኢህአዴግም ሆነ ወንበሩን የተረከበው ብልፅግና ፓርቲ ከግልፅነት ይልቅ ሕዝብን በጉልበትና በማሞኘት ለመግዛት የተንቀሳቀሱ ድርጅቶች ናቸው ቢባል ብዙዎችን ያስማማል።

ሙስናን፣ መልካም አስተዳደር እጦትን፣ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት ሕወሓት/ኢህአዴግ መተማመኛዬ ነዉ ብሎ ከሚያምንባቸዉ አካሎች ግንባር ቀደሙ ሕዝብ ነዉ። በሕዝብ ላይ እምነት ማሳደር ትክክለኛ እርምጃ ቢሆንም፤ ቀና የሆነ ግብረ መልስ ከሕዝቡ ሊኖር የሚችለዉ ግን የሕዝብን ይሁንታ የሚቀበል ሰዉ ወይም የፖለቲካ አካል ሲኖር ብቻ ነዉ። ይህንን የሌለዉ አካል ቀና የሆነ ግብረ መልስ ከሕዝብ መጠበቅ የሞራል ብቃት አይኖረዉም። በኢትዮጵያ ዉስጥ ለሕዝብ ድምፅ ቦታ ስላልተሰጠ ብቻ ሳይሆን ሙሰኛ ባለሥልጣናት በሕዝብ ላይ ሽብር እስከሚፍጠር ስለሚደርሱ የሕዝቡ ተነሳሽነት የለም እንኳን ባይባል በጣም አናሳ ይሆናል። ለዚህ አብነት ኢትዮጵያ ዉስጥ የተደረገ ጥናት ስለመኖሩ እርግጠኛ ባይኮንም የዩጋንዳ ሕገ- መንግስታዊ ገምጋሚ ኮሚሽን (Constitutional Review Commission) በዩጋንዳ ዉስጥ ስለተደረገዉ ምርጫ እአአ ታህሳስ 2006 አንድ ማጠቃለያ ሪፖርት አወጥቶ ነበር። ኮሚሽኑም የሕዝብ ትብብር ስለማነሱ የገለፀዉ ይኼው ሪፖርት *“The public is largely unaware, un-inspired, not motivated and not involved in issues of governance including the fighting*

*against corruption.* ***A feeling of powerlessness continues to grip the public.*** *The corrupt are powerful and easily buy off the poor. Some of those who would like to see changes in the use of public funds are intimidated."* በማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያም የመልካም አስተዳደር እጦት ሲጎረብጠዉ "አሁን ለማን አቤት ይባላል?" በማለት የተስፋ ቆራጭነት ስሜት ከማንፀባረቅ በስተቀር ሙስናንና ባለቤቱን ለማስወገድ ጊዜና ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ ከመጠበቅ በላይ ምንም ለማድረግ ምርጫ አላገኘም። በሌላም በኩል ብዙሃን ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ሆነው በሚኖሩባት ኢትዮጵያ አገር ዉስጥ በጣት የሚቆጠሩ የገዥ ፓርቲ አባላትና ተጠቃሚዎቻቸዉ እየደፋፉ የቅምጥል ኑሮ ሲኖሩ፤ የኅብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስር እየላላ፣ ያለዉ የሌለዉን ማግለሉ በስፋት እየታየ ይሄዳል እንጂ አይተባበሩም። ተቃዋሚ/ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቢኖሩም የመደመጥ ዐቅም ስለሌላቸው፤ እንኳንስ የሕዝብን መብትና ነፃነት ማስጠበቅ ቀርቶ የራሳቸው ሕልውና ራሱ አስጊ ነዉ። በተለይ አገሪቱ መልካም አስተዳደር የሚያሰፍን ሕግ ከሌላትና ያለዉም ሕግ በሥልጣን አከባቢ ላሉት የመንግስት አባላትና ተጠቃሚዎቻቸዉ በኔስ የሚያስገኝና የሚቀረፀዉ ሕግ ራሱ ለአንድ ወገን ብቻ በሚያዳላ ሁኔታ ተግባራዊ የሚደረግ ከሆነ፤ እርም ነዉ ይች አገራችን ሊታድግ አትችልም፤ ሊትወጣ የማትችል ቀዉስም ይጠብቃታል።

የመልካም አስተዳደር እጦቱ መሠረታዊ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉንና እግረ መንገዱንም የፓርቲ ፖለቲካ ስለሚያመነምኑት ነገሮችን እስቲ አንስተን እንመልከት። አሁን በሥራ ላይ ያለዉ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ሦስቱን የመንግስት አካላት ሥልጣንና ተግባራትን አስመልክቶ አንዱ የመንግስት አካል ሌላዉን ሊቆጣጠር የሚችልበትን አቅጣጫ አላስቀመጠም፤ የመስተዳድሩን የሥራ ዕድሜም አልወሰነም። ይህ በመሆኑም የመልካም አስተዳደር እጦት ችግር ከአገሪቱ መሠረታዊ ሕግ አቀራረፅ ጀምሮ እስከ አፈፃፀም ድረስ ሊከሰት ችሏል። ማሪያን ዲ አይሪሽ (1996፡ 86) "The legislative, executive and judicial departments

should be separate and distinct so that neither exercise the powers of properly belonging to the others.” በማለት የፃፈችው ይህ ችግር መሠረታዊ መሆኑን ሰፊ ጥናት ከአደረገችበት በኋላ ነዉ።

በሕግ የተደነገገ የሥልጣን ክፍፍል መኖር ማለት የሕግ አዉጪዉ አካል የአገሪቱን ሕግና ደንቦችን ያወጣል፣ ሥራ አስፈፃሚዉ የወጡትን የአገሪቱን ሕግና ደንቦች ሳያዛንፍ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የፍትህ አካሉ የሚወጡ ሕጎች ሆኑ ደንቦች ሲወጡም ሆነ ሲተገበሩ ሕገ መንግስቱን ያልተቃረኑ መሆኑን ማረጋገጥና አስፈፃሚዉ ደግሞ ሥራዉን የሚያከናዉነዉ በወጣዉ ሕግ መሠረት ብቻ መሆኑን እያረጋገጠ ሕግ በሥራ መተርጎሙን ያረጋግጣል ማለት ነዉ። የአንዱ የመንግስት አካል ሥልጣን ከሌላዉ የመንግስት አካል ሥልጣን አይበልጥም ወይም አያንስም። አንዱ የመንግስት አካል ሌላዉን መቆጣጠር ማለት ሕገ መንግስቱ በሦስቱም የመንግስት አካላት መሀከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖርና የዜጎች ሥራ እንዳይበደል ብቻ ሳይሆን ዜጎች እራሳቸዉ የአገራቸዉ ባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸዉ የሚያደርግ ቴክኒካዊ ግንኙነትን የሚያመቻች ሰነድ ነዉ። ሕግን የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠዉ ሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ራሱን ችሎ ሥራ ላይ ባለመኖሩ፤ ይህ ከባድ ሥራ በፓርቲ ዉክልና ለተመረጡና የአንድ ፓርቲ አባላት ለታጨቁበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ተላልፎ በመሰጠቱና የሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ሥራና የምክር ቤት ሥራ በአንድ ሙቀጫ ዉስጥ ገብቶ እንዲወቀጥ በመደረጉ የትም ሊደርስ አይችልም። ላቮስ አላን (2002፡ 62) ቬስታሊን የተባለዉን ፀሐፊ በመጥቀስ እንደፃፈችዉ *“The absence of independent constitutional court has led observers to claim that the Ethiopian [federal] system lacks the essential limits to the government to which a commitment to the principle of*

*constitutionalism should imply."* ብላለች።

ለጊዜው የሦስቱ መንግስት አካላት ማለትም የሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚን አለመለያየትና አንዱ ሌላውን አለመቆጣጠሩም ሆነ አለመደጋገፍ እንተወውና ለረጅም ጊዜ አገራችንን ሲያቆረቁዝ ስለነበረው የገዥው ፓርቲ-መንግስት መዋቅር ጥመርታ ገጽታዎችን ብንመለከት ነፃነት ስላጡት ዜጎች ብቻ ሳይሆን ነፃነት ስላጡት ተቋማትም ግልፅ ያደርግልናልና ቀጥሎ ባሉት መስመሮች እገልፃለሁ።

- ድርጅት ጽ/ቤት እየተባለ በያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የተዋቀረው የገዥው ፓርቲ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች ስብስብ የየመንግስት መስሪያ ቤቶቹ ከፍተኛ አማካሪዎችና ኤክስፔርቶች ተብለው የሥራ መዘርዝር ውስጥ የተካተቱ ሲሆን፤ በፓርቲ ጽ/ቤቶች መደበኛ የፓርቲያቸውን ሥራ እየሰሩ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሁም ተሸከርካሪ ጭምር ስለሚሰጣቸዉ በኑሮ ከሌላው ሠራተኛ በተሻለ ሁኔታ ይገኛሉ። በከፍተኛ አማካሪነታቸውና ኤክስፐርትነታ በሲቪል ሴርቪሱ ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ ያደርጋሉ። የሲቪል ሴርቪሱን ገለልተኝነትን ጥያቄ ምልክት ውስጥም ያስገባሉ።
- የገዥው ፓርቲ እና የመንግስት መዋቅር የተጣመረ ስለሆነ ፓርቲው ጽ/ቤትን የሚጠቀመው አንዳች ኪራይ ሳይከፍልበት ነው። አውሬው ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ጠይቆት የሚባለው ተረት እዚህ ጋ በሚገባ ሰርቷል። ሕወሓት/ኢህአዴግ እስከ ብልፅግና ፓርቲ ድረስ

ስለተጠቀሙበት የመንግስት ሕንፃዎች ከአገር አቀፍ ጀምሮ እስከ ታች ወረዳ ድረስ ሂሳቡ ቢሰላ በትንሹ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከገዥው ፓርቲ ይፈለጋል፡፡ ይህ ያልተከፈለ ወይም የማይከፈልም ገንዘብ ለገዥው ፓርቲ ትልቅ የሚባል አቅም ፈጥሮለታል፡፡

- ገዥው ፓርቲ ልቀናጣ ነው ካላለ በስተቀር የሚያካሂዳቸውን ስብሰባዎች አንዳች የአገልግሎች ሂሳብ ሳይከፍል ንብረትነታቸው የመንግስት በሆኑ አዳራሾች ነው፡፡ እንዲዚህ ዓይነት የገዥው ፓርቲ-መንግስት መዋቅር ጥመርታ ድርጊት (ከይቅርታ ጋር ለኔ ጽሑፍ በሚመች አድርጌ ልጠቀምና) “ፓርቲዎች ሁሉ እኩል ናቸው፤ አንዳንዱ ፓርቲ ግን የበለጠ እኩል ነው” የሚለውን የጆርጅ ኦርዌልን <u>የእንስሳት ዕድር</u> ምሳሌን ያስታውሰናል፡፡ ስለሆነም፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን ጨምሮ የመንግስት ንብረት አጠቃቀም ገደብ ሊበጅለት ይገባል፡፡
- ኢትዮጵያ ውስጥ ከነፍስ ወከፍ እስከ ቡድን መሳሪያ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ሲኖሩ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና አጃቢዎቻቸው መሳሪያ ይዘው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የሚይዙት መሳሪያ ከመንግስት ካዝና ወይም መጋዘን የሚወጣ ስለሆነ ለገዥው ፓርቲ ታማኝ እስከሆኑ ድረስ የተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ ከጉሸማ እስከ ማስፈራሪያ ድረስ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ገዥው ፓርቲ እንደፈለገ የሚጠቀምበትን መደበኛ ሠራዊትና በራሱ አቅም የሚንቀሳቀስ አማፂ ኃይልን ጨምሮ የጦር መሳሪያን አለአግባብ መጠቀም የሕዝብ ነፃ እንቅስቃሴን ይገድባል፡፡
- ሕገ መንግስታዊ አደረጃጀት የሌለው የየክልሎች ልዩ ኃይል

የሚባሉት መጠነ ሰፊ ትጥቅ ይዘው በመንቀሳቀስ በየክልላቸውም ሆነ ከክልላቸው ውጭ (የአማራ ፋኖን ምሳሌ መውሰድ ይቻላል) እርምጃ ይወስዳሉ። ከእርምጃ አወሳሰዳቸው ለመረዳት እንደሚቻለው እነዚህ ልዩ ኃይል የሚባሉት እርምጃ አወሳሰዳቸው ከሽምቅ ተዋጊ ኃይል ጋር ስለሚመሳሰል የየተደራጁበትን ሕዝብ መብትና ጥቅም እንኳን ሲጥሱ ይታያሉ። በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል አብዲ ኢሌ እና በአማራ ክልል በወሎ ኦሮሞ ላይ የተወሰዱትን አሰቃቂ እርምጃዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ከተግባራቸው ለመረዳት እንደተቻለው እነዚህ ልዩ ኃይል የሚባሉቱ የየተደራጁባቸውን ሕዝቦች መብቶችና ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋሙ አይደሉም። ልክ ሂትለር ዘ ቱሩፔርስ፣ ኃይሌ ሥላሴ ክቡር ዘበኛ፣ ሳዳም ሁሴን ሪፑበሊካን ጋርድ፣ ሙአመር ጋዳፊ አማዞን ጋርድ፣ እና መንግስቱ ኃይለማርያም ስፓርታ፣ መለስ ዜናዊ አጋዚ ብለው እንዳቋቋሙት ዓይነት አገልገሎት የሚሰጡና ግፋ ቢል የገዥውን ፓርቲ ካድሬዎችና ካቢኔዎችን ጥቅም ለመጠበቅ የተቋቋሙ ከመሆን አይዘሉም። አገራችን ኢትዮጵያ ከእንዲዚህ ዓይነቱ ምርታማ ካልሆነ ኃይል ግንባታ ካልተላቀቀች በስተቀር የዜጎች ነፃ ሐሳብ መንሸራሸር ማስተናገድ አይችልም። ከሕገ መንግስታዊ ሰነድ ውጭ የታጠቀ ኃይል ከመደበኛ ውጭ ተደራጅቶ ሲንቀሳቀስ ዜጎች የሥነ ልቦና ነፃነት አይሰማቸውም።

- ገዥው ፓርቲ እና መንግስት የተጣመሩ ስለሆነ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ላይ ስፍር ቁጥር የሌለው ተፅዕኖ ፈጥሮአል። የመፍትኼ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜው የረፈደ ቢመስልም ቀሪ ጊዜ ይበልጣል። የተፎካካሪ ፓርቲዎች ነፃ እንቅስቃሴ

ከተገደበ የአጠቃላይ ማህበረሰቡ አማራጭ ሐሳብ ማግኘትም እንደተገደበ ይቆጠራል።

- የገዥ ፓርቲ-መንግስት መዋቅር ጥመርታ ፍትህን አዛብቷል፤ ወደፊትም ያዛባል። ነገሩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ በቀደመው ጊዜም ይሁን በአሁኑ ጊዜ ፖሊስ እና የካቢኔ አባላት ዜጎችን ከቤታቸው፣ ከሥራ ገበታቸው፣ ከመንገዳቸው፣ ወዘተ ይዘው ያስራሉ፤ ያሳስራሉ። በሕገ መንግስቱ ከተቀመጠው ጊዜ ውጭ ለፍርድ ቤት ያቀርባሉ፤ ወይም ጨርሶም አያቀርቡም። ፍርድ ቤት ቀርበው አካሉም በነፃ ወይም በዋስ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤት የሚያዘውን ፖሊስና የካቢኔ አባላቱ አይለቁም። በዚህም የተነሳ ዜጎች ደህንነት አይሰማቸውም። የራሱ ደህንነት የማይጠበቀው ዜጋ እንኳንስ ስለ ፓርቲ ፖለቲካ ሊያወራ ከቤቱ ሲወጣና ሲገባ ምን ያጋጥመኝ ይሆን እያለ እየተጋለመጠ ይሄዳል።
- አስቂኝ ጥመርታም አለ። የገዥው ፓርቲ እና ተቃዋሚ ፓርቲ ነን በሚሉ አንዳንድ ፓርቲዎች መሀከል በደርግ ጊዜም የነበረ ነዉ፤ በወያኔ/ኢህአዴግ ጊዜም ነበረ፤ ዛሬ በቁጥር ሁለት ኢህአዴግ (ብልፅግና ፓርቲ) ጊዜም አለ። የሁሉም ጥመርታ ለበጎ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር። ተግባሩ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማጥበብና አንዱ ሌላውን እንዲያጠፋ ጥርነፋ ተብሎ የሚታወቅ ነው።

የዚህን ንዑስ ርዕስ ከማጠቃለሌ በፊት ለፌዴራሊዝም ግንባታም ሆነ ለኢትዮጵያዊያን ትስስር፣ ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ግንባታም ሆነ ለፓርቲ ፖለቲካ ግንባታ ከባድ እንቅፋት የሆኑ ሁለት ነጥቦችን ማስቀመጥ እፈልጋለሁ። እነሱም ነባር ታሪካዊና ከሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት

ግንባር ጋር የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው፡፡

ከነባር ታሪካዊ ችግሮች አንዱ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ግንባታ ሲሆን እሱም የተካሄደው በወረራና ወረራውን ተከትሎ በመጡት የገባርና የባርነት አገዛዝ ጊዜያት ውስጥም ከግጭትና ጦርነት ያልተላቀቀ እንደነበር ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ጎረቤት የደቡብ ሕዝቦችን በነፍጥ የተቆጣጠረው የምንሊክ የነፍጠኛ ቡድን የኢትዮጵያን የሀገረ መንግስት ግንባታን ለማጠናቀቅ ጉልበትና ሞራልን የሚነካ የጥላቻ አገላለፆችን ጭምር ተጠቅሟል፡፡ በአጭር ምሳሌ ለማስረዳትም አንድ ባንድራ፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሚስት፣ አንድ አገር፣ አንድ ሃይማኖት፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ከመጠቀማቸውም በላይ ዓላማቸውን ለማሳካት አማርኛ ተናጋሪ ያልሆኑትን ወይም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚጠቀሙትን ‘ተብታባ’ በማለት ሞራል በሚነኩ አባባሎች ተጠቅመው ለአገዛዛቸው አመቻችተዋል፡፡ ያ ጊዜ አልፏል፣ ሰዎቹም ዛሬ የሉም የሚባል ሙግት ቢነሳ ደግሞ የሐበሻ ተወላጆች የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችን በስልት ወደ ዳር መግፋትና ጥግ ማስያዝ በነፍጠኞች የልጅ ልጆችም አልቀረላቸውም፤ የሀገረ መንግስት ግንባታቸውም በሁለት ምክንያቶች እስከዛሬም አልተሳካም፡፡ አንደኛ ወራሪው የሐበሻ ጦር ከአውሮፓዊያን ጋር በፈጠረው ግንኙነት ዘመናዊ ገዳይ የጦር መሳሪያ ከመሸከሙ በስተቀር በወቅቱም ሆነ ቀጥሎ ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተሻለ የሚባል የአመራር ዕውቀትም ሆነ የሀብት ብቃት አልነበራቸውም፡፡ ይህንን በማጣቱ ደግሞ አንድነቱን የሚያጠናክር አንድ ማህበረ ኤኮኖሚ ሊገነባና የተፈለገውን የሀገረ መንግስት ግንባታ ሊያሳካ አልቻለም፡፡ ምንም ያህል የጦር መሳሪያ ብንጋጋ የሐበሾቹ የአእምሮም ሆነ የተፈጥሮ ሀብት ድህነታቸው ሕዝቦችን ሊያሰባስብ አልቻለም፡፡ በኢትዮጵያዊ አባባል ከሸፈጥና ተንኮል ፖለቲካቸው ተሻግሮ ለዕድገት ፈር ቀዳጅ ሆኖ ሕዝቦችን ማሰባሰብ የሚችል መርህ መፍጠር አልቻሉም፤ አሊያም የተወራሪውን ሕዝብ ጠቃሚ እሴቶችን አበልፅገዉ መጠቀም አልቻሉም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም ወራሪ ነፍጠኞችም ሆኑ ቀጣይ ትዉልዳቸው

የተወራረ ሕዝቦችን ማንነትና የማንነት መገለጫዎችን ዝቅ አድርገው በመመልከታቸው እንደለበጣ ወይም ለታይታ የሚነገረው ወንድማማችነት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የባንድራ ፍቅር የሚባለው ጠንክሮ ሊወጣ አልቻለም። እነዚህ ወራሪ ኃይሎች የሃይማኖት ሥፍራዎችን ሳይቀር በመቀማት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሥፍራ አድርገዋል። አዲስ አበባ አራዳ ጊዮርግስ አሁን ያለበት ቦታ የቱላማ ኦሮሞ የቱፋ ሙና ARADDAA ሲሆን፤ ዛሬ ቁሉቢ ገብርኤል ያለበት ቦታ ደግሞ የታዋቂዉ ቃሉ ሮባ ቁምቢ ማምለኪያ ሥፍራ ነበር። ሰለሞን ስዩም ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ ላይ እንደፃፈው “... የአንድነት ኃይሎች፤ የማንነት ጥያቄ ለሚያነሱ ቡድኖች የተለመደ ማሸማቀቂያ አድርገው የሚያቀርቡት ባህላዊ ማንነትን በዘረኝነት ለውጠው መተቸት ነው።” ብሏል። ይህ ብቻም አይደለም ሃይማኖትን በሚመለከት የአገሪቱ ግማሽ ሊሆን የሚችለውን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችን ከሰው ተራ እንዳይቆጠሩ ጭምር ያላቸውን ኃይል ተጠቅመው ሰርቷል። ራስ መኮንን “የሙስሊሙን መስጊድ አፍርሶ ቤተክርስቲያን ካልሰራሁ እምዬ ማርያም አትለመነኝ” ማለቱንና ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ደግሞ “እኔ በምኖርበት አገር እንዴት “አላሁ አክበር” ለማለት ደፈሩ?” ብለው እንደተገበዙ አህመዲን ጀበል ከላይ በተገለጸው መጽሐፉ ላይ ገልጿል። በአጭሩ፤ ሰው ያለውን የሚያጥላሉበትና የሚያሸማቅቁት የቀድሞዎቹም ሆኑ የዛሬው የአንድነት ኃይሎች ሰውን በቁሙ ከመግደል በመለስ እንዴት አድርገው የቀድሞውን ዓይነት የሀገረ መንግስት ግንባታን ለማስቀጠል እንደሚያስቡና አገራዊ አንድነትን እንደሚያልሙ፣ እንዲሁም የሕብረተሰቡን ትስስር እንደሚያጠናክሩ ግራ ይሆናል። ስለሆነም፤ አገራዊ አንድነትና የሕዝቦች ትስስር ታሪካዊ ከሚባለው መነሻም ሊገነባ ያልቻለና ለሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ግንባታም ሆነ ለኢትዮጵያዊያን ትስስር ብሎም ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ግንባታ ከባድ እንቅፋት ሊሆን ችሏል። ፕሮፌሰር ላጵሶ ጌታሁን ዴለቦ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገፅ 5 ላይ “... በበሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች አገርና ሕብረተሰብ ላይ የተመሰረተውና የሚመሰረተው አሃዳዊ የጭቆናና የብዝበዛ ኃይልና ሥርአት በአብዮታዊ

የሥልተ ምርትና የሥርአተ ማህበር እድገትና ለውጥ እስኪወገድ ድረስ የሕዝቡና የህብረተሰቡ ተዛማጅና ቀጣይ የሆነ የመሃይምነት፣ የረሃብ፣ የችግር፣ የችጋር፣ የመከራ፣ የአመፅ፣ የጦርነትና የሽብር ሕይወት፣ ባህልና ሥርአት የበለጠ እየሰፋ፣ እያደገና እየከፋ ይሄዳል” በማለት የፃፉት ታላቅ የማስጠንቀቂያና የማስተማሪያ ደወል ስለሆነ ለአሃዳዊያን ኃይሎች እንዲህ በቀላሉ ሊያደርጉት የሚፈልጉትን ማድረግ እንደማይቻላቸው ማስተዋል ነበረባቸው።

ሌላው ለኢትዮጵያ የሀገረ መንግስት ግንባታ ተግዳሮት የዘርና የዘረኝነት አናሳ ግንዛቤ ነው። በዓለም ላይ ዘረኝነት በስፋት የተንፀባረቀበት አገር ቢኖር አንዱ ደቡብ አፍሪካ ነው። ልብ ማለት የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር የቀድሞ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ አስቸጋሪ የነበረው ዘር ሳይሆን ዘረኝነት ነበር። እዚያ ልዩነቱ የተመሰረተው በነጭና ጥቁር ሕዝቦች መሀከል ብቻ ሳይሆን የነጩን የበላይነት እና የጥቁሩን የበታችነት በሚያሰፍነው ሥርአት ላይ ነው። እሱ ሥርአት ደግሞ አፓርታይድ (ዘረኝነት) ነው። የአፓርታይድ ሥርአት የሄርበርት ስፐንሰርን ሶሻል ዳርዊኒዝምን ማለትም ጥቁሮች የአእምሮ አስተሳሰባቸው ከነጮች ጋር እኩል አይሆንም፤ እንዲያውም ጥቁሮች የነጩን የአእምሮ ምርምር ውጤትን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው የሚለውን ንድፈ ሐሳብ ለመተግበር የተቀመረ ነው። አፓርታይድ ከተወገደ በኋላም የዕርቅ ኮሚሽን የሰራው ነገር ቢኖር በአፓርታይድ ሥርአት ውስጥ ጥቁሮችን ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ሁሉ የበደሉ ሁሉ በግልፅ ወጥተው ይቅርታ የጠየቁበትና ሥርአቱን መከታ አድርገው በደል የፈጸሙ ለፍርድ የቀረቡበት ሂደት ነው። አብዛኛው ሥራ የተከናወነው ግለሰቦችን ዒላማ አድርጎ ሳይሆን ሥርአትን አስመልክቶ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጉዳይ ግን ከጊዜ አንፃር ከደቡብ አፍሪካው ትንሽ ለየት ይላል። በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ወረራን ያካሄደው የምንሊክ አገዛዝ መሠረቱ የፊውዳል ሥርአት ነው። ያ የፊውዳል ሥርአት እንደሥርአት በ1967 ዓም ከመሬት አዋጅ ጋር ያከተመለት ስለሆነ ፀረ ብሔር ተኮር እንቅስቃሴ የያዙ አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦችን ይዞ ለመረበሽ ከሚያደርገው ብቅ ጥልቅ እንቅስቃሴ ውጭ እንደ ፖለቲካ

ሥርአት ራሱን መልሶ ለመገንባት ያለው ዕድል የመነመነ ነው። የፊውዳል ሥርአትን ተከትሎ የመጣውና የሶሻሊስት ሥርአትን ያነገበው ወታደራዊ አገዛዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ሙቷል ባይባልም በኢትዮጵያ ግን ከ1983 ወዲህ ያከተመለት ነው። በ1983 ሥልጣን የተቆናጠጠው ሕወሓት/ኢህአዴግ ደግሞ አንዴ የአልባኒያ ሶሻሊዝን፣ ሌላ ጊዜ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ መንግስት፣ አንዴ ነጭ ካፒታሊዝም ነኝ ሲል አንዱንም ሳይሆን መሸበት። ቢሆንም ግን ባዶ እጁን አልነበረም። የፊውዳል ሥርአት ቅሪተ ኃይሎችንና በፊውዳል ኢትዮጵያ ሥርአት ውስጥ ሰፊ መሠረት የጣለውን የብሔር ፖለቲካ ይዞ ብቅ ብሏል።

የብሔር ፖለቲካው ሦስት አቅጣጫዎችን ዒላማ ያደረገ ነው። አንደኛ በኢትዮጵያ ከ1957 ጀምሮ በነ ዋለልኝ መኮንን ሲቀነቀን የኖረውንና ከ1960ዎቹ ጀምሮ ደግሞ ቢያንስ ከአምስት በላይ ነፃ አውጪ ድርጅቶች የተቋቋሙለት፤ ከነሱ ውስጥም ኤርትራ ነፃነትን የተጎናፀፈችበት ክስተት ይዞ ያለ ነው። ሁለተኛዎቹ ደግሞ እኛ በቁም እያለን ኢትዮጵያዊ መባል እንጂ የብሔር ፖለቲካ እንዴት ይነሳል የሚሉ ኃይሎች ሲሆኑ፤ ሦስተኛዎቹ ደግሞ ብሔራቸውን መሠረት አድርገው በኢትዮጵያዊነቸው መኩራትን የሚከለክላቸው የለም የሚሉ ናቸው። በተለይ ሁለተኛዎቹ በብሔር ድርጅቶችና አባሎቻቸው ላይ ጫና ለመፍጠር ሲሉ ተራ ስድብ ሳይቀር ዘረኛ እያሉ ይሳደባሉ፤ የብሔር ድርጅቶችን ለማስወገድ የሃይማኖት ድርጅቶችን ጭምር በመጠቀም ግፊት ያደርጋሉ። ስትራቴጂያቸው ግን በፊውዳል ሥርአትና ወታደራዊ አገዛዝ ሥር የነበረውንና ለብሔር ብሔረሰቦች ባህል ደንታ ያልነበረውን አንድ አገር፣ አንድ ባንድራ፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ሃይማኖት የሚለውን የአሃዳዊነት አስተዳደርን መልሶ ሕዝብ ላይ ለመጫን እንደሆነ በግልፅ ይታይባቸዋል።

ይህም ሆኖ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይን ተከትሎ ያለው ችግር ድርጅቱ በሕገ መንግስት ደረጃ የቀረፀውን ብሔር ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ሥርአትንም ካለበት ጠባብ አመለካከት የተነሳ ከዳር ሊያደርስ አልቻለም። ለሄደበት የተወሰኑ እርምጃዎችም አንዳንዶች ፀረ አንድነት

ብለው ይፈርጁታል። ነገሩ የሕወሓት ፈተና የሚመነጨው ሲጀመር ትግራይን ብቻ ነፃ ለማውጣት መነሳቱና ይህ ደግሞ ከክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ማነስ አንፃር ትክክል እንዳልሆነ ሲገነዘብና በፈጣሪው ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ በተደረገበት ጫና ምክንያት የመጀመሪያ ስሙንና የትግራይ ሪፑብሊክ ምስረታ ሐሳቡን በማሻሻል ወይም በመቀየር ወደ መሀል አገር ሲንደረደር ጥንታዊ የዘር ቁርኝት ያላቸው ሐበሾች ተሸክመው ወደ መሀል ሀገር አስተላልፈውታል። ሕወሓት መሀል አገር ከገባ በኋላ ግን የሰራው ክፉ ሥራ ቢኖር በፌዴራል አስተዳደር ሥርአትም ቢሆን አገራዊ አንድነትን ሊያስቀጥሉ ወይም የአብሮነት ትስስሩን ሊያጠናክሩ የሚጠበቅበትን የመንግስት አደረጃጀቶችን የመከላከያ፣ የፖሊስ፣ የደህንነት፣ የፍትህ፣ በአጠቃላይ የመንግስት ሥራ ቤቶችን አፍርሶ በቦታቸውም የራሱን ኃይል በራሱ ቡድን ሰዎች መገንባቱ ነዉ።

ብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተሰባሰቡበትና ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገሮች ውስጥ የአንድ ቡድን ሰዎች የበላይነት አገራዊ አንድነትንም ሆነ ሀገረ መንግስትን ሊያስቀጥሉም ሆነ ሊያጠናክሩ አይችሉም። እዚህ ላይ ስለፈረሱት የመከላከያ፣ ደህንነትና ፖሊስ አስመልክቶ የነሱን ሕልውና ባሉበት ሁኔታ ጠብቆ በማቆየት ብሔራዊ ፌዴራሊዝሙን መገንባት ስለማይቻል መፍረሳቸው አግባብ እንደነበረ የሚከራከሩ ሊህቃን ቢኖሩም፤ እንደዚህ ፀሐፊ ግን መፍረሳቸው አንድ ነገር ሆኖ በቦታቸው የተገነቡትም ሕዝባዊ ወገናዊነትን ባለመላበሳቸው በሰፈሩት ቁና ተሰፍረው እራሳቸው የደርግ ባሉት መከላከያ፣ ፖሊስ፣ ደህንነት፣ ወዘተ እነሱም ገነባን ያሉት መከላከያ፣ ደህንነትና ፖሊስ የወያኔ ከመባል አላመለጡም፤ ወይም የኢትዮጵያ ሠራዊት መሆን አልቻሉም።

ከ2010 ዓል አጋማሽ በኋላ የኢህአዴግ ሕይወት ተሐድሶ በሚባል ፈሊጥ የተወጠረ ነበር። በኢህአዴግ የተሐድሶ ዘመን ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ተከናውነዋል። አንደኛው የኢህአዴግ ቁንጮ መሪ ድርጅት ሕወሓት ተሸንፎ ጠቅልሎ መቀሌ ገብቷል። መቀሌ መግባቱ ብቻ ሳይሆን ከአዲስ አበባው ቀሪ ኢህአዴግ ጋር ደግም ዳግም ላይገናኙ ያቆራረጠውን

የክልሉን ምክር ቤት አሰናብቶ ስድስተኛ ዙር ምርጫ በማካሄድ በአሮጌዎቹ የሕወሓት ቡድን አባላት ምትክ ነገር ፈለጋ በሚመስል መልኩ እነዚያኑ አሮጌ የሕወሓት ቡድን አባላትን መልሶ የትግራይ ክልል መንግስትን አቋቁሟል፡፡ ሲያካሂዱት የቆዩት የቃላት ጦርነትም ተለጥጦ ጦር እስከ ማማዘዝ ደርሷል፡፡ ቀሪዎቹ 3/4ኛው የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች (ኦህዴድ፣ ብአዴን፣ ደኢህዴን) ቀደም ሲል አጋዥ እየተባሉ በአጫፋርነት የነበሩትን የታዳጊ ክልሎች ፓርቲዎችን በመጨመር ብልፅግና ፓርቲን መስርተዋል፡፡ ግርምትን የሚፈጥር ነገር ቢኖር ግን መንግስቱ ኃይለማርያም ምንም ተቀናቃኝ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ በአሣር አንድ ፓርቲ ለማቋቋም ሁለት ዓመት የፈጀበትን ጊዜ በማሳጠር ተሃድሶውን ያጣደፈው የኢህአዴግ ፓርቲ አዴፓና ኦዴፓን ጨምሮ እስከ ብልፅግና ፓርቲ ድረስ ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አፍርሶና ብልፅግና የሚባለውን ፓርቲ ገንብቶ ተገኝቷል፡፡ መቀሌ የገባው ኢህአዴግ ቁጥር አንድ እና አዲስ አበባ ላይ የቀረው ኢህአዴግ ቁጥር ሁለት በጥቅምት ወር 2013 ዓም ብረት በመማዘዝ ስለተዋጉ የሆነ ተአምር ካልተፈጠረ በስተቀር ዳግም ላይገናኙ የሰው ሕይወት እንዲጠፋ አድርገዋል፡፡ በትግራይ እና ሌሎች አጎራባች ክልሎች ላይ በጣር የተገነቡ መሠረተ ልማቶችም ወድመዋል፡፡

እራሱን ብልፅግና ፓርቲ ብሎ አዲስ አበባ ላይ የቀረው ቁጥር ሁለት ኢህአዴግ ከስትራቴጂ አንፃር ቀደምቱን ሕወሓት/ኢህአዴግን ይመስላል፡፡ ይኼም ጠንካራ ተፎካካሪ የሚመስሉ ፓርቲዎችንና አባላቱን ባልተገባ ሁኔታ መግለፅ፣ ስም ማጥፋት እና መደምሰስ (define, defame and destroy) እርምጃዎችን ወስዶ ነፃና ዴሞክረራሲያዊ ምርጫ አካሂዳለሁ ይላል፡፡ ቀደምቱ ኢህአዴግ ተቃናቃኝ የሚመስሉትን ፓርቲዎች የአሸባሪነት ታፔላ እየለጠፈባቸው እስር ቤት እንዲገቡ፣ እንዲገደሉና እንዲሰደዱ ሲያደርግ እንደነበረ ሁሉ፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የሕወሓትን ወንበር የተረከበው የብልፅግና ፓርቲ ተቀናቃኝ የመሰሉትን ፓርቲዎችና ታዋቂ ግለሰቦችን ልዩ ልዩ ስም በመለጠፍና በሕግ ማስከበር ስም እስር ቤት እንዲታጎሩ አድርጓል፡፡ ለዚህ ነው የታክቲክ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር

ከስትራቴጂ አንፃር ብልፅግናና ሕወሓት ተመሳሳይነት አላቸው ለማለት የቻልኩት። ለዚህ ማሳያዬ ደግሞ ስም ለማጠልሸት ሳይሆን ብልፅግና ፓርቲ ራሱ "**ለውጡ ሪፎርም ነው ስንል ለውጡ ኢህአዴጋዊ፣ ሕገ መንግስታዊና ሕዝባዊ ሆኖ ሦስቱንም ዓላማዎች በጋራ የያዘና ያላንጠባጠበ መሆኑ መታወስ ይኖርበታል**" ሲል <u>ሀገራዊ የለውጥ እርምጃዎች፤ የለውጡ ምንነት፣ ስኬቶች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና መሻገሪያ ስልቶች</u> በሚል የካቲት 2012 ዓም ለአባላቱ በአወጣው መመሪያው ላይ ገልጧል። በአንክሮ መታየት ያለበት ነገር ቢኖር ኢህአዴጋዊነት ማለት አውራ ፓርቲነት፣ የአንድ ፓርቲ የበላይነት፣ ኢዴሞክራሲያዊነት፣ አምባገነንነት እና ሙሰኝነት የሆነዉን የብልፀግና ፓርቲ ሳያንጠባጥብ ይዞ መጓዙ ነዉ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ፤ የብልፅግና ፓርቲ መከሰት በተመሳሳይ ሁኔታ እንኳን ባይሆን ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደተባለው፤ የወታደራዊ ደርግ አነሳስ እና ሥልጣን መንጠቅና እዚያ ላይ መቆየትን ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝቦች 27 ዓመታትን ወስደው ሕወሓት/ኢህአዴግን ለመጣል ያደረጉትን የትግል እንቅስቃሴ በመጋቢት ወር 2010 ከዚያው ከኢህአዴግ መሀከል ብቅ ብሎ ሕዝባዊ ድሉን ነጠቀ። ልክ ደርግ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ስም እንዳደረገው ብልፅግናም በሽግግር ስም የ2013ቱን ምርጫ ለብቻው ተወዳድሮ ሥልጣን ላይ ሊቆይ ችሏል።

አንድ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነገር ይኖራል። እሱም ሕወሓት/ኢህአዴግ ከሃያ አምስት ዓመታት በላይ የውሸት ፓርቲዎችን ኢትዮጵያ ውስጥ አደራጅቶ የፖለቲካ ሙስናን እንደሰራ ሁሉ፤ በሚያስተዛዝብ መልኩ የብልፅግና ፓርቲም እነዚያን የውሸት ፓርቲዎችን ከሕወሓት ለመነጠል በሚመስል መልኩ በቀጥታ ወርሷቸው ሌላ የፖለቲካ ሙስና ሊፈጥር ስንቀሳቀስ ቆይቶ፤ ነገር ግን በምርጫ ቦርድ አማካይነት የተወሰኑትን ቢቀናንስም፤ ቀድሞ ሕወሓት ፓርቲም፣ መንግስትም፣ ሕዝብም ሆኖ ሲፈጥር የነበረውን ችግር የሕወሓትን ወንበር የተረከበው ብልፅግና ፓርቲም ተመሳሳዩን ነገር ለመድገም ሊገዳደሩኝ ይችላሉ የምላቸውን

ፓርቲዎች እንዳይኖሩ ለማድረግ መንገድ መንገዱን ይዟል።

በሌላም በኩል ለፌዴራሊዝም ግንባታውም ሆነ ለኢትዮጵያዊያን ትስስር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉና ትኩረት ሊነፈጋቸዉ የማይገቡ የኢትዮጵያዊያን ልዩነቶች ዛሬም ሳይቀር ብዙ ብዙ ቢሆኑም፤ ሕወሓትም ሆነ ብልፅግና ከጠባብ ዓላማቸው የተነሳ እንገዛለታለን ለሚሉት ሕገ መንግስታዊ ሥርአት፤ ማለትም ለሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ሊገዙ አልቻሉም። ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ ላይ የብልፅግና ፓርቲ እንደገለጸዉ "… እስካሁን ለብሔር ማንነት የሰጠነውን ትኩረት ያህል ለሀገራዊ ማንነት ባለመሰጠቱ _አደገኛ አስተሳሰቦች ተንሰራፍቶ ሀገሪቱን ወደ ትርምስና ከዚያም ላቅ ሲል የከፋ አደጋ ውስጥ ለመክተት እየተንደረደሩ እየተመለከትን ነው።_" በማለት (ሰረዝ የተጨመረ) ከሕገ መንግስቱ ማፈንገጣቸውን ገልጸዋል። በዚህም አንድ ብልፅግና ፓርቲ ሁለት እግሮች አሉኝ ብሎ ብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች በሚኖሩባት ኢትዮጵያ አገር ውስጥ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም አፍርሶ ሕብረ ብሔራዊ የሚመስል አሃዳዊነትን ለመገንባት ሲንደርደር ይታያል። ከዚህ መንደርደሩም ሆነ ሰላሳ ዓመታትን ወደ ኋላ ተመልሰን ከታሪክ የምንረዳው ነገር ቢኖር አፄ ኃይሌ ሥላሴ የኢትዮጵያን አንድነት ለማጠናክር ብሎ የኤርትራ ፌዴሬሽንን በማጠፉ ከሰላሳ ዓመታት አውዳሚ ጦርነት በኋላ በኤርትራ ነፃነት መታወጅ እንደተደመደመ ሁሉ፤ የወቅቱን የኢትዮጵያ ሕብረ ብሔራዊ ፌዴሬሽንን ማጠፍም ሆነ ትኩረት መንሳት ተመሳሳይ ችግር ላያስከትል እራሱ የብልፅግና ፓርቲም ሆነ የሚወግኑት ኃይሎች ለባለብዙ ብሔርና ብሔረሰብ አገራችን የሚሰጡት ተቻችሎ የመዝለቅ ዋስትና ስለመኖሩ ባይታወቅም፤ የስም ለውጥ የተደረገበት የተለመደ የጉልበት (de facto) መንግስት ለመቀጠላቸው እንጂ ተቀባይነት ስለማግኘቱ ግን አፍ ሞልቶ ደፍሮ የሚናገር የለም። ጆርጅ አንደርሰን፤ የፌዴራል መንግስት አወቃቀር መነሻ ነጥቦች በማለት የፃፈውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፌዴረሽን ምክር ቤት ለአምስተኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን (1995) መወያያ ጽሑፍ ውስጥ _መቻቻልና የፌዴራል ስርአት ግንባታ_

በሚል አርእስት ሥር የብሔረሰብ ብዝሃነትን እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል እንደሚከተለው ተገልጿል። "የብሔረሰብ ብዙህነት ባለባቸው ህብረተሰብ ውስጥ፤ የመቻቻልና የመፈቃቀድ ፖለቲካዊ ባህል ያስፈልጋል። ብሔረሰብ፣ ቋንቋ ወይም ሃይማኖትን የተከተለ አከላለል ባለባቸው ፌዴሬሽኖች ውስጥ ብዙህነትን በተመለከተ የመቻቻል ባህል ብቻ ሳይሆን ከዚያም አልፎ ብዙህነትን እንደ አገር መገለጫና እንደ እሴት ሰጪ በዝግጁነት የሚያቅፍ ባህል ሲኖር መረጋጋትን ማጠናከር ይቻላል።" በማለት አስቀምጧል። ችግሩ የኢህአዴጉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ይህንን ብሎ ይፃፍ እንጂ ሳይተገብረው በመቅረቱ ከሰባት ዓመታት በኋላ ተመሳሳይ አደጋ ላይ መዉደቁ አልቀረም።

## ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (ቅንጅት)

ማንም ሰው ስለኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሲናገር ወይም ሲጽፍ የ1997ቱን ሦስተኛ ጠቅላላ ምርጫና የቅንጅትን ሚና መዝለል አይችልም። ቅንጅት የቀስተ ዳመና፣ የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፣ የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኢዴአፓ-መድህን)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራትክ ሊግ (ኢዴሊ) ድርጅቶች ጥምረት ነበር። ቅንጅትን ለመመስረት ገፊ ምክንያቶች ሁለት እንደሚሆኑ ሲገመት፤ አንደኛው የሕወሓት/ኢህአዴግ የአገሪቱን መንግስት ቋንቋን መሠረት ያደረገዉን ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም የአገሪቱን አንድነት ይበታትናል በማለት የቅንጅት መስራች ፓርቲዎች ከአደረባቸው ሥጋት የተነሳና ይህንኑ ለመቋቋም ታስቦ የተመሰረተ ስብስብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በብሔራዊ ሎቴሪ አዳራሽ ውስጥ የአካዳሚ ነፃነት ብለው ካደረጉት ስብሰባ በኋላ ያጋጠማቸው እስር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን አገናኝቶ፤ እነሱም ባደረጉት የሐሳብ ልውውጥ የቅንጅት ጥንስስን ሳይጥሉ አልቀረም። በዋናነት የቅንጅቱ አባል ፓርቲዎች የተሰባሰቡት የ1997ቱን ምርጫን ለማሸነፍና የጥንት አባቶቻቸውን አሃዳዊ መንግስትን መልሶ ለማቆም ነበር። የመመስረታቸውም መመዘኛዎች አንደኛ ዘውግ ዘለልና ዜጋ ተኮር

መሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ የቅንጅቱ አባል የሚሆነው በአገሪቱ ሕግ መሰረት ምርጫ ቦርድ ዘንድ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ መሆን እንዳለበት ስምምነት ነበራቸው። ቅንጅቱም ጥቅምት 22/1997 ሁሉም አባል ፓርቲዎች ካሉባቸው ችግሮች ጋር፤ ለማሳያም ኢዴፓ-መድህን ገና ዉህደታቸዉን ሳያጣጥሙ ሕልው ሆነ።

ቅንጅት የፖለቲካ ፕሮግራም፣ የመተዳደሪያ ደንብና የዲስፒልን እርምጃ አወሳሰድ ሰነዶችን አጸድቆና የአመራር አባላትን መርጦ ወደ አጠቃላይ ስምምነትም ሆነ ወደ ምርጫ ዘመቻ የገባ ቢሆንም በኢዴፓ-መድህንና በኢዴአፓ መሀከል በተፈጠረ አለመተማመንና በአንዳንድ ግለሰቦች የሥልጣን ሽሚያ ምክንያት ገና ከጅምሩ ከመናቆርና ከመጠላለፍ እንዳላመለጡ የተተው ሰነዶች ይከስታሉ። ለመናቆራቸውና ለመጠላለፋቸው መንስኤ ይሆናል ከሚባሉት ጉዳዮችም ቅንጅት የተለያዩ ሥርአት ሰዎች የተሰባሰቡበት ስብስብ ስለነበረ እንደሆነ ከግምት በላይ ይነገራል። ከመሪዎቻቸው አንዳንዶቹ ከኃይሌ ሥላሴ የፊውዳል ሥርአት ጋር የተጋመዱ (ኢንጂኒየር ኃይሉ እና ፕሮፌሰር መስፍን)፣ አንዳንዶች ደግሞ በደርግ አገዛዝ ዘመን ከነበሩ የፖለቲካ ቡድኖች በተለይም ሁሉም ነገር ወዲያው ተፈጭቶ ወዲያው ተቦክቶ ወዲያው የሚጋገርና የሚበላ አድርገው የሚያስቡ፤ በከተማ ነውጠኝነታቸው የሚታወቁ የኢህአፓ ግርፎች (ዶክተር ብርሃኑ) የነበሩበትና ሦስተኛዎቹ ደግሞ በሕዝብና በዴሞክራሲ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ስብስቡ ስለተነጋገረበት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ የስብስቡ አባል የተነፈሰውን ወስደው ለወያኔ ሰዎች የሚያቀብሉና ላቀበሉት የወንድማቸው ምስጢር ደግሞ ረብጣ ክፍያና የመሳሪያ ትጥቅ የሚቀበሉ (ልደቱ አያሌው፣ አብዱራህማን፣ የመሳሰሉ) የፖለቲካ ነጋዴዎች ነበሩበት። በመሆኑም ቅንጅቶች ገና ወደ ምርጫ ሲገቡም አንድ የመሆን ሂደታቸው ገና ያላለቀለት ነበር።

ከብዙ ድክመቶቹ ጋርም ቢሆን ኦነግ በ1983/84 በኦሮሞ ብሔር አባላት ውስጥ ካስከሰተው ሕዝባዊ መነሳሳት ሌላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ትልቅ የሚባል የፖለቲካ መነሳሳትን፤ እንዲያውም በተሻለ ሁኔታ

ሕዝብ ለመብቱ መታገል እንዳለበት ያስገነዘበ ስብስብ ቢኖር ቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ግንባር ቀደም ነበር ማለት ይቻላል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ደግሞ ወያኔን የሚገዳደር ማንኛውንም ድርጅት ለመምረጥ ሕዝቡ የተነሳበት ጊዜና ቅንጅትም በበኩሉ የወያኔን የዴሞክራሲ ጭምብል አስወልቆ ድብቅ አምባገነናዊ ገጽታውን ፍንትው አድርጎ ለሕዝቡ ያሳየ ስብስብ ነው ቢባል ዕውነቱን መግለፅ እንጂ ማጋነን አይሆንም።

ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ የውስጥ ፓርቲ ጥንካሬ ላይ ሰፊ ጊዜ ተወስዶ ብዙ ሥራ ሳይሰራ በፊት የወያኔ ወሬ አቀባዮች የሚባሉት ፓርላማ መግባት ወይም አለመግባት በሚለው አታካሮ መሀከል አሸናፊ ሆነው በመውጣት፤ ፓርላማ አንገባም ያሉት አለመግባታቸው ብቻ ሳይሆን ጠንካራና ሕዝባዊ ተደማጭነት ያላቸው የቅንጅት አባላትን ወያኔ ስብስቦ እስር ቤት እንዲታጎሩ አድርገዋል። ይህ ወሰንየለሽ አምባገነናዊ እርምጃ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ፍላጎት ማቆጥቆጥን ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ያመከነ ነበር። ከዚህ ጋር መታየት ያለበት ነገር ቢኖር ቅንጅት እንዲያ ገንኖ ሊወጣ የቻለው በኢህአዴግ በተለይም በቁንጮ መሪው መለስ ዜናዊ በኩል በምዕራባዊያን ዕርዳታ ሰጪ አገሮች ዘንድ ዴሞክራት ሆኖ ለመታየት እና ማንም ምንም አያደርገኝም በሚል የተሳሳተ ስለት የፖለቲካ ምህዳሩን ገርበብ አድርጎ በመክፈቱ ነው።

የታሰሩት የቅንጅት አባላት በድርድርም ሆነ በክርክር ከተፈቱ በኋላ አቅምና ስልቱን ያላቸው ወደ ውጭ አገሮች በተለይም ወደ አሜሪካ አቀኑ። ኢዴፓ እና አባላቱን የመሳሰሉ አገር ውስጥ የቀሩና ቀድሞውንም ቢሆን የስብስቡን ጉዞ ለወያኔ በማቀበልና በማሰናከል ይጠረጠሩ የነበሩት ቅንጅትን ወደ ጎን ብለው በፓርቲያቸው ስም የፓርላማ ወንበር ይዘው ቀጠሉ። <u>የነፃነት ጎህ ሲቀድ</u> ብሎ የፃፈው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ፓርላማ የገባዉን የኢዴፓን አመራር በተለይም የአቶ ልዴቱ አያሌውን ባህርይ ሲገልፅ "ልደቱ ከወጣትነት ግፊት በላይ በጣም አደገኛ አስተሳሰብ ይዞ ይራመዳል" ካለ በኋላ በማከልም "የልደቱ የሎጂክ ስህተት የሚመነጨው

አንድ እርምጃ በመቃወም እንጂ አማራጭን በግልፅ አውቆ መፍትኼ አያመላክትም" በማለት ይኮንናል።

ይህ በዚህ እንዳለ ወደ ውጭ ያቀኑት የቅንጅት አባላት በዚያው ሆነው ግንቦት ሰባት የተባለውን የፖለቲካ ማህበር መሰረቱ። ከተግባራዊ እንቅስቃሴ ይልቅ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ሽፋን የነበረው ግንቦት ሰባት ሕልውናውን በገንጣይነት ከሚከሰው የኢሳያስ አፈወርቂ አገር ኤርትራ ውስጥ በማድረግ የወያኔን መንግስት በትጥቅ ለመፋለም ወታደራዊ ዝግጅት ያድርግ ነበር። ቆይቶ ሊታወቅ የቻለው ግን ግንቦት ሰባት ኤርትራ ውስጥ በስም እንጂ በሥራው ምንም እንቅስቃሴ ካልነበረውና መሰረቱን ጎንደርና ኤርትራ መሀከል አደረገ ከሚባል አርበኞች ግንባር ከሚባል ሌላ ድርጅት ጋር አርበኞች ግንቦት ሰባት የሚባል ግንባር መስርቷል። ወደኋላ መልሰው ሲያስቡት ግንቦት ሰባትም ሆነ አርበኞች ግንባርና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ቆይታቸውን ኤርትራ ውስጥ ያድርጉ እንጂ፤ እነሱም በተራቸው ኤርትራን የፖለቲካ ነፃነት በማጎናጸፍ ለኤኮኖሚው ሲባል ደግሞ ኢትዮጵያን ተስፋ ባደረገው፤ ለዚህ ዓላማው ስኬት ደግሞ ከጅምሩ የወያኔን የመገንጠል ዓላማ ሳይቀር ያስጣለው የኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ምርኮኛ ከመሆን አላመለጡም። የወያኔና የሻዕቢያ ድብቅ ዓላማም ቀስ በቀስ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ዋና ፀሐፊን የመን አገር ውስጥ አስጠልፎ ማሳሰርና የአርበኞች ግንባር ሰባት የተባለውና በውስጥ አርበኝነት ሲያገለግል የነበረው ክንፍ ተልዕኮውን ሲያገባድድ ሾልኮ አዲስ አበባ መግባት ጋር ተጠናቋል። በ2010 ዓም በኢህአዴግ ውስጥ በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ምክንያት ከሕወሓት ስልታዊ ወደ መቀሌ ማፈግፈግን ተከትሎ ግንቦት ሰባትም ሆነ ሌሎች ኤርትራ የነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የ1997ቱ ቅንጅት ቅሪትና (ኢዴፓን ሳይጨምር) ከኤርትራ የተመለሰው ግንቦት ሰባት አገር ውስጥ ከቆየው ሰማያዊ ፓርቲ ጋር በመቀላቀል የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሚባል ፓርቲ መስርተዋል ወይም ተቀላቅለዋል። ኢዜማ በፖለቲካ አቋሙ ከአዲስ አበባ ቀሪ የኢህአዴግ ጋር እየተሞዳሞደ አማካይ ሥፍራን የያዘ ቢመስልም፤ በቋንቋ ላይ

ከተመሰረተ ፌዴራላዊ የአስተዳደር ሥርአት ይልቅ የዜግነት ፖለቲካ በማለት ከ1983 በፊት የነበረውን አሃዳዊ ሥርአትን ለማስፈን ወይም ጂኦግራፊያዊ ፌዴራሊዝምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚንቀሳቀስና ከአመለካከት አንፃር ደግሞ  ወደ ቀኝ የሚያጋድል ይመስላል። ይህ አቋሙ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕልውና ጭምር ፈታኝ የሆነውን የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄን  በሁሉም ዘንድ ባይሆን በአብዛኛው ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ በተለይም በኢትዮጵያ ፖለቲካም ሆነ ኤኮኖሚ ውስጥ መሀከለኛ ሥፍራን ይዞ ባለውና ማግለል በማይቻለውና ማግለል ቢሞከር እንኳን አደጋን በሚያስከትለው የኦሮሞ ኢሊቶች ዘንድ አልተወደደለትም። ምክንያቱ ደግሞ ከፓርቲ ዓላማና ስብስብ በላይ ነባራዊ ሁኔታዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉና ነው። ለማንኛውም ግን ኢዜማ በከተሞች አከባቢ በሚያደርገው ሰፊ እንቅስቃሴ የቀድሞውን የኢህአፓን ዓላማ ያነገበ ይመስላል። ዉሎ አድሮ ግን የአዉራ ፓርቲነት ስሜት ከተጠናወተዉ የብልፅግና ፓርቲ እና ከከሃዲ አመራሮቹ ሊያመልጥ ባለመቻሉ የመበታተን አደጋ ተጋርጦበታል።

በቅንጅት መነሳትና መውደቅ ትርኢት ውስጥ በጣም አስደናቂ ነው ከሚባለው ሤራ ውስጥ፤ ቅንጅት እንደ የብዙ ፓርቲዎች ስብስብ ዳግም እንዳይነሳ ተደርጎ ከመበተኑም በላይ፤ ስብስቡ ራሱ እንደ አንድ ድርጅት ተቆጥሮ የቅንጅት ስምና ፈቃድ አየለ ጫሚሶ ለሚባል ግለሰብ በችሮታ መሰጠቱ ነው። ግለሰቡም ቢያንስ ለአስራ አራት ዓመታት ወያኔንና የግፍ አገዛዙን ሲያሞካሽና በታዋቂ ፖለቲከኞች ላይ ሞትን ሲጠይቅ ቆይቶ ወያኔ ከመንበሩ ሲወርድ በወያኔ ወንበር ተረካቢዎች ወደ ውጪ አገር መሸኘቱ የኢትዮጵያን ፓርቲ ፖለቲካ ከአገር ግንባታ ሕዝብ ብልፅግና ጋር አለመታየቱ ነዉ። አንድ ሊዘነጋ የማይገባ ነገር ቢኖር ግን የቅንጅት አመራር እስከ ታሰሩበት ጊዜ ድረስ የዴሞክራሲ ጥያቄን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ለማሰረፅ ያንቀሳቀሱ ስብስቦች እንደነበሩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ የማይዘነጋቸው ናቸዉ።

## ቀለም አልባው ሽብር

ኢትዮጵያ ውስጥ ለመድረሱ ወይም ላለመድረሱ ምንም ዓይነት ጥናት ላይ የተመሰረተ ማረጋገጫ ሳይኖር ኢህአዴግ ፀረ ሽብር ሕግ አወጥቷል። አዋጁ በአገራችን የፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለዉ በተለይ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ድርጅቶችና ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጎራ የተሰለፉ ዜጎች አምርረዉ የሚቃወሙት ስለሆነ ይህንኑ ጉዳይ በዚህ ምዕራፍ ሦስት ሥር ቀለም አልባው ሽብር ብሎ ንኡስ አርእስት ሰጥቶ ማየት ይጠቅማል።

በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ በመኢሶን እና በኢሕአፓ አማካይነት የተወሰዱ እርምጃዎች ቀይና ነጭ ሽብሮች ተብለዉ የሚታወቁት አደጋዎች ለይቶ ከደረሰባቸዉ ኢትዮጵያዊያን እናቶችን፣ አባቶችን፣ እህቶችና ወንድሞችን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ወገኖችን ያሸበረና ያሳዘነ ነበር። በዚያ ሽብር አገራችን ምትክ ያልተገኘላቸዉን ዜጎችን አጥታ የትዉልድ ክፍተት (generation gap) የፈጠረ ነው። እንደዚህ ተሰይሞ እንኳን ባይሆን ከቀደምት መሪዎች ወይም መንግስታት ጀምሮ ኢትዮጵያ ከመሪቿ በሚሰነዘር የሽብር ድርጊት የተላቀቀችበት ጊዜ አንድም በጣም ትንሽ ጊዜ ነዉ ወይም አልነበረም።

ከቀለም አልባው ጋር የምንመለከተው ሁለተኛዉና ወቅታዊዉ ሽብር ዓለም- አቀፍ ሽብርተኛነት ነዉ። ይህ ሽብር የተለያዩ ሰዎች ከተለያዩ ነገሮች ጋር፤ ለምሳሌ የሕዝብን ሠላማዊ ሕይወት ማናጋት፣ ሲቪል ዜጎችን መያዣ አድርጎ መንግስትን ማስገደድ፣ በሃይማኖት በመደራጀትና ማሸበር፣ የግለሰቦች ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ ሥልጣን መያዝና ሥልጣን ላይ መቆየት፣ ቡድኖችና ፓርቲዎች፣ በአጠቃላይ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸዉ ሰዎች የሚፈጽሙት ድርጊት እንደሆነ ትርጉም ይሰጠዋል። ዓለም-አቀፉ ሽብርተኛነት ዴሞክራሲያን የሚባሉ አገሮች ላይ የጣለዉን ስጋት ያህል ባይሆንም፤ ኢትዮጵያም የዓለም-አቀፉ ሥርአት አካል ስለሆነች በዲሞክራሲያን አገሮች ላይ ያነጣጠረው ስጋት

ኢትዮጵያንም ሳያሳስባት አልቀረም።

መንግስታት ከደረሰባቸዉ አደጋ ወይም ይደርስብናል ብለዉ ከሚገምቱት ሥጋት አንፃር አሸባሪዎች ናቸው የሚሏቸውን እንደሚሰይሙ ጥቅል የሆነ ግንዛቤ ይኖራል። የየትኛዉ ወገን ቀድሞ ተቀባይነት እንዳለዉ መስማማቱ አስቸጋሪ ቢሆንም መንትዬ ሕንፃዎቿን ዶግ አመድ ያደረገባትን ቡድን አሜሪካ አሸባሪ ነዉ ብላዋለች። ፈረንሳይ ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅትና ጋዜጠኞችን፣ ዘገይቶ ደግሞ በመዝናናት ላይ የነበሩ ዜጎቿን የቀጠፉባትን ኃይል አሸባሪዎች ናቸዉ ብላለች። እንግሊዝ በምድር ባቡር መጓጓዣዋ ላይ አደጋ አድርሰዉ የዜጓቹዋን ሕይወት የቀጠፉባትን አሸባሪዎች ናቸዉ ብላቸዋለች። እስራኤል ደግሞ ለፓለስታይን ነፃ መንግስት መመስረት የሚታገሉትን አማፅያን አሸባሪዎች ናቸዉ ትላቸዋለች። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የአፍሪካም ሆነ የሌሎች አህጉር መንግስታት የዲሞክራሲ ምህዳር ጠበበ፣ ሕዝባችን በገዥ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች መንግስታት ሥር አፈናና ጭቆና ደረሰባቸው ብለዉ ነፍጥ ያነሱትንና “ነፃነት ወይም ሞት” ብለው ዱር ቤቱ ያሉትን አሸባሪዎች ናቸዉ ብለዉ ፈርጅዋል። ለመጨበጥ ከሚያስቸግሩ ሥራዎች ውስጥ በአንዳንድ አገሮችና መንግስታት ዘንድ አሸባሪዎች ናቸዉ ተብለዉ የሚፈረጁት ቡድኖች በሌሎች አገሮች ጽህፈት ቤት ከፍተዉ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፤ ድጋፍም ይደረግላቸዋል።

ምንም እንኳን በሽብርተኝነትና አሸባሪነት ላይ በሁሉም ምሁራንና መንግስታት ዘንድ ወጥ እና አንድ ዓይነት ትርጉምና ግንዛቤ እንደሌለ ቢነገርም፤ አብዛኛዎቹ መንግስታት ለማለት ይቻላል ሽብርተኝነት ስልታዊ ማሳደድና ማስገደድ መሆኑን ይስማሙበታል። **ሽብርተኝነት በሲቪል ዜጎች ላይ ፍርሃትን በመንዛትና በመንግስት ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ዓላማቸዉን ለመጫን የሚሹ ኃይሎች የሚያደርሱት ዓይነት ስጋትና ጥቃት መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል**። ይህ ትርጉም ቢኖርም ከላይ የተጠቀሰውን በዜጎች ላይ የሚፈጽሙት በቡድን የተደራጁ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሥልጣን ይዘው

ጭቆናና አፈና በሚፈጽም መንግስታትም የሚከናወን ጭምር ነዉ። ምክንያቱም፤ እነሱ መንግስታት የሥልጣን ዕድሜያቸዉን ለማራዘም ሲሉ ሕዝብ መሆን የማይፈልገዉን ወይም የማይገባዉን እንዲሆን ሕገ መንግስታዊ መብቶችን እስከ መርገጥ ወይም ሕገ መንግስቱን ለነሱ የሥልጣን ዕድሜ መራዘም እስከ መቀየር የሚደርሱ መንግስታት ናቸው።

በሥልጣን ተቀናቃኝነትም ሆነ በሽብርተኝነት ወይም ምንነቱ ተለይቶ ባልታወቀ የፖለቲካ አቋም ሰበብ አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን ሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲባል፤ ገብቷቸውም ሆነ ሳይገባቸው ኢትዮጵያዊያን ሲገዳደሉ ማየት የተለመደ  ነው። ለምሳሌ ከስም በስተቀር የቅንጅትን አቋም ምኑንም ያልወረሰው አየለ ጫሚሶ የሚባለው ግለሰብ እንዲሁም ምንም ደጋፊ አባላት ወይም ማህበራዊ መሠረት ሳይኖረው ዝም ብሎ በገዥው ፓርቲ ሕወሓት/ኢህአዴግ ዘንድ ርካሽ ተወዳጅነትን ለማትረፍ ሲል ብቻ መልካም ዝናና ስብኢና ያላቸውን የፖለቲካ ሰዎች አሸባሪዎች ናቸዉ በማለት እንዲገደሉ ደብዳቤ ጽፎና ፈርሞ ጠይቋል። በማንም ይካሄድ በምንም ሽብርተኝነት ፖለቲካዊ ግብን ወይም ግለሰባዊና ቡድናዊ ጥቅምን ለማሳካት በሕዝብና በሕዝብ ሀብት ላይ የሚወሰድ ሕገወጥ እርምጃ ነዉ። ሙሰኝነት፣ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ዜጎችን ማስፈራራት፣ የሕዝብን መሠረተ ልማት ማፈራረስ፣ በግል፣ በቡድንና በተደራጀ ሁኔታም ይሁን በሌላ ተነሳስቶ ሕዝብ ላይ እየተኮሱ ጅምላ ግድያ መፈጸም፤ ደረጃቸዉ ይለያያል ካልተባለ በስተቀር አሸባሪነት ነዉ። አሸባሪነት በሁለት መንገድ የሚፈጸም ሲሆን፤ አንዱ በራሳቸዉ መንገድ የሚደራጁ ቡድን ወይም ቡድኖች ሲሆኑ፤ ሁለተኛዉ ደግሞ ኢዲሞክራሲያዊ በሆነ አካሄድ ሥልጣን የሚይዝና ከሕዝብ ፈቃድ ዉጭ ሥልጣን ላይ የሚቆይና የራሱን ዜጎች የሚያሸብር መንግስት ነዉ።

አገሮች ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ሲሉ ሕግ ያወጣሉ። የኢትዮጵያ መንግስት ግን የሕወሓትን የበላይነት አንቀበልም ያሉትን ግንቦት

ሰባትን፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርንና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስቀርቦ በአሸባሪነት አስፈርጇል። በተጨማሪም ሽብርተኝነትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ለማምከን በቂ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለማሰባሰብና ለማጠናከር፣ በሽብር የተጠረጠሩ ሰዎችን ወይም ድርጅቶችን ለሕግ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተጠናከሩ የምርመራና ክስ የማቅረብ አዳዲስ ስልቶችንና ስርአቶችን መዘርጋቱ አስፈላጊ በመሆኑ ብሎ ኢህአዴግ አዋጅ ቁጥር 652/2001 ቢያወጣም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ በበኩላቸዉ አባሎቻቸዉን ለመጉዳት ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ሥርአት አገሪቱ ዉስጥ እንዳያድግ ሆን ተብሎ በመንግስት የተጠነሰሰ ሴራ አድርገዉ ያማርራሉ። የሥጋት ምንጭ ከሚባለዉ የአዋጁ አንቀጽም “የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈፀሙ ወይም እየተፈፀመ ያለ ስለመሆኑ በሚገባ የሚጠረጠረዉን ማንኛዉንም ሰዉ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፖሊስ ለመያዝ” መቻሉና እስከ አራት ወራት ድረስ ቀጠሮ እየተጠየቀበት፤ ገደብ የለሽ እንግሊት እየተፈጸመባቸዉ እስር ሥር ማቆየት መቻሉ አስፈሪም ሆነ አሳሳቢ መንግስታዊ ሽብር መሆኑ ነዉ።

ይህንን የፀረ ሽብር አዋጅ በተለይ ራሳቸዉን ችለዉ የተቋቋሙ ፓርቲዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት የጥቃት ዒላማ የሚያደርግ ስለሆነ እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እስከመጠየቅ ደርሰዋል። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት የሚቀርብበትን ትችት ለመከላከል ፀረ ሽብር ሕጉ ከምዕራባዊያን መንግስታት ሕግጋት ጋር ተመሳሳይነት አለዉ ብሎ ቢከላከልም፤ ሕጉ የደቡብ አፍሪካ ነጮ ዘረኛ መንግስት (ተጨማሪ አንድ ወር የእስር ጊዜን ጨምሮ) የጥቁሮችን የነፃነት ትግል ለማፈን ከአወጣዉ ሕግ ጋር ንክኪ እንዳለዉ በግልፅ ይታያል። የኒልሰን ማንዴላ Long Walk to Freedom, 1994 በታተመው መጽሐፍ ገፅ 402 ላይ እንደተጠቀሰዉ በሜይ 1963 የወጣዉ *“The General Law Amendment Act, better known as the ninety-day detention laws waved the right of habeas corpus and empowered any police officer to detain any person*

*without a warrant on ground of suspicion of a political crime. Those arrested could be detained without trial, charge, access to a lawyer or protection against self incrimination for up to ninety days. The ninety day detention can be extended until this side of eternity."* ይላል። ይህንን ነው የኢህአዴግ መንግስት የሽብር ሕጉ ከምዕራባዊያን የተቀዳ ነው የሚለው።

ዘረኛዉ የነጮች መንግስት ያንን አፋኝ ድንጋጌ ያደረገዉ ለደቡብ አፍሪካ ዲሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብት መጠበቅ፣ እኩልነትና ነፃነት ለማስፈን፣ ፍትሓዊ ብልፅግና ለማጎናጸፍ ሳይሆን ለነዚሁ የሚታገሉ ድርጅቶችን ለመጨን ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ ዛሬ በሥልጣን ላይ የሚገኘዉን ኤኤንሲን ለመደፍጠጥ ያለመ ነበር። ሕገ ወጥ ጫና ለማሳረፍ የሚወጡ ሕጎችና የሚወሰዱ ዕርምጃዎች በኢትዮጵያም ቀለም አልባው ሽብር ሁለትን ሊያስከትል ይችላል ብሎ የሚናገር ወይም የሚጽፍ ወይም ስጋቱን የሚገልፅ ሰዉ ካለ እሱ ሰው የሌለ ፍርሃት ለመቀስቀስ ሳይሆን ለፓርቲ ፖለቲካ ኢትዮጵያ ዉስጥ መጎልበት ደንቃራ እንደሚሆን ከጥርጣሬ የዘለለ ክስተት መኖሩን ለመግለፅ እንደሆነ በወጉ መረዳት ያስፈልጋል።

ቀለም አልባም ሆነ ባለቀለም ሽብር በኢትዮጵያ እንዳይከሰት ለመግታት የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል። የሰማዕታት ሐውልት አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዳይደገም ብሎ ሰቅሎ ያልተተገበረዉን መፈክር ሳይጨምር፤ አንደኛ (እንዳያማ ጥራዉ እንዳይበላ ግፋዉ ዓይነት ከመሆን ያልዘለለ ቢሆንም) በሕገ መንግስታዊ አግባብ ተወዳድረዉና ተመርጠዉ ሥልጣን መያዝ የሚችሉ ፓርቲን ማቋቋም እንደሚቻል በመንግስት በኩልም አዋጅ ቁጥር 573/2000 ወጥቷል። የዚህ አዋጅ መግቢያ እንደሚያወሳዉ "በሕገመንግስቱ መሠረት ዜጎች የመደራጀት መብታቸዉን ተጠቅመዉ በሰላማዊና ሕጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የፖለቲካ ሥልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ" ካለ በኋላ በአዋጁ አንቀጽ 4(1) "ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ

የማቋቋም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለዉ” ይላል፡፡ እንግዲህ በዚህ አዋጅ መሠረት በሰላማዊና ሕጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሕግ ከተደነገገና ኢትዮጵያዊያን ፓርቲ ማቋቋም ወይም አባል መሆን መብት ካላቸዉ የሚሸበሩበትም ሆነ የሚያሸብሩበት አንዳች ምክንያት የለባቸዉም፡፡ ሁለተኛዉ ፓርቲ በማቋቋም ብቻ ሳያበቃ የሚያምኑበትን ፖሊሲ በመቅረጽ በዜጎች በኩል ደግሞ ሰላማዊ ትግል የሚያደርጉ ሕጋዊ ፓርቲዎች ተቋቁመዉ ሕዝብን ከጎናቸዉ ማሰለፍ ችለዉ እንደነበረና ቅንጅት፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዲን) እና የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) የ1997 ምርጫ ገብተው በመወዳደር የምክር ቤት ወንበር እስከመያዝ ደርሰዋል፡፡ አዋጁም ኖሮ ፓርቲዎችም ተደራጅተው፤ የአንድ ፓርቲ የበላይነት ለዚያዉም ደግሞ አናሳ ቁጥር ካለዉ ሕዝብ የሚፈጠር ፓርቲ የአዉራ ፓርቲ ስሜት በገነነበት አገር ዉስጥ በርግጠኛነት ሠላማዊ ትግል ማካሄድ ይቻላል ወይ? ብለዉ የሚጠይቁ ዜጎች ቀላል ቁጥር የላቸዉም፡፡

ግለሰቦችና ቡድኖች በተለይ ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ ሥልጣን ከያዙበት ዕለት ጀምሮ ሲፈክሩበት የኖሩትን ሕዝባዊ ዓላማ መርሳት ብቻ ሳይሆን፤ እነሱ ከሌሉ ምድር የሚገለበጥና ሰማይ የሚደፋ የሚመስላቸዉ ስግብግብ ፖለቲከኞች ባሉበት ዓለም ዉስጥ፤ በተለይም የፈለገ የሰው ሕይወት ጠፍቶ ሥልጣን ላይ ለመውጣትና ለመቆየት የሚንቀሳቀስ አገር ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ለመሆኑ በሕጋዊ መንገድ ፓርቲ መመስረት ከየት የተገኘ ፈሊጥና ድፍረት ነዉ ብለዉ የሚጠይቁም አሉ፡፡ በፖሊቲካ መስመር ልዩነት ብቻ ሕወሓት/ኢህአዴግ በሚያራምደዉ የጠላትነት ስሜት ዓይነት ሁኔታስ በሠላማዊ መንገድ ታግሎ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት መገንባትም ሆነ ለሥልጣን መብቃትስ ይቻል ይሆን? ብለዉ የግርምት ጥያቄ የሚያነሱ ስለመኖራቸዉ የማንጠራጠር ቢሆንም፤ መልሱ የጥያቄዉን ያህል የማይቀል ቢሆንም “ይቻላል” ብለዉ የገቡበት ዜጎች በመኖራቸዉ አካሄዱ እንደሚቻል ገሃድ ሐቅ ነዉ፡፡ ማለትም መስዋዕትነቱ የሚረዝምና የሚከብድ ቢሆንም በሰላማዊ ትግል መቋቋም እንደሚቻል ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ብዙ ናቸው፡፡ ለመሆኑ

ሠላማዊ ትግል ምን ይመስላል? እንዴትስ ተጀምሮ የትስ ስኬትን አስመዘገበ? ቀጥሎ የምንመለከተዉ ይሆናል።

ሠላማዊ ትግል መጀመሪያ መቼና የት እንደተጠነሰሰ ባይታወቅም ለሠላማዊ ትግል መሠረት የጣለዉ ሕንዳዊዉ ማሃንዳስ ካራማንች ጋንዲ ወይም አብዛኛዉም የዓለም ሕብረተሰብ በተስማማበት ስሙ ማህተማ ጋንዲ ነበር። የጨካኝ ገዥዎችን ሥርአት ለመቋቋም ጋንዲ የቀየሰዉ ሠላማዊ የሕዝብ እንቢ ባይነትን ነዉ። በ1921 እአአ የሕንድን ብሔራዊ ኮንግሬስ የተቀላቀለዉ ጋንዲ ሠላማዊ ትግሉ ጨካኝ ሥርአትን በማስወገድ ብቻ ሳይወሰን ድህነትን ጭምር በማስወገድ፣ የሴቶችና የሰዉ ዘርን እኩልነት ማስፈንና በተለይም የሕንድን ነፃነት ማረጋገጥ ዋና ትኩረቱ ነበር።

የጋንዲ የሠላማዊ ትግል መመሪያም ሕዝቡ በማንኛዉም ሁኔታ የአምባገነን ገዥዎችን አገዛዝ አለመቀበል ወይም እምቢ ባይነትን ሲሆን ለዚህም ዓላማ መሳካት የገጠር አርሶ አደሮችንና የከተሜ ሠራተኞችን አደራጅቷል። እንደ መሳሪያ የተጠቀመዉም በማንኛዉም ሁኔታ ከአምባገነን ገዥዎችና ጀሌዎቻቸዉ ጋር አለመተባበር የሚለዉ ትልቁ መመሪያው ነበር። አለመተባበርን በሚያሳዩበት ጊዜ ዉስጥ መሳሪያቸዉ መሆን ያለበት ዕዉነት፣ ሠላማዊ እንቢተኛነትና ለብቀላ አለመነሳሳት ናቸዉ። የትግል ስልቱ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆንም ሠላማዊ ትግል አሜሪካዊዉ ማርቲን ሉተር ኪንግን፣ የማያንመሩዋ ኦንግ ሳ ሱ ኪይን እና ደቡብ አፍሪካዊዉ ኒልሰን ማንዴላ የመሳሰሉትን ሊያፈራ ችሏል። አሜሪካዊው ቡጥኛ ሙሐመድ አሊ፤ በቀደመዉ ስሙ ካሽስ ክሌይ ቪዬትናም ሄዶ እንዲዋጋ ሲታዘዝ እንቢ ማለቱና በአገሩ ዉስጥ ደግሞ ለሰዉ ነፃነትና ሰብአዊ መብት መከበር ያደረገዉ ትግል ሠላማዊ ትግል ካካሄዱ ሰዎች ተርታ አሰልፎታል። ምንም እንኳን ገና ብዙ የሚቀሩ ነገሮች ቢኖሩም በአገራችንም ኢትዮጵያም ለአምባገነኖች፣ ለሙሰኞች፣ ለሽበርተኞች ይቅርታ የሚደረግበት አንዳች ምክንያት የለም በማለት ለሠላማዊ ትግል ስኬት ሀብታቸዉን፣ ዕዉቀታቸዉንና ሕይወታቸዉን

መስዋዕት ያደረጉና በማድረግ ላይ የሚገኙ ዜጎች ሰፊ ቁጥር አላቸዉ።

የሠላማዊ ትግል ጠቀሜታ ከነ ጋንዲና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች አልፎ ተቋም ተቋቁሞለት ሰፊ ጥናትም የተደረገበት በአሜሪካዊዉ ፖሊቲካል ሳይንቲስት በጂን ሻርፕ ነበር። እንደ ሻርፕ ጥናት መሠረት ሥልጣን ሊለወጥ የሚችል ነዉ። ሥልጣን በሥልጣን ላይ ካሉ ሰዎች ይሁንታ ወይም በበጎ ፈቃድ የሚሰጥ አይደለም። እንዲያዉም ሥልጣን የሚመነጨዉ (መዋቅራዊ ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) በሕዝብ ይሁንታ ነዉ። ይሁንታዉን የሚሰጠዉ ሕዝብ ጉልቤ ባለሥልጣናትን የማያከብር ከሆነ ገዥዎች ሥልጣን የሚባል ነገር የላቸዉም ወይም አይኖራቸዉም ማለት ይቻላል። የአንድ አገር ሕዝብ ለዚያው አገር መንግስት የሥልጣን ምንጭ መሆናቸዉን ራሳቸዉ የተረዱ ከሆነ፤ ለጨቋኝ ገዥዎቻቸዉ የሚኖራቸዉ አክብሮት ይቀርና የሥልጣን ማስከበሪያ መሳሪያ የሆኑ የፖሊስ፣ የፍርድ ቤቶችና የሌሎችም አስፈፃሚ አካላት መኖር የሚፈይዱት ነገር አይኖርም ይላል ሻርፕ።

ማህተማ ጋንዲን የተከተሉ ሰዎች በሕዝባዊ እምቢተኛነት አገራዊ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ሊመስርቱ ችለዋል። በኢትዮጵያችንም ተመሳሳይ ሁኔታ ለማስፈን የተነሳሱ ኃይሎች የዓይነት ልዩነት ቢኖራቸዉም ዛሬ ቀላል የማይባል ቁጥር ላይ ደርሰዋል። ቀደምት ተምሳሌቶች እንዳስተማሩን ከሆነ ነገሩ ያን ያህል ቀላል አይሁን እንጂ በኢትዮጵያም ባልተለመደ ሁኔታ ሥልጣን ላይ ካለዉ ፓርቲ ፍላጎት ዉጭ የመንግስት ሥልጣንን በሕዝብ ይሁንታ ከምርጫ ሳጥን ለማምጣት የሚቻልበት ሁኔታ እየተመቻቸ እንደሆነ እንረዳለን። ምንም እንኳን አካሄዱ እንዲህ ቀላል ሆኖ ባይገኝም፤ በሠላማዊ የሕዝብ እምቢተኛነት ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚቆጣጠረዉን የአገዛዝ ሥርአት እንዲቀየር እልህ አስጨራሽ ሠላማዊ ትግል ተካሂዷል። ሕዝቡ በምርጫ ጊዜ ወጥቶ መምረጥ ብቻ ሳይሆን ድምፄን አላሰርቅም ከሚልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል። ያንን ደረጃ አልፎ የሚመጣ ከሆነም ያልመረጥኩት ሰዉ ወይም ቡድን ሊያስተዳድረኝ አይገባም የሚል እምቢተኛነት

በኢትዮጵያም ከ2007ቱ ምርጫ በኋላ ለማየት ተችሏል። በርግጥም ሕዝብ ላልመረጠዉ አካል እና ጀሌዎቻቸው ትብብር ቢነፍግና በተለይ የመንግስት ሠራተኛዉ በገለልተኛነት ሕዝባዊ አገልግሎት ለማበርከት በቁርጠኛነት ከተነሳሳ፣ የተማረዉ ክፍል ለሙያ ሥነ ምግባር ተገዥ ቢሆን፣ ባለሀብቱም ያካበተዉን ሀብት መሠረቱ ሕዝብ መሆኑን ከተረዳ፣ በአጠቃላይም ኢትዮጵያ የጥቂቶች ብቻ ሳትሆን የጋራችን ነች የሚለዉ ዜጋ ቁጥር እየጨመረ ከሄደ፤ ሠላማዊ ትግሉ ከታለመለት ግብ የሚደርስበት ጊዜ ሩቅ እንዳልሆነ ያመለክታል። ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ ተናግሮት ነበር እየተባለ በቃል ለትዉልድ ሲተላለፍ ዛሬም ሕያዉ የሆነ አባባል አለ፤ "ከታንክና መድፍ የበለጠ የሕዝብ እንባ መንግስትን ይገለብጣል" ተብሎ ተነግሯል ይባላል። የሕዝብ እንባ ማለት አልቃሻነት ሳይሆን የሠላማዊ ትግሉ አንድ አካል መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ከፍ ሲልም የሕዝብ ትዕግስት ዘላለማዊ ፍርሃት እንዳልሆነ አምባገነኖች በቀላሉ ባይረዱም ቁርጡ ቀን ሲመጣ መራራውን ሽንፈት እንደሚጋቱ ማሳወቅ ነዉ።

**የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ**፡- ከአንድ ምዕተ ዓመት በፊት ጀምሮ የኢትዮጵያ ገዥዎችን የተጠናወተዉ ሥልጣንን በሰላማዊና ሕገ መንግስታዊ በሆነ ሁኔታ ያለማስተላለፍ በሽታ እነሆ ዛሬም ድረስ ቆይቶ በቀላሉም የሚላቀቀን አይመስልም። ሌላው ትልቁ ችግራቸው ደግሞ የዛሬው ገዥ ፓርቲ ባለሥልጣናት የቀድሞዎቹ ባለሥልጣናት እንዴት እንደወደቁ ጨርሶ አለማጠናቸው ነው። ቀደምት የኢትዮጵያ መሪዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ከሥልጣናቸዉ እንደተወገዱ በየቦታዉ የተመለከትን ሲሆን፤ ሕወሃት/ኢህአዴግ በትጥቅ ትግል ደርግን በማስወገድ ሥልጣን የያዘ ስለሆነ የሥልጣን አያያዙ ከሌሎች ቀደምት የኢትዮጵያ ገዥዎች የተወሰነ የቅርጽ ልዩነት ይታይበታል።

ከሥልጣን አያያዙ ሌላ ሕወሓትን ለየት የሚያደርገዉ ሌላ ጉዳይ አለ። አፄ ኃይሌ ሥላሴ ሥልጣን ተቆናጥቶ ከ1916 እስከ 1923 ለሰባት ዓመታት ያህል በቤተ መንግስት ውስጥ በማድፈጥ ከንግስት ዘዉዲቱ በስተጀርባ

ሲገዛ ኖሮ፤ ሕገ መንግስት የሚመስልና እራሱ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ ሆኖ የቆየበትን ሕገ መንግስት ደንግጎ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን። ያም ቢሆን በጉግ ማንጉግ ደብተራ አማካሪዎች በተቋቋመበት ቦታ ላይ ደርቆ መቅረቱ እንጂ የሱ የመጀመሪያ እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ አንድ እመርታ ወደፊት የተራመደ እንደሆነ ይገመታል። ነገር ግን ሕዝቡ ወደ ሥልጣኑ እንዳይመለከት ጭምር ለማድረግ "የኢትዮጵያ ንጉሴ ነገስት ከእየሩሳሌም ንጉስ ሰለሞንና ንግስት ሳባ ከተወለደዉ ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣዉ ከንጉስ ሳህለ ሥላሴ ዘር ከተወለደዉ ከቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ትዉልድ እንዳይወጣ በህግ ተወስኗል።" በማለት ኮፊያዉን ከፍ አድርጎ በመስቀሉ፤ እንኳንስ ሌላዉ ቀርቶ እራሱም ያንን ከፍ አድርጎ የሰቀለዉን ኮፊያዉን ማዉረድ አልቻለም። ያንን ኃያልና ቢነካ እንኳን ሰማይና ምድሩም እንደማይሆን ይሆናል ሲባልለት የነበረዉን ንጉስ ከሥልጣን ያስወገደዉ ደርግ በተራዉ ከዚያ ከደርጉ ዉስጥ አስፈሪ ሆኖ በወጣዉ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መሪ በመንግስቱ ኃይለማሪያም ድንጋጌዎች (decrees) ብቻ ለአስር ዓመታት ያህል ከገዛ በኋላ ብዙም ከኃይሌ ሥላሴ ያልተለየ ሕገ መንግስት ቀርፆ ሳይሰራበት በሕወሓት/ኢህአዴግ ተወገደ።

ሕወሓት/ኢህአዴግን ግን ትንሽ ለየት የሚያደርገዉ ነገር ያልኩትም ገና ሲጀምር ጀምሮ የሽግግር ሥርአት ሕግ በመቅረፅና የተለየ ሐሳብ ያላቸዉን ጭምር አሳታፊ በሚመስል ሁኔታ መንግስት በማቋቋም የተጓዘበት ሁኔታ ቢኖርም፤ ገና ከጅምሩም ቢሆን ይበል የሚያሰኝ አልነበረም። ነገር ግን የተቋቋመ ሕገ መንግስት አለመኖር ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል ሕወሓት አስቀድሞ የተረዳዉ ይመስል፤ ይህንኑ ክፍተት በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመሙላት ፌዴራላዊ የመንግስት ሥርአት የሚያሰፍን ሕገ መንግስት በመቅረፅ ለማሟላት ጥረት አድርጓል። በሕገ መንግስቱ በተቀመጠዉ መሠረትም የቁጩ በሚመስል ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ያሳታፈ ምርጫዎች የተካሄዱ ቢሆንም፤ ተቃዋሚዎቹ የሕዝቡን ድምፅ እንዳያገኙ፤ ቢያገኙ እንኳን ሕወሓት ራሱ በአምሳያው

በአደራጃቸዉ የደህንነት፣ የፖሊስና የመከላከያ ኃይሎች እንዲቀሙ በማድረግ ምርጫዎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ባህርይ እንዳይላበሱ አድርጓል። ምንም እንኳን ምርጫዎች በየአምስት ዓመቱ ቢካሄዱም ከሀብት ብክነት እስከ ሰዉ ሕይወት መጥፋት ከማስከተሉ በስተቀር ምርጫን የመሳሰሉ የዲሞክራሲ መገለጫዎች የሚባሉት በሚጠበቁት ዓይነት ሁኔታ ከቶዉንም አልሆነም። እየተመረጡ ሳይሆን እየተነቀሱ የመንግስት ሥልጣን ላይ የሚቀመጡ የሕወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣናት በሙሰኝነታቸዉ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸዉ የሆኑ ስለሆነ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት ብሎም ወሳኝነት አንዳች ግምት ሳያገኝ በመቅረቱ የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ የሰማይ ያህል እንደራቀ እንዲቆይ ተደርጓል።

ኢህአዴግ የፓርቲ ፖለቲካን ያቀጨጨበት አንዱ የመልካም አስተዳደር ጉድለትን በማስፈን ነው። የመልካም አስተዳደር እጦት ለፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት እንቅፋት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። ምክንያቱም፤ በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ላይ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚያስከትለዉን ችግር በፓርቲ ፖለቲካ ላይም የበለጠ እንደሚሆን ለማወቅ አዋቂ ቤት መሄድ ሳያስፈልግ፤ በአዉራ ፓርቲ ፖለቲካ ሥር የተጠረነፉ ሰዎች በተለይም የመንግስት ሠራተኞች አማራጭ ሐሳብ ይዘዉ ለሚቀርቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በገለልተኛነት ተገቢ አገልግሎት መስጠት አልቻሉም። በፋንታዉ ግን አውራ ፓርቲው ደካማ ፓርቲዎችን መፈልፈልና ጠንካራ ፓርቲዎችን ማዳከም፤ አልፎ ተርፎም ቢሮክራሲዉንና ፓርቲን አጣምሮ ማንቀሳቀስ ከመንግስታዊ ቢሮክራሲ መስፋፋት በተጨማሪም ሌላ የፓርቲ ቢሮክራሲን ሕዝቡ እንዲሸከምና የፀረ ዲሞክራሲ መሳሪያ እንዲሆን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እንዲያመሩ አድርጎ አስቀርቷል። የመልካም አስተዳደር ጉድለቱ ደግሞ ቀድሞም የዘር አመጣጥ፣ የሃይማኖት ልዩነት፣ የታሪክ ግጭት የነበረባቸውን የኢትዮጵያዊያንን የአንድነት ትስስር እንዲጠፋ ተደርጓል።

መልካም አስተዳደርን ለማሰረፅ በያንዳንዱ የመንግስትም ሆነ የግል

ድርጅቶች ዉስጥ የሥነ ምግባር መመሪያ ተብሎ አስራ አንድ ትዕዛዛት በየቢሮው በራፍ ላይ፣ የመንግስት ተቋማትን ግቢ እስከሚያጣብቡ ድረስ በማስታወቂያ ሰሌዳዎችና ግድግዳ ላይ የተለጠፉ ወረቀቶች እዚያዉ የተሰቅሉበት ቦታ አቧራና የሸረሪት ድር ተሸካሚ ሆነው ከመቅረታቸዉ በስተቀር፤ ሁሉም ኢህአዴግ ችግሮቹ ናቸዉ ከሚላቸዉ ጋር ቢፈተሹ፤ አንዳቸዉም ተግባራዊ ሆነዉ ያልተገኙ፣ ተግባራዊም ይደረጋሉ ተብለዉ ተስፋም የማይጣልባቸዉ መመሪያዎች ናቸዉ።

ዲሞክራሲ ማለት ሕዝብ መሪዎቹን ወይም ተወካዮቹን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ከመሪዎቹ ወይም ከአስተዳዳሪዎቹ የተሻለ አማራጭ ይዘዉ ከሚቀረቡት ፓርቲዎች አንዱን መምረጥ እንደሆነ በትክክል መገንዘብ አለባቸዉ። ይህ ብቻም አይደለም። ምርጫ ከዴሞክራሲ መገለጫዎች ቀዳሚ መሆኑ ቢታወቅም፤ ዜጎች የምርጫ ካርዳቸውን የምርጫ ሳጥን ውስጥ በሚጥሉበት ጊዜ ተወዳዳሪውን መምረጣቸው ብቻ ሳይሆን ለነፃነታቸው ማረጋገጫ ጭምር ድምፅ እንደሰጡ ተደርጎ ክብደት ሊሰጠው ይገባል። መምረጥ ብቻም አይደለም፤ ተመራጮቹ ዉጤታማ ሥራ የማይሰሩ ከሆነ ሕዝቡ ሊያወርዳቸዉ እንደሚችል ግንዛቤ መያዝ አንዱ የዴሞክራሲ ዕውቀት መሆን ይኖርበታል። ሕዝብ መሪዎቹን ከአንድ ፓርቲ ብቻ የሚመርጥ ከሆነ ምርጫዉ የሰሜን ኮሪያ ወይም የቻይና ዓይነት መንግስት መመስረት ሆነ ከማለት በስተቀር ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያስብለዉ አንዳች ነገር አይኖረዉም።

ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ባለመኖሩም ሐሳብን በነፃ ማንሸራሸር አይቻልም፣ ነፃ የፍርድ ሂደት አይጠበቅም፣ በአስተዳደሩ ውስጥ የሕዝቦች የጎለበተ ተሳትፎ አይኖርም፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት የመንግስት ሥርአት አይመሰረትም፣ የአገሩም ሆነ የሕዝቡ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እያነሰ ይሄዳል፣ የሕዝብና የሀገር ሰላም እና ደህንነት እየደፈረሰ ይሄዳል። አገሮች ወይም ሕዝቦች ከዴሞክራሲያዊ አመራር እየራቁ በሄዱ ቁጥር አምባገነናዊ ሥርአት እየገነነ ይሄዳል፤ አሊያም ደግሞ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ እንዳለው ሁኔታ ሕዝባዊ እንቢተኝነት እየበረታ ይሄዳል፤

በገዥ ኃይሎች በኩል ደግሞ የአውራ ፓርቲ ሥርአት ወይም “የተመራጩ አምባገነንነት" እየገነነ መሄድን ይፈጥራል፡፡

አዉራ ፓርቲ ባለበት አገር በተለይም ግራ ዘመም በሆኑ መንግስታትና የፖለቲካ ቡድኖች ዉስጥ የፓርቲዉ አባላት ታማኝነታቸዉን የሚያሳዩት የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ከሆነዉ ሕዝብ በላይ ረብጣ የሚዛቅበት ወንበር ላይ ላፈናጠጣቸዉ ፓርቲያቸዉ ወይም መሪያቸዉ ስለሆነ፤ እነሱ ዘንድ ስለዴሞክራሲም ሆነ ስለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማንሳት ከሕልም እንጀራ ውጭ አይሆንም፡፡ ፓርቲዉ ወይም ግለሰቦቹ ደግሞ በተራቸዉ ባለዉለታዎቻቸው ካድሬዎች የሙስና፣ የኪራይ ሰብሳቢነት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ በአጠቃላይ ወንጀል የሚባል ጥፋት እንኳን ቢገኝባቸዉ የፓርቲዉ ወይም የግለሰቡ ታማኝነት እስካላቸዉ ድረስ ሌላ የተሻለ ቦታ ሊያስቀምጧቸዉ ይችሉ እንደሆን እንጂ ለሕግ አካል አያቀርቧቸውም፡፡ ስለዚህ፤ እነዚያ ካድሬዎች ሙስና ከመፈጸምና ከኪራይ ሰብሳቢነት ስሜታቸዉ ሊላቀቁ አይችሉም፡፡ ከነዚህ ሰዎች ወይም አመራሮች መንግስታዊ አሸባሪነትን እንጂ መልካም አስተዳደርን መጠበቅ ራስን ማታለል ወይም የፖለቲካ ሞኝነት ነው፡፡ አምባገነናዊ ፓርቲዎችና ግለሰቦች አሣታፊ (inclusive) የመንግስት ተቋማትን ከመገንባት ይልቅ አግላይ (extractive) ፖሊሲዎችን ስለሚከተሉ አገርን ያበለጽጋሉ ተብሎም አይጠበቅም፡፡ የዚህ ሁሉ ምንጭ የሚሆነዉ ደግሞ የሙስኞችና የኪራይ ሰብሳቢዎች ምንጭ እንዲህም መልካም አስተዳደርን ከሚናገሩት ቃላት ባሻገር የማይተግብሩት፤ ሥልጣናቸዉ ከሕዝብ ምርጫ ያልመነጨ የመንግስትና የፓርቲ መሪዎች ናቸዉ፡፡

ሕወሓት/ኢህአዴግ አፋኙን ወታደራዊ ደርግ በማስወገድ ሥልጣን የያዘ ሲሆን፤ ከላይ እንደተገለጸዉ ሥልጣን ላይ የቆየዉ ደግሞ ሕገ መንግስታዊ አግባቢነት በሌለዉ ሁኔታ ሌሎች ፓርቲዎች አማራጮቻቸዉን ለሕዝብ እንዳያቀርቡ እንቅፋት በመሆን ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት እራሱ ያወጣዉን ሕገ መንግስት አንቀፅ 9(3) “በዚህ ሕገ መንግስት ከተደነገገዉ ዉጭ ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነዉ” የሚለዉን

በመጣስ ከሕግ አግባቢ ውጭ ሥልጣን የመያዝ ያህል የሚከብደዉን ከሕግ አግባቢ ዉጭ ሥልጣን ላይ ቆይቷል። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በመጫን አማራጭ ሐሳቦች ለሕዝቡ እንዳይቀርቡ በማድረጉ የአገሪቱን የልቀት ዕድገት በብዙ ዓመታት ወደኋላ ጎትቷል። በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በአገራችን የፓርቲ ፖለቲካና የዲሞክራሲ ሥርአት ግንባታ በሠላማዊ ትግል ሊያድግ አልቻለም። ስለሆነም፤ ረጅም ጊዜ የሚፈጀዉንና ብዙ መስዋዕትነትን የሚጠይቀዉን ሠላማዊ ትግል ትተዉ አንዳንዶች የትጥቅ ትግል ቢመርጡ አይፈረድባቸዉም።

በነበረው ሁኔታና ባህርይ ሲታይ የሕወሓት/ኢህአዴግ የሥልጣን ዘመን ከ2010 ዓም አጋማሽ በኋላ መቀጠል አልቻለም። ነገር ግን ወደ ሥልጣኑ ለመመለስ ሲል ከልጅነታቸዉ ጀምሮ ለክፉ ጊዜ ብሎ ያዘጋጃቸውን ግለሰብ ወጣት አመራሮችን ቦታ በመቀያየር ሊጠቀም ስትራቴጂ የነደፈ ቢሆንም፤ ከ2012 ዓም ጀምሮ የኢህአዴግ አዲስ አበባ ቀሪ ክፍሉ ስሙን ጭምር ብልፅግና በሚባል ፓርቲ ለዉጦ የማስመሰል ጥገናዊ ለዉጥ አካሂዶ ተከስቷል። በመቀጥልም መቀሌ በገባውና አዲስ አበባ በቀረው ኢህአዴጎች መሀከል ከሕዝብ ጫና ወይም ከሥልጣን ጥማት የተነሳ ይመስላል መናበብ አልተፈጠረባቸዉም። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አካሄድ ከ2010 በኋላ ያለው ሥራና ጉዞ ሁለት ገጽታ ይዞ ሄደ። አንድም ሕዝብ ኢህአዴግን መጥላቱን አምኖ በመቀበል ቁንጮ የኢህአዴግ አባላትን ከማዕከላዊ መንግስት ጥለው ወደ መቀሌ እንዲያፈገፈጉ ሲደረግ፤ ቀሪዎቹ 3/4ኛ የኢህአዴግ አባላት ደግሞ በተሃድሶ ስም ናባሩን ኢህአዴጋዊ ፕሮግራም ይዘው የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ በስደት ላይ የነበሩ ተቃዋሚዎችን ወደ አገር ቤት መመለስ፣ ከውጪ የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ ተቋማትን ወደ አገር ቤት መሳብ፣ በተለይ ደግሞ ከሕወሓት ሌላ ቀደም ሲል የኢህአዴግ አባላት የነበሩ ፓርቲዎችን በአዲስ መልክ ማደራጀት ሥራ በስፋት ተክዶበታል። ኢህአዴግ ቁጥር ሁለት በመባል የሚታወቁት የብልፅግና ፓርቲ አባላት ከላይ የተጠቀሱ ጊዜያዊ እርምጃዎችን በመዉሰዳቸዉ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ጀብድ የሰሩ አስመስለው ቢናገሩም፤ እነዚህን እርምጃዎች ባይወስዱ ኖሮ አንድም

ወደ መቀሌ ከአፈገፈጉት ጋር መጠቃለል ወይም የራሳቸውን ሕልውና ማክተሚያም መንገድ ያመቻቹ እንደነበር፤ በተጨማሪ ለአገሪቱ ሕልውና ራሱ አደጋ ላይ ይወድቅ እንደነበር እነሱ ራሳቸው ዘና ሲሉ የማይክዱት ሐቅ ነው።

ለማጠቃለል ያህል፤ የሕወሓት/ኢህአዴግ ኢዴሞክራሲያዊ ጉዞ በውስጥ ፓርቲ ተሃድሶ ስም ኢህአዴግን ሁለት ጊዜ በማፍረስ ሁለት ጊዜ አዳዲስ ፓርቲዎችን ከመመስረቱም በተጨማሪ ጊዜያቸው ያበቃላቸው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ከአምስተኛ ዙር ወደ ስድስተኛ ዙር በጥቂት አድርባይ የኢትዮጵያ ምሁራን አንጋሽነት መስከረም 25/2013 እንድደረግ የሥልጣን ዕድሜውን ልክ ቀዳሚው ደርግ እንዳደረገው ሁሉ በድንጋጌ የሚያስረዝም አዲስ መንግስት ተመሰረተ። የመሰረቱት መንግስት ግን ምንም ተባለ ምን እንጥፍጣፊ የሕዝብ ይሁንታ የሌለበት የጉልበት (de facto) መንግስት ነው። የጉልበት መንግስት ደግሞ ሕዝብን የሚገዛው በድንጋጌ (decree) እና በመግለጫ እንጂ ሕገ መንግስት ቢኖርም ሕገ መንግስታዊነትን ግምት ውስጥ በማስገባት አይደለም።

ከላይ በተጠቀሱት እና ከወቅታዊ ችግሮች የተነሳ ኢትዮጵያ ትበታተን ይሆን? ብለው የስጋት ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎች አሉ። መልሱ ሁለቱም ሊሆን ይችላል ነው። ሲጀመር የግጭትና የቅራኔ ምንጮችን አለመፈተሽና ለመፍትኼያቸውም አለመደማመጥ፤ በተለይም ሥልጣን ላይ ሙጭጭ ማለት ለከፋ ችግር ያጋልጣል። ኢትዮጵያንም ይይበታትናል። የሦስት ሺህ ዘመን የሀገረ መንግስት ምስረታ ሐበሾች በፈለጉት ዓይነት ሁኔታ አልተሳካም። ቢያንስ ለሃምሳ ዓመታት የታለመው ብሔር ተኮር ፌዴራሊዝሙም በሕወሓት/ኢህአዴግ ስውር ሴራ ተደናቅፏል። በዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ነፃነት፣ እኩልነትና ፍትሓዊ ተጠቃሚነት ዕውን ሊሆን አልቻለም። አለመቻቻልና ሰዎች የሚሉትን አለማድረግ ኢትዮጵያን ለብተና እንኳን ባይሆን እየተቆራረሰችና እያነሰች እንዲትሄድ ያስገድዳታል። ብዝሃ ሐሳብ የሚፈተንበት የፓርቲ ፖለቲካም

እንደማይሆን ሆኖ ቀርቷል፡፡

ምዕራፍ አራት፡ **በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ግንባታ ውስጥ የውጪ ኃይሎች ሚና**

ከዕለታዊ ጋዜጣ ላይ ባገኘሁ መረጃ ላይ ተመስርቼ ከአንድ የሩቅ ወዳጄ ጋር ስናወራ፤ እግሬ መንገዳችንንም የአገሮች ሀብት አጠቃቀም ጉዳይን አነሳንና ጎረቤት አገር ኤርትራ የዓሳ ምርት እንዱስትሪን ለምን አስፋፍታ በአገር ዉስጥም ሆነ በዓለም ገበያ ላይ ተጠቃሚ አትሆንም ብዬ ላነሳሁለት ጥያቄ፤ ይኸዉ ወዳጄ የቀድሞ ባህር ኃይል መኮንን ነበርና የባህር ሀብቱ ባለቤት የሆኑ አገሮች የአቅማቸዉን ያህል ቢያመርቱም የበለጠዉን ግን ኃያላን የሆኑ አገሮች መንግስታት የዓሳ ማምረቻ መርከቦቻቸዉን በጦር መርከቦቻቸዉ በማሳጀብ ቀናትና ወራት ወስደዉ የዚያን የአቅመ ደካማ መንግስት የባህር ክልል ላይ ይገቡና የባህር ሀብት በተለይ ዓሳን ዘርፈዉ ወደአገራቸዉ ይሄዳሉ ብሎ አጫወተኝ። በመጨመርም፤ እነዚያ ኃያላን መንግስታት የባህር ሀብት መዝረፍ ብቻ ሳይሆን ገዥ ፓርቲዎችንና መንግስታትን እቤተ መንግስታቸዉ ድረስ እየሄዱ ወይም ወደ መናገሻ ከተሞቻቸዉ እየጠሩና እየጠመዘዙ የሚፈልጉትን ነገር ማስደረግ እንደሚችሉ በተጨማሪነት አጫወተኝ። በእርግጥም ሲታሰብ ኃያላኑ መንግስታት ዱኩማን መንግስታትንና ፓርቲዎችን የመጠምዘዛቸዉ እዉነትነት የሚታወቅ ስለሆነና ምንም እንኳን በዚህ ርእስ ላይ መስራቱ ራሱን የቻለ መድብል የሚወጣዉ ቢሆንም፤ አጭር ማስታወሻን ከፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ጋር ማቅረብ ተገቢ ሆኖ ስላገኘሁት አምስት አገሮችን፤ ሁለት ኃያላንና ሦስት የኢትዮጵያ ጎረቤት መንግስታትን ለማንሳት ወደድሁ። በተጨማሪም ቢያምኑትም ባያምኑትም በራሱ ሚሊዮን ችግሮች የተተበተበውን የአፍሪካ አንድነት እና ወንበሩን ስለተረከበው የአፍሪካ ሕብረት አንስቼ አነስ የሚል ምልከታ አደርጋለሁ።

በአንድ አገር የፖሊሲ ቀረፃም ሆነ ትገበራ ዉስጥ ሁለት ወሳኝ ጉዳዮች፡- የአገር ዉስጥ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አሉ። በተለምዶ የአገር ዉስጥ ፖሊሲ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት በስፋት ቢገለፅም፤ ዓለም

አቀፍ ሁኔታዎችም ሆኑ ከጎረቤት አገሮች ጋር የሚኖረዉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነት የወሳኝነት ሚና የሚጫወቱበት ጊዜ ሰፊ ነዉ። ስለሆነም ነዉ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ስላላቸዉ ጥቂት አገሮች በተለይም በፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ዉስጥ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕ ያላቸዉን አገሮች ማንሳት የፈለኩት።

## የተባበረዉ የአሜሪካ መንግስት/USA

“በሰዉ ቁስል እንጨት ስደዱበት” የተባለዉን የአማርኛ ተረት ፈረንጆቹን ተርቱ ቢሏቸዉ “pocking stick into the wound of someone” እንደሚሉ አንባቢዎቼ ይረዱኛል ብዬ እገምታለሁ። ለዚህ ተረት መነሻ የሆነኝ የአሜሪካዉ ፕሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ ከሐምሌ 19 እስከ 21፣ 2007 በአገራችን ኢትዮጵያ ጉብኝት አድርገዉ በነበሩበት ጊዜ እሳቸዉ ሰጡት ተብሎ አዲስ ዘመን በተባለዉ ዕለታዊ የኢትዮጵያ መንግስት ጋዜጣ “በኢትዮጵያ የሚካሄደዉን የዲሞክራሲ ግንባታ ዕዉቅና ሰጥተዉ፤ አገራቸዉ አሜሪካ **በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠዉን የኢትዮጵያ መንግስት** በኃይልና በአመፅ ለመጣል የሚደረግ እንቅስቃሴን በፅኑ እንደሚያወግዙ ገለጹ፤ አገሪቱ እያካሄዳለች ያለዉ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለአፍታም እንዲደናቀፍ አሜሪካ እንደማትሻ አረጋገጡ” በማለት ጋዜጣው አትሞ አስነብቦናል። በጣም አስገራሚዉ ነገር ኦባማ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ መንግስት ብለዉ ያሞካሹት የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት እሳቸዉ ከተናገሩበት ቀን ጀምሮ ቢሰላ መሰንበት የቻለዉ ከሦስት ዓመታት ያነሰ ጊዜ ነዉ። ባዶ እጁን በተጋፈጠዉ የኦሮሞ ቄሮ/ቃሬ ተፈንግሏል።

ተጣብቆን አልላቀቅ ያለዉ የገዥዎቻችን የብዙ ዘመናት የፀረ ዲሚክራሲያዊነት አባዜ ዛሬም ድረስ አብሮን መኖሩን የራሳቸዉን ዜጎችንና የተለያዩ ተቋሞቻቸዉን እማኝ ጠርተን ልንፋረዳቸዉና ልንረታቸው እንደምንችል እየታወቀ ፤ ኦባማ በአደባባይ የሌለ

‘ዲሚክራሲያችንን’ ባላሞካሹና በቁስላችን ዉስጥ እንጨት ባልሰደዱ ነበር እላለሁ።

ከታሪክ አንፃር ትንሽ ጨልፎ ለማየት ያክል የኢትዮጵያና የአሜሪካ ፖለቲከኞች ግንኙነት ከተጀመረ ረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም የአሜሪካና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግንኙነት ግን ገና አልተጀመረም፤ ወይም ገና ይቀራዋል ማለት እችላለሁ። በምንም ዓይነት ሁኔታ ኢትዮጵያዊያንና አሜሪካዊያን ልብ ለልብ ከመናበብ ደረጃ ላይ አልደረሱም። ምክንያቱም፤ አሜሪካኖች መሪዎቻቸዉንና አስተዳዳሪዎቻቸዉን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ማዉረድ (recall) ወይም መቅጣት (impeach) ማድረግ እንደሚችሉ ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ወንድሞቻቸዉ ይህንን ማድረግ ቀርቶ አስበዉም እንደማያዉቁ ወይም እንደማይችሉ፤ አስበዉም ቢሆን ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚጠብቃቸዉ፤ የአሜሪካ ፖለቲከኞች አንድም አያዉቁትም፤ ወይም የአሜሪካ አስተዳደር ባለሥልጣናት ከራሳቸዉ ቁመት አኳያ እየገመቱ፤ ወይም ኢትዮጵያዊያንን ሊሸነግሉ፤ እነሱ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት የገነቡበት ጊዜ ማለትም 200 ዓመታት ወደኋላ መቅረታችን ግርምታ እየፈጠረባቸዉ፤ ኢትዮጵያዊያንን በዲሞክራሲ ግንባታ ለመርዳት ማሰብ ጉልበትና ገንዘብ የማባካን ያህል መስሎ ታይቷቸዉ ሊሆን በሚችል ዓይነት አገላለጽ፤ የሌለንን በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመምረጥ ዕድል እንዳለን አድርገዉ የተናገሩት። አሜሪካን ከወጣትነት እስከ ጎልማሳነት የኖረበትና የሚያዉቀዉ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ (1998፡ 580) “. . . የምዕራብ ሀብታም አገሮች እንደ ኢትዮጵያ ባለ ድሃ አገር ዲሞክራሲን ማስፈን እንደ ሁለተኛ ደረጃ ጉዳይ የሚመለከቱት ነዉ” በማለት ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፉ የተግባር ልምዱን አስቀምጦልናል። በዚህም ምክንያት ይሆናል የአሜሪካዉ ፕሬዝዳንት ከላይ በጋዜጣዉ የተጠቀሰላቸዉን ቃል በአገራችን መዲና በአፍሪካ ሕብረት አዳራሽ ተገኝተዉ የተናገሩት።

በመንግስታት መሀከል የተፈጠረዉ ሻካራም ሆነ ጤናማ ግንኙነት በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ሕዝብ መሀከል ወርዶም ተመሳሳይ የሆነ ነገር

ይከሰታል ብሎ ትንተና መስጠት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሊያስቸግር ይችላል። ምክንያቱም፤ የአሜሪካ ሕዝብ መንህስቱን እንደሚመርጥ ስለሚታወቅ፤ የአሜሪካን መንግስት ዉሳኔ የአሜሪካን ሕዝብ ዉሳኔ ነዉ፤ ብሎ የሚታሰበዉን ያህል፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የኢትዮጵያ መንግስትን ዉሳኔንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዉሳኔ ይሆናል ብሎ ለመዉሰድ የመንግስታቱን አመሰራረትና ሥልጣን አያያዝ ወደኋላ ተመልሶ መመልከትን ይጠይቅ ይሆናል። የአሜሪካን መንግስት በሰለጠነ ሁኔታ በአሜሪካዊያን ድምፅ ተመርጦ፤ ስለአለበት ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሚረዳዉን ያህል፤ የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያዊያን ድምፅ ባለመመረጡ የሚሰማዉ ኃላፊነትም ሆነ የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደዚያዉ ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም። ስለሆነም፤ የሁለቱን መንግስታት ዉሳኔን የሁለቱ ሕዝቦች ዉሳኔ አድርጎ መዉሰድ ከፍተኛ ስህተት ላይ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ትዝብት ላይ የሚጥል ነዉ።

የአሜሪካ መንግስት በዓለም ደረጃ ካለዉ የኃያልነትና የተሰሚነት ደረጃ የተነሳ የኢትዮጵያ ዓይነት መንግስታት ምንም ሊናገሯቸዉ አይችሉም። እንዲያውም አሜሪካንን በነገር መጎነጥ ራሱ አነሰ ከተባለ ለዲፕሎማሲያዊ ተፅዕኖ ከፍ ካለም ደግሞ ለንግድና ኤኮኖሚያዊ ማዕቀብ ሊያጋልጥ ይችላል። በተለያዩ ጊዜ ለማየት እንደተቻለዉ አሜሪካኖች የጓትሜላዉን ዳንኤል ኦርቴጋን፣ የጋናውን ቶማስ ሳንካራን፣ የመሳሰሉት በወታደሮቻቸዉ ከቤተ መንግስቱ በወረንጦአቸዉ ወሰዱ፣ የማዕከላዊዉን አፍሪካ ረፑብሊክ መሪ ጂን በዴል ቦካሳን፣ የዩጋንዳዉ ኢዲ አሚንን፣ የኢትዮጵያዉ አፄ ኃይሌ ሥላሴን ዕድሜ ልክ እንዲነግሱ አሜሪካኖች ድጋፍ ሲሰጧአቸውና አልጋቸዉ ላይ እንዳቆዩአቸው፤ በቃችሁ ካሏቸዉ ደግሞ እራሳቸዉ ወይም በተዘዋዋሪ አሜሪካዊያን አንስተዉ ያንኮታኳቷቸዋል፤ ወይም ልክ እንደአፄ ኃይሌ ሥላሴ ሲጠብቋቸዉ የነበሩ ወታደሮቻቸዉ ሲነሱባቸዉ ከቁብ ሳይቆጥሩ ዝም ብለዉ ይመለከቷቸዋል። ይኼ የአሜሪካኖችን የተፅዕኖ ስፋትና ጥልቀት ለማመላከት ነዉ።

ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ወደ ሥልጣን ከመጣ ከሃያ ዓመታት በኋላ ወደ ነጩ ቤተ መንግስት በመጥራት ለአንድ ጥቁር መሪ አድርገዉ የማያዉቁትን የሞቀ አቀባበል አድርገዉለታል ተብሎ ብዙ ተፅፎለታል፡፡ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኢትዮጵያን ለማሻሻል አሜሪካኖች አራት ነጥቦች ያሉትና ፖይንት ፎር በመባል የሚታወቀዉን ስምምነት በ1943 ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱም ኢትዮጵያ ዉስጥ ትምህርት ለማስፋፋት ማለትም ኢትዮጵያዊያን ወጣቶችን ወደ አሜሪካ ወስደዉ ማሰልጠን፣ የኢትዮጵያን የሰዉ ኃይል ዕዉቀትና ክህሎት ለማሳደግና የኢትዮጵያን የግብርና ምርት እንዲያድግ የአሜሪካንን የቴክኒክ እገዛ ማግኘት ያካተቱ ነበሩ፡፡ በጂማ እርሻ ምርምር ኮሌጅ ሥር የነበረዉ የአምቦ እርሻ ምርምር ኮሌጅና የመንግስት እርሻዎች ይባሉ የነበሩ ድርጅቶች (ካዱ፣ ዋዱ፣ አርዱ) የተቋቋሙት በፖይንት ፎር ፕሮግራም ሥር በተደረገዉ እገዛ ነበር፡፡ ከአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ የተደረገዉ እገዛ በዚህ ብቻ ያበቃ አልነበረም፡፡ በቅርብ በአዲስ አበባ ከተማ ዉጥ የተመሠረተውንና ውስብስቡን የበሽታዎች መቆጣጠርያ ማዕከልን ይጨምራል፡፡

በወታደራዊ መስኮችም አሜሪካኖች በኢትዮጵያ ቀላል የማይባል ተሳትፎ ነበራቸዉ፡፡ ልክ በኢህአዴግ መንግስት ጊዜ ሰዉ አልባ አይሮፕላን (ድሮን) አሰማርታ አልሸባብ የተባለዉን የሱማሊያ አሸባሪ ድርጅት (የኢህአዴግ መንግስትን የሚቃወሙትንም ሊጨምር ይችላል) እንደምትከታተል ሁሉ፤ መካከለኛዉ ምስራቅ አገሮችንና የቀይ ባህርን የንግድና ወታደራዊ መርከቦችን እንቅስቃሴንና የነዳጅ ማመላለሻ መስመሮችን ለመከታተል በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ላይ ከተቋቋመዉ ቃኘዉ የሳተላይት መገናኛ ጣቢያ በተጨማሪ ኢትዮጵያን ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከቆላ እስከ ደጋ፣ ከመሃይም እስከምሁር የሚከታተሉበት የሰላም ጓድ (Peace Corps) አባላት አሰማርተዉ ቢሰሩም፤ የኢትዮጵያ መንግስታትን ለሕዝብ ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለማሻሻል በቂ ነው በሚባል ሁኔታ አልሰሩም፡፡ ይህ ደግሞ ዛሬ የሚባል ብቻ ሳይሆን በደርግ መንግስት ዘመንም በግብፅ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበረዉ ዘመነ ካሰኝ ለፖል ቢ ሄንዝ ነገሮ እንደተፃፈዉ (2007፡ 218) “Zemene wishes Washington had pressed

Haile Sellassie earlier to take serious steps toward liberalization and appointment of more energetic young people to key positions.” በማለት አሜሪካኖች ኢትዮጵያን ለማሻሻል ብዙ መስራት እንደነበረባቸዉ፤ ነገር ግን የተፈለገዉ ያህል እንዳልተሰራ የገለጸበት ስሜት ነበር። ቂም መዘርዘር እንዳይሆንብኝ እንጂ የ1948ቱን የተሻሻለ የኃይሌ ሥላሴን ሕገ መንግስት በመቅረፅ ዉስጥ ሦስት አሜሪካዊያን ተሳትፈዋል። አሳዛኙ ነገር ግን ተሻሻለ የተባለዉ ሕገ መንግስት የንጉሱ ሥርአት ተከብሮ እንዲቆይ አደረገ እንጂ፤ በ1776 (ከሁለት መቶ ሰላሳ ዓመታት በፊት) የወጣዉን የአሜሪካ ሕገ መንግስት ዓይነት ዲሞክራሲ ያለው መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሸት ቅንጣት ታክል አልሞከሩም። እንዲያዉም ኢዲሞክራሲያዊ የነበረዉን መንግስት ተቀናቃኝ እንዳይነሳበትም ሆነ ተነስቶም ከሆነ በመምታት አሜሪካ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እገዛ አድርጋለች። ለአብነትም፤ በ1953 ዓም በንጉሱ ላይ የተቃጣዉን መፈንቅለ መንግስት በአዲስ አበባ ደረጃ ዕርቅ ብለዉ መሀል ገብተዋል፤ በሌላም በኩል ንጉሱ ከነበረበት ጉዞ ሲመለስ ያረፈዉ አስመራ አይሮፕላን ማረፊያ ሲሆን፤ የደህንነት ሽፋን የሰጡት ደገሞ በጠቅላይ ግዛቱ የነበሩ ቃኘዉ ሻለቃ በመባል የሚታወቀዉ የአሜሪካ አየር ኃይል ቤዝ ነበር።

በሌላም በኩል እንደመቀራረባቸዉ ሁሉ የኃይሌ ሥላሴን መንግስት አስተዳደር ለማሻሻል የወሰዷቸዉ እርምጃዎች ሁሉ የተፈለገዉን ዉጤት ባለማስመዝገቡ ወይም የተፈለገዉ ቦታ ላይ ባለመድረሱ አሜሪካኖችን አላረካም ይሆናል፤ ወይም የንጉሱ ጠቀሜታ ያበቃለት ሊሆን ይችላል፤ በ1967 ንጉሱ ከነ አልጋዉ በወታደራዊ ደርግ ሲገለበጥ ሊያድኑት ወይም ቢያንስ እንደ ጂን በዴል ቦካሳ ወይም እንደ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም አገር ጥሎ እንዲኮበልል እንኳን መንገዱን አላመቻቹለትም። ከከንፈር መጠጣ ያላለፈ አዘኔታ እንኳን ለንጉሱ አላደረጉም። ይበስ ብለዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዕዉር ድንብሩ ወታደራዊ ደርግ ሥር ሲወድቅ፤ የአሜሪካን መንግስት ያዘነላቸዉ በጣም ዘገይቶ ከመሆኑም በላይ በዚህን ጊዜም ቢሆን ዲሞክራሲ ኢትዮጵያ ዉስጥ

እንዲሰፍንና ዕድገት እንዲመጣ አሜሪካኖች በበቂ ሁኔታ አላገዙም። ደርግን ለመጣል በሚደረገዉ ትግል ዉስጥ የበኩሉን ጠጠር የወረወረዉና መንግስቱ ኃይለማርያምን ክዶ አሜሪካን አገር ጥገኝነት የጠየቀዉ የዳዊት ወልደጊዮርግስን መጽሐፍ ከማሰራጨት ጀምሮ፤ አራት ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸዉን (ሄርማን ኮሄን በዉጪ ጉዳይ ሚኒስተር የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት፣ ሮቤርት ፍሩዘር በብሔራዊ ፀጥታ ምክር ቤት የአፍሪካ ከፍተኛ ኦፊሴር፣ ሮቤርት ሆዴክ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ባልደረባ እና ፖል ቢ ሄንዝ የራንድ ኮርፖሬሽን ሠራተኛ) የመሳሰሉ ሰዎችን በመመደብ የቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ ያደረገዉን ያህል፤ ደርግ ከወደቀ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚመርጣቸዉ ተወካዮቹ እንድተዳደር ለማድረግ አሜሪካኖች በፖለቲካው መስክ ያደረጉት ብዙም እገዛ የለም። ዛሬ ድረስ (እስከ 2010 ዓም ማለት ነው) ዋልታና ሬድዮ ፋና የሚባሉ ሜዲያዎች ስማቸውን ቀያይረው የአፍዝ አደንግዝ አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ የሚያሰራጩትን የሕወሓት/ኢህአዴግ የሬድዮ ጣቢያ ሱዳን ዉስጥ ሲያቋቁሙና ድጋፍ ሲሰጡና የደርግን አምባገነን ሥርአት ሲጥሉ የተሻለ ነገር የሚሰራ ሳይሆን የሕወሓት/ኢህአዴግን ሥርአት ለመተካት እንደነበር አሜሪካኖች አላስተዋሉትም ብዬ አልገመትም።

ዓለምን በሁለት ተፃራሪ ፅንፎች ከከፋፈለዉ የምስራቅና የምዕራብ የርዕዮተ ዓለም ክፍፍል አሰላለፍ አንፃር ደርግ የሶሻሊስቱን ቡድን የተጎዳኘ ስለሆነ፤ አሜሪካዊያን ለሰብአዊ ዕርዳታም ቢሆን የሚደርሱት በጣም እየዘገዩ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ከሁለት ነገሮች አንዱ ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል፤ ኢትዮጵያዊያን ሳይወዱ በግድ አምባገነኑን ደርግ የተሸከሙትን በራሳቸዉ ፍላጎት እንደሆነ ቆጥረዋል፤ ወይም አሜሪካኖች ደርግን የሚተካ ሰዉና ድርጅት እስከሚያዘጋጁ ድረስ አለመነካካትን መርጠው ሊሆን ይችላል። ሁለተኛዉ የቅርብ ግምት ሳይሆን አይቀርም እላለሁ። የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት ጥላ እያጠላበት የመጣዉ ኢትዮጵያ ከ1960ዎቹ አጋማሽ በኋላ፤ በተለይም የምስራቁ ሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም በወጣቱ መሀከል እያቆጠቆጠ

መምጣቱን ተመልክተውም ሆነ በደርግ አመራርና በወቅቱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች አቋም አሜሪካ ከምትፈልገው አቅጣጫ ባለመሆኑ፤ አሜሪካ ደግሞ በዚያን ወቅት ወዳጅነቱ ምን ያህል እንደምዘልቅ ባታውቅም፤ ኢትዮጵያ ከሶቭዬቶች ጭራ ሥር መወሸቋ አለማራትም ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ዴቪድ ላምብ (1985፡ 189) እንዳሰመረበት "በአፍሪካ ቀንድ የታየዉ ወደኋላ መገለባበጥ የሚያሳየዉ የአፍሪካ የወደፊት ዕድል በምስራቅና በምዕራቡ እጅ መሆኑንና ሁለቱም ካምፖች አፍሪካን ወታደራዊና ኤኮኖሚያዊ ሀብት ሊያፈሱበት የምትገባ ጠቃሚ አህጉር አድርገዉ የወሰዷት መሆኑን ነዉ፡፡" እንዳለዉ አሜሪካኖች ብሔራዊ ጥቅማቸዉ በሚሉት ወይም በሌላ አይታወቅም ቆይተዉም ቢሆን ፊታቸዉን ወደ ኢትዮጵያ ማዞራቸዉ አልቀረም፡፡ ነገር ግን ፊታቸዉን ቢያዞሩም በዓለምም ሆነ በአፍሪካ በተለይም በሱማሊያ የተከሰተዉ የፀረ አሸባሪነት ትግሉ መሠረታዊ የሕዝቦች ፍላጎት ላይ እንዲያተኮሩ ያላስቻላቸዉ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም፤ አሸባሪነትም ሆነ ሃይማኖታዊ ፅንፈኝነት ለግለሰቦችም ሆነ ለአጠቃላይ ሕዝቦች ፈታኝ አደጋ ስላለው ነው፡፡

ደቪድ ላምብ እንደተነበየዉ አልቀረም፤ የኢትዮጵያን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ የተረዱትና ዳግም ለመቆጣጠር ወታደራዊዉ ደርግ እንደማያዋጣቸዉ የተገነዘቡት የአሜሪካ ባለሥልጣናት ሁለት አቅጣጫ ያለዉ ጦርነት አካሄዱ፡፡ አንድም የሶሻሊስቱ ካምፕ ቁንጮ የሆነዉ ሶቭዬት ሕብረት እንድትፈራርስና በርሷ ተፅዕኖ ሥር የነበሩ አገሮች ሁሉ በተስፋ ቆራጭነት ብዥታ ዉስጥ እንዲገቡ ማድረግ፤ እንዲሁም የሶሻሊስቱ ፈለግ ተከታዩን የኢትዮጵያዉን መንግስቱ ኃይለማርያምን የሚወጉ ኃይሎችን፤ በተለይም ሕወሓትን ሁለንትናዊ ድጋፍ በመስጠት፤ መንግስቱ ኃይለማርያምን በጓሮ በር ወደዚንባቡዌ ሲልኩ መለስ ዜናዊን በፊት ለፊት በር ወደ ፊንፊኔ ምኒልክ ቤተ መንግስት አስገብተዋል፡፡ አሜሪካ ይህንን ሁሉ ዳማ ዓይነት ፖለቲካ ስትጫወት ምስኪኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሜሪካንን የኩራቱ አንድ አካል አድርጎ ይመለከት ነበር፡፡ ያ ኩራት ዛሬም ያነጠፈ አይመስልም፤ ምክንያቱም በማንኛዉም

ጊዜ በኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ የተከፉ ዜጎች እግራቸዉ ሺህ ጊዜ ቢቀጥንም ተጉዘው ተጉዘው ማረፊያቸዉ አድርገዉ የሚያስቡት አሜሪካን ነዉ። የአሜሪካ ፍቅር እፍፍ የሚያደርጋቸዉ ኢትዮጵያዊያን፤ ያኔ ጥንት ሌላዉ ቀርቶ የአሜሪካ ስሪት የሆነዉ ጂንስ የፈለገዉ ዋጋ ተከፍሎበት ይለበስ ነበር። ከሕይወት አድን እገዛ አንፃርም በደርግ ቤታቸዉና መሬታቸዉ የተወረሰባቸዉ የፊዉዳል ልጆች ነፍሳቸዉ ከደርግ ቀይ ሽብር የተረፈዉ በሱዳን አድርገዉ አሜሪካ በመግባታቸዉ ነዉ። በቅርቡ ደግሞ የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በአሸባሪነት ፈርጆ የሚያሳድዳቸዉ ተራ ግለሰቦችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አሜሪካ ዉስጥ እንደልባቸዉ ንጹህ የፖለቲካ አየር እየተነፈሱ አገር ቤት ላለነዉም በአየር የሚልኩልን ከዚያው ከአሜሪካ ነው። ከኢትዮጵያ የመንግስት መሪዎች ደካማነት የተነሳ ለኢትዮጵያዊያን የምሹትን የዕድግት ዉጤት ለማየት እንደማይችሉ በመጠርጠራቸዉ ከሰብአዊ ዕርዳታ ዉጭ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ ለጀርመን ያደረጉትንና የኮሚኒዝምን መስፋፋት ለማቀብ ለኤሽያ አገሮች ያደረጉት ከፍተኛ የልማት ዕርዳታ ለኢትዮጵያ አላደረጉም።

ቀለምን ለይቶ እርስ በርስ እስከሚያጋድለዉ በነጭና ጥቁር ዜጎች መሀከል የሚታየዉ ልዩነት፣ የአገሪቱ አዛዥና ናዛዥ የአገሪቱ አንድ በመቶ የሆኑ ጥቂቶች ብዙኃንን የሚያዙባት የአሜሪካ ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አሜሪካ በአገሯ በዴሞክራሲ አራማጅነቷ ትታወቃለች። ማንም መሪም ሆነ ዜጋ ከሕግ በላይ ለመሆን የሚዳዳዉ ከሆነ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል። በአሜሪካ የዲሞክራሲ አተጋባበርና ሰብአዊ መብት አጠባበቅ ጋር በተያያዘ ከአሜሪካ ዜጎች የበለጠ እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደሰትላቸዋለን። አሁን አንድ ሰሞን አበበ ገላዉ የተባለ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ ፕሬዝዳንት ኦባማ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ጣልቃ ገብቶ ስለኢትዮጵያዊያን ችግር እየጮኼ ተናገረ። ንግግራቸውንም አቋረጠ። ኦባማ የወሰደዉ ወይም ያስወሰደዉ ዕርምጃ ነገር ቢኖር “ቆይ ልጨርስና አዳምጣሃለሁ” ነዉ ያለዉ። አቤቱታዉን ይቀበለዉ አይቀበለዉ የተገለጸ ነገር ባይኖርም፤ በአበበ ገላዉ ላይ የደረሰ የዴሞክራሲ እቀባም ሆነ የሰብአዊ መብት

ረገጣ እንዳልደረሰበት ይታወቃል። ይህ ቢያስደስት እንጂ ክፋት የለዉም። የአገራችን ሕዝቦች ከተገቢ በላይ ሊባል በሚችል ሁኔታ ከአሜሪካዊያን ጋር ፍቅር በመመስረታቸዉ፤ ምስኪኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልጅ እስከ አዋቂ ነጭ ባለፈ ቁጥር አሜሪካዊያን በዓይናችን ሥር ይሄዳሉ። ታሪክ ራሱን ደገመና አፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ እፍ ያለ ፍቅር አድሮበት መጠነኛ አፀፋ እንኳን እንዳላገኘ ሁሉ፤ የኋለኞቹ ኢትዮጵያዊያንም ከአሜሪካዊያን ፍቅር ታዞባቸዉ በአፀፋዉ ግን የኢትዮጵያዊያንን ወገብ የሚያጎብጥ የሕወሓት/ኢህአዴግ አምባገነንነት ከወደ አሜሪካ ሲታዘዝባቸዉ ምን ዓይነት አጋጣሚ እንደሆነ መግለፅ የሚችለዉ ፈጣሪና ጊዜ ብቻ ናቸዉ።

በሦስቱም የኢትዮጵያ መንግስታት (በኃይሌ ሥላሴ፣ ደርግና ሕወሓት) የምናዉቃቸዉ ኤሜሪካዊያን ነጭ ባለፈ ቁጥር ዓይናችን ሥር እንዲቆሙ ያስቻላቸዉ፤ ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ ጋር በተፈራረሙት የፖይንት ፎር ፕሮግራማቸዉ፤ በቅርብ ጊዜ ደግሞ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ግንባታ ሥራ ኢትዮጵያን በመርዳታቸዉና በቀጣይነት በሚመጸውቱት ሰብአዊ ዕርዳታ፤ በዚያ ምክንያትም ባሳደሩብን በጎ ተፅዕኖ (positive influence) የተነሳ ሊሆን ይችላል። በዚያን ጊዜም ቢሆን ዕርዳታቸዉ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር፤ ለምሳሌ ጀርመን ለሁለት ስትከፈል የምዕራቡ ጀርመን የእንዱስትሪ ባለቤት እስከሚሆኑ ድረስ ከጎናቸዉ ቁመዋል፤ የደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮችን ከኮሚንዝም መስፋፋት ለመከላከል ያደረጉላቸዉ ዕርዳታ ዛሬ እነ ሴንጋፖር፣ እንዶኔዢያ፣ ታይላንድ፣ ደቡብ ኮሪያ የደረሱበት ደረጃ (እኔ እንኳን ባላይም ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ የዓይን ምስክሮች ናቸዉና) አማላይ እንደሆነ ይገልጹታል። ደቡብና ሰሜን ኮሪያ ሸረኞች የሰሩባቸውን ወንጀል ከሩቁ ሳያስተውሉ ቀርተው በሁለት የርዕዮተዓለም ጎራ ምክንያት ሲለያዩ፤ ደቡብ ኮሪያ ዛሬ ከደረሰችበት ደረጃ ለመድረስ የአሜሪካ ዕርዳታ የአንበሳ ድርሻ ነበረዉ ብንል የተሳሳትን አይመስለኝም። ዛሬም ቢሆን በደቡብ ኮሪያ ዉስጥ የሚፈሰዉ የአሜሪካ ንዋይ ቀላል የሚባል አይደለም። ነገር ግን የአሜሪካን ዕርዳታ ለአፄ ኃይሌ ሥላሴ እየደረሰ በነበረበት ወቅት

የኢትዮጵያ  የመሬት ይዞታ ባለመሻሻሉ ኢትዮጵያዊያን በምግብ እህል እንኳን ራሳችንን ሳንችል የኖርንበት ዘመናት ከኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ዘመን ጋር ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ነዉ። እንዲያዉም በንጉሱ የአገዛዝ ዘመን መጨረሻዎች አከባቢ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት በኩል የተከሰተዉ ጠኔ ዜጎቻችንን አረግፏል። በተለያዩ ስሞችን ሥራዎች የኢትዮጵያን ጓዳ ጎድጓዳ ሲያስሱ የነበሩ አሜሪካኖች በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር መሪዎች ላይ በጎ ተፅዕኖ ለማሳረፍ ባለመቻላቸዉ ግንባራችን ብንቋጥርባቸዉ የመራር ዕዉነቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ይገባቸዋል ብዬ አስባለሁ።

በደርጉ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያና የአሜሪካ መንግስታት ግንኙነት የአጥፊና የጠፊ ግንኙነት ዓይነት ስለነበረ፤ የአሜሪካ መንግስት በደርግ ሥር ለነበረችዉ ኢትዮጵያ እገዛ ማድረግ ቀርቶ፤ ብዙ ኢትዮጵያዊያን እንደሚስማሙበት ደርግ ለኢትዮጵያዊያንም አደገኛ ስለነበረ፤ የአሜሪካኖች እገዛ ቀርቶብናል ብለን ማማረር አይቻልም። በሚያስመሰግናቸዉ አኳኋን እንኳን ባይሆን ደርግን ለማዉረድ ሕወሓትን ረድተዉልናል። እገዛቸዉን ጥቁር ነጥብ እንዲያጠላበት ያደረገዉ ደግሞ ሕወሓትን ለመርዳት ያን ያህል ዋጋ ከፍለዉ ለሥልጣን ሲያበቁ፤ በተጓዳኝም ስለዲሞክራሲና በአመለካከት የሚለያዩ ዜጎችን አቻችሎ ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚያተጋ ሥርዓት እንዲፈጠር አልነገሯቸዉም። ያለመንገራቸዉም ማረጋገጫም ፕሬዝዳንታቸዉ ኦባማ “ዴሞክራሲያዊ መንግስት አላችሁ” ብሎ ቁስላችን ላይ እንጨት ባልሰደደ፣ ጨዉ ባልነሰነሰ ነበር።

በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ አሜሪካዊያን ጥሩም መጥፎም ሚና ነበራቸዉ/አላቸዉ። የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ መልክ ለመስጠት የሞከሩት እነ ዶ/ር ሰናይ ልኬ፣ ዶ/ር አንድሪያስ እሼቴ የተማሩት ኃያሏ አሜሪካን አገር ነዉ። በ1953 በተደረገዉ መፈንቅለ መንግስት ዉስጥ ተሳታፊ የነበረዉና የኃይሌ ሥላሴን የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በመነቅነቅ የራሱን አሻራ አኑሮ ያለፈዉ የጀኔራል መንግስቱ ንዋይ ወንድም ግርማሜ ንዋይ የአሜሪካዉ አገር የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም

አቀፍ ግንኙነት ተማሪ ነበር። እነዚህንና ሌሎች የአሜሪካን ውርስ በመባል የሚጠቀሱ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። የፖይንት ፎርን ድጋፍ ጨምሮ ዛሬም ቢሆን በግልፅም ሆነ በስዉር ሊንቀሳቀሱባቸዉ የሚችሉባቸዉና ለሕወሓት/ኢህአዴግ ጥንካሬ እገዛ የሚያደርጉ እነ ዩኤስኤይድ፣ ፓዝፋይንደር፣ ፉድ ፎር ሃንገር፣ እና ሌሎች ረጃጅምና ጠንካራ ክንድ ያላቸዉ ድርጅቶችን አሜሪካኖች ኢትዮጵያ ዉስጥ አላቸዉ።

ከዚህ በተቃራኒዉ ቀላል ነዉ የማይባለዉ የአሜሪካን መንግስት አስተዋጽኦ ኃይሌ ሥላሴ በዓለም ፖለቲካ ዉስጥ ለነበረዉ የጎላ የፖለቲካ ተሳትፎ የአሜሪካዊያን አስተዋጽኦ ትልቅ ቢሆንም፤ ኃይሌ ሥላሴ ለኢትዮጵያዊያን ማድረግ የነበረበትን የመንግስት ግዴታ እንዲወጣ ግፊት ያደረጉበት አይመስልም። ልክ የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ጂን በዴል በካሳና የዩጋንዳዉ ኢዲ አሚን በሕዝቦቻቸዉ ላይ ይፈጽሙ የነበረዉን ጭካኔ፤ አፄ ኃይሌ ሥላሴም በኢትዮጵያዊያን ላይ ሲፈጽምና ሲያስፈጽም አሜሪካዊያን ከብሔራዊ ጥቅማቸዉ አንፃር ብቻ በማየት የኢትዮጵያዊያን ጉስቁልና ደንታም እንዳልሰጣቸዉ ማረጋገጫዉ የአሜሪካ ወዳጅ የሆነው ንጉስ ኃይሌ ሥላሴ በ1967 ከሥልጣን ሲወርድ፤ ኢትዮጵያ የነበረችበትን የድህነት ደረጃን መገመት ብቻ በቂ ነው።

ከንጉስ ኃይሌ ሥላሴ ወዲህ ወደ ነጩ ቤተ መንግስት የተመላለሰዉ የኢትዮጵያ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ነዉ። በዚህ የሕወሓት/ኢህአዴግ መንግስትም የኢትዮጵያዊያን ስብእና ከትቢያ ተደባልቆ እየታየ፤ የኢትዮጵያዊያን አቤቱታ ሳይደመጥ ከመቆየቱም በላይ፤ ጋዜጠኛ አበበ ገላዉ በአደባባይ እንዲጮኽልን አስገድዷል። ሱዳን ዉስጥ የሚገኘዉን የአሜሪካንን ኤምባሲ መረማመጃ በማድረግ ደርግን አፍርሶ ሕወሓትን ለሥልጣን ያበቃዉና በኋላም በኢትዮጵያ የዜግነትና የመኖሪያ ፈቃድ ያገኘዉ ፖል ቢ ሄንዝ (2007፡ 108) ልቦናችን የሚያዉቀዉን እዉነት ለመሸፋፈን ሲባል *"... I had not been in the U.S Government for ten years, and that I felt free of all constraints of government status; [but] I had no basic disagreement with U.S. Government politics*

*on Ethiopia and the Horn of Africa.”* በማለት በአሜሪካን መንግስት ድጋፍ ለመፈንቀል ለተንገዳገደዉ የመንግስቱ ኃይለማርያም መንግስት ሲያትት፤ ዋሽንግቶን ላይ አይሁን እንጂ ካርቱም ዉስጥ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹና አዲስ አበባ ዉስጥ ከሚገኙ የአሜሪካ ኤምባሲ ዴፕሎማቶች ጋር የእርሻ ምርምር ፕሮጋራሙን ተገን በማድረግ፤ ሕወሓትን ለሥልጣን የማዘጋጀት ቀላል የማይባል ሥራ ሰርቷል። ያ ባይሆን ኖሮ አፕሪል 3 እና 5፣ 1990 እንደቅደም ተከተላቸው ጠዋትና ከሰዓት በኋላ እራትን ጨምሮ የሕወሓቱን ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊን ወደ ዋሽንግተን ጠርቶ ስለወደፊት የሥልጣን መደላድል ባላወያየ ነበር። እዚህ ላይ ያ ሁሉ ችግር ባይሆንም ሕወሓት/ኢህአዴግ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ያደረጉት የያኔ  ጥረትም ሆነ እስከ ዛሬዋ የአሜሪካ መራሄ መንግስት ኦባማ ድረስ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አካሂዳችኋል ብለዉ ባላሾፉና ቁስላችን ዉስጥ እንጨት ባልሰደዱ ነበር።

በ1983 አሜሪካኖች ለሕወሓት/ኢህአዴግ የአዲስ አበባ ሥልጣን መዉሰድ ዕዉቅና በሰጡበት ሂደት ዉስጥ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ያሉት ነገር ቢኖር “ዴሞክራሲ ከሌለ ዕርዳታ የለም” የሚል እንደነበረና ከዚያን ወዲህ ዲሞክራሲዉ ባይኖርም ዕርዳታዉ ግን አልተቋረጠም። በአሜሪካኖቹ ጫማ ዉስጥ ራሳችንን አስቀምጠን ብንመለከት ደግሞ የአሜሪካኖችን ፈለግ መሪዎቻችን የሚባሉ አለመከተላቸዉ አሳዝኖናል ብንል ሚዛናዊነታችንን ያረጋግጥልናል። ምክንያቱም፤ አሜሪካኖቹ እገዛ ከማድረግ በበለጠ ዴሞክራሲያችንን እንዲሰሩልን መጠበቅ የለብንም።

ሁለት በተፃራሪነት የሚጋጩ ሐሳቦች ከወደ አሜሪካ በኩል ይደመጣሉ። እዚያዉ በአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ካርተር ሴንተር እና ግለሰብ ባለሥልጣናት ሳይቀሩ፤ በኢትዮጵያ ዉስጥ የምርጫ መዛባት፣ የዴሞክራሲ መደፍጠጥና የሰብአዊ መብት መደፈር እጅጉን እንደሚያሳስባቸዉ ሲናገሩ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ እስከ ኦባማ ድረስ ያሉ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል፣ በውጪ ጉዳይ ሚኒስተር የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊዎችና ፕሬዝዳንት ኦባማ ጭምር የኢትዮጵያ

መንግስት አመራር በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንደተመረጠ ይናገራሉ። እንዲያዉም ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነች ሱዛን ራይስ በሟች ጠቅላይ ሚኒስቴር የቀብር ሥነ ሥርአት ላይ ተገኝታ “ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ አባቷን እንዳጣች” በመናገር በሌላ ገጹ የምናዉቀዉንና ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ምንም ፍቅር ሳያትርፍ ሁለት ሞት የሞተን ሰዉ አንገት አስረዝማለች። አንዳንድ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ከሚጠበቅባቸዉ አግባብ ውጭ በመዉጣት ለኢትዮጵያ ገዥ ፓርቲ የሕወሓት/ኢህአዴግ በማድላት  የሕግ አዉጪዎቻቸዉን ወይም የምክር ቤት አባላት ላይ ተፅዕኖ እስከመፍጠር (lobby) ድረስ ሄደዉ የተዛባ መረጃ በማስተላለፍ የአገራችን የፓርቲ ፖለቲካ በነፃነት እንዳያድግ ጫና እስከ ማድረግ ደርሰዋል። ይህ ብቻም አይደለም የአሜሪካ ፖሊሲ አዉጪዎችን አእምሮ መጠምዘዝ የሚችሉ ጸሐፊዎች ሳይቀር ለሕወሓት/ኢህአዴግ ወግነዉ ለሰብአዊ መብት መደፈርና ለዴሞክራሲ በኢትዮጵያ መጨፍለቅ ደንታም እንደሌላቸዉ አሳይተዋል። ላቮስ አላን (1998፡36) እንደገለጸቸዉ *“Henze, [an American who worked for RAND corporation and staunch supporter of EPRDF], who has been involved in research on Ethiopia from the Haile Sellassie era, has been criticized for being too sympathetic to the current government and for closing his eyes to the human rights violations and undemocratic practices of the EPRDF.”* ብላ በጥናቷ ዉስጥ የፃፈችዉ አንድ ማስረጃ ነዉ።

በሌላም በኩል ሕወሓትን በማቋቋምም ሆነ ረጅሙን ጉዞ በማስጓዝ የሕወሓት የራሱ ድርሻ የጎላ ሥፍራ እንደሚይዝ መካድ ባይቻልም፤ ሕወሓት ከትግራይ ነፃ አዉጪነት ወደ ኢትዮጵያ ነፃ አዉጪነት ደረጃ እንዲሸጋገር የአሜሪካን መንግስት ሚና ያን ያክል ቀላል ተደርጎ የሚወሰድ አይሆንም። ሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ለመያዝም ሆነ ሥልጣን ላይ ለመቆየት  የአሜሪካን መንግስት ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑና በተለይም ዓለም አቀፍ አሸባሪነትን ለመታገል በሚል ሰበብ አሜሪካኖች ሕወሓት የሚመራዉን መንግስት እንደልባቸዉ እየተጠቀሙበት ስለሆነ፤ ከ1983/1991 ወዲህ ሌላ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ፓርቲ ማገዝ ቀርቶ

ሕወሓት/ኢህአዴግን የሚግዳርደር ሌላ ፖለቲከኛ ሲያጋጥም፤ አንድም እንደ1984ቱ ኦነግ በታትኖ ለምት ማዘጋጀት ነዉ፤ ወይም እንደ 1997ቱ ምርጫ ጊዜ በቪኪ ሀድልስተን ያለዕረፍት በመስራት የቅንጅት የአዲስ አበባ ምርጫ ወንበር እንዲያጡ ማድረግና እስር ቤት እንዲታጎሩ ማድረግ የአሜሪካኖች ሴራ አንዱ አካል ነው፡፡

ከዚህ በተፃራሪ ግን አንዳንድ ግለሰቦች አሜሪካ ለሕወሓት/ኢህአዴግ ተከላካይነት ጠበቃ ቆማ በክሮሽያ፣ ቱኒዚያ፣ ሊቢያ፣ ግብፅ፣ እንዳደረገች ሁሉ በኢትዮጵያም የቀለም አብዮት እንዲካሄድ መንገድ ለማመቻቸት በናሽናል እንዳዉሜንት ፎር ዲሞክራሲ ተቋም ውስጥ ጥናት እንዲያካሄዱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን (ዶ/ር መረራ ጉዲናን በምሳሌነት በመጥቀስ) ትጋብዛለች ብለዉ ያላዝናሉ፡፡ በተቋሙ ዉስጥ የሰለጠነዉና ጥናታዊ ወረቀት ያቀረበዉ የዶ/ር መረራ ጩኸት ሳይደመጥ ቀርቶ፤ ፕሬዝዳንት ኦባማ ያረጋገጠዉ ሐቅም የጥናቱ ተቃራኒ ሆኖ፤ የአሜሪካ መንግስት ከሕወሓት/ኢህአዴግ ጎን መሆኑንና ሌሎች የአሜሪካ ባለሥልጣናት ዲሞክራሲ ተደፈጠጠ፣ ሰብአዊ መብት ተረገጠ የሚሉት ከማላዘንና የሽፋን ቶክስ ከመስጠት ያላለፈ ጉንጭ አልፋ ንግግር መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡ ነገር ግን የሽግግር መንግስቱ ማቋቋሚያ ኮንፈረንስ ሊካሄድ ሲልና ከዚያም በኋላ እነ ፖል ሄንዝ የተንቀሳቀሱት የተባለዉ የአሜሪካዉ የጥናት ተቋም በመደበላቸዉ በጀት በመሆኑ ናሽናል እንዳዉመንት ፎር ዲሞክራሲ የረዳዉና እስካሁንም እየረዳ እንደሆነ የሚጠረጠረዉ ተቃዋሚዎችን ሳይሆን የተለመደዉ ሕወሓትን ነዉ፡፡ ለዚህ ደግሞ አስረጂ ሊሆን የሚችለዉ የአሜሪካ መንግስት በዲሞክራሲ መደፍጠጥና በሰብአዊ መብት መደፈር ምክንያት በብዙ የዓለም አገሮች መንግስታትና የፓርቲ መሪዎች ላይ የሚያሳርፈዉን የፖለቲካም ሆነ የኤኮኖሚ ጫና በሕወሓት/ኢህአዴግ አባላትና መንግስት ላይ ለማሳረፍ አልጨከነም፡፡ በርግጥ ከላይ በተጠቀሱት አገሮች ዉስጥ ብጥብጥ ተነስቶ የነበረ መሆኑ ባይካድም፤ ተጠያቂ የሚሆኑት ግን የአሜሪካኑ የጥናት ተቋም ወይም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸዉ ሳይሆኑ፤ አንድም ያለ ምርጫ ወይም በዉሸት ምርጫ

ሥልጣን የያዙና ሥልጣን ላይ የቆዩ አምባገነን የኢህአዴግ ገዥዎች ናቸዉ፡፡ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂዉ አምባገነናዊ የሕወሓት/ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያ ሥርአት ይሆናል እንጂ የአሜሪካ ተቋም ወይም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አይሆኑም፡፡ ከላይ የተጠቀሰዉ ውንጀላ ለምን እንደተሰነዘረ ከጥርጣሬ በዘለለ ሁኔታ የምናስበዉ አንድ የአምባገነኖች ባህርይ አለ፤ ይኸዉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚደርስባቸዉ ተፅዕኖ አመፅ እንዲያነሱና በዚሁ ሰበብ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ብቻ ሳይሆን ፊት የነሳቸዉን ገለልተኛ ዜጋ ሳይቀር ለማሰር፣ ከሥራ ለማባረርና ሌሎች እርምጃዎችን ለመዉሰድ ለማሴር እንደሆነና እንዲያዉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምንም ሳያደርጉ ቢቀሩ፤ በምንቀሳቀሱበት ቦታዎች ሁሉ እየተከታተሉ ለጥቅማቸዉ ያደሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አስመሳይ አባላትንና ሰላዮችን በመግዛት በሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዉስጥ በማሰረግ ረብሻ እንዲያነሱባቸዉና እንዲበታትኗቸዉ ያሴራሉ፡፡ ሕወሓት በሸረበው ሸር የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) እና ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተበተኑ ናቸው፤ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ደግሞ በሸሩ እንድንገዳገድ ተደርጓል፡፡

አሜሪካ ከማንኛዉም የዓለም አገሮች የኃይሌ ሥላሴን፣ የደርግንና የሕወሓትን ፖለቲካ በመቃወም የሚሰደዱትን የኢትዮጵያ ዜጎችን በማስጠጋት የዋለችዉ ዉለታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የኃይሌ ሥላሴና የሕወሓት መንግስቶችን በመደገፍ ሂደት ዉስጥ ኢትዮጵያዊያን እንዲጎዱ ለፈጸሙት ወንጀል (በ1983 ሕወሓት አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ጊዜ በአበሻ ቀኝ አክራሪዎች በአሜሪካን ኤምባሲ ፊት ለፊት ከተደረገዉ ሰላማዊ ሰልፍና ከተወረወረዉ ድንጋይ በስተቀር)፤ ቂም በቀል ተይዞባቸዉ ቆንጥር ሳይቆነጠጣቸዉ፣ ጠጠር ሳይወረወርባቸዉ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከባለአምስት ኮከብ ሆቴል እስከ ተራ መሸታ ቤት ተዘዋዉረዉ ይዝናናሉ፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ አሜሪካንን በመቃወም ወይም በመጥላት ደረጃ የተከሰቱ ድርጊቶች ተመዝግበዉ ነበር ቢባል እንኳን ከኃይሌ ሥላሴ መንግስት መዉደቅ ጋር

የአሜሪካ መንግስት ከኃይሌ ሥላሴ መንግስት ጋር ወግኖ ለንጉሱ የሰጠዉ ድጋፍ ኢትዮጵያዊያንን ጎድቶ ስለነበረና በተለይም ደርግ የመረጠዉ ሶሻሊስት የፖለቲካ መስመር ለአሜሪካኖች ባለመጣሙና በዚህም የተነሳ የአሜሪካ መንግስት ተቋማት ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተደረገበት ሁኔታ ለአሜሪካ መንግስት አስተዳደሮች ጥሩ ስሜት አልፈጠረባቸዉም ነበር። ከዚህ ሌላ በቀበሌዎች አስገዳጅነት ሰልፍ ወጥቶ በአብዮት አደባባይ ከመንግስቱ ኃይለማሪያም ፊት ቁሞ ወይም የደጀን ወረዳ አስተዳዳሪ ቆምጬ አምባዉ ዓይነት ዙሪያ ሆኖ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ለመደመሰስ መፈከር ከማንሰት የዘለለ አንዳች የሆነ ነገር በአሜሪካ ዜጎች ላይ የፈጠረዉ ችግር አልነበረም። በመደገፍም ሆነ በማፍረስ ሥራቸዉ ዉስጥ አሜሪካኖች በሌሎች አገሮች ዉስጥ የንብረት ብቻ ሳይሆን የሕይወት ዋጋ እንደሚያስከፍላቸዉ እያወቁ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለሕወሓት ወግነው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በነፃነት የሚያንቀሳቅሳቸው አልነበረም።

የአሜሪካ ፖለቲከኞች ለኦሮሞ ፖለቲከኞች ያላቸው አመለካከት እስከዛሬም ቢሆን ሾላ በድፍን ነው። ይህ ከምን እንደመነጨ መናገር የሚችሉት ራሳቸው አሜሪካኖች ቢሆኑም፤ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቁጥር አኳያ የኦሮሞ ሕዝብ ከፍተኛ መሆኑና ካለበት የቦታ አቀማመጥ የተነሳ እንዲህ በቀላሉ አይታዘዝም ብለው ዕምነት ካለመጣቸውም በላይ የኦሮሞ ብሔር ሕዝብ ሙስልም የሚበዛበት ስለሆነ ወደ እስልምና አክራሪነት ሊያደላ ይችላል ብለው በመስጋታቸው የኦሮሞ ፖለቲከኞች ላይ ዕምነት አልጣሉም ይሆናል። ለአብነትም፤ ብዛት ያላቸዉ የሐበሻ ተወላጆች ወደ አሜሪካ መጓዝን የዉሃ መንገድ ሲያደርጉ፤ የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊን ጨምሮ ብዙ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ከወዳጆቻቸዉ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ለጉብኝት ወደ አሜሪካ ለመጓዝ ስፈልጉ ቪዛ አይመታላቸዉም።

ከሃያ አምስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ የሕወሓትን ቀይ መስመር ላለማለፍ ሲባል በአሜሪካ ላይ ጣቱን የቀሰረ ማንም አልነበረም።

የሕወሓት/ኢህአዴግ መሪና የአሜሪካ ታላቅ ወዳጅ የነበረዉ መለስ ዜናዊ ከሞተ በኋላ አፍቃሬ ሕወሓት/ኢህአዴግ የሆነዉ ሪፖርተር ጋዜጣ በቅፅ 17 ቁጥር 50/1288 የእሁድ፣ ነሐሴ 27 ቀን 2004 ዕትሙ ላይ፤ የአቶ መለስ ዜናዊን ሞት አስመልክቶ ባለራዕዩን መሪ ለምን አጣን በሚል አርእስት ሥር "የአገራቸዉ የዕድገት ሞተር የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ … ለመጨረሻ ጊዜ ለሕልፈተ ሕይወታቸዉ መዳረሻ ከሆነዉ በአሜሪካን በተዘጋጀዉ የስምንቱ የበለፀጉ አገሮች ጉባኤ ላይ ተገኝተዉ ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸዉ እንኳን በቅጡ ሳይነገር፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መታመማቸዉና ለሕክምና ወደ ውጪ አገር የሄዱ መሆኑ ዘገይቶ ተገለፀ። … ነሐሴ 15 ቀን 2004 ዓም ላይ ዜና ዕረፍታቸዉ በሜዲያ ተነገረ [ካለ በኋላ] … መሪም ይሁን ሳይንቲስት አሊያም ተራ ሰዉ በሞት ሊያልፍ ተፈጥሮአዊ ግዴታዉ ነዉ። ሆኖም ግን አንዳንድ አማሟቶች በልብ ዉስጥ ጥርጣሬ የሚያጭሩ፣ የሚያስቆጡ፣ አንጀት የሚበሉና መሪር ሐዘን ይሆናል" በማለት ስለእንጂነር ቅጣዉ እጅጉና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአሜሪካ ዉስጥ እና ከአሜሪካን ጉዞ መልስ አማሟታቸዉ ፈራ ተባ እያለም ቢሆን የተሰማዉን ጥርጣሬና ሐዜነታውን ገልጿል። ሪፖርተር ጋዜጣ አሜሪካ ላይ ያለዉን ጥርጣሬ በዚህ ዓይነት ሁኔታ አስተያየት ይሰጥበት እንጂ ምስኪኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአሜሪካን እና በኢትዮጵያ መንግስታት መሀከል ያለዉን መሞዳሞድ አጥርቶ ያዉቀዋል።

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ወዲህ በተለይም ከሶቪዬት ሕብረት መፈረካከስና ከሶሻሊስቶች መበታተን ወዲህ እንዲሁም ዜጎቻቸው ሶማሊያ ውስጥ የኃይል እርምጃ ከተወሰደባቸው ወዲህ፤ አሜሪካኖች በሌሎች አገሮች በተለይም በአፍሪካ ውስጥ የሚወስዱት ፖለቲካዊ እርምጃ እዚህ ግባ የማይባል ሲሆን፤ ነገር ግን በ1997 በሕወሓት/ኢህአዴግ እና ቅንጅት በሚባለዉ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሀከል ግጭት ተከስቶ በነበረበት ወቅት የአሜሪካን መንግስት ኤምባሲ ጉዳይ አስፈፃሚ ያለ ምግብና እንቅልፍ ውላ በማደር፤ በአዲስ አበባ ዉስጥ

ብጥብጥ እንዳይፈጠርና ነገሮችን ለሕወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ለማመቻቸት የተጫወቸዉ ሚና በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ ዉስጥ የአሜሪካ መንግስት ሚና አንድ ጥቁር ነጥብ የጣለ ሲሆን፤ ይባስ ብሎም የ2007 የኢትዮጵያ ጠቅላላ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ነበር ብሎ በፐሬዝዳንት ባራክ ሁሴን ኦባማ መነገሩ የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ዕድገት ቁልቁል የመድፈቅ ያህል ነዉ። የባሰ አታምጣ ይላል የሐበሻ ሰው፤ የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ካላቆማችሁ የተመደበላችሁን ዕርዳታ አታገኙም ብለው የወቅቱ የአሜሪካ ፕረዝዳንት በመጨረሻ የሥልጣን ዘመናቸው መወሰናቸው ዛሬም ቢሆን የአሜሪካን መንግስት አስተዳደር ለኢትዮጵያ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑን ያሳያል። አሜሪካኖች ቢረዱልንም ባይረዱልንም በኢትዮጵያ ዉስጥ ሕግ አዉጪም፣ ሕግ አስፈፃሚም ሕግ ተርጓሚም ያዉ ሕወሓት/ኢህአዴግ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሕወሓት/ኢህአዴግን ወንበር የተረከቡ የብልፅግና ፓርቲ አባላት ከመሆን የዘለለ ነገር የለም። አሜሪካኖች ይህንኑ ዲሞክራሲያዊ ነዉ ብለዉ ከሆነ በቁስላችን ዉስጥ እንጨት ሰደዋልና ኢትዮጵያዊያን እያመመን እንደሆነ መግለጹ የግድ ነው። አሜሪካ ከምትቆረቆርላቸው በመካከለኛ ምስራቅ ከሚገኙ እስራኤልና ግብፅ እንዲሁም በእስያ ከምትገኝ ደቡብ ኮሪያ በተጨማሪ በፀረ አሸባሪነት ትግል ዉስጥ ሕወሓት/ኢህአዴግ ለአሜሪካን አስፈላጊዉ እንደሆነ ሁሉ፤ በሁለቱም በኩል ለአሸባሪነት የሚሰጠዉ ትርጉም የተለያዩ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ነገር ግን የሕወሓትን የተዛባ የዕድገት ፖሊሲ የሚያውቁ፣ ኢሰብአዊ እርምጃውን፣ ፀረ ዲሞክራሲነቱና አምባገነንነቱን አሜሪካዊያን አንድም ከኛ በላይ ያዉቁታል ወይም ከኛዉ እኩል ያዉቁታል የሚል ከግምት በላይ የሆነ ግንዛቤ ይኖረኛል። ስለሆነም የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ መዘወር ለአሜሪካኖችም ሆነ ለኢትዮጵያዊያን በተለይም ለሕወሓት/ኢህአዴግ አስተዳደሮች ምንም አይጠቅምም። ከዚህ ጋር አሜሪካዊያን ሊያዉቁት የሚገባቸዉና እንደማያጡትም የሚታሰበዉ ኢትዮጵያም ሆነች የአፍሪካ ቀንዱ ጉዳይ የሚረጋጋዉና በፀረ-ሽብር አቋም ምክንያት አሜሪካ ለወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት የምትሰጠዉ ድጋፍ የተሟላ መልስ ሊያገኝ የሚችለዉ ልክ እንደ

አሜሪካዊያን ኢትዮጵያዊያንም በመረጡት ተወካዮቻቸዉና ኃላፊነት በሚሰማቸው አስተዳዳሪዎቻቸዉ መተዳደር ሲችሉ ብቻ መሆኑ ነዉ። የአንድ ወገን በተለይም በቁጥር አናሳ ከሆነዉ ሕዝብ የሚወጡ ፓርቲዎችን በማገዝ የተከደበት የአሜሪካን መንግስት እርምጃ የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ጉዞ ቢያሰናክል እንጂ ዝንዝር ያህል አያስከድም።

## እንግሊዝ

"አዉሮፓዊ በምንም ዓይነት ለአፍሪካ ዕድገት ተጨንቆ ቅንጣት ያሳሰባቸዉ ነገር አልነበረም። የእነሱ ዕድገት አዉሮፓን እስካልጠቀመ ድረስ ቦታ የለዉም። ሕግና ሥርአት እስከተጠበቀ ድረስ የቀረዉ ሁሉ ሁለተኛ ደረጃ ነዉ።" ብሏል አምባቸዉ ከበደ የአፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ መጻሐፍ ተርጓሚ። በዓለም ላይ በነበራት የቅኝ ግዛት ብዛት የተነሳ እንግሊዝ "ፀሐይ የማትጠልቅበት ኢምፓየር" ተብላ ትታወቅ ነበር። ዛሬም ቢሆን ኮማን ዌልዝ የሚባል ስብሰብ አባላትን በመያዝ ብዙ የሚባሉ አገሮች ዘንድ ተደርሳለች። በአገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ ይኸ ሰዉ እንግሊዝ ነዉ ከተባለ ድብቅ ባህርይ እንዳለዉ ለማመላከት እንደሆነ በቃል ከሚተላለፉት አባባሎች ለማወቅ ይቻላል። ድብቅ ባህርይ በጎጂነቱ እንጂ በገንቢነቱ እንደማይታወቅ እየተረዳን፤ እንግሊዝ እንዴዚህ እንዲትባል ያስቻለው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወራሪውን የጣሊያንን ኃይል ከኢትዮጵያ ካባረረች በኋላ በወታደራዊ የበላይ ጠባቂነት ስም ኢትዮጵያን የራሷ ቅኝ ግዛት አድርጋ ለመደላደል ያደረገችው ስልታዊ ጥረትን ሰበብ በማድረግ ነው።

አፍሪካዊያን አዉሮፓዊያንን የሚያዉቁት በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ማለትም በባሪያ ንግድ፣ በቅኝ አገዛዝና በስዉር ቅኝ አገዛዝ ናቸዉ። በሦስት መቶ ሃያ ዓመታት የባርያ ሽያጭ ጊዜ ዉስጥ ሃምሳ ሚሊዮን የሚሆኑ በዕድሜ ለጋ የሆኑ ወጣቶች፣ ጡንቻ ያላቸዉና አምራች የሆኑ ዜጎች፣ ወጣት በመሆናቸዉ ተዋልደዉ ትዉልድን መተካት የሚችሉ

አፍሪካዊያን ወደ አረብ አገሮች፣ አዉሮፓና አሜሪካ አገሮች በባሪነት ተግዘዋል። በውጤቱም ለዛሬዋ አፍሪካ በዕድገት የዓለም ጭራ መሆን የሚችልና ይህም ድርጊት በአፍሪካ ዉስጥ የትውልድና የዕድገት ሂደት ክፍተት እንዲፈጠር ያስገደደ እና ለመግለፅ እንኳን የሚያስቸግር የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመበት ድርጊት ነበር።

ከሦስቱ ድርጊቶች ኢትዮጵያ (ኢትዮጵያ ማለት ሲቀነስ ኤርትራ) ከላይ እንደገለፅኩት በሦስቱ ቅኝ ገዥ ኃይሎች (እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን) መሀከል በነበረው መግባባትና በተለያዩ ምክንያቶች በነጮች ቅኝ አገዛዝ አልተጠቃችም። ቅኝ አገዛዝ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ባለመያዟ የቀረባት ነገር ከቁጥር አይገባም ማለት ባንችልም፤ የቅኝ አገዛዝ ከሚያሳድረዉ የሥነ-ልቦና ተፅዕኖ፣ ከድቃላ ፖለቲካ፣ ኤኮኖሚና ባህል ኢትዮጵያ በአንፃራዊነት ነፃ ነበረች ለማለት እንችላለን። ነገር ግን በአጭሩ የጣሊያን ወረራ ሥር ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች በተለይ ደቡቦቹ ገባሮች የመሬት ስሪቱ ቀፍዳጅ ከሆነው የምንሊክና ኃይሌ ሥላሴ የፊውዳል አገዛዝ ነፃ ወጥተዉ ነበር ለማለት ይቻላል። ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ጣሊያን፣ ጀርመን፣ ስፓኝ፣ ፖርቱጋል፣ ሆላንድ፣ ቤልጅግ፣ ሌሎችም አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት የተቀራመቱ ሲሆን፤ ከቅኝ አገዛዝ በፊትም ሆነ በቅኝ አገዛዝ ወቅት በኢትዮጵያ ላይ ሰፊ ተፅዕኖ ለማሳረፍ ከቻሉት አገሮች አንዷ እንግሊዝ ነበረች። እንግሊዝ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ላይ የራሷን ዜጎች በመመደብ እንዳስተዳደረችዉ ሁሉ፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ለየት ባለ ሁኔታ ከፋፋይ የመግዛት ፖሊሲን በመጠቀም በተለይ የኢትዮጵያ ገዥዎችን በማበረታታትና ሕዝቦች ላይ ጫና በማድረግ የእንግሊዝ ተፅዕኖ እንዲስፋፋ አድርጋለች።

የማያባራ ግርምታን ከሚፈጥሩ ነገሮች ውስጥ ከመሃይምነት፣ ከረሃብ፣ ከችግር፣ ከችጋር፣ ከመከራ፣ ከአመፃ፣ ከሽብር፣ ከግጭት፣ ከአምባገነንነት፣ ከሙስና፣ ከመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ ከውሸት፣ ከድህነት፣ ከፍርሃት፣ ከልመና፣ ወዘተ ያልተላቀቀችው ኢትዮጵያ፤ ዛሬ ሰልጥነው የተሻለ

ሕይወት ይመራሉ ከሚባሉ እንግሊዝን ከመሳሰሉ አገሮች ጋር ግንኙነት የጀመሩት ረጅም ዓመታትን እንዳስቆጠረ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ለአብነትም የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ግንኙነት ከመቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ እንደሆነ በጽሑፍ የተቀመጡ ማስረጃዎች ያወሳሉ። ከመቶ ዓመታት በፊት የነበረዉ የእንግሊዛዊያን ዜጎች በኢትዮጵያ መገኘት የግል ጉዳይ የሚመስል ነበር ቢባልም፤ በመንግስት ደረጃ ግን በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ወደ ወቅቱ ኢትዮጵያ አከባቢ መጥቶ የነበረዉን የካፒቴን ዳግላስ ካሜሮን ሰሜናዊ ኢትዮጵያን የረገጠዉ በ1860ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር። አፄ ቴዎድሮስ አገዛዙን በጦር መሳሪያና በቴክኖሎጂ ለማጠናከር የነበረዉ ፍላጎት ከፍ ያለ ስለነበር፤ ይኼው ፍላጎቱ ዳር ይደርስ ዘንድ መልዕክት ጽፎ ለእንግሊዝ መንግስት እንዲያደርስ የተላከው ካሜሮንና ሌሎች የእንግሊዝ ዜጎች መልዕክቱን ባለማድረሳቸው ወደ መቅደላ አፋፍ ተወስደው እንድታሰሩ በመደረጉ የፈጠረዉ ቅሬታ ለቅማንቴዉ ቴዎድሮስ መሞትም ሰበብ ሆኗል።

ለአፄ ቴዎድሮስ ሞት ተጠሪዉ እራሱ አፄ ቴዎድሮስ ቢሆንም፤ የእንግሊዝ ወታደሮችን መርቶ በማስገባት ግን የአፄ ዮሐንስ ድርሻ አነስተኛ እንዳልነበር ሲገለጽ፤ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ይፋዊ የክብር ግንኙነት የተጀመረዉ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግስት እአአ በ1884 ሰኔ ወር ላይ ነበር። የአፄ ዮሐንስ የአገዛዝ ዘመንም በሸዋዎች ሸፍጥና በውጪ ኃይሎች ወረራ ምክንያት ብዙም የተሳካ ባይሆንም፤ በአፄ ዮሐንስ እግር የተተካዉ አፄ ምኒልክ ግን ከእንግሊዝና ከጣሊያን በተገኘዉ መሳሪያ ተጠቃሚ በመሆን የደቡቡን ጎረቤት ነፃ ግዛቶችን ወርሯል። አፄ ምንሊክ ከወረራዎቹ በኋላ በጤና መጓደል ምክንያትም ይሁን አርቆ ለማሰብ ባለመቻል፤ እንደ አዉሮፓዊያኑ ቅኝ ገዥዎች መሠረት ልማትን ማስፋፋት አይቻል እንጂ የአዉሮፓዊያኑን ፈለግ በመከተል ወይም እነሱኑ በመፎካከር ቅኝ ግዛቱን አስፋፍቷል።

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በአዲስ መልክ የተጀመረዉ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሰት፤ በተለይም ከአድዋ ድል ጋር

በአሸበረቀ ሁኔታ በ1896 ነበር። እንግሊዝ ከአድዋ ድል በኋላ ወዲያዉኑ መልዕክተኛ ሲትልክ፤ የተልዕኮዉ ዓላማም በኢትዮጵያና እንግሊዝ መንግስታት መካከል የንግድና የፖለቲካ ግንኙነት ለመመስረትና እንዲሁም በእንግሊዝ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶች፤ ማለትም በሱዳን፣ በኬኒያ በእንግሊዝ ሱማሊላንድ እና በኢትዮጵያ መሀከል ሊፈጠር የሚችለዉን የድንበር ግጭት ለማስወገድ የታሰበ ነበር። ምኒልክም በወረራ የተቆጣጠራቸዉን ነፃ ግዛቶች ላይ የተቀዳጀዉን የበላይነት ለማስረገጥ ወዲያዉኑ በእንጦጦ ሥር ያለ ቦታን አንድ ጋሻ መሬት ለእንግሊዝ ኤምባሲ ሰጡ። ዲፕሎማቶቹ እንግሊዞች እንደ ወታደሩ ናፒየር የሰዉን መሬት ሰጠኼን ብለዉ እንቢ ሳይሉት ተረክበዉ እነሆ ለምኒልክ ቀጣይ ትዉልድም ባለውለታነታቸዉን እያሳዩ ነው። ነገር ግን ምንሊክ ከሞተ በኋላ በራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው ሞግዚተነት ንጉሳዊ ሥልጣኑን የተረከበው ልጅ እያሱ የእንግሊዝ መንግስት እንደሚፈልገው ሆኖ አልተገኘም። ለአቤቶ ኢያሱ የተሰየሙት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው ሁለት ዓመት እንዳገለገሉ ድንገት በመሞታቸው አቤቶ ኢያሱ የመንግስቱን አስተዳደር ጠቅልለው በመያዝ መንግስታቸውን ከጀርመንና ከቱርክ ጋር በማቀራረባቸውም ሆነ በእንግሊዝ ላይ ላመፀው የእንግሊዝ ሱማሌ ባለባት መጠለያ በመስጠትና መሳሪያ በማቀበል ጠርጥሯቸው ስለነበረ የእንግሊዝ መንግስት ደስተኛነት እንዳልተሰማው ተፈራ ሣህለ ሥላሴ ከላይ በተጠቀሰው መፅሐፋቸው ውስጥ በስፋት ገልጸዋል። በዚህ ምክንያትም በኢያሱ ግድያ የእንግሊዝ መንግስት እጅ እንዳለበት የሚጠረጥሩ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉ ፀሐፊዉ ያወሳሉ። ከቤተሰብ ምንጩም ሆነ ከአመለካከት አድማሱ ስፋት ጋር ሲስተያይ ሰፊ መሠረት ሊይዝ ይችል የነበረው ልጅ ኢያሱ በመገደሉ ቀደም ሲልም በኢትዮጵያዊያን መሀከል የነበረውን መጠራጠር ሲያሰፋ፤ እንግሊዞችም ለዚህ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው እሙን ነው።

ከዚህ ሌላ ከእንግሊዞች ጋር መሠረተ ሰፊ ግንኙነት የነበረዉ አፄ ኃይሌ ሥላሴ ነበር። ተፈሪ መኮንን ገና እንደራሴ እያለ እአአ በ1921 ሎንዶንን የጎበኘ አፍሪካዊ ወጣት መሪ ሲሆን፤ ጉብኝቱንም በማስታከክ ኢትዮጵያ

የባህር ጠረፍን አስመልክቶ የነበረዉን ፍላጎት ከእንግሊዝ ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግሯል። ከዚያ በመለስም ግንኙነቱ እየጠነከረ የሄደዉ የኢጣሊያ ፋሽስት ጦር ኢትዮጵያን ወርሮ በነበረበት ከ1928 እስከ1933 ድረስ ንጉሱ ተጠልሎ የነበረዉ እንግሊዝ አገር ባዝ በሚባል ቦታ እንዲሁም በእንግሊዝ ተፅዕኖ ሥር በነበረ አገር (ሱዳን) ዉስጥ ነበር። የጣሊያንና የጀርመን ጦሮች (ሴንተራል ፓወር) አዉሮፓንና እንግሊዝን ጭምር በማጥቃታቸዉ በሌላም በኩል እንግሊዝ በጣና ሐቅ ላይ ሊትገነባ ያሰበችውን ግድብ እንዳትሰራ ያልተገባ ሰበብ በመደርደር ጣሊያን እንቅፋት ስለሆነች ከኢትዮጵያ ለማባረር ሲሉ የንጉሱ የመወሰን አቅምን በሚያሳንስ ሁኔታ ከጎን በመቆም መልሰው ለቤተ መንግስቱ አብቅተውታል። በዚህን ጊዜ እንግሊዞች ሁለት ስሌት ያለዉ ዕቅድ፤ አንደኛዉ ጣሊያንን ከጫና ፈጣሪነት ጨዋታ ለማስወጣትና እግሬ መንገዳቸዉንም ከቅኝ አገዛዝ ባልተናነሰ ኢትዮጵያያን በወታደራዊ የበላይ ጠባቂነታቸዉ ሥር ለማቆየት ነበር።

አፄ ኃይሌ ሥላሴ ከ1928-33 በነበረዉ የስደት ቆይታዉ በእንግሊዝ ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ከበረታ የነበረዉ አፍሪካዊ መሪ የነበረና የፋሽስቶች ወረራም ከኢትዮጵያ አልፎ ለነሱም የሚያሰጋቸዉ መሆኑን ትንቢት የተናገረ ሰው ነበር። እንደተነበየዉም አልቀረም የፋሽስቱ ሞሶሎኒና የናዚዉ ሂትለር ጦሮች ተባብረዉ አዉሮፓን በተለይ ደግሞ ሎንዶንን በመደብደባቸዉ፤ ለዚህም ሰፊ የአፀፋ እርምጃ ለመውሰድ በነበራቸው ዓላማ መሠረት የእንግሊዝ ወታደሮች ከሱዳንና ኬንያ ቅኝ ግዛቶቻቸዉ በመነሳት ለኢትዮጵያ አርበኞች በማገዝ የወራሪዉን የጣሊያንን ጦር ወግተዉ፤ ንጉሱን ወደ ሥልጣን መልሰዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ “እንግሊዝ ለአርበኞችና ለንጉሰ ነገስቱ ያገራቸው ነፃነት እንደሚመለስላቸው ተስፋ የሰጠችው የኢትዮጵያን ነፃነት የማሰመለስ ጉዳይ በመሠረቱ ተገቢ መሆኑን አምነውበት አልነበረም። ዋና ዓላማዋ ሱዳንና ግብፅ [ኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈረውን ግዙፍ የጣሊያን ጦር] እንዳይወረር ለመከላከል” እንደሆነ ተፈራ ኃይለ ስላሴ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገልጸዋል። ከጣሊያን መባረር በኋላ ከንጉሱ ፍላጎት ውጪ እንግሊዞች በኢትዮጵያ

ላይ በበላይ ጠባቂነት ለመቆየት ያደረጉት ጥረት ግን ከንጉሱ ጋር ሳያቀያይማቸዉ አልቀረም። ዘውዴ ረታ ከላይ በተጠቀሰው መፅሐፋቸው ይድረስ ለአንባቢያን በተባለ የመግቢያ ጽሑፍ ላይ "… የዓለም ጦርነት ተፈፅሞ የሰላም ጉባኤ እስኪደረግና ጠቅላላ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ኢትዮጵያ የጣሊያን ኮሎኒ ሆና … በጣሊያን ፋንታ አስተዳዳሪዋ የታላቋ ብሪታንያ መንግስት ነው ብለው መግለጫ አወጡ" ብለዋል። እንዴዚህ ዓይነት ድርጊት ሳይሸሹ ዘር ብለዉ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ማሰባቸዉን ያሳብቃል። እንግሊዞቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ቆይታቸው ወቅት ግን በፋይናንስ አማካሪነት፣ በንግድ አማካሪነት፣ የኢትዮጵያን የፖሊስ ኃይል መልሶ በማቋቋም፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች እንግሊዘኛ እንዲማሩና በኢትዮጵያ የትምህርት መስጫ ትምህርት ተቋማት ዉስጥም የእንግሊዝ ቋንቋ በመደበኛነት እንዲሰጥ አቀነባብረዋል። ለምሳሌም እንደ ጀኔራል ኦርዴ ዊንጌት የመሳሰሉ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝ ሞዴልን ተከትለዉ እንዲቋቋሙ ተደርገዋል። በነገራችን ላይ በመካከለኛ ምስራቅ በተለይም ለእስራኤል በመወገን ሰፊ የስለላ ሥራ በመስራትና እስራኤላዊያንን ያቋቋመው ታዋቂው ጀኔራል ኦርዴ ዊንጌት እአአ 1941 የጣሊያንን ወራሪ ኃይል በመውጋት በኩል ለአፄ ኃይሌ ሥላሴ ወደ አልጋው መመለስ ሰፊ ሥራ የሰራ ሰው ነበር። ከዚህም በተረፈ በኢትዮጵያ ንጉሳዊያን ዘንድ የእንግሊዞችን ተወዳጅነት ከፍ ለማድረግና ለውለታቸዉም ሲባል ተቋማትና መንገዶች (ቸርችል ጎዳና፣ ወቬል መንገድ፣ ካኒጋሃም መንገድ፣ ዊንጌት ትምህርት ቤት) በእንግሊዝ ፖለቲከኞችና ጀኔራሎች ስም እንዲሰየሙ ቢደረግም "… የእንግሊዝ መንግስት ትኩረት ለፊውዳል ስርአቱ ዘመናዊ ቅርፅ ለመስጠት እንጂ ዴሞክራሲያዊ መንግስት እንዲቋቋም ሙከራ ለማድረግ አይደለም" ይላሉ ተፈራ ኃይለ ስላሴ። ለማስረጃም የእንግሊዝ መንግስት ኢትዮጵያን በጦር አስተዳደር ይመራ በነበረበት ሁለት ዓመታት ውስጥ ሥልጣንን ለንጉሱ ከማስረከቡ በፊት የእንግሊዝ ዓይነቱን ርዕሰ ብሔርነት በፓርማው መስተዳደር ሥር ማድረግ ይችል እንደነበር ተፈራ ኃይለ ሥላሴ የእንግሊዝን መንግስት ሸር በትክክል አስቀምጠዋል። ከዚህ በተረፈ ግን ብዙም ዕድገት ያልታየበት ግንኙነታቸው ለታይታ በሚመስል

መልኩ እአአ በ1945 ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በልዕልት ኤልሳቤጥ ንግስ ዝግጅት ላይ ከመገኘቱም በላይ እአአ በ1958 ንግስቲቱም ኢትዮጵያን ጎብኝታለች።

ይህ ብቻም አይደለም፤ እንግሊዞች ጣሊያንን ከኤርትራ በማስወጣትና ለአስር ዓመታት በወታደራዊ የበላይ ጠባቂነት ካስተዳደሩ በኋላ፤ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንዲትቀላቀል ለኃይሌ ሥላሴ ወግነዉ ሰርተዋል። በመቀጠልም በኃይሌ ሥላሴ መንግስት ላይ የተነሱ የራያ፣ የባሌና የጎጃም ገበሬዎች አመፅን ከየመን ቅኝ ግዛታቸው በመነሳት በአየር በመደብደብ የተለያዩ ወታደራዊ፣ ቁሳዊና ቴክኒካዊ ዕገዛዎችን በማቅረብ የኃይሌ ሥላሴን መንግስት ረድተዋል። ተቋረጠ ተብሎ ባይደመደምም እንኳን የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ግንኙነት የተቀዛቀዘዉ በአብዮቱ ጊዜ ከ1967 እስ1980 ለአስራ ሦስት የደርግ አገዛዝ ዓመታት ነበር። ይህም ሊሆን የቻለዉ በወቅቱ ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረዉ ደርግ አቋሙ ከምዕራባዊያን ካፒታሊስቶች ይልቅ ወደ ምስራቁ ሶሻሊስቶች በተለይም ወደ ሶቭዬት ሕብረት በማጋደሉ ነበር። በዚህን ጊዜ ዉስጥ አነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴና ከአሜሪካኖች ጋር የስለላ ሥራ ከሚሰሩ፤ እንዲሁም ለኢትዮጵያዊያን ሰብአዊ ዕርዳታን ከሚሰጡ ጥቂት የእንግሊዝ ድርጅቶች በስተቀር ኢትዮጵያ ዉስጥ አይንቀሳቀሱም ነበር።

ግንኙነቱም በኦፊሴላዊ መንገድ ከሚያደርጉት የንግድና ሰብአዊ ዕርዳታ ጎን ለጎን የደርግን መንግስት ለሚቃወሙ ንቅናቄዎች፤ በተለይም ለሕወሓት ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ ቦብ ገልዶፍ የተባለዉ አርቲስት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዝብ በድርቅና በረሃብ ለተጎዱ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ለመርዳት ከበጎ አድራጊዎች የሰበሰበዉን ገንዘብ ከ90 በመቶ በላይ ለሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ/ሕወሓት ሰጥቷል። ሕወሓትም ለጦር መሳሪያ ግዥና ለሕወሓት ባለሥልጣናት ጥቅም በውጭ አገር ባንኮች ጭምር እንዲያካብቱ ተደርጓል። ይህ ደግሞ ከእንግሊዝ መንግስት ዕውቅና ውጭ የተከናወነ አልነበረም ተብሎ ቢገመት ግምት ብቻ ተደርጎ የሚጣጣል አይሆንም። ሕወሓትም ከክልሉ

ተወላጆች ያላሰለሰ ድጋፍና በውጪ ፀረ ደርግ ኃይሎች ድጋፍ በ1983 ሥልጣን ሲይዝ፤ የእንግሊዞች የሞራልም ሆነ የማቴሪያል ድጋፍ ከአጠገቡ አልጠፋም። ለመጥቀስም የሕወሓቱ መሪ የመጨረሻ የሥልጣን ርክክብ ሥነ-ሥርአቱን የጀመረዉ በአሜሪካን አስተባበሪነት በሎንዶን አስተናጋጅነት ነበር።

ከ1983 የሽግግር መንግስት ምስረታ ወዲህ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ መንግስታት ግንኙነት በተጠናከረ ሁኔታ ቀጥሏል። ሪቻርድ ፓንክራስት (1996፡ *18) እንዲህ በማለት ምስክርነቱን ጽፏል።* "Bilateral cooperation gradually increased during the period of the Transitional Government, this was followed, with the establishment of the Federal Government, by the first bilateral aid talks. These focused particularly on education, agriculture, the police and revenue collection, and set the path for future cooperation." *ብሎ ፅፏል።*

ከዚህ በላይ ሪቻርድ ፓንክራስት እንደአብራራዉ ኢትዮጵያን የመሳሰሉ ድሃ አገሮችን የበለፀጉ አገሮች መርዳት የተለመደና ምስጋና የሚቸረዉ ቢሆንም፤ ነገር ግን ዕዉቀት ያልዞረበት ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ ዉድቀት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነዉን የትምህርት ፖሊሲ እንግሊዞች እጃችን አለበት ማለታቸዉ አሳዛኝ እንደሆነና አሁንም እንዳለ የኢትዮጵያዊያን ጩኼት ነው። በዕዉቀት ላይ የተመሠረተ ዕገዛ የተደረገላቸዉ የደቡብ ምስራቅ እስያ አገሮች በአገኙት እገዛ ዛሬ የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ለማስመዝገብ የፈጀባቸዉ ጊዜ ከ25-30 ዓመታት ዉስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሕዝቦች ተርታ ሲሰለፉ፤ በአደገዉ የእንግሊዝ መንግስት የታገዘዉ የኢትዮጵያ ግብርና ግን እስከዛሬም በምግብ እህል ራሳችንን አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን በእነሱ እገዛ ያደገዉ የግብርና ኤኮኖሚያችን የተፈጥሮ ክስተት የሆነዉን ድርቅን ለአንድ ዓመት እንኳን መቋቋም እንዳልቻለና ሌላው ቢቀር እንኳን ለኢትዮጵያ ግብርና ማዳበሪያ አቅራቢ ድርጅት አንድ ብቻ፤ ለዚያም የገዥዉ ፓርቲ የንግድ ድርጅት አምባሴል ብቻ መሆኑ እንግሊዞችን ምን ያህል ትዝብት ላይ እንደሚጥላቸዉ

መገመት አያዳግትም።

ከዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ ደግሞ የዜጎችን ሰብአዊ መብት መዳፈር ቀርቶ ምርጫቸዉን ከማክበር ውጭ የትም ውልፍት የማይባልበት፣ ከሕግ አግባብ ውጭ ማንንም እንግሊዛዊ መቆንጠጥ እንኳን የማይችለዉ የእንግሊዝ የፖሊስ አመራር በሕዝብ ላይ የሚተኩስ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጽህፈት ቤት ሰብሮ የሚበረብር፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን አሳድዶ የሚያስር፣ በይስሙላ ምርጫ ጊዜ ኮሮጆ የሚጎትት የኢትዮጵያ ፖሊስ ለማሰልጠን እገዛ አድርጌያለሁ ማለቱ ከማሳዘን በላይ የሚያሳፍር ይሆናል። በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ፖሊስ መዋቅራዊ አደረጃጀት የፈረሰዉ ሁለት ጊዜ ሲሆን ቀዳሚዉ በጣሊያን ወራሪ ኃይል ሲሆን ድኃሚዉ የፈረሰው ሕወሓት/ኢህአዴግ በ1983 በድል አድራጊነት አዲስ አበባ ሲገባ ነዉ። ያጋጣሚ ይሁን የታቀደ ሁለቱንም ጊዜ መልሶ የማደራጀቱን እገዛ ያደረገዉ የእንግሊዝ መንግስት መሆኑ ነዉ። የአንድ ተቋም መፍረስ ማለት ግን ተቋሙን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን ቀስ በቀስ ማደግ የነበረበትን የአደረጃጀት እሴቶችን ጭምር ያጠፋና ሕዝባዊ ወገናዊነቱንም ሊሸረሽር እንደሚችል ከኢህአዴጉ የፖሊስ ሕዝባዊ ወገናዊነት መጉደል መረዳት ይቻላል። ሕገ ወጥነትን ስለሚቆጣጠር “የቤንዚን አመድ፣ የፖሊስ ዘመድ የላቸውም” እንዳልተባለ ሁሉ ፖሊስ ለገዥው ፓርቲ ወግኖ የምርጫ ኮሮጆ ከመጎተት እስከ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አፈና ተሰማርቶ ተገኝቷል። በቅርቡ በሕዝብ ዜና ማሰራጫዎች ሲነገር እንደነበረዉ የእንግሊዝ መንግስት እስከ ማስትሬት ደረጃ ሲያሰልጥን የነበረዉን የደህንነት ኃይሎች ሥልጠና ማቆሙ የተነገረ ቢሆንም፤ ማሰልጠኑ እስከቆመበት ጊዜ ድረስና በቀጣይነትም የኢትዮጵያን የዲሞክራሲ ሂደትና የኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካን እጅ የዃሊት ሲጠመዘዝና የአውራ ፓርቲ (dominant party) ፖለቲካ በኢትዮጵያ እንዲሰራንፋ፤ ከዚህ ጋርም የብዙኃን ፓርቲ ፖለቲካ (multi party politics) ደብዛዉ ጠፍቶ በአመለካከት ልዩነት ብቻ ዜጎች በአገራቸዉ ልማት ላይ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው መከልከላቸዉና የዜግነት ኩራት እንዳይሰማቸዉ በማድረጉ ዉስጥ የእንግሊዝ መንግስት እጅ

እንዳለበት ለአፍታም እንደማንጠራጠረዉ የሚያደርገን ፓንክራስት ከፃፈዉ ማስረጃ በመነሳት ነዉ። በተረፈ እነ ቶኒ ብሌር 'የመሪያችን' የአቶ መለስ ዜናዊ የቅርብ ወዳጅና የተለያዩ የእንግሊዝ መንግስት ድርጅቶች (ዩኬኤይድ፣ ዲኤፍአይዲ) የመሳሰሉት ከገዥዉ ፓርቲ ጎን ቁመዉ ሰፊ ሥራ ሲሰሩ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራችን ቁልቁል እንደምደፍቅ ሳያስተውሉ ቀርተዉ አይደለም።

በእርግጥ እንግሊዛዊያን የኢትዮጵያዊያንን የቤት ሥራ ይሰራሉ ተብሎ ባይጠበቅም፤ ኢትዮጵያዊያን የራሳቸዉን የቤት ሥራ ሲሰሩ እንግሊዞች እንዲበላሽ ከማድረግ እጃቸዉን ባለመሰብሰባቸዉ ብቻ ሳይሆን፤ ከገዥ ፓርቲ በላይ ሕዝብን ማዕከል አድርገዉ መንቀሳቀስ እንደነበረባቸዉ እንግሊዞች ይጠፋቸዋል ተብሎ አይጠበቅም፤ አስተዋሽም የሚያስፈልጋቸዉ አይመስለኝም። የአዉሮፓ ሕብረት አባልነት ጎረበጠን ብለው የሕዝብን ዉሳኔ የጠየቁ እንግሊዞች የኢትዮጵያን ሕዝቦች ስቃይ ማየት የሚፈልጉበት ምክንያት መልስ አሁንም ከእንግሊዞች ዘንድ ይጠበቃል።

**ሱዳን**

ሱዳን እአአ ከ2013 በፊት በነበረዉ ገጽታዋ ወይም ደቡብ ሱዳን ራሱን የቻለ ነፃ አገር ሳይሆን ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጣችዉ እአአ በ1956 ነዉ። የሱዳን የቅኝ መገዛት ሁኔታ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ቅኝ መገዛት ጋር ሲስተያይ ትንሽ ለየት ይላል። ይኸዉም እንግሊዝ በዋናነት ግብፅን ቅኝ ትገዛለች። ግብፅ ደግሞ በእንግሊዝ የበላይነት ሱዳንን ታስተዳድራለች። በእንግሊዘኛዉ "Anglo- Egyptian condominium" የሚባለዉ ዓይነት ማለት ነዉ። በአጭሩ ድርብ ወይም ለሁለት አገሮች ቅኝ መገዛት ማለት ነዉ።

በስተሰሜን በኩል የሚኖረዉ የሱዳን ሕዝብ ከጥቁር አፍሪካዊነት ይልቅ የአረባዊነት ስሜትና ገጽታ የሚያመዝንበት ሲሆን፤ ልክ ኢትዮጵያ ውስጥ

አበሾች ፖለቲካዉን እንደሚዘዉሩት ሁሉ በሱዳንም እነዚህ አረባዊ ዝርያ ያላቸው ሰሜነኞች የሱዳንን ፖለቲካ ያሽከረክሩታል ማለት ነዉ። ሌላኛዉ የደቡቡ ሕዝብ የሰሜነኞቹን ባህል፣ ሃይማኖት፣ የአመራር ሁኔታ በመጥላት ለረጅም ዓመታት የተዋጉ ሱዳናዊያን (አብዛኛዎቹ የድንካና ኑዌር ብሔር አባላት የሆኑ) በቅርቡ ከሱዳን አገዛዝ ነፃ በመዉጣት (የገቡበት የእርስ በርስ ግጭት አሳሳቢነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) በአፍሪካ ሌላ ነፃ አገር ለመመስረት የበቁ ናቸዉ። በስተምዕራብ የሚገኘዉና ከኒጀር ጋር የሚዋሰነው ዳርፉር ተብሎ የሚታወቀዉ አከባቢ ደግሞ አሁን ከሱዳን ማዕከላዊ መንግስት ጋር ከገባበት አጣብቂኝ የተነሳ፤ የወደፊት ዕጣ ፋንታ የራሱ ነፃ መንግስት ወይም ከዋናው ሱዳን ጋር ይቆይ አይቆይ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ቢከብድም፤ ነፃነትን ይጎናጸፋል ወይም ሰፋ ያለ የዉስጥ አስተዳደር ነፃነት ሊኖረዉ ይችላልና በትዕግስት መከታተሉ በቂ ነዉ።

ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነት በኢትዮጵያ ሥልጣን እንደያዙ መንግስታት ዓይነት ይለያያል። ወይም ከኢትዮጵያ የሚትፈልገዉ ወይም የሚትጠይቀዉ ጉዳይ እንኳን ቢኖር የራሷን ጉዳይ ወደ ጎን ትታ ኃያላን የሚባሉ መንግስታትና ጎረቤቷ ግብፅ በምታሳድርባት ተፅዕኖና የግንኙነት ሁኔታ መነሻ በማድረግ ላይ የተመሠረተ ይመስላል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያና የሱዳን የግንኙነታቸዉ አካሄድ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ላይ ሲያሳድር የነበረዉ ተፅዕኖ እንደ ኤርትራዉ የፖለቲካ ተፅዕኖ ሁሉ እንዴዚህ ቀላል ነበር ተብሎ ሊደመደም የሚችል አይደለም።

ሱዳን ነፃ አገር ከተባለች ከአንድ አምስት ዓመታት በኋላ በ1960ዎቹ አከባቢ ትግል የጀመረዉ የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ጦር ከኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ሕወሓት/ኢህአዴግ ዘመነ መንግስት ድረስ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያን ተገን አድርጎ ሲንቀሳቀስ ነበር። እአአ በ1964/65 የኢትዮጵያዉ ንጉስ አፄ ኃይሌ ሥላሴ በሱዳን ማዕከላዊ መንግስትና በአማፂዉ የደቡብ ሱዳን ኃይል መሀከል ዕርቅ እንዳወረደ ቢነገርም፤ የኤርትራ ነፃነት ግንባር በሱዳን ዉስጥ ስለምንቀሳቀስ

በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል የበቀል አፀፋ ሥራ መስራትና አንዱ የሌላዉን ፖለቲካ ከመፈታተን ባለፈ የተፈጠረ የእርቅ ነገር እንዳልነበር በኋላ ሲታይ የነበረዉ የፖለቲካ ግንኙነት በግልጽ ያሳይ ነበር። የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር (ጀብሃ) በኤርትራ ሕዝባዊ የነፃነት ግንባር (ሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ) ተሸንፎ ከጠፋ በኋላ አባራሪዉ ራሱ መሠረቱን ያደረገዉ በሱዳን ሆኖ ደርግን ተፋልሟል። ይህንኑ ለመበቀል ሲል ደርግ ዶ/ር ኮሎነል ጆን ጋራንግ ለመሳሰሉ የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ጦር አመራር አባላት ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል።

ከኃይሌ ሥላሴ መንግስት መዉደቅ እና የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ በስተቀር ለማለት ይቻላል፤ ሱዳን ደርግን ለተቃወሙ ንቅናቄዎች ሁሉ፤ ማለትም የኤርትራ ሕዝብ ነፃነት ግንባር፣ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ፣ መላዉ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት፣  እና ሌሎችም በደርግ መንግስት ላይ ያኮረፉ ግለሰቦች ሳይቀሩ በሱዳን ዉስጥ ከትንፋሽ መውሰድ እስከትጥቅና ስንቅ ማደራጀት ድረስ እንድንቀሳቀሱ ፈቅዳለች። ያንን እንዲያደርጉ ያስገደዳቸዉ ደግሞ የኮሚኒስት ሥርአት ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን እንዳይስፋፋ ኃያሉ የአሜሪካ መንግስት በሱዳን ዉስጥ ለተጠለሉት ጸረ-ደርግ እንቅስቃሴዎች የሚያደርገዉን ድጋፍ በሱዳን በኩል ስላደረገ ነዉ። በ1967 ደርግ የገጠር መሬትን፣ በ1968 ደግሞ የከተማ ትርፍ ቤትና ቦታን የወረሰባቸዉ የፊዉዳል ተወላጆች ደርግን ለመፋለም በኢሕአፓ ሥር ተደራጅተዉ የታገሉትና ከቀይ ሽብር አምልጠዉ ወደ አዉሮፓና አሜሪካ የወጡት አብዛኛዉ ወጣቶችና የተማረው ክፍል የወጣው በሱዳን በኩል ስለነበረ፤ ሱዳን ባለዉለታቸዉ እንደሆነች ይቆጥሩታል። በሌላም በኩል ከደርግ አገዛዝ መውደቅ በኋላ፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል የሚገኘዉን ድንበር ከኢትዮጵያ ጋር በሚመቻት ዓይነት ሁኔታ ለመካለል ፍላጎቷን ግምት ዉስጥ በማስገባት በሚመስል መልኩ ከሕወሓት መንግስት ጋር የሚኖራትን ግንኙነት በጥንቃቄ ለመያዝ በማሰብ ይመስላል፤ ሱዳን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር

የነበራት ግንኙነት ከማንኛዉም ጊዜ የበለጠ የተለሳለሰ ነበር ለማለት ይቻላል። በግልባጩም ሕወሓትም ቢሆን ብዙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ቡድኖች ሱዳን ዉስጥ ተሰባስበዉ የሚጎላበቱ ከሆነ ሊከተል የሚችለዉን ችግር ከራሱ ልምድ ጀምሮ ስለሚያዉቅና ያ እንደገና እንዳይደገም ስለተጠነቀቀ ሊሆን ይችላል፤ ሱዳንና ኢትዮጵያ አንዱ በሌላዉ ፖለቲካ ጉዳይ ዉስጥ ጣልቃ የመግባቱና አንዱ በሌላው ላይ ችግር የመፍጠሩ ሁኔታ እጅግ አናሳ ነዉ። በአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ላይ ለመገኘት መጥተዉ የነበሩትን የግብፁን ፕሬዝዳንት ኦስኒ ሙባረክን ከቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ እንደወጡ የግድያ ሙከራ ተቃጥጦባቸዉ በነበረበት ጊዜ፤ የቃጡትም የሱዳን ዜጎች መሆናቸዉ ስለተጠረጠረ፤ ወይም የሱዳንን ምድር ተጠቅመዉ ስላመለጡ፤ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በሱዳንና በኢትዮጵያ መንግስታት መሀከል መቆራቆስ ተከጅሎ የነበረ ቢሆንም “በመስተዋት ቤት የሚኖሩት ድንጋይ አይወራወሩም” ያሉት ይመስላል ወይም ሊያስከትል የሚችለዉን ችግር ተረድተዉ ከግጭት እጃቸዉን ቶሎ ሰብስበዋል። ነገር ግን ትኩረት ሰጥቶ ለተከታተለ ሰዉ አንድ አስገራሚ ነገር አለ። ይኼዉም ሱዳን ለራሷ እየፈረሰች የኖረችና እየፈረሰችም ያለች አገር ሆና ሳለ፤ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እንዴት አድርጋ እራሷን ትዶላለች የሚል ሰዉ ቢኖር አይፈረድበትም። ሕወሓት/ኢህአዴግ ከሥልጣን ወርዶ ወደ መቀሌ ከአፈገፈገና ከአዲስ አበባ ቀሪ ክፍል ጋር ደም አፋሳሽ ጦርነት ዉስጥ ሲገቡ፤ ሱዳን የኢትዮጵያን ደካማ ጎን በመገመት በምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል በተለይም ጎንደር በሚባል አቅጣጫ ቀላል የማይባል ኪሎ ሜትሮችን ወደ ዉስጥ በመግባት መሬትን ተቆጣጥሯል።

እንግሊዞች በ1902 ከንጉስ ምንሊክ ጋር ተፈራርመው ነበር እየተባለ የሚታማውን የመሬት አለኝታ ለማስመለስ ወይም ከአማራ ክልል የኢትዮጵያን መሬት ቆርሰው ለመውሰድ አስበው እንደሆነ አይታወቅም ወይም ከምን ጋር እንደተያያዘ የታወቀ ነገር ባይኖርም፤ ከኃይሌ ሥላሴ መውደቅ በኋላ ሱዳን የደርግን መንግስት ለሚቃወሙ ኃይሎች ሁሉ ሰፊ ቦታ ሰጥታ እንደነበረ ከላይ ተገልጿል። በተለይ በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይንቀሳቀሱ ለነበሩት የደርግ መንግስት

ተቃዋሚ ኃይሎች ቢያንስ መዉጫና መግቢያቸዉ በሱዳን ምድር በኩል እንደነበርም ገልጫለሁ። በተለይም ሕወሓት/ኢህአዴግ እና ኦነግ በሱዳን ዉስጥ ጽ/ቤት ከፍተዉ ሲንቀሳቀሱ እንደነበር በኋላ ላይ እየወጡ ያሉ ማስረጃዎች ይገልፃሉ።

ምንም ይሁን ምን በየተራ የተነሱ የሱዳን መንግስታት አምባገነንና ፀረ ዲሞክራሲ ሆነዉ እያለ ተመሳሳይ አቋም የነበራቸዉን የኢትዮጵያ መንግስታት የሚወጉ ኃይሎችን ሱዳን ዉስጥ ማስጠለል ለምን እንዳስፈለገ ተብሎ ለሚነሳ ጥያቄ ወይም ሐሳብ ለጊዜዉ ይህ ነዉ ተብሎ የሚነገር ነገር ባይኖርም፤ መገመት የሚቻለዉ ግን ሱዳኖች ወደፊት በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ድንበሮች ለሚያነሱት የመሬት የይገባኛል ጥያቄ የራሳቸዉን ልብ አዉቃ መንግስት በኢትዮጵያ ዉስጥ እስከሚያገኙ ወይም እስከሚያስቀምጡ ድረስ ያደረጉት ነገር እንደሆነ መገመት ይቻላል። ከዚህ ባገደመ ደግሞ ሱዳኖች የምስራቁን ሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም መስፋፋትን ለመቆጣጠር ያለ ዕረፍት ሲሰሩ ለነበሩ የዉጪ ኃያላን መንግስታት ለእርሻ ሳይሆን ለመረማመጃ መሬታቸዉን እያከራዩ የራሳቸዉን ቢዝነስ መስራታቸዉ እንደሆነ ይገመታል። ለምሳሌም ደርግ የሚወገድበትን ሥልት ሲቀይስ የነበረዉና የአሜሪካ ኮንግሬስ ፊት ቀርቦ ምስክርነቱን የሰጠዉ ስፔንሰር የተባለዉ አሜሪካዊን በመጥቀስ አንዳርጋቸዉ አሰግድ (1992፡ 358) እንደፃፈዉ “… በሌላም በኩል ሱዳን ስለኢትዮጵያ ባላት የፖለቲካና የጦር ሁኔታ ዕውቀት ለዚህ ተግባር ጠቃሚ ሊትሆን ትችላች።” ብሏል። በሌላም በኩል ቤተ እስራኤላዊያንን በሱዳን በኩል አሾልኮ በማስወጣት በኩል ሱዳኖች የግላቸዉን ቆንጆ ቢዝነስ ሰሩ ከማለት ውጭ ወዴትም መጠርጠር አይቻልም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ሱዳን ነዳጅ አምራች ሀገር ስለሆነች ከቅርበት አንፃር ለኢትዮጵያ አዋጪ በመሆኑ ወደብ አልባዋ ትልቅ ሀገር ኢትዮጵያ በሱዳን ቁጥጥር ሥር ናት። ለማንኛዉም ሱዳኖች ለኢትዮጵያዊያን ጥሩም መጥፎም ጎረቤት ናቸዉ ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም፤ የሱዳን መንግስት ዲሞክራሲያዊ ሆኖ አምባገነን የኢትዮጵያ መንግስታትን ለመጣል የዕርዳታ እጃቸዉን ሰነዘሩ ተብሎ

አይታሰብም፤ እንዲያዉም ከዚያ በፊት የነበሩትን ትተን ፕሬዝዳንት አልበሽር በሰብአዊ መብት ረገጣና ዳርፉር ዉስጥ ለተፈፀመዉ ጭፍጨፋ በዓለም ሸንጎ ፊት የሚፈለግ ሰዉ ሆኖ እያለ፤ ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነትና ሌሎች የአፍሪካ ኅብረት አባል አገሮች በመተባበር በወሰዱት አቋም የሱዳኑ  ፕሬዝዳንት እንዲያዝ የወጣዉን የዓለም አቀፉን ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማንም አይጠቅምም በማለት ተቃዉመዉታል፤ ወይም ሥራ ላይ አላዋሉትም። መሪ ማግኘት ያን ያህል ቀላል ባይሆንም ሕዝብን መተካት ግን እንደማይቻልና ከሕዝብ ሰብአዊ መብት መከበርና ከሕግ የበላይነት ይልቅ፤ ለምን እንደሆነ ለመግለፅ ቢያስቸግርም፤ የአንድ የሱዳን ፕሬዝዳንት ክብር ከሕዝብ በልጦባቸዉ ዴሞክራሲያን ነን የሚሉት የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች አልበሽርን ከአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ተጠያቂነት መታደጋቸዉ አስገራሚ ነዉ። አልበሽርን ለመታደጋቸው ምክንያት ነው ቢባል እንኳን እነሱም በሚፈጽሙት ወንጀል ነገ ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመስጋት ብቻ ይሆናል።

ስለሱዳን ውለታ አጭርና ግልፅ ቃል የሰጡት ሁለት የሕወሓት አመራር አባላት፤ አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ብርሀነ ገብረክርስቶስ ስለሱዳን ውለታ ከአፍቃሬ ሕወሓቱ አሜሪካዊ ሄንዝ (2007፡ 190) እና (2007፡265) ጋር ሲነጋገሩ እንደመሰከሩት *“The Beshir government has not restricted us in any way.”* ብሎ አቶ መለስ ሲመልስ፤ ብርሀነ ገብረክርስቶስ ደግሞ *“All our supplies and support come through Sudan.”* ብሏል።

በተረፈ፣ ኢትዮጵያና ሱዳን ረጅም የየብስ የተፈጥሮ ድንበርና አባይን ጨምሮ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች የሚፈስሱ ወንዞች ያስተሳስሯቸዋል። ይህንኑ ትስስር ከፍ ለማድረግም ኢትዮጵያ ከሕዝቧ ሳይተርፍ ለሱዳን መንግስት የኤሌክትሪክ ኃይል ለመሸጥ ስምምነት ከማድረጋቸዉም በላይ ቀደም ብሎ ደግሞ የሱዳን ነዳጅን በቧንባ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ስምምነት መደረጉ ይታወቃል። ሌሎች ጉዳዮች ጥናት የሚፈልጉ ቢሆንም፤ ሱዳን ከአሜሪካም ሆነ ከእንግሊዝ ባልተናነሰ ሁኔታ የኢትዮጵያን ፓርቲ ፖለቲካ ለመጠምዘዝ ግልፅና ድብቅ ሚና

ስትጫወት እንደነበረችና በቀጣይነትም ሊትጫወት እንደሚትችል፤ ከግብፅና ወዳጆቿ በሚደረግባት ጫና ምክንያት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ከሱዳን ቅርብ ርቀት ላይ በአባይ ላይ በሚገነባው የኃይል ማመንጫ ግድብ ላይ ተፅዕኖ ከማሳደር እንደማትታቀብ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ።

## ሱማሊያ

ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለን ሱማሊያ ሰሜናዊ ግዛቷ ሐርጌሳን ዋና ከተማዉ አድርጎ ብርቲሽ ሱማለላንድ ይባል እንደነበረና ደቡባዊዉ ደግሞ ሞቃዲሾን ዋና ከተማዉ አድርጎ የኢጣሊያ ሱማሊላንድ ተብሎ ለሁለት ተከፍለዉ ይታወቁ እንደነበር አስታዉሳለሁ። ለማንኛዉም ሱማሊያ እአአ ጁላይ 1፣ 1960 ፖለቲካዊ ነፃነቷን የተቀዳጀች እንደሆነች ይታወቃል።

ቅኝ አገዛዝ ለማንም የአፍሪካ አገር ያልበጀዉን ያህል ሳይሆን ሱማሊያንዊያንን ደግሞ እጅጉን በድሎዋቸዋል። ቅኝ ገዥዎች ሱማሊያዊያንን በአራት ቦታ (በራሱ በሱማሊያ፣ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በጂቡቲ) እንዲከፋፈሉ ከማድረጉም በላይ በቅርቡ ዕውን መሆኑ ጨርሶ ሊታመን የማይቻል፤ ነገር ግን በቅኝ ገዥዎች ተቀብሮ እየቆየ ጊዜን ጠብቆ የሚፈነዳ ‘ታላቋ ሱማሊያ’ን የመገንባት ሕልምን በሱማሊያዊያን አእምሮ ዉስጥ በመጫሩ፤ እንደገናም ሱማሊያዊያን ከጎረቤት አገሮች ጋር በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ግልፅ እና ድብቅ ጦርነት እያካሄደች እንዲትኖር አድርገዋታል።

የኢትዮጵያ ሱማለዎች ድንበር አልፈዉ ከብት ያግዳሉ፣ አደን ያድናሉ፣ የተለያዩ ሀብቶችን ይሰበስባሉ በማለት አስቀድመዉ ከወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት ጋር እሰጥ አገባ ዉስጥ የገቡት የሱማሊያ መንግስት መሪዎች ሳይሆኑ የእንግሊዝ ቅኝ ጌቶች ነበሩ። እነዚያ ቅኝ ገዥ ጌቶች ተገድደዉ ከሱማሊያ ሲወጡ የሱማሊያ መንግስትና የኢትዮጵያ መንግስታት

እየተጋጬ እንዲኖሩ ለማድረግ የግዛት አለኝታንና ታላቋ ሱማሊያ የሚባለዉን የነገር ፖለቲካ ትተዉ ሄደዋል፡፡

በነዚህ በቀላሉ ሊጨበጡ በማይችሉ ጉዳዮች የተነሳ ሱማሌዎች በመከፋፈላቸዉ እነሱም በጎረቤት አገሮች ፖለቲካ ዉስጥ ጣልቃ እንዲገቡ ብቻ ሳይሆን፤ የሌሎች አገሮች መንግስታትም በሱማሊያ ፖለቲካ ጉዳይ ዉስጥ ጣልቃ እንዲገቡ፤ ሱማሊያ መንግስት ይኑራት አይኑራት የሚለዉን እስከሚወሰን ድረስ እንዲሄዱ ጋብዞአቸዋል፡፡ በተለመደዉ አባባል በተለይ እንግሊዝ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦንብ በሱማሊያዊያንና ጎረቤት አገሮች መሀከል ቀብራ እንደነበርና በአፍሪካ ቀንድ የሱማሊያና የሌሎች የፖለቲካ ሁኔታ መረጋጋትን ማጣት ለመላዉ የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ እንደማይበጅ መገንዘብ ብዙም ምርምር የሚያስፈልገዉ አይሆንም፡፡

ሱማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ሰፊ የየብስ ድንበር ትጋራለች፡፡ አብዛኛዉ የሱማሊያ ምድር በረሃማ ስለሆነ፤ ወደ ኢትዮጵያ የተቆረጡ ሱማሌዎችንም ፊለጋ ሆነ እግረ መንገዳቸዉንም የበረሃማ መሬታቸዉ ማካካሻ የሚሆን መሬት ከኢትዮጵያ ድንበር ቢያገኙ ደስታዉን አይችሉትም፡፡ ይህንን ዕውን ለማድረግም አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ሲወጡ በነበሩበት ድንበር እንዲወሰኑ የሚለውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ሕገ ደንብ ወደ ጎን እየተው፤ ከሕጋዊነት የበለጠ በሕገ ወጥ መንገድ ለማስፈጸም ሰፊ ሙከራ አድርገዋል፡፡ አንዱም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዕዉቅና የተከለከለዉን የመሬት አለኝታ ጥያቄ በማቅረብ ነዉ፡፡ ሌላዉ የሱማሊያ መንግስት የራሱን የመሬት ጥያቄ ድብቅ ፍላጎት ለማሳካት ሲባል በኦሮሞ ስም የሚጠሩ እንደኦሮሞ አቦ፣ የምዕራብ ሱማሊያ ነፃነት ግንባር የመሳሰሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች አደራጅተዉ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር በማሰረግና ቀጥሎም በመደበኛ ወታደር ወረራ በመፈጸም ጦርነት እንዲቀሰቀስ አድርገዋል፡፡ “… ለመገንባት ለሚያልሟት ታላቋ ሱማሊያ በሚሊዮናት የሚቆጠረውን የኦሮሞ ሕዝብ እንደ ጥሬ ዕቃ ይታያቸው ነበር፡፡” ይላል የኦሮሞ ጉዳይ መጽሐፍ ጸሐፊ

ሰለሞን ስዩም። እሱም ሳይሳካላቸዉ ሲቀር የኢትዮጵያን ኃይል ለማዳከም ካደረባቸው ስሜት ተነስተው በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል ዞረዉ የራሱን ነፃ ግዛት ለመመስረት ለሚዋጋዉ ሻዕቢያ እና፤ ወደ መጨረሻ ላይ ደግሞ የደርግ መንግስትን ለመጣል ለታገለዉ ሕወሓት የተለያዩ ድጋፎችን ሰጥተዋል። ይህም ስለመሆኑ የሕወሓት መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ለፖል ቢ ሄንዝ (2007፡ 190) እንዳረጋገጠዉ *"The Somalis gave us passports, and most of us travel as Somalis."* ብሏል። የነዚህ ድርጊቶች ድምር ዉጤት ሲገመገም፤ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሕልዉና ላይ የሱማሊያ መንግስት ሲያሳርፍ የነበረው ተፅዕኖ እንዲህ ቀላል እንዳልነበር ያመለክታል። ይህንኑ ለመበቀል አስበዉ ሊሆን ይችላል የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም መንግስት ጦርና ሰላይ ልኮ የሱማሊያን መንግስት አሽመደመደ፤ ከዚያን ወዲህ የኢትዮጵያን በትረ መንግስት ሥልጣን የተረከቡትና ከሶማሊያ አስፈላጊዉን ድጋፍ ሲያገኙ የነበሩ ሕወሓቶች ደግሞ የሱማሌዎችን ዉለታ ወደ ጎን ገፍተዉ፤ ኢትዮጵያን የሚፈታተኑ አሸባሪዎች ሱማሊያን መረማመጃ በማድረግ በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል እየገቡ ለመንግስቴ ያሰጋሉ በሚል ውንጀላ ጦርነት ስለከፈተባቸዉ፤ ሱማሌዎች እስከዛሬም በማዕከል ብቻ የተወሰነ ደካማ መንግስት እንዲኖራቸዉ ተደርገዉ ቀርተዋል። ይህም ብቻም አይደለም ሱማሌዎች ራሳቸዉ በጎሳ እየተቧደኑ እንዲዋጉ ተደርገዋል። በዚሁ የእርስ በርስ ዉጊያ አቅሙን ያለዉ ሱማሌ ሲሰደድ በኢትዮጵያም በብዛት እንደሚገኙ ይታወቃል። አልሸባብ ሊያመጣ የሚችለዉን ወረራና አሸባሪነትን ከሩቁ ለመከላከል ሲባል የሕወሓት ጦር ሱማሊያ ድረስ ገብቶ ተዋግቷል። በጣም አሳዛኙ ነገር ከርስ በርሱ ጦርነት ሸሽት የሱማሌ ዜጎች ወደ ጎረቤት አገሮች በሚሰደዱበት ጊዜ የሱማሊያ ቋሚ ንብረቶች ሳይቀሩ ወደ ጎረቤት አገሮች ተወስደዉ በሳንቲም ደረጃ ዝቅ ተደርገዉ ሲሸጡ፤ ከመንግስት አመራር ባልተደበቀ ሁኔታ ኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶችም ከሱማሊያ መንግስት መንኮታኮት አትርፈዋል። ሲዉል ሲያድር የሱማሊያና የኢትዮጵያ ፖለቲካ የቱ ጋ እና እንዴት ተመልሶ አንሰራርቶ ምን ሊሆን እንደሚችል ጊዜዉ ሲደርስ ከማየት በስተቀር ነገ እንዲህ ይሆናል ብሎ መተንበይ

ያስቸግራል። በተለይም የኢትዮጵያ ሱማሌዎችን ነፃ ለማዉጣት በኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ ሥር ተደራጅቶ የሚንቀሳቀሰዉ የፖለቲካ ቡድን ጥያቄ ግምት ዉስጥ ገብቶ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። ከ2008 ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተው የለውጥ ፍላጎት እንቅስቃሴ የተነሳ፤ በተለይም ከ2010 ጀምሮ በኢህአዴግ ውስጥ በተከሰተው የሥርአት ሳይሆን የወንበር ወይም የኢህአዴግ የሥልጣን ሽግሽግን ተከትሎ ኦብነግም ወደ ኢትዮጵያ ሱማሌ ክልሉ ተመልሰዋል። ሆኖም ግን በኦብነግ ውስጥ ራሱ ከፊሉ ወደ ኢህአዴግ ወንበር ተረካቢው ብልፅግና ፓርቲ ሲጠጉ ከፊሎቹ ደግሞ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄአቸው አጥጋቢ መልስ ያላገኘ በሚመስል መልኩ ከፌዴራሉ ማዕከላዊ መንግስት ጋር ያላቸው ግንኙነት የተፈለገውን ያህል የተለሳለሰ አላደረጉም። ሊከተል የሚችለውን ነገር ጊዜ ከመጠበቅ በስተቀር ይህ ጽሑፍ እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የሶማሊያ የፖለቲካ ሁኔታ እየተናጠ ይገኛል። መናጡ በራሱ የማያበቃና ለኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ግንባታ ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅዖኖ ማሳረፍ እንደሚችልም ይታመናል።

ሱማሊያን በተመለከተ የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ዕትም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከተጠቃለለ በኋላ፤ በ2016 ዓም ደግሞ በአዲስ ክስተት ኢትዮጵያና ሱማሊያን የሚያወዛግ ክስተት ተከስቷል። ይኼዉም በደካማና ስግብግብ የሕወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ወደ ባህር መዉጫ በር ያጣዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ይህንን የባህር በር ያግኝ ዘንድ የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት ገዥ የሱማሊያ ፌዴራል መንግስት አካል ከሆነች ሱማሊላንድ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ። ይህ የመግባቢያ ስምምነት ቀድሞም ቢሆን ጥንቃቄ የሚፈልገዉን የኢትዮጵያና የሱማሊያን ግንኙነት አደፈረሰ። ምንም እንኳን የእሳቅ ጎሳ የሚበዛበት የሱማሊላንድ ክልል ሕዝብ ከቀድሞዉ የሱማሊያ አምባገነናዊ መሪ በደረሰበት ግፍ የተነሳ ለብቻዉ አፈንግጦ መኖር ከጀመረ ከሰላሳ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም፤ ከላይ እስከ ተጠቀሰ ጊዜ ድረስ ዓለም አቀፍ ዕዉቅና አላገኘም። ምንም እንኳን ለኢትዮጵያዊያን የባህር በር የሚያስፈልግ ቢሆንም እሱን ለማግኘት የተከደበት መንገድ ከሱማሌ ጎረቤት ሕዝብም

ሆነ ከዓለምአቀፍ ሕብረተሰብ ጋር የሚያጋጭ ሆኖ ተገኝቷል። እዚያ ዋና ሱማሊያ ዉስጥም ሆነ እዚህ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ሱማሌ ዉስጥ እሳት ስላለ፤ የሚፈጠረዉ ነገር ሁሉ በጊዜ መፍትኼ ካልተበጀለት፤ ፖለቲካዉንም ሆነ የፓርቲ ፖለቲካችንን መጉዳቱ አይቀርም።

## በኢትዮጵያ የኤርትራ ፖለቲካ ተፅዕኖ

የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ መሠረት መጣል የጀመረዉ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት መሆኑን ከላይ መግለፄ ይታወሳል። በዚያን ጊዜ ደግሞ ኤርትራም የኢትዮጵያ አካል ስለነበረች የዚህን የወቅቱ ጠቅላይ ግዛት የዛሬዉን ልዑላዊ አገር በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ማንሳት አስፈላጊ መሆኑን ተረድቻለሁ። ይህ ብቻም አይደለም ከጣሊያን ወረራ ጋር የኤርትራዊያን ለአዉሮፓ የፓርቲ ፖለቲካ ተጋላጭነትንና በኋላቀር የኢትዮጵያ ፊዉዳል ፖለቲካ ላይ አሳድረዉ የነበረዉን ምንነቱ ያልተለየ ተፅዕኖ ጉዳይ በጥቂቱ ነካክቻለሁ። ዛሬም ድረስ የኤርትራ ግዛት ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበረበት ወይም አልነበረበትም ጉዳይ ሲነሳ አንድም በመቃወም ወይም በመደገፍ በደም ፍላት የሚናገሩ ሰዎች ይኖራሉ። በተለይም የአሃዳዊነት አቀንቃኝ ኢትዮጵያዊያን የቁጣቸዉ ምንጭ የታሪክ ከሆነ የታሪክ ሰዎች መርምረዉ እቅጩን እስኪነግሩን፤ ወይም ችግራቸዉ የባህር በር ከሆነ ደግሞ ሰጥቶ መቀበል *(win/win)* የተባለዉን ሥልጡን የፖለቲካ ዲፕሎማሲ የሚያዉቁ ዜጎች ሚናቸዉን እንዲጫወቱ ማስቻል ይገባል እንጂ ተቆርጦ ለተገነጠለ ኢርትራ ደርሶ ቁጡ መሆን ብዙም የሚፈይደዉ ነገር አይኖርም። ማለትም ኤርትራ ነፃ አገር ለመሆኗ በወቅቱ ኢትዮጵያን ያስተዳድር የነበረዉ መንግስት አምኖ የተቀበለና ዓለም የተስማማበት ስለሆነ፤ ለመቀልበስ የሚደረገዉ ምኞት አጸፋዉ ደግ እንደማይሆንና ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚ የሚያደርግ የጋራ ፖለቲካ ከማሰብ ጎን ለጎን፤ አስቀድሞ ግን የኢትዮጵያን ፖለቲካ ዲሞክራሲያዊ ማድረግ ለአፍታ የሚዘነጋ አይሆንም።

አሁን ለያዝኩት የፓርቲ ፖለቲካ አርእስተ ጉዳይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ አየር ሁኔታ ሲነሳ የኤርትራ ፖለቲካ ያሳርፍ የነበረዉ ተፅዕኖ ቀላል ስላልነበረ ዝም ብሎ ማለፍ አይቻልም ከሚል ስሜት የተነሳ ነዉ ይህች ክፍል የታከለችበት። ከተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ለማወቅ እንደሚቻለው ቀደምት ስሟ ምድረ ባህሪ የሆነው ኤርትራ፤ ጥር 1/1890 የወቅቱ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክርሲፒ በአፍሪካ ቀንድ የቅኝ ግዛት ይዞታን በማግኘቱ የወጣለት ስም እንደሆነ የታሪክ ባለሙያዎች ያስጨብጣሉ። ዛሬ ኤርትራ የኢጣሊያዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንቼስኮ ክርሲፒ ያወጣላትን ስም እንኳን መቀየር ሳያስፈልጋት ራሷን የቻለች ልዑላዊት የኢትዮጵያ ጎረቤት አገር ቢትሆንም የፖለቲካ ማይም ካልሆነ በስተቀር ዛሬም ድረስ በኤርትራ የሚኖረዉ የፖለቲካ ትኩሳት በአንድም ወይም በሌላ የኢትዮጵያን የፖለቲካ የደም ሥር ሳይነዝር የሚያልፍ አይሆንም። ስለዚህ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አጀንዳ ማንሳቱ ካልቀረ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ ላይ ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችሉ የጎረቤት አገር የኤርትራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የፈጠረዉ ተፅዕኖ ምን እንደሚመስል አስታኮ መፈተሹ ተገቢ ሆኖ አግኝቻለሁ። ባህሩ ዘዉዴ (2007፡ 229) "በኤርትራ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ለአስራ ሦስት ዓመታት ያህል የጸናዉ እንቅስቃሴ በራሱ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ በኢትዮጵያ በነበረዉ የፀረ ሥርአቱ ተቃዉሞ ላይ ባሳደረዉ ተፅዕኖ ለሥርአቱ መገርሰስ ዐቢይ አስተዋጽኦ አድርጓል" በማለት የኤርትራ ፖለቲካ ጉዳይ ቀላል ግምት መሰጠት እንደሌለበት ያሰምሩበታል። በዚያ ብቻም ሳይወሰን ዛሬም ቢሆን በድንበር ጉዳይ፣ በንግድ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በስደተኛ ዝዉዉር፣ አንዱ የሌላ ተቃዋሚን በማስተናገድ፣ ወዘተ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግንኙነት የተጠላለፈ ስለሆነ፤ እንዲህ በቀላሉ የሚተዉ አይሆንም። በኢትዮጵያ የትግል እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ አይረሴ የሆነው የ60ዎቹ ጉዳይ በሚወሳበት ጊዜ የኤርትራዊያን የትግል ልምድ ወደ 50ዎቹ መጀመሪያ ላይ በተለይም ወደ ፌዴሬሽኑ መፍረስ የሚወስደን ስለሆነ፤ ቀሪዎቹ ኢትዮጵያዊያን ከንጉስ አምልኮት ሳይላቀቁ (ለነገሩ ዛሬም ያልተላቀቁ መኖራቸው ሳይዘነጋ) ኤርትራዊያን የነፃነት ትግላቸውን ዘር ዘርተዋል። እነዚያው የኤርትራ ኤሊቶች በ1960ዎቹ

መጨረሻ ደግሞ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ታጋዮችን በራሳቸው አምሳል ሰርተዋቸዋል። ስለሆነም፤ የኤርትራን ግዛት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ሊያሳድሩ የቻሉትንና የሚችሉትን ሚና አሳንሰው ማየት አይመከርም።

ይህንን ጉዳይ በማነሳበት ጊዜ አንድ ጥንቃቄ እንዲወሰድልኝ የምፈልገዉ ግን ዓላማዬ የኤርትራንም ሆነ የኢትዮጵያን ቀደምት የአከባቢ ሁኔታ ታሪክ ለመመርመር አይደለም። ለዚህ ተገቢ የሆኑ የታሪክ ባለሙያዎች ይኖራሉ ብዬ አስባለሁ። እኔ በፖለቲካ ትግል ዉስጥ የትኛዉ አጀንዳ ከየትኛዉ አጀንዳ ጋር ይዛመዳል ብሎ ማንሳትና ግንዛቤን ፈጥሮ ለፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ ሰፊ አጀንዳ አያያዝ እንዲያመች ካደረብኝ ፍላጎት የመነጨ ነዉ። ለምሳሌ፤ የኦባማ ኢትዮጵያን መጎበኘት አሜሪካ ካላት የኃይል የበላይነት የተነሳ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ አንደምታ ይኖሯል ብለን እንገምታለን እንበል። የጫናዉ ክብደት እኩል ባይሆንም፤ እንደዚሁም ኤርትራዊያን በኢትዮጵያዊያን የፓርቲ ፖለቲካ ዉስጥ የተጫወቱትን ሚና ለማሳየት፤ በተለይም ኢትዮጵያዊያን በምን ምክንያት የራሳቸዉን የበሰለ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ መስራት እንዳልቻሉ ለመዳሰስና ለመፍትኼ አቅጣጫ ሲባል የኤርትራን ጉዳይ ማዉሳት አስፈላጊ ይሆናል። ካልሆነማ በአንድ ሉዑላዊ አገር የዉስጥ ጉዳይ ላይ ገብቶ ማድረግ የሌለብንን ለማድረግ አይደለም። አዋጪ የፖለቲካ ስልትም አይሆንም። በሌላም በኩል ዛሬ የኤርትራ ፖለቲከኞች እንደሚያወሩት ኤርትራ ዉስጥ የፓርቲ ፖለቲካ የላቀ ደረጃ ላይ ደርሷልም ለማለትም አይደለም። ምክንያቱም፤ የኤርትራ ፖለቲካ ልክ እንደሌሎች የአፍሪካ መንግስታት የፖለቲካ አመራር ከቅንጣት የፓርቲ ፖለቲካ ወይም ካንድ ሰዉ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሲጠቃለልም ከተለመደዉ ፊዉዳላዊ መኮፈስ ያመለጠ አይደለምና ነዉ።

በግርድፉም ቢሆን የታሪክ ሰነዶችን ስንመለከት ኤርትራ ለስድሳ ዓመታት ይህል የጣሊያን ቅኝ ግዛት እንደነበረች ከላይ ገልጫለሁ። ዓለምሰገድ ቦጋል አዳል <u>የኤርትራዉ እንቆቅልሽ</u> በሚለዉ መፅሐፉ ገጽ 14

ላይ እንደፃፈዉ “ኢጣሊያዊያዉ አባ ጁሰፔ ሣፔቶ የተባለዉ የሚሲዮን ቄስ በህዳር ወር 1860 ዓም በአሰብ የባህር ዳርቻ በዘመኑ ከነበረዉ የአከባቢዉ ሱልጣን መሬት በስምንት ሺህ አንድ መቶ ብር ገዝቶ ወዲያዉኑ ለጣሊያን የንግድ መርከብ ኩባንያ አዛወረዉ።” ብሏል። በዚህ የጣሊያን ሞኖክሴ ሰላይ አማካይነት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጣሊያን እግሩን በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ተክሎ ኤርትራ የሚትባል ቅኝ ግዛት ያዘ ማለት ነዉ። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የሆነውን እንዳልሆነ የሚያስቡ ካልሆነ በስተቀር የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ሲያንስ በኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ውስጥ ሲበዛ ደግሞ ትልቋ ኢትዮጵያ ውስጥ እግሩን የተከለው በሚስዮናዊ ቄስ ጁሰፔ ሣፔቶ አሳሽነት ነው ማለት ይቻላል። ከዚያ በፊት ግን አፄ ዮሐንስ ከደርቡሾች ጋር በነበረዉ ጦርነት የሰዉ ኃይሉ በመመናመኑ አጋጣሚዉን የተጠቀመ የመሰለዉ የጣሊያን ጦር እስከ ትግሬ ግዛት ድረስ ዘልቆ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ገዥዎችና የኤርትራ ተወላጆች የቅራኔ ምንጭ የተለያየ ነበር የሚሉ የተለያዩ ወገኖች ቢኖሩም፤ በዉጫሌ ዉል ምክንያት የኤርትራ ፖለቲከኞች በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ግዛት ላይ፤ በተለይም በምኒልክ አስተዳደር ላይ ቂም እ ን ዴ ቋጠሩ ይነገራል። ምክንያት፤ በአድዋ ጦርነት ምክንያት የዉጫሌ ዉል የፈረሰ ቢሆንም፤ አፄ ምኒልክ አሰብ እና ምፅዋ ድረስ ተጉዘው እንደመዋጋት “መረብ ምላሽ” የሚባለውን ስምምነት ተፈራረሙ? ለሚለዉ ጥያቄ እራሳቸዉ የሰጡት መልስ በጣም አጭርና ግልፅ ነበር። “ኤርትራ አገሩ ስላልሆነች” ግድ አልሰጠዉም የሚል ነበር። የምኒልክ ወገን የሆነዉ ግን በሰዉ ኃይል መቀነስ፣ የቀለብ ማነስ፣ የህዳር በሽታ መባባስ፣ ወዘተ የሚባሉ ሰበቦችን ቢደረደሩም ሰበቦቹ በኤርትራዊያን ፖለቲከኞች ዘንድ ከሰበብነት አልፎ ተቀባይነትን አላገኙም። ምንም ይሁን ምን ምንሊክን መወንጀል የሚፈልጉ ኃይሎች ወደኋላ ተመልሰዉ በጣሊያን የተያዙ ጠረፋማ የኤርትራ አከባቢዎችን በተለይም ስለኤርትራ በአጠቃላይ መገንዘብ የነበረባቸዉ ነገር ቢኖር፤ ከምንሊክ ቀደም ብሎም ኢጣሊያዊዉ ሰላይ ሞኖክሴ አሰብ አከባቢ የሚገኘዉን መሬት ገዝቶ ለጣሊያን ድርጅት ማስተላለፉ፣ እአአ ከ1885

ጀምሮ ጣሊያኖች አሰብ ላይ ባንዲራቸዉን መትከላቸዉና አከባቢዉን ራሱን ኤርትራ ብለዉ እስከመሰየም መድረሳቸዉ፤ በተለይም ራስ አሉላ አባነጋ ዉጊያ ሊያደርጉ ሲሉ አፄ ዮሐንስ ደግሞ ትኩረት እንደነፈጉት እየታወቀ፤ የኤርትራን በጣሊያን መያዝ ከምንሊክ የዉጫሌ ዉል ስምምነት መፍረስና መረብ ምላሽ ፊርማ ጋር ብቻ አያይዞ መውቀሱ ሚዛናዊነት ይጎድለዋል። ሰበብም ተደረደረ፤ ምክንያትም ቀረበ ጣሊያን ከመረብ ምላሽ ወደ ስድሳ ዓመት ገዝቶ በ1941 በቃል ኪዳን አገሮች ኃይል ተገፍትሮ ከኢትዮጵያ ቢወጣም፤ በሌላም በኩል በቦታዉ ተተክቶ ኤርትራን በሞግዚትነት ያስተዳደረው የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር በመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችል አውሮፓዊ የፖለቲካ ድባብ በኤርትራ ሰፍኗል ማለት ይቻላል። በዚህ አስተዳደር ሥርም ምስኪኗ ኤርትራ ለአስር ዓመታት ያህል በእንግሊዞች ሥር ከተገዛች በኋላ ‹‹… የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር [በቃል ኪዳን ኃይሎቹ] አዋጅ ቁጥር 136/1952 ሥልጣን አስረክቦ፤ ከመስከረም 11 ቀን 1952 ጀምሮ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ተቀላቀለች።” ይላል ዓለምሰገድ በጋለ አዳል። ስለሆነም የኤርትራ ጉዳይ መታየትም ካለበት አዉሮፓዊያን በተለይም እንግሊዞች ከሚቀብሩትና እየቆየ ከሚፈነዳዉ የፖለቲካ ፈንጂ ጋር ነዉ እንጂ በምንሊክ ላይ ብቻ እንደማይሆን ግንዛቤ መፍጠሩ አስፈላጊ ይሆናል።

ለአሃዳዊት አስተዳደር ኢትዮጵያና ለኤርትራ ፖለቲካ ግንኙነት መበላሸት፤ በሌላ አቅጣጫ መታየት ካስፈለገም የፌዴሬሽኑ ሕልዉና ብዙም ሳይረጋጋ የንጉሱ እንደራሴ የነበረዉ ቢትወደድ አንዳርጋቸዉ መሳይ የፌዴሬሽኑን ተሿሚዎችን በማመሳቀሉ የተወሰኑቱ ኤርትራዊያን ብዙም ሳይቆዩ ወደ በረሃ ማቅናተታቸዉ አብሮ መፈተሽ ያለበት ነዉ። በዓለም አቀፍ ሸምጋዮች ፊት ስምምነት የተደረገበት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ባለመስራቱ ሸሸትና ስደትን እንዲመርጡ የተገደዱት የኤርትራ ዜጎች ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ብዙም ሳይቆዩ አንድ የፖለቲካ ማህበር በ1953 ላይ ኢ.ፕ.ኤል.ኤፍ ‹‹የኤርትራ ነፃ አዉጪ ግንባር›› የሚባለዉን መሠረቱ።

የኤርትራ ነፃ አዉጪ ግንባር መመስረት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መስመር የያዘ የፖለቲካ ትግል ለማካሄድ ያግዛል ተብሎ የታሰበ ቢሆንም፤ ነገር ግን በቆላና በደጋ፣ በእስልምናና ክርስቲያን፣ በሐማሴንና በሌላ ብሔረሰቦች፤ ከፍ ብሎም በጀባሃና በሻዕቢያ መካከል የመከፋፈል ፖለቲካ በሽታ እየተፈጠረ ከአስከተለዉ ግጭት የተነሳ ለነፃነት የተቋቋመዉን ድርጅት ብዙም ሊያንቀሳቅስ አልቻለም። እነዚህ ተጠቃሽ ክፍፍሎች ቢኖሩም በማናቸዉም ሁኔታ የሐሳብ ልዩነት መኖሩ የሚጠበቅ ቢሆንም ኢፕኤልኤፍን ያቋቋሙ ሰዎች የኤርትራ ጥያቄ ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ የሚደረግ ትግል ጉዳይ ስለመሆኑ አንዳችም ጊዜ ነፋስ ሳይገባበት ለ1983ቱ ነፃነት አብቅቷቸዋል። በነሱ አቋም ላይ ነፋስ አለመግባቱ ብቻ ሳይሆን የኋላ የኋላ ላይ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወይም ኢትዮጵያን አስመልክቶ በዉጪም ሆነ በአገር ዉስጥ በተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የየኤርትራዊያኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ዕርዳታና ምርቃት በመሻታቸዉ፤ የኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት ጥያቄን ከመርህ አንፃር እንዲቀበሉ ከፍተኛ ጫና አድርጉባቸዉ እንደነበረ፤ የኢሕአፓንና የሕወሓትን መሠረተ ታሪክ መለስ ብሎ የመረመረም ይህንኑ ሊገነዘብ ይችላል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ ጉዳይ ለመናገር ወይም ለመፃፍ ሲያስፈልግ የግድ የኤርትራን የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ፤ ሲሰፋም ደግሞ የኤርትራን ዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ ታሪክ እንዲሁ በቸልተኝነት ማለፍ እንደማይቻል መገንዘብ ያሻል። ኤርትራዊያንን ንቁ የፖለቲካ አራማጅ ያደረጋቸዉ ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም ተጠቃሽ ከሚባሉት ጉዳዮች አንዱ ምንሊክ ከጣሊያን ጋር የተፈራረመው የመረብ ምላሽ ስምምነት ነዉ። የተባሉት የአፄ ምኒልክ ወገኖች ማማሃኛ ሰበቦች ባይኖሩና የዉጫሌ ዉል ማፍረሻ የሆነዉና ጣሊያንን ከአድዋ ያባረረዉ የኢትዮጵያ ጦር ከኤርትራም አባርሮ አስወጥቶ ቢሆን ኖሮ፤ ኤርትራዊያንና ኢትዮጵያዊያንን የሚያለያየዉ አንዱ ቀዳዳ እዚያዉ ከጅምሩ በተዳፈነ ነበር የሚል አመንክዮ የያዙ ኢትዮጵያዊያን አሉ።

ሁለተኛዉ የኤርትራ ሕዝብ ከስድሳ እስከ ሰባ ዓመታት የሚሆነዉን ጊዜ

በጣሊያን ቅኝ አገዛዝና በእንግሊዝ ወታደራዊ የበላይነት አስጠባቂ አስተዳደር ሥር ነበር ብያለሁ። እዉነቱን ነገር ለመናገር የኤርትራ ሕዝብ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የአዉሮፓ የፖለቲካ ጨዋታ ምን እንደሚመስል በፓርቲ ፖለቲካ አደረጃጀት ቅድሚያ ካላቸዉ ከአዉሮፓዊያኑ ቅኝ ገዢዎች ስለሚያይና ስለሚሰማ ያለምንም ማጋነን በራሱና በአገሩ ጉዳይም ተነሳሽነት ቢኖረዉ ቶሎ የደረሰች ማሽላ አያስመስልበትም። ለዚህም ነዉ እስከ ነፃነት ጥያቄ የደረሰ ተነሳሽነትን ያሳየዉና ወጤታማም ሊሆን የቻለዉ ነው ብለን ብናስብ፤ ዕውነቱን መግለፅ እንጂ አጉል ለኤርትራዊያን ወይም ለሻዕቢያ የተቆረቆርን አይመስለኝም።

ሦስተኛዉ ችግርና የኤርትራ ፖለቲከኞችን ልብ ያሸፈተዉ የኢትዮጵያዉ ንጉስ የአፄ ኃይሌ ሥላሴ የቃል ክህደት ነዉ። ይኸዉም፤ በወቅቱም ሆነ በዛሬዉ የሕብረተሰብ ዕድገት አንፃር የተሻለ ነዉ የተባለዉንና ሐሳብ ሰጭ የዉጪ ሰዎችም ሆኑ ኤርትራዊያን የተስማሙበትን የኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን እንደአደገኛ አርአያ ቆጥረዉ፤ ሕዳር 5፣ 1955 ኮንፌዴረሽኑን አፍርሰዉ ኋላቀር ፊውዳላዊ አሃዳዊ ፖለቲካ ሥር እንዲሆኑ ማስገደድ እና ወደ አንድ ሰዉ አምባገነናዊ አስተዳደር ሥር መመለስ ከድርጊትም፣ ከታሪክም፣ ከዕድገት ትንታኔም አንፃር ተቀባይነት አልነበረዉም።

አራተኛዉና የመጨረሻዉ የኤርትራ ዜጎችን አነሳስቷል ተብሎ ሊታመን የሚችለዉ ዉጫዊ ሁኔታዎች ሆኖ፤ ግን ቀላል የማይባል ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ነዉ። ይኼዉም <ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት> የሚለዉ አባባል ጎረቤት ሙስሊም መንግስታትን ሳያበሳጭ አልቀረም። እነዚያ መንግስታት ደግሞ ጉርብትናቸዉ አነሰም በዛም ሊጎዱ እንደሚችሉ ከግምት ዉስጥ ያስገባ አንድም የአገዛዙ ሰዉ አልነበረም። ደሴት ማለት በዉሃ የተከበበ መሬት ነዉ። <የክርስቲያን ደሴት> የሚሉቱ የግብፅ ኮፕቲክ መልቻይቶች ቀርጸዉ በሰጧቸዉ ፍትሐ ነገስት የሚተዳደሩት የኢትዮጵያ የክርስቲያን ገዢዎች አገሪቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊም ዜጎች እያላትና በዙሪያቸዉም ለሚገኙ ሙስሊም አገሮች አነስተኛ ግምት

በመስጠት እንደዚያ መመፃደቁ ተገቢ አልነበረም። ተገቢ አልነበረም ማለት ብቻ ሳይሆን በፌዴሬሽኑ መፍረስ ምክንያት አኮረፈዉ ዱር ቤቴ ላሉ ለኤርትራ ፖለቲከኞች አስፈላጊዉን ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ እንዲያገኙ አግዟቸዋል።

በሌላም በኩል ኤርትራዊያን ድርጅት አቋቁመዉ እራሳቸዉ መዋጋት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ኢሕአፓ እና ተሀት/ሕወሓት ተቋቁመዉ የራሳቸዉን የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስታት እንዲወጉላቸዉ አድረገዋልና የኤርትራ የፖለቲካ ጉዳይ ያደረሰዉን ተፅዕኖ ቸል ማለት ዕዉነቱን መካድ ይሆናል ያልኩት ይህንን በማስረገጥ ነዉ። ለጊዜዉ ተርፈዋል እንጂ የኤርትራ ነፃነት የፖለቲካ ድርጅቶች ትግላቸዉ የኤርትራን ነፃነት መጎናጸፍ ብቻ ሳይሆን፤ ዓለምሰገድ በጋለ አዳል እንደፃፈዉ ‹‹የወልደአብ የወደፊት ዓላማ የትግራይ ክፍለ ሀገር ተገንጥሎ ከኤርትራ ጋር ተደርቦ ራሱን የቻለ መንግስት ማቋቋም እንጂ ኤርትራን ብቻ ነፃ ማዉጣት አልነበረም።›› (ገፅ 66) በማለት አነሳሳቸዉ በኤርትራ ብቻ እንደማይወሰን አስምሮበት ገልጿል። እንግዲህ የኤርትራን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማኮሰስ ሳይሆን፤ ኤርትራዊያን የኢትዮጵያ ለሆነ ለአንድ ክፍለ ሀገር ማለትም ለትግራይ ክፍለ ሀገር ፓርቲ በማቋቋም የራሳቸዉን ዓላማ ጭምር እንዲፈፅሙላቸዉ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ፖለቲከኞች ነበሩ ለማለት ነዉ።

የሩቁን ትተን የቅርቡን እንኳን ብናነሳ የኤርትራ ፖለቲከኞች ተሀት/ሕወሓትን ከማቋቋም ጀምሮ አራት ኪሎ ምኒልክ ቤተ መንግስት እስከሚገቡ ድረስ አብሮአቸዉ መዓዝ ብቻ ሳይሆን፤ ሕወሓት ፈታኝ ሁኔታዎች ሲገጥሙት፤ በተለይም የደርግን ወታደራዊ ኃይል መቋቋም አቅም ሲያንሳቸዉ የሻዕቢያ የፖለቲካ ሰዎችና በተለይም የኤርትራ መካናይዝድ ብርጌድ የተጫወተዉ ሚና ቀላል እንዳልነበረ እዉነትን የማይሸሽጉ የግንባሩ ሰዎች ማለትም የቀድሞ የሕወሓት ታጋዮች ይናገራሉ። በተለይም በ1983 ሕወሓት/ኢህአዴግ ወደ አዲስ አበባ በሚያደርገዉ ጉዞ ላይ የኢትዮጵያን አየር ኃይል ምድብ በመያዝና

የምስራቁን አቅጣጫ ይዞ የመከላከል እርምጃ ለመዉሰድ የተንቀሳቀሰዉን የጀነራል ተስፋዬ ገብረኪዳንን ልዩ ጦር በመካናይዝድ ብርጌዱ እንዳልነበር ያደረገዉ የሻዕቢያ ጦር እንደሆነ እማኞች ይመሰክራሉ። የኤርትራ ሠራዊትና የፖለቲካ ሰዎች እገዛ ዘልቆ በ1984 የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሠራዊት ትጥቁን ፈትቶ ካምፕ እንዲገባ፤ ከዚያም የጅምላ ጭፍጨፋ በማካሄድ በኩል የአሜሪካን ሰላዮችና የሻዕቢያ ጦር የተጫወቱት ሚና የሕወሓት/ኢህአዴግን ሥልጣናቸዉ ላይ መደላደልን ፈጠረ።

ቀደምት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም ኢሕአፓንና ሕወሓትን በራሳቸዉ አምሳያ የቀረፁት የኤርትራ የፖለቲካ ልሂቃን፤ ዛሬም ድረስ ካላቸዉ የጅኦፖለቲካ ጠቀሜታ የተነሳ በኢትዮጵያ፣ በምስራቅ አፍሪካና በመካከለኛዉ ምስራቅ ዉስጥ ጭምር የሚጫወቱት የፖለቲካ ተፅዕኖ (የዲፕሎማሲ ሥራቸዉ ድክመት እንዳለበት ማወቁ እንደተጠበቀ ሆኖ) እንደዚህ ቀላል ነዉ ተብሎ አይገመትም። ስለሆነም፤ የኤርትራዊያን የፖለቲካ ሚና ዛሬ እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያለዉን የኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ጉዳይ የቀረፀና እየቀረፀም ስለሆነ ቀላል ግምት ሊሰጠዉ አይገባም ብንል የተሳሳትን ስለማይስለኝ ተረጋግቶ ማብሰልሰልን ይጠይቃል። ብዙ ዝርዝር ዉስጥም ባይገባ የኤርትራን የፖለቲካ ጨዋታ ከግምት ባሻገር ማሰብና የሁለቱን አገሮች ሕዝቦች ግንኙነት ዕድልና ግጥምጥሞሽ ጭምር በአዎንታዊ አስተሳሰብ መረዳት ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት የኤርትራ ፖለቲከኞች ተፅዕኖ ከሃያላኑ መንግስታት ተፅዕኖ እኩል ቢሆን እንጂ ያነሰ አይደለም ማለት ስህተት ላይ የሚጥል አይሆንም። የጎረቤት አገሮች ግንኙነትም የአጋምና ቁልቋል ጉርብትና ባይሆን ደካማ የፖለቲካ አስተሳሰብ አያስብልም።

የዚህ መጽሐፍ 2ኛ ዕትም በሚዘጋጅበት ጊዜ ደግሞ የኤርትራ ጦር ለኢህአዴጉ አዲስ አበባ ቀሪ ክፍል በመወገን ድንበር አቋርጦ የሕወሓትን ኃይል ትግራይ መሀል ድረስ ገብቶ በመዋጋቱና ጦርነቱ በከፊልም ሲቆም ተመልሶ ለመውጣት በማንገራገሩ ዛሬም ቢሆን የብልፅግና ፓርቲ ፖለቲካ

ጉዳይ በእጅ አዙርም ቢሆን ከኤርትራ ተፅዕኖ ነፃ እንዳልሆነ ያመለክታል። ስለሆነም፤ የኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ዕድገትም ሆነ ዝግመት ከኤርትራ ተፅዕኖ ነፃ እንዳልሆነ መናገርም ሆነ መፃፍ ተገቢ ነው።

## በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተፅዕኖ

መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አሉ። ዓለም አቀፍ ድርጅት ማለት በዓለም ላይ የሚገኙ መንግስታትና ድርጅቶች የተሰባሰቡበት ሁሉ ባይሆንም ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ አገሮች ወይም ከሁለትና ከዚያ በላይ ከሆኑ አገሮች ድርጅቶች የሚወከሉበትና የታቀፉበት ድርጅት ነዉ። ይህንን እንደ መግቢያ ለማንሳት ተፈልጎ ነዉ እንጂ ለማንሳት የተፈለገዉ ነገር፤ እነዚህ ዓለም አቀፍ የሚባሉ ድርጅቶች በዓለም አገሮች ፖለቲካ ላይ በተለይም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ያሳደሩትንና ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተፅዕኖ ለመመልከት ተፈልጎ ነዉ።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዛሬ ደግሞ የአፍሪካ ሕብረት እንደተቋቋሙለት ዓላማ ረሃብ፣ ድህነትና በሽታን እናጠፋለን፣ ሰላምን እናሰፍናለን በማለት ይሰራሉ። በርግጥ በነዚህ በሰዉ ልጅ ጠላቶች ላይ ሲሰሩ ጣት ሊቀሰርባቸዉ አይገባም። ነገር ግን ሊሰመርበት የሚገባዉ ነገር ቢኖር ረሃብ፣ ድህነትና በሽታ መኖራቸዉና እነሱን ማጥፋትም እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ነገር ግን የእነዚህ ችግሮች መንስኤ በአባል አገሮች ዉስጥ የቆሙ መንግስታት ወይም ድርጅቶች በሕዝብ የተመረጡ ወይም ሕዝባዊ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ወስደዉ የማይሰሩ መሆናቸዉ እየታወቀ፤ በመፈንቅለ መንግስት ሥልጣን ለያዘ ወይም በሕገ መንግስቶቻቸዉ ሥልጣናቸዉን የሚገደብ አንቀፅ የሌላቸዉ መሪዎች፣ ወይም ሕገ መንግስታቸዉን ወደሚያመቻቸዉ የሚጠመዝዙ መሪዎች ያሉበትን አገሮች መንግስታት፣ ሲበዛም ደግሞ የሕዝቦችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚደፈጥጡ አምባገነኖችና ሕዝቡን ለረሃብ፣ ድህነትና በሽታ የሚያጋልጡ መንግስታትና የመንግስት መሪዎችን ዓመታዊ በዓላቸዉን ወይም ስብሰባቸዉን እየጠበቁ የእንኳን

አደረሰህ የመልካም ምኞት መግለጫ ማዥጎድጎዳቸዉ፤ የዚያ አገር መሪዎች የታቀፉባቸዉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ ሕዝብ የሚጥልባቸዉ እምነት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሸረሸረ ይሄዳል። ይህ ችግር በአፍሪካ ላይ ደግሞ ገንኖ የሚታይ ነዉ። አንድ ምሳሌ ብቻ ማስቀመጥ በቂ ይመስላል፤ የቀድሞዉ የዩጋንዳ ፕሬዝዳንት ኢዲ አሚን ዳዳ ጨካኝ አምባገነን የአገሩ መሪ ከመሆኑም በላይ የሰዉ ሥጋ የቀመሰ ስለመሆኑ ወሬዉን ሳይሰሙ ያልቀሩ የአፍሪካ መሪዎች፤ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ ላይ ከወንበራቸዉ ብድግ ብለዉ በጭብጨባ ሲቀበሉት ያለፈ ተረት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ተመሳሳይ ወንጀል የሚፈጽሙ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎችን መታደጉ በሕዝቦች መብት ላይ መቀለድ ማለት እንደሆነ መግለፅ አያስቸግርም።

አገራችን ኢትዮጵያ አገራዊም ሆነ አከባቢያዊ ምርጫዎችን ሲታካሄድ የአፍሪካ ሕብረት በታዛቢነት እንዲገኝ ይደረጋል። በነዚህ ምርጫዎችና በሌሎችም ጉዳዮች ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ተበደልን፣ ድምፃችን ተዘረፈ በሚሉበት ወቅት ላይ የአፍሪካ ሕብረት ታዛቢዎች ለገዥዉ ፓርቲ ሕወሓት/ኢህአዴግ በመወገን ምርጫዉ ዲሞክራሲያዊ፣ ተአማኒና ተቀባይነት ያለዉ ነዉ በማለት መግለጫ ያወጣሉ። መጥፎ ድርጊታቸዉም የሕብረቱ ክፉ ባህል ሆኖ ብዛት ያላቸዉና ዋና ዋና የሚባሉ ፓርቲዎች ያልተሳተፉበትን 6ኛዉን የቁጩ ምርጭ የአፍሪካ ሕብረቱ ኮሚሽነር ሙሳ ፋኪ ማሃሜት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ነዉ አረፉት። እነዚህ ድርጊቶች በተራቸዉ፤ ሥልጣን ላይ ላሉት ጥቂት ቡድኖች ማድላታቸዉ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጎ አመለካከት የሌላቸዉ መሆኑን ከማመላከቱም በላይ እንደዚያ ዓይነት መግለጫ የሚሰጡ የአገር መሪዎችና ተወካዮች በየአገሮቻቸዉም ትክክል ያልሆነዉን ትክክል ነዉ የሚሉ ፍጡራን እንደሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። ይህንንም በማድረጋቸዉ በኢትዮጵያ ፓርቲ ፖለቲካ ላይ ወንጀል የሰሩ ናቸዉ። ዴቭድ ላምብ የተባለዉ ጸሐፊ የአፍሪካን አህጉር የገለጸበት ሁኔታ የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ የጠመዘዙ የአፍሪካ ሕብረት ሰዎችን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገልጽ ነዉ። እሱም እንዳለው (1984፡ 7) “በመቶ

ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዘራቸዉ ምክንያት ብቻ የሚገደሉበትን አህጉር እንዴት አድርጎ መግለፅ ይቻላል? የአንግሊካን ሊቀ ጳጳስን ጨምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳዊያንን የጨፈጨፉት ኢዲ አሚን ለዓመታዊ ስብሰባ አፍሪካ አዳራሽ ሲገቡ በከፍተኛ አድናቆት እያጨበጨቡ የሚቀበሏቸዉ መሪዎች ያሉበትን አህጉር ምን ብሎ መግለፅ ይቻላል?" ብሎ በግርምታ የገለጸበትን ሁኔታ ኢትዮጵያዊያን በተለይም የፓርቲ ፖለቲካ የሚያራምዱ ዜጎች የሚረዱት የታሪክም የወቅቱም ዕዉነት ስለሆነ ነዉ። እንደ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ (1998፡ 415) ምስክርነት ደግሞ የ1997ቱን "የኢትዮጵያ ምርጫ ነፃና ፍትሐዊ እንደነበር የመሰከረዉ ብቸኛ ድርጅት የአፍሪካ ኅብረት ነዉ።" ሲል፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶቹ አያስፈልጉንም ባይባል እንኳን ኢትዮጵያዊያንን የሚጎዳ እንደዚያ ዓይነቱን ሪፖርት ሲሰጥ ሕዝቦች ከሚጠብቁት በታች ስለመሆናቸው አሌ የሚል አይኖርም።

በሌላም በኩል ይኼዉ አህጉራዊ ድርጅት በመፈንቅለ መንግስት ሥልጣን የሚይዙትን ኃይላት ከአባልነት እስከ ማግለል እርምጃ ይወስዳል። ነገር ግን የምርጫ ኮሮጆ ሰርቀዉና ሕገ መንግስቶቻቸዉን ጠምዝዘዉ ሥልጣን ላይ ስለሚቆዩ አምባገነን መንግስታት ወይም ፓርቲዎች ጋር የሰንበቴ ማህበሩን ግንኙነት ያለምንም ጥያቄ ይቀጥሉበታል። ያለፈው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ሆነ የወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት የመንግስታትን ሉዐላዊነት በማክበር ስም በአባል አገራቱ ውስጥ የሚካሄደውን የመብት ረገጣ አይተው እንዳላዩ የሚያልፉ በቁሙ የሞተ ድርጅት ነው። መሠረቱን አዲስ አበባ ከአደረገዉ በዚህ ድርጅት ከተበደሉት ሕዝቦች ኢትዮጵያዊያን አንዱ ናቸዉ። ስለሆነም፤ ኢትዮጵያዊያን አገሪቱ አባል ከሆነችበት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚፈልጉት እንኳን ባይሆን የሚገባቸዉን ከበሬታና ጥቅም አላገኙም። በመሆኑም የኢትዮጵያን የፓርቲ ፖለቲካ አካሄድ እንዲዳከም የአፍሪካ ሕብረት እንደ እብድ ገላጋይ ዱላ ያቀበለ ነዉ። መቀመጫውን አዲስ አበባ ላይ ያደረገውና ከፍጥርጥሩ ጀምሮ እስከ አመራሩ ድረስ ድክመት ያለበት የአፍሪካ ሕብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ነፃ እና ፍትሓዊ ነበር ብሎ የውሸት ምስክርነት የሰጠ ከዓለም ብቸኛ ድርጅት ሲሆን፤ ከዚህ የተነሳም

ለሌላ ጉዳይም ቢሆን በሕብረቱ ላይ እምነት መጣል አይቻልም።

ይህንን አርእስት ከማጠቃለሌ በፊት ቀዳሚው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ሆነ ወራሹ የአፍሪካ ሕብረት ወቅታዊ ጊዜ እና ሁኔታዎች የሚጠይቋቸውን አሁናዊ ፈተናዎችን ለመመለስ የሚያስችላቸው ደረጃ ላይ የደረሱ አይምስልም። ምክንያቱ፤ የአውሮፓ ሕብረት የመሰሰሉ አህጉራዊ ድርጅቶች አባል አገሮቻቸውን ለማስገደድ አንድም የተሟሉ ሕግጋትን ቀርፀው ይንቀሳቀሳሉ፤ በሌላም በኩል አባል አገሮች የሆነ ችግር ሲገጥማቸው ሊያግዙ ይችላሉ። የሚከበር የተሻሻለ ሕገ ደንብ የሌለውና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለአባላቱም ሆነ አባላቱ ላይ ምንም ማድረግ የማይችል ድርጅት ማሰቡ ራሱ አስቸጋሪ ነው። አህጉራዊ ድርጅቱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ቀጣናዊ ድርጅቶችም እንደሚወክሉት ቀጣና ችግሮቻቸው እጅግ ሲበዛ ሰፊ ነው። ለምሳሌ፤ የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናዊ ድርጅት ኢጋድ አባል አገራቱ ከኬንያ በስተቀር የውስጥና የድንበር ግጭቶች አሏቸው። ይህ ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ ምርጫ ውስጥ የኮሮጆ ግልበጣ ሥራ ሲሰራ የነበረ ሰው እንዴት አድርጎ ከጥቅም ግጭት ራሱን ነፃ አድርጎ የኢጋድን ጽ/ቤት በመወከል የኢትዮጵያን ወቅታዊ ምስቅልቅል ችግር ለመፍታት አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚለው ጥያቄ መልስ ቢኖረውም ለጊዜው ግን ፈታኝ ነው።

የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ፡ ኢትዮጵያዊያን ፖለቲከኞች የቤታችንን የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ከምቀኝነትና ከሽፍጥ በፀዳ መልኩ ለመስራትና ለመምራት ባለመቻላችን የቅርብም ሆነ የሩቅ አገር መንግስታት፣ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች በአገራችን ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡ ጋብዘናል። አንዲት ኮሪያ ለሁለት ልትሰነጠቅ የቻለችው ኮርያዊያን የሸፍጠኞችን ሴራ በትክክል ለመረዳት ባለመቻላቸው እንደሆነ ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም የውስጥና የውጪ የፖለቲካ ሸፍጠኞችን በትክክል ሳንረዳ በመቅረታችንና ብዙውን ጊዜ ከተሸናፊነት ሥነ ልቦና የሚያላቅቀን ንቃት ያለዉ ዜጋ (active citizenship) እና ብቃት ያለዉ መንግስት (effective state) ባለመገንባታችን አገራችንን ከደህነትና ኋላቀርነት ማላቀቁ ቀርቶ ለብተና

እንዳንዳርግ መለስ ብሎ ማሰቡ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ግዴታ ነው። ከምቀኝነትና ሽፍጥ የፀዳ የፖለቲካ ሥራ መምራት አለመቻል ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን አድርገን እንዳናስብ ስለሚያደርግ፤ የአገራችን ዕድገት አዝጋሚ እንዲሆን ወይም ወደኋላ እንዲጎተት የሚያደርግ ሲሆን ዉሎ ሲያድር ግን በኋላቀርነታችን የዓለም ቱሪስቶች መስህብ እንዳንሆን ያሰጋል።

## ምዕራፍ አምስት፡ ከፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ እንደመውጫ፡

ዛሬ ዓለማችን ከሁለት መቶ በላይ በሚሆኑ አገሮች ተከፋፍላ ትገኛለች። አፍሪካ ለብቻዋ 55 ያህል አገሮችን አዋጥታለች። ወደፊት ተጨማሪ አገሮችን ታዋጣለች፣ አታዋጣም ጊዜ ብቻ ሊመልሰዉ የሚችለዉ ነገር ነዉ። በሱማሊያ፣ በኢትዮጵያ፣ በሱዳን፣ በማሊ፣ ወዘተ ተጨማሪ ትናንሽ አገሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ግን አመላካች የሆኑ የችግር ምልክቶች አሉ። ከችግሮቹም ለመቀንጨብ ያሕል የዲሞክራሲ መቀጨጭና የአምባገነንነት መንሰራፋት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ የድህነት ሥር መስደድ፣ የገበያ አለመረጋጋት፣ የመሳሰሉ ችግሮች ለብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች መፈጠር አመላካቾች ናቸው። ችግሩም ከሚታይባቸዉ አገሮች ዉስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ነች ቢባል ራስን ዝቅ አድርጎ እንደማየት እንደማይቆጠርብኝ አምናለሁ።

እነዚህ ከሁለት መቶ በላይ የዓለም አገሮች የደረሱበት የዕድገት ደረጃም ያደጉ፣ በማደግ ላይ የሚገኙና ኋላቀር አገሮች በመባል በሦስት ደረጃ ይፈረጃሉ። ለሁለት እንክፈላቸው ከተባለም የበለጸጉና ድሃ አገሮች ተብለው ይመደባሉ። አገራችን ኢትዮጵያ ሌላው ቢቀር ራሷን መመገብ ያልቻለች ኋላቀርና ድሃ ከሚባሉ አገሮች መደዳ ትሰለፋለች። የአገሮቹ የዕድገት ደረጃ በሦስት ወይም በሁለት ደረጃ ይከፈል እንጂ የአንደኛዎቹና የሦስተኛዎቹ ደረጃ መራራቅ የትየለለ ነዉ። በዜጎች ደረጃ ደግሞ የመጠቁ ሀብታሞችና ፍጹም የደኼዩ የድሃ ድሃዎች የሚባሉ በኢትዮጵያ ይገኛሉ። ምድራችን የተፈጠረችዉ አንድ ሰሞን ቢሆንም የሚኖራቸዉ የሀብት ልዩነት ሰፊ ነዉ። አንዳንዱ አገር የተንበሸበሸ የተፈጥሮ ሀብት ሲኖረዉ አንዳንዱ ደግሞ ራቁቱን የተወለደና ራቁቱን የቀረ ይመስላል። አስገራሚዉ ነገር ግን የተንበሸበሸ የተፈጥሮ ሀብት ሳይኖራቸዉ የተንበሸበሸ ሕይወት መምራት የቻሉ አገሮች ለምሳሌ ጃፓንን የመሳሰሉ አገሮች ከማደግም በላይ ተመንድገዉ የሚገኙ አገሮች መሆናቸዉ ነዉ።

ለአገሮች የዕድገት ልዩነት ተጠቃሽ እና ተከሳሽ የሚሆኑ ነገሮች አሉ።

የተፈጥሮ ሀብት በብዛት የመኖርና ያለመኖር ልዩነት፣ የአየር ንብረት ምቹነት፣ የአየር ንብረት ብልሹነት፣ ታታሪ የሰዉ ኃይል መኖር፣ ስንፍና ጎጆ የሰራባቸዉ ሰዎች በብዛት መኖር፣ የአምላክ ቁጣ፣ ብልሹ አስተዳደር፣ መሀይምነት፣ ኋላቀር የአመራረትና አጠቃቀም ባህል፣ ለምርታማነት የማያመቹ አሳሪ አምልኮ የመሳሰሉ ክስተቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ደግሞ የጥሬ ሀብት ዘረፋ፣ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ዝርፊያ (የባሪያ ሽያጭ፣ ቅኝ አገዛዝ፣ ስዉር ቅኝ አገዛዝ፣ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ማስኮበለል) የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ለኢትዮጵያችን ኋላቀርነት ሁሉም የየራሳቸዉ መዋጮ እንዳደረጉና ከድህነት ማጥ እንዳንወጣ የተፈረደብን ሁኔታ እንዳለ ነዉ፡፡ የሩቅ አካልን ከመኮነን ታቅበን እይታችንን ወደ ዉስጥ ብንመልስ ደግሞ ሕብረተሰባችን መሀይም በመሆኑ፤ ስለዕድገት መብት የሚጠይቅ ንቁ ማህበረሰብ ፈጥረን ወደ ዕድገት የምናመራበት መንገድ ገና ብዙ ሩቅ ነው፤ ወይም ወጣ ገባነቱ ረጅምና አድካሚ ነው፡፡ አብዛኛዉ የሕብረተሰባችን ክፍል ማንበብና መጻፍ አይችልም ብቻ ሳይሆን ተማረ የሚባለውም የምርምርና የፍልስፍና ጽሑፎችን ማንበብ ቀርቶ ዘር ብለው ዱሮ የተማሩበትን ደብተር የማያነሱ ሰዎች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡ ቁጥሩ ወደ ጠቅላላ ሕዝቡ ግማሽ የሚጠጋ ሕዝባችን በድህነት የሚማቀቁም ስለሆነ ሁለትና ሦስት መብላት የሚባል ነገር ቀርቶ አንዱም ጊዜ በጣር የሚሆንበት ሁኔታ ስለመኖሩ አንድና ሁለት የለዉም፡፡ ይህ የተጎሳቆለ ኑሮ የሚኖር ሕዝብ ደግሞ ስለምርምር፣ ፍልስፍና እና ስለፓርቲ ፖለቲካ ማወቁ ቀርቶ መስማቱንም አያስታዉስም፡፡ ያገራችን ገዥዎች ደግሞ “መሀይምና ድሃ ከፖለቲካ ውጭ ነዉ” የሚለዉን ስለሚያዉቁ፤ ይህንን ተጠቅመው የአገዛዛቸዉን ዕድሜ ማራዘሚያ መረማመጃ ስለሚያደርጉ፤ ስለሕዝቡ ከመሀይምነት መላቀቅ የሚለው ደንታም አይሰጣቸዉም፡፡ ገዥዎች ማጅራታቸዉና ቀፈታቸዉ እያበጠ በሄደ ቁጥር የወጡበትን ሕዝብ ከመርሳታቸዉ የተነሳ እንወክላለን የሚሉት ሕዝብ ቢያንስ ከውሃ ወለድ በሽታ አለመላቀቁን አያስቡትም፡፡ ሲጠቃለል፤ እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች፤ አንዳንዴም በባሰበት ሁኔታ አሳታፊ የፖለቲካ ሁኔታ እና ሃላፊነትና ተጠያቂነት የሚንፀባረቅበት የፖለቲካ አውድ ኢትዮጵያ ውስጥ

የለም።

በዚህ መፅሐፍ ዉስጥ በተለያዩ ምዕራፎች ለመግለፅ እንደተሞከረዉ የአስተዳደር ሁኔታ ምቹ ባለመሆኑ አገራችን ኢትዮጵያን የድሆች ድሃ እስከማስባል አድርሷል። በ1847 አፄ ቴዎድሮስ ሥልጣን የያዘበት ጊዜ እንደነበር ገልጫለሁ። አምባገነናዊ አስተዳደር መሠረቱን የጣለው ያኔ እንደነበር የሚገልፁ ሰዎች  የመኖራቸውን ያህል፤ ባለራዕዩ ንጉስ ባይነሳ ኖሮ የዛሬዋ ኢትዮጵያ አትኖርም ነበር ብለው አፄውን የሚያሞካሹ የተለያየ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች አሉ። ምንም እንኳን በሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች ገዥዎች የሚመራ ብዛት ያላቸው የእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት የነበሩ ቢሆንም፤ የዛሬውን የኢትዮጵያን አንድነት ለመፍጠር ወይም የሀገረ መንግስት ግንባታ ሂደት ውስጥ የተከፈለ ዋጋ ቢሆንም በሺህዎች የሚቆጠሩ ሕዝቦች በግፍ ስለመጨፍጨፋቸው የሚካድ አይደለም። አፄ ቴዎድሮስ የወቅቱን ኢትዮጵያን በዕደ ጥበብ (ቴክኖሎጂ) ለማሳደግ ሕልም የሰነቀ መሪ ነበር ብለዉ የሚያምኑ ቢኖሩም፤ ቴዎድሮስ ጨርሶም ባይፈጠር ኖሮ እስከዛሬ ድረስ የሚታየዉ ክፉ ምቀኝነትና ዜጎችን ያለርህራሄ ጭፍጨፋ መሠረቱን ባልጣለ ነበር የሚሉ የመኖራቸዉ ነገር ሳይዘነጋ፤ የቴዎድሮስ የትኩረት አቅጣጫው ግን ተቀናቃኞቹን ለማጥፋት ከጦር መሳሪያ ምርት ከማግኘት የዘለለ አልነበረም። አስቂኙ ነገር ግን ተከትለው የመጡትና የሰለጠነ ሀገራትን በአካል ያዩ የኢትዮጵያ መሪዎች ነን የሚሉት ሰዎች አፄ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር፣ መንግስቱ ኃይለማርያም ታሪካዊ ኃላፊነት የተጣለብኝ ነው ሲል፣ መለስ ዜናዊ ያለአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሌላው አመለካከት አሸባሪ ነው ያለትና ዛሬም በ21ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ሳይቀር ለኢትዮጵያ ወቅታዊም ሆነ የቆዩ ችግሮች መፍቻ ቁልፍ አንድ ´መደመር` ነው የሚሉት ዘይቤ ለኢትዮጵያዊያን ድህነትና ኋላቀርነት እንዲሁም ለፓርቲ ፖለቲካ መቀጨጭ ተጠቃሽ ናቸው።

የአፄ ተክለ ጊዮርግስና የአፄ ዮሐንስ የአገዛዝ ዘመናት የውጭ ወረራን ለመፋለም በተደረገዉ ትግል ዉስጥ ያለፈ ስለነበር፤ ለወቅቱ  የኢትዮጵያ

ዕድገት ሐሳብ ለማመንጨትም ሆነ መሬት ለማስያዝ ጊዜዉንም ሳይኖራቸዉ ሁለቱም አልፈዋል፡፡ በተለይም ቴዎድሮስን ለመጣል ከእንግሊዙ ናፒየር ጋር የተመሳጠረዉ አፄ ዮሐንስ ሥልጣን መቆናጠጡ እንጂ የጣሊያን በቀይ ባህር አከባቢ እግር መትከል ብዙም ያሳሰበው አይመስልም፡፡

አፄ ምኒልክ ወገኖቹን መግቦ ለማኖር ድብቅ የኢኮኖሚ ጉዳይ ይዞ ወደ ደቡብ አጎራባች ነፃ ሕዝቦች እና አገሮች መዝመቱ ዛሬ ድረስ የምኒልክ ጫማ ዉስጥ ለሚኖሩ የአበሻ ልጆች ትክክል ነበር ማለት ብቻ ሳይሆን ወቅታዊም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምኒልክ የምዕራቡን ዓለም ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ያደረገዉ ጥረትና የፈጸመዉ ሥራ በዚያን ዘመን ላይ ሆነዉ ቢመለከቱት ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የተሸነፈዉ ሕዝብ ለዘላዓለሙ መቀጣጫ እንዲሆን ተብሎ የተወሰደበት ጡትና ብልት የመቁረጥ እርምጃ በቀጣይ ትውልድ ላይ ላይደገም መወገዝ ሲገባ ባለመወገዙ ወይም ተደስብሶ በመታለፉ በሚናገሩትም ሆነ በሚያደበስብሱት መሀከል አንድ የወንጀል ቅርስ አኑሮ ያለፈ ነበር፡፡ በተለይም ከሐበሾች ገዥ ቡድኖች ውጪ ያሉ ሕዝቦች ማህበራዊ ዕሴቶቻቸዉ መጨፍለቅ ለወቅቱም ሆነ ተከትለው በመጡት ጊዜያት ውስጥ ለተከሰቱት ማባሪያ ላልተገኘላቸው መናቆሮች መሠረቱን የጣለ ነው፡፡ ከፍ ተብሎም ሲታይ የምኒልክ አስተዳደር በራሱ ብቻ ያበቃ ሳይሆን በቀጣዮቹ መንግስታት ማለትም ከአፄ ኃይሌ ሥላሴ እስከ ሕወሓት/ኢህአዴግ ድረስ የቀጠለዉ መጠላለፍ በምኒልክ መሠረቱን የጣለ ነበር ለማለት እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም ኢያሱን፣ ዘዉዲቱን፣ ጣይቱን ጠልፈው የጣሉት እና ተፈሪን ለሥልጣን ያበቁት የደብተራ ኃይሎች በምኒልክ አገዛዝ ዉስጥ መፈልፈል የጀመሩት የሕዝቦች ፍቅርና አንድነት ጠላፊዎች እንደነበሩ ማሰብ ቂም በቀል መቋጠር አያስብልም፡፡

የወቅቱ የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ ከደረሰበት ዕድገት ደረጃ አንፃር፤ በተለይም ደግሞ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት ማክተም በኋላ ከአገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መዉጣት ጋር ሲነፃፀር የአፄ ኃይሌ ሥላሴን አገዛዝ

የተሻለ አስተዳደር ማድረግ ነበረበት። በወቅቱም ቢሆን አደጉ ከሚባሉት አገሮች ጋር ንጉሱ የነበረዉ ግንኙነትና ቀረቤታ ያን ያህል ዝቅተኛ ነው የሚባል አልነበረም። ምኒልክ እንኳ ወገኖቹን ለመመገብ ሲል ወደ ደቡብ ነፃ ጎረቤት አገሮች (ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ሃዲያ፣ ከንባታ፣ ወላይታ፣ ሐረር፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ወዘተ) የዘመተዉን ያህል አፄ ኃይሌ ሥላሴ የመሬትን ምርታማነት ለማሻሻል ያደረገዉ ጥረት ባለመኖሩ ወደ ሥልጣኑ ማክተሚያ አከባቢ ማለትም በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ለሳሎን ውሻው ጮማ ሲቆረጥ ሕዝቡ በጠነ ይረግፍ ነበር። በጥቅሉ የኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ኢትዮጵያን ሌሎች የዓለም አገሮች ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ አለማድረሱ ብቻ ሳይሆን የራሱ ቤተሰባዊ የሥልጣን ቅብብሎሽ ሳይቀር ቀጣይነት ባለዉ መልክ እንድሄድ ለማድረግ የነበረዉ ተነሳሽነት ጨርሶም ስላልነበረ የሕዝብን ወሳኝነትና የፖለቲካ ሀሁን በማያዉቁ ወታደሮቹ ሊገለበጥ ችሏል።

ዓለም በሁለት ጎራ ተከፋፍላ በነበረችበት ወቅት ላይ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የምስራቁን ዓለም ጎራ በመምረጡ ስህተት ላይሆን ይችላል። ከመረጠዉ ርዕዮተ ዓለማዊ ባህርይ ወይም ከአመራሩ እንደሆን አይታወቅም፤ መስመሩን የሚቃወም ሁሉንም ሰዉ የአብዮቱ ጠላት ብሎ ከመፈረጁም በላይ የአብዮቱ ወዳጅ የሚላቸዉንም ጭምር በጥርጣሬ መመልከቱ የደርግን ሥልጣን ለመቀማት የተንቀሳቀሱ ብቻ ሳይሆኑ ዝምታን የመረጡ ዜጎች ሳይቀሩ በጠራራ ፀሐይ ከየቤታቸዉ፣ ከሥራ ቦታቸውና ከመንገድ እየተጎተቱ ተጨፍጭፈዋል። ደርግ የሰለጠነ ፖለቲካ የሚባለዉን ማራመድ የሚለዉ እሳቤ ከደጃፋም ባለማለፉ በጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይቶ ችግሮችን መፍታትና ልዩነቶችን ማቻቻል የሚለዉ አየር ባለመፈጠሩ ብሔራዊ የአርነት ንቅናቄዎች እንደአሸን ፈልተውበታል። ፀረ ሶሻሊስትና ፀረ ደርግ አቋም በነበራቸዉ መንግስታት የተደገፉ ኃይሎች ከየአቅጣጫዉ ስለወጉትና በመጨረሻም የሶሻሊስት ኃይሎችን ካምፕ ለማዳከም የተንቀሳቀሱ ካፒታሊስት ምዕራብ አገሮች የሶሻሊዝም ቁንጮ የሆነችዉን አገር ሶቭዬት ሕብረትን ስለበታተኑ፤ ኢትዮጵያም ሁለት አገሮች (ቀደምቷ ኢትዮጵያና ኤርትራ) እንዲወጧት

ተደርጎ፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ) መንግስት ግብአተ መሬት ግንቦት ወር 1983 ተደመደመ። ሲነፃፀር ግን ደርግ ጦርነትን እየተዋጋ ያስመዘገበዉ የኢትዮጵያ ዕድገት ከረጅሙ የኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነበር ማለት ይቻላል። ነገር ግን ሌሎች አገሮች በተለይም ቅኝ አገዛዝ ሥር የነበሩ አገሮች ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ አንፃር ሲመዘን የሕዝቡ ዕድገት ኋላቀር ከሚባል አኗኗር የተላቀቀ አልነበረም ማለት ብቻ ሳይሆን ዕድገትን ያመጣሉ የሚባሉ የአገሪቱ የተማሩ ዜጎችና ትንሽም ቢሆን ዓይናቸዉን የከፈቱ ሰዎች ሕይወታቸው ተቀጥፏል፤ የተቀሩትም ሕይወታቸዉን ለማትረፍ ሲሉ ከአገር እየኮበለሉ በዓለም ላይ የተሰራጩበት ጊዜ ቢኖር ደርግ ይገዛ በነበረበት ከ1967 እስከ 1981 በነበረዉ ጊዜ ዉስጥ ነበር። ይህንን ተከትሎም የአገር ግንባታዉ አመራር በዓመት አንድ ጋት ማስከድ ለማይችሉ ጉልበተኞች ተላልፎ ተሰጥቶ ነበር። ከደርግ አስከፊ ወንጀሎች አንዱ የሆነዉ ዜጎች በአገራቸዉ ፖለቲካ ዉስጥ እንዳይሳተፉ ለማድረግ፤ ቀደምት ፓርቲዎችን መኢሶንና ኢሕአፓን በፀረ አብዮትነት፤ ሌሎችን ደግሞ በመዋጥና በመጨፍለቅ በተለይም ምሁራን በአገራቸዉ ጉዳይ ኃላፊነት ተሰምቷቸዉና አእምሮአቸዉን ጨምቀዉ እንዳይሰሩ ጋሬጣ መሆኑ ነበር። ምሁራኑ፤ ያኔ የወደቀዉ ሞራላቸዉ ዛሬ ድረስ ሊያንሰራራ ባለመቻሉና ከነገሰባቸዉ ፍርሃት ሊላቀቁ ባለመቻላቸዉ የአምባገነኖች ጨካኝ እርምጃ የወቅቱን ብቻ ሳይሆን ቀጣዩን ትዉልዱን ጭምር አንድም እንደሚገድል ወይም የገዢዎቹ ባርያ እንደሚያደርግ ከዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ምሁራን ክፉ ሥራዎች ማየት እንደሚቻል ለአፍታም መዘንጋት አይቻልም። ሌላም ክፉ ነገር አለ። ይኼውም፤ አውሮፓ ውስጥ አስኳል የፈጠሩት መኢሶንና ኢሕአፓ አገር ቤት ተመልሰው፤ መኢሶን ከደርግ ተጠልሎ ኢሕአፓን ጠልፎ መጣሉ አንድ ማህበራዊና ፖለቲካዊ በሽታ እንደሆነ አይጠፋንም የሚል እሳቤ አለኝ። ቢሆንም ግን አምባገነኖች ተገፍትረዉ መዉደቃቸዉ አይቀረ መሆኑ እየታወቀ፤ አስተዋይ ልቦና ያላቸው ሰዎች ባለመፈጠራቸዉ እንጂ የኢትዮጵያ ገዢዎች አወዳደቅ በተመሳሳይ ሁኔታ መሆኑ ትምህርት መሆን ነበረበት። የኢትዮጵያ መሪዎች የሚባሉት

ሁላቸውም ሲወለዱ ወይም ሥልጣን ላይ ሲፈናጠጡ ተገፍትራቸሁ ትወድቃላችሁ የሚል ዐረፍተ ነገር ግንባራቸዉ ላይ የተፃፈላቸዉ ይመስል ተራ በተራ ተገፍትረዉ ወድቀዋል።

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን በትጥቅ ትግል በማስወገድ አልጋዉን የተረከበዉ ሕወሓት/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ዜጎች በሁለት ልብ ተቀብለዉታል። አብዛኛዉ የሚባለዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የግንዛቤ ደረጃዉም ዝቅተኛ በመሆኑና በቀደመዉ መንግስትም የተጎዳ ስለሆነ፤ ከደርግ የማይሻል መንግስት አይመጣም በሚል እምነት እጃቸዉን ዘርግተዉለታል። ውስን የሆነዉ ሕዝብ ግን በጥርጣሬ መመልከቱ አልቀረም። በጥርጣሬ ከመመልከትም አልፈዉ ሠላማዊ ሰልፍ የወጡ አእምሮአቸዉ ብሩህ የሚባሉ ሰዎች ነበሩ ብለን በኩራት የምናስታዉሳቸዉ ዜጎች ነበሩ። ምክንያታቸዉ ደግሞ ለሁሉም ሰው ግልፅ ባይሆንም፤ ሕወሓትን ለአዲስ አበባ፣ ሻዕቢያን ለአስመራ ቤተ መንግስቶች ያበቃቸዉ ሕዝባዊነታቸዉና ዲሞክራሲያዊነታቸዉ ሳይሆን ፀረ-ሶሻሊስት አቋም ከሚያራምዱ ምዕራባዊያን ሀብታም አገሮችና ከፊውዳሉ ቅሪቶች የተለገሱት ገደብ የለሽ የመሳሪያና የገንዘብ ዓይነት ዕርዳታ መሆኑን በወጉ ስለተረዱበት ነበር። ጥርጣሬያቸዉም ከተራ ጥርጣሬ ያለፈ ስለመሆኑ ብዙም ሳይቆይ ኢህአዴግ ሥልጣኑን ተቆጣጥሮ ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ የሽግግሩን ሥርአት ለመመስረት በተጠራዉ የሠላም ኮንፌረንስ ላይ ፓርቲዎች የኋላ ታሪካቸዉ እየተመዘዘ ኮንፌረንሱን እንዳይሳተፉ በመደረጉ ነዉ። ለምሳሌ ኢሕአፓ በ1965 በኤርትራ በረሃ በኩል ወደ አገር ዉስጥ ከሚገባበት ጊዜ ጅምሮ ከሕወሓት ጋር በነበረዉ ቁርሾ የተነሳ እስከነመኖሩም የተረሳ ፓርቲ እንዲሆን መደረጉና የኢሕአፓ ሕልዉና ጥያቄ ምልክት ዉስጥ መውደቅ ሳይሆን የሕወሓት/ኢህአዴግ የማግለል ተንኮል መሆኑ የማይካድ ነው። መኢሶንም ብዙም ከኢሕአፓ ባልተለየ ሁኔታ አንደኛ ምናልባትም አደረጃጀቱ ሕብረ ብሔራዊ ስለሆነ፤ ሁለተኛ ሕወሓት ከሚያራምደዉ የብሔር ፖለቲካ ጋር ባለመጣጣሙ፤ በሦስተኛም መኢሶን ከደርግ ጋር ወግኖ ሲያራምድ በነበረዉ የፖለቲካ መስመርና ዕርምጃ አወሳሰድ ጋር

በተያያዘ ከሕወሓቱ ኮንፈረንስ እንዲገለል ተደርጓል። መኢሶንን በማግለል ብቻ ሳይበቃው አባሉ የነበረውን አበራ የማነአብን ግፍን የማይፈራው ሕወሓት በግፍ አስራ ሁለት ዓመታትን አስሮ አሰቃይቶታል።

በሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ዉስጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተካሰዉ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ለማለት ይቻላል። ይኸዉም በአፄ ኃይሌ ሥላሴ አገዛዝ አንድም የተደራጀ የፖለቲካ ኃይል እንዳይኖር የተደረገበት ጊዜ ሲሆን፤ በደርግ ጊዜ ደግሞ ምንም እንኳን ጥቂት የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደጠዋት ጤዛ ታይተዉ ረፋዱ ላይ የተነኑበት ሁኔታ ያጋጠመ፤ በሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ግን የፓርቲዎች መፈልፈያ ማሽን ኢትዮጵያ ዉስጥ የገባ ይመስል ብዙ ፓርቲዎች የተቋቋቀሙበት ሁኔታ መፈጠሩ ነዉ። ታሪክ ራሱን ይደግማል ሲሉ ቀላል አባባል አይደለምና ሕወሓት/ኢህአዴግም ሆነ ወንበሩን የተረከበው ብልፅግና ፓርቲ ሌሎች ተቀናቃኝ ሊሆኑ የሚችሉ እንደቀደመው ደርግ ፓርቲዎችን በአውራ ፓርቲነት ስሜቱ በማመናመን ስልት ያጠፏቸዋል። ስለሆነም የፓርቲ ፖለቲካ ሚና በኢትዮጵያ ውስጥ አንዳች ዕድገት ሊያሳይ ሳይችል ቆይቷል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝን ብቻ ሳይሆን ቀድሞ የነበረውን የአገዛዝ ዓይነቱንም ቀይሯል። ማለትም መንግስታዊ የአስተዳደር ሥርአቱን ከአሃዳዊነት ወደ ሕብረ ብሔራዊ ፌዴራላዊነት ለማፈንጠቅ ተንቀሳቅሷል። ነገር ግን ፌዴራሊዝሙ ዴሞክራሲያዊ ገፅታን ባለመላበሱ ኢሕአዴግ መንግስታዊ አስተዳደርን እንጂ አምባገነናዊ የአገዛዝ ሥርአትን መቀየር አልቻለም። ወቅቱን ጠብቆ ምርጫ ለማካሄድ ምርጫን የሚያስፈፅሙ አካላት ቢቋቋሙም ተመዳቢዎቹ ራሳቸዉን ችለዉ ነፃነት የሚመስል ነገር አላቸው ቢባልም በገዢዉ ግንባር ከተጠረነፉበት ሥርአት አልወጡም። የራሳቸዉ የፖለቲካ አጀንዳ ኖሮአቸዉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢኖሩም ሕዝብ ዘንድ እንዳይቀርቡ በስልት የታገዱበት ሁኔታ ነበር። እንዲያዉም የሕወሓት/ኢህአዴግን ስልት ያላወቁ አንዳንድ ሰዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች

ምርጫ ሲመጣ ብቻ ድምፃቸዉ የሚሰማ ስለሆነ መኖራቸዉ ከደርጉ ጊዜ ያልተሻለ ነዉ የሚሉም አሉ። ላይ ላዩን ሲመለከቱት ነገሩ እውነት የሚመስል ቢሆንም፤ እነዚያ ተቺዎች ያላወቁት ነገር ቢኖር ወይም እያወቁት ለማደናገር ፈልገዉ ካልሆነ በስተቀር፤ ኢትዮጵያ ዉስጥ የፓርቲ ፖለቲካ ሰለመኖሩ ኢህአዴግ የሚገለጸዉ አበዳሪ ወይም ዕርዳታ ሰጪ የውጭ መንግስታት ተወካዮች ዘንድ ሲደርስ ብቻ እንደሆነ አይረዱም። እነዚያ ተቺዎች ያልተረዱት ነገር ቢኖር ምርጫ ተብሎ የሚነገረዉ ነገር በጣጣ የሚገኘዉን የሕዝብ/መንግስት ንብረት ከማባከን ያላለፈ መሆኑን መረዳት ነበረባቸው። ምክንያቱም፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሕጋዊ መንገድ ተቋቁመዉ፤ እንወክላለን የሚሉት ሕዝብ ዘንድ ቀርበዉ እንዳያነጋግሩ እየተደረጉ፣ አባላትን ማፍራት ካልቻሉ፣ ከደጋፊዎቻቸዉና አባሎቻቸዉ መዋጮ መሰብሰብ ካልቻሉ፣ ጽህፈት ቤት ማቋቋም የማይችሉና የሚያቋቁሙትም ጽ/ቤት በገዢው ፓርቲ መንግስት ኃይሎች በላያቸው ላይ የሚቸነከር ከሆነ ወይም ተሰብሮ የሚዘረፍ ከሆነ፣ በሠላማዊ መንገድ እንታገላለን ብለዉ ጽ/ቤቶቻቸዉ የሚበረበርና አባሎቻቸዉ፤ ለዚያዉም የሥራ አስፈፃሚዎቻቸዉ እስር ቤት የሚወረወሩ ከሆነ፣ ምርጫ ቦርድ የሚሰጣቸዉን ሴርቲፊኬት ፋይላቸው ውስጥ ከማስቀመጥ የዘለለ ምንም ፋይዳ እንደሌለ እነዚያ ተቺዎች ረጋ ብለው እራሳቸዉን መጠየቅ ነበረባቸዉ። ፓርቲዎቹም የምርጫ ሰሞን ብቻ ብቅ ይላሉ መባልም የለባቸዉም። ይህንን እያወቁ ነቀፋ የሚሰነዝሩ ካሉ ደግሞ እነሱ ገለልተኛ ሰዉ ወይም ድርጅት ሳይሆኑ በአካል እንኳን ባይበል በመንፈስ የሕወሓት/ኢህአዴግ በመቀጠልም የነሱ ወንበር ተረካቢዎች አባል ወይም ዓላማ አራማጆች ናቸው ብሎ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል። እንዴዚህ ዓይነት ዝንባሌ ከሚታይባቸዉ ድርጅቶች፤ ሪፖርተር የተባለዉ አፍቃሬ ሕወሓት ጋዜጣ እሁድ ሐምሌ 19/2006 በርዕሰ አንቀጹ “ገዥዉ ፓርቲና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቆም ብለዉ ያስቡ” በማለት የፃፈዉ አለአዋቂ ሳሚ ዓይነት ትችት ስንዘራና ሚሚ ስብሃቱ የሚትባል በሸገር ኤፍ ኤም የሬድዮ ሥርጭት ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የረባ ፖሊሲ የላቸዉም ብላ የሚታኮስሰው የደንቆሮ ትችት የሚጠቀሱ ናቸው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያካሂዱትን ስብሰባና

የሚሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ ለሕዝብ የማያቀርብ የገዥዉ ፓርቲ ዜና ማሰራጫዎችና ጋዜጠኞች ባሉበት አገር ዉስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፖሊሲ እንዳላቸው መጠየቋ ምን እንደሚፈይዳጽ ግልጽ አይደለም።

የሕወሓት ድርጊት አንደምታዉም ልክ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት እንዳያድግ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጠልፎ ለመጣል የወሰደዉን ዕርምጃ ዓይነት ሆነ እንጂ ሌላ ሊባል የሚችል ነገር አይደለም። የሕወሓት ሥጋት የመነጨዉ ደግሞ እራሱ አራምዳለሁ ከሚለዉ ብሔር ተኮር ብሎ ከመሰረተዉ ፌዴሬሽን የመነጨ ሲሆን ዲሞክራሲ የሚያብብ ከሆነና የብዙሃን ፓርቲ ፖለቲካ ሥርአት ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ፤ በብዙሃን ፓርቲ ዲሞክራሲ ዉስጥ ብዙ ሕዝብ ባላቸዉ ፓርቲዎች የመዋጥ ዕድል ይገጥመኛል ብሎ እራሱ ከፈጠረዉ ሥጋት የተነሳ ይሆናል። ሕወሓት/ኢህአዴግም ሆነ ወራሹ የብልፅግና ፓርቲ ከመሰል ሥጋት ለመላቀቅ ያደረጉት ነገር ቢኖር አንድም መንግስታዊ ተቋማትን በመጠቀም የኃይል ዕርምጃዎችን መውሰድና ልክ እንደደርግ ተንበርካኪና ጠልፈው የሚጥሉ ፓርቲዎችን በመያዝ፤ በተለይም ከ2013ቱ የይስሙላ አገራዊ ምርጫ በኋላ ለአንዳንድ ፓርቲዎች (ምሳሌ ለመጥቀስም የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)፣ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፓ)፣ የጋምቤላ ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ (ጋሕነን)፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)፣ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣ የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ) ለመሳሰሉት ብቻውን ተወዳድሮ አሸነፍኩበት ያለውን የምክር ቤትንና ጥቂት የአስፈፃሚውን ወንበር በመሸለም፤ በአቋማቸው የፀኑትን ፓርቲዎችን ደግሞ ሲያመች ማስፈራራትና ሲጠነክር ደግሞ አባሎቻቸውን ማሰርና ጽ/ቤቶቻቸውን በመዝጋት ከፍ ሲልም ከሕዝብ በመነጠል እንዲሁም ሕዝቡን በውሸት በማባበል የፈፀመው የፖለቲካ ሸፍጥ ነው። በሌላም በኩል ተቃዋሚ ነን የሚሉት ፓርቲዎችም ተቀራራቢ ዓላማ አለን በሚሉት ዙሪያ ተሰባስበው የገዥውን ፓርቲ የውሸት ዴሞክረሲ ለመገዳደር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አንድም የለም ወይም እጅግ አነስተኛ ነው።

ዲሞክራሲ ሊያብብ የሚችለዉ ሁለት ነገሮች ጎን ለጎን መከናወን ሲችሉ ነዉ። አንድም በውድድር ላይ የተመሠረተ ነፃ ምርጫና ነፃ ሚዲያ መኖር አለባቸዉ። ነፃነት ለሰዉ ልጅ ከፈጣሪ የተሰጠ ገጸ በረከት ነዉ። ነፃ ምርጫ የተሻሉ የሚባሉ ሰዎችን ወደ አመራር እንዲወጡ ያደርጋል። ብቃት ያላቸዉ ሰዎች ኃላፊነት መሸከም ይችላሉ፤ ተጠያቂነትም ይሰማቸዋል። የተሻሉ ሰዎች በውድድር ለአመራር የሚቀርቡ ከሆነ፤ በግል ተነሳሽነትም ሆነ በፓርቲዎቻቸዉ ፖሊሲ ላይ ተመስርተው ዕድገት የማስመዝገብ ብቃታቸውም ያንኑ ያህል አስተማማኝ ይሆናል።

አራተኛ የመንግስት አካል በመባል የሚታወቀው ነፃ ሚዲያ ደግሞ መረጃን ለሕዝብ የሚያዳርስ ነዉ። የሰዉ ልጅ የሚተነፍሰዉ አየር የሚያስፈልገዉን ያህል መረጃንም ያስፈልገዋል። መረጃ ማለት የተደበቀ ነገር ሳይሆን ምን ጉዳይ የት፣ መቼ፣ እንዴት፣ ለማን፣ ለምን እንደተፈጸመ ፍንጭና ዕዉቀት የሚሰጥ ነዉ። ይህንን መረጃ ማንሸራሸር የሚችል ደግሞ ነፃ ሚዲያ ነዉ። ሰዉ መረጃን ከሚደግፋቸዉም ሆነ ከሚቃወማቸዉ ፓርቲዎች ወይም ከዜጎች ካላገኘ ዲሞክራሲ አለ፣ ምርጫ አለ፣ ብሎ ማውራት ምንም ፋይዳ የለውም። ደካማና አምባገነን መንግስታትና መሪዎቻቸዉ መረጃን በመከልከል እፎይታን ያገኙ ይመስላቸዋል። የሁለት ነገሮች ማለትም ዲሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታና ነፃ የመረጃ ምንጭ አለመኖር ለፓርቲ ፖለቲካ መሠረት አለመኖር ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው።

በዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ዉስጥ ነፃና ያልተዛባ መረጃ ማስተላለፍን የመሰለ ሥራ የሚሰሩ ተቋማትን የመገንባት ያህል የሚከብድ ሥራ የለም። ምክንያቱም አስቀድሞ ነፃ የሰው አእምሮ ማነፅን ይፈልጋልና ነው። ነፃ የሰው አእምሮ የሚገነባው በትምህርት ነው። እሱ ደግሞ በዚህም በዚያም ተብሎ እንዲወድቅ ተደርጓል። ማሳያውም 2ኛ ድግሪ ይዘው በአፋን ኦሮሞ፣ በአማርኛም ሆነ በእንግሊዘኛ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም ፓራግራፍ አሳክተው የማይፅፉ በብዛት ስላጋጠሙኝ ነው። እንግዲህ ነፃ ሚዲያ መገንባት ዋና ጥቅሙ መንግስት ተጠሪነቱ ለሕዝብ

መሆኑን በሚገባ ለማሰረፅና የሕዝብ ሚናም ወቅታዊ ምርጫ ላይ ቀርቦ ድምፅ በመስጠት ብቻ የሚወሰን እንዳልሆነ በጥልቀት ማሳወቅ ነዉ። ይህ ቢሟላ የፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ የመንግስትና ሕዝብ አገናኝነቱን ሚና በሚገባ ተጫውቶ የአስተሳሰብ ሕዳሴን ሊያመጣ የሚችል ስለሆነ፤ ዕድገትን ሆድ ከመሙላት ባሻገር ማሰብና መረዳት ያስፈልጋል።

የፓርቲ ፖለቲካ መቀጨጭን ጨምሮ የኢትዮጵያ ችግሮች መንግስት በተለዋወጠ ቁጥር ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ ስለሆነ እንዲህ በቀላሉ የመውጫ መንገድ ይበጅለታል ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን ስልጡን የፖለቲካ አመራር ካገኘ ማለትም ሕዝብ መሪዎቹን የመምረጥ መብቱን እንዲጠቀም ከቻለና የመንግስት ሥራና ሥራ ቤቶች በኃላፊነትና ተጠያቂነት መስዋዕትነት የሚከፈልበት ከሆነ በፓርቲ ፖለቲካም ሆነ በሕግ የበላይነት እንዲመራ ማስቻል ይቻላል።

## ምዕራፍ ስድስት፡ ስለፀሐፊዉ

ጥሩነህ ገምታ ወዬሳ (Xurunaa Gamtaa Wayyeessaa) (እንደተወለደው ሳይሆን እንደተመዘገበው ዕድሜ በሐምሌ ወር 1947) በዛሬው አጠራር በኢሉ አባቦራ ዞን ሱጴ ሶዶ ወረዳ ኦቦሎ በሚባል ቀበሌ ዉስጥ ነዉ። ኦቦሎ ማለት አቀራርቦ ሲተረጎም ወንድም ወይም ወንድማማቾች ማለት ነዉ። ስሜ ጥሩነህ (Xurunaa) እንዲባል የመረጠዉ አባቴ ሲሆን፤ ከግምት ባላለፈ ሁኔታ በሱጴ አከባቢ ይኖር ከነበረዉ ፊታወራሪ Xurunaa ከሚባል የጎረቤት ኦሮሞ ነፍጠኛ ምስለኔ ገዥ ጋር እንዲመሳሰልለት ነዉ።

ሁሉም አከባቢዎች የየራሳቸው የተፈጥሮ መለያ እንዳላቸው ሁሉ ኦቦሎም የራሱ መለያ አለው። የአየሩ ሁኔታ ወይናደጋ ሆኖ ከሰሜን በኩል ከተራራ ይልቅ ጉብታ ሊባል የሚችል ከፍታ ቦታ ሲከልለው፣ ከደቡብ በኩል ደግሞ ጎበራ (Goboora) የሚባል ውሃ አቆር ጫፌ ቦታ ያዋስነዋል። በምዕራብ በኩል የሮ የሚባል ቀበሌ አለ። እንደ ምኞቴ ቢሆን ኖሮ የጎበራ ውሃ ታቸኞቹን ተፋሰሶች በማይጎዳ መልኩ ተገድቦ በምዕራብ ኦሮሚያ መለስተኛ ሰዉ ሰራሽ ሐይቅና የባህር ምግቦች ማምረቻና መዝናኛ ቦታ ቢደረግ የተሻለ ነገር ይወጠዋል ብዬ አስባለሁ።

ጥሩነህ ገምታ እንደማንም የገጠር ልጅ ጥጃ፣ በግ፣ ከብትና እህል መጠበቅ ከቻለ በኋላ አልጌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቻለሁ። አልጌ ከተማን የቆረቆሩትና አልጌ ትምህርት ቤትንም መጀመሪያ ያሰሩት የኔዉ የጎሳ ዝምድና ያለን ባታ ዱሬሶ (አባ ዋሪ) የሚባሉ የአገሬው ባላባት ነበሩ። እኚህ ሰው የቤተክህነትም ሆነ ዘመናዊ አስኳላ አልተማሩም፤ በአፋን ኦሮሞ ከመናገር በስተቀር በማንኛውም ቋንቋ መፃፍና ማንበብ አይችሉም። ነገር ግን ትምህርት ቤት ከማቆም ጀምሮ የአልጌን ከተማ የቆረቆሩት፣ ገበያ ያቆሙትና ቤተክርስትያን ያስተከሉት እሳቸው ነበሩ። ባታ ዱሬሶ በዚያን ጊዜ በተፈጥሮ የታደሉት ችሎታ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው የሚያስገርም ነበር ማለት ብቻ አይበቃም። ለአከባቢዉ ዕድገት

ያበረከቱት አስተዋጽኦ ታሪክ የማይረሳዉና እሳቸውም የሰው ፍቅር የነበራቸው ሰው ነበሩ። አባዋሪ (ባታ ዱሬሶ) እንዲህ ዓይነት ብሩህ አእምሮ ኖሮአቸወ አከባቢያቸውን ለመለወጥ ሲታትሩ፤ ነገር ግን የነበራቸው መሬት በመጤ አበሾች እየተቆነጠረ መንምኖ መንምኖ ትንሽ የሚባል ሲቀራቸው እሳቸው አስቀድመው ሞቱ፤ እሳቸዉ ሞተዉ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አብዮቱን ተከትሎ የመጣዉ የ1967ቱ መሬት አዋጅ ወሰደና ሁሉንም አሳረፈ። ያንን የመሬት አዋጅ ተከትሎ ምንም ጥናት ባልተደረገበትና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሕብረተሰብ ክፍል ሳያሳምን የተሰራው የመንደር ምስረታ፣ የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት የዘረፋ ግኘ እና በገበሬዎች አምራቾች የሕብረት እርሻ በሚባል ባይጨናገፍ ኖሮ በውነቱ የመሬት አዋጁ የጭሰኛና የፊዉዳልን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ፊውዳሊዝምንም ሆነ ኤኮኖሚው የተመሰረተበትን ከመሬት ከሚገኝ ገቢ ጋር የተያያዘ ንጉሳዊ አገዛዝንና ሲሶ ተብሎ የሚታወቀዉን የቤተክህነት ብዝበዛን በማያዳግም ሁኔታ ያቋረጠና የወታደራዊዉ ደርግም ቅርስ ሊባል የሚችል እርምጃ ነበር።

ከአልጌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፈተና አልፌ ወደ ጎሬ ቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመራሁ። ከኦቦሎ እስከ ጎሬ ያለዉ መንገድ ዱሮ ጣሊያን የሰራዉ የመንገድ ምልክት ካልሆነ በስተቀር መንገድም አይመስልም፤ የሚሄድበት መኪናም ስላልነበርና ቢኖርም በሳምንት ወይም በወር አንዴ ብቻ ስለሚሆን፤ ቢያንስ 100 ኪሎ ሜትር የሚሆነዉን መንገድ በልጅነት ዕድሜ ከታላላቅ ልጆች ጋር ሙሉ ቀን ተጉዞ ለትምህርት መድረስ የግድ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ከወላጅ ሲለይ ሆድ ብሶኝ የነበረ ቢሆንም፣ እራሱ ሳይማር የትምህርት ጥቅም የገባዉ አባቴ ዱላ እንደሚያነሳብኝ ተገንዝቤ ወደዚያው አመራሁ።

ከማይምነት ጋር ቂም ይዘው ከተነሱት ውስጥ አንዱ አባቴ ገምታ ወዬሳ ሲሆን፤ ከኔ በፊት ስምንተኛ ክፍል ላይ ያቆመው ከታላቅ ወንድሜ ሌላ በመጨረሻ የተወደለችውን እህቴን (ሴት ልጅን) በማስተማርና ለድግሪ በማብቃት በወቅቱ ከቀበሌዉ ነዋሪዎች የመጀመሪያውን ረድፍ የያዘ

ነው። እዚህ ላይ ታላቅ ወንድሜ አበራ ገምታ እቤት ፊደል አስቆጥሮኝ ስለነበረ፤ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል የወሰደብኝ ጊዜ አራት ዓመት ብቻ ነበር።

በ1961 እና 1962 ሰባትና ስምንት ክፍሎችን ጎሬ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዳጠናቀኩ ሁለት ችግሮች ገጥመዉኛል። ይኸውም ከስምንተኛ ክፍል በጥሩ ውጤት በማለፌ የነፃ ትምህርት ዕድል በአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ትምህርት ኮሌጅ ባገኝም፤ የአይሮፕላን መጓጓዣ ወጪ ብር 90.00 ባለማግኘቴ ዕድሉን ሳልጠቀምበት ቀርቻለሁ። የዚያን ጊዜ ዘጠና ብር ሦስት ሰንጋዎች ቢሸጡም አይሸፍኑም ነበር። ዘጠነኛ ክፍል መማር እንደጀመርኩም በጉበት እንፌክሽን በመታመሜ ሀገር ቤት ተመልሼ ባህላዊ መድሃኒት ለመጠቀም በመሄዴ ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገደድኩ። ከበሽታውም ለማገገም ሆነ የተሳሳተ አቅጣጫም በመያዜ፤ በ1963 ትምህርት ባቋረጥኩበት ጊዜ ውስጥ በትዉልድ መንደሬ ከአከባቢ ነዋሪዎች ጋር አዲስ ጫካ መንጥረን በቆሎ ተክለን እኔም ጥሩ ምርት አገኝሁና ለከርሞ በሬም ገዝቼ ጥሩ ገበሬ እሆናለሁ የሚልም ስሜት አድሮብኝ ትምህርት ማቋረጡን ወድጄ ነበር። በ1964ትም በቆሎው ሲደገምና ቡቃያውም ተስፋ ሰጪ ሲመሰል፤ ከየት መጣ የተባለዉ በረዶ መታውና ቡቃያው ከመበሰበሱም በላይ ከመጥፎ ሽታው የተነሳ ዝንጀሮ እንኳን መብላቱን ተጠየፈው። በእርሻ ሥራው መቀጠሉን ተስፋ በመቁረጥ ታላቅ ወንድሜ ወዳለበት ወደ ጎሬ ትምህርት ቤት አመራሁ። መተማመኛዬም ጎሬ ላይ ሥራ የጀመረው ከላይ የጠቀሱኩት ታላቅ ወንድሜ ነበር። በአንድ ቀን ጉዞ ጎሬ ገብቻለሁ። ወቅቱም 1965 ሲሆን፤ ይህ ወቅት ንጉሱን ከአልጋ ያስወገደ አብዮት መባቻ ላይ የነበረ ሲሆን፤ ወከባዉ እንዳለ ሆኖ የ9ነኛ እና 10ኛ ክፍል ትምህርቶችን በጥሩ ሁኔታ አጠናቀኩ። ሕዝባዊ ንቅናቄው በርትቶ ንጉሱ ሲወገድ፤ በ1967 እና 68 ዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በመውጣቴ በትምህርቴም ሆነ ከሕይወቴ ላይ ሌላ ሁለት ዓመት ባከነ። መች በዚህ ያበቃና አብሮኝ በአንድ ጣቢያ ከተመደብነዉና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዉስጥ የዘመቱና የፖለቲካ ንቃታቸዉ ከፍ ያለ

ተማሪዎች፤ ቀደም ሲል በአካዳሚዉ የተሻሉ ናቸዉ የሚባሉትን እየመረጡ የፖለቲካ ንቃት ሲያስታጥቁ፤ እኔም እዚያ ዘመቻ ጣቢያ ላይ በአንዱ ሳልጠመቅና ሰለባ ሳልሆን የቀረሁ አይመስለኝም። የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግን ከየት እንደጀመርኩ በእርግጠኛነት እስከ ማስታዉሰዉ ድረስ ከዕድገት በህብረት የዕዉቀትና ሥራ ዘመቻ ነበር ለማለት እችላለሁ። ሌላ ቢኖር ደግሞ ዛሬ ላይ ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስብ ለኔ ወደ ፖለቲካዉ ዓለም መሳብ የአባቴ አስተዋጽኦም የነበረበት ይመስለኛል። እንደኔ ግምት እሱ በሚያዉቀዉ ሁኔታ ገምታ ወዬሳ ከአከባቢው ፊውዳሎች ጋር የተናነቀ ታጋይ ነበር። በምሳሌ ላስረዳ። በ1962 የስምንተኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ተፈትኜ በክፍል ፈተናም መጽሐፍ ተሸልሜ ነበርና ከሌሎች ልጆች ቀድሜ ወደ ገጠር ተመልሼ የአባቴ ቤት በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ የተሸለምኩትን መፅሐፍ እያነበብኩ ሣለሁ፤ ባለመሬት የነበረዉ ፊውዳል በደጃፋችን ላይ ሲያልፍ አይቶኝ ኖሮ፤ አንዱን ገባር በስም ጠርቶ "የገምታን ልጅ ጥራውና ለበቅሎዬ ሣር ይጨድ" ብሎ አዘዘ። ወዲያውኑ አባቴ ትዕዛዙን ሰምቶ ኖሮ በደም ፍላት "ልጄ ተማሪ እንጂ ያንተ ገባር አይደለም፤ ነገ ተምሮ ያንተን ልጅንም ሊበልጥ ይችላልና ያንተን በቅሎ ሣር አያጭድም፤ ይልቅስ ያንተ ገባር እኔ ነኝና ማጭድና ገመድ ከተሰጠኝ እኔዉ እራሴ ያንተን በቅሎ ሣር ሄጄ አጭዳለሁ" በማለቱ በፊዉዳሉና በአባቴ መሀከል ዱላ ቀረሽ ጥል ተነስቶ እንደነበረ አቻዬ የነበሩና በወቅቱ ቦታዉ ላይ የነበሩ ሰዎች ነግረዉኛል። ከዚያ በኋላ ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ማለትም እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ማለት ነው አባቴ ለፊዉዳሎቹ የሚሰፍረዉን እርቦ ዋናዉን እንጂ ተጨማሪ ነገሮችን ሳይሰራ ለሁለት ዓመታት ያህል ቆይቶ ነበር። ይህ ብቻም ሳይሆን የአከባቢውን ነፍጠኛ ሰፋሪ ፊዉዳልን አዲስ አበባ እሚገኙ ከፍተኛ ፊዉዳሎች ላይ ለመክሰስ ከጓደኛው ገመዳ ቱሜ ጋር ከአቦሎ-ግምቢ ድረስ በእግሩ፣ ከግምቢ አዲስ አበባ ድረስ ደግሞ በመኪና የተጓጓዘ ሰዉ ነበር። ይህ ብቻም አይደለም፤ ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ ወረዳ ገዥዉ አቶ ቢሆን በቀለ የሚባል በእሁድ የገበያ ቀን አባቴን ከመንገድ ጠርቶ ሙክት ገዝተህ አምጣ ብሎት ዘጠኝ ብር ይሰጠዋል። አባቴም ዘጠኙን ብር ተቀብሎ ወደ ቤቱ ሄዶ በሳምንቱ እወረዳ ገዥዉ

ፊት በመቅረብ የዘጠኝ ብር ሙክት አላገኘሁም ብሎ ገንዘቡን እንደመለሰለት አስታዉሳለሁ። እንዲህ ቁርጠኝነት የተመላበት የአባቴ እርምጃዎች በኔ የፖለቲካ ዝንባሌ ላይ በጎ ተፅዕኖ ሳያሳርፍ አልቀረም እላለሁ። የአባቴን ድርጊት ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስተውለው ገባርነት ከራሱ ወደኔ ልጁ ሰፋ ሲል ደግሞ ወደ ልጆቹ እና የሕብረተሰቡ ልጆች እንዳይተላለፍ የታገለ ጀግና ገበሬ ነበር ለማለት እችላለሁ።

ከዕድገት በህብረት ዘመቻ መልስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀኩት መቱ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር። የ2ኛ ደረጃ ዉጤቴ ለድግሪ ፕሮግራም ትምህርት የሚያበቃኝ ቢሆንም፤ የደርግ ቀይ ሽብር ሰለባ በሆነዉና በጎሬ ከተማ ተወላጁ ድቤኩሉ ላቀዉ አስጀማሪነት፣ በእስራኤል መገርሳና ፍቃዱ ሻረዉ አጠናካሪነት በማርክስዚም ሌኒኒዝም ጠበል ተጠምቄ፤ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት/ማሌሪድን በመወከል የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት የወረዳ ካድሬ ሆኜ ከነሐሴ 1፣ 1970 ጀምሮ በብር 230.00 ተቀጥሬ ወደገጠሪቱ ኢሉ አባቦራ መጀመሪያ ወደ ሁሩሙ ወረዳ አመራሁ። በ1971 ግንቦትና ሰኔ ወራት ፖለቲካ ትምህርት ቤት ከመግባቴም በላይ አዲስ አበባን ለመጀመሪያ ጊዜ ረገጥኩ። ሰዉ መጀመሪያ አዲስ አበባ ሲገባ ደስታ ወይም ግራ መጋባት ስሜት ሊያድርበት ይችላል፤ የኔ ግን ማትሪክ አልፌ ተመደቤበት የነበረዉን የአራት ኪሎ ሳይንስ ፋካልቲና የቀድሞ ክፍል ጓደኞቼን ሳይ መግቢያ ጠፍቶኝ ብስጭት ብጤ አድሮብኛል። ምክንያቱ ደግሞ እኔ ሳስጠናቸዉ የነበሩ ልጆች የዩኒቬርሲቲ ተማሪዎች ሆነዉ የምሁርነት ባህርይ ሲያንፀባርቁብኝ ያለምንም መሸፋፈን የበታችነት ስሜት ተሰምቶኝ ስለነበር ነዉ።

የተወሰኑ የከተማ ልጆች እናቶቻቸዉ ሆድ ዉስጥ ሆነዉም ቢሆን የሚጀምሩትን ፊልም መመልከት የጀመርኩት፤ ስርጭቱ ከቴሌቪዥን ፋይል ይሁን ከሌላ ለይቼ ባላውቅም ፊልም የሚባለውንም ማየት የጀመርኩት በዚሁ ዓመት ወደ አዲስ አበባ በሚደረገው ጉዞ ጊዜ ውስጥ ጂማ ላይ በአደረኩት የቆይታ ጊዜ ነው። ፊልም ማየቴን ለመግለፅ ሳይሆን የፊልሙ ይዘት እስከ ዛሬም አልተረሳኝም። በፊልሙ ውስጥ ዋና

ባህርይ ይዞ የሚጫወተው የአንዷን ሴት ሕይወት በማጥፋት ወንጀል ሰርቶ ማንም አላየኝም ባለበት ሰዓት ላይ አስከሬኗን ሲያስወግድ አንድ ልጅ እግር ያያዋል። ገዳዩ እሱን ያየውን ልጅ ለማጥፋት ሲያሳድድ የሌሎች አስራ ሦስት ሰዎችን ሕይወት ያጠፋል። ከፊልሙ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ወንጀል የሚሰሩ ብዙ ሰዎች የተሰራውን ወንጀል ለመሸፈን ሌላ ወንጀል ሲሰሩ እንጂ ወይ ለፍርድ ለመቅረብ ወይም ይቅርታ ሲጠይቁ አሁን ባለሁበት ዕድሜ ላይ ሆኜም ቢሆን ለማየት አለመቻሌ ነው።

1971 ከፖለቲካ ትምህርት ቤት ስልጠና መልስ ቦታ ተቀይሮብኝ ያለደመወዝ ጭማሪ ከኋላቀሩ ኢሉ አባቦራም በጣም ኋላቀር ወደ ሆነዉ ዲዱ ወረዳ ሲመደብ፤ በቅርቡ ከወዝሊግ ተገለባብጦ ሰደድ የሆነዉ ወረዳ አስተዳዳሪ አጋጠመኝ። ደግነቱ ሁሉም የመንግስት ሠራተኛ ለማለት ይቻላል አይወዱትም ነበር። የየትኛው ድርጅት አባል እንደሆንኩ ከየት እንደሰማዉ ባላዉቅምም ወረዳ አስተዳዳሪዉ ያንተ ማሌሪድ እዚህ አይሰራም አለኝ። ብልጫ እንዲኖረኝ ያደረገኝ ግን ሁሉም የመንግስት ሠራተኞች ወይይት ክበብ የሚባለዉን ሳምንታዊ ፕሮግራም፤ መምህራን ጭምር ስለሚሳተፉ፤ ሁላችንም ስለማርክስዝም ብዙም የጠለቀ ዕዉቀት ባይኖረንም፤ ወረዳ አስተዳዳሪዉ አስር አለቃ ብዙም ተሰሚነት ስላልነበረዉ ከውይይቱ መዉጫ ሰዓት ላይ በመምህራን ተከብቤ እየተንጫጫን ስንሄድ አስር አለቃዉ ስለሚገለል የመንቀሳቀስ ዕድሌን ሰፋ አድርጎልኛል። በአውራጃ ላይ የማሌሪድ ተወካይ የነበረው አዲሱ ውብሸት ከመኢሶን ወደ ወዝ ሊግ በተመለሰዉ ሰው ስለተፈነገለ ስጋቴ ባይጠፋም፤ ከሕዳር ወር 1973 ጀምሮ የሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች ሕልዉና ደብዝዞ፤ ነገር ግን የሰደድ ድርጅት ገንኖ እንዲወጣ ካድሬው እንደገና እንዲሰለጥን ተደርጎ የካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ገባን። ወደዚህ ትምህርት ቤት መግባትን አስመልክቶ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ማለት ቢቻልም ከብዙ መጥፎ ነገሮች ዉስጥ አልፎ አልፎ ቀለል ያለ መጥፎ ነገር አይጠፋምና የኢሠፓአኮ ዓላማን ከግብ ለማድረስ ሁሉም ካድሬ ፖለቲካ ትምህርት ቤት እንዲከት በጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም ትዕዛዝ ተሰጥቶ፤ እስር ቤት የነበሩ ጭምር ከየነበርንበት ወረዳ አዲስ

አበባ የካቲት 66 ፖለቲካ ትምህርት ቤት ገባንና፤ ከዘጠኝ ወራት ስልጠና በኋላ በማምረቻ፣ አገልግሎት መስጫ ድርጅቶችና ፓርቲ መዋቅሮች ዉስጥ ምደባ ተሰጠና እኔና ጓደኞቼ በተምታታ ሁኔታ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዉስጥ በመሠረታዊ ድርጅት ተጠሪነት ተመደብኩ። እንደዚህ ዓይነት የሚኒስተር መስሪያ ቤት ባይኖርም የኢትዮጵያ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ለማለት ተፈልጎ ይሆናል በሚል ወደዚያዉ ብናመራ ትክክል ሆኖ ተገኘ። እኔ ደግሞ በምን ብልጫ እንዳለኝ ምኑም በማይታወቅ ሁኔታ የመሠረታዊ ድርጅቱ ተጠሪ ሆኜ ተመደብኩ። አበሳዉ ከዚህ በኋላ ያለዉ ነዉ።

በየተመደብንባቸዉ ድርጅቶች ዉስጥ በግምት ከስድስት ወራት የመተዋወቂያ ቆይታ በኋላ የኢሠፓአኮ አባላት ምልመላ ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ እንድናካሄድ ተወሰነ። ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ሲባል ፓርቲዉን በሐቀኛ አባላት ለመሙላት ሲደሰኮር ከነበረዉ ሁኔታ አንፃር ሲሆን፤ ዕዉነቱ ግን ብዙዎቻችን የማናዉቀዉ ሆኖ ጥቂቶቹ ግን የዛሬዉን ዓይነት ባይመስልም የተለያዩ ጥቅሞቻቸዉን ሳያስጠብቁበት አልቀሩም። ቀደም ሲል ቀጣና ተብሎ በሚታወቀዉ ሥር የኢሠፓአኮ አባላት ሆነዉ መስሪያ ቤቱ ዉስጥ ከነበሩት ጋር ትዉዉቅ አድርገን ወደ ምልመላ ገብተን ሰፊ ክርክር ተካሂዶበት ብዙ ሰዎች ስንመለምል፤ አልሰሜን ግባ በሉት እንደተባለ ሆነና አይመጥኑም ያልናቸዉንም ግለሰቦች ከነምክንያቱ ገልጸን ለቀጣናዉ አስተላለፍን። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግንባር ቀደም ይሆናሉ ብለን የመለመልናቸዉ የተወሰኑ ሰዎች ቀርተዉና መሠረታዊ ድርጅታችን ያልመለመላቸዉ ሰዎችም ታክለዉበት የአባላት ዝርዝር ተመለሰልን። መሠረታዊ ድርጅታችን ካልመለመላቸዉና ቀይ ደብተር ከታደላቸዉ ዉስጥ አንዱ ቀደም ሲል የኮንስትራክሽን ባለሥልጣኑ የሕግ አገልገሎት ኃላፊ (ስሙን መጥቀስ ያን ያህል አስፈላጊ ስላልሆነ አልፌአለሁ) የነበረዉና ተመድበን ከመጣን በኋላ ወደ አስተዳደር መምሪያ የተዘዋወረዉ ሰዉዬ ይገኝበታል። ይህ ሰዉ በምልመላችን ወቅት ተቀባይነት ያላገኘዉ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ በሰራበት ረጅም ጊዜ ዉስጥ ድርጅቱ ሲከስም ሆነ ሲከሰስ የድርጅቱን

ጥቅም አሳልፎ የሰጠና በእጅ አዙርም፤ በዛሬዉ አጠራር ሙሰኛ ሆኖ እራሱን ተጠቃሚ ያደረገ ሰዉ ነዉ ተብሎ ብዛት ያላቸው መረጃዎች ስለቀረቡበት ነበር።

የተባለው ሰው አባል መሆኑ ቢገለጽልንም በመሠረታዊ ድርጅቱ እንዳይመለመል የተወሰነበት ነገር እንዲያኮርፍ ሳያስገድደዉ አይቀርም፤ በመሠረታዊ ድርጅት ደረጃ ስሙ በመዝገብ ከመያዙ በስተቀር ሳምንታዊ ስብሰባ ላይም በሥራ ብዛት በማሳበብ አይገኝም ነበር። በመሠረታዊ ድርጅት ተጠሪነት እየሠራሁ እያለሁ መሀል ላይ ግን አሳማኝ ባልሆነ ሁኔታ ከሚሰጠኝ ድርጅታዊ ሥራ አንፃር ከቀጣናዉ ኢሠፓአኮ ጋር እያቃቃረኝ ሄዶ፤ የኢሠፓአኮን ተልዕኮ መወጣት እንደማልችልና በእጄ የሚገኘዉን ሁሉ አስረክቤ እኔ እንድወርድና ጎንደሬው መክብብ ገብረማርያም የሚባል ሰዉ የመሠረታዊ ድርጅቱን ተጠሪነት ከኔ እንዲረከብ በቀጣናዉ ተጠሪ ይወሰናል። (ደብዳቤው በስተመጨረሻ ላይ ታትሟል) ተሿሚዉን ለማስተዋወቅ በተጠራዉ ስብሰባ ላይ የአስተዳደር መምሪያ ኃላፊዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገኘ። ይመስለኛል አዲሱን ተሿሚ እንኳን ደስ ያለህ ለማለትና እኔን ደግሞ በተዘዋዋሪ እንኳንስ ተፈነገልክ ማለቱ መሆኑ ወዲያኑ ገባኝ። ኢሠፓአኮ ወደ ኢሠፓ ሽግግር ሊያደርግ ጥቂት ጊዜ ሲቀሩት ያ ሰዉ ራሱ የመሠረታዊ ድርጅት ተጠሪነትን ጠቀለለና ሥራዉ ሁሉ እኔን ከአባልነት ማባረር የሚችልበትን ስልት መቀየስ ሆነ። በ1976 በመሠረታዊ ድርጅት ደረጃ ኢሠፓ ሲመሠረት እንደማንኛዉም አባል ስብሰባዉ ላይ ብሳተፍም፤ ግን ማታ ድል ያለ ግብዣ ሲደረግ እኔ አልጠራም ነበር። በሥራ አከባቢም በተፈጠረብኝ ተፅዕኖ የተነሳ በትምህርት ዝግጅት እኩል የነበርነዉን ጓደኞቼን ለይቶ የተሻለ ደመወዝና ደረጃ ሲሰጣቸዉ እኔን በትንሹ ያልፈኝ ነበር።

ከዚህ ከአዲሱ የመሠረታዊ ድርጅት ተጠሪ አስከፊ ሁኔታዎች እንደሚመጡብኝ ጥርጣሬ ብኖረኝም ያለኝ ትዉዉቅም ሆነ ትስስር ጠባብ በመሆኑ በየት በኩል እንደሆነ ግን ማወቁ አንዱ ችግሬ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ የስብሰባዉ መነጋገሪያ

አጀንዳም በኔ ላይ ሂስ ለማቅረብ እንደሆነ ተጠቅሶ ለዉይይት ቀረበ። ለዚህም ሁለት ገፅ በጽሑፍ የቀረበ ጥቆማ እንዳለና ለጥንቃቄ ሲባልም የጠቋሚዉ ስም እንደማይጠቀስ ተደረጎ ተነበበ። ሁለት ሰዎችን ጠረጠርኩ፤ አንደኛዉ በጣም በቅርብ የተግባባን፤ ከመግባባትም ባሻገር ከሴት ልጅ ጓደኛዉ ጋር የፍቅር ጨዋታ ሊጫወት ሲፈልግ የቤቴን ቁልፍ የሰጠሁትና አብረን ምሳ ካልበላን፤ አንድ ነገር እንደጎደለብኝ የምቆጥረዉ ጓደኛዬ፤ አፈወርቅ ከበደ የሚባልና በመስሪያ ቤቱ በቅደም ተከተልም የዕዳ ማጣሪያና የትራንስፖርት ክፍል ሠራተኛ ሆኖ ተገኘ። ይህ ሰው በራሱ ፈቃድ ተነስቶ ከአንዲት የክፍሉ ሴት ሠራተኛና በደህንነት ሥራ ወደ አሜሪካ ተመድቦ ከሄደዉ ወንድሟ ጋር ወደዚያ ወደ አሜሪካ ከተጓዘችዉ ጋር አስተዋዉቆኝ፤ ለወደፊቱ የሕይወቴ ዕጩ አድርጌያት እንደነበርም አስታዉሳለሁ። ልጅቱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ ሆና ኖራ፤ ከፓርቲ ዲስፒልን ዉጭ ከጴንጤ ጋር ተሻርኳል ብሎ ይኼው አፈወርቅ ከበደ በእጅ አዙር ወንጅሎኝ እንደነበረም በጣም ዘገይቶ በምስጢር ከተቀመጠው ፋይል ወጥቶ ተሰጥቶኝ ደርሼበታለሁ። በወሽካታነቱም የትዳር ፍላጎቴንም ሆነ የእንጀራ ገመዴን በጥሶታል። ልጅቱም ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ በባለሥልጣን ወንድሟ አማካይነት ወይም የእሱን እግር በመከተል ወደ አሜሪካን አገር ሲትበር ደህና ዋል እንኳን አላለችኝም። አልተቀየምኳትም፤ ምክንያቱ ዕድለኞቹ ምድር አሜሪካ ገብታ ርጉማን አገር የቀረውን ምስኪን ጥሩነህን ዞር ብላ የማየት የሞራል ግዴታ አለባት ብዬ ራሴን አልሸነገልኩምና ነው። አፈወርቅ ፅፎ ባቀረበዉ ዉንጀላ ምክንያት ጉዳዩ ወደ ወረዳ ፓርቲ ኮሚቴም ሪፖርት ተደርጎ፤ የወረዳዉ ፓርቲ ኮሚቴ የዲስፕሊንና ቁጥጥር ኮሚቴ ተወካይ በተገኘበት ክርክር ተደርጎበት በአብላጫ ድምፅ ነፃ ወጣሁ ልበልና ነፃ ነህ ተባልኩ። ነፃ በተባልኩ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ቀደም ሲል ስሜ ባይተላለፍም የበላይ አካል የጠየቀዉ ተጨማሪ የሰዉ ኃይል ጥያቄ ነዉ ተብሎ በ1978 በተጨማሪነት በድርቅ የተጎዱ ሰዎች ወደሚሰፍሩበት የመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ወደ አንገር ጉቲን፤ ወለጋ ተላኩ። (በነገራችን ላይ ስለኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የትግል ዓላማ ፍንጭ ያገኘሁት ኡኬ የምንግስት እርሻ ጣቢያ እና ጉቲን መንደር ዉስጥ ከሚደረጉ የሐሳብ

ልዉዉጥ ነዉ።) እዚያም ግዳጄንም ተወጥቼ ተመለስኩ። ነገሩ የቆየ ቢሆንም አፈወርቅ ከበደ የፃፈዉን ሁለት ገፅ የጥቆማ ደብዳቤ ለኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅት ጽ/ቤት ቤተኛ የሆነ ሰዉ ዋናዉን አወጥቶ ሲሰጠኝ፤ ስካን በማድረግ ከዚህ ጋር ታትሟል። አፈላልጌ ለባለቤቱ ለወይዘሮ ሠናይት ልነግር ፈልጌ፤ ግን ደግሞ እሷ በማታዉቀዉና በሰንካላዉ የኢሠፓ ስርአት ችግር ምክንያት የሰዉን የትዳር ሕይወት ላለመበጥበጥ ብዬ ትቻለሁ። ለአፈወርቅ ግን የሱኑ የእጅ ጽሑፍ ኮፒ አድርጌ ሰጥቼዋለሁ። እሱም ከዚያ በኋላ ይቅርታ ጠይቆኛል። የይቅርታ ጥያቄዉንም የተቀበልኩ ቢሆንም ይቅርታ አጠያየቁ ከለበጣ የዘለለ ባለመሆኑ ለትምህርታዊነቱ ሲባል ብቻ ግልፅ እንዲወጣ በሚል ስሜት እዚህ መጽሐፍ ዉስጥ እንዲካተት አድርጌአለሁ። የለበጣ ይቅርታ ጥየቃ ደግሞ አገራችን ዉስጥ ከግለሰቦች ጀምሮ እስከ ትልቁ ድርጅት መንግስትም ድረስ የተለመደ ስለሆነ ተጎጂዎች የሸንገላ ይቅርታ ተጠይቀዉ በሁሉም እንደተጎዱ እንዲቆዩ ይገደዳሉ። ለአብነትም፤ በአገር ደረጃ ሳይቀር በዳዮች በሚያስተዳድሩት ሜዲያ ብቅ ብለው ምስኪንና ምንም ማድረግ የማይችሉትን ዜጎች ይቅርታ ይላሉ፤ አልፎ ተርፎም በዳዮች ሕዝቡን የሽግግር ፍትህ አቋቋምንልህ ብለው ያላግጡበታል።

ከዚያ በኋላ ሊመጣብኝ የሚችለዉን ችግር በመፍራት የሚሰጡኝን ሥራዎች ሁሉ በጥንቃቄ እየሰራሁ፤ አንድም ከአገር መዉጣት፣ ይህም ካልተሳካ በማታዉ ክፍለ ጊዜ ተምሬ መስሪያ ቤት መቀየር እንደነበረብኝ ተረድቼ ትምህርት በጀመርኩ በሦስተኛዉ ዓመት፤ ዘጠነኛ ክፍል ስገባ ጊዜ አሞኝ የነበረዉ የጉበት እንፌክሽን በሽታ እንደገና አመመኝ። በደከመ ዉጤትም ቢሆን ቀጠልኩ። ወደ ዉጪ አገር መሰደድንም ማሰቡን ትቼ ትምህርቱንም እየቀጠልኩ ትዳር መሰረትኩ።

ከባለቤቴ ጋር የተዋወቅነዉ በዓኛዬ ሠርግ ላይ ነዉ። እሷ ደግሞ ታላቅ እህቷን ሲትድር። ዉቤቷን ያየሁት ወላጆቻቸዉ ሩቅ ገጠር ነዋሪ በመሆናቸዉ ወንድሟ እንደአባት እሷ ደግሞ እንደእህትም እንደእናትም ሆነዉ እህታቸዉን ሲድሩ ነዉ። እንደነገሩ የለበሰች ቢሆንም እህቷን

ለመዳር ሲትንጎዳጎድ ከተጨናበሰችበት ጭስና ከተቀባችዉ ጥላሸት ጋር ለኔ ውብ፣ የውብም ውብ ሆና ታይታኛለች። በርግጥም ደግሞ በውበቷ ከኔ ቢትበልጥ እንጂ አታንስም። የዳዳኛዬ መልስ ዕለት የኔ ጉዳይ መብላት መጠጣት ሳይሆን ይህችኑ ዓይኔና ልቤ ዉስጥ የገባችዉን ፍቅር መከታተል ነበር። በሳምንቱ ሁሉንም ምሳ ጋብዤ፤ እዉስጤ የተፈጠረዉንም ፍቅር ዘርግፌ ነገርኳት። አላስከፋችኝም፤ ትንሽ እንዲቆይ ብቻ ነግራኝ ተሰነባበትን። ደቡብ አፍሪካዊያን የዙሉ ጎረምሰዎች የተገረዙ ዕለት ድምፃቸዉን ከፍ አድርገዉ ሰዉ ሆንኩ እንደሚሉት ዓይነት፤ እኔም ይህች ሴት የፍቅር ፊት ሲታሳየኝ፤ ከዚህ ቀን በኋላ ሙሉ ሰዉ የመሆን ስሜት በዉስጤ አንሰራራ። ለምን መሰላችሁ፤ ኢሠፓን በሆነ ሁኔታ ለመበቀል ስወጣና ስወርድ፤ ጓዴኞቼ ሁሉ አግብተዉ ወደቤታቸዉ ሲጠቃለሉ፤ እኔ ወደኋላ ቀርቼ ስለነበር፤ ከዉጭ እራት በልቶ ወደ ቤት መመለሱ አለመመቸቱ ብቻ ሳይሆን ትንሽ አምሽተዉ ውሃ ነገር ከቀማመሱ ደግሞ ለሕይወት የሚሰጠዉ ዋጋ ራሱ ይዘነጋ ስለነበር ነዉ። ከአንድ ዓመት ከመንፈቅ በኋላ ተጋብተን፣ እነሆ ሦስት ወንዶች ልጆች (አብዲ፣ ሱራ እና ኤባ) በመዉለድ በፍቅር እየኖርን እንገኛለን ልበላችሁ። ለእግዚአብሔር ምን የሚሳነዉ ነገር አለና እሱም ዘግኖ ካሰኝ፤ እኔም በምስጋና እየከፈልኩት ነው።

ወደ ኋላ ልመልሳችሁና ከ1977ቱ ከኢሠፓ ምስረታ በኋላ የደርግ ኃይል እየተዳከመ በመሄዱ የከፋ ችግር ባይደርስብኝም፤ ከቀጣናው ኢሠፓ በሚመነጬና ከባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ከሚደርስብኝ ጫና የተነሳ በየሁለት ዓመት ለአጠቃላይ ሠራተኞች ከሚደረግ የእርከን ጭማሪ በስተቀር የትምህርት ዝግጅቴን በተወሰነ ደረጃ ባሻሽልም የደረጃ ዕድገት የሚባል ሳላይ፤ የ1983ቱ የመንግስት ለዉጥ ገላገለኝ። ከዚያ በፊት ግን የደረጃ ዕድገት ለማግኘት ብዙም ሳንጣጣም ከኖርነዉ ከኮንስትራክሽን ሚኒስትሩ እግር ላይ ወድቄ ይቅርታ እንድጠይቅና የደረጃ ዕድገትም እንደሚሰጠኝ ተነገሮኝ ነበር። መልሴ ግን አጭርና ግልፅ ነበር። እንኳን እኔ ፊደል የቆጠርኩ ሰዉ ቀርቶ ፊደል ያልቆጠረ አባቴም እንዲህ ዓይነት የወረደ ሐሳብ ቢቀርብለት አያደርገዉም የሚል ነበር። ገምታ ወዬሳ ልጁ

ጥሩነህ ለፊዉዳል በቅሎ ሳር አያጭድም ያለውን የገምታ ወዬሳን ቃል ረግጬ እኔ ፊደል ቆጠርኩ የምለው ሰዉ አንድ ሚኒስትር እግር ሥር ስወድቅ ይቅርታ ስጠይቅ ጨርሶ የማይታሰብ ሆነ። ለዚያም ደግሞ ተበዳይ ሆኜ በዳይን ይቅርታ ስጠይቅ ይታያችሁ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ተማሪ በመሆኔ የ1983ቱ የመንግስት ለዉጥ አዲስ ክስተት አልሆነብኝም። እንዲያዉም ወያኔ አዲስ አበባ ከተማ እንዳይገባ ለመከላከል የኢሠፓ ፓርቲ አባላቱ ለሥልጠና ወደ ሰንዳፋ ሲያመሩ፤ ሕይወቴን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ፤ አዲስ አበባ የገባዉን ወያኔን ለመከላከል ለሥልጠና ወደ ሰንዳፋ አልሄድም ብዬ በወቅቱ የመሠረታዊ ድርጅቱን አመራር ያስደመመ ንግግር ተናግሬ እንደነበረ አስታዉሳለሁ።

እስከ ምንጊዜዉም ቢሆን ከአእምሮዬ የማይጠፋዉ ነገር ቢኖር ግን ወያኔን ለመዉጋት ሥልጠና ሳልሄድ፣ ነገር ግን ለሁሉም የፓርቲ አባላት ኤስ. ኬ. ኤስ የሚባል ጠመንጃ ታድሎ ራሳቸዉንና አከባቢያቸዉን እንዲጠብቁበት ሲደረግ፤ ሄጄ ምንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ያልወሰድኩ ሰዉ፤ ዛሬም ቢሆን የጦር መሳርያ መያዝን የማልወድ ሰውዬ፤ ሕወሓት/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ተቆጣጥሮ ከሁለት ወራት በኋላ በሁለት የትግራይ ተወላጆች ጠያቂነት ነው ተብሎ በሐምሌ ወር 1983 በአቶ አለማየሁ ኃይሌ ሥላሴ (ዓለማየሁ ፊኛ) በሚመራዉ የሠላምና መረጋጋት ኮሚቴ አስተባባሪነት ወደ እስር ቤት ተወረወርኩ። ከሰባት ወራት እስር በኋላ ተፈትቼ፣ ከወራት መንገላታት በኋላ በመከራ ወደ ቀድሞ ሥራዬ ተምልሼ ዓመትም ሳልቆይ በ1985 የሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላያኔ በሚመራው የሕወሓት ወታደራዊ ወረራ ተዘጋ። በዚህ ምክንያት ሊያልቅ የነበረዉ ትምህርትም ተቋርጦ፤ እንደገና ሥራ ፈለጋ ተደርጎ፤ በአንድ የኮንስትራክሽን ድርጅት ዉስጥ በቀን ሠራተኛነት፤ በመቀጠልም በኦሮሚያ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ዉስጥ ሥራ ተገኝቶ፣ መቋቋም ተደርጎ ወደ ትምህርቱም ተመለስኩ። የ40 ወይም የሰማኒያ ወይም

የስንት ቀን ዕድል እንደሆነ ለመናገር ቢያስቸግረኝም የመጀመሪያ ድግሪ ትምህርት ለመጨረስ ድፍን አስራ ሦስት ዓመታትን ፈጅቶብኛል። በጣም አሳዛኙ ጉዳይ ከእስርና ሥራ ማፈላለግ በኋላ ወደ ትምህርቱ ስመለስ በመጀመሪያ ዓመታት የወሰድኳቸዉ ኮርሶች በቆይታና ከመንግስት ሥርአት ሳይሆን ከመንግስት አስተዳደር ለዉጥ ጋር ተያይዞ ከትምህርት አሰጣጡ ስርአት ውጭ ስለተደረጉ ኮርሶችን ድግሜ ለመዉሰድ ተገድጃለሁ። አንዱን የትምህርት ዓይነት ሁለት ጊዜ ሄጄበታለሁ።

ከሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሥራ መቋረጥ በኋላ ኦሮሚያ ሥነ ሕዝብ እስከሚቀጠር ድረስ ሁለት ነገሮች ትዝ ይሉኛል። አንዱ ቀድሞም የተጠራቀመ ጥሪትም ስላልነበር፣ እስር ቤትም ስለነበርኩ ሕንፃ ኮንስትራክሽን ሲዘጋ ለችጋር ለመጋለጥ ብዙ ጊዜ አልፈጀብንም። በእስሩ ጊዜ እኔና ጓደኞቼ የታሰርነዉ ስዉር መንደር ዉስጥ በመሆኑ የምንበላዉ ምግብ በማነሱ፤ እስረኞች ተመካክረን አንድ መፍትኼ ተገኘ። የታሰርንበት ቤት መደበኛ እስር ቤት ሳይሆን በየጉራንጉሩ ዉስጥ በነበሩ ቤቶች ዉስጥ ስለነበረና ቤቱም የቀድሞዉ የምስራቅ ጅርመን ሚሊታሪ አታቼ ይኖርበት የነበረዉ ቤት ዉስጥ ሲሆን፤ እሱም አቤሰሎም ይደጎ የሚባል ኤርትራዊ ሀብታም ሰዉ ጎረቤት ስለነበር፤ በአቀረብንለት ተማፅኖ መሠረት በቀን ሁለት ዳቦ ሊገዛልን ተስማማ። ከ1984 ወደ 1985 የዘመን መለወጫ ዕለት ግን አራት አራት ዳቦ ተደርጎልን ለቤተሰባችንም ልናካፍል ችለናል። በዚህ አጋጣሚም የአቤሰሎም ይደጎ ውለታም የማይረሳና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይሆንም።

ሁለተኛዉ ትዝታዬ ድርጅታችን ሕንፃ ኮንስትራክሽን መዘጋቱ አግባብ አለመሆኑን በሰላማዊ ሰልፍ ለመግለፅ በመንግስት ተፈቀደልንና ከመስቀል አደባባይ ተሰልፈን ወደ ወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ታምራት ላይኔ ጽህፈት ቤት አመራን። መፈክር እያነሳን ሂልተን ሆቴል አከባቢ ስንደርስ “ወድደዉ አይስቁም” የሚባል አለ አይደለም፤ ሳልወድ በግድ ለመሳቅ ተገደድኩ። ሲነሳ የነበረዉ መፈክር “የኢህአዴግን ዓላማ

እንደግፋለን፣ ድርጅታችን መዘጋቱን እንቃወማለን" የሚል ይገኝበታል። በአንድ ራስ ሁለት ምላስ መሆኑን ተረድቼ፤ እስከ ዛሬም ድረስ ለማከብረዉ አንድ ጓደኛዬ ብነግረዉ እሱም ገርሞት ኑሯልና አፍራሹን የኢህአዴግን ዓላማ ደጋፊና የሕንፃ ኮንስትራክሽንን መፍረስ የሚቃወም ሰልፍ አቁመን ሰልፉ ሳያበቃ ተያይዘን ወደ ቤታችን ተመለስን።

በ1986 በሁለት የግል ኮንስትራክሽን ድርጅቶች ውስጥ በቀን ሥራ ተቀጥሬ ባሬላ ከመሸከም ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን ሰርቻለሁ። አንደኛው ሥራንና ሰብአዊነትን አጣምሮ የሚረዳ ሲሆን ሁለተኛውና ጉልበቴን ሊሸጥለት የተቀጠርኩበት ሰውዬ ጉልበቴንም በተገቢ ዋጋ አልገዛኝም፤ ሰብአዊነቴንም አላከበረልኝም። ባሌ-ጎባ ለሥራ ጉዳይ ሄጄ በቀን ሰራተኞች ከመዋከቤም በላይ እዚያ ሄጄ የሰራሁበትን አበል ሳልቀበል ባዶ እጄን ሄጃለሁ። ቆይቶም ቢሆን ያለፈውን ጠብ ከመነካካት ተቆጥበን ወደ ከአንገት በላይ ወዳጅነት ተመልሰናል። ከዚያ ባለሀብት አንድ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ውስጥ የሀብታሞች ሀብት መጠን መለኪያው ከጉልበት ብዝበዛዉ ሌላ አንዱ የቁጡነት ባህርይ ተካትቶበት እንደሆነ ተረድቻለሁ።

ቀጥሎ የሰራሁበት ኦሮሚያ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ከኅዳር ወር 1987 እስከ1990 ሰርቼ ይህም በመዋቅር ማስተካከል ስም ጽ/ቤቱ ለሁለት እንዲከፈል በመደረጉ በሠላም ተሰናብቼ ወደ ፊንፊኔ የደን ልማትና ገበያ ድርጅት ሄድኩ። ነገር ግን ኦሮሚያ ሥነ ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት ስሰራ አንድ የማልረሳዉ ነገር ቢኖር፤ የተባበሩት መንግስታት የሥነ ሕዝብ ጉዳይ ፈንድ (UNFPA) ለተመሳሳይ ሥራ የተቋቋሙ የመንግስት ድርጅቶችን ይረዳ ነበርና፤ ከዚሁ ዓለም አቀፍ ድርጅት በነፃ የተሰጠዉን ባለቀለም ፎቶ ኮፒየርና ፕሪንተር ከዓለምአቀፉ ድርጅት በሰነድ ወጥቶ አየር በአየር ተሸጦ፤ ወንጀሉም ለሚመለከታቸዉ መንግስታዊ አካላት ጥቆማ ደርሶ ሁሉም ድርሻ ድርሻዉን የወሰደ ይመስለኛል፤ ደብዛዉ እንደጠፋ መቅረቱ ነዉ። ወደ ፊንፊኔ የደን ልማትና ገበያ ድርጅት ስሄድ በዉድድሩ ላይ አድልኦ ተደርጎልኛል። ነገር ግን ለሁለትና ሦስት ዓመታት ያህል በሠላም

ከሠራን በኋላ፤ አንዳንዶች ሊጠቀሙበት እንደሚፈለጉት ሰዉ አልሆንኩላቸዉም፡፡ ከአስተዳደግም ይሁን ከሕይወት ተሞክሮ የገጠር አስተዳደግ ሕይወት ተፅዕኖ አሳርፎብኝ እንደሆነ አላዉቅም፤ በሙስና ዉስጥ ቶሎ መዘፈቁን አልመርጥኩም፡፡ ስለሆነም ወደ ጎን የመገፋት ዕድል ይሞካክረኝ ጀመር፡፡ በዚህ ድርጅት በተለይ ሙስና ከሚያጠቃቸዉ ሥራዎች ዉስጥ የቁም ደን ሽያጭ ጨረታ ደህና አድርጎ እንደሚያበላ የድርጅቱ ሠራተኛ ብቻ ሳይሆን በደኑ አከባቢ የሚኖር አርሶ አደር ሁሉ የሚያወቀዉ ጉዳይ ስለነበር፤ በማኔጅሜንት ኮሚቴ ዉስጥ ለመጣላትም ሆነ ለመፋቀር ይኼዉ የቁም ደን ጨረታ ሽያጭ ማሳለፍም ሆነ መጣል ዓይነተኛ ምክንያት ነበር፡፡

ከሁለትና ሦስት ዓመታት በኋላ በፊንፊኔ የደን ልማትና ገበያ ድርጅት ጥሩም ሆነ መጥፎ አጋጣሚ ተፈጠረብኝ፡፡ ጥሩ አጋጣሚ ያልኩት አንድ የነበረዉ የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ለሁለት ተከፍሎ የአስተዳደር አገልግሎትና የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሆኑ ሲወሰን፤ የደረጃ ዕድገትና ከፍተኛ የሚባል የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎልኝ ወደ አስተዳደር አገልግሎት ኃላፊነት ተዛወርኩ፡፡ ለብዙ ሠራተኞችም አዲስ ምደባና ቦታ ተሰጥቶ፤ ባዶ ለቀሩት ቦታዎች ማስታወቂያ በማዉጣት ከዉስጥና ከዉጭ እንዲያድጉበትም ሆነ እንዲቀጠሩበት ተወሰነ፡፡ ከዉስጥ ማሳደጉንም ሆነ ከዉጭ መቅጠሩን ጎን ለጎን ማካሄድ እንደሚቻል በመገመት የዉጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረጌ፤ የዉስጥ ማስታወቂያዉ ሳይጠናቀቅ እንዴት የዉጭ ማስታወቂያ ይወጣል የሚሉ ከሳሾች ተፈጠሩብኝ፡፡ በዚህ መሀከል ሥራ አስኪያጅ የነበረዉ ሰዉ በሕመም ምክንያት አቶ ታሪኩ ጂንፌሳ የሚባለዉንና የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ኃላፊን በመወከል ዕረፍት ወጥቶ ሳይመለስ ሞተ፡፡ እንደኔ ሐሳብ ግን በዉስጥ ማስታወቂያዉ መሠረት የተመዘገቡ ሠራተኞች መረጣ ከተጠናቀቀ በኋላ የዉጭዉ እንደሚቀጥል ፍላጎት ቢኖረኝም ሰሚ አላገኘሁምና ክሱም የክልሉ ፕሬዝዳንት የሕግ ጉዳዮች አማካሪና የቦርድ ሰብሳቢ በሆነዉ አቶ እሼቱ ኢረና ዘንድ በመድረሱ፤ ነገሩን ለማርገብ ብቻ ሳይሆን አካሄዱን የተሳሳትኩ መሆኑን ገልጮ ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ አቶ ታሪኩ

ጅንፌሳንም ሆነ የቦርድ ሰብሳቢዉን ይቅርታ ብጠይቅም ሰሚ አላገኘሁም። በዚህ ምክንያትም ከደመወዝና ከደረጃ ዝቅ ተደርጌ ወደ ሆነች ክፍል ተወረወርኩ። ሥራም ወደኔ እንዳይመጣ ተደረገ። እራሴን ሥራ ብዙ ለማድረግ ሳስብ፤ አልፋ ዩኒቨርስቲ የርቀት ትምህርት እንደሚሰጥ ተገንዝቤ በሕግ የድግሪ ፕሮግራም የርቀት ትምህርት ጀመርኩ። ጠዋት ክፍሏ ዉስጥ ገብቼ ለምሳ ብቻ እየወጣሁ ማንም ሳይረብሸኝ የተሻለ የሚባል ዉጤት እየሰበሰብኩ ሳለ፤ ከጊዜ በኋላ ደግሞ እኔ ከተነሳሁ በኋላ የአስተዳደር አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ ከተቀጠረዉ ሰዉ ጋር አለመግባባት ሲፈጥሩ ለክፍተት ማሟያ እኔዉ እራሴ ወደ አስተዳደር አገልግሎት ኃላፊነት ተመለስኩ።

ወደ መሀከሉ ላይ ሊያቆራርጠን የቻለዉ ግን ከቁም ደን ጨረታ ሌላ ከአቶ ታሪኩ ጂንፌሳ እና አቶ ሙላቱ ከበደ ጋር ያጋጨንን ሳልገልፅ ማለፍ አልፈልግም። አቶ ታሪኩ የሥራ አስኪያጅነት ቦታ ፀድቆለት እየሰራ እያለ፤ እሱ ሲቀጠር የነበረበትን የማስረጃ ክፍተት እንዲያሟላ እኔ ስለጠየቁሁትና አለቃን የመጋፈጥ ሆኖ ስለተሰማዉ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ የጥቃት በትሩን ሰንዝሮብኛል። የማስረጃ ክፍተቱም ከፍተኛ ትምህርቱ ወዳጅ አገር ሶቭዬት ሕብረት ዉስጥ በመሆኑ፤ በወቅቱ ማንም ሰዉ እንደሚጠየቅ የማስረጃዉን አቻ ግምት እንዲያቀርብ ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታም አቶ ሙላቱ ከበደ (ደን ልማት መምሪያ ኃላፊ) ከእንግሊዝ አገር ፖስት ግራጁዌት ሴርቲፊኬት እንዳለዉ አዘዉትሮ ይናገር ነበርና ከእንግሊዝ መጣ የተባለዉ ሴርቲፊኬት የተሟላ የሚሆነዉ ትራንስክርፕት፣ ፊርማና ማህተም እንዲኖረዉ ስለሚያስፈልግ፤ ይህንን አለኝ የሚትለዉን ሴርቲፊኬት ወይም የትምህርት ማስረጃን በተማሪ ዉጤት እንዲያሳጅብ ስናገረዉ፤ ከዚያ በኋላ ከኔ በቀር ሌላ ሰዉ ጠላቱ አላደረገም። የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዉ፣ አቶ እሼቱ እና የቦርድ አባል የነበረዉ አቶ ገላና ኑሬሳ ዘንድ ተመላልሶ ስላስጠመደኝ፤ አቶ እሼቱም የአቤቱታ ማመልከቻዬን እንኳን ተቀብሎ መልስ ሳይሰጠኝ ይቀራል። በነገራችን ላይ አቶ ሙላቱ ማለት አንድ ሩሲያዊ ጸሐፊ

ስለይሁዳ የፃፈዉ ዓይነት ሰዉ ይመስላል። ሩሲያዉ እንደፃፈዉ ይሁዳ ከሃዲ ሳይሆን ቢዝነስ መስራት የሚወድ ሰዉ ስለሆነ ብቻ ወገኑን ክርስቶስን በሰላሳ መክሊት ሸጠ ብሎ ተጽፎ አንብቤአለሁ። ይሁዳን የመሳሰሉ ከሃዲዎች በየቦታዉ የመኖራቸዉ ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ስለኪራይ ሰብሳቢነት ሳወሳ ደግሞ ሀብት በሁለት መንገድ ይሰበሰባል ብያለሁ፤ በመፍጠርና በመዝረፍ። የፊንፊኔ ደን ልማትና ገበያ ድርጅት ኃላፊዎች የቦርድ አባላትን ጨምሮ በመዝረፍ ሀብት ሰብስበዋል። በወቅቱ ላፍቶ አከባቢ በአምቦ ድንጋይ የተሰራዉ የሙላቱ ቤት የተሰራዉ በፊንፊኔ ደን ልማትና ገበያ ድርጅት ተሸከርካሪ በማመላለስ ነዉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ከሙላቱ ከበደ ጋር ብዙዉን ጊዜ ለማለት ይቻላል ስለአገራችን ፖለቲካም በሰፊዉ እናወራ ስለነበረ፤ ከዕለታት በአንዱ ቀን ዉለታ እንደዋለልኝ ቆጥሮ ዉሃ ሲጠፋ የምንጠቀመበት ደረቅ መፀዳጃ ቤት ዉስጥ “ጥሩነህ ኦነግ ነዉ የሚል ጽሑፍ አይቼ፤ እንደሱ ከሆነ እሱ ወንድ ነዉ ብዬ ከሥር ፃፍኩ” ብሎ አወራልኝ። እንዳመሰግነዉ ወይም እንዳደንቀዉ የፈለገ ዓይነት መሆኑን ብረዳም ምንም ለማለት አልፈለኩም፤ ምክንያቱም እኔም ጽሑፉን አይቼ የሁለቱም የፊደል አጣጣሎች አንድ ዓይነት ስለሆኑና እንደዚህ ዓይነት ሸር መስራትም ከሱ ሊያልፍ እንደማይችል ስለተገነዘብኩ ዝም ብዬ አሳለፍኩ። ይህንንም ያደረገዉ በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ ኦነግ ሥልጣን ላይ ባለዉ ፓርቲ ዘንድ ምን ትርጉም እንዳለዉ ስለሚያዉቅ፤ የጥቃቱ ዒላማ ዉስጥ እኔንም አስገብቶ ሊያስወቅጠኝ እንደሆነ ስለታወቀኝ ነበር። ቢሆንም ግን እኔ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያ ንቅናቄ/ኦፌዲን አባል መሆኔን ነገሬዉ ሳበቃ፤ ይኼም በነጋታዉ እንጦጦና ሰበታ ላይ ይሰሩ የነበሩ የሥራ ባልደረቦች ዘንድ ደርሶ መልሰዉ ነገሩኝና የመረጃቸዉ ምንጭ ደግሞ ሙላቱ ከበደ እንደሆነ ጨምረዉ ገለፁልኝ። ሙላቱ፤ እራሱ ከሚያደርስብኝ ጥቃት ሌላ አፋን ኦሮሞ ተናጋሪ፤ ግን ኦሮሞ ያልሆነች የድርጅቱ ሠራተኛ የሆነችን ሴት አነሳስቶ ተራ የሆነ ስድብ ጭምር እንዲትሰድበኝ ሁሉ አድርጓል።

ጊዜ ቢለወጥም ፊንፊኔ የደን ልማትና ገበያ ድርጅት ዉስጥ የነበረዉ ችግሬ በዚህም አላበቃልኝም። የደን ሀብቱ ሸዋ ዉስጥ ሆኖ እያለ፤ የድርጅቱ አመራር ለረጅም ጊዜ በወለጋ ልጆች ተይዞ ነበር ተብሎ ስለሚታማ፤ የሸዋ ልጆች በተዘዋዋሪ መንገድ ተደራጅተዉና ክልሉን ከሚያስተዳድረዉ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ተሞዳሞደዉ ሥልጣኑ በእጃቸዉ እንዲገባ አደረጉ። የሸዋ ተወላጅ ግለሰቡም የሥራ አስኪያጅነቱን ሥልጣን ተቆጣጥሮ የማኔጅመንት አባላቱን ሲሰይም የሱን መመዘኛ አያሟሉም ከተባሉት ውስጥ በመጀመሪያ ረድፍ ላይ ተገኘሁ። የኛ አይደለም የሚሉትን ሰው ወደ ጎን ማድረግ ሥራቸዉ ሆነ። እንዲያዉም ወደ መጨረሻዉ አከባቢ የድርጅቱ ሠራተኞችና የሸዋ ልጆች ነን ባዮች (መኮንን ደረሳ እና ጫሊ ጉተታ) ማስፈራሪያ ብጤ ሰላደረጉብኝ፤ ሥራ ሳፈላልግ ከጋዜጣ ካየሁት ማስታወቂያ መሠረት ተወዳድሬ ፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ የሕዝብ ግንኙነትና እስቴት አገልግሎት ኃላፊ ሆኜ ሄድኩ። በጣም ተጠቃሚ የሆንኩበት የሥራ ዝዉዉር ነበር። እዚያም ሁለት ዓመት ያህል በሠላም እንደሰራሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ሕይወቴን አደጋ ላይ ለመጣል የደረሰ ችግር ደረሰብኝ።

በፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ ዉስጥ የኦህዴድ መሠረታዊ ድርጅት ተጠሪ የነበረዉና የዚሁ የፖለቲካ ድርጅት አባል እንድሆን ያዘዘኝ እኔ በምመራዉ አገልግሎት ሥር በሦስተኛ ረድፍ ላይ የሚገኝ የጥበቃ ፎርማን የሆነ ጌታቸዉ አራርሳ የሚባል ነበር። አባል መሆኑ ላይ ችግር እንደሌለብኝ ነግረዉ፤ ነገር ግን የኦህዴድን ምስረታ ታሪክ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት። አገር የሚያስተዳድርን ድርጅት ምን ሲሆን ነው እንደዚህ ዓይነት ጥያቄ የሚጠየቀዉ ብሎኝ እንደማስፈራራትም ከጅሎት ኖሮ፤ በማስፈራራትም ሳያበቃ እኔ የተቀመጥኩበት ወንበር አባል ለሆነ ሰዉ ብቻ የሚገባ መሆኑን ልኬን ነገሮኝ ከቢሮዬ ወጣ። ከዚያ በኋላ ብቅላ የሚባል የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ካድሬ ተጨምሮበት ከማስፈራራት እስከአፈና ሙከራ ተደረገብኝ። የኦህዴድ አባል ላለመሆን የያዝኩትን አቋም የምገፋበት ከሆነ ሦስት ምርጫዎች፤ (ማባረር፣ ማሰር፣ መግደል) የሚሉት በእጅ ስልኬ ላይ ተደዉሎ ተነገረኝ። ባሁን ጊዜ

እራሱም ተባርሮ የት እንደሚገኝ የማላውቀውና የቀጠረኝን የፋብሪካዉን ሥራ አስኪያጅ አቶ ደረጀ ጉተማን ባማክረዉም፤ ከኔ የበለጠ ከነሱ ጋር መስራት እንደሚበልጥበት ከወንበሩ ተነስቶ አስረዳኝ ሳይሆን አረዳኝ። እኔ ለሥራ ጉዳይ ስጠቀምበት የነበረዉን የድርጅቱን መኪና ቁልፍ ተቀብሎኝ፤ ሞራሌን ለመንካት አስልቶ ለመሠረታዊ ድርጅቱ ተጠሪና እኔ በምመራዉ አገልግሎት ሥር በሦስት ደረጃ ዝቅ ብሎ ላለዉ የጥበቃ ፎርማን ለአቶ ጌታቸዉ አራርሳ ሰጠ። ጌታቸዉ የማያዉቀዉንና ለማወቅም የዕዉቀት ዝግጅቱ የማይፈቅድለትን ሰዉ የኦህዴድን ምስረታ ታሪክ መጠየቁ ከፋ እንጂ፤ ኦህዴድ ትግራይ ክልል አዴት ወረዳ መመስረቱን ሃያ አምስተኛ ዓመቱን ሲያከብር በ2007 ነግሮናል። ከዚያ በኋላ እኔና ጌታቸዉ ተገናኝተን ተሳስቀን ተላልፈናል። በፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ ቆይታዬ ሥራዬ ጥሩ መሆኑ ተገልጾ ሁለት ጊዜ ደመወዝ ተጨምሮልኛል፤ በመጨረሻ ሲያልቅ አያምርም የሚባለዉ ዓይነት ሆነና፤ ከሌሎች ሁለት ትዉልዴ አበሻ ከሆኑ አማራር ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር ከተቀጠርክበት ጊዜ ጀምሮ ዉጤታማ ሥራ አልሰራህም ተብሎ በተመሳሳይ ሰዉ በአቶ ደረጀ ጉተማ ደብዳቤ ተባርሬ ጉዋዜን ጠቅልዬ አዲስ አበባ ገባሁ።

አዲስ አበባ ለመግባት ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት አከባቢ ከፊንጫኣ የወጣሁ ሰው አምቦ የደረስኩት ከሌሊቱ አምስት ሰዓት አከባቢ ሲሆን መኝታ የያዝኩት ምሽት መኝታ በሚያፈላልጉ ልጆች አማካይነት ነው። እራት ስላልገተኘ በባዶ አንጀት መኝታውን ገልጬ ስገባ የተቀበሉኝ የትኋን፣ የቁንጫና የቅማል ሠራዊት ወረራ በወያኔ/ኢህአዴግ ከተዋለብኝ ግፎች ውስጥ አንዱ ስለሆነ፤ ሌሎች ነገሮችን እንኳን ብረሳ በሕይወት እስካለሁ ድረስ ያ ምሽት አይረሳኝም። በፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ የደረሰብኝን በደል ዘርዝሬ ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ባመለክትም፤ ወጣቱ የተቋሙ ኦፊሴር ማመልከቻዬን ሊቀበልኝ ፈቃደኛ አልሆነም። እኔም ወደዚያ እየተማላለስኩ ጊዜና ገንዘቤን ማባከኑን አልፈቀድኩምና ትቼ ሌላ ሥራ ፊለጋ ገባሁ። ወቅቱም ደግሞ ከ2002 የቁጩ ምርጫ በኋላ የኢህአዴግን ዓላማ የማይደግፍ ሁላ ተሰብስቦ እስር ቤት የሚከተትበት

ጊዜ ላይ ስለነበረ፤ መነዛነዙን አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም።

አንድ ነገር ልመርቅላችሁ። የፊንጫኣ ስኳር ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ የነበረዉ ደረጀ ጉተማ ከኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ጋር የመመሳሰል ባህርይ አለው። አንድ ሰሞን ሥራዬን በመዉደዱ የተነሳ ወደ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ጽ/ቤቶች ለሥራ ጉዳይ ሲመላለስ ከኔ እና አቶ ኢታና ገርቢ ከሚባሉ ሰዉ ጋር መሄድ ይወድ ነበር። ነገር ግን እነዚያዉ የሆሮ ጉዱሩ ከፍተኛ ካድሬዎች ፋብሪካዉ ድረስ መጥተዉ ስለኢህአዴግ ዲሞክራሲ ሊያስተምሩን፤ ጥያቄ፣ አስተያየት፣ ሐሳብ ካልሰጣችሁን ብለዉ የሙጥኝ ሲሉ፤ እኔን ጨምሮ ብዙ ሠራተኞች እንኳንስ ዲሞክራሲያን መሆናችሁ ቀርቶ በዲሞክራሲ ደጃፍም አላለፋችሁም ብለን ዶቃ ማሰሪያቸዉ ድረስ ነገርናቸዉ። ከዚያ በኋላ አቶ ደረጀ ጉተማ ወደ ቢሮዬ መምጣትና ወደ ቢሮዉም እኔን ጠርቶ ስለሥራ ክፍሌ ሥራ መነጋገርም ቀረ፤ በምግብ አዳራሽ ብቻ ስንገናኝ መንግስቱ ኃይለማሪያም ያደርግ እንደነበረዉ ስቆ ተጨዉቶ ያልፈኛል። እኔም ካራ እየሳለብኝ መሆኑ ለአፍታም አልጠፋኝም። ልክ እንደ መንግስቱ ኃይለማሪያም ስቆ ተጫዉቶ ማለፉ ጉዱጓድ እየማሰልኝ መሆኑን ተገንዝቤ፤ ሌሎችም ስለነገሩኝ አስፈላጊዉን ጥንቃቄም አድርጌያለሁ። አብሼ ገርባንና ሌሎች ጀግኖችን ያፈራችዉ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ በጣት የሚቆጠሩ አሽክላዎች ቢገኙባትም፤ የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊው ስባኑ ገለቱን የመሳሰሉ ወገኖች ስለነበሩ አንዳች ጉዳት ሳይደርስብኝ ከስኳር ፋብሪካው ሸለቆ እንዲወጣ አግዘውኛልና ባለዉለታዬ ናቸዉ። አሁንም በነገራችን ላይ ልበልና ደረጀ ጉተማን አደስ አበባ ከተማ ዉስጥ በሆነ ዝግጅት ላይ ተገናኘንና እጁን ለሰላምታ ሲሰድልኝ ፊት ነሳሁት።

እንደመረጋጋትም፣ እንደመናደድም ብዬ ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ ሥራ ሳፈላልግ ዴቬሎፕሜንት ኤክስፐርትስ ሴንተር በሚባል አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ዉስጥ በአገር ቤት ልጅ አማካይነት ተቀጥሬ የቢሮ ዉስጥ ሠራሁ። ከዚያም፤ ይህን ሰዉ ምን ነካዉ በየሄደበት

መባረር ነዉን ቢትሉም እንደማልፈርድባችሁ እያሳሰብኩ፤ በወያኔ ፖለቲካ ጣጣ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅትም ተባረርኩ። ምክንያቱ ደግሞ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ኦፌዲን እና የኦሮሞ ሕዝብ ኮንግሬስ/ኦሕኮ እሁድ ሐምሌ 22 ቀን 2004 ዉህደት ሲያደርጉ፤ የስብሰባዉ ተሳታፊና ቃለ ጉባኤም ፀሐፊ ስለነበርኩ፤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም በአቀረበዉ ዜና ላይ ፎቶዬን በግልፅ ያሳይ ስለነበረ፤ አገር ሠላም ነው ብዬ ሐምሌ 23 ጠዋት ወደ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅቱ መደበኛ ሥራዬ ሲገባ፤ አቶ አንለይ አሜንቴ ገምቴሳ፣ የዴቨሎፐሜንት ኤክስፐርትስ ሴንቴር ባለቤትና ሥራ አስኪያጅ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ጠበቀኝ። ምክንያት፤ አቡነ ጴጥሮስ እኔ በምመራው አገር ውስጥ እንዴት አላሁ ኩባር ይባላል እንዳሉት ዓይነት፤ እሱ ከወያኔ መንግስት ጋር ተግባብቶ እየሰራ ባለበት አገር ዉስጥ፤ እኔ የአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ አባል፣ ለዚያዉም በዶክተር መረራ ጉዲና እና በአቶ ቡልቻ ደመቅሳ በሚመሩ ፓርቲዎች ዉህደት ላይ ተገኝቼ፤ በቀጣይነትም ከሱ ጋር መስራት ማለት እሱንም በግሉ፣ ድርጅቱንም እንደድርጅት ሊጎዳ የሚችል ስለሆነ፤ ዕለቱኑ ድርጅቱን ለቅቄ እንዲሄድለት አዘዘኝ። እኔ አባል የሆንኩበት የፖለቲካ ድርጅት የገዥዉ ፓርቲ ተቃዋሚ እንጂ የመንግስት ተቃዋሚ እንዳልሆነ ቢነግረዉም፤ እንኳን ሊያዳመጠኝ ቀርቶ ለመናገርም ዕድል ስለነፈገኝ ቃል አልተነፈስኩም። የእሱ ድርጅት ዉስጥ ሥራ ሲቀጠር በአንዳች የፖለቲካ ጉዳይም ሆነ ከፖለቲካ ድርጅት ጋር በግል ተሳትፎ አላደርግም የሚል ስምምነት ካለማድረጌም አልፎ ተርፎ፤ እሱ ለገዥዉ ፓርቲ እና በሥሩ ለሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች ከሚበትነዉ ገንዘብ የፖለቲካ አቋሙንም ለመገመት በመቻሌ፤ በምሳ ሰዓት እንኳን ቢሆን ከሱ ድርጅት ሠራተኞች ጋር የፖለቲካ ጉዳይ አንስቼ የጠበቀ ዉይይት አድርጌ አላዉቅም ነበር። ምክንያቱ ደግሞ ስለፖለቲካ ማውራት ከፍርሃት የመነጨ ሳይሆን የሥራ ቦታም ሆነ የመዝናኛ ቦታዎች ሁሉም በፖለቲካ ንትርክ ወይም ሆነ ጨዋታ እንዲታጨቁ ስለማልፈልግ ነው። የምን ደረቅ ፖለቲካ ብቻ የሚሉ ሰዎች ደስ ይሉኛል።

አቶ አንለይ ሲቀላምድብኝም በፖለቲካ ድርጅቱ የተሳትፎዬ ደረጃ ምን እንደሆነ በጽሑፍ ሪፖርት እንዳቀርብለት ሲያዘኝ፤ ብዙም ጭቅጭቅ

ውስጥ መግባት አልፈለኩምና አለፍኩት። አቶ አንለይ አሜንቴ ገምቴሳ የኢሉ አባቦራ ዞን የዶራኒ ወረዳ ተወላጅ ሲሆን፤ ከተዘፈቀበት የሙስና ወንጀል የበለጠ የኔ የኦሮሞ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን እጅግ በጣም አሳስቦት እንደነበር ዛሬ ድረስ ሳስበዉ ይገርመኛል። ከአስቂኝ ንግግሩ ዉስጥም የኔ የፓርቲዉ ስብሰባ ላይ መገኘት ከሱ ዕዉቀት ዉጬ የተፈጸመ ስለመሆኑና የሚጠይቀዉ ሰዉ ወይም አካል ቢኖር ለማሳየት ይቻለዉ ዘንድ ያልተጠቀምኩበትን ጊዜ፤ አምስት ቀናት ወደኋላ ተመልሼ የዓመት ፈቃድ እንዲሞላና ስብሰባዉንም የተሳተፍኩት በዕረፍት ጊዜዬ መሆኑን ለመግለፅ አስቦ ያስደረገኝ ነበር። ይህንንም እሱ በሚፈልገዉ ዓይነት ሁኔታ ፈጸምኩለት። ወደሌላ አካል ለማመልከትም ሆነ ለማሳበቅ አልደፈርኩም፤ ምክንያቱም አገሩ ኢትዮጵያ ነዋ! የሐሳብ ልዩነት የሚያገዳድልበት የደደቦች ፖለቲካ የሚካሄድበት! ፈጣሪ ጥሎ አይጥልምና ይህ በተከሰተ ሰሞን አቶ አንለይ ወደ ዉጪ አገር ይሄድ ኖሮ፤ ከተወከለዉ የፕሮግራም ዳይሬክተር ጋር በመመካከር መባረሬ ቀርቶ ወደ ጡረታ እንዲዞርልኝ ተደረገ። የጡረታ መዉጫ ጊዜዬ ሳይድረስ አምስት ዓመት አስቀድሜ በመዉጣት፤ እነሆ ጡረታ ላይ እገኛለሁ። ግን ጡረታን ጥሩ ተኛ አላደረኩትም፤ ይህችን መጣጥፍ አበርክቻለሁ።

ሲጠቃለልም፤ ይህ ግለሰብም ሆነ ሌሎች ከሥራ ሲያባርሩኝ፣ ሲያፈናቅሉኝ፣ እኔና ቤተሰቤን ለረሃብ ሲያጋልጡ በግል ተነሳሽነታቸዉ ወይም የመንግስት ፖሊሲ መሆን አለመሆኑን እስከዛሬም ለይቼ ማወቅ አለመቻሌ ነዉ። እርግጠኛ መሆን የሚቻለዉ ግን በእጅ አዙር መንገድ ካልሆነ በስተቀር ይህ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመንግስት ፖሊሲ አለመኖሩን ነዉ። የጊነዉ ሴኩቱሬ ተናገሩት ተብሎ የሚነገር አንድ አባባል አለ። “በባርነት ሀብታም ከመሆን ይልቅ በነፃነት ድህነትን መምረጥ”፤ ነፃነት ኖሮ ሀብት ባይመጣ እንኳን ከሕሊና ባርነት ነፃ ያደርጋል። ነፃነቱን ለባርነት የሚሸጥ ርካሽ ሰዉ ብቻ ነዉና። ስሰራ የተሳሳትኩበት ጊዜ ብዙ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ኦሮሞነቴንም ሆነ የግል ነፃነቴን ለባርነት ሸጬ አላዉቅም ለማለት ፈልጌ ነዉ።

የኢትዮጵያ፡ጊዜያዊ፡ወታደራዊ፡መንግሥት
ETHIOPIAN PROVISIONAL MILITARY GOVERNMENT

ህዳር 13 ቀን 1967 ዓ.ም.

ለደርጉ የዘመቻ [illegible]
አዲስ አበባ።

በጣም፡የሚያስቸኩል

ጉዳዩ ፦ <u>በቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የተላለፈውን ከፍተኛ የሞት ቅጣት ተግባራዊ ስለማድረግ ይመለከታል።</u>

በአገራችን በፊውዳሉ አስከፊ ሥርዓት ላይ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አብዮት [illegible] [illegible] [illegible] አብዮታዊ ደርጉ የአገሪቱን ሥልጣን ተረክቦ በመምራት ላይ ይገኛል።

አብዮታዊ ደርጉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የዘውዱ አገዛዝ [illegible] የቀድሞ ባለሥልጣናትን በቁጥጥር ስር አውሎ ጉዳያቸውን ሲያጣራ የቆየ ሲሆን [illegible] ላለፉት 40 ዓመታት [illegible] ሕዝብ ሲረግጡ በመዝበር [illegible] ከፍተኛ [illegible] ባለሥልጣናት ላይ ከፍተኛ የሞት ቅጣት ውሳኔ አስተላልፏል።

ስለዚህ የደርጉ አባላት ባደረጉት ከፍተኛ ስብሰባ በአንድ ድምፅ የሞት [illegible] ከዚህ ትእዛዝ ጋር የተያያዘው የቀድሞ ባለሥልጣናት ላይ አብዮታዊ እርምጃ [illegible] የደርጉ አባላት በአንድ ድምፅ ወስኗል።

<u>ትእዛዝ</u>

፩/ ሌ/ጄኔራል አማን አምዶም [illegible] ወህኒ ቤት [illegible] እንዲፈጸም [illegible]

፪/ [illegible] ለ54 ሰው [illegible] እስከ 5ሰ [illegible] ከፍተኛ [illegible] ባለሥልጣናት [illegible] እንዲቀበሩ [illegible]

ከሌሊቱ 8፡00 / 0200/ ሰዓት በወታደራዊ [illegible] በአንድ ላይ በጥይት [illegible] እናስታውቃለን።

[illegible]
መንግሥቱ፡ኃይለ፡ማርያም

[illegible] ፲፱፻፸[illegible] ዓ.ም

[illegible]

[illegible]

አዲስ አበባ

ጉዳዩ [illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

ዩዒሬሽ ገስ ዳ ሽክፋሮቹ ገዐች

1ኛ. ገዐ በዩና ገልተ

2ኛ. ገዐ ተስፋ ዲናሞ

3ኛ. ገዐ ኬሬርሬ ኬዬጣሎ

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]

[illegible]

በኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን
የአውራጃ ኮሚቴ ጽሕፈት ቤት

ስልክ ቁ. ..........
ፖ.ሣ.ቁ. ..........

ቁጥር [illegible]3/348/75
ቀን ታኅሣሥ 11 ፲፱፻ 75

ለጓድ ጥሩነህ ገምታ
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢሠፓአኮ መ.ድ በሕንፃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ጉልህ የሆነ የመበታተን ሁኔታ ታይቶበታል ። ይህ ሊታረም ባለመቻሉ መሠረታዊ ድርጅቱ አደገኛ ለሆነ ድክመት ተጋልጦ ይገኛል ። እርስዎም ቢሆኑ ይህን መ.ድ አሰባስቦ አመራር ለመስጠት ከፍተኛ ድክመት የተጫጫነዎት መሆኑን ደርሰንበታል ። ይህንንም በየአጋጣሚው አንስተን ሂስ ሁሉ ተለዋውጠንበታል ግን ሊያርሙ አልቻሉም ።

1. የሚሰጠዎትን ድርጅታዊ ተልዕኮ በሰንካላ ምክንያት አይወጡም
   ሀ. በሠራተኛው ማህበር ምርጫ
   ለ. በሠርቶአደሩ ቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫ
2. በቀጣና ደረጃ የወጣቶች ጉባኤ ተጠርቶ የሕንፃ ኮንስትራክሽን አዳራሽ እዚያ የሚገኙ የመ.ድ ጓዶችን አሰባስበው እንዲያስናዱ ቢታዘዙ የጉዳዩን አሳሳቢነት ከምንም ሳይቆጥሩ አዳራሹን ሳያዘጋጁ የጉዳዩን ተፈፃሚነት ለማየት የቀጣና ጓዶች ወደአዳራሹ ቢሄዱ እርስዎ በሥፍራው ባለመገኘትዎ፣ አዳራሹ ሳይዘጋጅ አድሮ ከአንድ ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የተዘጋጀው ትምህርታዊ ሴሚናር ከጧቱ በ2 ሰዓት መጀመር ሲገባው ከቀኑ 4 ሰዓት በኋላ ስብሰባው በመጀመሩ በስፋት የተከናዳው ፕሮግራም ተጨናንቆ ሥርዓተቢስ እንዲሆን ምክንያት /መሰናክል/ ሆነዋል ።

.../2

ስለዚህ የመ.ድ ተጠሪነቱንና በእጅዎ የሚገኙትን የኢሠፓአኮ ንብረት ለጓዱ መከበብ ገ/ማሪያም እንዲያስረክቡ በቁጥር ከሀ8-ፓ4-ሕድ10-ሠ1/39 በተፃፈ ደብዳቤ የበላይ አካል ያዘዘ ስለሆነ ይህ ማስታወሻ ከደረሰዎ አንስቶ በትዕዛዙ መሠረት አከናውነው እርስዎ በመ.ድ አባልነት እንዲሰሩ ይሁን ::

የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ ተልዕኮ በተግባራችን ይሟላል

የአዲስ አበባ ቀጠና 3 አውራጃ የኢሠፓአኮ ተጠሪ

ግልባጭ ፣

ለአ.አ ኢሠፓአኮ ኮሚቴ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ 85ቱ ብሄር ብሄረሰቦች ስም

ኦሮሞ
አማራ
ሶማሌ
ትግራይ
አፋር
ሲዳማ
አገው
ወላይታ
ከምባታ
ሀዲያ
ጋሞ
ጉራጌ
ኢሮብ
አርጎባ
ቅማንት
ስልጤ
ሺናሻ
አኝዋክ
ኑዌር
ሀመር
ኩናማ
ጉሙዝ
በርታ
በና
አሪ
ሙርሲ
ቡሜ
ካሮ
ፀማይ

ኮንሶ
ዳሰነች
አላባ
ኤርቦሬ
ባጫ
ቤንች
ባስኬቶ
ቡርጂ
ጫራ
ጋዋዳ
ጌዲኦ
ጊዶሌ
ጎፋ
ሐረሪ
ከፊቾ
ሻኪቾ
ኮንታ
ኒያንጋቶም
ማኦ
ቀቤና
ሱርማ
ጠንባሮ
የም
ወርጂ
ዲዚ
ዶንጋ
ዳውሮ
ዲሜ
ምዓን

ኮሞ
ማረቆ
ሞስዬ
ኦይዳ
ቦዲ
ፈዳሼ
ኮሬ
ማሌ
ማኦ
መዠንግር
ቀዋማ
ቀጨም
ሸኮ
ዘይሴ
ዘልማም
ሽታ
ቤተ እስራኤል
ማሾላ
ኮጉ
ድራሼ
ቁጫ
ጋባቶ
ጌዲቾ
ብራይሌ
ሙርሌ
ኮንቶማ ....

የኢትዮጵያ ታሪክ ከሚል የተወሰደ

ጌታቸው ጎንፋ ሆርዶፋ ፌቡ ላይ ከለተጠፋት

## ዋቢ መፃሕፍቶች

1. እስክንድር ቡላቶቪች፣ ከእንጦጦ እስከ ባሮ፣ ትርጉም ዶ/ር አምባቸዉ ከበደ፣ አዲስ አበባ፣ 2005
2. ታቦር ዋሚ፣ የዉገና ድርሰቶችና የታሪክ እዉነቶች፣ አርቲስትክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 2006
3. Dirribi Demissie Bokku, Oromo Wisdom in Black Civilization,Finfnnee Printing and Publishining SC, Finfinnee, Ethiopia, April 2011
4. Joseph Stigltz, The Price of Inequalty, W.W. Nortone and Company, New York, London, 2012
5. ኦላና ዞጋ፣ ግዝትና ግዞት፣ አዲስ አበባ፣ 1985
6. እሸቱ ኢረና ዲባባ፣ የኦሮሞ ታሪክ፤ 2001፤ አዲስ አበባ
7. ተስፋዬ መኮንን፣ ይድረስ ለባለታሪኩ፣ ጥቅምት 1985
8. ነቢዩ እያሱ፣ አፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ፣ ትርጉም፣ በሌ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ ታህሳስ 1984
9. ተፈራ ኃይሌ ሥላሴ፤ ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ ከ1789 እስከ 1967 አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ፕሬስ 1999 ዓ.ም
10. Paul B. Henz, Ethiopia in Mengistu’s Final Years, vol. 2 Shama Books, Addis Ababa, Ethiopia, 2007
11. Getachew Jigi (PhD), Bu’aa Ba’ii Qabsoo Ummata Oromoo, (Sirna Gabarummaa Irraa Gara Bilisummaatti), Beeljiyeem, 2014
12. አዲስ ዘመን፣ ጉብኝቱ የአገሮችን ግንኙነት ወደአዲስ ምዕራፍ ያሸጋገረ ነዉ፣አዲስ አበባ፣ ዓርብ ሐምሌ 24 ቀን 2007
13. ሪፖተር፣ ባለራዕዩን መሪ ለምን አጣን፣ አዲስ አበባ፣ ነሐሴ 27 ቀን 2006
14. Donald N. Levine, Meles Zenaw and the Politics of Ethnicity, Ethiopian Review, vol. 2 No. 9, Los Angelos, USA, Sept. 1992
15. የፖለቲካ ፓርቲዎችን የምርጫ ሥነ ምግባር ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 662/2002
16. Charles W. Kegley and etel, World Politics, Trend and Transformation, St Martins Press, New York, 1981
17. Amy Jacques Garvey, Philosophy and Opnions of Marcus

Garvey, Studies in American Life vol. 1 & 2 New York, 1982

18. ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ የነፃነት ጎህ ሲቀድ፣ ኤም ኤም አታሚዎች፣ ዩጋንዳ፣ ካምፓላ፣ 1998
19. ማሞ ዉድነህ፣ መጪዉ ጊዜ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1985
20. መረራ ጉዲና ዶ/ር፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፣ ግራፍክ አታሚዎች፣ 2006
21. ሰለሞን ሥዩም፣ የኦሮሞ ጉዳይና የኢትዮጵያ ብያኔ፣ አዲስ አበባ፣ 2007
22. አለምሰገድ ቦጋለ አዳል፣ የኤርትራዉ እንቆቅልሽ፣ በሌ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ 1985
23. Merera Gudina, Ethiopia: Competing Ethnic Nationalism and the Quest for Democracy; 1960 – 2000, Chamber Printing House, Addis Ababa, 2003 226
24. Richard Pankhurst, Britain in Ethiopia, 1896 – 1996; Centnary of the British Deplomatic Presence in Addis Ababa, 1996
25. Lovis Aalen, Journal of Democracy, 1998, as quoted in Ethnic Federalism in Dominant Party State
26. Lemma Degefa, Leadership, Living and Serving, An African Practioner's Perspective, 3 rd ed, Addis Ababa, Ethiopia, 2012
27. Lovis Aalen, Ethnic Federalism in a Dominant Party State, The Ethiopian Experience, 1991 – 2000, 2002, (unpublished)
28. Mohammed Ali (Ambassador), Oromo Politics; Reflections and Statements, Ethiopian International Institute for Peace and Development, Addis Ababa, Ethiopia, 2013
29. አንዳርጋቸዉ አሰግድ፣ በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ፤ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ዉስጥ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ የካቲት1992
30. ባህሩ ዘዉዴ (ፕሮፌሰር)፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከ1847 እስከ 1983፣ አዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ 2007
31. መስፍን ወልደማርያም (ፕሮፈሴር) አዳፍኔ፣ ፍርሃትና መክሸፍ፣ 2007 ዓም
32. ሞቲ ቢያ፣ ኦሮሚያን በፈረቃ??፣ አቢሲኒዮክራሲ ወይስ ዲሞክራሲ?

ጂቱ የሥነ ጥበብ የሕትመትና የማስታወቂያ ሥራ፣ አዲስ አበባ፣
ኢትዮጵያ፣ 1996/1998

33. አማኑኤል አብርሃም፣ የሕይወቴ ትዝታ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፣ 1992
34. ሰለሞን ስዩም፣ የኦሮሞ ጉዳይ፣ መጋቢት 2007፣ አዲስ አበባ
35. ሰለምን ስዩም፤ የኢህአዴግ ፍፃሜ፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣2005

36. Nelson Mandela, Long Walk To Freedom, Abacus Animprint of Little, Brown Book Group, London, UK, 1994
37. Milton A. Gonsalves, Right and Reason, Ethics in Theory and Practice, 9th ed., Merrill Publishing Company, USA, 1986
38. Elizabeth B. Hurlock, Develomental Psychology: A Life-Span Approach, 9 th ed., Tata McGraw-Hill Publishing Company Ltd, New Delhi, 1990
39. Jack Kennedy, Introduction To Human Rights, Decembere 5, 1995 USA
40. መረራ ጉዲና (ፐሮፌሰር)፤ በኢትዮጵያ የሀገረ መንግስት ግንባታ የታሪክ ዳራ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተች አገር ለመፍጠር የተደረጉ ሙከራዎች፣ ያጋጠሙን የታሪክ ፈተናዎችና ያመለጡን ዕድሎች በብሔራዊ መግባባት መነፅር ሲታይ፤ ፊንፊኔ፤ ነሐሴ 16/2012 (ያልታተመ)
41. ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይሌ ሥላሴ፤ አዲስ አበባ፤ 2000 ዓም
42. አህመዲን ጀበል፣ 3ቱ አጼዎች እና ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች፤ ጥር 2008፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
43. ፀጋዬ ሸንብር፤ ክብረ ነገስት፣ ንግስት ሳባና ብቸኛ ልጇ ምንሊክ 2009 ዓም
44. James Boggs; Racism and the Class Struggle, New York and London, 1970
45. አሰፋ ጫቦ፤ የትዝታ ፈለግ፤ በኢትዮጵያ ህትመትና ስርጭት ነባዳን የሚዲያ ማማከር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ እአአ 2016
46. ወጋየሁ በለው ተገኘ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ ትንሹ እና የነፃነት ንቅናቄው (ሕልም አለኝ)፤ ትርጉም፤ ቀለም ማተሚያ ቤት፤ 2009፤ ኢትዮጵያ
47. ላጵሶ ጌታሁን ዴሊበ (ፐሮፌሰር)፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ 2012/2020 ዓም፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
48. ዘውዴ ረታ፤ የቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት 1ኛ መጽሐፍ 1923-1948፤ ሻማ ቡክስ፤ ሮኖቦት አታሚዎች ኃ.የተ.የግ.ማ. 2005፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
49. ደስታ ዲንቃ ጎሴ፣ መቋጫ ያጣው የኢትዮጵያዊያን የነፃነት ትግል፤ ነሐሴ 2011 ዓም፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
50. ኤርሚያስ ለገሰ፣ የመለስ ልቃቂት፣ ነፃነት አሳታሚ ድርጅት
51. Rick Stapenhurst (ed.), Curbing Corruption, Toward a Model for Building National Integrity, EDI Development Studies, The World Bank, Washington, D.C, 1999.
52. Daron Acemoglu & James A. Robinson, Why Nations Fail, Profile Books, Crown Publishers, Great Britain, 2012
53. Christian Krell (Ed.); Thinkers of Social Democracy, Germany, 2016
54. በረከት ስምኦን፣ የሁለት ምርጫዎች ወግ፣ ናዳን የገታ አገራዊ ሩጫ፤ 2003 ዓም
55. አምሃ ዳኘው ተሰማ፤ ሐገራዊ ብሔረተኝነት እና ዘውጋዊ ብሔረተኝነት በኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ በመስቀለኛ መንገድ ላይ (ለኢጥዮጵያ የፖለቲካ ችግር የቀረበ አማራጭ የመፍትኼ ሐሳብ፤ ጥር 2012
56. ጆርጅ አንደርሰን፤ ፎረም ኦፍ ፌዴሬሽንስ እንዳዘጋጀው፤ የፌዴራላዊ መንግስት አወቃቀር መነሻ ነጥቦች፣ መጋቢት 2001፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
57. James Bunting, Adolf Hitler, Jalco Publishing House, Bombay, India, 1973.
58. ውብሸት ሙላት ጽጌ፤ አንቀጽ 39፣ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፤ 2007
59. ተስፋዬ ፉፋ ኡሉማ፤ የኩሽ ሀገር ኢትዮጵያ በሀገረ መንግስት ምስረታ ስም ስንት ግፋ ተሰራ! አዲስ አበባ 2013
60. P.T.W Baxter and et al (editors): Being and Becoming Oromo; Historical and Anthropological Enquiries, Nordiska Afrikain Instituteti UpPSAIA 1996
61. Greg and et al The Asian Aspiration: Tang Xiaoyang. Tsinghua University, China 2020
62. Georg Schwarznberger: Power Politics: A Study of World Society, 3rd ed., Sevens & Sons Limited, London, 1964

ደራሲው



